www.abyssinialaw.com

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ችሎት
# ውሣኔዎች

## ቅጽ - 14

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

መስከረም 2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

www.abyssinialaw.com



<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

ለተመሳሳይ ጉዳዮች በጣም የተራራቁ ውሣኔዎችን በመስጠት ይታይ የነበረውን ችግር በመቅረፍና የውሣኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ የሰበር ውሣኔዎች አስገዳጅ መሆን ከፍተኛ ውጤት አስገኝቷል ማለት ይቻላል፡፡ አልፎ አልፎ በውሣኔዎች ጥራትና ስርጭት ሊታዩ የሚችሉ ችግሮች ሥርዓቱ እየተጠናከረ ሲሄድ የሚፈቱ ሲሆን እነዚህን ችግሮች ለማቃለል እኛም ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፣ ጥረታችን ሊሣካ የሚችለው በውሣኔዎቹ ላይ በሕግ ምሁራንና ባለሙያዎች ገንቢ የሆኑ ትችቶችና አስተያየቶች ሲቀርቡ ነው፡፡

ለሰበር ውሣኔዎች ጥራትም ሆነ ለፍርድ ቤቶች መጠናከር እና በአጠቃላይ ለሥራችን መሻሻል ሊረዱ የሚችሉ አስተያየቶች ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

የሰበር ውሣኔዎችን ቶሎ ቶሎ ለማሣተም ባደረግነው ጥረት ቅጽ 14ን በአጭር ጊዜ ማሣተም የቻልን ሲሆን ይህን የ2005 ዓ.ም. ውሣኔዎች የያዘውን ቅጽ 14ን ጨምሮ ከዚህ በፊት የታተሙትን ቅጾች በሙሉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረ ገጽ www.fsc.gov.et ላይ ማግኘት እንደሚቻል ማስታወስ እወዳለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

www.abyssinialaw.com

# በ2005 ዓ.ም. የሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | 1 |
| 1. | በአሰሪ ከተደረገ የሥራ ቦታ ዝውውር ጋር በተያያዘ ሠራተኛው ወደነበረበት ሥራ ቦታና መደብ እንዲመለስ በፍ/ቤት ሲወሰን አሰሪው ሠራተኛው የሥራ ዝውውሩ ከመከናወኑ በፊት ይሰራበት ወደነበረበት ቦታና የሥራ መደብ በትክክል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ፣ | 78536 | በደሌ ቢራ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ አልማው ቤዛ | ታህሳስ 5/2005 | 2 |
| 2. | ሠራተኛ ተቀጥሮ የሚሰራበትን አሰሪ ተቋም መልካም ስምና ዝና እንዲሁም ጥቅምና ህልውና አደጋ ላይ በሚጥሉ ተግባራት የሚፈጽመው ጥፋት መጠንና ደረጃ እና የሚወሰድበትን እርምጃ ለመወሰን ሠራተኛው ከሚሰራው የሥራ አይነትና ባህሪ እንዲሁም ከአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መንፈስና ዓላማ አንፃር መታየት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ)(ረ) | 77134 | ወሰኔ የህክምና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና<br>ዶ/ር ክብረወሰን አለማየሁ | ጥቅምት 8/2005 | 5 |
| 3. | የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሰው በሌላ የመንግስት ሥራ | 72341 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | ህዳር 21/2005 | 8 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተቀጥሮ ያለአግባብ የወሰደው የጡረታ አበል እንዲመለስ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑና የይርጋ ጊዜውም ግለሰቡ በሌላ የመንግስት ሥራ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣<br>• አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ መልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በቋሚነትም ይሁን በጊዜያዊነት እንዲሁም ደመወዙ ከጡረታ አበሉ ያነሰ ሆነም አልሆነ ከደመወዙና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 46(1) (2)<br>አዋጅ ቁ.209/55 አንቀጽ 30(2)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1677(1) | | እና<br>አቶ ታዬ አበራ | | |
| 4. | የሥራ ክርክር ችሎት አንድን ሠራተኛ ያለአግባብ የተሰናበተ ነው በሚል ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ወደኋላ ቀደም ብሎ ካለ ጊዜ ጀምሮ አሰሪው ወደ ሥራ እንዲመልስ በሚል ውሣኔ የሰጠ እንደሆነ ሠራተኛው ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ ደመወዝ ለማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ፣ | 83012 | ዝዋይ ሮዝ ድርጅት<br>እና<br>ወ/ሮ ፋንቱ ያሲን | ጥር 14/2005 | 13 |
| 5. | የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው የህግ ባለሙያ በሙያው አገልግሎት ለመስጠት ከ3ኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ውል የሚፈጠረው ግንኙነት በእውቀት ሥራ ውል ላይ የተመሠረተ እንጂ ሠራተኛውን እንደ የስራ መሪ ወይም ተቀጣሪ የማያስቆጥረው ስለመሆኑ፡<br>በአዋጅ ቁ.377/96 የማይገዛ ስለመሆኑ፣ | 81405 | አቶ አህመድ ሲራጅ<br>እና<br>የአወሲያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት | ጥር 29/2005 | 19 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6. | አንድ ሠራተኛ መብቱን ለማስከበር በአሰሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መመስረቱ ብቻ ከአሠሪው ጋር ለወደፊት የሻከረ ግንኙነት ይፈጥራል የማያስብልና የስራ ውሉ እንዳይቀጥል ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ስላለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43(3) | 82336 | የአብጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>ማርታ አበበ | ጥር 02/2005 | 21 |
| 7. | ቀደም ሲል ስናገኘው የነበረው የደመወዝ መጠን የተቀነሠ ስለሆነ እንዲስተካከልልን በማለት በሠራተኞች የሚቀርብ ክስ የወል የሥራ ክርክር ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ | 78865 | የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት<br>እና<br>እነ አቶ ገ/ስላሴ ኃ/ማርያም (ስምንት ሰዎች) | ጥር 28/2005 | 24 |
| 8. | ከሥራ ቅጥር ግንኙነት ጋር በተገናኘ አንድ ሥራ "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>• አንድ ሥራ በባህሪው "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስራው ረዘም ላለ ጊዜ መስራቱን ብቻ ሣይሆን የሥራው ባህሪ ከአሠሪው ድርጅት (ተቋም) አይነተኛ ሥራ ጋር የሚሄድና በመደበኛነት የሚከናወን መሆኑን ጭምር ማረጋገጥ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣ | 80350 | ሸራተን አዲስ<br>እና<br>እነ አቶ ገናናው ከበደ (ሃምሳ አንድ ሰዎች) | ጥቅምት 20/2005 | 27 |
| 9. | የጡረታ መውጫ እድሜ ወሰንን በተመለከተ አሰሪው ከሠራተኛ ማህበር ጋር የሚያደርገው ስምምነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው በተመሣሣይ ጉዳይ ለሠራተኛ በህግ ከተደነገገው ይልቅ የህብረት ስምምነቱ የተሻለ (የበለጠ) ጥቅም የሚያስገኝ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 134(2),24(3) | 80079 | የመቶ አለቃ ጥላሁን ታችበሌ<br>እና<br>ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር | ህዳር 19/2005 | 33 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 715/2003 አንቀጽ 17(1) | | | | |
| 10. | አንድ ሠራተኛ በባህሪው ቀጣይነት ባለው ሥራ ላይ መቀጠሩ መረጋገጡ ብቻ ሠራተኛው ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ፡<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24(1) | 79853 | የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን<br>እና<br>እነ አቶ ጌታቸው ደበበ (14 ሰዎች) | ህዳር 04/2005 | 36 |
| 11. | ሥራና ሰራተኛን ከመምራት እና ከመቆጣጠር ባለፈ በሠራተኛ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድም ሆነ ከሥራ ለማሠናበት ስልጣን በሌለው የቅርብ አለቃ ሠራተኛው ሥራ እንዲለቅ የተነገረ መሆኑ የሥራ ውል ተቋርጧል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ስላለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ) | 79212 | ሮያል ከረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ወ/ሪት ፀሐይ ብርሀኑ | ጥቅምት 19/2005 | 40 |
| 12. | የሥራ ውል ወይም በሌላ ሠነድ ሠራተኛው ስምምነቱን ባልሰጠበት ሁኔታ አሰሪ የሆነው አካል እህት ድርጅት ወደ ሆነ ተቋም (ድርጅት) ሰራተኛውን አዛውሮ ለማሰራት አሠሪ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 83068 | ዲ.ኤች.ገዳ ብርድልብስ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ወ/ሪት ቅድስት ጌታቸው | ታህሳስ 30/2005 | 43 |
| 13. | አንድ ሠራተኛ በሥራው አፈፃፀም ምዘና ደካማ ነው በማለት የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚቻለው ምዘናውን ሠራተኛው በተቀጠረበትና በተመደበበት የሥራ አይነት (መስክ) ላይ በማድረግ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 42, 43(1) | 82335 | ሆሊ ኤንጀልስ ት/ቤት ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>መ/ር መልካም አለማየሁ | ጥር 01/2005 | 46 |

www.abyssinialaw.com

| | ውል | | | 50 | |
|---|---|---|---|---|---|
| 14. | • በተዋዋይ ወገኖች በተደረገ የጽሁፍ ሰነድ ላይ የሚገኝ የስምምነት ቃል እንዲሁም በሰነድ ላይ ስለተመለከተው (ስለተፃፈው) ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ውሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው በሚል ለመደምደም የሚቻለው እንደ ውለታው አይነት የጽሁፉ ውል አደራረግን በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተዘጋጀና የያዘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>•የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት በህጉ አግባብ ባልተደረገበት ሁኔታ በውሉ ላይ የሠፈሩት ማናቸውም የውል ቃሎች ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዳሉ የሚታመኑና በማናቸውም የሰው ምስክርነት ቃል ማስተካከል አይቻልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>•አንድ ውል በህግ ፊት የፀና ነው እንዲባል በህግ ውሉ የሚደረግበትን አግባብ በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በተመለከተ የተደረገ ካልሆነ በቀር ውሉን መሠረት በማድረግ እንደውሉ ይፈፀምልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ2005(1),1678(ሐ),1719(2,1723) | 78398 | እነ አቶ ሽፈራው ደጀኔ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ሲሳይ አበበ | ጥቅምት 19/2005 | 51 |
| 15. | •የአላቂ ነገር ብድር ውል ጋር በተገናኘ፣ የመመለሻ ጊዜው በግልጽ ተለይቶ የተሰጠን የገንዘብ ብድር በተመለከተ አበዳሪው በውሉ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላ ተበዳሪው የብድሩን | 74950 | ወ/ሮ ዙብዳ ኑረ ኬርሰማ<br>እና<br>ወ/ሮ ሚሊዮን ዳግም ሙሴ | ህዳር 5/2005 | 55 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ገንዘብ እንዲመለስ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ፣<br>•የብድሩ ገንዘብ መክፈያ ጊዜው በተወሰነ የብድር ውል ስምምነት ገንዘብ የተበደረ ወገን የመክፈያ ጊዜው ካለፈበት (ካበቃበት) ጊዜ ጀምሮ ወለድ ለመክፈል ስምምነት ያልተደረገ ቢሆንም፣ በድሩን ከነ ህጋዊ ወለዱ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2482(2)(3),2483, 2489(1),1676, 2478 | | (አራት ሰዎች) | | |
| 16. | • ከውል አመስራረትና መቋቋም ጋር በተገናኘ ዝምታ በመርህ ደረጃ ውልን እንደመቀበል ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑና አንድ ውል፣ ተሻሽሏል ለማለት የሚቻለው ማሻሻያው አስቀድሞ በተደረገው የአፃፃፍ ስርዓት አይነት የተከናወነ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• የግልግል ጉባኤ አንድን ጉዳይ በማየት የዳኝነት መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው ተከራካሪ ወገኖች ከተስማሙበትና የሚፀና ወይም ዋጋ ያለው ግዴታ መኖሩን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1682,1683,1684,1722,2001<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 356(ሀ) | 63063 | ኢትዮ ቴሌኮም<br>እና<br>ፒቲኢ ኢንተርናሽናል ኢንኮፖሬትድ | ህዳር 03/2005 | 58 |
| 17. | ከውርስ ሽያጭና ከስጦታ ውል የመነጨን የባለቤትነት መብት አስመልክቶ በሚነሣ የንብረት ክርክር የይርጋ ጉዳይ በተነሣ ጊዜ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ለጉዳዩቹ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው የህግ ክፍል እና የህግ ይዘት | 71537 | እነ ወ/ሮ የሻረግ ከበደ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን | ታህሳስ 02/2005 | 68 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ | | | | |
| 18. | የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አመዘጋገብ ጋር በተያየዘ በተፈፀመ ስህተት ንብረቱን በመያዣ የያዘው ወገን የሚደርስበትን ጉዳትና ኪሣራ ኃላፊነቱን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመወጣት ስህተቱን የፈፀመው የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ጉዳትና ኪሣራውን በመያዣ በተያዘው ንብረት ዋጋ መጠን ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1640(2), 3052, 3053(1),3081 | 75743 | የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት ፍትህ ቢሮ፣ ዐ/ህግ<br>እና<br>እነ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 17/2005 | 72 |
| 19. | ከዋስትና ውል ጋር በተገናኘ ዋስ የሆነ ወገን በውሉ ላይ የተመለከተውን ፊርማ የእርሱ አለመሆኑን ወይም የውሉን ቃል በተመለከተ በመካድ በግልጽ ባልተከራከረበት ሁኔታ ውሉ በሁለት ምስክር ፊት የተደረገ አይደለም በሚል የሚቀርብ ክርክር የዋሱን ግዴታ ተፈፀሚነት የሚያስቀር ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1727(2)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.83,235 | 79907 | ልዩ የገንዘብ እገዛ ተቋም<br>እና<br>እነ ወ/ሮ የወይንሐረግ ትዕዛዙ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 02/2005 | 76 |
| 20. | ገቢ ለማስገኘት በተዘጋጀ ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በተደረገ ጨረታ ተሣታፊ በመሆን የጨረታውን ገንዘብ በመክፈል መሬት ተረክቦ ለልማት ለማዋል በሚል ጨረታው ተወዳድሮ የጨረታው አሸናፊ የሆነ ወገን ጨረታውን ካዘጋጀው አካል ጋር የውል ስምምነት እንዳደረገ የሚቆጠር በመሆኑ በጨረታ ያሸነፈበትን የገንዘብ መጠን ለአዘጋጁ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ፤ህ/ቁ.1771(1),1688(2),1757 | 76825 | ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>የአዳማ ከተማ የባኩ ሸነን ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት | ጥር 14/2005 | 79 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 21. | በብድር የሚሰጥ ገንዘብ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ሊያቋቁሙት ስለሚችሉት የወለድ ምጣኔ (መጠን)፣<br>የውል ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም ያዘገየ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ስለሚከፍለው የኪሣራ መጠን፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1803(2),1790(2),1800,2479(3),2488,2489 | 81857 | አቶ አብዱልቃድር ጁሐር<br>እና<br>አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ጥር 13/2005 | 82 |
| 22. | ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በመካከላቸው የሚነሣን አለመግባባት (ክርክር) በግልግል ዳኝነት እንዲያይ በሚል በውሉ የተሰየመ አካል በከሰመ ጊዜ ተዋዋዮች በጋራ ስምምነት ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት የሚያይ አዲስ አካል ለመሰየም ከሚችሉ በቀር አስቀድሞ የተሰየመው አካል በመክሰሙ ምክንያት ፍ/ቤት ጉዳዩን በግልግል ለማየት የሚችል አካል ለመሰየም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3336(1),3328(2),3337,3331,3325-3344,3329 | 80722 | የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፓርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>ዲ ኤም ሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር | ጥር 01/2005 | 86 |
| 23. | • ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተገናኘ የሚከፈል ክፍያ የሥራው ባለቤት የሆነው አካል በግንባታው ሂደት የሥራ ትዕዛዞችን እየሰጠ የሥራውን አካሄድ የመወሰንና ሥራውን በሚፈቅደው አይነት እንዲፈፀም የሥራ ተቋራጩን የማዘዝ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣<br>የሥራ ተቋራጩ ከሥራው ባለቤት ጋር የተደረገውን የግንባታ ሥራ ውል፣ በሥራው ባለቤት በተሰጡት ፕላኖች፣ ግንባታ ዲዛይን አይነቶችና የዋጋና የሥራ ማስታወቂያ መሠረት ግንባታውን የማካሄድ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የሥራው ባለቤት በግንባታው ሥራ ውል ሰነዱ ላይ ከተመለከተው ክፍያ ውጪ | 71972 | አቶ ካሣሁን አያሌው<br>እና<br>የምስራቅ ጎጃም ጎዛምን ወረዳ ጤና ጽ/ቤት | ጥር 1/2005 | 90 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በተጨማሪነት በባለቤቱ ፈቃድና ትዕዛዞች መሠረት ለተሠሩ ሥራዎች ክፍያ ለመክፈል አልገደድም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በህጉ አግባብ በባለቤቱ የተሰጡ ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዞች የሥራ ውሉ አካል ተደረገው የሚወሰዱ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3244,3225,(1)(2),3152(1),3266(1),3263,3265(3) | | | | |
| 24. | በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ከወጣው መመሪያ ቁ.3/2004 አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የንግድ ቤቱን በማከራየት ከሚያገኙት ገቢ ውጪ ሌላ ገቢ የሌለውና በእድሜ አዛውንት የሆነ ተከራይ የኪራይ ውል ሊቋረጥ የማይገባ ስለመሆኑ፣<br>መመሪያ ቁ.3/2004 አንቀጽ 6(1) | 83448 | እነ ወ/ሮ ሙሉወርቅ ኃ/ገብርኤል (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሪት ጽጌ መብራቱ | ጥር 30/2005 | 96 |
| 25. | በአንድ ውል የተመለከተን እዳ ለማረጋገጥ ሲባል አዲስ ሰነድ በተዋዋይ ወገኖች የማደራጀት ተግባር የውል መተካት አድራጐት ነው ለማለት የሚቻለው በሁለተኛው ውል በግልጽ የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>በባህር ላይ የሚደረግ የማጓጓዣ ውልን አስመልክቶ አንዡ ለውሉ ምክንያት የሆነው እቃ (ንብረት) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው አቤቱታ ዕቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣<br>የባህር ህግ ቁ.146,203<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1826,1828,1829(ሀ) | 80642 | የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>ባርጉባ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ታህሳስ 02/2005 | 102 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 26. | አንድ ውል የአስተዳዳር ውል ነው ለማለት በህግ ወይም በተዋዋይ ወገኖች ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ነው የተባለ እንደሆነ ወይም ደግሞ ተዋዋዮቹ ውል ያደረጉበት ጉዳይ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር ተያያዥና ለሥራ ውሉ አፈፃፀም የአስተዳዳር አካልን (ፍ/ቤትን) ተካፋይነት ያለማቋረጥ የሚጠይቅ መሆኑን እንዲሁም በአጠቃላይ የውሉን አይነትና ባህሪ፣ የውለታውን አይነተኛ ጉዳይ ብሎም የተዋዋዮችን ማንነት መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3132<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) | 80464 | ወይራ እንጨትና ብረት ሥራ ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማህበር<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ | ታህሳስ 16/2005 | 106 |
| 27. | • የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው በሚል የተደነገገው ድንጋጌ የይርጋ የጊዜ ገደብን የሚደነግግ ሣይሆን የመያዣ ውሉ ቀሪ የሚሆንበት ወይም በህግ ውድቅ የሚደረግበት (Lapse of Mortgage Right) ስለመሆኑ፣<br>የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘ ባንክ በመያዣው ላይ ያለው መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆነው የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት በመያዣ መብቱ መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 (1)(3) | 78444 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>አቶ ጥጋቡ ተፈራ | ጥቅምት 22/2005 | 109 |
| 28. | •በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት የጉዳት ኪሣራ እንዲከፈል በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በውሉ | 69797 | ወ/ሮ ሂሳላ ሱሌማን<br>እና | ታህሳስ 04/2005 | 113 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለዚሁ ዓላማ ተዋዋዮቹ ካመለከቱት የገንዘብ መጠን በላይ እንዲከፍል ለማስገደድ የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>•የመልካም ሥራ አፈፃፀም ቦንድ መሰረታዊ ዓላማ በውል የተመለከተው ጉዳይ እንደውሉ ስለመፈፀሙ (የሚፈፀም ስለመሆኑ) ለማረጋገጥ ስለመሆኑ፣<br>•አንድን ዕቃ ማቅረብ ጋር በተያያዘ የተደረገ ውልን አስመልክቶ በአቅራቢው በኩል ከእቃው ዋጋ ጋር በተገናኘ በመንግስት የታወቀ የዋጋ ግሽበት መከሰቱ አቅራቢው ውሉን ሙሉ ለሙሉ ለማቋረጥ የሚያስችለው በቂ ምክንያት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3183(2),3188(1),1731,1734,1732,1889 | | ጎንደር ዩኒቨርስቲ | | |
| **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | **120** |
| 29. | አንድ ለእዳ መክፈያነት በአፈፃፀም በጨረታ እንዲሸጥ በተደረገ ንብረት ጨረታ ላይ በመካፈል የጨረታው አሸናፊ ከሆነ በኋላ የጨረታ ሽያጩን ለመፈፀም ያልቻለ ወገን ንብረቱ በቀጣይ በወጣ ጨረታ ቀርቦ ሲሸጥ የተገኘው የሽያጭ ዋጋ ዝቅተኛ የሆነ እንደሆነ የመጀመሪያው ጨረታ አሸናፊ ለተከሰተው የዋጋ ልዩነት ለፍርድ ባለዕዳው በካሣ መልክ እንዲከፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429 | 72017 | አቶ ጐታ ኤጀታ<br>እና<br>አቶ ሙደሲር ረዲ | ጥቅምት 20/2005 | 121 |
| 30. | • በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ተቋማት (ወገኖች) በድሀ ደንብ ዳኝነት ሳይከፍል በፍ/ቤት ለመስተናገድ የሚያቀርቡት | 79555 | ቤተልሄም ፋርማሲ ቲዩካል ኃ/የተ/የግል ማህበር | ታህሳስ 02/2005 | 124 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጥያቄ ተቋሙ ከሚገኝበት የገንዘብ አቋም አኳያ ተገናዝቦ መታየት ያለበት ስለመሆኑና ተቋሙ የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም (Financial status) ለመለየት ተቀባይነት ስለሚኖረው የማስረጃ አይነት፣<br>• ለዳኝነት የሚከፈለውን ገንዘብ ለመክፈል አልችልም በሚል በድሀ ደንብ ለመስተናገድ የህግ ሰውነት የተሰጠው ተቋም የሚያቀርበው አቤቱታ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 467<br>የንግድ ህግ | | እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | | |
| 31. | • በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገባ የተደረገ 3ኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሣ ስለሚችለው የክርክር አይነትና አድማስ፣<br>• 3ኛው ወገን ሊያነሣ የሚችላቸው የክርክር ፈርጆች በአንድ በኩል ከተከሣሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሣሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሣሽ እግር ተተክቶ ተከሣሽ ለከሣሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፣ ኃላፊነት አለበት የሚባል ቢሆን እንኳን ሊከፈል የሚገባው የካሣ ክፍያ መጠን ላይ ከከሣሽ ጋር ንጽጽር በማድረግ መሟገት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሣሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር ስለመሆናቸው፡፡<br>• 3ኛ ወገን ጣልቃ ገብ በክርክር ሂደቱ መሟገት የሚችለው ከተከሣሽ ጋር ብቻ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ | 79465 | ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ<br>እና<br>እነ አቶ አገኘው ገረመው<br>(ሁለት ሰዎች) | ጥር 14/2005 | 126 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 አስፈላጊነት ተከታታይ ክስ ሳይኖር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በአንድነት እንዲታዩ በማድረግ የኃላፊነት መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት ለመስጠት ስለመሆኑ፣<br>•በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 መሠረት ጣልቃ የሚገባ ወገን ከመነሻውም ከተከሳሹ ጋር የህግ ወይም የውል ግንኙነት የለኝም በማለት ክርክር ያቀረበ እንደሆነ በመካሄድ ላይ ባለው ክርክር ተሣታፊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር ስለመሆኑና ይህን መሰል ክርክር ራሱን በቻለ ሌላ መዝገብ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43(1),76<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1896,1897,1908,1909<br>የንግድ ህግ ቁ.687,688,683 | | | | |
| 32. | የወጪና ኪሣራ ክፍያ ጉዳይ ሊስተናገድ ሊወሰን የሚገባው በዋናው ጉዳይ ፍርድ (ውሣኔ) በተሰጠበት መዝገብ ስለመሆኑ፣<br>• ወጪና ኪሣራ ክፍያን በተመለከተ ማን መክፈል እንዳለበት በዋናው ጉዳይ ላይ ተለይቶ ከተወሰነ በኋላ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት በተመለከተ ደግሞ ዋናው ፍርድ ባረፈበት መዝገብ የወጪና ኪሣራ ዝርዝር ቀርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ስለቀረበው የወጪና ኪሣራ አስፈላጊነት ስለመጠኑ እና በእርግጥም ወጪና ኪሣራ ስለመውጣቱ በተመለከተ የበኩሉን ክርክር ካቀረበ በኋላ የወጪና ኪሣራ ልኩ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ | 83701 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ ህንደያ እንድሪስ ወኪል አብዲ ዓሊ | ጥር 27/2005 | 129 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 183, 378, 462-464 | | | | |
| 33. | አንድን ክርክር ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ህጋዊነት አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክር ሊቀርብና ታይቶ ሊወሰን የሚገባው በዚያው ዋናው ጉዳይ በቀረበበት ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣ | 74890 | ወ/ሮ ሚስጢር ሰለሞን<br>እና<br>እነ አቶ ፍቃዱ ካሣሁን (አምስት ሰዎች) | ጥር 30/2005 | 131 |
| 34. | አንድ መዝገብ ላይ የተከሰሱ ሰዎች የኃላፊነት ምንጩ ከተለያየ የህግ ማዕቀፍ (ክፍል) በሆነ ጊዜ አንደኛው ወገን የተነሣው የይርጋ ክርክር በሌላኛው ወገን እንደተነሣ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣<br>በአንድ ክስ (መዝገብ) ተጣምረው በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት አለባችሁ ተብለው ከተከሰሱ ወገኖች መካከል አንደኛው ወገን የሚያነሣው የይርጋ መቃወሚያ ያለቅድመ ሁኔታ በሌላኛው ተጣምሮ የተከሰሰው ወገን ላይ ተፈፃሚነት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• በፍ/ብሔር ጉዳይ የአንድነትና የነጣላ ኃላፊነት ከተለያዩ የህግ ክፍሎች እና ከተለያዩ ምክንያቶች ሊመነጭ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1852<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.244(3),36 | 80723 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር<br>እና<br>እነ ዋቅቶሉ አብደሳ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 29/2005 | 134 |
| 35. | • ለተሰጠ የብድር ገንዘብ አመላለስ በመያዣ የተያዘ በኪሣራ የፈረሰ ማህበር (ድርጅት) ንብረት በሀራጅ ጨረታ የተሸጠ በመሆኑ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ለማየት | 84353 | ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር ሒሣብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች<br>እና | ጥር 02/2005 | 138 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>በመያዣ የተያዘውን ንብረት በባንኩ በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በባለዕዳው በኩል ቢሸጥ የተሻለ ዋጋ ያስገኝ ስለነበረ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>•በህግ የተቋቋመ ባንክ በብድር የሰጠው ገንዘብ በአዋጅ ቁ.97/90 እና 216/92 መሠረት አስቀድሞ ለብድሩ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ ከያዛቸው መያዣዎች መካከል አንዱን በመምረጥ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል፣ ለመሸጥ የተንቀሳቀሰበትን የመያዣ ንብረት ከመሸጥ ድርጊት ይታቀብ ይህም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልን በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ህግን ባለመከተል የፈፀመው ስህተት ቢኖርና በባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ግን ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለዕዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ሀራጁን ለማስቆም ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>የሰበር ችሎት የሚሰጠው አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም አንድ ክርክር የቀረበበት ጉዳይ (ድርጊት) ከተፈፀመ በኋላ ስለሆነ የተሰጠው የህግ ትርጉም በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449,224<br>አዋጅ ቁ.97/90 አንቀጽ 3,4 | | ወጋገን ባንክ አ/ማህበር | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ.216/92<br>አዋጅ ቁ.98/90<br>አዋጅ ቁ.2584 | | | | |
| 36. | • አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን መስጠቱ ፍርዱ ለከሣሽ በሚጠቅም መልኩ (መንገድ) የመወሰኑን ሁኔታ በአስገዳጅነት የሚያስከትል ነው ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• የማህበር ሲቀመንበርን ከስልጣን ለማንሳት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 70(ሀ) | 82427 | ዩኒስ ቡራሌ ሲጋል የራይስ ጫት ላኪዎች ማህበር<br>እና<br>አቶ አብዲ አልሚ መሐመድ | ጥር 27/2005 | 144 |
| **የንግድ ሕግ** | | | | | **147** |
| 37. | • የእሽሙር ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሌለው እንዲሁም በጽሁፍ መረጋገጥና ሌሎች የንግድ ማህበሮችን በተመለከተ የተደነገጉት የማስታወቅና የማስመዝገብ ሥርዓቶች የማይፈፀምበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ የእሽሙር ማህበርን አስመልክቶ ማህበሩ እንዲፈረስ በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዬችን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• የእሽሙር ማህበር የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርገው በሽሪኮቹ ስም ስለመሆኑና ሽሪኮቹም እንደተራ ተዋዋይ ወገኖች የሚታዩ ስለመሆናቸው<br>የንግድ ህግ ቁ. 212(1),272 | 76394 | አቶ ወርቁ ወ/ፃዲቅ<br>እና<br>እነ የአቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወራሾች (ሰባት ሰዎች) | ህዳር 18/2005 | 148 |
| 38. | •አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) የሚጨበጥና የማይጨበጥ | 80599 | ጀሽዋ ኢነድ ካሌቤ ኃ/የተ/የግል | ጥር 15/2005 | 151 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲሁም የሚንቀሣቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መብቶች ምን ምን እንደሆኑ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ስለመሆኑ<br>• አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ሥራውን የሚያከናውንበት የንግድ ቦታ ኪራይ መብት የማህበሩ ህልውና ጋር የሚያያዝ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>•የንግድ ድርጅቱ የፈረሰ ቢሆንም የንግድ ሥራውን ሲያከናውንበት የነበረውን ቦታ በሌላ ጉዳይ በፍርድ እንዲለቅ በተወሰነ ጊዜ የማህበሩ ሒሳብ ተጣርቶ አለመጠናቀቅ ቦታውን ላለማስለቀቅ ምክንያት ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣ | | ማህበር<br>እና<br>ወ/ሮ እንቁጣጣሽ አሰፋ | | |
| **ቤተሠብ** | | | | | **155** |
| 39. | በአንድ ቦታ ከተደረገ በኂላ በሌላ ጊዜ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ እንዲረጋገጥና ማህተም እንዲደረግበት የተደረገ የኑዛዜ ሰነድ በህጉ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት እንደተደረገ ኑዛዜ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.881,882 | 74734 | ወ/ሮ ትዕግስት ሽባባው<br>እና<br>እነ እህት አለማው ወርቁ<br>(ሁለት ሰዎች) | ህዳር 20/20085 | 156 |
| 40. | የኮንዶሚኒየም ቤትን በጋብቻ ወቅት እያሉ የደረሳቸው ባልና ሚስት የቤቱ ቅድመ ክፍያ በጋብቻ ወቅት ከተፈራ የጋራ ሀብት የተከፈለ እንደሆነና ቤቱን ለማሳመርና ለሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ከጋራ ሀብቱ ወጪ በማድረግ ጥቅም ላይ በዋለበት ሁኔታ ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ እንደሆነ ቤቱ ለተጋቢዎቹ፣ | 74451 | አቶ ደረጀ ማዘንጊያ<br>እና<br>ወ/ሮ ፍሬህይወት ጴጥሮስ | ጥቅምት 20/2005 | 160 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊከፋፈል ስለሚችልበት አግባብ፣<br>በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ቤተሰብ የመመስረት መብት በመጠቀም ጋብቻ የፈፀሙ ወንዶች እና ሴቶች በጋብቻው አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመን እንዲሁም በፍቺ ጊዜ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 35(1) | | | | |
| 41. | • የኑዛዜን ፎርማሊቲና የይዘቱን ህጋዊነት አስመልክቶ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ተቃውሞውን አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ወገን በሌላ ጊዜ በድጋሚ የኑዛዜው ይዘት ጋር በተገናኘ ተናዛዡ ከውርስ ነቅሎናል፣ እንዲሁም ሊደርሰን ከሚገባው ድርሻ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ደርሶብናል በሚል ኑዛዜው እንዲሻር የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• ኑዛዜ የህጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ነው በሚል በፍ/ቤት መጽደቅ ኑዛዜው መብታችንን ይነካል በማለት ክርክር የሚያቀርቡ ወገኖች ክርክራቸውን ለዳኝነት አካል ከማቅረብ የማይከለክል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.51, 216, 217<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123 | 77169 | እነ አቶ ተሾመ ገበየሁ<br>እና<br>ወ/ሮ ሊሻንወርቅ ገበየሁ | ጥር 17/2005 | 163 |
| 42. | • የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ቀደም ሲል ጋብቻ የነበረው እንደሆነ የጠፋው ሰው መመለስ በመጥፋት ውሣኔው የፈረሰውን ጋብቻ እንደገና ተመልሶ ህይወት እንዲዘራ (እንዲፀና) የማድረግ ውጤት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ | 74791 | ወ/ሮ ውቢት ሕሩይ<br>እና<br>የሀዋሣ ከተማ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት | ጥር 17/2005 | 167 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | •በፍ/ቤት የተሰጠ የመጥፋት ውሣኔ መሻር በመጥፋት ውሣኔው መሠረት የፈረሰን ጋብቻ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ (ግለሰቡ ከተመለሰበት ቀን ጀምሮ) መልሶ እንዲቋቋም (እንዲፀና) ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.170,171 | | | | |
| 43. | አንድ ወራሽ የወራሽነት መብት በሌለው ንብረት ላይ ከህግ ውጪ የወራሽነት ሠርተፍኬት መያዙ በተረጋገጠ ጊዜ ይኸው ማስረጃ እንዲሰረዝ አቤቱታ ሊቀርብ ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.998(1) | 73247 | አቶ ልዑል ኪዳነማርያም<br>እና<br>እነ ሰብለ ኪዳነማርያም (ሶስት ሰዎች) | ጥር 14/2005 | 171 |
| **ጉምሩክ/ግብር/ ታክስ** | | | | | **174** |
| 44. | • በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቅቆ ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ወይም ወደ ውጪ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>• "የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠናቀቀ" ማለት ስለሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 66(1), 2(17),66(29),66(2) | 71070 | ተሸአብ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | መስከረም 21/2005 | 175 |
| 45. | የተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው በተሽከርካሪው የተፈፀመ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ህግን የመጣስ ወንጀል ከራሱ እውቀት ወይም ፈቃድ ወጪ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደሆነ የተፈፀመው ወንጀል ክብደት እየታየ የገንዘብ መቀጮ ከፍሎ | 76976 | የጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሊሻን ከተማ ገብሬ | መስከረም 22/2005 | 178 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተሽከርካሪው ሊለቀቅለት (ላይወረስ) የሚችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 109(1)<br>የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መመሪያ ቁ.50/2003 አንቀጽ 6(2) | | | | |
| 46. | የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር ያለህጋዊ እውቅናና ፈቃድ ማስወጣት የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ድርጊትን የፈፀምኩት ባለማወቅ ነው በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለውና ህግን አለማወቅ ይቅርታ የማያሰጥ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99<br>አዋጅ ቁ. 591/2000 አንቀጽ 20(3)<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(2),25,23(2),81(1)(3) | 80296 | አቶ ሳምሶን መንግስቱ<br>እና<br>የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ጥር 30/2005 | 180 |
| **ንብረት** | | | | | **184** |
| 47. | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ህጋዊነትና ተቀባይነት ጋር በተናኘ የምስክር ወረቀቱ ሊሰጥ የቻለው የንብረት ባለሀብትነት መብትን ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እንዴት መተላለፍ እንዳለበት በህጉ የተመለከተውን ደንብና ሥርዓት ሳይከተል ስለሆነ የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆን የህግ ግምት መውሰጃ የሆነው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ቀሪ ነው፣ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት | 75414 | ወ/ሮ ዋሪቴ ቡቡሳ<br>እና<br>እነ የጎልጀታ ከተማ አስተዳደር (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 22/2005 | 185 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊረጋገጥ የሚችል የዳኝነት ጥያቄ እንጂ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195,1196 | | | | |
| 48. | • በአንድ ወቅት የነበረን የተገነባ የመንገድ ደረጃ መነሻ (መሠረት) በማድረግ በመንገዱ ግራ ቀኝ አዋሣኝ በሆነ ይዞታ ላይ ተገቢውን ርቀት በመጠበቅ ንብረትን ያፈራ ሰው በሌላ ጊዜ የመንገዱ ደረጃ ከፍ እንዲል በመደረጉ የተነሣ በአዋሣኝ ይዞታው ላይ ግለሰቡ ያፈራቸው ንብረቶች ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ፣ ጉዳት ያደረሰው ወገን ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት (የሚኖርበት) ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 65/1936 አንቀጽ 2(ሀ)<br>አዋጅ ቁ. 66/1936 አንቀጽ 1(ለ)<br>አዋጅ ቁ. 455/1997,የኤ.ፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(8) | 75343 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ በላይ ሀሰን | ህዳር 17/2005 | 188 |
| 49. | • አንድ ሰው የሌላ ሰው ንብረት ይዞ ሲጠቀም ከቆየና ንብረቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ንብረቱን ከጥፋት ወይም ከብልሽት ለማዳን ሲል ተገቢውን ወጪ ያወጣ እንደሆነ ይኸው ወጪ በህጋዊ ባለሀብቱ እንዲተካለት ለመጠየቅ የሚችለው ወጪው የግድ አስፈላጊ ከሆነና በቅን ልቦና የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• ወጪው በክፉ ልቦና የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ግን እቃውን (ንብረቱን) እንዲመልስ የተደረገው ሰው እንዲተካለት የጠየቀውን ወጪ መጠን ዳኞች ሊቀንሱት ወይም ጭራሹንም ሊያስቀሩት የሚችሉ ስለመሆኑ፣ | 81081 | ወ/ሮ ፍሬህይወት መብራህቱ ገ/መድህን<br>እና<br>እነ አቶ መብራህቱ ገ/መድህን /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 13/2005 | 191 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | •በንብረቱ (እቃው) ላይ የተደረገው ወጪ «በክፉ ልቦና የተደረገ ነው» የሚባለው ወጪው በተደረገበት ጊዜ (ወቅት) ወጪው እንዲተካለት የሚጠይቀው ሰው ንብረቱን (እቃውን) ለባለቤቱ ለመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያወቅ እንደነበር ወይም ማወቅ ይገባው የነበረና ርትዕም ሲያስገድድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2172(1),2171(1),2168,2169 | | | | |
| 50. | • የመኪና ሽያጭ ውል መደረጉን (መኖሩን) ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት፣<br>• የመኪና /ተሽከርካሪ/ ባለሀብትነት (ስመ ሀብት) እንዲተላለፍለት የሚጠይቅ ሰው ሊያቀርባቸው ስለሚገቡና ተቀባይነት ስላላቸው ማስረጃዎች<br>አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ፣<br>• አከራካሪ ሆኖ የቀረበን አንድ ፍሬ ነገር ማስረዳት ስለሚቻልበት የማስረጃ አይነት አግባብነት ባለው ህግ በተለይ የተቀመጠ ግለጽ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ አቅርቦ ጉዳዩን ለማስረዳት ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1186(1),(2),2001(1)<br>ስለ ተሽከርካሪ መለያ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁ.681/2002 አንቀጽ 6(3)(4) | 81406 | እነ አቶ አህመድ ኢብራሀም (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አመሀ ተ/ወይኒ | ጥር 13/2005 | 195 |
| 51. | • የመሬት ባለ ይዞታ የሆነ አርሶ አደር ይዞታውን ሳለበት እዳ ለ3ኛ ወገን በመያዣነት ለመስጠት ወይም በስጦታ የቤተሰብ | 79394 | አቶ አብደላ ኢብራሒም<br>እና | ጥቅምት 06/2005 | 199 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አባል ላልሆነ ሰው ለማስተላለፍ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>•በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ እና/ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻው ውጤት የሌለውና ፈራሽ ስለመሆኑ፣<br>የውሉ መሠረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 130/99<br>አዋጅ ቁ.89/89 አንቀጽ 2(3)<br>አዋጅ ቁ. 456./97 አንቀጽ 8(2),1) | | አቶ ኡሶ አብዲ | | |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | | 202 |
| 52. | የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳዳር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሚኒኬሽን ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እንዲሁም ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታን ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሚኒኬሽንና በኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑና በዚህም የተነሳ በቸልተኝነት ግንባታ በማከናወን ጉዳት ያደረሰ ወገን በኃላፊነት የሚጠየቅ ስለመሆኑ፣ | 77238 | ኢትዮ ቴሌኮም<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ተፈራ | ህዳር 03/2005 | 203 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ.464/97 አንቀጽ 3(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027(1),2035(1),2028(1),2091<br>አዋጅ ቁ.49/89 አንቀጽ 23(1) | | | | |
| | **የዳኝነት ሥልጣን** | | | | **207** |
| 53. | • አንድ ሰው በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰን የሚችለው ከህግ የመነጨ መብት ያለው መሆኑን በክሱ ውስጥ በዝርዝር በፍሬ ነገር ደረጃ ማመልከት የቻለ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>• ሀይማኖታዊ (መንፈሣዊ) ትምህርት ለመስጠትና ለማስልጠን በሚል ከሚቋቋሙ ተቋማት ጋር በተገናኘ በተማሪነት ማን እንደሚመለመል፣ ምን ምን መስፈርቶች ሊሟሉ እንደሚገባ፣ የመስፈርቶቹ መሟላትና አለመሟላት እንዲሁም በተቋሙ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ከትምህርት አቀባበል ሂደት ወቅት ሊገልጿቸው ስለሚገቡ የዲሲፕሊን ጉዳዩች ወዘተ በሀይማኖት ተቋማቱ የሚወሰን ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮችን መደበኛ ፍ/ቤቶች አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>• የግለሰብ ፍትህ የማግኘት መብት በፍ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለው በፍርድ ሊያልቁ የሚባቸው ጉዳዩችን በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 | 77479 | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅድስት ሥላሴ መንፈሣዊ ኮሌጅ<br>እና<br>አቶ አሰግድ ሣህሉ | ጥቅምት 06/2005 | 208 |
| 54. | •የፌዴሬሽን ምክር ቤት የኢፌዴሪ ህገ መንግስትን ለመተርጐም ባለው ስልጣን ተጠቅሞ የሚሰጠው ውሣኔ | 43511 | እነ የአቶ ዋሲሁን መኮንን ሚስትና ወራሾች /8 ሰዎች/ | ጥቅምት 23/2005 | 211 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የመጨረሻና ጉዳዩ በሚመለከተታቸው አካላት መከበርና መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ፣<br>• የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ የሚቀርብለትን አቤቱታ ህጋዊነት መርምሮ በመወሰን ሂደት ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል (quasi judicial body) እንደመሆኑ መጠን በህገ መንግስቱ የተጠበቁትን ፍትህ የማግኘት፣ የመሰማትና በእኩል ሚዛን የመታየት (የመዳኘት) መብት በሚያስከበር መልኩ ክርክሮችን ሊያስተናግድና ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 62(1),37<br>አዋጅ ቁ. 251/93 አንቀጽ 3(1),56(1)<br>አዋጅ ቁ. 87/86 አንቀጽ 8,9<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337, 336, 339 | | እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | | |
| 55. | የአቃቤ ህግ ሙያን በሹመት የሚያከናውኑ ሰዎች ጋር በተገናኘ ቅጥር፣ ዝውውርና የደረጃ እድገትን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል የአቃቤያነ ህግ አስተዳደር ጉባኤ ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>ደንብ ቁ.24/99 አንቀጽ 46(3), 41, 44, 2 (4)<br>አዋጅ 568/2000 አንቀጽ 2(7),3,10(1),4,5<br>የአ/አ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ.6/2000 አንቀጽ 2(5)(ሐ) | 75034 | አዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>አቶ መኮንን ተክሉ | ህዳር 03/2005 | 216 |
| 56. | የፍ/ቤቶች የግዛት ስልጣን በዋነኛነት መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበት ቦታ ለተከራካሪ | 75788 | እነ አቶ በረከት ኃ/ኪሮስ (ሶስት ሰዎች) | ህዳር 05/2005 | 220 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት ሲሆን የሥረ ነገር ስልጣን መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣ የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደትና መጠን እንዲሁም የጉዳዩን የውስብስብነት ደረጃ ስለመሆኑ፣<br>ፍርድን የማስፈፀም ጉዳይ በስረ ነገር ክርክር ተረጋግጠው የፍርድ ሀይል ያገኙትን የተከራካሪ ወገኖች መብቶችና ግዴታዎች በሥነ ሥርዓት ህጉ የተደነገገውን የአፈፃፀም ስርዓት ተከትለው እንዲፈፀሙ ከማድረግ ውጪ አዲስ መብትና ግዴታ የሚቋቋምበት ሂደት ስላለመሆኑና የማስፈፀም ስልጣን በመርህ ደረጃ የፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣንን የሚከተል ስለመሆኑ፣<br>አስፈላጊ እና ተገቢ በሆኑ ሁኔታዎች ሥረ ነገሩን የወሰነ ፍ/ቤት በአፈፃፀም ጉዳዮችን በውክልና የሥረ ነገር ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፍ ስለመቻሉ፡<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371, 372, 9, 10 | | እና<br>አቶ ጎይቶም ኃ/ኪሮስ | | |
| 57. | የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ (የኮንትራት) ሠራተኞች ቅጥር ጋር በተገናኘ በሠራተኛ እና በቀጣሪው መካከል የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ የመደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ ክስም ሆነ በይግባኝ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 22(3) ,2(1)<br>የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ | 81963 | አቶ አስፋው ጉደታ<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ታህሳስ 03/2005 | 224 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 58. | በአዋጅ ቁ. 515/1999 መሠረት የተቋቋመና የሚተዳደር የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ ተቋሙ በራሱ ገቢ የሚተዳደር በመሆኑ ምክንያት አዋጅ ቁ. 377/96 ን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96<br>አዋጁ ቁ. 515/99<br>አዋጅ ቁ. 553/99 አንቀጽ 6(1), 14(2)(ለ)<br>አዋጅ ቁ. 545/99 | 80005 | የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ቦጋለ ዱንፋ | ጥቅምት 09/2005 | 226 |
| 59. | • የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ መብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ክርክርን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ስለመሆኑ፣<br>• የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የቀረበላቸውን ጉዳይ በህጉ አግባብ ያስተናገዱና ውሣኔ የሰጡ መሆኑን የማረጋገጥና የመቆጣጠር ኃላፊነትና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.9,231<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10(22)<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2(1)<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 142, 147 | 83425 | አብጀታ ሻላ ሶዳ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አብጃታ ሶዳ አሽ መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር | ጥር 02/2005 | 228 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 345/95<br>አዋጅ ቁ. 209/55<br>አዋጅ ቁ. 715/2003<br>ደንብ ቁጥር 202/2003 | | | | |
| | | **ወንጀል** | | | **233** |
| 60. | በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር ጋር በተገናኘ ፖሊስ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ላይ የሚያደርገው ምርመራ የይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጠው ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ.221 106(1), 420(2), 271 (1) (ሠ) 219 (2) | 77097 | እነ አቶ ሀይላይ ተክሉ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የመቀሌ ከተማ ሰሜን ምድብ ዐ/ህግ | ጥቅምት 20/2005 | 234 |
| 61. | • አንድ ተከሳሽ የተከሰሰበትን የወንጀል ክስ ይዘት በሚገባ ተረድቶና አድራጎቱን በተመለከተም እንደቀረበበት የወንጀል ክስ በዝርዝር መፈፀሙን ገልፆ በማመን የእምነት ቃሉን ሰጥቷል በሚል መነሻ በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ በአግባቡ ተሰጥቷል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>• ፍ/ቤቶች ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ በተመለከተ በድርጊቱ አፈፃፀም ረገድ የገለፀውን ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታ በመዝገብ ላይ ባለማስፈር በደፈናው ክሱን አምኗል በማለት የሚሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ.134(1)<br>የወ/ህ/አ.23 | 77842 | አቶ ሳሚ ሁሴን<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ታህሳስ 03/2005 | 237 |
| 62. | ተከሳሽ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ | 73514 | ተስፋዬ ጡምሮ | ህዳር 06/2005 | 240 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርባቸው ስለሚችላቸው መከራከሪያዎች<br>ተከሳሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት የሚያቀርባቸው መቃወሚያዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130 ላይ የተመለከተቱት ጉዳዩች ጋር ብቻ በተገናኘ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ የማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ በነበረው ህግ ከተመለከተው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑና ዳኞች ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ክስ የቀረበበት ድርጊት ወንጀል ስለመሆኑ የሚደነግገው ህግ ፀንቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉ ስለመሆኑ፣<br>ፍ/ቤቶች በዐ/ህግ የቀረበ የወንጀል ክስ በህገ-መንግስቱና በወንጀል ህጉ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የተቀመጡ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 5(2) ,13(1), 22(1 )<br>የወ/ህ/አ. (414/96)3,402,419,5(2)<br>የወ/ህ/ቁ.(214/74) | | እና<br>የፌዴራል የሥነ ምግባርና<br>የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት (ICCPR) አንቀጽ 15(1)<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130(2)(1) | | | | |
| 63. | • አንድ የንግድ ድርጅት (ማህበር) የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግንና ማሻሻያውን ተላልፏል በሚል በወንጀል ጥፋተኛ ሊሰኝና ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>•የህግ ሰውነት የተሰጠው (legal personality) ድርጅት የወንጀል ተካፋይ ሊሆን የሚችልበት አግባብ፣<br>• የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው ኃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም ህጋዊ ግዴታን በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ስለመሆኑና የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተከስሶ የጥፋተኛነትና የቅጣት ወሣኔ እስከተሰጠበት ድርስ ድርጅቱ የወንጀሉ ተካፋይ እንደሆነ የሚቆጠር ስለሆነ ጥፋተኛ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 34(1),(2)<br>አዋጅ ቁ. 285/95 አንቀጽ 56(1) | 74237 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አብካለ እንደሻው ጠቅላላ የንግድ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር | ጥቅምት 19/2005 | 245 |
| 64. | ፍ/ቤቶች በወንጀል ረገድ የሚሰጧቸው ማናቸውም ውሣኔ በወ/ህ/አ. 2 የተደነገገውን የህጋዊነት መርህ መሠረት በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ | 75387 | እነ አቶ ወርቁ ፍቃዱ (ሁለት ሰዎች)<br>እና | ጥር 17/2005 | 249 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በሚል ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉት በወንጀል ህግ በግልጽ የተደነገገ ድንጋጌ የተመለከተ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>በወንጀል ጉዳይ አንድ ንብረት (ሀብት) እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሊወሠን የሚችለው ንብረቱ (ሀብቱ) አንድን ሰው ለወንጀል ሥራ እንዲያነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳው ወይም ደግሞ ወንጀሉን ለፈፀመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው ወይም ሊሠጠው የታቀደን ማንኛውም ጥቅም የተመለከተ ንብረት (ሀብት) ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ ወይም ንብረቱ (ሀብቱ) የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም ያገለገለ ወይም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች ጋር የተያያዘ ወይም የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 98,100,140, 2(1) (2) | | የቤ/ጉ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ህግ | | |
| 65. | • በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በቅጣት አወሣሠን መመሪያው የተሸፈነ እንደሆነ ቅጣቱ በመመሪያው አግባብ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• በወ/ህ/አ 539(1)(ሀ) ድንጋጌ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ሊቀነስለት የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 539(1)(ሀ)<br>የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁ.1/2002 አንቀጽ 16(7) | 82572 | መሪጌታ ፍቅረማርያም ካሴ<br>እና<br>የቤንች ማጂ ዞን | | 252 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ባንክና ኢንሹራንስ | | | | 255 |
| 66. | መድን ሰጪ የሆነ አካል በመድን ውሉ ለተመለከተው አደጋ ብቻ ለመድን ገቢው የመድን ሽፋን ለመስጠት የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁ. 663(1),665(1) | 76977 | ኒያላ ኢንሹራንስ (አ.ማ)<br>እና<br>እነ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ)<br>(ሁለት ሰዎች) | ህዳር 07/2005 | 256 |
| | አፈፃፀም | | | | 260 |
| 67. | በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰው ሰው ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ንብረቱ በቅጣት ለመንግስት እንዲወረስ በተወሰነ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ ከአጥፊው (ወንጀለኛው) ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወትና መተዳደሪያ ሊውል የሚገባውን ድርሻ ለመወሰን ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>በውርስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ከተወሰነው የአጥፊው (የወንጀለኛው) ሀብትና ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወት መተዳደሪያ ሊውል የሚገባው ድርሻ ሊሸፍናቸው የሚገባው የወጪ አይነቶችና መጠናቸው፣<br>• የአጥፊው (ወንጀለኛው) ጋር ጋብቻ የመሠረተ ሰው እንዲወረስ ከተወሰነው ንብረት ግማሽ ድርሻ የነበረው መሆኑን መሠረት በማድረግ በአፈፃፀም የሚያነሣው የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ጥያቄው እንደ መብት አቤቱታ ሊቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(ለ)(መ), 98(3) (ለ) | 79860 | ወ/ሮ ራኬብ መለሰ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ህዳር 06/2005 | 261 |
| 68. | • ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ በአንድ በቀረበ የዋና ጉዳይ | 81616 | ወጋገን ባንክ አ.ማ. | ጥር 15/2005 | 265 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክርክር ሒደት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ንብረት በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ በአፈፃፀም ደረጃ በተጠቃሹ ንብረት ላይ አፈፃፀም እንዲቀጥል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• ቀደም ሲል በዋና ጉዳይ ክርክር በፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲታገድ የተደረገ መሆኑ የታወቀ ንብረት ላይ በድጋሚ በተመሳሳይ ንብረት ላይ መብትን ለማስከበር በሚል በሌላ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ ጥያቄ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | | እና<br>እነ ወ/ሮ ሠላማዊት ጥላሁን /ሁለት ሰዎች/ | | |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | **268** |
| 69. | ባለ ሶስት አውታር (three dimention) ቅርጽ ሥራ ከባለቤቱ ፈቃድና ፍላጐት ውጪ በወረቀት ላይ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ማድረግ የቅጂ መብት ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 34(4) | 78856 | የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወዳጆችና ቤተሰቦች ማህበር<br>እና<br>አቶ ኤሊያስ አሰጋኸኝ | ታህሳስ 15/2005 | 269 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | **274** |
| 70. | ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተገናኘ በወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ የተጣለበትን ቅጣት ፈጽሞ ያጠናቀቀ ሰው በፍርድ ቤት መሰየም በግለሠቡ የጡረታ መብት ላይ ስለሚኖረው ውጤት በመሰየም ሊገኝ የሚችለው መብት ግለሰቡ ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን መብት ሳይሆን ግለሰቡ ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ፊት ሊጠበቅለት የሚገባውን መብት በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣ | 61221 | አቶ አከለ ምህረቱ<br>እና<br>የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | መስከረም 22/2005 | 275 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የመንግስት ሰራተኛ የነበረና የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሠው በወንጀል ጉዳይ ተከስሶና ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በፍ/ቤት ቢያንስ የ3 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት በመሆኑ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ የተደረገ ሠው ከቅጣቱ በኂላ በፍ/ቤት መሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን የጡረታ መብቱን መልሶ ለማግኘት የማያስችል ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 231,235(1),232<br>አዋጅ ቁ. 209/55<br>አዋጅ ቁ. 5/67<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 52/1/ | | | | |
| 71. | ከጡረታ መብት ጋር በተገናኝ በሠራተኞች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በኤጀንሲው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ሠራተኛ ቅሬታውን ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ በፍሬ ነገር ረገድ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ቅሬታ ያለው ሠራተኛ አቤቱታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀጽ 56(1) (4), 57 | 72928 | አቶ አበራ ኪዳኔ<br>እና<br>የጋሞ ጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት | ጥቅምት 09/2005 | 279 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 72. | ከጡረታ መብት አበል ተጠቃሚነት ጋር በተገናኘ የእድሜ አቆጣጠርና ውጤቱን በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያለው የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በውሣኔው ቅሬታ ያለው ወገን ለኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>በኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጥ ውሣኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለው በማለት አቤቱታ ያለው ሠራተኛ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀጽ 4(1),54(3),56(4)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343, 9, 231 | 80964 | የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ አቶ አበረ ቦከን (ሶስት ሠዎች) | ጥቅምት 23/2005 | 281 |
| 73. | የመንግስት ዩኒቨርስቲ መምህራንን በተመለከተ ከዲሲፕሊን ግድፈት ጋር በተገናኘ የሚሰጥ ውሣኔ በአስተዳደር ፍ/ቤት በይግባኝ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>አዋጅ ቁ. 515 /99 አንቀጽ 2(8),22(3),32(3)<br>አዋጅ ቁ. 650/2001 አፀከት 44(ነ) | 78945 | ደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ<br>እና<br>መምህር ባዬ ዋናያ የዳ | መስከረም 22/2005 | 286 |
| 74. | በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ በሌላ በኩል የጉምሩክ ደንብ በመተላለፍ ወንጀል ባለቤቱ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦበት ተሽከርካሪውም በመንግስት እንዲወረስ ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ በህግ ፊት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊፈፀም ስለሚገባው ጉዳይ | 81215 | ወጋገን ባንክ (አ.ማ.)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ጥር 03/2005 | 290 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ ከመያዣው በኋላ በኮንትሮባንድ ወንጀል ምክንያት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን በፍ/ቤት የመጨረሻ ፍርድ ባረፈበት ጊዜ ባለመያዣው በተሽከርካሪው ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት እንዲሁም የውርስ ትዕዛዙ (ውሣኔው) ተፈፃሚ ሊደረጉ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2828, 2857(1), 3059<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(1)<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91(2) | | | | |
| 75. | የሥራ ግዴታን ካለመወጣት ጋር በተገናኘ ሠራተኛ የሆነ ሰው ከአሰሪው የተረከበው ንብረት ላይ ጉዳት እንዲከሰት በማድረጉ ወይም ንብረቱ እንዲጐድል (እንዲጠፋ) በማድረጉ ምክንያት በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በተመሣሣይ ጉዳይ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በፍትሐብሔር ሊጠየቅ ስለመቻሉ፣<br>ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበትን ንብረት በተመለከተ በፍትሐብሔር ተጠያቂ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 515<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149 | 78414 | የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና<br>እነ አቶ ቶላ መገርሣ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 07/2005 | 295 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 76. | አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበስብ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ፡<br>አዋጅ ቁ. 621/2001 አንቀጽ 2(2),(3)(4),14(5), 14(2), 6, 90, 111(2), 112,108,110,<br>ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18(3),10(2),36 | 74036 | የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ እና<br>የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ | መስከረም 23/2005 | 299 |

www.abyssinialaw.com

# አሠሪና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ. 78536

ታህሳስ 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- በደሌ ቢራ አክሲዮን ማህበር ነገረ ፈጅ አቶ ታዬ ይገዙ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አልማው ቤዛ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በፍርድ ባለመብት በሆነው በአሁኑ ተጠሪና በፍርድ ባለ እዳ በሆነው በአሁኑ አመልካች መካከል በነበረው የአፈጻጸም ክስ ክርክር የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በመ/ቁ/37192 ያቀረቡትን ክርክር በ29/06/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በመመርመር የሰጠውን ትዕዛዝ የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በማጽናቱ ነው፡፡

የአፈጻጸም ትዕዛዙም የፍርድ ባለመብቱ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ቀደም ሲል የተወሰነ ከመሆኑም በላይ በመ/ቁ. 37299 የፍርድ ባለመብቱ በበደሌ በዕቅድና ምርታማነት አሰራር ማሻሻያ ቡድን አስተባባሪነት መመደቡ አግባብነት ያለው መሆኑን ፍርድ ቤቱ የወሰነ ስለሆነና ውሳኔውም በይግባኝ እስካልተለወጠ ድረስ የስራ መደቡን፣ ደመወዝ፣ የሥራ ቦታ እና የስራ መጀመሪያ ቀን በመጥቀስ የስራ ምደባ ደብዳቤ የፍርድ ባለዕዳው ሊሰጥ ይገባል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ለዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 36405 በቀን 17/08/2003 ዓ.ም. ተጠሪው የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ የወሰነውን የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ. 69498 ጥር 02/2004 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ ያጸናው ሲሆን ከዚሁ ውሳኔ ውጪ እንዲሁም ተጠሪው በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በሁለት የሥራ መደቦች ተወዳድረው የተቀመጡትን መስፈርቶች ማለፍ አለመቻላቸው ተረጋግጦ እያለ በእቅድ ምርታማነትና አሰራር ማሻሻያ ቡድን አስተባባሪነት መደብ እንዲሰጣቸው የታዘዘው ህግን የሚጻረር ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች በፍርዱ መሰረት ምደባ ማድረጉን ገልጾ የሚከራከር ቢሆንም ምደባውን ያደረገው ከደረጃና ከደመወዜ ዝቅ በማድረግ ነው፡፡ ምደባው በመሰረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ የተሰጠ

ነው በማለት ያቀረበው ክርክርም ቢሆን መጀመሪያውኑ ከሥራና ደመወዝ እንድገለል ወስኖ የነበረው አስቀድሞ አመልካች ያስጠናው የሰው ሀይል ምደባ እና ደመወዝ እስኬል በመዋቅር ተጠንቶ ሥራ ላይ ከዋለ ከ5 ወር በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተደረገ ምደባ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሱ ክርክሩን በማጠናከር አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ቀደም ሲል የፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/36405 በሰጠው ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 69498 ባጸናው መሰረት ፈጽሟል? ወይስ አልፈጸመም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመ/ደ/ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መዝገብ በሰጠው ፍርድ ላይ በአሁኑ የሰበር አመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በመ/ቁ. 69498 ጥር 02 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ፍርድ በማጽናት የስራ ውሉ የተቋረጠው በአመልካች ህገ ወጥ ድርጊት ነው በማለት የ6 ወራት ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ መወሰኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ለዋናው ክስ መነሻ የነበረውም ተጠሪው ከሚሰሩበት ከአዲስ አበባ የሽያጭ ማስተባበሪያ ቢሮ በገበያ ጥናትና ማስታወቂያ ክፍል ሀላፊነት እንዲነሱ ተደርጎ በደሌ ሄደው በ29/02/2003 ዓ.ም. ሪፖርት እንዲያደርጉ ታዘው በተባለው ጊዜ ሪፖርት ሳያደርጉ ዘግይተዋል በሚል በአመልካች በመሰናበታቸው ሲሆን ይህ በ23/02/2003 ዓ.ም. የተጻፈው ደብዳቤ ይዘትም ደረጃቸውና ደመወዛቸው ሳይቀነስ በደሌ በሚገኘው የአመልካች ዋና መ/ቤት በእቅድና አሰራር ማሻሻያ ቡድን አስተባባሪነት መመደባቸውን የሚያሳይ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት የተቻለ ሲሆን ይህ ችሎትም ተጠሪውን አመልካች ያሰናበታቸው በህገ ወጥ መንገድ ነው በማለት የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ካጸናው በኋላ አመልካች እንደ ፍርዱ መፈጸሙን ለመግለጽ ሁለት ደብዳቤዎችን ለተጠሪው ስለመጻፉ ተረጋግጧል፡፡ ደብዳቤዎቹ የተጻፉት ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም. እና መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም. ሲሆን ጥር 12/2004 ዓ.ም. ከተጻፈው በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተጠሪው በሚመደቡበት የሥራ መደብ ሥራ እንዲጀምሩና የ6 ወራት የተጣራ ደመወዝም እንዲከፈላቸው የሚል መሆኑን ነው፡፡ መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ/ም ከተጻፈው ደብዳቤ የተረጋገጠው ደግሞ ቀደም ሲል ያገኙት በነበረው ያልተጣራ ደመወዝ ብር 3745 ላይ ብር 35 ተጨምሮ የደመወዝ ማስተካከያ ተደርጎላቸው ያልተጣራ ደመወዝ ብር 3780 እያገኙ በንብረት ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ተመድበዋል የሚል መሆኑን ነው፡፡ ከእነዚህ አመልካች ከዋናው ፍርድ በኋላ እንደፍርዱ መፈጸሙን ለመግለጽ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ደግሞ ከዋናው ፍርድ በፊት አመልካች ወደ በደሌ ተመድበው ሲላኩ እንዲሰሩ ከተደረገው የሥራ መደብ የሚለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ የፍርድ ባለ እዳው ፍርዱን ለመፈጸም የማያስችለው በቂ ምክንያት አለመኖሩን ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ያረጋገጠ እንደሆነ ፍርዱ እንዲፈጸም ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 386(3) እና 392(1) ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ያለ በቂ ምክንያት እንደፍርዱ አለመፈጸሙን ከጻፋቸው ደብዳቤዎችና በአፈጻጸም ወቅት ካቀረባቸው የቃል ክርክሮች የሥር ፍርድ ቤቶች በማረጋገጥ ተጠሪው ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ ወደ በደሌ ሲላኩ በተሰጣቸው የስራ መደብና ደረጃ አመልካች እንዲመድባቸው በሰጡት ትእዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/37192 በቀን 29/06/2004 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝና የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በ/ቁ/116259 በቀን 01/08/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ተጠሪውን ቀድሞ በተመደቡበት በበደሌ ዋና መ/ቤት በዕቅድና ምርታማነት አሰራር ማሻሻያ የቡድን አስተባባሪነት የሥራ መደብ እንዲመልሳቸው ሲሉ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በአፈጻጸም መ/ቁ.37192 ተጀምሮ የነበረው የአፈጻጸም ክስ ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 77134

ጥቅምት 8 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወሰኔ የህክምና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ዶ/ር ክብረወሰን አለማየሁ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች ከህግ ውጭ የሥራ ውሌን ያቋረጠ ስለሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ በተደጋጋሚ ሠዓት የማያከበር፣ ከታካሚዎች ጋር ጠብ የሚፈጥር በመሆኑ ከሥራ ተሰናብቷል ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ ተጠሪ የተካሚዎችን የግል ሚስጥር ለሶስኛ ወገኖች አላግባብ የሚገልጽና የሙያ ሚስጥር የማይጠበቅ መሆኑ፣ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ከሚመጡ ታካሚዎች ጋር ጠብ መፍጠሩና ሠዓት ስለማያከብር ታካሚዎች ለካርድ የከፈሉትን ገንዘብ አስመልሰው የሄዱ መሆናቸው ተመስክሮበታል፡፡ ተጠሪ ይህንን በመከላከያ ማስረጃ አላስተባበለም፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪ በተደጋጋሚ የሥራ ሠዓት ባለማክበሩ በሥራው ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሷል የሚለውን አተረጓጎም የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1) ሀ እና (ለ) አቀራረጽና ይዘት የተከተለ አይደለም፡፡ የህክምና ዲስፐሊንን አለማክበር በሥር ውላቸው በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል ምክንያት አይደለም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች የካቲት 9 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የድርጅቱን መልካም ስምና ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የሙያ ስነ ምግባር በማክበር ሥራውን የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ከሙያ ሥነ ምግባር ውጭ የሆኑ ተግባራትን እንደፈፀመ ተረጋግጦ እያለ የሥራ ውልን ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት አይሆንም በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ አመልካች ያቀረበቻው ምክንያቶች የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ አይደሉም የሚል ይዘት ያለው መልስ ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቀርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው የህግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ደንብን በመተላለፍ በአመልካች የህክምና ተቋም የህክምና አገልግሎት ያገኙ ታካሚዎችን ሚስጥር የሚገልጽ ስለመሆኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው የሰው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ለምርመራ የቀረቡለትን ተካሚዎች የተሳደበ መሆኑንና ከታካሚዎች ጋር ጠብ የፈጠረ መሆኑ በወቅቱ በታካሚነት ቀርበው የነበሩ ሰዎች የምስክርነት ቃላቸውን በሥር ፍርድ ቤት ሰጥተዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ደንብ በመተላለፍ በአመልካች መልካም ስምና ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበውን ማስረጃ ሲመዘን የሥር ፍርድ ቤት ስህተት ሰርቷል የሚል የፍሬ ጉዳይ የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ የሌለው መሆኑን ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ በተለይም ተጠሪ  የአመልካቹ ሠራተኛ ሆኖ ሲሰራ ያገኘውን የአመልችን ደንበኞች ምስጥር ለማይመለከታቸው ሶስተኛ ወገኖች የሚገልጽ መሆኑና የሥራ ውሉ ሊቋረጥ አካባቢ የአመልካችን አንዲት ደንበኛ ስም በመግለጽ ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ አለባት ብሎ ለሶስተኛ ወገን ሲገልጽ የሰማች መሆኑን የአመልካች ምስክርና የተጠሪ የሥራ ባልደረባ አስረድታለች፡፡ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደ አመልካች ሄደው ተጠሪ እንዲመረምራቸው ቀርበው የነበሩ ታካሚዎች ተጠሪ የሰደባቸውና በማበሳጨት ለጠብ ጋብዟቸው የነበረ መሆኑን በማረጋገጥ የመስከሩ ሲሆን፣ በዚህ ምክንያት ወደ አመልካች የህክምና አገልግሎት ለማግኘት መሄዳቸውን እንዳቆሙ መስክረዋል፡፡ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለውን የአመልካች ምክስሮች ቃል ታዓማኒነትና ክብደት  ያለው መሆኑን ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባለው የሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛው ፍርድ ቤትም የአመልካች ምስክሮች ቃል ታዓማኒነት እና ክብደት የሌለው ነው የሚል ውሣኔ አልሰጠም፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በአመልካች ምስክሮች የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ እውነትነት ያላቸው ቢሆኑም የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በሚል ምክንያት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ለውጦታል፡፡

ተጠሪ የአመልካች ደንበኞች ታካሚዎችን የግል ሚስጥር መግለፁና የህክምና አገልግሎት ለማግኘት የመጡ ታካሚዎችን መሣደቡ የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ቃል ታዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ መሆኑ አከራካሪ ባልሆነ፣ እነዚህ ተጠሪ በሥራ ሂደት ፈፀማቸው የተባሉ ጥፋቶች የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው ነጥብ አመልካች ከሚሰጠው የህክምና ግልጋሎት ባህሪና ካለበት ኃላፊነት፣ ተጠሪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግና በሙያ ሥነ ምግባር ደንቡ ከተጣበለት ግዴታና ኃላፊነት እንደዚሁም የተጠሪ አድራጎት በአመልካች ላይ ከሚያስከትለውን ጉዳት አንፃር መመዘን ያለበት ነው፡፡

ማንኛውም ሠራተኛ በስራ ውሉ ላይ የተመለከተውን ሥራ ራሱ የመሥራትና በሥራ ውሉና በሥራ ደንቡ መሠረት በአሠሪው የሚሰጠውን ትእዛዝ የመፈፀም ግዴታ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13

www.abyssinialaw.com

ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም ተጠሪ የተመደበበትን የህክምና ሥራ ሲሰራ ለሙያ ሥነ ምግባር ደንቦች ተገዥ በመሆን፣ ህሙማኑን በአክብሮት ማነጋገርና የማስተናገድ እንደዚሁም የህሙማኑን የግል ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ተጠሪ ይህንን የሙያ ሥነ ምግባርና ደንብ የማስከበርና በአመልካች ድርጅት ውስጥ በሠራተኝነት ከቀጠለ አመልካች የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ የተሰጠውን ፈቃድ ለማሣገድ ወይም ለማሰረዝ የሚችል ምክንያት ስለመሆኑ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 174/1986 ዓ.ም አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የአመልካችን ደንበኞች የግል ሚስጥር አለመጠበቁና ለማይገባቸው ሶስተኛ ወገኖች መግለፁ እንደቀላል ጥፋት የማይታይና በወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል የሚችል የወንጀል ድርጊት መሆኑን ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 399 እና አንቀጽ 400 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ ሆኖ ሲሰራ እንደፈፀማቸው የተረጋገጡት ድርጊቶች በውጤት ደረጃ የአመልካችን መልካም ስምና ዝና በማጉደል ፈቃድ ባገኘበት የህክምና አገልግሎት የመስጠት የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዳይሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ አመልካች ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ ለአመልካች ከመንግስት የተሰጠውን ፈቃድ ሊያሣግድ ወይም ሊያሠርዝ የሚችል ጥፋት መሆኑን ከላይ ከገለጽነው የደንብ ቁጥር 174/4986 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የፈፀማቸወ ጥፋቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) መሠረት በሚያክማቸው ህሙማንን የመሣደብና የጠብ ጫሪነት ተግባር የፈፀመ መሆኑ የሚያሣዩና፣ የህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ደንብን በመጣስ፣ የአመልካችን መልካም ሥምና ዝና እንደዚሁም ጥቅምና ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ ተግባራት ናቸው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ) ድንጋጌም አመልካች ከሚሰጠው የህክምና ግልጋሎት ልዩ ባህሪና ተጠሪ ከሚጠበቅበት ከፍተኛ የሆነ የሥነ ምግባር ብቃት አንፃር ባለማክበሩ፣ በአመልካች ላይ የደረሰውን ወይም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት በማያሻማ ሁኔታ መተርጎም ያለበት መሆኑን ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማ ከድንጋጌው ይዘትና ስለህክምና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ የወጡ የህግ ማእቀፎችን ይዘት በመመርመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የፈፀማቸው ጥፋቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) እና (ሸ) የሚሸፈኑና አመልካች የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ ጥፋቶች የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችሉ አይደለም በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 1(ረ) እና (ሸ) ድንጋጌዎች በተመሣሣይ መንገድ በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በህግ አግባብ ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኝ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 72341

ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የማኀበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ታዬ አበራ - ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ደመወዝ መቀበሉ ሲረጋገጥ የጡረታ መብት ተጠቃሚ መሆኑ የሚቀጥል መሆን ያለመሆኑን ጥያቄውን የሚያቀርበው ወገን ክሱን ቀሪ የሚያደርገው የይርጋ ዘመን መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በጡረታ መለያ ቁጥር ወ/515371 በሆነው ከግንቦት 01 ቀን 1984 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ የጡረታ አበል እየወሰዱ ባለበት ሁኔታ ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀጥረው የመንግስት ደመወዝና የጡረታ አበል በመቀበል ላይ መሆናቸውን ገልፆ ይህ የተጠሪ ተግባር በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/1955 አንቀጽ 30(2) እና በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46(1) መሰረት ሕጋዊ ያለመሆኑን ጠቅሶ ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ በየወሩ ብር 105.00 የወሰዱት ለሰባ አምስት ወራት ያህል ተባዝቶ የሚመጣውን ውጤት ብር በድምሩ ብር 7,575.00 (ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰባ አምስት ብር) እንዲሁም ከሐምሌ 01 ቀን 1996 ዓ.ም. እስከ ሀምሌ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ድረስ በየወሩ ብር 115.50 የወሰዱት ታስቦ የሚመጣውን ድምር ብር 4,045.50 (አራት ሺህ አርባ አምስት ብር ከሀምሳ ሳንቲም) ከወጪና ኪሳራ እንዲሁም ከሕጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሠጡት መልስም ከጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጋር የፈፀሙት የቅጥር ውል መኖሩን ሳይክዱ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ፣ መብቱ ቀሪ የሚሆነውም በአዲስ መልክ ሲቀጠሩ የሚያገኙት ደመወዝ ከብር 200.00 በላይ ከሆነ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ክስ ተጠሪ ከተቀጠሩበትና የጡረታ አበል መቋረጥ ከሚገባበት ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ከአስራ ሁለት አመታት በላይ ቆይቶ የቀረበና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎች አኳያ ሲታይ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አመልካች ዳኝነት እየጠየቀ ያለው ያለአግባብ የተከፈለውና ተጠሪ የበለፀጉበትን ገንዘብ ነው የሚል ምክንያት ይዞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ዘመን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) ስር የተመለከተው

መሆኑን ገልጾ የአመልካችን ክስ በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለጉዳዩ ይርጋ የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ተጠሪ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥረው ደመወዝ እየተቀበሉ ባሉበት ጊዜ የተቀበሉትን የጡረታ አበል ሊመልሱ አይገባም ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 209/1955 አንቀጽ 30(2) እና አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46(1) ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርመሮም ተጠሪ ያላግባብ የተከፈለውን ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት አመልካች ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) ድንጋጌ መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረጉት የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46/1/2/ የጡረታ አበል አመላለስን በተመለከተ የይርጋ ጊዜ የለውም በሚል መነሻ በሌሎች ሕጐች ያሉትን የይርጋ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ የአዋጅ ቁጥር 209/1955 እና አዋጅ ቁጥር 345/1995 ስር ያሉት ድንጋጌዎች ከሕግ ውጪ የተከፈለ የጡረታ ገንዘብ ይመለስ ጥያቄ መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ አላስቀመጡም፡፡ ይህ ማለት ግን ጥያቄው የሚቀርብበት ጊዜ ገደብ የለውም ወደሚለው ድምዳሜ የማያደርስ ስለመሆኑ ከይርጋ ፅንሰ ሀሳብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ስለ ይርጋ የጊዜ ገደብ በግልፅ ያስቀመጠው ድንጋጌ ከሌለ በአገራችን የሕግ ስርአት የተዘረጋው መፍትሔ በውል ሕጉ የተመለከቱት ደንቦች የሚፈፀሙ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ያላግባብ መበልፀግን በተመለከተ የሚደነግጉ ድንጋጌዎች የይርጋ ደንብ የይርጋ ጊዜን በተመለከተ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ከሌለ ተፈፃሚ የሚሆንበትን አግባብ የሚያሳይ ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክፍያው ያላግባብ ተወስዷል የሚል ነው በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) ድንጋጌን ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አለው በማለት የስር ፍርድ ቤት ያስቀመጠውን ድንጋጌ መለወጡ የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በአስር አመት የይርጋ ጊዜ ጉዳዩ መታየት እንደአለበት የሰጠው ምክንያት ተገቢ ሁኖ የተገኘ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ይርጋው መቆጠር የሚጀመርበትን ጊዜ በተመለከተ ግን ተጠሪ ከተቀጠሩበት ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ ነው በማለት የወሰደው ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የጡረታ አበሉንና በቅጥር የሚያገኙትን ደመወዝ በአንድ ላይ መቀበሉን በተከታታይ ሲፈጸሙበት ቆይተው ገንዘቡን ከሕግ ውጪ ሲቀበሉ የቆዩ መሆኑን አመልካች በማረጋገጥ የጡረታ አበሉን ለተጠሪ መክፈል ያቆመው ከነሐሴ 30 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ሲሆን ተጠሪ ከሕግ ውጪ የወሰዱትን የጡረታ አበል እንዲመልሱ ክስ ያቀረበው ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ/ም ነው፡፡ ስለሆነም የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን አቆጣጠሩም መሆን ያለበት ወደኋላ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላ ሲቆጠር አስር አመት ያላለፈበት የጡረታ ገንዘብ ክፍያ ለአመልካች ሊመለስ

የሚገባው ይሆናል፡፡ አመልካች የይርጋው መቆጠር ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1847 መሰረት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር በየጊዜው የሚከፈለውን ገንዘብ የሚቀበል ሰው ክፍያው ሲቋረጥ መብቱን ለማስከበር የሚችልበትን የይርጋ ጊዜ ለመቁጠር የሚያስችለውን አግባብ የሚያሳይ በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካች ክፍያ ተቀባይ ሳይሆን ከሕግ ውጪ የከፈለውን ገንዘብ እንዲመለስለት የሚጠይቅ በመሆኑ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ክሱ ከተመሰረበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላ አስር አመት ያላለፈውን የጡረታ ገንዘብ መኖር ያለመኖሩን ስንመለከት አመልካች ገንዘቡ እንዲመለስ የጠየቀው ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ/ም በብር 105 ሂሳብ ለሰባ ወራት ይህል፣ እንዲሁም ከሐምሌ 01 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1998 ዓ/ም ድረስ ደግሞ ለሰላሳ አምስት ወራት ያህል በየወሩ ብር 115.50 የተከፈለውን የጡረታ አበል ክፍያ ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ከጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ኋላ አስር አመት ሲቆጠር አስር አመት የማይልፍበት የጡረታ አበል ክፍያ ከጥቅምት 19 ቀን 1993 ዓ.ም. ወዲህ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ከጥቅምት 18 ቀን 1993 ዓ/ም ጀምሮ ወደ ኋላ ያለው ማለትም ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 18 ቀን 1993 ዓ/ም ድረስ ያለው የጡረታ አበል አስር አመት ያለፈበት በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ሊሆን የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ የይርጋው ጊዜ ያላለፈ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለማድረግ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) በሚያዘው መሰረት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለስ የሚቻል መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህንኑ ለመፈፀም ግን ተከሳሽ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የሚነጥር የፍሬ ነገር ክርክር ማቅረባቸውን ያለማቅረባቸውን ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ አይነተኛ አላማ ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር የተጠሪን ክርክር ስንመለከተው የፍሬ ነገር ክርክር ሳይሆን የሕግ ክርክር በመሆኑ ለዚህ ነጥብ ሲባል ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ ከውጪ፣ ጊዜና ጉልበት አንፃር ተገቢ ሁኖ ስላልተገኘ የሕግ ጥያቄውን በዚህ ችሎት እልባት መስጠቱ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት ጥያቄ ተጠሪ ለአመልካች ሊመልሱት የሚገባው የጡረታ አበል ክፍያ መጠን ምን ያህል ነው? የሚል ነው፡፡

በቅድሚያ ተጠሪ በቅጥር የሚያገኙት ደመወዝ ከ200.00 በታች በመሆኑ የጡረታ አበሉን ለመመለስ በሕግ እንደማይገደዱ ገልፀው ያቀረቡትን ክርክር ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

በመሠረቱ በዚህ ጉዳይ ክስ የተመሠረተው ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም. በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 345/1995 ከመሆኑም በላይ በአዋጅ ቁጥር 209/1955 እና 345/1995 የተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት ጥበቃ ሊደርግላቸው እንዲሚገባ በአዋጁ አንቀጽ 59(1) ስር ተመልክቷል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 209/1995 አንቀጽ 30/2/ እና የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 52(1) ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲነበቡ ደግሞ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ መልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ከተቀጠረ ከደሞዙ እና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ እንደሚኖርበት በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሥራው ደሞዝ የሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ መሆኑን እንጂ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነት ይሁን በቋሚነት እንዲሁም ደመወዙ ከጡረታ አበል ያነሰ ይሁን የበለጠ የሚል መስፈርት ከግምት ውስጥ አያስገባም፡፡ የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46(1) ሲታይም የአገልግሎት የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት እንደገና በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ደመወዝ ማግኘት ከጀመረ የጡረታ አበሉ ይቋረጣል በማለት በአስገዳጅነት

www.abyssinialaw.com

ያስቀመጠ ሲሆን ሕጉ ቅጥሩ ቋሚ ይሁን ጊዜያዊ ወይም በኮንትራት ስራ እንዲሁም በቅጥር የተገኘው ደመወዝ መጠንን አነስተኛ መነሻ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም። የሕጉ ግልጽ አነጋገር የጡረታ ባለመብቱ እንደገና በሌላ መንግስታዊ ስራ ተቀጥሮ ከጡረታ ገንዘብ በተጨማሪ ሌላ ደመወዝ ካገኘ የጡረታ መብቱ የሚቆም መሆኑን ነው የሚያሳየው። በመሆኑም ደመወዝ የሚያስገኝ መንግስታዊ ቅጥር እስከተፈጸመ ድረስና ሕጉ ያስቀመጠው የቅጥር አይነትና የደመወዝ መጠን ልዩነት እስከሌለ ድረስ ሕጉ ተግባራዊ ሲደረግ የሚገባው ለማንኛውም የቅጥር ዓይነትና የደመወዝ መጠን እንጂ ለአነስተኛ ደመወዝ ሲሆን አይገባም ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም። የሕጉ መንፈስ ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በመ/ቁጥር 25899፣ በሰ/መ/ቁጥር 37111 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ሰጥቷል። በመሆኑም ይህ ጉዳይም በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት መታየት ያለበት በመሆኑ ተጠሪ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥረው ደመወዝ ማግኘታቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ደመወዙ ከብር 200.00 በታች ነው በማለት በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው አይደለም። ይህ ውጤት የሚኖረው የጡረታ አበል ወይም ደመወዝ ከሁለት አንዱን በመመረጥ ለመመለስ ነው እንጂ በጠቅላላው አመልካች ጥያቄውን ለማቅረብ ለመከልከል አይደለም። ተጠሪ ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ ተቀጥረው ሲያገኙት የነበረው ደመወዝ ከጡረታ አበል ያነሰ ስለነበር ይህንኑ ለመመለስ የሚፈልጉ መሆኑን ገልጸው አልተከራከሩም። በመሆኑም ተጠሪ ሊመልሱ የሚገባው የጡረታ አበሉን መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል።

እንግዲህ ተጠሪ የጡረታ አበሉን መመለስ አለባቸው ከተባለ መጠኑ ሊለይ የሚገባው ነው። በዚህም መሰረት ከሐምሌ 01 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ድረስ ያለው የጡረታ አበል ገንዘብ መጠኑ ብር 4,042.50 ሲሆን ይህ ጊዜ ከላይ በተመለከተው የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር የአስር አመት የማይልፈበትን ጊዜ በግልጽ ያካተተ በመሆኑ እንዳለ ሊያዝ የሚገባው ሲሆን ከ1/10/1989 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 30/12/1995 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ተጠሪ የተቀበሉት ብር 7,575.00 ግን የአስር አመት ጊዜ የሚልፈበትን ጊዜ አካትቶ የተሰራ በመሆኑ ይሔው ጊዜ ሊለይ የሚገባው ነው። በዚህም አግባብ ከ01/10/1989 እስከ ጥቅምት 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለው የአርባ ወራት የጡረታ አበል መጠኑ በወርሃዊ የጡረታ አበል ብር 105.00 ሲታሰብ ብር 4,200.00 (አራት ሺህ ሁለት መቶ ብር) የሚመጣ በመሆኑ ይኼው ገንዘብ በአስር አመት ይርጋ ሊታገድ የሚገባው ሁኖ ቀሪው ከሕዳር 01 ቀን 1993 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ ለሰላሳ ሶስት ወራት ለተጠሪ የተከፈለው ገንዘብ ብር በወር ብር 105 ሲታሰብ ብር 3,465.00 (ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር) በይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ ለአመልካች ተጠሪ ሊመልሱት የሚገባ ሁኖ ተገኝቷል።

ሲጠቃለልም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ይርጋ የአስር አመት ጊዜ በመሆኑና ይህ ጊዜ መሰረት ተደርጎ ሲሰላም አመልካች ከተጠሪ ሊመለስለት የሚገባው የገንዘብ መጠን በድምሩ ብር 7,665.00 (ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት ብር) ሁኖ ተገኝቷል። በመሆኑም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሠጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ደግሞ የድምዳሜ ክፍሉ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

www.abyssinialaw.com

**ው ሣ ኔ**

1. በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03844 ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 118234 ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. ምክንያቱ ተለውጦ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ዘመን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች መሰረት አስር አመት ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ከክሱ ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ የአስር አመት ይርጋ ያላለፈውን ብር 7,665.00 (ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት ብር) ከሕግ ውጪ የወሰዱት በመሆኑ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 83012
ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዝዋይ ሮዝ ድርጅት

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ፋንቱ ያሲን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በአዳሚ ቱሉ በወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን የሰበር ተጠሪ የአፈጻጸም ከሳሽ አመልካች ደርጅት ደግሞ የአፈጻጸም ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28572 በቀን 24/01/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረት የአፈጻጸም ተከሳሽ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ይታዘዝልኝ የሚል ነው፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም፡- በ17/04/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት የተቻለው የፍርድ ባለመብቷን የፍርድ ባለዕዳው ወደ ሥራ እንዲመልሳቸው መወሰኑን እንጂ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ባለመሆኑ የፍርድ ባለዕዳው የፍርድ ባለመብቷን ወደ ሥራ መመለሱን በ17/04/2004 ዓ.ም. ለፍርድ ቤቱ ከጻፈው ደብዳቤ የተረጋገጠ በመሆኑ እንደፍርዱ ፈጽሟል በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአፈጻጸም ከሳሽም በወረዳው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ቅሬታ፡- ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 በ24/01/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የፍርድ ባለዕዳው ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ የወሰነ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም ወደ ሥራ እንድመለስ ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ በሞዴል 85 መልስ ሰጪው እንዲያይዝ ካደረገ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ መልስ ሰጪው ይመልሳት ይላል እንጂ ስለ ክፍያው በግልጽ የሚለው ነገር የለም በማለት ገንዘቡ እንዲለቀቅ ማዘዙ ተገቢ ባለመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመለስ ከተወሰነበት ቀን አንስቶ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ መልስ ሰጪው እንዲከፍል ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

መልስ ሰጪ ድርጅትም ቀርቦ ባለመከራከሩ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቀደም ሲል በመ/ቁ. 28527 በቀን 17/09/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ከመረመረ በኋላ በውሳኔው ይግባኝ ባይዋ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ከመባሉ በስተቀር ከሥራ ከታገዱበት ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው

ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያልተወሰነ በመሆኑ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

የፍርድ ባለመብትም በስር ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ/ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር እንዲሁም የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ቁጥሩ 28527 የሆነውን መዝገብ አስቀርቦ በመመርመር በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ውሳኔ በመ/ቁ/28527 ተደርጎ በነበረው ክርክር አመልካች ተጠሪዋን ከሥራ በህገ ወጥ መንገድ ስለማሰናበቱ ካለማስረዳታቸውም ሌላ ተጠሪውም አመልካችን አለማሰናበታቸውን ጠቅሶ በመከራከሩ ፍርድ ቤቱ በ24/01/2004 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ወደ ሥራ እንዲመለሱ ሲወስን ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በግልጽ የወሰነው ነገር ባይኖርም ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ሲል ውሳኔ መስጠቱ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንጽ 43(5) ጋር ተገናዝቦ ሲታይ አንድ በህገ ወጥ መንገድ ከሥራ ተሰናብቷል በሚል ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚወሰን ሠራተኛ በመጀመሪያ የሥራ ክርክር ችሎት እስከ 6 ወር ደመወዝ፣በይግባኝ የታዬ እንደሆነ ደግሞ እስከ አንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ሊወሰን እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን በዚህ በተያዘውም ጉዳይ የፍርድ ባለመብት ወደ ሥራ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ይመለሱ ተብሎ መወሰኑ ከዚሁ ቀን ጀምሮ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ማለትም እስከ 24/01/2004 ያለው ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ የተወሰነ መሆኑን ስለሚያስገነዝብ ከ17/09/2003-24/01/2004 ያለው ውዝፍ ደመወዝ ታስቦ ሊከፈላቸው ይገባል በሚል የወረዳው ፍርድ ቤትና ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሠጡትን የትዕዛዝ /የውሳኔ ክፍል ሽሯል፡፡

አመልካችም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ተጠሪ የሥራ ውሌ በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ክስ ቢያቀርቡም ይህንኑ በማስረጃ ያላረጋገጡ በመሆናቸው በአመልካች ህገ ወጥ ድርጊት ውሉ አልተቋረጠም በማለት ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የህግ ስህተት የለበትም በሚል ካጸናው በኋላ በአፈጻጸም ወቅት ግን በውሳኔ ያልተገለጸውን ውዝፍ ደመወዝ አመልካች ሊከፍል ይገባል ሲል መወሰኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 በሰጠው ውሳኔ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን በፊት ያለውን ጊዜ በመጥቀስ ከዚሁ ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ አመልካች ወደ ሥራ እንዲመለስ የወሰነው ያልተከፈለውን ውዝፍ ደመወዝ አመልካቹ እንዲከፍል በሚል ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ላለመክፈል ሲል ያቀረበው ክርክር ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡ ተጠሪዋ ላቀረቡት መልስ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ለተጠሪዋ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፍል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካችና ተጠሪን በዋናነት እያከራከራቸው ያለው ለአፈጻጸም ክሱ መነሻ የሆነው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 በቀን 24/01/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ነው፡፡ በዚህ ፍርድም ተጠሪዋ

www.abyssinialaw.com

ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ከመወሰኑ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በግልጽ አለመጠቀሱን የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ አንድ የአፈጻጸም ክስ የቀረበበት ሰው ደግሞ ሊገደድ የሚችለው እንዲፈጸም በቀረበው ፍርድ መሰረት መሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 378 እና ከተከታይ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ እንዲሁም ፍርዱን የሚያስፈጽም ፍርድ ቤት በፍርዱ ወይም በውሳኔው መሰረት ከሚያስፈጽም ውጪ በአፈጻጸም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት አለመኖሩን ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/29344 እና በሌሎችም በርካታ መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይም በዋናው ፍርድ አመልካች ወደ ሥራ ተጠሪዋን እንዲመልሳቸው ከመወሰኑ በተጨማሪ ውዝፍ ደመወዛቸውን እንዲከፍል የተወሰነ መሆን ስላለመሆኑ መመርመር የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመ/ቁ 28527 በቀን 24/01/2004 ዓ.ም. በተሰጠው ፍርድ ተጠሪዋ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የተወሰነው ከ17/09/2003 ጀምሮ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ፍርዱ ከተሠጠበት ከ24/01/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ተጠሪዋ ወደ ሥራ እንዲመለሱ መወሰን የሚችል ቢሆንም ወደ ኋላ ያለውን ጊዜ ወስዶ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የወሰነው በዚህ ችሎት እምነት ለተጠሪዋ ከዚሁ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በሚል ነው፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ውዝፍ ደመወዝ ለተጠሪዋ እንዲከፈላቸው ለመወሰን የማይገባ መሆኑን ቢያምን ኖሮ በ24/01/2004 በተሰጠ ፍርድ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የሚልበት ምክንያት ስለማይኖር ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተሰጠውን ፍርድ ደግሞ አመልካች ውዝፍ ደመወዙን ለመክፈል በቂ ምክንያት የለም የሚል ከሆነ በይግባኝ አቅርቦ ሳያስለውጥ ከቀረ በኋላ በአፈጻጸም ወቅት ውዝፍ ደመወዝ በዋና ፍርድ ላይ አልተወሰነም ሲል መከራከሩ የፍርዱን ይዘት መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ በተገለጹት ምክንያቶች የተነሳ አመልካች ለተጠሪዋ ከ17/09/2003 ዓ.ም.ጀምሮ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ የወሰነው ተገቢ ሆኖ በማግኘታችን በአብላጫ ድምጽ በውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በሚል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.147105 በቀን 28/12/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ አጽንተናል፡፡
2. ለተጠሪዋ አመልካች ከ17/09/2003 ዓ.ም. እስከ 24/01/2004 ዓ.ም. ያለውን ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍላቸው የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት የወሰነው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የልዩነት ሐሣብ

የፍርድ አፈፃፀም ሥርዓትን አመራር አስመልክቶ ከላይ ከፍ ሲል የተገለፀውን ፍርድ ለመስጠት የአብላጫው ድምፅ በሰጠው የሕግ ትርጉም ባለመስማማት በፍርዱ ላይ ስማችን በተራ ቁጥር 1 እና 5 ላይ የተመለከተው ዳኞች የፍርዱ አፈፃፀም ሊመራ የሚገባበትን የተለየ የትርጉም መስመር እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የመጨረሻ ፍርድ የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሣኔ እንደምርኩዝ አድርጎ የጠቀሰው በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ ድንጋጌ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ በእራሱ ፍርድ የአማርኛ ትርጉም ገጽ 2 የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ እንደገለፀው ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁ. 28527 መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም ፍርድ ሲሰጥ የአሁን አመልካች ተጠሪን ሕገ- ወጥ በሆነ መንገድ ከሥራ አሰናብቷታል የሚለውን መሠረት በማድረግ አይደለም ይልቁንም የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ሕገ- ወጥ ድርጊት የተሰናበተች ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጠችም፤ አሠሪውም እኔ ከሥራ አላናበትኳትም በማለት መከራከሩን ሁሉ መሠረት አድርጎ ወደ ሥራዋ ትመለስ በማለት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የተነሣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ ወደ ሥራ ትመለስ የተባለችበትን ምክንያት ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፍርድ የተገለፀውን እና በማስረጃ የተረጋገጠውን የፍሬ ነገር ጉዳይ በውል ካለመገንዘብ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አለው የሚለውን የአዋጁን አንቀጽ 43/5/ በመመርኰዝ ምክንያት ከተሳሳተ መነሻ ተነስቶ ወደ ተሳሳተ የፍርድ መደምደሚያ ሊደርስ እንደቻለ የጉዳዩ አመጣጥ አስረጂ ነው፡፡

ምናልባት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት እየወሰነ የአሁን ተጠሪ ከግንቦት 17/2003 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሥራዋ ትመለስ ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው አከራካሪ ነጥብ ከላይ የተመለከተውን የአዋጁን አንቀጽ 43/5/ ድንጋጌ ከጉዳዩ ጋር በማመሳሰል ለጉዳዩ ተፈፃሚነት እንዲኖረው አድርጎ ነው ከተባለም ይኸው የሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃውን ጠብቆ በቀረበለት የአፈፃፀም ጉዳይ ላይ በአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን የፍርድ ይዘት አድማስ በማስፋት እና ለጥጦ ለመተርጎምና ይህንኑ የተለጠጠ ትርጉም ሁሉ ጨምሮ ፍርድን ለማስፈፀም የሚያስችል ሥልጣን በአገራችን የህግም ሆነ የዳኝነት አመጣጥ ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

ይልቁንም የአንድ ፍርድ ይዘት አሻሚ ሆኖ እንደ አሁኑ ያለውን ክርክር እንዳያስነሳ ሙግት ተከናውኖ ካበቃ በኋላ ፍርድ እንዴት ሊሰጥ እንደሚገባው እና ምን ምን ሁኔታዎችን ማካተት እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182 እና 183 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህም ፍርድ ሊሰጡ የሚችሉት ፍ/ቤቶች ዋናውን ጉዳይ ተመልክተውና አከራክረው በጉዳዩ ላይ ዳኝነት በመስጠት በጎንዮሽም ሆነ ከታች ወደ ላይ በተዘረጋው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር በቀጥታም ሆነ በይግባኝ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገረ ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡

በዚህ አኳኋን የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 372 መሠረት ሥልጣን ያላቸው የአፈፃፀም ችሎቶች ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶች በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን አልተሰጣቸውም፡፡

በዚህ ረገድ በኦሮሚያ ክልል የአዳሜ ቱሉ ወረዳ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በቀረበላቸው ጉዳይ "ፍርዱ" የአሁን ተጠሪ ከግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ አሠሪው ወደ ሥራዋ ይመልሣት በሚል በግልፅ ከመቀመጡ በቀር ከውዝፍ ደሞወዝ ጋር በሚል ስላልተወሰነ ከፍርዱ ይዘት አድማስ በመሻገር ለማስፈፀም የሚያስችል ሥልጣን የለንም በማለት የሰጡት ትርጉም የፍርድ አፃፃፍ ሥርዓት በየትኛው ፍ/ቤት እንደሚከናወንና የአፈፃፀም ችሎት ሥልጣን ውሉን እስከምን እንደሆነ ስለአፈፃፀም ሥርዓት አመራር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአኳያው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀረበለት የአፈፃፀም መዝገብ ላይ ፍርዱ ከተሰጠበት ዕለት ወደ ኋላ በመመለስ ሠራተኛው ወደ ሥራ ትመለስ በማለት መወሰኑ /መፈረዱ ትመለስ ከተባለቼበት ዕለት ጀምሮ ውሣኔ እስከተሰጠበት ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ይከፈላት ለማለት ካልሆነ በቀር የተለየ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም በማለት ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነውን የፍርድ ይዘት በማስፋት የሰጠው ትርጉም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው በሕግ ባልተሰጠው ሥልጣን ከመሆኑም በላይ ይህ ዓይነት የአተረጓጎም መስመር ስለዋናው ጉዳይ ፍርድ አሰጣጥ እና ፍርዱን ስለማስፈፀም ሥርዓት አስመልክቶ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ጉዳዮች በሥርዓት እንዲመሩ በማድርግ በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ጊዜና ወጭ እንዲቋጩ ማድረግን ታሳቢ አድርጐ የያዘውን ዋነኛ ዓላማ የሚንድ፤ ይህን ዓይነት የአተረጓጉም መስመር ከተከተልን ዳር ድንበር ለሌለው ሙግት ተከራካሪ ወገኖችን የሚዳርግ የሙግት አመራር ሥርዓትን የሚያፋልስ የአገሪቱ የፍርድ አሰጣጥ እና የአፈፃፀም ሥርዓት ተገማች እንዳይሆን ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ ከህጉም ሆነ ከየትኛውም መመዘኛ አንፃር ከቶውንም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በተለይም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3)(ሀ) እና ይህንኑ ሕገ መንግስትዊ ድንጋጌ ለመስፈፀም በወጣው ዝርዝር ሕግ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ስለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን መደንገግ ያስፈለገበት ዋነኛ የሕጎች መነሻ የአገሪቱን ሕጐች በማስፈፀምም ሆነ በመተረጐም ረገድ ወጥ የሆነ አሠራር እንዲሰፍን ለማድረግ በመሆኑ ይህም ስለመሆኑ እነዚህ ሕጐች ከወጡ በኋላ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የዳኝነት አካል ላይ የአስገዳጅነት ባህሪ ይኖረዋል በሚል በአዋጅ ቁጥር 454/97 የተደነገገው አስረጅ ነው፡፡

ከእነዚህ ሕጐች አንፃር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደ አሁኑ ያለ አጠቃላይ የፍርድን አመጣጥና የአፈፅፀም ሥርዓት የሚመለከት ጉዳይ በሁለት ተከራካሪ ወገኖች ክርክር መነሻ ሲቀርብለት በዚህ ዓይነት ጉዳይ በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ላይ የተፈፀመን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በማረም ለእነዚህ ተከራካሪ ወገኖች ሕጉን መሠረት ያደረገ ዳኝነት ከመስጠቱ ባሻገር ዐበይት ተግባሩ ወደ ፊት ይህን መሰል ክርክር ቢነሳ ሕጉን መሠረት ያደረገ ትርጉም በመስጠት ወደ ፊት ለሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ትርጉሙ ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ለማስፈን እንጂ የአፈፅፀም ጉዳይን እየተመለከተ ያለ ፍርድ የአፈፃፀም ፍ/ቤት እንደ አግባብነቱ ለፍርዱ ትክክለኛ ትርጉም በመስጠት ፍርዱን በተሟላ መንገድ የማስፈፀም ሥልጣን አለው የሚለው ትርጉም ሕጋዊ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት አይተውና ሰምተው ፍርድ ለመስጠት የሚችሉትንና እንደፍርዱ የሚያስፈፅሙትን ችሎቶች ሥልጣን

www.abyssinialaw.com

የሚቀላቀል፣ የሚተረጐም ፍርድ አለ የለም? የሚተረጐምስ ከሆነ እንዴት ይተርጐም የሚሉትንና ለመሳሰሉት ወሰን ለሌላቸው ክርክር የሚጋብዝ፤ የአፈፃፀምን ጉዳይ በዘፈቀደ እንዲመራ የሚያደርግ እንጅ የፍርድ አሰጣጥና የፍርድ አፈፃፀም በሥርዓት እንዲመራ በማድረግ ወጥ ለሆነ የሕግ አፈፃፀም እና አተረጓጐም እንቅፋት የሚፈጥር በመሆኑ ትርጉም ሕጉንና ሕጐችን ለማውጣት ያስፈለገበትን ግብና መነሻ ሐሳብ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡

ስለሆነም በዚህ በተያዘው ጉዳይ ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን ፍርድ የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪን አሠሪው ከግንቦት 17/2003 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሥራዋ ይመለሳት ሲል ፍርድ በመስጠቱ የተነሣ በአፈፃፀም ጊዜ ከግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ፍርድ እስከተሰጠበት እስከ መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ይጨምራል ወይስ አይጨምርም? ለሚለው ቀጥተኛ መልስ አይሰጥም፤ ፍርዱን ለማስፈፀም ያስቸግራል ውዝፍ ደመወዝ እንደተነፈገ ሊቆጠርብኝ ይችላል? የሚለው በፍርድ ግልጽ አለመሆን የሚጐዳው ወገን ፍርዱንና ጠይቆት ከነበረው ዳኝነት ጋር በማነፃፀር በበላይ ፍ/ቤት እንዲታረም ከማድረግ በቀር፡፡

እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከላይ በተገለፀው አኳኋን ፍርዱን ሊሰጥ የቻለበትን ምክንያት በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር እና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት እና አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ስለፍርዱ ይዘት አድማስ ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው ዋናውን ጉዳይ ሰሚው ከታች እስከ ላይ የተዋቀሩት ፍ/ቤቶች እንጂ ፍርዱን እንዲያስፈጽም የአፈፃፀም ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት የፍርዱን ይዘት በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችለው ሥልጣን ሰጭ ድንጋጌ እና ሥርዓት የለውም ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተተ የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል በሚል ሊተርጐም ይገባል የሚለውን የፍርድ ሐሳብ ሰጥተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 81405

ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ ሲራጅ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የአወሊያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ አቶ አሕመድ ሙዲ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(1) መሠረት የስራ መሪ በመሆናቸው ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚዳኝ አይደለም የሥራ ክርክር ችሎቱም ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ እና በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ በማሰናበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ስራ ክርክር ችሎት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርመሮ አመልካች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ መሠረት በሰራተኛ ውስጥ የሚካተት ሳይሆን የስራ መሪ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ሊስተናገድ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ክርክር ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚስተናገድ አይደለም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሐግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በ07/03/04 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡት ክስ ይዘት ተጠሪው ድርጅት በሕግ አማካሪነት ቀጠሮ ሲያስራኝ ከቆየ በኋላ አላግባብ ከስራ ያሰናበተኝ በመሆኑ የስራ ውሉ መቋረጥ ሕገወጥ ነው ተብሎ ተጠሪው የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፣የስራ ስንብት ክፍያ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ያደረጉት ክፍያ ለጠቅላላ ሰራተኛ የተሰጠውን የ40% የደመወዝ ጭማሪ እና መሰል ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ ውሳኔ ይሰጠኝ የሚል እና የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሰጡት አመልካች የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአሰሪና

www.abyssinialaw.com

ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 የሚዳኝ አይደለም በማለት ቢሆንም በበኩላችን ግን በመዝገቡ ከቀረበው ክርክር አንፃር ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ግንኙነት የቅጥር ውል ነው ወይስ የእውቀት ሥራ ውል ነው? የሚል መሆኑን በመገንዘብ ከዚሁ ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ከመሰረቱበት ጊዜ በፊት ጀምሮ የሰራ ግንኙነቱ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ፈቃድ አውጥተው የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆኑንን ተጠሪው በሰበር መልሱ ላይ የገለፀ ሲሆን አመልካችም የተጠሪው ስራ ብዙ በመሆኑ በጥብቅና ፈቃዴ ሌላ ስራ ልሰራ አልቻልኩም ከማለት በስተቀር በጥብቅና ስራ አገልግሎት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆኑን አላስተባበሉም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የስራ ግንኙነት ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ.2632-2638 በተመለከተው መሠረት በእውቀት ስራ ውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንጂ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(1) እና (2) መሠረት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ባለመሆኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 መሠረት ሰራተኛም ሆነ የሰራ መሪ ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ የግራ ቀኙ መብትና ግዴታም የሚወሰነው ከላይ በተጠቀሱትና አግባብነት የሚኖራቸው ሌሎች የፍ/ብሔር ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 በግራ ቀኙ መካከል ላለው ግንኙነት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም፡፡ በዚህም ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች ለውሣኔያቸው የሰጡት ምክንያት የተሳሳተ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ውሳኔው ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23650 በ19/08/04 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 119028 በ13/10/04 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በውጤት ደረጃ ፀንተዋል፡፡
2. በሰበር ደረጃ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራቸውን ይቻሉ፡፡
3. ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

የሰ/መ/ቁ. 82336

ጥር 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአብጃታ ሶዳ አሽ አክሲዩን ማህበር

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማርታ አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-በአመልካች ድርጅት ከግንቦት 16 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ደመወዝ ብር 1560.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ብር) እየተከፈላቸው ሲያገለግሉ እንደቆዩና ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ደብደቤ ከነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የስራ ውሉ ያተቋረጠ መሆኑን አመልካች ያሳወቃቸው መሆኑን ዘርዝረውና የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ መሆኑን ጠቅሰው የሞራል ካሳ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የስራ ውልን መቋረጥን ተከትሎ የሚከፈሉ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ በሐኪም ውሳኔ መሰረት በእርሷ ጤናና ሙያ የሚመጥን የስራ መደብ ባለመኖሩ ድርጅቱ ባገኘው አማራጭ፤ክፍት የስራ መደብ ላይ መብታቸውን ሳይነካ እንዲሰሩ ቢደረጉም ቦታው ደረጃዬን አይመጥንም በማለት ስራቸውን ትተው ፍርድ ቤትና ህክምና በመመላለስ የስራ ጊዜአቸውን የሚያባክኑ ስለሆነ በአማራጭ የተመደቡበትን፣ሌላ የስራ መደብም ላይ እየሰራች ለመቀጠል ፍቃደኛ እንዳልሆኑ በመዘርዘር እርምጃው የሕብረት ስምምነቱንና ህጉን መሰረት ያደረገ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪን የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደ ሰራቸው ሊመልሳቸው ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በሐኪም አስተያየት ለጤናቸው የሚመጥናቸው የስራ መደብ ሲሰጣቸው ሊሰሩ ፍቃደኛ ያለመሆናቸው በመረጋገጡ ስንብቱ የተከናወነ መሆኑን የሚያረጋግጥ የአመልካች ማስረጃ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገው የማስረጃውን ይዘት ካለማገናዘብ የተነሳ መሆኑንና ተጠሪ ወደ ስራ ይመለሱ ቢባል እንኳን ከአመልካች ጋር ሰላማዊ የሆነ የስራ

www.abyssinialaw.com

ግንኙነት የሚኖራቸው ባለመሆኑ ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ያለመወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ተምኖበት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28(1(ለ)) አኳያ የተፈፀመው የስራ ውል ማቋረጥ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪን የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደ ስራ ይመልስ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት የስራ ስንብቱ የተከናወነው ከሕግ ውጪ ነው በሚል ምክንያት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ስንብቱ በሕጉ አግባብ የተደረገ መሆኑን ገልፆ በመከራከሩ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን በመመርመር ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የደመደመውን ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ስራ አልፈልግም በማለት ያስታወቁ መሆኑን አመልካች በማስረጃዎቹ ያለማረጋገጡን፣ይልቁንም ተጠሪ ለአመልካች በሰጡት መልስ በቀድሞው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው የገለጹ መሆኑ መረጋገጡንና በጤናቸው ላይ የደረሰው የስራ ጉዳትም የስራ ግዴታቸውን ለዘለቄታው ለመፈጸም የማይችሉ መሆኑ ያለመረጋገጡ በክርክሩ ሂደት መታወቁን በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ ከዚህ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልፅ መረዳት የሚቻለው ውሳኔው የግራ ቀኙን ማስረጃና ክርክር በመመዘን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ስንብቱ በአመልካች ከሕግ ውጪ መከናወኑን ወይም አመልካች ስንብቱን በሕጉ አግባብ ያከናወነ መሆኑን በማስረጃዎቹ ያላስረዳ መሆኑን ሲሆን ይህ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ድምዳሜ የተያዘው ማስረጃን በመመዘን መሆኑን ነው፡፡ይኸው ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነጥብ የመጨረሻ ነው፡፡እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን በበታች ፍርድ ቤቶች ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈጸም ማረም እንጂ በማስረጃ ምዘና ላይ የሚያተኩር ክርክር የመመርመርና ስህተቱን የማረም ስልጣን የለውም፡፡በመሆኑም በተያዘው ጉዳይም የአመልካች ክርክር ማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑና አመልካች በስራ ላይ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ስራውን ለዘለቄታው መፈጸም የማይችሉ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 28(1(ለ)) ድንጋጌ አግባብ ያላረጋገጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ከተጠሪ ጋር የመሰረተው የስራ ግንኙነት ከሕግ አግባብ ውጪ ተቋርጧል ቢባል እንኳን ከተጠሪ ጋር ለወደፊቱ መልካም ግንኙነት ሊኖር ስለማይችል ተያያዥ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ተጠሪ ሊሰናበቱ ይገባ ነበር በማለት ነው፡፡በእርግጥ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል መልካም ግንኙነት መኖር ለኢንዱስትሪው ሰላምና ምርትና ምርታማነትን ከፍ በማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ ተገቢውን አስተዋጽኦ ለማበርከት አስፈላጊ በመሆኑ ሰላማዊ ግኙነት እንደማይኖር የሚያሳዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ጉዳዩን ለመመልከት ስልጣን

www.abyssinialaw.com

ያለው አካል የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ቢደርስ እንኳን ሰራተኛው ወደ ስራ እንዲመለስ ከማድረግ በምትኩ ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ እንደሚገባ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(3) ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ይህ ድንጋጌ ተግባራዊ ሲደርግ ግን የስራ ዋስትና ዋጋ በማያጣበት አግባብ ሊከናወን የሚገባ መሆኑ የድንጋጌው መንፈስ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሕግ አጠቃላይ ዓላማና በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀጽ 42 ስር ከተቀመጠው ድንጋጌ አንጻር ጋር ተዳምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ከአመልካች ጋር በሕጉ አግባብ የቅጥር ውል መስርተው በስራ ላይ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ከጤናቸው ጋር በሚመጥን ቦታ አመልካች ተጠሪን መድቦ እንዲያስራ በፍርድ ቤት ተወስኖ የነበረ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን በዚህ ውሳኔ መሰረት ሳይፈጸም ግን አመልካች ሊሰሩ ፍቃደኛ አልሆኑም፣ስራውንም ለመፈጸም አይችሉም በሚሉ ምክንያቶች የስራ ውሉን ከነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ አቋርጧል፡፡ይህ የሚያሳየው አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰውን የስራ ጉዳት ምክንያት በማድረግ ለጤናቸው ተስማሚ በሆነው የስራ መደብ ላይ ለማሰራት ፍቃደኛ ባለመሆን የፀና መሆኑን ነው፡፡ይህ ደግሞ ሕገ ወጥነት ያለው ተግባር ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 377/196 አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ መንፈስ መሰረት አመልካችና ተጠሪ መልካም የሆነ ግንኙነት አይኖራቸውም ብሎ ለመደምደም እና የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ለማድረግ የሚበቃ ሕጋዊ ምክንያት አይሆንም፡፡ አንድ ሰራተኛ መብቱን ለማስከበር ፍርድ ቤት መሄዱ ብቻውን ከአሰሪው ጋር ለወደፊትም የሻከረ ግንኙነት ይፈጥራል ተብሎ የሚገመትበት ህጋዊ አግባብ የለም፡፡ይልቁንም በፍርድ ቤት ውሳኔ መብቱን በማረጋገጥ የሚሰራ ሰራተኛ ለኢንዲስትሪው ሰላም ችግር የማይፈጥር ሰላማዊና በሕግ ልዕልና ከፍተኛ እምነት ያለው ነው ተብሎ የሚገመት መሆኑ ይታመናል፡፡በመሆኑም አመልካች ተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባል በማለት የሚያቀርበው አማራጭ ዳኝነት በተጠሪ ላይ ደረሰ ከተባለው የስራ ጉዳትና ከሕጉ አጠቃላይ መንፈስ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 116264 ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

በዚህ ችሎት ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.78865

ጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት

ተጠሪዎች ፡- 1. አቶ ገ/ስላሴ ኃ/ማርያም
2. ወ/ት እቴቱ ለማ
3. ወ/ት አማረች መንግስቴ
4. ወ/ሮ ለምለም እንዳለ
5. አቶ አካለወርቅ ሳልልህ
6. አቶ አርአያ ውብነህ
7. ወ/ሮ በቀለች ከበደ
8. አቶ እስማኤል ዓሊ

ጠበቃ ዘነበ ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሆኖ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ድርጅት ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- ተከሳሽ ድርጅት ባካሄደው የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መሰረት በተጠናው የደመወዝ እስኬል ለእያንዳንዱ የሥራ መደብ መነሻ ደመወዝ ሲወሰን ከሳሾች በተመደብንበት የሥራ መደብ ማግኘት የሚገባንን ሲወስን ቀደም ሲል ስናገኝ የነበረውን ደመወዛችንን የቀነሰብን ስለሆነ ያለአግባብ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክልልን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ለክሱ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ፤-በተከሳሽ ድርጅት መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተደርጎ በመንግስት ከጸደቀ በኋላ በአማካሪ ድርጅት የተጠናውን አዲስ የደመወዝ እስኬል መነሻ በማድረግ ከሳሾች ክሱን ያቀረቡ ስለሆነና የደመወዝ ጭማሪን የሚመለከት ክስ የወል የሥራ ክርክር ስለሚሆን መቅረብ ያለበት ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በቀጥታ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ደ/መቃወሚያ ላይ በሠጠው ብይን፡- ከሳሾች ባቀረቡት ክስ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ጠቅላላ የደመወዝ እስኬል አሰራርን የሚነካ በመሆኑና ውጤቱም በሌሎች ሠራተኞች ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ

ተጽዕኖ ሊያስከትል ስለሚችል በወል የሥራ ክርክር የሚሸፈን በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ክሱን ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በሚል የክሱን መዝገብ ዘግቷል፡፡

የስር ከሳሾችም የመ/ደ/ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሠጠው ፍርድ ይግባኝ ባዮች ባቀረቡት ክስ ላይ የሚወሰነው ጭብጥ ተቋረጠብን የሚሉት የደመወዝ ጭማሪ ነው? ወይስ ድጎማ ነው? የሚለው ሲሆን በዚሁ ጭብጥ ላይ የሚሰጠው ውሳኔም ከይግባኝ ባዮች አልፎ የሁሉንም ሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚነካ ባለመሆኑ ጉዳዩ በግል የሥራ ክርክር የሚታይ ነው በማለት የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በመሻር በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ክርክሩን መልሶለታል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 147(2) መሰረት በወል ሥራ ክርክር የሚሸፈን ሆኖ እያለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በግል የሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው በማለት ጉዳዩን የሥራ ክርክር ችሎት እንዲወስነው የመለሰው ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- ክሱ የቀረበው አመልካች ድርጅት ሲከፈለን በነበረው ደመወዝ ላይ መዋቅሩን መሥራት ሲገባው ደመወዛችንን በመቀነስ መዋቅሩን የሰራ በመሆኑ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክል ዳኝነት የጠየቅንበት እንጂ ክርክራችን በተሰራው መዋቅር ላይ ባለመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ክሱ በግል ሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው ሲል የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለው ሊጸና ይገባል በሚል ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ድርጅትም ለተጠሪዎች መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በወል የሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው? ወይስ በግል ሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የግል የስራ ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሚታዩ ስለመሆናቸው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138 መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የወል ሥራ ክርክር ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሚታይ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 142(1)፣147(1)(ሀ) ተመልክቷል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ምላሽ የሚሻው ጉዳይ ግን አንድ ጉዳይ የግል ወይም የወል የሥራ ክርክር ሊባል የሚችልበት አግባብ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/18180 በቀን 29/11/1997 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በዚሁ የህግ ትርጉም መሠረትም አንድ ጉዳይ የወል የሚያሰኘው የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ሲሆን ክርክሩ የግል ነው የሚባለው ደግሞ ዉጤቱ በተከራካሪ ሠራተኛ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሲሆን ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ቀደም ሲል ሲናገኙ የነበረውን ደመወዝ አመልካች ያለአግባብ በመቀነስ በተሰራው መዋቅር ላይ ያስቀመጠው ስለሆነ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክል ይወሰንልን በሚል ክስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም ቀደም ሲል በድጎማ መልክ ከደመወዛቸው ጋር ሲከፈላቸው የነበረው ገንዘብ ከደመወዛቸው ተቀንሶ በተሰራው መዋቅር ላይ ከመቀመጡ በስተቀር በደመወዛቸው እስኬል መሰረት ማግኘት የሚገባቸው ገንዘብ አልተቀነሰም በሚል ተከራክሯል፡፡ ይህ ከሆነ

www.abyssinialaw.com

ደግሞ ቀደም ሲል መዋቅሩ ከመሰራቱ በፊት ሲከፈላቸው የነበረው የደመወዝ መጠን የድጎማ ክፍያ ተጨምሮ ነው? ወይስ ሳይጨመር ነው? ድጎማው ተቀናሽ ተደርጎ በተሠራው መዋቅር መሰረት የደመወዝ እስኬል ሲቀመጥ ተጠሪዎቹ ማግኘት ከሚገባቸው የደመወዝ መጠን ቀንሷል? ወይስ አልቀነሰም? የሚሉ ነጥቦች ከተጣሩ በኋላ የሚሰጠው ውሳኔ ደግሞ ከተጠሪዎች አልፎ የሌሎች የድርጅቱን ሠራተኞች መብትና ጥቅም በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ሊነካ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች መዋቅሩ ሲሠራ ቀደም ሲል ስናገኝ የነበረው የደመወዛችን እስኬል ተቀንሶብናል በማለታቸው ብቻ ጉዳዩ የወል ሥራ ክርክር ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት ባለመኖሩ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዎቹ ያቀረቡት ክስ በግል የሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው ሲል በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/115821 በቀን 10/7/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በግል የስራ ክርክር የሚሸፈን በመሆኑ ሊቀርብ የሚገባው ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ነው በሚል ከፍተኛው ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 80350

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- ሸራተን አዲስ - ጠበቃ ተካ አስፋው ቀረቡ

ተጠሪ፡-

1. አቶ ገናናው ከበደ
2. አቶ ገ/ሥላሴ በላይ
3. አቶ ቢንያም እያሱ ወ/ኪዳን
4. አቶ አቢይ አድነው
5. አቶ ጕመረው ለማ
6. አቶ ተሻገር ትእግስቱ
7. አቶ ሳሙኤል ሹመት
8. ወ/ሪት መዓዛ ቁምላቸው
9. አቶ ኢዩቤል አሰፋ
10. ወ/ሪት እመቤት ፀሐይ
11. ወ/ሪት መሰረት ፍስሃ
12. አቶ ቦንያስ ስይፉ
13. አቶ ኤልያስ እንዳለ
14. አቶ ቴዎድሮስ አሸብር
15. አቶ ብርሃስላሴ ሐይሉ
16. ወ/ሪት ናርዶስ በላይ
17. አቶ ደጉ ተስፋዬ
18. አቶ ታዲዮስ ደርቤ
19. ወ/ት ሂሩት መልካ
20. ወ/ሪት ነጻነት በፈቃዱ
21. አቶ ብርሃነ ለገሰ
22. ወ/ሮ አነኒ ታደሰ
23. ወ/ት ባዩሽ ገብሬ
24. ወ/ት ስንዱ ሹምዬ
25. ወ/ት አስቴር ፍቅሩ
26. ወ/ሮ ሃና ዘሪሁን
27. አቶ ጌታቸው ተሾመ
28. ወ/ሮ አቦነሽ ከፍያው
29. ወ/ሪት እየሩሳሌም ታንኪ
30. አቶ ነጻነት ሽዋልዑል
31. ወ/ት ፍቅርተ ተፈሪ
32. ወ/ት አበባ እሸቱ
33. ወ/ሮ ጺጋነሽ ሄሊሶ
34. ወ/ት ጽጌሬዳ እሸቱ
35. ወ/ሮ አየለች ባነጫ
36. አቶ መላኩ ታደሰ
37. አቶ ፍቅረማሪያም ወርቅ
38. ወ/ት ሰርካለም አሰፋ
39. ወ/ት ሀይማኖት ጉተማ
40. አቶ ገረመው ወርቁ
41. ወ/ት አዜብ በየነ
42. ወ/ት አስናቀች ቢተው
43. አቶ ክብሮም ግደይ
44. አቶ ፈቃደ ታደሰ
45. ወ/ት ቃልኪዳን ሲሳይ
46. ወ/ት ሉባባ በያን
47. አቶ እዩብ ፅጌ

www.abyssinialaw.com

48. አቶ ሱራፌል ፍቃደ
49. ወ/ት ረድኤት ታደሠ
50. ወ/ት ስርካለም ኤርምያስ
51. ወ/ት ሀረገወይን ባንቲ

- ለሁሉም ጠበቃ ግርማ ኃይሌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው። የተጠሪዎች ክስ ይዘት ሲታይም በአመልካች ድርጅት በተያለያዩ ጊዜአት ተቀጥረው የተለያዩ የአገልግሎት ዘመን እንዳላቸውና በባንኪቶት እና እስቲዋርዲንግ የስራ ዘርፎች እያገለገሉ እንደሚገኙ፣አመልካች ድርጅት በቅጥር ስርአት ላይ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ከተደነገገው ውጪ በሰራተኞች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት በመፍጠር በተመሳሳይ የስራ ሰዓት ርዝመትና ስፋት የክፍያ ልዩነት በመፍጠር ለተጠሪዎች በሕግ የተሰጠውን መብት በመጣስ ከሕግ ጋር የሚጻረር ውል በማዘጋጀት እያስፈረመ በሕግ የተሰጣቸው ተገቢውን ክፍያና ጥቅማ ጥቅም መንፈጉን፣የስራ ሰዓት በወር 208 እንዲሆን በመገደብ በሰዓት ብር 5.50(አምስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) እያሰበ እንደሚከፍላቸውና በቀን ስምንት ሰዓት ለማሰራት በሕጉ የተጣለበትን የአሰሪነት ግዴታን ያለመወጣቱን፣ተመሳሳይ የሥራ መደብ ላላቸው ሰራተኞች የክፍያ ልዩነት መፍጠሩንና ለልዩነቱ የቅጥር ሁኔታ አልፎ አልፎ ለሚሰራ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኛ እንደቋሚ ሰራተኛ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ሊጠበቁለት አይገባም በማለት በሕግ እውቅና የሌለውን ምክንያት መሰረት ማድረጉን ዘርዝረው ተጠሪዎች ለሰሩት ዘመን የተከለከሉትን ሰርቪስ ቻርጅ፣ቲፕ፣ቦነስ በሕግ አግባብ የስድስት ወር እንዲታሰብላቸው፣የአመት ፈቃድ፣የሕክምና አገልግሎት ፣የ24 ሰዓት የሰራተኞች የሕይወት ኢንሹራንስ ሽፋን፣የደመወዝ ጭማሪ፣ፕሮቪደንት ፈንድ የማጠራቀም መብት እንዲጠብቅላቸው እንዲሁም የትርፍ ስራ ሠዓት ሥራ ክፍያ፣የበዓላት እና የእሁድ ቀናት ስራ በመስራት ጥቅም የማግኘት መብት ዘርዝረውና በገንዘብ የሚተመነውን መብት መጠን በገንዘብ ለይተው ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪዎች የተቀጠሩት አልፎ አልፎ የሚሰራን ሥራ ለመስራት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ሰርቪስ ቻርጅ፣ቦነስና ቲፕ የመክፍል፣የፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ የማድረግ፣ኢንሹራንስ የመግባት ግዴታ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ወይም በህብረት ስምምነት ወይም ሁለቱም ወገኖች በየግላቸው በተፈራረሚቸው የስራ ቅጥር ውሎች ግዴታ ያልተጣለበት መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ተቀባይት የለውም ሲል ተከራክሯል። ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ውል የጊዜ ገደብ ያለው ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ቢያስረዳም ተጠሪዎች ሲሰሩ የነበሩት ስራ ተከታታይነት ያለው ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ገልጾ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜና ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው፣እንዲህ ከሆነ በጥቅማ ጥቅም ማግኘት ደረጃ ከቋሚ ሰራተኞች የሚለዩበት ምክንያት የለም በማለት ለእየንዳንዳቸው በወር 4,956.70(አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከሰባ ሳንቲም) ታስቦ ክሱ ከመቅረቡ በፊት ላለው ስድስት ወራት በድምሩ ብር 1,576,230.60 (አንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሰርቪስ ቻርጅ እንዲከፈላቸው፣አመልካች ድርጅት መደበኛ ሰራተኞች ለሚላቸው የሚሰጣቸው

ቲፕ (ጉርሻ) ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲያዝላቸው፣የአመት ፈቃድ ማግኘት መብታቸው እንደየአገልግሎታቸው እንዲያዝላቸው፣ፕሮቪደንት ፈንድ የማጠራቀም መብት እንዲጠበቅላቸው ሲል ወስኗል። በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የበታች ፍርድ ቤት ሰርቪስ ቻርጁንና ጉርሻን በተመለከተ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ ሽሮ በሌሎች ነጥቦች ላይ የሰጠውን ውሳኔ ግን ሙሉ በሙሉ በማፅናት ወስኗል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ስራ አመልካች ድርጅት በመደበኛነት የሚሰራው ስራ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚሰራ በመሆኑ ግራ ቀኙ ይህንኑ ተገንዝበው ውል ያደረጉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የውል ስምምነቱ ታልፎ ተጠሪዎች የሚሰሩት ስራ ተከታታይነት ያለው ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ለመደበኛ ስራተኞች የተጠበቁ መብትና ጥቅማ ጥቅሞች ለተጠሪዎችም ሊጠበቁ ይገባል ተብሎ የተወሰነው የአመልካች ድርጅትን የስራ ባህርይ፣የመዋዋል ነፃነትንና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 9፣10፣14(ረ)፣53(2) እና 134 ድንጋጌዎችንና ይዘትና መንፈስ ውጪ እንዲሁም ከአዋጁ ዓላማ ጋር እና አስገዳጅነት ያላቸውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ይዘት ባላገናዘበ መልኩ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪዎች በሰጡት የፅሑፍ መልስ የተጠሪዎች የቅጥር ውል ሕጋዊ ያለመሆኑና ተጠሪዎች ለረዥም አመታት ይሰሩበት የነበረውና አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰሩ ስራዎች ናቸው የሚላቸው በተከታታይነት የሚሰሩ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ከአመልካች ማስረጃዎች ጭምር ስለማረጋገጡ በመገንዘብ የሰጡት ውሳኔ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 11924 እና 25526 ከሰጣቸው አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች፣ከአለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት ደንብና አግባብነት ባላቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች በበኩሉ አስገዳጅነት ያላቸው የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጡት ተገቢውን ማጣራት አድርገው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች አመልካችን ሊከሱት የቻሉት ቅጥሩ አልፎ አልፎ ለሚሰራ ስራ የተደረገ ነው በሚል ምክንያት በሕጉ ሊጠበቁ የሚገባቸውን ጥቅማ ጥቅሞችን አልጠበቀልንም፤ከልክሎናል በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካች ተጠሪዎች ይገባናል የሚሏቸውን መብቶች የከለከላቸው መሆኑን ሳይክድ እርምጃውን ሕጋዊ በማለት ነው የሚከራከረው የተጠሪዎች ቅጥር አመልካች በመደበኛነት የሚሰራቸውን ስራዎች ለማሰራት የተደረገ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙት ስራዎች እንደ ስብሰባ ዝግጅት፣የሰርግ ፣የፌስቲቫል እና የምርቃት ፓርቲ፣ከክብረ በዓላት እና ኢዩቤልዩ ሲከበር የሚሰሩትን ስራዎች ለመስራት አውቀውና ወደው በውል በመተሳሰር ተጠሪዎች ስራዎቹን ሲሰሩ የቆዩ በመሆኑ ለመደበኛ ስራ ሰራተኞች የተጠበቁት ጥቅማ ጥቅሞች ሊጠበቅላቸው አይገባም፣ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መሆኑን ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ

www.abyssinialaw.com

የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ተጠሪዎች አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰሩ ስራዎች ናቸው የሚላቸውን በተከታታይ ፕሮግራም እየወጣላቸው ሲሰሩ የነበሩ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡ ስራዎቹ ቀጣይነት ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው በሚል ምክንያት መሆኑንም ከውሳኔዎቹ ግልባጮች ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ሕግ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 9 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ ይህ የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችለው በተጠቀሰው አዋጅ አንቀፅ 10 በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ነው፡፡ አሰሪው በዚህ አንቀጽ ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች ቅጥሩ መፈፀሙን ካስረዳ በአዋጁ አንቀጽ 9 ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት እንዳስተባበለ የሚቆጠር ሲሆን እርምጃውም ከዚሁ አንጻር ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የሥራው ባህርይ ቀጣይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ጊዜን በመቁረጥ የሚደረግ የቅጥር ውል ስምምነት ሕጋዊ ጥበቃ የማይደረግለት ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 11924፣25526 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10(ሐ) መሰረት ተደርጎ የተመሰረተ መሆኑ ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክርና በክርክሩ ሂደት የተረጋጠውን ፍሬ ነገር ተጠሪዎች የሚሰሩት ስራ ቀጣይነት ያለውና አመልካች ድርጅት መደበኛ ስራ ላይም ተጠሪዎችን ማሰራቱ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ሳይቀበሉት ቀርተዋል፡፡ በእርግጥ ከላይ የተጠቀሱት አስገዳጅነት ያላቸው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች የስራው ባሕርይ ቀጣይነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ አሰሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 10 መሰረት የስራ ውሉ ተደርጓል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው እንደማይገባ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የሰበር ሰሚ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መንፈሱ በጥንቃቄ ታይቶ ግንዛቤ ካልተወሰደበት ከሕጉ ዓላማና መንፈስ ጋር የማይሄድ ውጤትን ማስከተሉ የማይቀር መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስለሆነም የስራው ባሕርይ ቀጣይነት ያለው ነው ለማለት መታየት ያለበት ነጥብ ስራው ለተከታታይ ሳምንታት፣ወራት ወይም አመታት በገበያው አመቺነት ምክንያት መቀጠሉን ነው ወይስ ከገበያው ምቹነት ሳይሆን ስራው ራሱ ብቻውን ሲታይ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው? ከሚለው ጥያቄ ጋር ሊለይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም አግባብ ጉዳዩ ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10 መሰረት ተደረገ ተብሎ የሚቀርበውን የቅጥር ውል ውድቅ ለማድረግ የስራው ቀጣይነት የሚለው መለኪያ መሰረት ማድረግ ያለበት ስራው በገበያው አመቺነት ረዘም ላሉ ጊዜያት መሰራቱን ብቻ ሳይሆን ስራውን በባህርው እና ከድርጅቱ መሰረታዊ አላማ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ቀጣይነት ያለው መሆኑ መረጋገጥን ጭምር የሚጠይቅ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ድምዳሜ ውጪ የሚያዘው ድምዳሜ በአንድ ድርጅት ላይ ተገቢ ያልሆነ የሰው ኃይል እንዲኖር የሚያደርግ እና የድርጅቱን ተወዳዳሪነት በመፈታተን ለአገር ኢኮኖሚ ሊጫወተው የሚገባውን ሚና ሁሉ የሚገድብ ነው፡፡ የአንድን ድርጅት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለአገር ኢኮኖሚ የሚያበርክተውን አስተዋጽኦ የሚገድብ እርምጃ ደግሞ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማን የሚጻረረ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን አከራክሮ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል አንድን ስራ በባሕርይው ቀጣይነት ያለው ነው ብሎ ለመደምደም ስራው ረዘም ላለ ጊዜ መሰራቱን ብቻ ሳይሆን የስራው ባህርይ ከድርጅቱ አይነተኛ ስራ ጋር የሚሄድና ቀጣይነት ያለው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይህ ድምዳሜ ሲያዝም የድርጅቱ አጠቃላይ ተቋማዊ ሁኔታው በውል ሊታወቅ

www.abyssinialaw.com

ይገባል፡፡ ይኼውም ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ፣ሊሸከመው የሚገባው የሰራተኛ ቁጥርና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በተገቢው መንገድ ተጣርተው ሊታወቁ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች የተቋቋመበት መደበኛ የመኝታ፣የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን መስጠት መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪዎች ይሰሩበት የነበረውን ስራ አልፎ አልፎ የሚሰራና የአመልካች ድርጅት መደበኛ ስራ ያለመሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሚሰራቸው መደበኛ ስራዎች አይነት እና ብዛት፣በእነዚህ መደበኛ ስራዎች የሚይዛቸው የሰራተኞች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ፣አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰራቸው ስራዎች አመልካች በቀጣይነት የሚሰራቸው መሆን ያለመሆኑ፣ስራዎቹ በቀጣይነት የሚሰሩበት ሁኔታ እንዴት ሊከሰት እንደሚችልና የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ስራውን ለመስራት በቀን ወይም በወር ለአንድ ሰራተኛ ሊመደብ የሚችለው የስራ ሰዓት ምን ያህል እንደሆነ በአመልካች ማስረጃም ሆነ በተጠሪዎች ማስረጃ ነጥረው የወጡ ነጥቦች አይደሉም፡፡ ፍርድ ቤቱም የሚመለከታቸውን አካላት እንዲያጣሩለት ያደረገበት የክርክር አመራር ደረጃ ያለመኖሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በክርክሩ ሂደት የተነሱትና ለጉዳዩ አወሳሰን ወሳኝ የሆኑት ፍሬ ነገሮች በማስረጃ ሳይነጥሩ ትክክለኛና ፍትሃዊ ዳኝነት መስጠት የማይቻል መሆኑን የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓታችን ያስገነዝበናል፡፡ ዳኝነት ሰጪ አካል የሆነው ፍርድ ቤት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የተከራካሪ ወገኖችን ማስረጃ አስቀርቦ ሣይመለከት፤ሳይሰማና ከተያዘው ጭብጥ ጋር አገናዝቦ ሣይመረምር በሕግ ባልተመለከተ ምክንያት የማስረጃ መስማት መብትን በማለፍ ወይም ፍርድ ቤቱ ራሱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል ሊነጥር የሚገባውን ፍሬ ነገር ራሱ በሚያስቀርበው ማስረጃ ሳያነጥር ፍርድ የሚሰጥበት አካሄድ የዳኝነት አሰጣጥ ስርኣታችን የሚቀበለው ጉዳይ አይደለም፡፡ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ መወሰን ደግሞ መሰረታዊ የሆነ የፍርድ አካሄድ ጉድለት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣137፣145፣264፣272፣345 እና ሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡን ሐቅም ይኼው ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች በተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች ወይም በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በሚቀርቡ የሚመለከታቸው አካላት ወይም የባለሙያ ማስረጃዎች ባልነጠሩበት ሁኔታ የተጠሪዎች ስራ አልፎ አልፎ የሚሰራ አይደለም ተብሎ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ባልተሟላ የፍርድ አካሄድ የተሰጠና በአመልካች ድርጅት ላይም ተገቢ ያልሆነ የሰራተኛ ኃይል የመጫን ውጤት ያለው በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ስለአገኘን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61589 ጥር 14 ቀን 2004 ዓ/ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 116137 ግንቦት 27 ቀን 2004 ዓ/ም ተሻሽሎ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የሚሰራቸው መደበኛ ስራዎች አይነት እና ብዛት፣በእነዚህ መደበኛ ስራዎች የሚይዛቸው የሰራተኞች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ፣አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰራቸው ስራዎች በቀጣይነት የሚሰራቸው መሆን ያለመሆኑ፣ስራዎቹ በቀጣይነት የሚሰሩበት ሁኔታ ከነበረና ካለም እንዴት ሊከሰት እንደቻለና ወደፊትም ሊከሰት የሚችልበት ሁኔታ መኖር ያለመኖሩን፣ለስራዎቹ የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ስራውን ለመስራት በቀን ወይም በወር ለአንድ ሰራተኛ ሊመደብ የሚችለው የስራ ሰዓት ምን

www.abyssinialaw.com

ያህል ነው? የሚሉትን ፍሬ ነገሮችን፤ የአመልካችን ድርጅታዊ አቋም ባጠቃላይ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ በማጣራት ክርክሩን በመዝገብ ቁጥር 61589 እንዲቀጥል በማድረግ ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 80079

ህዳር 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የመቶ አለቃ ጥላሁን ታችበሌ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች ከሥራ በጡረታ ምክንያት በአሰሪ መሰናበታቸው እና ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የሕብረት ስምምነት ነው ወይስ የጡረታ አዋጅ ነው የሚለው የሕግን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለመመርመር ነው፡፡ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ያቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት በጥበቃ ሰራተኝነት ተቀጥረው እስከ ታህሣሥ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ማገልገላቸውና ተጠሪ ድርጅት ጡረታን ምክንያት አድርጎ መብታቸውን ሳይጠብቅ ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውላቸውን ያቋረጠ በመሆኑና ስንብቱ ሕገወጥ በመሆኑ ሕጉ በሚፈቅደው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጠይቋል፡፡ ተጠሪ ድርጅት በሰጠው መልስ በድርጅቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 32.5 መሠረት ተጠሪ የሠራተኞችን የጡረታ መውጫ ጊዜ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ አመልካችም ዕድሜያቸው 55 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የፕሮቪደንት ፈንዳቸው ተከፍሏቸው በልዩ ሁኔታም የሁለት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ተሰናብቷል፡፡ ስንብቱም በአግባቡ የተከናወነ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር ያደመጠው የሥር ፍርድ ቤት ስንብቱ በሥራ ላይ ባለው የሕብረት ስምምነት የተፈፀመ በመሆኑ ሕጋዊ ነው፡፡ ምንም ክፍያ መጠየቅ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሥልጣኑ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት የይግባኝ ባይ ቅሬታን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አፅንቷል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤቱ ፈጽሞታል ያሉትን የሕግ ስህተት በመዘርዘር ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ በአመልካች አቤቱታ ከተዘረዘሩት የቅሬታ ነጥቦች የጡረታ ዕድሜ በሕግ እንጂ በሕብረት ስምምነት ሊወሰን እንደማይገባ፤ አሰሪው /ተጠሪ/ ተቋም ሕገወጥ ስንብት የፈፀመ በመሆኑ የ6 ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲከፍላቸው እንዲወሰንላቸው አመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ 1ኛ የሥራ ክርክር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በመ/ቁ 62433 ህዳር 11 ቀን 2004 ችሎት የጡረታ ዕድሜ አግባብ ባለው ሕግ እንጂ

በሕብረት ስምምነት የሚወሰን አይደለም በማለት የሰጠው ውሣኔ እንዲታይላቸው አያይዘው አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት በተጠሪና በሠራተኞች ማህበር መካከል በተፈረመው የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 32.5 መሠረት ነው፤ ተዋዋይ ወገኖችም የጡረታ ዕድሜን ሊወስኑ እንደሚችሉ የሕብረት ስምምነቱን የፈረሙት ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙ በመሆኑና አመልካች በዚህ አግባብ በሕጋዊ መንገድ የተሰናበተ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው እንዲባልለት አመልክቷል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቅሬታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚገዙ ሠራተኞች የጡረታ ዕድሜ የሚወሰነው አግባብ ባለው ሕግ ነው ወይስ በሕብረት ስምምነት? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር በጥበቃ ሠራተኛነት ሲሰሩ እንደነበረ፤ በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 32.5 መሠረት 55 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በጡረታ ከሥራ እንዲሰናበቱ ተጠሪ መወሰኑ ከሥር ፍርድ ቤቶች መዝገብ መገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች የጡረታ ጉዳይ መታየት ያለበት በሕግ እንጂ በሕብረት ስምምነት አለመሆኑን አጥብቀው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ የሕብረት ስምምነቱ በተጠሪ ድርጅት እና በሠራተኛ ማኀበር የተፈረመና ተግባራዊ መሆኑ ከሕግ እንደማይቃረን አመልክቷል፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የነበረው የሥራ ውል ግንኙነት ከሚቋረጥባቸው መንገዶች አንዱ ሠራተኛው በጡረታ ሲገለል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ጭብጥ የጡረታ መውጫ ጣሪያ ዕድሜ ስንት ነው? በሕግ ነው የሚወሰን ወይስ በሕብረት ስምምነት የሚለው ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የጡረታ ዕድሜ ጣሪያ በግልጽ አልደነገገም፡፡ ይሁንና አዋጁ በአንቀጽ 24/3/ "ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በጡረታ ሲገለል" የሥራ ግንኙነቱ በሕግ አግባብ የተቋረጠ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ ማህበር የሚፈረመው የሕብረት ስምምነት በተመሣሣይ ጉዳይ ለሠራተኛው በሕግ ከተደነገገው ይልቅ የሕብረት ስምምነቱ የበለጠ ጥቅም የሚሰጠው ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው በአንቀጽ 134/2/ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ያለፈቃዳቸው በጡረታ ከሥራ እንዲሰናበቱ የተደረገ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪም የስንብት ድርጊቱ የተፈፀመው ለሠራተኛው የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በስንብት ስርዓቱ የሕብረት ስምምነት የተፈፀመ ነው ይበል እንጂ የሕብረት ስምምነቱ አግባብነት ካለው ሕግ በተሻለ መንገድ ለሠራተኛው የጠቀመ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ክርክር አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የሕብረት ስምምነቱ የጡረታ ዕድሜን ከመወሰን አኳያ የተፈፃሚነት ወሰን ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም በቀር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁለት የተለያዩ ምድብ ችሎቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24/3/ አተረጓጐም ላይ የተለያየ አቋም ወስደዋል፡፡ ይህ ደግሞ አዋጁን ወጥ በሆነ አግባብ ከመተርጎም አንፃር የራሱ የሆነ ውስንነት እንዳለው እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን በሕግ ፊት እኩል የመዳኘት መብት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ አንደኛው ምድብ ችሎት በሕብረት ስምምነት የተወሰነውን የጡረታ ዕድሜ ጣሪያ ሲቀበል ሌላኛው ምድብ ችሎት አግባብነት ያለው ሕግ ማለት የሕብረት ስምምነት አለመሆኑን በመጥቀስ ውድቅ አድርጐታል፡፡

www.abyssinialaw.com

አከራካሪው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሕግ የምንለው የትኛው ነው የሚለው ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው የሕብረት ስምምነቱ በአንቀጽ 24/3/ የተመለከተውን ትርጓሜ የማይካተት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሕግ የምንለው ሥልጣን ባለው አካል የወጣ ሕግ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በአስፈፃሚው አካል የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የሚያካትት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የጡረታ ዕድሜ መውጫን በተመለከተ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተለያየ የዕድሜ ጣሪያ የተቀመጠ ቢሆንም በሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ እንዲሁም የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 17/1/ የሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት መሆኑን ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ እንደ አግባብነቱ ወይም የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ሆኖ ሳለ የሕብረት ስምምነቱን መውሰዳቸው መሠረታዊ የሕግ አተረጓጉም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት በኮ.መ.ቁ 63787 በ27/02/2004 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 115690 በ02/8/2004 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. ግሎባል ሆቴል ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የተቋሙ ሠራተኞች ማህበር የፈረሙት የሕብረት ስምምነት የጡረታ መውጫ ዕድሜን በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፡፡
3. ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር በተነሱት የክፍያና ተያያዥነት ያላቸው የመብት ጥያቄዎችን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 79853

ህዳር 04 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

መኰንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ነገረ ፈጅ አቶ ጌታቸው ለማ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ጌታቸው ደበበ ቀረቡ
2. አቶ ሽመልስ ኃይሉ ቀረቡ
3. ወ/ሮ ካሡች በርሄ ቀረቡ
4. ወ/ሮ እመቤት ሙሉጌታ ቀረቡ
5. ወ/ሮ ፋናዬ ኢዶኮ ቀረቡ
6. ወ/ሮ ምሳነሽ ተሰማ ቀረቡ
7. አቶ ወዳጄ ስጦታው ቀረቡ
8. ወ/ሮ መኪያ ከድር ቀረቡ
9. አቶ ወጋየሁ አበራ ቀረቡ
10. አቶ አማረ ወርቁ ቀረቡ
11. አቶ ጀማል ሞሳ ቀረቡ
12. ወ/ሮ በቀለች ፀጋዬ ቀረቡ
13. ወ/ሮ ሸሽግ ኃይሌ ቀረቡ
14. አቶ ብርሃኑ ጉንፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 116131 ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለበት በማለት ፍርዱ እንዲሻር እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19101 ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ይፀና ዘንድ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲሆን ተጠሪዎች ከሣሾች ነበሩ፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ስንመለከት ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ተከሣሽ /በአሁኑ አመልካች/ በተለያዩ ጊዜያት በጉልበት፣ በፌራዮነትና ረዳት ፌራዮነት በተለያየ የደመወዝ መጠን ቀጥሮ ሲያሰራን ቆይቶ አለአግባብ ከሥራ ያሰናበተን ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ሥራችን ይመልሰን ዘንድ ይወሰንልን ካልሆነም ያለአግባብ የሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር በተያያዘ ሊከፍለን የሚገባውን ክፍያዎች ይከፍለን ዘንድ ይወስንልን የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ /የአሁኑ አመልካች/ በሰጠው መልስ ከሣሾች /የአሁኑ ተጠሪዎች/ የደመወዝ መጠን የተለያየ መሆኑ የሥራ ውሉም የተቋረጠው ተጀምሮ የነበረው የፕሮጀክት ሥራ በመጠናቀቁ ስለሆነ የጠየቁት ክፍያ የሚገባቸው አይደለም ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተከሣሽ /የአሁኑ አመልካች/ ከሣሾችን /የአሁኑ ተጠሪዎች/ ሥም ዝርዝር ያለበትና በተለያየ ሙያ ሲሰሩ መቆየታቸው እና የበጋ ወራት ከጥቅምት 01 ቀን ጀምሮ ፕሮጀክቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የተቀጠሩ ለመሆናቸው የሚያሣይ ሰነድ ከሐምሌ 02 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ያቀረበ ሲሆን ይህም ከሣሾች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑ ያመለክታል፡፡ 2ኛ እና 4ኛ ከሣሾችም ያቀረቡት የምስክር ወረቀት ላልተወሰነ ጊዜ ለመቀጠራቸው አያመለክትም በማለት ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 77 መሠረት የዓመት ዕረፍት የ14 ቀን ክፍያ ለከሣሾች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

ከሣሾችው በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ መልስ ሰጪ ቅጥሩ ለተወሰነ ጊዜ ነው ቢልም የሥራ ቅጥር አላቀረበም፣ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎችም ውስጥ ለውስጥ ራሱ የተፃፃፈባቸው ናቸው፣ ይግባኝ ባዮች ከ6 እስከ 14 ዓመት ያገለገሉ ለመሆናቸው ተረጋግጧል፣ ቋሚ ሰራተኞች ናቸው ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ፤ መልስ ሰጪ ለይግባኝ ባዮች የስንብት ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ እና የዓመት ዕረፍት ክፍያዎችን ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በተወካዩ አማካኝነት ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ አጠር ባለመልኩ፡- ተጠሪዎቹ ለ2002 ዓ.ም የበጀት ዓመት ለበጋ ወራት መቀጠራቸው እየታወቀ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ናቸው ሲል መወሰኑ የሕግ ሥህተት ነው ማስረጃችንንም አልመረመረም፡- ተጠሪዎቹ የቅጥር ጊዜ በማለት በክስ ማመልከቻቸው ላይ ከመግለፃቸው ባለፈ በማስረጃ ሣያረጋግጡ ተጠሪዎች ከ6 እስከ 14 ዓመት ድረስ አገልግለዋል ሲል ፍ/ቤቱ መወሰኑ፤ ተጠሪዎቹ የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑ የሥር ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24/1 መሠረት የሰጠውን ውሣኔ ቅጥሩ በአዋጁ አንቀጽ 39 እንደሆነ በማስመሰል የስንብት ካሣ ክፍያ ይክፈል ሲል መወሰኑ የሕግ ሥህተት ፈጽሟል፡፡ ተጠሪዎቹ የቀን ሰራተኞች እንደመሆናቸው መጠን በወር 22 ቀናት እንደሚከፈላቸው እየታወቀ ክፍያው በ30 ቀናት እንዲታሰብ ማድረጉ አግባብ ስላልሆነ፤ ችሎቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ያፅናልኝ የሚል ነው፡፡

ችሎቱ የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፡" ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለፕሮጀክት ሥራ መሆኑንና ሥራው መጠናቀቁን አመልካች ቢያስረዳም፣ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪዎች በክሳቸው ላይ

የገለፁትን የአገልግሎት ዘመን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎች ለረዥም ጊዜ ሲሰሩ የቆዩ በመሆናቸው ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት የተለያዩ ክፍያዎችን ይከፈላቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት ይቅረብ " ሲል አዟል፡፡

የሰበር ችሎቱ ተጠሪዎቹ የሰበር አቤቱታው እንዲደርሣቸው በማድረግ፣ መልስ እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪዎቹ ሐምሌ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት 4 ገጽ መልስ፡-ተጠሪዎች ከ2002 ዓመት በፊት ለመሥራታችን የ1999 ዓ.ም እና የ2000 ዓ.ም የመልካም ሥራ አፈፃፀም የምስክር ወረቀት አቅርበናል፡፡ መልስ ሰጪ ከ6 እስከ 14 ዓመት ላለመስራታችን አላስተባበለም " እኛ ግን ምስክሮቻችን አስረድተውልናል" ተጠሪዎች የተቀጠርነው በዋና ቱቦ ማምረቻ ምርት ክፍል ሲሆን ሥራው በጋ እና ክረምት ሣይል ሁሌ የሚሰራበት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የቀጠርኳቸው ለበጋ ጊዜ መንገድ ሥራ ነው ያለ ቢሆንም በየትኛው የአስፋልት ሥራ ለመሆኑ አልጠቀሰም፡፡

ደሞዝን በተመለከተ አመልካች ይከፍለን የነበረው በወርሃዊ የሂሣብ ክፍያ ሲሆን ቅዳሜ እና እሁድ እናርፍ የነበረው በዓላት በመሆናቸው ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ የተፈፀመ የሕግ ሥህተት የለም በማለት ውሣኔውን በማጽናት ያሰናብተን የሚል ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 2004 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የመልስ መልስ የአመልካች መሥሪያ ቤት ከተቋቋመበት እስከ ተጠሪዎች ስንብት ድረስ 12 ዓመት ከ3 ወር የሚሆነው ሲሆን፤ ተጠሪዎቹ እስከ 14 ዓመት ድረስ የአገልግሎት ጊዜ ነበረን ማለታቸው እውነታ የሌለው ነው፡፡

የምስክር ወረቀትን በተመለከተ ከ2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በስተቀር ምስክር ወረቀት ያቀረበ የለም፡፡ ምስክር ወረቀቱም ቢሆን በየዓመቱ ለሠራተኛ የሚሰጥ እንጂ ቋሚ ሥራን የሚመለከት አይደለም፡፡

ተጠሪዎች በጊዜያዊነት የተቀጠሩት በቱቦ ሥራ ፕሮጀክት ቢሆንም ቅጥራቸው ለበጋ ወራት አስፋልት ሥራ ፕሮጀክት ነው የሚል ነው፡፡

ችሎቱም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ቋሚ ሠራተኞች ናቸው ሲል በመወሰኑ፣ የፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለ ወይስ የለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሯል፡፡

ፍ/ቤቱ አመልካች ተጠሪዎችን ለተወሰነ ጊዜ ቀጥሯቸዋል ያለበት ምክንያት አመልካች የሥራ ቅጥር ውል አላቀረበም በሚል ነው፡፡ ግራ ቀኙ የሥራ ቅጥር ውል ያላቸው ለመሆኑ አልተካካዱም፡፡ አመልካች የሥራ ቅጥር ውል ካላቀረበ ቅጥሩ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪዎች ናቸው ያለበት ሌላው ምክንያት አመልካች ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ለውስጥ የተፃፃፈባቸው ናቸው በሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ለቀረበው ክስ እና ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት አላቸውን? በሚለውን ጥያቄ ዙሪያ መታየት ያለበት የሥራ ቅጥሩ ለተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ ላልተወሰነ ጊዜ የሚለውን ጭብጥ ከማስረዳት አንፃር ታይቶ መወሰን ሲገባው ሰነዶቹ አመልካች ራሱ የተፃፃፈባቸው ናቸው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ የሚደረጉበት አግባብ የለም፡፡

www.abyssinialaw.com

በሥር ፍ/ቤትም ቢሆን አመልካች ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በማስረጃነት የተቀበላቸው ማስረጃዎቹ የሥራ ቅጥሩ ለፕሮጀክት ሥራ ሆኖ የበጋ ወራት የአስፋልት ሥራ መሆኑን እና ሥራውን ማብቃቱ የሚያመላክቱ በመሆናቸው ሲሆን እነዚህ ማስረጃዎች ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት የሌላቸው ስለመሆኑ ያስተባበሉት ነገር የለም፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ ከስድስት እስከ አስራ አራት ዓመት የሥራ አገልግሎት አላቸው ሲል የደመደመው ተጠሪዎቹ በክስ ማመልከቻዎቻቸው ጠቅሰውታል በሚል እንጂ ተጠሪዎቹ ይህን ያህል የአገልግሎት ዘመን ያላቸው ባለመሆኑ ያመለከቱበት ደጋፊ ማስረጃ የለም፡፡

2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በ1999 ዓ.ም እና 2000 ዓ.ም ተሰጠን የሚሉት የመልካም ሥራ አፈፃፀም የምስክር ወረቀትም ቢሆን አመልካች ይህ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ምስክር ወረቀት ለሁሉም በየዓመቱ የሚሰጥ ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን ማስረጃው ሁለቱ ተጠሪዎች በተጠቀሱት ሁለት ዓመት የምስክር ወረቀቶቹ የተሰጣቸው ለመሆኑ ከሚያሣይ በስተቀር ተጠሪዎቹ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ለመሆኑ የሚያሣይ አይደለም፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎቹ አላስተባበሉም፡፡

ተጠሪዎቹ የተቀጠርንበት የቱቦ ሥራ ቀጣይነት ያለው ነው ያሉ ቢሆንም ተጠሪዎቹ ቀጣይነት ባለው የቱቦ ሥራ ለተወሰነ የሥራ ጊዜ የተቀጠሩ ከሆነ ሥራው ቀጣይነት ስላለው ብቻ ቅጥሩ ላልተወሰነ ጊዜ ነው በማለት ፍ/ቤቱ መወሰኑ የሕግ ሥህተት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 116131 ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቀጥር 19101 ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡

3. ተጠሪዎቹ ለተወሰነ የሥራ ጊዜ የተቀጠሩ ናቸው፡፡

4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን የየራሣቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 79212

ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም .

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኰንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- ሮያል ከረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አቶ መድህን መሐሪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ፀሐይ ብርሀኑ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጠሪ የሥራ ስንብት በአሠሪው (በአመልካች) አነሣሽነት የተፈፀመ ነው ወይስ በተጠሪ (በሠራተኛዋ) ጠያቂነት የተፈፀመ ነው የሚለውን ጭብጥ የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከህግ ውጭ ከሥራ ያሰናበተኝ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለየዩ ክፍያዎች እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ሥራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁት ከቅርብ አለቃቸው ጋር ባለመግባባታቸው ነው፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ (ከሣሽ) ወደ ሥራቸው እንድትመለስ በቃልና በጽሑፍ የጠየቋት ቢሆንም ከሣሽ (ተጠሪ) ወደሥራዋ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነችም፣፣ ከሣሽ (ተጠሪ)ን ከሥራ ለማሰናበት ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ የሥራ ውላቸው አልተቋረጠም፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ ፈቃድ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአሠሪው ነው ወይስ በሠራተኛው ተነሣሽነትና ፈቃድ የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ ተጠሪ ሥራውን የለቀቅሁት የቅርብ አለቃዬ ሥራውን እንድለቅና እንድሄድ ስላዘዙኝ ነው በማለት ጭብጥ አስይዘው ምስክሮች አስምተዋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ከሥራ ውጪ ካላት በኃላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የቀረበችበት ደመወዝ ተከፍሏት ከቅርብ አለቃዋ ጋር የተፈጠረው ችግር ተስተካክሎ ሥራውን ለመቀጠል የምትችል መሆኑን ተጠይቃ ተጠሪ እንቢተኛ መሆኗን አመልካች አስረድቷል፡፡

ስለዚህ ተጠሪን ከሥራ የማስናበት ሥልጣን የሌለው ሰው ከሥራ ውጪ በማለት ተናግሮኛል በማለት ወደ ሥራ እንድትመለስ ብትጠየቅ እንቢተኛ በመሆኗ የሥራ ውሉ የተቋረጠ በመሆኑ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ

ፈቃድ (አነሣሽነት) ነው በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 520 (አምስት መቶ ሃያ ብር) የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተቀይሮ ብር 190.67 (አንድ መቶ ዘጠና ብር ከስልሣ ሰባት ሣንቲም) እና የዘጠኝ ቀን ደመወዝ ብር 48 (አርባ ስምንት ብር) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይግባኝ ባይ በቅርብ አለቃቸው ከሥራ እንዲወጡ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡ የይግባኝ ባይ የቅርብ አለቃ ሠራተኛ የማሰናበት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑና ይግባኝ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ተጠይቀው ወደ ሥራ ለመመለስ አለመስማማታቸው ስንብቱን ህጋዊ አያደርገውም፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ በመሆኑ፣ የመጀመሪያ ደረጃው ፍርድ ቤት ከወሰናቸው ክፍያዎች በተጨማሪ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ መልስ ሰጭ ለይግባኝ ባይ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የቅርብ አለቃዋ ሥራዋን እንድታቋርጥ ከተናገራት በኂላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ስራዋን እንድትቀጥል የነገራትና እንቢተኛ ሆና ከሥራ ገበታዋ የቀረች መሆኑ እንደተረጋገጠ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ ህግ ወጥ ስንብትን ያሣያል በማለት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረታዊ ዓላማ ያልተከተለና የህግ መሠረት የሌለው ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በቅርብ አለቃዬ ተዘልፌና ሞራሌ ተነክቶ ነው፡፡ ሥራ አስኪያጁም ይህንን የቅርብ አለቃዬን ተግባር ደግፈዋል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው መባሉ ተገቢ ነው በማለት ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም መልስ ሰጥታለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበታት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ የማስጠንቀቂያና የካሣ ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርመረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ከስራ እንድትወጣ የተናገራት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ሥራ ለቅቃ እንድትወጣ ከተናገራት በኂላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪን ቢሮ ድረስ በማስጠራት በቅርብ አለቃዋ የተሰጠው ትእዛዝ ተገቢ እንዳልሆነ፣ የቀረችበት ቀን ደመወዝ እንደሚከፈላትና ወደ ሥራዋ እንድትመለስ ጠይቋት ተጠሪ ወደ ሥራ ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነች መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪን ሥራ ለቅቃ እንድትሄድ የተናገራት የተጠሪ የቅርብ አለቃ በድርጅቱ ያለው ኃላፊነት በሥራ መሪነት የሚያስመድበውና፤ በሥራ መሪነቱ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነትም ሠራተኛ ለማሰናበት የሚያስችለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) በአዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለው ተጠሪ አላስረዳችም፡፡ በሌላ በኩል የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የቅርብ አለቃ ስራዋን እንድትለቅ መወሰኑ ተገቢነት

www.abyssinialaw.com

የሌለው በመሆኑ ተጠሪ ወደ ሥራዋ እንድትመለስ ተጠሪን ጠይቀዋት ተጠሪ እንቢተኛ በመሆኗ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሠራተኛ ከሥራ ለማሰናበት ስልጣንና ኃላፊነት የሌለው የቅርብ አለቃው ከሥራ ለቅቆ እንዲሄድ ስለተናገረው ብቻ፣ አሠሪው የሥራ ውሉን አቋርጦታል ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ሠራተኛው የሥራ ውሌ ተቋርጧል ከማለቱ በፊት የቅርብ አለቃው በሥራ ያለውን ሠራተኛ፣ ከመምራትና ከመቆጣጠር ባለፈ በሠራተኛው ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ለመውሰድና ያለውን ሥልጣን በተለይም ከሥራ የማስናበት ሥልጣን ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን የማወቅና የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የቅርብ ኃላፊዋ ሥራ ለቅቃ እንድትወጣ ቢናገራትም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የቅርብ አለቃዋ እሷን ከሥራ የማሰናበት ስልጣን እንደሌለው ገልፀው ወደ ሥራ እንድትመለስ ጠይቀዋል፡፡

ይህ ከሆነ አመልካች የሥራ ውል ለማቋረጥና ተጠሪን ከሥራ ለማስናበት ሥልጣንና ኃላፊነት ባለው የሥራ መሪ በኩል የሥራ ውልን አቋርጧል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በቅርብ አለቃዋ ሥራ እንድትለቅ የተናገራት መሆኑ ብቻ የሥራ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደርገዋል፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ወደ ሥራ እንድትመለስ መጠየቁ ህገ ወጥ ስንብቱን ህጋዊ አያደርገውም በማለት የሰጠውን የህግ ትርጉም የአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ.83068

ታህሣሥ 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- ዲ.ኤች ገዳ ብርድ ልብስ ፋብሪካ ኃ.የተ.የግ. ማሕበር ነ/ፈጅ አቶ ስንታየሁ ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ቅድስት ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክር ስሆን የአሁኗ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ከሣሽ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክሱም ይዘት ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥራ በማገልገል ላይ እያለች ተከሣሽ ድርጅት ሕጋዊነት የሌለውን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ ከሣሽ የስራ ውል ወዳልፈፀመችበት ዲ.ኤች ገዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነቀምቴ ቅርንጫፍ እንዳዛወራት እርሷም ዝውውሩን በመቃወም ክስ አቅርባ እያለ በተዛወርሽበት ቦታ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በስራ ላይ አልተገኘሽም በሚል ምክንያት ተከሳሽ የስራ ውሏን አላግባብ እንዳቋረጠባት የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ከስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ እንዲወሰንላት ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ ተከሣሽ በበኩሉ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10.2 በሚፈቅደው መሠረት ከሳሽ ወደ ነቀምቴ ቅርንጫፍ እንድትዛወር የተደረገ ቢሆንም ዝውውሩን ተቀብላ በስራ ገበታዋ ላይ ባለመገኘቷ እንድትሰናበት የተደረገው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) መሠረት በአግባቡ መሆኑን እና የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የስራ ውሉን ለማቋረጥ በቀ ምክንያት ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በመ.ቁ.37778 በ04/03/01 በትርጉም አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ የሰጠበት መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አሰሪ አንድን ሰራተኛ ጥቅሙን ሳያጓድል ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት እንድሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 13(2) እና (7) የተመለከተ መሆኑን ሰራተኛውን ከአንድ እህት ኩባንያ ወደ ሌላ እህት ኩባንያ አዛውሮ ማሰራት እንደሚቻል በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 10.2 የተመለከተ መሆኑን በዝርዝር ገልጾ ክሱን ውድቅ በማድረግ ተከሣሽ የ14 ቀን የዓመት ፈቃድ በገንዘብ ለውጦ እንዲከፍልና የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በአሁኗ ተጠሪ የቀረበለትን ይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሳሽ ድርጅት በሰበር ውሳኔውም መሠረት ቢሆን አንድን ሰራተኛ ማዛወር የሚችለው የራሱ ቅርንጫፍ ወደሆነ ሌላ የስራ ቦታ እንጂ በእህት ኩባንያ ስም ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ወዳለው ሌላ ማሕበር ባለመሆኑ ዝውውሩም ሆነ ዝውውሩን ተከተሎ የተወሰደው የስንብት እርምጃ አግባብነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውስኔ ሽሮ ከስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ውስኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ሲሆን በከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት አመልካች ከሰራተኞች ጋር ካቋቋመው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10.2 አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአሁኑ አመልካች የወሰደው የዝውውርም ሆነ የስንብት እርምጃ አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስንብትና ተያያዥ ክፍያዎችን ለተጠሪ ሊፈጽም ይገባል በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች በሰበር ደረጃ አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዋ ተዛውራበት የነበረው የነቀምቴ የሽያጭ ማዕከል ለስራው አመራር አመቺነት ሲባል ብቻ የአመልካች እህት ኩባንያ በሆነው ዴ.ኤች ገዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ፤ ማህበር ስር እንዲተዳደር የተደረገ ቢሆንም በተለይ ከብርድልብስ ሽያጭ ጋር ተያይዞ የአመልካች ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ እንጂ የእህት ኩባንያው ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪዋን ያዛወረው ወደ እህት ኩባንያ እንደሆነ አድርጎ ፌ/ከ/ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት የለውም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የክርክሩን ፍሬ ነገር በማጣራትና የቀረበላቸውን የጽሑፍ ማስረጃ በመመዘን አመልካች ተጠሪዋን ያዛወረበት የነቀምቴ የሽያጭ ማዕከል የራሱ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ ሳይሆን የእህት ኩባንያው ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ እንደሆነ በተመሳሳይ ሁኔታ ማረጋገጣቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት በሕግ የተሰጠው ስልጣን በስር ፍ/ቤቶች የተጣራውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምሮ ውሳኔ ከመስጠት ውጪ ፍሬ ነገር በማጣራትና በማስረጃ ምዘና ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበትን ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የሚያስችለው አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች ተጠሪዋን ያዛወረው ወደ እህት ኩባንያው መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ቀጥሎ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች የዚህ ዓይነቱን ዝውውር ለማድረግ የሚያስችል መብት አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡ በመሠረቱ ተጠሪ የቅጥር ውል ያቋቋመችው ከአመልካች ጋር ብቻ መሆኑ በአመልካች ያልተካደ ሲሆን የአመልካች እህት ኩባንያ ወደሆነ ሌላ ማሕበር ጭምር ተዛውራ ለመስራት በስራ ውሉ ወይም በሌላ ሰነድ በግሏ ወይም በጋራ የሰጠችው ስምምነት ወይም የገባችው ግዴታ ስለመኖሩ አመልካች በስር ፍ/ቤቶችም ሆነ በሰበር ደረጃ የቀረበው ክርክር አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ረገድ ይደግፈኛል በማለት ጠቅሶ የሚከራከርበት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት

ቀደም ሲል በመ.ቁ. 37778 የሰጠው ውሳኔ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደገለፀው ወደ አሰሪው ድርጅት ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ የሚደረግ ዝውውርን እንጂ ወደ እህት ኩባንያ የሚደረግ የሰራተኛ ዝዉውርን የሚመለከት ባለመሆኑ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 116426 በ14/12/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል
2. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል፡፡
3. የውሳኔው ቅጂ ይላክ፡፡ ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ .82335

ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሆሊ ኤንጀልስ ት/ቤት ኃ/የተ/የግል ማህበር

ተጠሪ ፡- መ/ር መልካም አለማየሁ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሲሆን በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክሱም፡- በተከሳሽ (በአሁን የሰበር አመልካች) ት/ቤት በ2003 ዓ.ም በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ተቀጥሬ እየሰራሁ ተከሳሽ ከጊዜ በኋላ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳስተምር ጠይቆኝ እኔም ችግሩን በመገንዘብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ስላለኝ በተጨማሪነት እያስተማርኩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር እንደተቀጠርኩ በመቁጠር በህገ ወጥ መንገድ ከሥራ ስላሰናበተኝ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅትም ለክሱ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት የተቀጠሩት በመንግስት መስሪያ ቤት ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ጡረታ ከወጡ በኋላ ሲሆን የተቀጠሩትም የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ ቢሆንም በማስተማር ሥራ ድክመት በማሳየታቸው በተለያዩ ጊዜያት ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ማሻሻል ባለመቻላቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 36 እና 38 መሰረት በተከሳሽ የታመነ ክፍያ በመፈጸም በህጋዊ መንገድ የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል፤ ከሳሽ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የተለያዩ ክፍያዎች በተመለከተም፡- የስንብት ክፍያ ሊከፈል የሚገባው ከ 5 ዓመት በላይ ላገለገለ ሠራተኛ በመሆኑ ከሳሽም ከዚሁ ከተጠቀሰው ጊዜ በታች ያገለገሉ በመሆናቸው ሊከፈላቸው አይገባም ፣ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው ያሉትም ቢሆን የመምህራን ዕረፍት በክረምት ወራት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያም ድርጅቱ ከሳሽን ያሰናበታቸው ማስጠንቀቂያ አስቀድሞ በመስጠት ስለሆነ የሚከፈል አይሆንም ፣ የካሳ ክፍያም የሥራ ውሉ በህጋዊ መንገድ የተቋረጠ በመሆኑ ሊከፈላቸው አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም፡- ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽ ከመንግስት መ/ቤት የሥራ ችሎታውን በመጨረስ በጡረታ የወጡ መሆናቸውን የሚያምነው ጉዳይ ሲሆን ከሳሽ ትምህርት እንዲማሩ ወይም ድክመታቸውን እንዲያሻሽሉ አድርጎ ማሻሻል አለመቻላቸውን የሚገልጽ ማስረጃ አላቀረበም፣ ከሳሽ ግን በአማርኛ ቋንቋ ተመርቀው ለ28 ዓመታት በአማርኛ ቋንቋ ስለማገልገላቸው ማስረጃ አቅርበዋል፣ በመሆኑም በተመረቁበት የአማርኛ ቋንቋ ሙያ

ተመዝነው ዝቅተኛ ዉጤት ስለማምጣታቸው ወይም በዚሁ የሥራ መደብ ድክመታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ተከሳሽ ሳያቀርብ ከሳሽ ባልተመረቁበትና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ተከሳሽን ለመርዳት ባስተማሩበት ከሚጠበቀው ደረጃ በታች ዉጤት አግኝተዋል በሚል የሥራ ውሉን ማቋረጡ ህጋዊ አይደለም ብሏል፡፡ ከሳሽ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተም፡- ከሳሽ ከሥራ ሲሰናበቱ ሲያገኙ የነበረው የደመወዝ መጠን ብር 1206 መሆኑን በክሳቸው የገለጹ ሲሆን ተከሳሽም በዚሁ የደመወዝ መጠን ላይ ያቀረበው ክርክር ባለመኖሩ እንደተቀበለ ይቆጠራል በሚል ለከሳሽ የሚገባቸውን ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ ባለመክፈሉ ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ ፣ ለስራ ስንብት ክፍያ የ1 ወር ደመወዝ ፣ ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የ2 ወር ደመወዝ፣ በአዋጁ አንቀጽ 42 እና 43(1) መሰረት የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ በመቋረጡ የ2 ወር ደመወዝ ፣ በአንቀጽ 43(4)(ሀ) መሰረት ካሳ እንዲከፈቸው ሲል ሲወስን የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን በተመለከተ ግን የመምህራን የዕረፍት ጊዜ በክረምት በመሆኑ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ውድቅ አድርጓል፡፡

በሥር ተከሳሽ ድርጅት ይግባኝ ጠያቂነት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሠጠው ውሳኔ መልስ ሰጪው የተቀጠሩበት የሥራ መደብ በመምህርነት መሆኑን የቅጥር ማስረጃ የሚያመለክት ሲሆን በሌላ ማስረጃ ደግሞ የተቀጠሩት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተብሎ ስለመሆኑ የተሟላ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ መልስ ሰጪው ተቀጥረው ይሰራሉ ተብሎ የሚታሰበው የሥራ መደብ የትምህርት ማስረጃ የወሰዱበት ነው ተብሎ ይገመታል ፣ ይግባኝ ባይም መልስ ሰጪውን በእንግሊዘኛ ቋንቋ ቀጠርኩ ይበል እንጂ ማስረጃው መልስ ሰጪው በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሰልጠናቸውን የሚያሳይ ባለመሆኑ መልስ ሰጪው የእንግሊዝኛ ቋንቋን በተጨማሪነት እንዳስተምር ይግባኝ ባይ ሰጥቶኛል የሚሉት እውነት ነው ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡ በመሆኑም የግራ ቀኙ ወገኖች ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃዎች ሲመዘኑም ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪውን ያሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የወረዳው ፍርድ ቤት መድረሱ የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብሏል፡፡

ለመልስ ሰጪው እንዲከፈላቸው የወረዳው ፍርድ ቤት የወሰነላቸውን ክፍያዎች በተመለከተም፡- ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪው ማግኘት የሚገባቸውን ክፍያዎች በህጉ በተቀመጠው ጊዜ የከፈላቸው ስለመሆኑ መዝገቡ ስለሚያሳይ ክፍያ ለዘገየበት የጠየቁትን ክፍያ የወረዳው ፍርድ ቤት እንዲከፈላቸው የወሰነው ተገቢ አይደለም ፣ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 42 እና 43(1) መሰረት የሚፈጸም የቅጣት ክፍያ በሌለበት በእነዚህ ድንጋጌዎች ሥር ክፍያ የወሰነው አግባብነት የለውም በማለት ከተወሰነላቸው ክፍያ ውስጥ በድምሩ ብር 6030.00 ተገቢነት የለውም ሲል በመሻር ሌሎች የተጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተ ግን የወረዳው ፍርድ ቤት የወሰነው ተገቢ ነው በሚል በማጽናት በድምሩ ብር 7236.00 ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪው እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካችም በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በሚል የሰበር አቤቱታውን ውድቅ በማድረጉ አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም ሲጠቃለል ተጠሪው ለተማሪዎች ተገቢውን ትምህርት የማይሰጡ ከመሆናቸውም ሌላ የተማሪዎችን ደብተር ሲያርሙ ትክክል የሆነውን ትክክል እንዳልሆነ ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ትክክል እንደሆነ በማደናገር ስለሚያርሙ የተማሪዎች ቤተሰቦች በየጊዜው አቤቱታ በማቅረባቸውና

ተጠሪውም በዕድሜ መግፋት የተነሳ ድክመታቸውን ማሻሻል ባለመቻላቸው እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪው ማስጠንቀቂያ አልሰጠም ቢባል እንኳን ማስጠንቀቂያ ያለመስጠት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል ሊያደርግ ከሚችል በስተቀር ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ሊያሰኝ የሚያስችል ባልሆነበት አመልካች ያቀረብኳቸውን ማስረጃዎች ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ በማድረግ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የአመልካችን ክርክር ዋጋ ያሳጡት ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- የሰለጠንኩትና ለ28 ዓመታት በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገልኩት በአማርኛ ቋንቋ ነው ፣ እንዲሁም በአመልካች ድርጅት የተቀጠርኩት በሰለጠንኩበት የአማርኛ ቋንቋ ስለመሆኑ የውል ሰነዱ ያመለክታል፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋም ቢሆን በማስተማር ሂደት ላይ ጉልህ የሆነ ስህተት ወይም ድክመት ያሳየሁት ስለመኖሩ አመልካች በማስረጃ አስደግፎ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር የለም ፤ በመሆኑም አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግበት የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ለተጠሪው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ተጠሪውን ያሰናበታቸው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል የተለያዩ ክፍያዎችን ለተጠሪው እንዲከፍል የስር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካችና ተጠሪን በዋናነት የሚያከራክራቸው ነጥብ ተጠሪው በአመልካች ድርጅት የተቀጠሩበት የሥራ መደብና ተጠሪው አሳይተዋል የተባለው የሥራ ድክመት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪው የተቀጠሩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሥራ መደብ ነው ሲል ተጠሪው ግን ቅጥሩ የተፈጸመው በአማርኛ ቋንቋ የሥራ መደብ ነው ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪው በአማርኛ ቋንቋ የሰለጠኑ መሆናቸውን የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተጠሪውን የቅጥር ማስረጃ በመመርመርና በመመዘን ማረጋገጣቸውን ከውሳኔው መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው የተቀጠሩት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ የሥራ መደብ ነው በሚል ለዚህ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ የስር ፍርድ ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር ወጪ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪው የተቀጠሩበት በሰለጠኑበት የአማርኛ ቋንቋ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋጠ ደግሞ ድክመት ያለባቸው መሆን አለመሆኑ ደግሞ ሊመዘን የሚገባው በተቀጠሩበት የሥራ መደብ እንጂ ባልተቀጠሩበት የሥራ መደብ ሊሆን አይገባም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ አመልካች ተጠሪው ከተቀጠሩበት የሥራ መደብ ወይም ሙያ ውጪ በመመዘን ድክመት አሳይተዋል በሚል ከሥራ ያሰናበታቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል የወሰኑት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም፡፡ ተጠሪው እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተም የወረዳው ፍርድ ቤት ለተጠሪው እንዲከፈል ከወሰነላቸው የክፍያ ዓይነቶች ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች በመመርመር ሊከፈላቸው የማይገቡትን ክፍያዎች በመለየት ከሰረዘ በኂላ ተገቢነት ያላቸውን ክፍዎች ብቻ አመልካች እንዲከፍል የወሰነው በአግባቡ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት ሆነ ጉዳዩን በየደረጃው ያዩት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የሥራ ውሉ በአመልካች አነሳሽነት በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል ሲሉ በሠጡት ውሳኔም ሆነ ክፍያን አስመልክቶ ከፍተኛው

www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤት በማሻሻል በሠጠው ውሳኔና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ በማጽናት በሰጠው ትዕዝዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 13235 በቀን 03/08/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.147956 በቀን 03/11/2004 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. የሥራ ውሉ በአመልካች ህገ ወጥ ድርጊት ተቋርጧል በሚል የተወሰነው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ለተጠሪው የስንብት ክፍያ ፣ ካሳ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፍል ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወሰኑት ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ተጀምሮ የነበረው የአፈጻጸም ክስ ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በአ/ፈ/መ/ቁ/58289 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ በመሆኑም ለአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲያውቀው ትዕዛዝ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

www.abyssinialaw.com

# ውል

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 78398

ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1ኛ አቶ ሽፈራው ደጀኔ ቀረቡ

2ኛ ወ/ሮ ፀሐይ ተስፋዬ በወኪልና 1ኛ አመልካች ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሲሳይ አበበ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ቤትን በሚመለከት ግራ ቀኙ ያደረጉት የቤት ሽያጭ የሰነድ ውል ቤቱ በምን ያህል ዋጋ ተሸጧል? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በማስረዳት ረገድ ይኸው የጽሑፍ ውል ያለውን የማስረጃ ተቀባይነት ከግራ ቀኙ ክርክር ጋር አገናዝቦ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ተከሳሾች እና እኔ ሐምሌ 17 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረግነው የቤት ሽያጭ ውል በሉኬ ከተማ በአሁን 1ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት በብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ ሸጠውልኛል፡፡ ነገር ግን በውሉ መሠረት የሽያጭ ዋጋውን ተቀብለው ከወሰዱ በኋላ የተሸጠውን ቤት እና የቤቱን ሰነድ ለማስረከብ እምቢተኛ ሆነዋል፡፡ ስለሆነም እንደ ግዴታቸው እንዲፈፅሙ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም በተከሳሽነታቸው የሰጡት መልስ ሐምሌ 17 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረግነው የቤት ሽያጭ ውል አድራሻው የተገለፀውን ቤት በብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ ሸጠናል፡፡ በዚህ የሽያጭ ሰነድ ላይም ገዥው የቤቱን ዋጋ በ10 ቀን ውስጥ ለመክፈል ግዴታ ገብቷል፡፡ ይሁን እንጂ የግዥውን ዋጋ በቀብድም ሆነ በሙሉ የከፈለው ክፍያ የለም፡፡ ስለሆነም ገዥው እንደ ግዴታቸው የቤቱን ዋጋ በጊዜው ባለመክፈሉ የተነሳ ቤቱን ለመረከብና ስመሀብቱ እንዲዛወር ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑ ታውቆ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንድንሰናበት ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት በምስራቅ ወለጋ መስ/ዞን የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤትም አከራካሪው ቤት የተሸጠው በስንት ዋጋ ነው የሚለውን ነጥብ ለመለየት የግራ ቀኙን የሰው ማስረጃዎች ከሰማ በኃላ በመ/ቁ 19594 ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቀን 17/11/2003 ዓ.ም ግራ ቀኙ የቤት ሽያጭ ውል ማድረጋቸውን አምነው የቤቱን ዋጋ

በመክፈልና አለመክፈል እንዲሁም በተሸጠው የቤት ዋጋ ላይ ተካክደዋል፡፡ ሆኖም በቤቱ የሽያጭ ውል የቤቱ ዋጋ ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ መሆኑንና ይህም ዋጋ መከፈሉን በውሉ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005 (1) እንደተደነገገው በፅሑፍ ማስረጃ ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ ቃልና ቀን በፈረሙት ሰዎች መካከል እምነት የሚሰጠው ማስረጃ ነው፡፡ በዚሁ የፅሑፍ ማስረጃ ላይ የሚገኘውን ቃል መቃወም የሚቻለው በመሃላ ቃል ብቻ እንጂ በሰው የምስክርነት ቃል ማስተባበል አይቻልም፡፡ ስለሆነም ሻጮች ግዴታቸውን ስላልተወጡ ቤቱን ለከሳሽ እንዲለቁ እና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በማቅረብ ድጋፍ ያድርጉ፤ እንደ ግዴታቸው ባለመፈፀማቸውም ገደብ ብር 10,00.00 /አስር ሺህ ብር/ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመቀጫ ገንዘቡን ከማንሳቱ በቀር በተመሳሳይ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በዚህ ከላይ በተገለፀው መሠረት በየደረጃው የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኝነት በመስጠቱ ይህ የሰበር ጉዳይ ለዚህ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር በሥር ፍ/ቤት አንስተው የተከራከሩበትን የሚያብራራ እና የሚያከራክር እንጂ በይዘቱ የተለየ አየደለም፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2005 እንደተደነገገው በፅሑፍ ሰነዱ ላይ ስለሚገኘው የስምምነት ቃል እንዲሁም ስለ ተፃፈው ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ብሎ ሊደመደም የሚችለው እንደውለታው ዓይነት የጽሑፍ ውል አደራረግን ሥርዓት አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 (ሐ)፣ 1719(2) የተመለከተውን በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል ለመያዝ አስፈላጊ የሆነውን የውል አደራረግ ሥርዓት አሟልቶ የያዘ ስለመሆኑ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ) እና 1719 (2) መሠረት የውሉ አደራረግ ሥርዓት በተለየ አኳኋን እንዲደረግ በህግ ተለይቶ ከተመለከተው ድንጋጌ አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 (1) የተመለከተው ይገኝበታል፡፡ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለን የባለቤትነት መብት በሽያጭ ለማስተላለፍ ሲባል የሚደረገው የውል ስምምነት በፅሑፍ ሆኖ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አኳኋን ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት መደረግ አለበት የሚለውም የህግ ማሟያ ክፍል አስፈላጊነት የሽያጭ ውል ተደርጓል ወይስ አልተደረገም? ተደርጎ ከሆነስ መቼ በምን ያህል ዋጋ፣ የትኛው ንብረት ወዘተ የሚለውን አስመልክቶ አላስፈላጊ የሆኑ ሙግቶችን ለማስቀረት ታስቦ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ የባለቤትነትን መብት የሚያስተላልፉ ውሎች ውሉ ስለመኖሩ እስካልታመነ ድረስ በአዋዋይ ፊት መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ በተያዘዉም ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005 (1) እንደተመለከተው በፅሑፍ ሰነድ ላይ ስለሚገኘው የስምምነት ቃል እንዲሁም በላዩ ላይ ስለተፃፈው ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው

የሚለው ድንጋጌ ከላይ በተገለፀው አኳኋን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ)፣ 1719(2) እና 1723 (1) ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ለማናቸውም የፅሑፍ ውል ስምምነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡

ይህ አከራካሪ የሆነው ሽያጭ ውል የተደረገው የማይንቀሳቀስ በሆነው ንብረት በቤቱ ላይ ነው፡፡ ውሉ የተደረገውም በፍ/ሕ/ቁ 1723 የተመለከተውን ድንጋጌ አሟልቶ አይደለም፡፡ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ተደርጎ ቢሆን ኖሮ የቤቱን ዋጋ እና ይህንኑ ዋጋ ተቀብለዋል አልተቀበሉም የሚለውን አስመልክቶ በፅሑፍ ከሠፈረው ቃል ውጭ የመቅረብ ማናቸውም ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005(1) እንደተደነገገው ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም፣ ከፅሑፍ ሰነዱ በቀር የሚቀርብ ማናቸውም ማስረጃ የሰውም ምስክሮች ቃል ተቀባይነት የለውም በማለት መደምደም ባልተቻለ ነበር፡፡

ስለሆነም በህግ ፊት ሊፀና በሚችል ውል ለመመደብ ቋሚ ማሚያ ሆኖ የተያዘውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 (ሐ)፣ 1719(2) እና 1723 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ የተደረገ ስምምነት ባለመሆኑ ይህ ዓይነት ስምምነት በህግ ፊት ዋጋ ያለው ሆኖ፤ ሊፀና የሚችል ስምምነት ነው ብሎ ውጤት ለመስጠት የሚቻል ባለመሆኑ የአሁን ተጠሪ ይህን በህግ ፊት ሊፀና የማይችለውን ውል መነሻ በማድረግ እንደ ውሉ ይፈፀምልኝ በማለት በአመልካቾች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካቾች ይህንኑ ቤት በብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ ሸጠናል በማለት በፍሬ ነገር ረገድ ገልፀው የተከራከሩ ከመሆኑ እና የሽያጭ ዋጋም አልተቀበልንም በማለት የተከራከሩ በመሆኑ የአሁን ተጠሪ በዚሁ አመልካቾች በጠቀሱት የሽያጭ ዋጋውን ከፍለው ቤቱን ለመረከብ እና አስፈላጊ ሰነዶችን ለመጠየቅ ከፈለጉ ግን ይህ ውሳኔ ይህንኑ መብቱን ቀሪ ሊያደርግ የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ሁሉ ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ሽያጭ ውል የማይንቀሳቀስ የሆነውን ቤትን አስመልክቶ የተደረገ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005 (1) የተመለከተው ድንጋጌ አፈፃፀም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ሳይመለከት በዚህ በውል አዋዋይ ፊት ባልተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ላይ የሠፈሩት ማናቸውም የውል ቃሎች ሁሉ ያለቅድመ ሁኔታ እንዳሉ የሚታመኑ ናቸው፤ በማናቸውም ዓይነት የሰው ምስክርነት ቃል ማስተካከል አይቻልም በሚል የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን መስተዳደር የጎቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 19594 በቀን 17/5/04 የሰጠው ውሳኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27455 በቀን 28/06/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፋ.ቁጥር 139094 በቀን 11/07/2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፋ.ቁጥር 147416 በቀን 18/7/2004 የሰጠው ትዕዛዝ ሁሉ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ክርክር ያስነሳው ቤት ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገን የቤት ሽያጭ ውል መሠረት አድርጎ ያቀረበው የቤት ክርክር ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፤
3. ሆኖም ሻጮች ባመኑት ዋጋ መሠረት የሽያጭ ዋጋውን የመክፈል ግዴታ በእራሱ በኩል ከተወጣ ክርክር ያስነሳውን ቤት እና በዚህ ቤት ላይ ያለን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ አስፈላጊ ከሆኑት ሰነዶች ጋር ያለውን የመረከብ መብት ይህ ውሳኔ አያግደውም ብለናል፡፡

4. በሥር ፍ/ቤቶችም ሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከትለው ማናቸውም ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የመስማሚያ ሀሳብ**

እኔ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምፅ በደረሰበት መደምደሚያ የምስማማ ሲሆን አብላጫው ድምፅ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 (1) እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005ን በማጣመር በሰጠው ትርጉም አልተስማማሁም፡፡ በእኔ እምነት የአመልካቾችን የትምህርት ሁኔታ በማጣራት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1728 ንዑስ አንቀፅ 3ን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መወሰን የተሻለ ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 74950

ህዳር 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይምሰል

አመልካች ፡- ወ/ሮ ዙቤዳ ኑር ኬርሰማ ጠበቃ አቶ ባህሩ መኮንን ቀረበ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ሚሊዮን ዳግም ሙሴ

2. አቶ ምንተስኖት ሀብታሙ

3. አቶ ደርባቸው ሀብታሙ

4. ወ/ት የትናየት ሀብታሙ

(1–4) ጠበቃ አቶ መኮንን በዛብህ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የወለድ የገንዘብ ብድር የወሰደ ተበዳሪ የብድር ገንዘቡን መመላሻ ጊዜ ካሣለፈ የብድሩን ገንዘብ ብቻ ሣይሆን ከህጋዊ ወለድ ጋር የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማጣቀስ ለመለየት ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከአሁን 1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና ከሌሎች ተጠሪዎች አባት ከሟች ከአቶ ሐብታሙ ብርሃኑ ታህሣስ 26 ቀን 1995 ዓ.ም በተደረገ የብድር ገንዘብ ብር 237,000.00 /ሁለት መቶ ሰላሣ ሰባት ሺህ ብር/ መበደራቸውና ይህንኑ የብድር ገንዘብ ጥር 30 ቀን 1995 ዓ.ም ለመመለስ ግዴታ የገቡ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

ተጠሪዎች ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ ተበዳሪው ዋናውን የብድር ገንዘብና ይህንኑ የብድር ገንዘብ መክፈል ከነበረበት ጊዜ ከየካቲት 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ሲጠይቁ የአሁን አመልካች ወለድ ለመክፈል በብድር ስምምነቱ ላይ ግዴታ ያልገባሁ በመሆኑና የመክፈያው ጊዜ እንዳለፈም ገንዘቡን እንድመልስ በማስጠንቀቂያ ያላሣወቁኝ ስለሆነ ወለድ የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር በኮ/መ/ቁ. 97284 ተመልክቶ ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የብድር ውሉ አልተካደም ጥር 30 ቀን 1995 ዓ.ም ለመመለስም ተበዳሪው

ግዴታ ገብቷል፡፡ የብድር መመለሻ ጊዜው በዚህ አኳኋን ቁርጥ ያለ ጊዜ ስለተቀመጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1775(ለ) መሠረት ይህ ጊዜ ካለፈ በኂላ ገንዘብ ጠያቂው ማስጠንቀቂያ መስጠት አያስፈልገውም፡፡ ስለሆነም ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጠኝ ወለድ ልከፍል አይገባም የሚለው ክርክር ተቀባይነት ስለሌለው ተበዳሪ ከየካቲት 01 ቀን ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ዋናውን የብድር ገንዘብ ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ ከላይ የተመለከተው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ ረገድ ቅሬታን የሚያስከትል አይደለም፡፡ በማለት መልስ ሰጭዎችን ሣይጣራ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበውም የአሁን አመልካች ይህ በጉዳዩ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡትን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉበትን የመከራከሪያ ነጥብ በመጥቀስ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎችም በበኩላቸው ውሣኔው በህግ መሠረት የተሰጠ ነው የሚሉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር መልሳቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም እንደ ሥርዓቱ ለዚሁ መልስ የመልስ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተው ተመልክተናል፡፡ የአሁኗ አመልካች ወለድ እንዲከፍል በገንዘብ ብድር ውሉ ላይ ግዴታ ስለመግባቱ ሣይገለጽ፤ እና ማስጠንቀቂያም ሣይደርሰኝ በወለድ ገንዘቡን ትከፍላለህ የሚለው ዳኝነት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1775 (ለ) የተመለከተው ድንጋጌ በአግባቡ ሣይታይ በመተርጎሙ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ይልቁንም በብድር ስምምነቱ ላይ ወለድ የመክፈል ግዴታ ባልተጠቀሰ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1478 እንደተደነገገው ወለድ የመክፈል ግዴታ እንደሌለብኝ ግልጽ ነው፡፡ የሚሉትን ነጥቦች በመጥቀስ በሥር በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሆኖም ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ጉዳይ የገንዘብ ብድር ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሣን ክርክር ስለዚሁ ጉዳይ የሚገዛው ልዩ የህጉ ክፍል ተፈፃሚ በማድረግ ምላሽ የሚሰጠው ሆኖ ከተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1676 እንደተመለከተው ጉዳዩ በዚህ ለጉዳዩ በቀጥታ ተፈፃሚነት ባለው የህጉ ክፍል መሠረት የሚታይ እንጂ ስለውሎች በጠቅላለው በሚለው የህግ ክፍል የተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብነት አይኖራቸውም፡፡ ከዚህ አንፃር ይህንኑ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን በፍ/ብሔር ህጉ የሚያልቅ ነገር ብድርን አስመልክቶ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2478 ላይ ተበዳሪው ወለድ እንዲከፍል የውል ቃል ከሌላ በቀር ለአበዳሪው ወለድ መክፈል የለበትም በሚል የተቀመጠው ድንጋጌ ተዋዋይ ወገኖች ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ተጠቅመው በገንዘብ ብድሩ ውል ስለወለዱ አከፋፈል የጠቀሱት ጉዳይ ባይኖር ይህ መሰል የገንዘብ ብድር ውል ስምምነት የወለድ ክፍያ ግዴታን ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? የሚል ክርክር እንዳያስነሣ ህጉ ክፍተቱን ለመሙላት ማስቀመጡ እንጂ ተበዳሪው በገባው ግዴታ መሠረት የብድር ገንዘቡን በመመላሻው ጊዜ አለመክፈሉ ቢረጋገጥ ይህ የመክፈያ ጊዜው ላለፈበት ጊዜ ወለድ የማይከፈል መሆኑን ሁሉ የሚሸፍን አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

ይህም በመሆኑ ነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2489(1) ተበዳሪው የተበደረውን ነገር ከመመለስ ወይም ከመክፈል የዘገየ እንደሆነ ስለውሎች በጠቅላላው በሚለውና አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ጊዜ በማሣለፍ የሚከፈለውን ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት በሚል የተደነገገው፡፡ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ የወለድ ግዴታን ሳካተተም ሳላካተተም ጭምር እንደሆነ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2489(1) የተመለከተው ስለውሎች በጠቅላላው የህግ ክፍል አፈፃፀም እንደብደሩ ዓይነት እያታየ ተግባራዊ የሚሆኑ እንጂ ለማናቸውም የብድር ገንዘብ መቼም ቢሆን ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2482 እና 2483 ድንጋጌ ንባብ አስረጂ ነው፡፡

በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2482 እንደተደነገገው ይህ ክርክር ያስነሣው የብድር ስምምነት የብድር ገንዘቡን መመለሻ ጊዜ አስቀድሞ ወስኖ ያስቀመጠ በመሆኑ እና ወለድ የመክፈል ግዴታም ያላስቀመጠ በመሆኑም እንደዚህ ያለ የብድር መመለሻ ጊዜ ተወስኖ ከሆነ የብድር ገንዘቡን ከዚህ መመለሻ ጊዜ በፊት የመክፈል ግዴታውን በተበዳሪው ላይ የሚጣል እንጂ ይህ የመክፈያ ጊዜ ካለፈ በኃላ አበዳሪው ለተበዳሪው ጊዜው እልፏልና ክፈለኝ በማለት ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የለበትም፡፡ አበዳሪ የማስታወቅ ግዴታ የሚኖርበት በብድር ውሉ ላይ የብድሩን ገንዘብ መመለሻ ጊዜው በውሉ ያልተወሰነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ ተከታይ በሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2483 ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ብቻ እንጂ ወለዱንም ጨምረው ለመክፈል ግዴታ ያልገቡበት ስምምነት በመሆኑ እና የመክፈያ ጊዜው በወሉ ላይ ተወስኖ የተቀመጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2482(2) እና (3) መሠረት በመመላሽ ጊዜው የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተረድቶ ጊዜው ከማለፉ በፊት አለመክፈሉ እስከተረጋገጠ ድረስ የብድር ገንዘቡን ከህጋዊ ወለድ ጋር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት በውጤት ደረጃ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 71668 ነሐሴ 09 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ የብድር ገንዘቡን ከየካቲት 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ከፍለው እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ከህጋዊ ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ በሰበር መ/ቁ. 74950 ታህሣስ 11 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርዱ መሠረት በመ/ቁ. 111637 የተጀመረው የአፈፃፀም ጉዳይ ታግዶ ይቆይ በሚል ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.63063

ህዳር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም - ነገረጅ ፈቃዱ ኃይሌ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፒቲኢ ኢንተርናሽናል ኢንኮፖሬትድ - ተወካይ ዶ/ር ብርሃነ ገብራይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከስራ ውል ጋር ተያይዞ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በግልግል ጉባኤ ነው፡፡ የግልግል ጉባኤው ግራ ቀኙ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 ዓ/ም በፈረሙት ውል መሰረት የተቋቋመ ሲሆን ግልግሉ በውሉ መሰረት ከተቋቋመ በኋላ ክሱን ያቀረበው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአሁኑ ተጠሪና በአሁኑ አመልካች በታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ተደርጎ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 በተፈረመና ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ/ም እስከ ነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ ውል ተዋውለው እንደነበር፣ ውሉ የተደረገውም አመልካች አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም ኩባንያ ለመፍጠር እገዛ ለማድረግ ተግባር መሆኑና በውሉ መሰረት ተጠሪ የአመልካችን የሰው ኃይል ችሎታ ከፍ በማድረግ የአሰራር ሂደቶችን፣ ፖሊሲዎችንና የአሰራር ደንቦችን ለማጎልበት፣ አመልካች የአሰራር ሂደቱን ለመደገፍ በጥቅም ላይ ያዋለውን ቴክኖሎጂ እንዲረዳ ለማስቻል፣ የአሰራር ሂደቱ ከቴክኖሎጂው ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥና ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም በጥቅም ላይ የዋሉ ሲስተሞችና ሥርዓቶችን በተግባር ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣ ለአመልካች ፐርሶኔል /የሰው ኃይል/ ተገቢ የሆነ መዋቅርን በማቅረብ እነዚህን ቴክሎኖሎጂዎችና የአሰራር ሂደቶችን በተሳካ ሁኔታ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማስቻል፣ በትራንስፎርሜሽን /ለውጥ/ ሂደት ተሳትፎ የሚያደርጉ ፐርሶኔሎችን መሰረታዊ የስራ መስፈርቶችን ለማቅረብ፣ የስልጠና ፕሮግራሙ በተሳካ ሁኔታ መስጠት እንዲቻል ተገቢ የሆኑ ይዘቶችን እና አስፈላጊ የሆኑ ፋሲሊቲዎችን መለየትና የመፍትሔ ሃሳብን ለማቅረብ ግዴታ መግባቱን፣ አመልካች ለዚህ የተጠሪ ስራ $ 4,289,189.60 (አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከስልሳ ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር) ለመክፈል መስማማቱንና ተጠሪ ደግሞ አስራ አራት አማካሪዎችን ለማስማራትና ከእነዚህ ውስጥ አምስቱ ለስምንት ወራት በቋሚነት እንዲሰሩ እና ስድስቱ ደግሞ ለሰባት ወራት እየተቀያየሩ የሚሰሩ አማካሪዎች እንዲሁም ቀሪዎቹ ደግሞ ለአራት ወራት እየተቀያየሩ የሚሰሩ አማካሪዎችን መድቦ የነበረ መሆኑን፣ በውሉ መሰረትም የአከፋፈሉ ሁኔታ ለመጀመሪያ ሶስት ወራት (ጥር፣ የካቲትና መጋቢት) ለተሰሩት ስራዎች

የውሉን ዋጋ 40%፣ ለሁለተኛው ሶስት ወራት (ሚያዚያ፣ ግንቦትና ሰኔ) ለሚሰሩት ስራዎች እንዲሁ የውሉን 40%፣ ቀሪውን የውሉን 20% ደግሞ በሁለት ወራት (ሐምሌና ነሐሴ) ለሚሰሩት ስራዎች እንደሚከፈል መገለጹን፣ 12% የሚሆነው የውሉ ዋጋ ደግሞ ከእያንዳንዱ ክፍያ ከመጀመሪያው ክፍያ ጀምሮ እየተቆረጠ ተይዞ እንደሚቆይ ስምምነት መደረጉና ተጠሪ ስራዎችን በትክክል አከናውኖ የስራ አፈጻጸምና በውሉ አስፈላጊ የሆኑት ተመጣጣኝ ደረሰኞችን ቢያቀርብም በውሉ አንቀፅ 11.4 መሰረት ሊከፈለው የሚገባው የተያዘ ገንዘብ መኖሩን ገልፆና የውሉ ዘመን ማብቃቱን ጠቅሶ አመልካች $293,050.12 (ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ሃምሳ ከአስራ ሁለት ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር) የተያዘ ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል፣ በዚህ ገንዘብ ላይ ከነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያበቃ ድረስ ወለድ እንዲታሰብለትና ለክሱ የወጡት ወጪና ኪሳራዎች እንዲተኩለት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስም በግራ ቀኙ ውሉ መኖሩን ሳይክድ ተጠሪ የሚጠበቁበትን ግዴታዎችን፣ መስራት ያለበትን ስራዎችን በሙሉ በመስራት ያላሟላ መሆኑን፣ የታቀደው በስራ ላይ ይውላል ተብሎ የነበረው አዲሱ ኩባንያ በተጨባጭ ሁኔታ ሊታይ እንዳልቻለና በውሉ መሰረት ስራው መጠናቀቅ በነበረባቸው የስምንት ወራት ጊዜ ውስጥ ያለመስራቱን፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሩብ አመታት በውሉ መሰረት መጠናቀቅ የነበረበት ስራ 80% የነበረ ሁኖ በተጨባጭ የተጠናቀቀው ግን 41.5% ብቻ መሆኑን፣ በሁለተኛው ግምገማም የውሉ ዘመን ካለቀ በኋላ የተከናወነው ስራ 71.3% ብቻ መሆኑ መረጋገጡንና በአጠቃላይ የተጠሪ የስራ አፈጻጸም እንደውሉ ያልተናከናወነና አጥጋቢና ስኬታማ ያልነበረ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረበ ሲሆን እንደ ውሉ ባለመፈጸሙ የደረሰውን ኪሳራ ዘርዝሮ $428,918.96 (አራት መቶ ሀያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት ከዘጠና ስድስት ሣንቲም የአሜሪካን ዶላር) በተጠሪ እንዲከፈለው ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተገቢ ነው ያለውን መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የግልግል ጉባኤውም ተጠሪ በውሉ መሰረት የገባውን ግዴታ ያለመወጣቱ መረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለተጠሪ ሊከፈል ይገባ ከነበረው $4,289,189.60 ውስጥ በተሰራው ስራ መጠን $2,442,084.39 ወይም የውሉን 56.93% መክፈሉ ስራው በድጋሚ እንዲገመገም ከተደረገ በኋላ እና አመልካች ቴክኒካዊ ፐርሶኔል ክፍል የድጋፍ ደብዳቤ ከተፃፈ በኋላ $726,498.55 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል መደረጉንና በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ውል ለማቋረጥ መስማማቱ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ ለመልካም ስራ አፈጻጸም የተያዘው 12% ገንዘብ ከተሰራው ስራ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ሊለቀቅ የሚገባው እንጂ በአመልካች የሚያዝበት አግባብ የለም ሲል አመልካች ለተጠሪ $87,169.02 ከነሐሴ 09 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ (9%) ጋር እንዲከፍል፣ በዚሁ ገንዘብ መጠን የጠበቃ አበል 10% እንዲከፈል የወሰነ ሲሆን የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነትን ክስ ግን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በግራ ቀኙ ውል የግልግል ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑ በመገለፁ ምክንያት አቤቱታው ለዚህ ሰበር ችሎት በቀጥታ ቀርቧል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በግራ ቀኙ መካከል ከታሀሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የተደረገው ውል በሕጉ አግባብ ሳይሻሻልና ይህንኑ ተጠሪ ባላረጋገጠበት ሁኔታ የዳግም ግምገማ ውጤቱን መሰረት በማድረግ የመልካም ስራ አፈጻጸም መያዣ ገንዘብ በተሰራው ስራ መጠን ሊለቀቅ ይገባል

www.abyssinialaw.com

ተብሎ መወሰኑም ሆነ ተጠሪ እንደ ውሉ ግዴታውን ያልፈጸመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኞች እ.ኤ.አ መስከረም 15 ቀን 2008 በተደረገው የመልሶ ግምገማ (Re-evaluation) በግራ ቀኙ መካከል ውሉን ለመቋጨት የታለመ ስምምነት መደረጉን ያመላክታል በማለት እና በዚሁ መልሶ ግምገማ አመልካች ተፈጻሚነቱ ባበቃው ውል የነበረውን የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ የማቅረብ መብቱን ትቷል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ከመደረጉም በላይ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎትም የቃል ክርክር እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ከነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ የሚቆይ የአለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም ኩባንያ ለመፍጠር ሲባል የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑበትን ስምምነት ማድረጋቸውን ግራ ቀኙ የማይካካዱበት ጉዳይ መሆኑን፣ ግልግል ጉባኤውም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል የጊዜ ገደብና በውሉ በተገለፀው መሰረት ስራው ውጤታማና ስኬታማ በሆነ መንገድ በተጠሪ ምክንያት ያልተፈጸመ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ዳግም ግምገማ ተካሄዶ ስራው 71.3% መሰራቱ በአመልካች ተወካዮች ተረጋግጦ የውሉ ገንዘብ በዚሁ በተሰራው ስራ መጠን ብር $726,489.55 እንዲሆን ተደርጎ ለተጠሪ እንዲከፈል ሲደረግ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ በተሰራው ስራ ልክ መለቀቅ ሲገባው ያላግባብ የተያዘበት መሆኑን ገልጾ ይኸው ገንዘብ እንዲለቀቅለት መሆኑን፣ አመልካች የሚከራከረው ደግሞ በዳግም ግምገማ ጊዜ የቀድሞው ውል ያልተሻሻለ መሆኑንና ክፍያ እንዲፈፀም የተደረገውም በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ለማቋረጥ በማሰብ የአከፋፈሉ ሁኔታ የቀድሞውን ውል መሰረት በማድረግ ሊሆን እንደሚገባ መስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈው ደብዳቤ ይዘት የሚገልፅ መሆኑና በጠቅላላው የቀድሞው ውል በሕጉ አግባብ ባልተሻሻለበትና ተጠሪ ግዴታውን እንደ ውሉ አልፈጸመም ተብሎ በተረጋገጠበት አግባብ አመልካች ለተጠሪ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ ሊለቅ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ስለ ውል መሻሻል የሚደነግጉትን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችንና የግራ ቀኙን ውል ይዘትና በጉዳዩ ላይ የተጠየቀውን ዳኝነት እንዲሁም የማስረጃ አቀራረብና የዳኝነት አሰጣጥ ስርአትን ያልተከተለ ነው በማለት መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በግልግል ዳኝነት ክሱን ሲያቀርብ የቀድሞው ውል በህጉ አግባብ ተሻሽሏል በሚል ዳኝነት ያለመጠየቁንና ውል ስለመሻሻሉ የሚያሳይ ማስረጃ አለ ብሎ የማይከራከር መሆኑን በዚህ ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር ያረጋገጠው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ በግልግል ጉባኤው የተደረገው የክርክር ሂደትም አመልካች ውሉ ተሻሽሏል በማለት ያቀረበው ክርክር የሌለ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ በውሉ መሰረት ስራውን ሙሉ በሙሉ ሰርቼአለሁ ብሎ የማይከራከርና 71.3% ብቻ መስራቱን መረጋገጡን የማይክደው ፍሬ ነገር ሲሆን በውሉ ላይ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ በተሰራው ስራ ልክ መለቀቅ ያለበት ስለመሆኑ ስምምነት ተደርጓል በማለት የማይከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ በተሰራው ስራ መጠን ሊለቀቅ ይገባል በማለት የሚከራከረው በግራ ቀኙ

መካከል ያለውን ግንኙነት ለመቋጨት ዳግም ግምገማ እንዲደረግ ተደርጎ የተሰራው ስራ መጠን ተጣርቶ በዚህ አግባብ ክፍያ እንዲከፈል አመልካች በተወካዮቹ አማካኝነት ስምምነት ላይ ደርሷል በሚል ምክንያት መሆኑንም ተረድተናል፡፡ አመልካች የዳግም ግምገማው ሪፖርት ተቀባይነት ላይ ክርክር የሌለውና የዚህ ሪፖርት አላማ በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን ግንኙነት ወደፊት ቀሪ እንዲሆን ታስቦ የተከናወነ መሆኑንም የሚቀበለው ጉዳይ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ስለሆነም ምላሽ የሚያሻው የጉዳዩ ጭብጥም አመልካችና ተጠሪ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 (እ.ኤ.አ አፕሪል 17 ቀን 2008) ያፀደቁት የሥራ ውል ተሻሽሏል ወይንስ አልተሻሻለም? የሚለው ነው፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ከማየታችን በፊት ግን የተጠሪ ወኪል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሷቸው ነጥቦች ላይ ምላሽ መስጠቱ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

የተጠሪ ወኪል አመልካች የሰበር አቤቱታውን በጊዜ ገደቡ ያለማቅረቡንና በግልግል ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን ግራ ቀኙ የተስማሙት መሆኑን ገልጸው ጉዳዩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ አይገባም በማለት ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሰበር አቤቱታውን እንዲያቀርብ በሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁጥር 62141 በሕጉ አግባብ የፈቀደለት በመሆኑ የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ማለፉን መሰረት በማድረግ የተጠሪ ወኪል ያቀረቡትን ተቃውሞ አልተቀበልነውም፡፡ እንዲሁም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ስምምነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው የሚል ቢሆንም እንኳ የሰበር ሰሚ ችሎቱን ስልጣን በስምምነት ለማስቀረት የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 42239 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ተቃውሞም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስም በመሰረቱ በውል አመሠራረት ሂደት ውል ተቀባይ ተብሎ የሚታወቅ ወገን ውሉን መቀበሉ በጽሁፍ፣ በልማዳዊ ምልክት ወይንም በተግባር ካላመለከተ በስተቀር መልስ ሣይሰጥ ቢቀር በግራ ቀኙ መካከል የውል ግዴታ ተቋቁሟል ለማለት እንደማይቻል ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1682 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ድንጋጌ የሚሳየው በመርህ ደረጃ ዝምታ ውልን እንደመቀበል ሊቆጠር እንደማይችል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ ሁኔታዎች ዝምታ ውልን እንደመቀበል እንደሚያስቆጥር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1683 እና 1684 ድንጋጌዎች ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም አግባብ አስቀድሞ በግራ ቀኙ መካከል የውል ስምምነት ባለ ጊዜ አንድ ወገን ይህንን ውል ለማደስ፣ የውሉን ዘመን ለማስረዘም፣ ለማሻሻል ወይም ከቀድሞው ውል ጋር በተዛመደ አኳኋን ተጨማሪ ውል ለማድረግ የሚያቀርበው ጥያቄ በበቂ ጊዜ ውስጥ በሌላው ተዋዋይ ወገን አሉታዊ ምላሽ ካልተሰጠበት ዝምታው መቀበልን እንደሚያስከትል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1684 ስር ተደንግጓል፡፡ የፍ/ሕ/ቁጥር 1722 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ቀድሞ የነበረ ውል በሚሻሻልበት ጊዜ አስቀድሞ በተደረገው የአፃፃፍ ሥርዓት መከናወን እንዳለበት በግልፅና አስገዳጅነት ባለው መልኩ ሰፍሯል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ግራ ቀኙ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የሥራ ውል ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ከነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ የሚቆይ አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም ኩባንያ ለመፍጠር ሲባል የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑበትን ስምምነት ማድረጋቸው በግራ ቀኙ የታመነ ቢሆንም በውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብና የአፈጻጸም ጥራት ስራው ያልተከናወነ መሆኑን ተጠሪ የማይክደው፣ እንዲሁም የግልግል

www.abyssinialaw.com

ጉባኤውም በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄውን ያቀረበውም የቀድሞው ውል በሕጉ አግባብ ተሻሽሏል በሚል ምክንያት ስላለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያረጋግጠው ነጥብ ሲሆን ተጠሪው ለጥያቄው መሰረት ያደረገው መስከረም 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገው የመልሶ ግምገማ አመልካች ለተጠሪ ለተሰሩ ስራዎች ክፍያ እንዲፈፀም ስምምነት አድርጓል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ መስከረም 5 ቀን 2001 ዓ/ም በአመልካች መስሪያ ቤት ኃላፊዎች ተቀባይነት አግኝቷል የተባለው የመልሶ ግምገማ ሪፖርት ውጤት ተጠሪ ቀድሞ በተደረገው የውልና እና የጥራት ደረጃ 71.3% (ሰባ አንድ ነጥብ ሶስት ከመቶ) ብቻ የሰራ መሆኑ መረጋገጡን አመልካች በማመን አሁን አጥብቆ የሚከራከረው ይህ የመልሶ ግምገማ ሪፖርት በቀድሞው ውል ስለ ክፍያ አፈፃጸም የተመለከተውን ሌሎች የተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታ ቀሪ ያደረገ ባለመሆኑ ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ስለመሰራቱ ከተረጋገጠው የስራ መጠን ጋር ተዛምዶ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አመልካች ለተጠሪ ሊለቅ የሚገባበት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለም በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን እንደተመለከተው ተጠሪ የቀድሞ ውል የተሻሻለ ስለመሆኑ መሰረት አድርጎ ክስና ክርክር ያላቀረበ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1722 መሰረትም የተሻሸለ ውል ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 መሰረት መብቱን ያስረዳበት የክርክር ሂደት የለም፡፡ ተጠሪ የሚጠይቀውን ክፍያ ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አኳኋን በተጠሪ በኩል የቀረበ የውል ማሻሻል ጉዳይ በሌለበት ሁኔታ አመልካች የመስከረም 5 ቀን 2001 ዓ/ም የመልሶ ግምገማ ውጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1684 መሠረት በዝምታ ተቀብሏል ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብም ሊኖር አይችልም፡፡ ይልቁንም የአመልካች መስሪያ ቤት ኃላፊ የመልሶ ግምገማ ሪፖርቱን ከተመለከቱ በኋላ ተጠሪ አለኝ የሚለውን ክፍያ በቀድሞው ውል መሰረት እንዲከናወን በሚያስገነዝብ መልኩ ጠቅሰው በመልሶ ግምገማ ሪፖርቱ ላይ ማዘዛቸውን አመልካች በአቀረበው የሰነድ ማስረጃ ይዘት የተረጋገጠ ስለመሆኑ በጉባኤው ላይ የተደረገው የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የመስከረም 5 ቀን 2001 ዓ.ም. የመልሶ ግምገማ ሪፖርት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1722 መሠረት የቀድሞው ውል የተሻሸለበት መሆኑን ባልተረጋገጠበትና በሪፖርቱ ላይ የክፍያው አፈጻጸም በቀድሞው ውል ከተገለፀው ውጪ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ በቀድሞው ውል አንቀፅ 11.4 ድንጋጌ መሰረት ተጠሪ ከሚገባው ክፍያ በተሰራው ስራ መጠን መሰረት 12% እንደሚለቀቅለት በግልጽ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ግልግል ጉባኤው የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ በመልሶ ግምገማ መሰረት በተረጋገጠው 71.3% ስሌት መሰረት እንዲለቀቅ መወሰኑ የውል ወይም የሕግ መሰረት በሌለበት ሁኔታ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ አንድ የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን በማየት የዳኝነት መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች በተስማሙበትና በሚጸና ወይም ዋጋ ያለውን ግዴታ በመከተል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 356(ሀ) ድንጋጌ አቀራረፅ፣ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ ይህ ድንጋጌ የግልግል ወይም የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ተከራካሪዎቹ ወገኖች የተስማሙበት ነው በማለት በማይጸና ወይም ዋጋ የሌለውን ግዴታ በመከተል ወይም ባለጉዳዮቹ ያላቀረቡትንና ያልተከራከሩበትን ጉዳይ መሰረት በማድረግ ብይን የሰጡ መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩ ይግባኝ የሌለው መሆኑን ቢስማሙም እንኳን ይግባኝ ለማቅረብ መሰረት ከሚሆኑ ነገሮች መካከል እንደሆኑ ጠቅሷል፡፡በመሆኑም የግልግል ጉባኤው የመልካም ስራ አፈጻጸምን በተመለከተ ተጠሪ ስለመስራቱ በመልሶ ግምገማ በተረጋገጠው መጠን ስሌት መሰረት ታስቦ ሊመለስለት ይገባል በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ከመልሶ ግምገማ በኋላ የቀድሞ ውል በሕጉ አግባብ የተሻሸለና ዋጋ ያለው ስምምነት ስለመኖሩ ባልተረጋጠበት ሁኔታ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ የተከሳሽ ከሳሽነትን ክስ መሰረት ያደረገ የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ ነው፡፡ በክርክሩ ሂደት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገው ውል በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለመከናወኑና የተሰራው ስራም በውሉ የተገለፀውን ያህል መጠን ያለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የጉዳት ካሳ ጥያቄን መሰረት ያደረገውም ስራው በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያለመሰራቱና በውሉ አንቀፅ 17 የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ በውሉ አንቀፅ 17 ስር ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ግዴታውን ካልተወጣ ሌላው ወገን የጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑንና ሊጠየቅ የሚገባውን የጉዳት መጠን ምን ያህል እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ የመልካም ሥራ አፈጻጸም (ቦንድ) ሰነድ የውል አፈፃፀምን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የዋስትና ሰነድ መሆኑን፣ ይህም በባለገንዘብ እና በባለ እዳ መካከል የተደረገን ውል አፈፃፀም ለመጠበቅ የሚገባ ግዴታ መሆኑ ከሰነዱ አይነተኛ ዓላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የመልካም ስራ አፈፃፀም ቦንድ መሰረታዊ አላማ ስራው በውሉ መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ የሚገባ ግዴታ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ የጸናው ውል በአንቀጽ 11.4 ስር ከመጀመሪያ ክፍያ ጀምሮ እየተቀነሰ 12% የሚሆነው የውሉ ዋጋ እንዲያዝ የሚደረግ መሆኑንና የውሉ ዘመን ካለቀ ከ15 ቀናት በኋላ ስራዎቹ በስኬታማ ሁኔታ መጠናቀቃቸውን በሃርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ ከተረጋገጠ በኋላ የሚለቀቅ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ በዚሁ በውሉ ድጋጌ ውስጥ ".....ስራዎቹ በስኬታማ ሁኔታ መጠናቀቃቸው----" የሚለው ሐረግ ሲታይ የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ ስራዎቹ በስኬታማ ሁኔታ ባይጠናቀቁ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ ጭምር ታስቦ የተገባ ግዴታ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካች ተጠሪ በተከሳሽ ከሳሽነት በውሉ አንቀጽ 17 መሰረት የጠየቀው የጉዳት ካሳ መጠን በውሉ አግባብ ሳይሰራ በዘገየበት ጊዜና ስራውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ በተጨማሪነት አስፈላጊ የሆነውን ጊዜ መሰረት በማድረግ ተሰልቶና በአመልካች እጅ ይገኛል ከተባለው የመልካም ስራ አፈጻጸም ገንዘብ መጠን የበለጠ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን ግንኙነት መሰረት በማድረግ የተሰራውን ስራ መልሶ በመገምገም በተሰራው ስራና ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ በጸናው ውል መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም የተደረገ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ ስራውን በጊዜ ለማጠናቀቅ ባለመቻሉና ስራውን ወደፊት ሰርቶ ለመጨረስ የሚያስፈልገው ጊዜ ላይ ካሳ ለማስከፈል አመልካች ሃሳብ የነበረው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን ግንኙነት መሰረት አድርጎ በተሰራው የስራ መጠን ለተጠሪ ክፍያ በመፈጸም የውሉ ማጠናቀቂያ ጊዜ ከሆነው ከነሐሴ 2000 በኋላ ስራው ለዘገየበትና ስራውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ለሚያስፈልገው ተጨማሪ ጊዜ ያልተሰራውን ስራ 0.1% ያህል የክፍያ መጠን ለእያንዳንዱ ቀን ወይም የውሉን ጠቅላላ ዋጋ 10% በጠቅላላው የጉዳት ካሳ ከተጠሪ የሚጠይቅበት አግባብ ስለመኖሩ በማስረጃ ያላስደገፈው የክርክር ነጥብ ነው፡፡ ይልቁንም አመልካች ስራው በውሉ በተቀመጠው ጊዜና ጥራት ያለመጠናቀቁን እያወቀ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ቀሪ እንዲሆን መስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገው የመልሶ ግምገማ ሪፖርት መነሻነት ስምምነት አድርጓል፡፡ ይህ ስምምነት የሚያሳየው ውሉ በጊዜው ባይጠናቀቅም በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት አቋርጧል፡፡ የተቋረጠ ውል ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች መካከል እስከተቋረጠ ድረስ እንጂ ውሉ ከተቋረጠ በኋላ ባለው ጊዜ ወይም ወደፊት ውጤት የሚያስከትልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1819(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ የሆነው የመስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. የመልሶ ግምገማን ሪፖርት አመልካች በመቀበል ስራውን ለወደፊት ለመስራት የሚያስፈልጉ

www.abyssinialaw.com

ጊዜያትን ቀሪ በማድረጉ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የግልግል ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ነሐሴ 06 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 353 መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. ተደረገ የተባለው የመልሶ ግምገማ ሪፖርት ስምምነት በመካከላቸው ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. የተደረውን ውል ያላሻሻለ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ በመልሶ ግምገማ መሰረት ስለመሰራቱ በተረጋገጠው 71.3% ስራ መጠን መሰረት የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ ለተጠሪ የሚለቅበት አግባብ የለም ብለናል፡፡ የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ከተደረገው ውል አንቀፅ 11.4፣ 17 ይዘትና መንፈስ ከመስከረም 5 2001 ዓ.ም. የመልሶ ግምገማ ሪፖርትና ውጤቱ ጋር ባገናዘበ መልኩ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## *የሐሳብ ልዩነት*

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ በከፊል ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ ከሙያ ባልደረቦቼ በከፊል የማልስማማባቸውና በከፊል የምስማማባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጀመሪያው ልዩነቴ የግራ ቀኙን ክርክር ለመፍታት የሚያስችል ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያስፈልጋል የሚል ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ "አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት የሥራ ውል ተሻሽሏል ወይስ አልተሻሻለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝና ይህንኑ ጭብጥ ለመወሰን አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1722፣ የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1684 እና የውሉን ኃይለ ቃሎች በመተርጎምና መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በእኔ በኩል የግልግል ጉባኤው አብዛኛውን የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በመሆኑ አሁን በሰበር የሚከራከሩበትን ጉዳይ ለመወሰን ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ውል በአመልካችና በተጠሪ ስምምነት ተቋርጧል ወይስ አልተቋርጠም? ውሉ በተዋዋዮቹ ፈቃድና ስምምነት ተቋርጧል የሚባል ቢሆን የውሉ መቋረጥ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች ካልተያዙና ስለ ውል መቋረጥ መሠረታዊ ባህሪይ፣ አፈፃፀምና ውጤት የሚደነግጉ የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ውሣኔ

www.abyssinialaw.com

ካልተሰጠ የግራ ቀኙን ክርክር በአግባቡ ለመፍታት አይቻልም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ምክንያቱም አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የሥራ ውል መሠረት ተጠሪ 71.3% ሥራ የሠራ መሆኑን ግራ ቀኙ ያልተካካዱበትና የግልግል ጉባኤው ያረጋገጠው፣ ይህ የሰበር ችሎትም ትክክል ነው ብሎ የተቀበለው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን ውል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ለማቋረጥ (terminate) ለማድረግ መስማማታቸውና ውሉ በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆኑ (terminate) መደረጉ በግልግል ጉባኤው ተረጋግጧል፡፡ አብላጫው ድምፅም አመልካች በአፀፋ ክስ ውሉ በአግባቡ ባለመፈፀሙ ተጠሪ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ የግልግል ጉባኤው ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የግልግል ጉባኤውን ውሣኔ በከፊል ያፀናው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆኑን (terminate) መደረጉን በመጥቀስ ነው፡፡

ተጠሪ በውሉ መሠረት 71.3% ሥራ ከሠራ በኋላ ውሉ በአመልካችና በተጠሪ ስምምነት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት መቋረጡ (ቀሪ) መሆኑ ካላከራከረ፣ አመልካችና ተጠሪ ውላቸውን በስምምነት ቀሪ ማድረጋቸው አመልካች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሚሆን ነው በማለት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ 87,169.02 የአሜሪካን ዶላር አላግባብ የቀነሰብኝ ስለሆነ እንዲከፍል በማለት ተጠሪ ባቀረበው ጥያቄ ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? በተመሣሣይ ሁኔታ የውለታው በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆን አመልካች ተጠሪ ውሉን አሟልቶ ባለመፈፀሙ ለደረሰብኝ ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ባቀረበው አፀፋ ክስ ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚሉትን ነጥቦች መመርመር ይጠይቃል፡፡

ውለታን ለማስቀረት በተዋዋይ ወገኖች በፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደረግ ስምምነት፣ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1675 በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ ውል አቋቁመውት የነበረውን ግዴታቸውን ለማስቀረት ያደረጉት ውል ነው፡፡ ይህም ማለት አመልካችና ተጠሪ ውሉን ለማቋረጥ (ቀሪ) ለማድረግ በሚያደረጉት ስምምነት ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በስተቀር በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711 መሠረት የመሰላቸውን የመወሰን መብት ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ ውሉ በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆኑ (terminate) መደረጉ የሚያስከትለውን ውጤት በመረዳት አመልካችና ተጠሪ ውሉን ለማቋረጥ ሲስማሙ ፈቃዳቸውን የሰጡባቸውን መሠረታዊ ጉዳዮችና ስለውል መቋረጥ (termination of contract) የተደነገጉ የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ አከራካሪውን ጭብጥ መወሰን የሚጠይቅ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

2. አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ ሲስማሙ፣ አመልካች ተጠሪ ለሰራው ሥራ 657,408.51 የአሜሪካን ዶላር የተጣራ ክፍያ ለመክፈል መስማማቱን የግልግል ጉባኤው አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የተጠሪን የትራንስፖርት ወጭ፣ የአየር ትኬትና የቤት ኪራይ ወጭ መሸፈኛ የሚሆን 69,000 የአሜሪካን ዶላር ለመክፈል መስማማቱ በግልግል ጉባኤው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች እነዚህን ክፍያዎች በመፈፀም ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ (ለመዝጋት) የተስማማ መሆኑን አይክድም፡፡ የግልግል ጉባኤው ውሣኔ የሰጠበትና አመልካችንና ተጠሪን ያላግባባውና እስከ ሰበር ያከራከረው፡፡ አመልካች ተጠሪ ለሠራው ሥራ ከሚከፍለው

www.abyssinialaw.com

657,408.51 የአሜሪካን ዶላር፣ ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረግሁት የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 መብት ይሰጠኛል በማለት 12% በመቀነስ ክፍያ መፈፀሙና በተመሣሣይ ሁኔታ አመልካች ለትራንስፖርት፣ ለአየር ትኬትና ለቤት ኪራይ የወጣ ወጭ መሸፈኛ ለመክፈል ከተስማማው 69,000 የአሜሪካን ዶላር 12% ቀንሶ ማስቀረቱ ነው፡፡

ተዋዋይ ወገኖች በውል አቋቁመውት የነበረውን ግዴታ በፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በስምምነት ቀሪ ሲያደርጉ የተለየ ፎርም መከተል እንዳለባቸው የሚደነግግ አስገዳጅ ድንጋጌ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን የሥራ ውል በስምምነት ማቋረጣቸው አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡ የውለታ በተዋዋዮች ስምምነት መቋረጥ (terminate) መደረግ ከውል መፍረስ ወይም ከውል መሠረዝ የተለየ ባህሪና ውጤት ያለው መሆኑን አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ድንጋጌዎች ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ እንደዚሁም ውል በስምምነት ቀሪ ማድረግ (termination of contract) ውልን ከማሻሻል (ውል ከመለወጥ) (variation of contract) እና ውል ከመተካት (Novation of contract) የተለየ ባህሪ፣ ይዘትና ውጤት ያለው መሆኑን፣ የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1722 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1826 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ስመለከተው አመልካች ከተጠሪ ጋር በተደረገው ስምምነት ቀሪ የሆነውን ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ተደርጎ የነበረው የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1722 በሚደነግገው መሠረት ያልተሻሻለ በመሆኑ ለተጠሪ ከምከፍለው ክፍያ 12% ቀንሶ የማስቀረት መብት አለኝ በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ውልን በስምምነት ቀሪ በማድረግና ውለታን በማሻሻል መካከል ያለውን ልዩነት ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

የውሉ በተዋዋዮቹ ፈቃድና ስምምነት መቋረጥ (ቀሪ) መሆን የተዋዋይ ወገኖች የወደፊት የውል የመፈፀም ግዴታ የሚያስቀር መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም የውሉ መቋረጥ /ቀሪ/ መሆን ያለፈውን ሁኔታ የማይነካ መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውል ቀሪ መሆን (termination of contract) ተዋዋዮቹ በውል አቋቁመውት የነበረውን መብትና ግዴታ ቀሪ የማድረግ ውጤት የሚኖረው መሆኑን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1807 /ለ/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርጎት የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ ሲስማማ ተጠሪ ለሰራው ሥራና ውሉን ለመፈፀም የወጣውን ወጭ ለመሸፈኛ እንዲሆን በድምሩ 726,408.51 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ በመክፈል ውለታውን ለማቋረጥ የሰጠው ፈቃድና ስምምነት ውሉን ለማሻሻል የተሰጠ ፈቃድ ሳይሆን ውሉን ለማቋረጥ የተደረገው ስምምነት ልዩ ሁኔታና ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ውሉን ለማቋረጥ ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት ውል ያቋቋሟቸው መብቶችና ግዴታዎች ተቋርጠዋል (ቀሪ ሆነዋል)፡፡ አመልካች የውሉ ሕልውና በስምምነት ቀሪ የሆነውን ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ተደርጎ የነበረውን የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በማድረግ ለተጠሪ ውሉን ሲያቋርጥ ለመክፈል ከተስማማው ገንዘብ አሥራ ሁለት ፐርሰንት ቀንሶ ለማስቀረት የሚያስችለው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ መብት የለውም፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን ውል ቀሪ ለማድረግ ያደረገው ስምምነት እንደ ማናቸውም ውል በተዋዋዮቹ ላይ የሕግ ያህል ገዥነትና አስገዳጅነት የሚኖረው መሆኑን የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ከፍታሐብሔር ሕግ

www.abyssinialaw.com

ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ጋር በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ቀሪ ለማድረግ ሲስማማ ለመክፈል ፈቃዱን የሰጠበትን ገንዘብ ሣይቀናነስ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ አመልካች ውለታን ቀሪ ለማድረግ ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት ገዥነቱና ተፈፃሚነቱ ቀሪ የሆነውን የሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 በመጥቀስ 87,169.2 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ ከሚከፍለው ክፍያ ቀንሶ ማስቀረቱ ከላይ በዝርዝር የገለፅኳቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መሠረት የሌለው ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ይህንን የአመልካች አድራጎት የግልግል ጉባኤው የሕግ መሠረት ስለሌለው ቀንሰህ ያስቀረኸውን ገንዘብ ለተጠሪ ክፈል በማለት መወሰኑ ተገቢና የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

3. አመልካች በስምምነት ሕልውናው፣ አስገዳጅነቱና ተፈፃሚነቱን ቀሪ ያደረገውን ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርጎት የነበረውን የሥራ ውል በመጥቀስ ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታውን አጠቃልሎ ያልፈጸመ በመሆኑ፣ ውሉ ባለመፈፀሙ ተጠሪ ካሣ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበውን የአፀፋ ክስ የግልግል ጉባኤው ውድቅ አድርጎታል፡፡ የግልግል ጉባኤው የአመልካችን የአፀፋ ክስ ቀሪ ያደረገው ውሉን ለማቋረጥ (termination) ለማድረግ ስትስማሙ በውሉ አለመፈፀም ለደረሰ ጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብት ያለህ ስለመሆኑ አልተገለፀም፡፡ በአንፃሩ ውሉን ቀሪ ለማድረግ የተስማማኸው በውሉ አለመፈፀም ካሣ የመጠየቅ መብትህን በመተው ነው በማለት ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ ይህ የግልግል ጉባኤው ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያደረገ መሆኑን በመዘርዘር በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎ የግልግል ጉባኤው የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶቷል፡፡ እኔ በዚህ የውሣኔ ክፍል አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ የምስማማበት ነጥብ ነው፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና ተራ ቁጥር 2 በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች አመልካች የሕግ ወይም የፀና የውል መሠረት ሣይኖረው ቀንሶ ያስቀረውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው ብዬ ስለማስብ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 71537

ታህሣስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች:- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

አመልካቾች ፡- 1. ወ/ሮ የሻረግ ከበደ - ከጠበቃ አቶ ሐጎስ ደበሉ ጋር ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሃና አድማሱ - ከጠበቃ አቶ አለማየሁ ታደሰ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን ቀረቡ

ይህ በሰበር መ/ቁ. 71537 የተሰየመው መዝገብ በቀጥታ የአሁን 1ኛ አመልካችና የአሁን ተጠሪን የሚመለከት ቢሆንም፤ የአሁን 2ኛ አመልካች ወ/ሮ ሃና አድማሱና የአሁን ተጠሪ ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን በሰበር መ/ቁ 72381 የሚከራከሩበት ጉዳይ ለሰበር መ/ቁ. 71537 መነሻ ከሆነው ከፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ. 75093 ጋር አብሮ የተነሣ ክርክርም ሆነ ውሣኔ ማስረጃው አብሮ የተሰማና በአንድ ቀን በአንድ ላይ ውሣኔ የተሰጠበት በመሆኑ እና ሁለቱም አመልካቾች በየፊናቸው ራሱን የቻለ የሰበር መዝገብ በማስከፈታቸው ምክንያት ተለያይቶ የቀረበ መሆኑን ሁሉ በማየት በሰበር መ/ቁ. 72381 የተነሣውን ጉዳይ ከዚህ ሰበር መ/ቁ. 71537 ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት እና በአሁን አመልካቾች ተከሣሽነት የተነሣውን ክርክር ተመልክቶ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 75093 የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ በከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበው ክስ ላይ የአሁን አመልካቾችን 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች በማድረግ ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃል በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 19 የቤት ቁጥር 423 በተመዘገበው ቤት በ2905 ካ.ሜትር ውስጥ የሚገኘውን ቤት 1ኛ ተከሣሽ ወ/ሮ የሻረግ ከበደ ከሰኔ 14 ቀን 1986 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ያላግባብ ይዘው እየተገለገሉበት ስለሚገኝ በዚህ በቤት ቁጥር 423 ውስጥ የሚገኘውን ሁለተኛውን ቤት ከእነ ማእድ ቤቱ ደግሞ ሁለተኛ ተከሣሽ ወ/ሮ ሃና አድማሱ ከግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በኃይል በመያዛቸው ቤቶችን ከኪራይ ክፍያ ጋር ያስረክቡኝ የሚል ነው፡፡

ለዚህም ክስ በማስረጃነት ያቀረቡት ወ/ሮ አለሙሽ አዲሱ ክስ የቀረበበትን ቤት ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል ለከሣሽ ያስተላለፉ መሆኑን የሚገልጽውን የስጦታ ውል ቤቱ በወ/ሮ አበበች ወልደዮሐንስ ስም ግብር የተከፈለ መሆኑን የሚያሣይ የግብር ክፍያ ደረሰኝ እንዲሁም በመ/ቁ. 2525/89 እና 0691 በ24/2/98

በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ፤ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 5865 በ11/3/94 ዓ.ም የተሰጠውን ውሣኔ በማያያዝ አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁን 1ኛ አመልካች ወ/ሮ የሻረግ ከበደ በሰጡት መልስና ቤቱን ያላግባብ ይዛለች ከተባለበት ከሰኔ 14 ቀን 1986 ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲሰላ ክሱ በይርጋ ሊቋረጥ ይገባል፡፡ ስጦታው ክርክር የተነሣበትን ቤት የሚያመለክት አይደለም፡፡ ክስ የቀረበበትን ሁለት ክፍል ቤቶች ከወ/ሮ አበበች ወ/ዮሐንስ በስጦታ ያገኘሁትን ኩሽና ቤት አፍርሼ የሰራሁት የእራሴ ሀብት ነው ይኸው ክስ የቀረበበት ቤትም የስጦታ አድራጊ የተባሉት የወ/ሮ አለሙሽ ርስት ስለመሆኑም ማስረጃ የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሁለተኛ አመልካች በበኩላቸውም በኃይል ንብረቱን ወስዳለች ከተባለበት ከግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ በህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም. ተደረገ የተባለው የስጦታ ውል በይርጋ ቀሪ ከመሆኑም በላይ ያልተመዘገበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም እኔ እራሴ በእርሷ በከሣሽ ላይ ያቀረብኩት ክስ እየታየ ስለሆነ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበው ክስ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን በማስረጃነትም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 80684 የተሰጠ ውሣኔ አቅርበዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ 1ኛ ተከሣሽ የአሁን 1ኛ አመልካች ወ/ሮ የሻረግ ከበደ በቤት ቁጥር 423 በተመዘገቡ ሁለት ቤቶች መካከል በስጦታ ከወ/ሮ አበበች ወ/ዮሐንስ በመረከብ አፍርሰው ሁለት ቤቶችን መሥራታቸውን ጠቅሰው ቢከራከሩም የተሰጣቸው የስጦታ ውል በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም ተብሎ በውሣኔ የፈረሰና ሰራሁ ስለሚሉትም ለቤቱ የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ባለማቅረባቸው ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በአኳያው ክርክር የተነሣበትን ቤትና ይዞታ ከሣሽ ከእናታቸው ከወ/ሮ ዓለሙሽ አድማሱ በ12/3/66 በስጦታ ያገኙ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ቀርቧል፡፡ የአሁን ሁለተኛ አመልካች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ከከሣሽ ጋር በመከራከር ላይ እገኛለሁ ቢሉም ቤቱን እንዲረከቡ አልተፈረደላቸውም፡፡ ቤቱም በወ/ሮ አበበች ወ/ዮሐንስ የተመዘገበና ለጊዜውም በባለቤትነት የምታወቀው እኔ ነኝ በማለት ከመከራከራቸው በቀር ሁለተኛውን ቤት አልያዝኩም በማለት በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ስለሆነም ሁለቱም ተከሣሾች ክስ የቀረበበትን ቤት ለከሣሽ እንዲያስረክቡ ይገደዳሉ፤ ያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

ይህንን ውሣኔ በ1ኛ አመልካች አቤቱታ መሠረት በይግባኝ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 68052 ሰኔ 06 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እንደተደነገገው መዝገቡን ዘግቷል፡፡ እንዲሁም በሁለተኛው አመልካች ይግባኝ ባይነት በይ/መ/ቁ. 67759 ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተመሣሣይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥረ 337 መሠረት በመዝጋቱ የአሁን ሁለቱም አመልካቾች በየፊናቸው እንደቅደም ተከተሉ ለዚህ የሰበር ጉዳይ ማለትም በሰበር መ/ቁ. 71537 አና በሰበር መ/ቁ. 72381 ምክንያት የሆነውን የሰበር ቅሬታ በማቅረባቸው በእነዚሁም የሰበር መዛግብት ላይ ሁሉም ያላቸውን የጽሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሰበር አመልካቾችም ሆነ ተጠሪ በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት አንስተው የተከራከሩባቸውን ነጥቦች የሚያብራሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የዚህ የሰበር ጉዳይ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተውን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው እንደ ጉዳዩ አነሣስና ይዘት በዚህ ጉዳይ በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው አከራካሪ ነጥብ የአሁን አመልካቾች የቀረበብን  ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ካነሱት ነጥብ አንፃር ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህንን አከራካሪ ነጥብ አስመልክቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 75093 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሳሽ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ የባለቤትነት መብትን የሚመለከት በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ አይችልም የሚል ትርጉም ሰጥቶ ክሱ በይርጋ አይታገድም የሚል ዳኝነት እንደሰጠበት ከመዝገቡ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

በንብረት ላይ ያለን የመፋለም ክስ አስመልክቶ ይህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 43600 ጥር 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደማይገባ ተንትኖ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በዚሁ ትርጉም በተሰጠበት ውሣኔ ላይ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት ከውርስ ከሽያጭ እና ከስጦታ ውል የመነጨን የባለቤትነት መብት አስመልክቶ በሚነሳ የንብረት ክርክር የይርጋ ጉዳይ በተነሣ ጊዜ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ለጉዳዩቹ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው የህግ ክፍል እና የህግ ይዘት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ በተለይ አኳኋን ተመልክቶ ትንታኔ የሰጠበት እንጂ ማናቸውም በንብረት ላይ ያለን የባለቤትነት መብት ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ የሚችል አይደለም በሚል አልወሰነም፡፡

ይህም አሁን በግራ ቀኙ የተነሣውን ክርክር እንዳየነው የአሁን ተጠሪ በስጦታ ውል ከወ/ሮ አለሙሽ አድማሴ የተላለፈልኝን ቤት ተከሣሾ /የአሁን አመልካቾች/ ያለአግባብ ይዘውብኛል በሚል መነሻ የቀረበ የንብረት መብት ማስከበር ጥያቄ እንደመሆኑ ከስጦታ ውል የመነጨውን የንብረት መብት ለማስከበር የሚቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም? የይርጋ ክርክርን ሊጋብዝ የሚችል ከሆነስ የይርጋ ዘመኑ ምን ያህል ነው? የሚሉትና ተያያዥነት ያላቸው ክርክሮች ስለስጦታ ውል አመሰራረት ውጤት እና የመሳሰሉትን ዝርዝር ጉዳዮች በሚገዛው የህግ ክፍል እና የአፈፃፀም ወሰን መሰረት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ 42691 መጋቢት 22 ቀን 2002ዓ.ም በዋለው ችሎት ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ ይህም ጉዳይ በዚሁ ትርጉም መሰረት ሊታይ የሚገባው እንጂ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደሰጠው ትርጉም በይርጋ የሚታገድ የክርክር ዓይነት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከዚህም አንፃር የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ ላቀረቡት ቤት ይመለስልን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ የቤት ቁጥር 423 ባለንብረት የነበሩት እና ወ/ሮ አለሙሽ አድማሱ ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል አስተላልፈውልኛል በሚል እንደሆነ በፍሬ ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ለክርክሩ መሰረት ያደረጉት የስጦታ ውል ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም የተደረገ ሆኖ የተሻሻለ ክስ እስከ መሰረቱበት እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ሆነ ንብረቱን ተከሳሾች ያለአግባብ ይዘዋል እስከተባለበት እስከ ሰኔ 14 ቀን 1986 እስከ ግንቦት 30 ቀን 1999 ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ እንኳ ከ20 ዓመት በላይ ነው፡፡ በዚህ ስጦታ ተደረገ በተባለበት በህዳር 1966 ዓ.ም እና ንብረቱ ያለአግባብ ተይዟል እስከተባለበት ጊዜ ድረስ የስጦታ

ውሉ ውጤት ይኖረው ዘንድ መብትን ለማስከበር የቀረበ እንቅስቃሴም ሆነ ለአፈፃፀም የቀረበ አለመሆኑን ክርክሩ አስረጅ ነው፡፡ ይህም ከሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 42691 እንደሰጠው ትርጉም የስጦታ ጉዳዩን የሚገዛው የህግ ክፍል ሰለይርጋ በተለየ መንገድ የደነገገው ጉዳይ ባይኖርም ስጦታ ውል እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676/1/ እና 1845 ድንጋጌዎች መሰረት ከስጦታ ሊመነጨ የሚችል የግዴታ አይነት በ10 ዓመት የጊዜ ገደብ ሊገደብ የሚገባው ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ንብረቱን በስጦታ እግኝቻለሁ ካለበት ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ንብረቱን ተከሳሾች ያዙብኝ እስካሉበት ጊዜ ድረስ ከ20 ዓመት በላይ በሆነው ጊዜ ውስጥ በስጦታ ውሉ መሰረት ንብረቱን በእጅ ስለማድረጋቸው ወይም ክርክር ያስነሳውን ቤት በስጦታ ውሉ መሰረት በይዞታቸው ስር እንዲሆን በውሉ መሰረት እንዲፈፀሙላቸው ያቀረቡት ጥያቄ እንደሌለ በክርክርም ሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ የስጦታ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ስጦታ ውሉ ለማስፈፀም ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ደግሞ ከ10 ዓመት /ከአስር ዓመት/ በላይ የሆነ ጊዜ አልፎታል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ከስጦታ ውል የመነጨ የንብረት ጥያቄ በመሆኑና ጥያቄውም የቀረበው ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የህግ ክፍል የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኂላ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአሁን አመልካቾች ያቀረቡትን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረጉበት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 75093 የካቲት 30 ቀን 2003ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና በዚህ ፍርድ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 68052 በ06/10/2003 እና በይ/መ/ቁ 67759 በ3/10/2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም ተደርጓል ያሉትን የስጦታ ውል መሰረት አድርገው በአሁን አመልካቾች በወ/ሮ የሻረግ ከበደ እና በወ/ሮ ሀና አድማሱ ላይ ያቀረቡት የቤት ይለቀቅልን ጥይቄ በይርጋ የታገደ ነው፡፡ አመልካቾች ቤቶችን ለተጠሪ ለወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን ለማስረከብ አይገደዱም ብለናል፡፡
3. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ሁሉም ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ
4. የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ የመ/ቁ 75093 በመጣበት አኳኋን ይመለስ፡፡
5. የዚህ ክርክር ውጤት እስኪታወቅ ድረስ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ በሰበር መ/ቁ 71537 ህዳር 06 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገበ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 75743

ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት ፍትህ ቢሮ - ዐ/ህግ እዮብ ጌታቸው

ተጠሪዎች ፡- 1/ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ - አልቀረቡም

2/ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ተመስገን ዘውዴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አመዘጋገብ ስህተት ላደረሰ ኪሳራ ካሳ የመክፈል ኃላፊነትን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአንደኛ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረችው ወ/ሮ ዘውዴ ሽፈራው ጥር 14 ቀን 1988 በተፈረመ የብድር ውል ለሆቴል ህንፃ ግንባታ የሚውል ብር 110,800 (አንድ መቶ አስር ሺህ ስምንት መቶ ብር) ከከሳሽ (አንደኛ ተጠሪ) ተበድራ ወስዳለች፡፡ ተበዳሪዋ ይህንን ገንዘብ የወሰዱት የካርታ ቁጥሩ 614/935/61 በሆነው ይዞታ ላይ የሰፈረውን የድርጅት ቤት በመያዣነት እንዲያዝ በመስማማት ሲሆን ይሕ የመያዣ ውል እንዲመዘገብልን ጠይቀን የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት (አመልካች) በቁጥር 642/4188 ጥር 24 ቀን 1988 ዓ.ም የማይንቀሳቀስ ንብረቱን ለከሳሽ ብድር የመጀመሪያ መያዣ አድርጎ የመዘገበው መሆኑን አረጋግጦልኛል፡፡ ሆኖም ሁለተኛ ተከሳሽ (ተበዳሪዋ) በብድር የወሰደችውን ገንዘብ ባለመክፈሏ፣ ከሳሽ (ሁለተኛ ተጠሪ) መያዣውን በሀራጅ በመሸጥ የብድር ገንዘቡን ለመሰብሰብ ሲንቀሳቀስ፣ ይኸው የተበዳሪዋ የማይንቀሳቀስ ንብረት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሀምሌ 11 ቀን 1987 የብድር ውል ሲይዝ ቤቱን በመያዣነት የያዘው መሆኑን በመግለፅ ደብዳቤ ፅፏል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ (አመልካች) ቤቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ላበደረው ብድር መያዣ መሆኑን ቢገልፅልኝ ኖሮ የብድር ገንዘቡን ለሁለተኛ ተከሳሽ አልሰጥም ነበር፡፡ ስለዚህ ከተበዳሪዋ የምንፈልገውን ብር 265,661.40 እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ለንብረቱ ሁለት የይዞታ ማረጋገጫ ያልሰጠሁ በመሆኑ በኃላፊነት አልጠየቅም፡፡ ከሳሽ መጀመሪያ የተበዳሪዋን ንብረት በመከታተል ዕዳውን ለመሰብሰብ ሳይሞክር ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለተኛ

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ ቤቱ መያዣው ስለነበር በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሰጠው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተከሳሽ ብድር ስናበድር ቤቱ የማይሸጥ የማይለወጥ ፣ የዕዳ መክፈያ መያዣ መሆኑን በቁጥር 30/2834 ሀምሌ 13 ቀን 1987 በፃፈው ደብዳቤ መያዣውን መዝግቦ አረጋግጦልናል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሁለተኛው ተጠሪ በመያዣነት የተያዘ መሆኑን ለአንደኛ ተጠሪ ባለመግለፁ በአንደኛ ተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ኪሳራ ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ አመልካች ኃላፊ የሚሆነው አንደኛ ተጠሪ በመጀመሪያ የሁለተኛ ተከሳሽን ንብረት በማፈላለግ ዕዳውን ለማስከፈል ተገቢውን ትጋት አድርጎ ሳልተከፈለው ገንዘብ እንደሆነና አመልካች የሚከፍለው ካሳ መጠን በመያዣነት ተሰጥቶ የነበረው የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሚያወጣው ዋጋ በላይ መሆን እንደሌለበት በመግለፅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን በሰበር የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት አሰናብቶታል፡፡

አመልካች መጋቢት 7 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ንብረቱ የሁለቱን ባንኮች ዕዳ የሚሸፍን ከሆነ መያዣው ሊመዘገብ የሚችልበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ አመልካች ጥፋት እንደፈፀመ መታየቱ ተገቢነት የለውም፡፡ መያዣው አስር ዓመት ያለፈው ስለሆነ ህጋዊ ውጤት ስለማይኖረው አመልካች መጠየቁ ተገቢ አይደለም፡፡ የመያዣው የገንዘብ መጠን ያለተገለፀ በመሆኑ ውሉ ውጤት የለውም፡፡ ስለዚህ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ አመልካች ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ በማድረግ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ በአንደኛ ተጠሪ ላይ የደረሰውን ኪሳራ የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ነሐሴ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በፅሁፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች እኔን በተጠሪነት መዝግቦ የሰበር አቤቱታ የሚያቀርብበት ምክንያት የለም በማለት ነሐሴ 30 ቀን 2004 ዓ.ም መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መስከረም 10 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ለሚደርሰው ኪሣራ በመያዣያ የተያዘው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚያወጣውን ዋጋ ያህል በኃላፊነት ይጠይቃል በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ ለነበረችው ወ/ሮ ዘውዴ ሽፈራው የሆቴል ህንፃ መስሪያ ብድር ገንዘብ ለመስጠት ተበዳሪዋ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት እንድታቀርብ መጠየቁና ተበዳሪዋም በካርታ ቁጥር 614/935/61 በሆነው ይዞታ ላይ ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ በመጀመሪያ ደረጃ መያዣነት ለመስጠት ለመስማማቷ አመልካች ይህንን ንብረት የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጎ እንዲመዘገብለት አንደኛ ተጠሪን የጠየቀና አመልካችም ንብረቱን አንደኛ

ደረጃ መያዣ አድርጎ በመመዘገብ ለአንደኛ ተጠሪ ያሳወቀው መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ ዕዳውን ለማስከፈል የሚያስችል የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ መብት አለኝ በማለት የብድሩን ገንዘብ ለተበዳሪዋ የለቀቀ(የሰጠ) መሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የማይንቀሳቀሰውን ንብረት የአንደኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጎ የመዘገበው በመሆኑና በፅሁፍ ያረጋገጠው ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም እንደሆነ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

ሆኖም የአመልካች የማይንቀሳቀስ ንብረት ለአንደኛ ተጠሪ ብድር የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ መሆኑን በማረጋገጥ እንደመዘገበው ለአንደኛ ተጠሪ ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም ከመግለፁ በፊት ይህንኑ ተመሣሣይ ንብረት ሁለተኛ ተጠሪ ለወ/ሮ ዘውዱ ሽፈራው ሀምሌ 11 ቀን 1987 በተደረገ የብድር ውል ለሰጠው የብድር ገንዘብ የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጎ የመዘገበ መሆኑን ሀምሌ 11 ቀን 1987 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ለሁለተኛው ተጠሪ እንዳረጋገጠና፣ ይህንን ዕውነታ ለአንደኛው ተጠሪ ያልገለፀ መሆኑን በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ምክንያት ባለዕዳዋ ወ/ሮ ዘውዱ ሽፈራው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በመጀመሪያ ሁለተኛ ተጠሪ ለወሰደችው ብድር መያዣ እንደሆነ ተስማምታና መያዣውም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 በአመልካች ተመዝግቦ በሁለተኛ ተጠሪ ገንዘብ ተበድራ ከወሰደች በኋላ ሰባት ወራት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ይህንኑ በዕዳ ያስያዘቸውንና ያስመዘገበችውን ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጋ ለአንደኛ ተጠሪ በማቅረብ የብድር ገንዘብ የወሰደች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ በመያዣው ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት በመጠቀም ለዕዳው መክፈያ እንዲሆነው ንብረቱን የሸጠው በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የነበረውን የመያዣ መብት ሙሉ በሙሉ ያጣና በዚህም ምክንያት ዕዳውን ለማስከፈል ችግር ላይ የወደቀና ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የማይንቀሳቀሰው ንብረት የተጠሪዎችን ዕዳ እንደሚሸፍንና ጥፋት እንዳልፈፀመ በመግለጽ የሚያቀርበው ክርክር በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ነባራዊ እውነታ መሰረት ያላደረገና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለባለዕዳዋ ላበደረው ብድር መያዣ አድርጎ የያዘ መሆኑን ሀምሌ 11 ቀን 1987 ዓ.ም በፅሁፍ አረጋግጧል፡፡ ይህም ሁለተኛው ተጠሪ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት /የመጀመሪያ ደረጃ የመያዣ መብት/ የሚኖረው ሁለተኛው ተጠሪ መሆኑን የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3081 ድንጋጌዎችን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ንብረቱ የሁለተኛ ተጠሪ መያዣ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች ሀምሌ 11 ቀን 1987 ዓ.ም ከመዘገበ፣ ይኸው ንብረት አንደኛ ተጠሪ በጥር ወር 1988 ዓ.ም ለሰጠው ብድር የመጀመሪያ መያዣ የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ስለዚህ አስቀድሞ በመያዣነት የተያዘውንና የተመዘገበውን የባለዕዳዋን ቤት በመጀመሪያ መያዣነት መዝግቤአለሁ በማለት አመልካች ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም ለአንደኛ ተጠሪ የሰጠው ማረጋገጫ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3081 አስገዳጅ ህግ ድንጋጌዎች የሚቃረንና ህጋዊ ውጤት የሌለው አንደኛ ተጠሪንም ያለመያዣ ያስቀረ ተግባር ነው፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ የሚመዘገበው ንብረቱ በሚገኝበት አገር ርዕተ መዝገብ መሆኑንና ንብረቱ እንዲመዘግብ ጥያቄ የቀረበለት የመንግስት አካል (ሰራተኛ) የመያዣ ውሉን የሚመዘግበው በህግ ስለማንቀሳቀሱ ንብረቶች አመዘጋገብ ሥርዓት የተደነገጉትን ደንቦች መሰረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር

www.abyssinialaw.com

3052 እና የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3053 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በመጀመሪያ ደረጃ መያዣነት ይዣለሁ በሚል እምነት ያለምንም መያዣ ለባለዕዳዋ ገንዘብ ያበደረው አመልካች (የአመልካች) የሚመለከታቸው ሠራተኞች ንብረቱ ቀደም ብሎ በሁለተኛው ተጠሪ የተያዘና መያዣውም በማይንቀሳቀስው ርዕተ መዝገብ የተመዘገበ መሆኑን በጥንቃቄ በመመርመር ስላልገለፁለት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 1640 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት፣ አመልካችን በአንደኛ ተጠሪ ላይ በደረሰው ጉዳት በኋላፊነት የሚያስጠይቅ እንደሆነ ከህጉ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ንብረቱ ቀደም ብሎ በመያዣነት ሁለተኛው ተጠሪ የያዘውና መያዣውንም ያስመዘገበው መሆኑን ባለመግለፁ አንደኛው ተጠሪ በንብረቱ ላይ የአንደኛ ደረጃ መያዣ መብት አለኝ በሚል ዕምነት ለባለዕዳዋ በብድር ገንዘብ በመስጠት ለደረሰበት ኪሣራ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑንና አመልካች በመያዣነት ተመዝግቦ የነበረው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚያወጣውን ዋጋ ያህል ብቻ በኃላፊነት እንደሚጠይቅ ይህም ባለዕዳዋ ለመክፈል ሣትችል ስትቀር መሆኑን በመግለፅ የሰጠው ውሳኔ ከላይ የተዘረዘሩትን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአማራ ክልል የምዕራብ ጉጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 79907

ጥር 2 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ልዩ የገንዘብ እገዛ ተቋም ጠበቃ ሺፈታ በለጠ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. ወ/ሮ የወይንሐረግ ትዕዛዙ ጠበቃ አበበ ጥላዬ ቀረቡ

2. አቶ ፀጋየሁ ጋሹ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ከዋስትና ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ጉዳዩ በተጀመረበት በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኖቹ ተጠሪዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የነበረ ሲሆን 1ኛ ተከሣሽ የነበረው ደግሞ የሰበር ክርክሩ አካል ያልሆነውና በአሁኑ አመልካች /በስር ከሳሽ/ መስሪያ ቤት በሰራተኛነት በተቀጠረበት ጊዜ የአሁኖቹ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ለብር 50,000.00 /ሀምሣ ሺህ ብር/ የዋስትና ግዴታ ገብተውለት ነበር የተባለ ግለሰብ ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው 1ኛ ተከሳሽ ይዞት የተሰወረውን ገብዘብ ብር 109,487.95 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች በዋስትናቸው መጠን ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ለማስወሰን ሲሆን የተጠሪዎቹን የዋስትና ውሎች አያይዞ አቅርቧል፡፡
የዋስትና ውሉን አስመልክቶ 1ኛ ተጠሪ በወቅቱ በዋሰትና ውሉ ላይ ለመፈረም ወደ ከሳሽ ተቋም ሄጄ የከሳሽ ተወካይና ምስክሮች ስላልነበሩና ስላልፈረሙ ውሉ ረቂቅ ሆኖ ቀርቶአል፡፡ ከሳሽ የራሱን ተወካይ እና ምስክሮቹን ያስፈረመው በሌላ ጊዜ ነው በእጄ በሚገኘውና በማስረጃነት ባቀረብኩት የዋስትና ውሉ ቅጂ ላይ የከሳሽ ተወካይና የምስክሮች ፊርማ የለበትም በማለት የተከራከረች ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ የዋስትና ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ ከሳሽ የቀረበው የዋስትና ውል የተሟላ ቢሆንም በ1ኛ ተጠሪ/በስር 2ኛ ተከሳሽ/ በኩል የቀረበው የዋስትና ውል ግን የከሳሽና የምስክሮች ፊርማ የማይታይበት መሆኑን ከሳሽ ያቀረበው የዋስትና ውል በኮምፒተር ጽሑፍ የተዘጋጀ ሆኖ የምስክሮች ስም ግን በእጅ ጽሑፍ የተፃፈ መሆኑን ይህም የዋስትና ውሉ የተደረገው በሁለት ምስክሮች ፊት እንዳልሆነ እና ከሳሽ ምስክሮቹን ያስፈረመው ውሉ ከተደረገ በኂላ እንደሆነ መንዘብ የሚያስችል መሆኑን 2ኛ ተጠሪን /የስር 3ኛ ተከሳሽን/ አስመልክቶ በዋስትና

ውሉ ግርጌ በእጅ ጽሑፍ ተሞልቶ የሚታየው የአንድ ምስክር ስም እና ፊርማ ብቻ እንደሆነ እና የዋስትና ውል በጽሑፍ ሆኖ በሁለት ምስክሮች ካልተረጋገጠ ውጤት እንደማይኖረው በፍ/ሕ/ቁ 1725/ሀ/ እና 1727/2/ ተደንግጐ የሚገኝ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ 1ኛ ተከሳሽ እንዲከፍል 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ግን እንዲሰናበቱ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ግድፈት የለበትም በማለት የአሁኑ አመልካች ያቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ አሰናብቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ሲሆን የዋስትና ውሉ በጽሑፍ ሆኖ በሁለት ምስክሮች ስላልተረጋገጠ የፍ/ሕ/ቁ 1727/2/ መስፈርትን አያሟላም ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የዋስትና ውል በፍ/ሕ/ቁ 1727/2/ መሰረት በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ ውጤት አይኖረውም ሲሉ የአሁኖቹን ተጠሪዎች በማሰናበት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርመረናል፡፡

በዚህም መሰረት 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ አመልካች ለስር ፍ/ቤት በማስረጃነት ያቀረበው የዋስትና ውል የተጠሪዋ የአመልካች ተወካይ እና የሁለት ምስክሮች ፊርማ የሚታይበት መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡ በውሉ ላይ መፈረሚንም 1ኛ ተጠሪ አልካደችም 1ኛ ተጠሪ በወቅቱ ውሉን ለመፈረም ወደ ከሳሽ ተቋም ሄጄ የተቋሙ ተወካይና ምስክሮች ስላልነበሩና ስላልፈረሙ ውሉ ረቂቅ ሆኖ ቀርቶአል ከማለት በስተቀር የሰበር ከሳሽ በማስረጃነት ያቀረበውና በተጠሪዋ ያልተካደው ፊርማ የሚገኝበት የዋስትና ውል የተሟላ ቅጅ በከሳሽ እጅ እንዴት ሊገባ ወይም ሊገኝ እንደቻለ ተጠሪዋ በግልጽ ያቀረበችው ክርክር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ነገሩን በመሸሽ የቀረበ የዚህ ዓይነት ክርክር ደግሞ ውሉ በሁለት ምስክሮች የተረጋገጠው እርሷ በፈረመችበት ጊዜ እንደሆነ ተጠሪዋ አምና እንደተቀበለች የሚያስቆጥር መሆኑን ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 83 እና 235 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የተጠሪዋን ክርክር በዚህ አግባብ ተገንዝበው ውሣኔ መስጠት ሲገባቸው ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት መረጋገጡን እንደካደች አድርገው መውሰዳቸው በክርክሩ ስነስርአታዊ አመራር ረገድ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለቱም ተጠሪዎች በተናጠል የገቡት የዋስትና ውል በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተረጋገጠ ነው ቢባል እንኳን ተጠሪዎቹ በፍ/ሕ/ቁ 1727 የተመለከተውን የፎርማሊቲ መስፈርት ጠቅሰው የሚከራከሩት ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት አልተረጋገጠም በማለት እንጂ አልፈረምንበትም በማለት አይደለም፡፡ በመሰረቱ ሕጉ የውሉን በሁለት ምስክሮች ፊት የመረጋገጥ አስፈላጊነት የደነገገው በውሉ መደረግ ወይም ይዘት ወይም መሰል ሁኔታዎች ላይ በተዋዋዮች መካከል ሊነሳ የሚችለውን አለመግባባት ወይም ክርክር ውሉ ሲደረግ በነበሩ ግለሰቦች እገዛ ጭምር ለመፍታት እንዲያስችልም በማሰብ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎቹ ውሉን ስላለመፈረማቸው ወይም ስለውሉ ቃል ያቀረቡት ማናቸውም ዓይነት ክርክር አለመኖሩን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ስለራሳቸው ፊርማ እና ስለ ውሉ ቃል በተጠሪዎቹ የተካደ ነገር ከሌለ ደግሞ እነዚህ ነጥቦች ቢካዱ ኖሮ በአስረጅነት ሊቀርቡ ይችሉ ነበር የሚባሉት ምስክሮች በውሉ ላይ ሳይፈርሙ መቅረታቸው የተጠሪዎቹን የውል ግዴታ ተፈፃሚነት ሊያስቀር የሚችል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩን በዚህ አግባብ መምራት ሲገባቸው የዋስትና ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ስላልተረጋገጠ አይፀናም ሲሉ ተጠሪዎቹን በማሰናበት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቶአል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. ተጠሪዎቹን አስመልክቶ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 171276 በ25/03/04 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 119159 በ01/08/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል።
2. በስር 1ኛ ተከሣሽ በአቶ ተስፋዬ በላይ ላይ የተወሰነውን ገንዘብ ተጠሪዎቹ በገቡት የዋስትና ግዴታ መጠን ከተከሳሹ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ወስነናል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. የውሣኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ።
5. ክርክር ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቶአል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማ/ጥ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 76825

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ሪታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ተጠሪ ፡- የአዳማ ከተማ የቦኩ ሸነን ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ የሰበር አመልካችም ተከሳሽ ነበር፡፡ ከሳሽ አሻሽሎ በ01/08/2002 ዓ/ም ያቀረበው ክስ የከተማው አስተዳደር ለከሳሽ ቀበሌ ለልማት ሥራ ድጋፍ በሚል 400 ካሬ ሜትር ቦታ በመስጠቱ በተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን ቦታውን በጨረታ ለመሸጥ ጨረታ ተድርጎ ተከሳሽም በጨረታው ተወዳዳሪ በመሆን በብር 370,000.00 ካሸነፈና የቦታውን ካርታ ከተቀበለ በኋላ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ሲጠየቅ የአራት ወር ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ የተሰጠው ቢሆንም ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ወጪና ኪሳራ ተጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ለክሱ በሠጠው መልስ ክስ የቀረበበት መሬት በሊዝ ስምምነት የተሸጠ ሲሆን ሽያጩም ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ የሽያጭ ውሉ በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ በሊዝ ህግና ደንብ መሰረት የተፈረመ የውል ስምምነት የለም፣ገንዘቡን ለመክፈል የ4 ወር ጊዜ ጠይቄ እያለሁ በችኮላ የቀረበ ክስ ነው፣ጨረታው ውድቅ ከሆነ ያስያዝኩት ገንዘብ ቀሪ ከሚሆን በስተቀር ጠቅላላውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ሲሉ ተከራክሯል፡፡

ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስትም ሆነ በክልሉ ህገ መንግስት መሬት የማይሸጥ እና የማይለወጥ የመንግስትና የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም በስጦታ ወይም በኪራይ የባለይዞታነት መብት ማስተላለፍ የሚቻል ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 456/2005፣272/2002 እና በሊዝ ደንብ ቁጥር 1/1987 እንደተሻሻለው ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በሚያከራክረው ጉዳይም ተከሳሽ ጨረታውን ተወዳድሮ በብር 370,000.00 በማሸነፉ መሬቱ ወደ ተከሳሽ በሊዝ

www.abyssinialaw.com

ተላልፎለት ወዲያዉኑ ሳይት ፕላን የተሰጠው ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ገንዘቡን ለከሳሽ የመክፈል ግዴታ አለበት ብሏል፡፡

የስር ተከሳሽም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ በዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት አጽንቷል፡፡

አመልካችም በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- በአመልካች እና በተጠሪው መካከል የተፈረመ የሊዝ ውል ሳይኖር ጨረታው የተደረገበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ ብቻ የጨረታውን ዋጋ እንድከፍል የሥር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 9(1)(2) እና የፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1723ን የሚቃረን ከመሆኑም ሌላ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ//ህገ መንግስት አንቀጽ 79(3) ዳኞች ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም በሚል የተደነገገውን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ የቀበሌው አስተዳደር ወደ አዳማ ከተማ ሲጠቃለል አዲስ በመሆኑ ምክንያት የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ለነዋሪው ህዝብ ለሟሟላት ሲባል በተዘጋጀው ቴሌቶን 400 ካሬ ሜትር ቦታ አመልካች በጨረታ ተወዳድሮ በማሸነፍ በብር 370,000.00 በመግዛቱ ወዲያውኑ ከከተማው ከንቲባ እጅ የቦታውን ሳይት ፕላን መረከቡ የተረጋጠ ሲሆን የይዞታ ማረጋጫ የምስክር ወረቀትም በከተማው የመሬትና የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተዘጋጅቶለት እያለ ፎርማሊቲውን አሟልቶ መሬቱን እንዲረከብ እየተነገረው እያለ መሬቱ በሊዝ አዋጅ መሰረት እንደተላለፈለት በማስመሰል የሊዝ አዋጁ ፎርማሊቲ ስላልተሟላ በጨረታው አልገደድም ያለው ተገቢነት ስለሌለው ገንዘቡን እንዲከፍል የተወሰነበት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ተጠሪው ላቀረበው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች በጨረታው ተወዳዳሪ ሆኖ ጨረታውን ማሸነፉን የሚያምነው ጉዳይ ሲሆን በዋናነት ክርክሩን እያቀረበ ያለው ግን ጉዳዩን ከሊዝ ህግ ጋር በማገናኘት ነው፡፡ በወቅቱ ተፈጻሚ በነበረው የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/1994 የሊዝ ውሉ በተዋዋዮቹ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 9(1) መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የይዞታ ማረጋጫ የምስክር ወረቀትም የሚሰጠው ይሔው የሊዝ ውል ስምምነት ከተደረገ በኋላ ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ የክፍያ አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታም በሊዝ ውሉ ወስጥ መካተት ያለበት ስለመሆኑ ድንጋጌው በንዑስ አንቀጽ 2 ተጠቅሷል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ለተጠሪው ቀበሌ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ለመዘርጋት በተዘጋጀው ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በተደረገው ጨረታ ተሳታፊ በመሆን ጨረታውን አሸንፎ የቦታውን ሳይት ፕላን ያገኘ በመሆኑ ለገንዘቡ አከፋፈል የሊዝ ውል ስምምነት አልተፈረመም የሚለውን ቅድመ

www.abyssinialaw.com

ሁኔታ ሊያቀርብ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በአመልካች እና አግባብ ባለው አካል መካከል የተፈረመ የሊዝ ውል አለመኖሩ ግልጽ ቢሆንም በመካከላቸው የውል ግንኙነት የተመሰረተ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም፡፡

የውል ግዴታ መፈጸም የሚጠበቅበት ተዋዋይ ይህንኑ ግዴታ ባልፈጸመ ጊዜም በራሱ በኩል ያለውን ግዴታ የፈጸመው ተዋዋይ በፍ/ህ/ቁ/1771(1) እንደተደነገገው ሌላኛው ተዋዋይ የበኩሉን ግዴታ እንዲፈጽም የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ውሉ ተዋዋዮቹ በአንድነት የሚፈጽሙትን ግዴታ (simultaneous performance) የሚጥል ሆኖ ከተገኘም ተዋዋዩ የተዋዋለበትን ግዴታ በውሉ እንደተመለከተው እንዲፈጸምለት የሚጠይቀው ወገን ከውሉ ስምምነት የተነሳ እሱም በበኩሉ ያለውን ግዴታ ወዲያውኑ መፈጸም ወይም ለመፈጸም የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባው መሆኑን የፍ/ህ/ቁ/1757 ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ መሰረትም አመልካች የጨረታው አሸናፊ መሆኑ እንደተረጋገጠ በፍ/ህ/ቁ/1688(2) የተደነገገውን በመከተል ተጠሪው ሳይት ፕላኑን ለአመልካች በማስረከብ የበኩሉን ግዴታ በመፈጸም ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ሲያስታውቅ አመልካችም የክፍያው ጊዜ እንዲያራዝምለት በመጠየቁ በጥያቄው መሰረት የተራዘመለት ቢሆንም ለመክፈል አለመፈለጉን የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የሚያጣሩ የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም በአመልካች እና በተጠሪው መካከል በተመሰረተው ውል መሰረት በጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈውን ገንዘብ በመክፈል ቀሪውን መሟላት የሚገባቸውን ነገሮች ተጠሪው ወይም አግባብ ያለው አካል እንዲያሟላ አመልካች መጠየቅ ሲገባው ህጋዊ መሰረት የሌላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ በማድረግ ያሸነፈበትን የጨረታውን ዋጋ ገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ በሚል በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/09324 በቀን 1902/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሠጠውን ውሳኔ፣የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ10981 በቀን 30/03/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በ/ቁ/117557 በቀን 28/05/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 370,000 (ሶስት መቶ ሳባ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/10556 ተጀምሮ የነበረው የአፈጻጸም ክስ ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ በመሆኑም እንዲያውቀው ይጻፍ ብለናል፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 81857

ጥር 13 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱልቃድር ጁሐር - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠበቃ አረጋ ፀጋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲሆን ክሱን የመሰረተው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ግራ ቀኙ በ30/03/89 እና በ04/04/89 ባደረጓቸው የሰሊጥ ሽያጭ ውሎች መሰረት ተከሳሽ ሰሊጡን ተረክበው እያለ ዋጋውን ያልከፈሉ በመሆኑ በገቡት የውል ግዴታ መሰረት ገንዘቡን መክፈል ከነበረባቸውን ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ሲሆን ተከሳሹም የበኩላቸውን የመቃወሚያና የፍሬ ጉዳይ ነጥቦች በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሽ አንዱን ኩንታል በብር 299.65 ሂሳብ በድምሩ 4,143.55 ኩንታል ሰሊጥ ለተከሳሽ ማስረከቡና ተከሳሹም ክፍያውን መፈፀም ይገባቸው የነበረው በ10/05/89 ዓ.ም መሆኑ መረጋገጡን፣ ተከሳሽ ወለዱ በ14% የታሰበው ከፍ.ሕ.ቁ. 2479(3) ውጪ ነው ቢሉም የወለድ ምጣኔው ተከሳሽ በውል ግዴታ የገቡበት ከመሆኑም በላይ ገንዘቡ የብድር ውልን የሚመለከት ባለመሆኑ ምክንያት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የፍ.ሕ.ቁ 2479(3) ሳይሆን 1803(2) መሆኑን እና ተከሳሽ ያቀረቧቸው የመቃወሚያና ሌሎች የፍሬ ነገር የክርክር ነጥቦች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በዝርዝር በመግለፅ ተከሳሽ ብር 1,241,641.75 ከ10/05/89 ዓ/ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት 24/05/99 ዓ.ም ድረስ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር እንዲሁም በዋናው ገንዘብ ላይ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ የሚታሰብ 9% ወለድ ከወጪና ኪሳራ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ይግባኝ ሰርዞ አሰናብቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረቡት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን በዋናው የገንዘብ ዕዳ ላይ የ14% ወለድ እንዲታሰብ የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ሕ/ቁጥር 2479(3) ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር አቤቱታው በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባዋል በመባሉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከላይ ከተጠቀሰው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የፍ/ሕ/ቁ 2479 የሚናገረው በብድር በሚሰጥ ገንዘብ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ሊያቋቋሙ ስለሚችሉት የወለድ ምጣኔ ጣሪያ እና ብድሩ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ከሆነ በብድር ገንዘብ ላይ ሊታሰብ ስለሚገባው የወለድ ምጣኔ ጣሪያ ሲሆን የፍ/ሕ/ቁ 1803(2) ድንጋጌ ደግሞ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሳይከፈል በቀረ የገንዘብ ዕዳ ላይ የሚታሰበው የወለድ ምጣኔ ተዋዋዮቹ የተስማሙበት መጠን እንደሆነ የሚደነግግ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ሁለቱ ድንጋጌዎች ሁለት የተለያዩ የውል ግንኙነትና አፈፃፀም ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑን ነው፡፡ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሳይከፈል የቀረን የገንዘብ ዕዳ የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁ 1803 ድንጋጌ በፍ/ሕ/ቁ 2479 መሰረት ተቋቁሞ ነገር ግን በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያልተከፈለ የብድር ገንዘብን ጭምር የሚመለከት መሆኑን ከፍ/ሕ/ቁ 2488 እና 2489 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ተከሳሽ ኃላፊ የተደረጉበት ገንዘብ ከብድር ውል የመነጨ ካለመሆኑም በላይ የውል ግዴታ ገብተውለት የነበረው የገንዘብ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ካለፈ አስር ዓመታት ያህል ማስቆጠሩ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ለክርክሩ አወሳሰን አግባብነት የሚኖረው አመልካች እንደሚከራከሩት የፍ/ሕ/ቁ 2479(3) ሳይሆን የስር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የቁጥር 1803 (2) ድንጋጌ ነው፡፡

በሌላ በኩል የውል ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም ያዘገየ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ የሚከፍለው የኪሳራ መጠን የግዴታው አለመፈፀም ወይም መዘግየት ካስከተለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንደሚገባው በፍ/ሕ/ቁ 1790(2) እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙን ውል መሰረት በማድረግ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሰጡበት የ14% የወለድ መጠን በተጠሪ ላይ ከደረሰው የጉዳት መጠን የበለጠ ነው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ ካለመገኘቱም በላይ በተጠሪ የተጠየቀው የወለድ መጠን ከደረሰበት ጉዳት በላይ ስለመሆኑ አመልካች በፍ/ሕ/ቁ 1800 መሰረት ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 11300 በ19/09/03 የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 77002 በ24/08/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ፀንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡
3. ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

## *የሃሳብ ልዩነት*

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ የአብላጨውን ድምፅ የወሰድ መጠኑን በተመለከተ በሰጠው የህግ ትርጉም በደረሰበት መደምደሚያ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ ከሙያ ባልደረቦች የተለየሁባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ተጠሪና አመልካች ህዳር 30 ቀን 1989 እና ታህሳስ 4 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት የሰሊጥ ሽያጭ ውል መሰረት፣ አመልካች ከተጠሪ የተረከቡት ሰሊጥ ዋጋ እንዲሆን፣ አመልካች ቼክ ቆርጦ የሰጠ ሲሆን፣ አመልካች በቂ ስንቅ የሌለው በመሆኑ ምክንያት አመልካችና ተጠሪ ውላቸውን በማሻሻል የአንድ ኩንታል ሰሊጥ ዋጋ በብር 299.65 (ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከስልሣ አምስት ሳንቲም ሒሳብ) እስከ ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም በጠቅላላው ብር 1,448,250 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ለመክፈል፣ ከጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በኂላ ክፍያ ከዘገየ ወለድ 14% (አስራ አራት በመቶ) ለመክፈል የተስማማ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች የሰሊጡን ዋጋ በውሉ በተገለፀው ጊዜ (ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም) ያልከፈለ በመሆኑ በውላችን መሰረት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር ታስቦ እንድከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ክስ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመቀበል፣ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ አብላጫው ድምፅም አመልካች በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ የሰሊጡን ዋጋ ያልከፈለ በመሆኑ፣ 14% ወለድ በውሉ መሰረት እንዲከፍል መወሰኑ የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1803 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌን መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል የህግ ትርጉምና ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
2. እኔም በሀሳብ የተለየሁት፣ በዚህ የህግ ትርጉም ባለመስማማት ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2311(1) በሚደነግገው መሰረት ዋጋውን ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም. ለመክፈል፣ በመስማማት በዱቤ ሰሊጥ የገዛ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ አመልካች የገዛውን የሰሊጥ ዋጋ በውሉ በተገለፀው ጊዜ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2310(3) ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሰሊጡን ዋጋ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ካልከፈሉ በተጠሪ ላይ ኪሳራ የሚደርስበት ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈፀሙ ለተጠሪ የሚከፍለው የኪሳራ መጠን "አስራ አራት ፐርሰንት" ወለድ እንደሆነ በመግለጽ ያደረጉት ስምምነት ህጋዊ ተፈፃሚነትና ውጤት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ይህንን ነጥብ አስመልክቶ የገንዘብ ዕዳ የሚከፈልበትን ጊዜ በማሳለፍ ስለሚከፈል ወለድ፣ የሚደነግገውና ጠቅላላ የውል ድንጋጌ የሆነው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1803 ንዑስ አንቀጽ (2) በውለታ ውስጥ የበለጠ ወለድ የታሰበ እንደሆነ በዚሁ በከፍተኛው ወለድ መታሰቡ ይቀጥላል" በሚል መንገድ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የዚህ ድንጋጌ ትርጉም በዱቤ የሸጠ ሰው፣ ገዥው የዕቃውን ዋጋ ለመክፈል በተስማማበት ጊዜ ካልከፈለ፣ በውሉ ከፍተኛ መጠን ያለው ወለድ እንዲከፍል በውሉ ከተገለፀ፣ ከፍተኛ የሆነ የወለድ መጠን እንዲሰበስብ የአገራችን የህግ ሥርዓት እንደሚፈቅድ ተደርጎ ሊተረጎም አይገባውም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1803 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ፣ ተዋዋዮች የመሰላቸውን ጉዳይ በውል የመወሰን ነፃነት ሕግ የከለከላቸውና የወሰናቸው ነገሮችን እንደማይጨምር በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1711 ከተደነገገው መሰረታዊ መርህና

“ገዥው ዋጋውን ሳይከፍል በሚዘገይበት ጊዜ በሕግ በተወሰነው ወለድ መሰረት የመዘግየት ወለድ መክፈል አለበት” በማለት ከሚደነግገው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2361 ንኡስ አንቀጽ (2) ልዩ ድንጋጌና ተዋዋዮቹ በወለድ የሚከፈለውን ገንዘብ በዓመት በመቶ አስራ ሁለት በላይ እንደሆነ ለማዋዋል አይችሉም ከሚለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2479 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አንፃር መታየትና መተርጎም ይገባዋል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

ስለሆነም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1803 ንኡስ አንቀጽ 2 በገንዘብ ዕዳ ምክንያት ከአስራ ሁለት በመቶ በላይ ወለድ እንዲከፍል የተደረገ ሥምምነት ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው በማሰብ ህግ አውጭው የደነገገው ድንጋጌ አይደለም፡፡ ለማናቸውም የገንዘብ ዕዳ በተለይም በዱቤ ለተፈፀመ ሽያጭ የሚከፈለው ገንዘብ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈለው ወለድ በህጉ የተወሰነው የወለድ መጠን መሆን እንዳለበት ስለ ልዩ ውሎች በተለይም ስለሽያጭ ውል የተደነገገው የፍ/ብ/ህግ/ቁጥር 2361 ንኡስ አንቀጽ 2 የሚደነግግ በመሆኑ አመልካች የሰሊጡን ዋጋ ጥር 10 ቀን 1989 ካልከፈለ ወለድ አስራ አራት ፐርሰንት ለመክፈል የተስማማው ስምምነት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2479 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ወደ ዘጠኝ በመቶ ዝቅ ተደርጎ ሊከፈል ይገባል በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

ሰ/መ/ቁ 80722

ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት ነገረ ፈጅ መላኩ መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዲ አም ሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ውልን አስመልክቶ የሚነሳን ክርክር በግልግል ዳኝነት እንዲያይ በውሉ ላይ የተሰየመው አካል በከሰመ ጊዜ ክርክሩ በማን ሊታይ ይገባል? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው የሽምግልና ዳኝነት አካል ይቋቋምልኝ ሲሆን የክሱም ፍሬ ቃል ከአመልካች ጋር መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረግነው ውል ህንፃ ለመስራት ተስማምተናል፡፡ በውሉ መሠረት አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳያችን በግልግል ዳኝነት ዕልባት እንዲያገኝ ተሰማምተናል፡፡ በዚህ መሠረት በመካከላችን የተፈጠረው አለመግባባት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት የግልግል ዳኝነት ተቋም እንዲታይ አቅርቤ እርሱም ቀርቦ ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ማየት የሚችለው የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ባቋቋመው የዳኝነት ተቋም ሊሆነ ይገባል በማለት ለግልግሉ ፈቀደኛ ሳይሆን ስለቀረ ጉዳያችንን አይቶ ለሚወስንልን የግልግል ተቋም እንዲመራልን በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጥልን የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ለዚሁ የክስ አቤቱታ በሰጠው መልስ ግራ ቀኛችን ባደረግነው ውል አንቀጽ 67 ላይ በመካከላችን የሚፈጠርን አለመግባባት በግልግል የሚዳኘው የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም እርሱ የሚወከለው አካል እንደሆነ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ተመልክቷል፡፡ በአሁን ጊዜ ይህ የግልግል ተቋም የግልግል ተግባሩን መሥራት በማቆሙ፤ ሚኒስቴሩ የወከለው ሌላ አካል ባለመኖሩ ጉዳዩ ወደ ግልግል ተቋም ሊሄድ አልቻለም፡፡ ስለዚህ ይህ የግልግል የዳኝነት አካል በሌለበት ወይም ሁለታችንም ያለልዩነት የመረጥነው ሌላ የዳኝነት አካል በሌለበት ሁኔታ በሌላ የግልግል ዳኝነት ተቋም እንዲታይ አስገዳጅ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ከሳሽ ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተውም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 03283 ሚያዚያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት፡- በውሉ አንቀጽ 67 እንደተጠቀሰው አለመግባባት በሚከሰትበት ጊዜ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም በተፈቀደለት ወኪሉ እንዲፈቱ ተስማምተዋል፡፡ ጉዳዩን እንዲያይላቸው የመረጡት አካል በአሁኑ

ጊዜ እንደሌለ ተከሳሽ ገልጿል፡፡ ከሳሽም ይህንኑ አልተቃወመም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3336(1) ላይ አንድ የዘመድ ዳኛ ሆኖ የተመረጠ ወገን የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ በእርሱ ምትክ ሌላ ዳኛ የሚመረጥ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ጉዳይ በግራ ቀኙ የተሰየመው የግልግል ዳኛ ችሎታ ያጣ ወይም በአሁኑ ጊዜ የግልግል ሥራውን የማይሠራ በመሆኑ ጉዳዩ በሌላ የግልግል ዳኛ ሊታይ የሚገባ መሆኑን ፍ/ቤቱ አረጋግጧል፡፡

ከሳሽ ይህንኑ ተገንዝቦ ጉዳዩ በሌላ የዳኝነት አካል ቀርቦ እንዲታይ የሞከረ ቢሆንም ተከሳሽ በዚህ ከሳሽ በመረጠው አካል ለመዳኘት አልተስማማም፡፡ ስለሆነም በሁለቱም ወገኖች የተነሳውን አለመግባባት ሁለቱም በመረጡት ሌላ ተቋም እንዲታይ መስማማት ካልቻሉ ፍ/ቤቱ በሚመድበው አካል ሊታይ ስለሚገባ ክርክራቸው በጋራ በስምምነት በመረጡት የግልግል ዳኛ/ ተቋም/ ይታይ፡፡ በስምምነት የመረጡት አካል ከሌለ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዋና ሬጅስትራር በኩል ወደ ግልግል ዳኛ/ ተቋም/ ይመራ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ የአሁን አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 እንደተደነገገው ተቀባይነትን ባለማግኘቱ በዚህ አኳኋን በሥር ባሉት ፍ/ቤቶች በየደረጃው የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እና በሰበር አቤቱታው በዝርዝር በማመልከት ጉዳዩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ የአሁን አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ይህ የሰበር ጉዳይ ቀርቧል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ የሰበር ጉዳይ የበኩሉን ክርክር እንዲያቀርብ ጥሪ ቢደረግለትም ሊቀርብ ባለመቻሉ ክርክሩን በፅሁፍ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው የግራ ቀኙን አለመግባባት ተቀብሎ በግልግል ዳኝነት ለማየት የሚችል የግልግል ተቋም ፍ/ቤት በሚሰጠው ትዕዛዝ አማካኝነት ለመሰየም ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3328 ንዑስ ቁጥር (2) እንደተመለከተው አመልካችና ተጠሪ መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉትን የግንባታ ውል አስመልክቶ ወደ ፊት ክርክር በደረሰ ጊዜ ከዚሁ ውል ሊነሳ የሚችለውን ክርክር በግልግል ዳኛ ወይም ለግልግል ተቋም ለማቅረብና ዳኝነት ለማግኘት የሚችሉ ስለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 67 ጠቅሰው የተስማሙ ለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህም በቀር ይህንኑ ከውሉ ሊመነጭ የሚችለውንም የግልግል ዳኛ/ተቋም/ ማንነት ሁሉ በስም ጠቅሰው የተስማሙ ለመሆኑም አላከራከረም፡፡

ከዚሁ መሰከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ከተደረገው ውል የመነጨውን ክርክሩን የአሁን ተጠሪ በዳኝነት አካል አቅርቦ ለማስወሰን በፈለገበት ጊዜ ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት ተመልክቶ ዳኝነት እንዲሰጥበት በስም የተሰየመው የግልግል ተቋም የግልግል ዳኝነት ተግባሩን ማከናወን እንዳቆመም የተረጋገጠ የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡

ከላይ በፍሬ ነገር ረገድ ከተረጋገጡት ሶስት ጉዳዮች በመነሳት ግራ ቀኙን ያከራከረውን ጉዳይ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት የሚቻለው የትኛው የዳኝነት አካል እንደሆነ ለይቶ ለመወሰን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3337 የተመለከተው እንጂ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3336 እንዳልሆነ የሁለቱ ድንጋጌዎች ጥምር ንባብ አሰረጂ ነው፡፡ ይኸውም የአሁን አመልካችና ተጠሪ ከላይ

ከተመለከተው ውል የመነጨ ክርክር ቢያጋጥማቸው ይህንኑ ክርክራቸውን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስና በግልግል ዳኝነት ጉዳዩን የሚያየውን አካል ሳይቀር በስም ሰይመው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3328(2) እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3331 መሠረት በስምምነት ለይተው ያመለከቱ ወይም የመረጡ በመሆኑ በዚህ አኳኋን የተመረጠው የግልግል ዳኛ/ተቋም የግልግል ተግባሩን ማከናወን ማቆሙ ከተረጋገጠ ይህንኑ የግልግል ዳኛ/ተቋም/ ተክቶ የግልግል ዳኝነት ተግባሩን ሊያከናውን የሚችል ሌላ አካል ለመሰየም የሁለቱ የጋራ ስምምነት የግድ አስፈላጊ መሆኑን፣ ይህ ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ ያደረጉት ስምምነት ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3337 በግልፅ በመደንገጉ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ይኸው ድንጋጌ በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3336(1) "....እንደሆነ የዘመድ ዳኛው ስምምነቱ ቀሪ ይሆናል፡፡" ማለት ጉዳዩን እንደታሰበው በግልግል ለመጨረስ አድርገውት በነበረው ስምምነት ሊገደዱ እንደማይችሉ እንጂ በውሉ ላይ በተሰየመው የግልግል ዳኛ ባይሆንም በፍ/ቤት አማካኝነት በማሰየም ሌላ የግልግል ዳኝነት ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ ያደረጉት ስምምነት የፀና ነው የሚል ትርጉም ሊያሰጥ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3325 እና 3344 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን ግራ ቀኝ ወገኖች ካደረጉት የዋናው ጉዳይ ስምምነት ይዘት አንፃር ሲታይ ጉዳይቸውን በግልግል ዳኝነት አይቶ የሚወሰነው በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም እርሱ በሚወክለው አካል በማለት አስቀድመው በያዙት ውል ላይ በግልፅ ያመለከቱት ጉዳዩን በግልግል አይቶ ለመወሰን በጉዳዩ ላይ በቂ ዐቅምና ዕውቀት ያለውን ነው የሚል ሀሳብ ይዘው እንደሆነ ከተዋዋሉበት የውሉታ ጉዳይ መገንዘብ ስለሚቻልና እንደዚያ ያለ አከራካሪ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜም የዘመድ ዳኛ ሥልጣንን አስመልክቶ በውል ላይ የተመለከቱት የስምምነት ቃሎች በጠባቡ መተርጐም እንዳለባቸውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3329 ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ግራ ቀኙ መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ካደረጉት የግንባታ ውል የመነጨውን ክርክር አይቶ ሊወስንላቸው የሚችለውን የግልግል ዳኛ/ተቋም/ በግልፅ በስም ጠርተው የሰየሙ በመሆኑ ክርክሩ በተነሳበት ጊዜም ይህ የግልግል ዳኛ የግልግል ዳኝነት ተግባሩን ማከናወኑን በማቆሙ ምክንያት ሁለቱም ወገኖች እንደነበራቸው ሀሳብ አሁንም ጉዳያቸውን በግልግል ተመልክቶ ሊያይላቸው የሚችለውን ወገን ሁለቱም ወገኖች በጋራ ስምምነት ከሚሰየሙ በቀር፤ ጉዳዩን ተመልክቶ ሊወስን የሚችልን የግልግል ተቋም ወይም አካል ፍ/ቤት የመወሰን ሥልጣን የለውም፡፡

የአሁን ተጠሪ ከውሉ የመነጨውን ክርክሩን በዳኝነት አካል አቅርቦ የማስወሰንና ፍትህ የማግኘት መብቱ ሊጣበብ ስለማይገባም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3337 የተመለከተው ድንጋጌ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ይህንን ጉዳይ በጋራ ስምምነት በሚሰይሙት አካል አቅርበው የማስወሰን መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በጉዳዩ ከተካተተው የገንዘብ መጠን እና ከተከራካሪ ወገኖች ማንነት አንፃር በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5፣ 11(1) እንደተደነገገው ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊሆን ይገባል በማለት መተርጐም ሲገባ ያለ የጋራ ስምምነት የሽምግልና ዳኛ ሊያቋቁም የሚያስችል ትዕዛዝ በሥር ፍ/ቤቶች መሰጠቱ ከላይ በፍርድ ሐተታው እንደተገለፀው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 03283 በቀን 22/8/2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድም ሆነ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁጥር 118971 ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ ከዚህ ቀደም መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት መሠረት በመካከላቸው ከዚህ ውል የተነሳውን አለመግባባት በጋራ ስምምነት ሊያይላቸው የሚችለውን የግልግል አካል በእራሳቸው ከሚያቋቁሙ በቀር በፍ/ቤት የግልግል አካል ሊቋቋም አይቻልም ብለናል፡፡
3. ይህ የጋራ ስምምነት ካልተገኘ የአሁን ተጠሪ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ጉዳዩን አቅርቦ የማስወሰን እና ፍትህ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ የሰበር ችሎት ክርክር ምክንያት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/ 71972

ጥር 1 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ካሣሁን አያሌው - ጠበቃ አቶ ፈንታ አያል ቀረቡ

ተጠሪ፡- የምስራቅ ጎጃም ጎዛምን ወረዳ ጤና ጽ/ቤት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለግንባታ ሥራ የሚከፈል ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በጎዛምን ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ተከሳሽ (ተጠሪ) የተመላላሽ ህክምና መስጫ አንድ ብሎክ ህንፃ ለማሰራት የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቶ እኔ ተወዳድሬ አሸንፌአለሁ፡፡ ከተከሳሽ ጋር ሚያዝያ 2 ቀን 1999 ዓ.ም የግንባታ ስራ ውል ተዋውለን ግንባታው የሚከናወንበትን ቦታ አስረክቦኛል፡፡ ግንባታውን ሰርቼ የመጀመሪያ ክፍያ ጠይቄ፣ ከጠየቅሁት በመቀነስ ክፍያ እንዲፈጽም ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ደብዳቤ ፅፏል፡፡ እኔም ክፍያው የተሰራውን ሥራ የማይሸፍን መሆኑን በመግለጽ የግንባታውን ሥራ በመቀጠል ሁለተኛ ክፍያ በተቆጣጣሪ መሀንዲሱ ከፀደቀ በኂላ ተከሳሽ እንዲከፍለኝ ጥያቄ አቅርቤያለሁ፡፡ ተከሳሹ የክፍያ ሰርተፊኬቱ ለዞን ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ያላከውና በውጤቱ ያልተስማማ መሆኑን በመግለፅ የግንባታ ሥራው ለጊዜው እንዲቋረጥ ሚያዝያ 3 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አሳውቆኛል፡፡ ከዚህ በኂላ የጀመርከውን የግንባታ ሥራ በውሉ መሰረት አጠናቅቀህ እንድታስረክብ በማለት ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ/ም ደብዳቤ የፃፈልኝ ሲሆን እኔ ያቀረብኩትን የክፍያ ጥያቄ መልስ አልሰጠኝም፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ለሰራሁት ሥራ መክፈል የሚገባውን ሁለተኛ ክፍያ ብር 88,913.39 (ሰማኒያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሦስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) እዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው አርባ ዘጠኝ ፐርሰንት ጭማሪ ያለው ነው፡፡ በግንባታ ሥራ ደንብና መመሪያ መሰረት ተጨማሪ ሥራና የሚከፈል ክፍያ ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ የዞኑ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ስለ ክፍያው የሰጠው አስተያየት በጉዳዩ

ተፈፃሚነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፎችና የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሉም ከሳሽ (አመልካች) በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ህንፃውን ሰርቶ አላስረከበም፡፡ የግንባታ ሥራው የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ያለፈ በመሆኑ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ለወረዳው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ አመልካች፣ የተከሳሽ ከሳሽ የዳኝነት ያልከፈለ በመሆኑ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን ሥርዓቱን አሟልቶ አላቀረበም፡፡ ግንባታው በወቅቱ ያልተጠናቀቀው የተከሳሽ ከሳሽ የግንባታ ሥራው ለጊዜው እንዲቋረጥ በፅሁፍ በማዘዙና በተከሳሽ ከሳሽ ጥፋት በመሆኑ ተጠያቂነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት፡-

1ኛ የከሳሽ የክፍያ ጥያቄ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?

2ኛ/ ከሳሽ የጠየቀው ከግንባታ ሥራ ውሉ ውጭ ነው ወይስ አይደለም?

3ኛ/ የግንባታ ሥራው የተቋረጠው በተከሳሽ ጥያቄ ነው ወይስ አይደለም?

4ኛ/ ከሳሽ በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ግዴታውን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ከሳሽ በተሰጠው ዲዛይን መሰረት መስራት የሚገባውን ሥራ የሠራ ስለመሆኑ በተከሳሽ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ በማረጋገጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት አጽድቋል፡፡ የዋጋው ልዩነት የተፈጠረው በመጀመሪያ በዲዛይኑ መሰረት ሥራውን ለመስራት የሚያስፈልገው የግንባታ ቁሳቁስና ሥራ መጠን (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ) ተቆጣጣሪ መሀንዲስ ሲያወጣ ዝቅተኛ ግምት በማውጣቱ መሆኑ የዞኑ ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ባደረገው ሙያዊ ምርመራ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ከሳሽ የግንባታ ውሉን በተሰጠው ዲዛይን መሰረት ሥራውን የሰራ በመሆኑ ተከሳሽ ከሳሽ የጠየቀውን ብር 88,913.39 (ሰማንያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት አንደኛውንና ሁለተኛውን ጭብጥ ወስኗል፡፡ እንደዚሁም የግንባታ ሥራው የተቋረጠው በተከሳሽ ጥያቄ በመሆኑና ከሳሽ በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ኃላፊነቱን የተወጣ በመሆኑ፣ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም በማለት የተከሳሽን የተከሳሽነት ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ተከሳሽ ክፍያውን ለከሳሽ እንዲከፍል፣ ከሳሽ በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ግንባታውን አጠናቅቆ ለተከሳሽ እንዲያስረክብ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ተጠሪ በወረዳ ፍ/ቤት መከራከሪያ አድርጎ አቅርቧቸው የነበሩ ነጥቦችን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው በላይ በመሆኑና የግንባታ ሥራ ውሉ በተዋዋዮች መካከል የህግ ያህል አስገዳጅነት ያለው የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 1731 የሚደነግግ በመሆኑ ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) ለመልስ ሰጭው (አመልካች) የተጠየቀውን ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ሀምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የግንባታ ሥራውን ለመስራት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኜ ያሸነፍኩት ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ሰርቶ ለማስረከብ ነው፡፡ የህንፃው ዲዛይን የግንባታ ሥራ ውሉ ክፍል እንደሆነ በግንባታ ሥራ ውሉ ተገልጿል፡፡ ዲዛይኑ ተሰርቶ የተሰጠኝ በተጠሪ ነው፡፡ የዋጋ ልዩነቱ የተከሰተው የስራውንና ስራውን ለመስራት ያስፈልጋል ተብሎ በተጠሪ በኩል የተገመተውና በውሉ የተገለፀው መጠን (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ) የግንባታ ሥራው በዲዛይኑ መሰረት በሚሰራበት ወቅት የማነስ ወይም የመብለጥ ሁኔታ በመከሰቱ ነው፡፡ ይህም የቁፋሮና ገረጋንቲ ሥራ በውሉ ሰላሳ ሁለት ሜትር ኪውብ እንደሚሆን የተገለፀ ቢሆንም ሥራው ሲከናወን መጨረሻ ላይ ሲለካ አርባ ስምንት ሜትር ኪውብ መሆኑ፣ የቢም የፎርምወርክና የጣውላ ስራ አስራ ሰባት ሜትር ኪውብ እንደሚሆን በውሉ የተገለፀ ቢሆንም በዲዛይኑ መሰረት ተሰርቶ ሲለካ ዘጠና አራት ሜትር ኪውብ መሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲሱና በስራና ከተማ ልማት መመሪያ መረጋገጡና በአንፃሩ 366 ካ.ሜትር እንደሚሆን በውሉ የተገለፀው የላይኛው አፈር ማንሳት ሥራ በዲዛይኑ መሰረት ስራው ሲሰራ ሁለት መቶ ሃምሳ ካሬ ሜትር እንደሆነ፣ በአጠቃላይ በዲዛይኑ መሰረት የግንባታ ሥራውን ለመስራት የሚያስፈልገውን የግንባታ ማቴርያልና የስራ መጠን ከሙያ አንፃር በአግባቡ ባለመሰራቱና ባለመገመቱ የተፈጠረ ልዩነት ነው፡፡ ስለዚህ እንደተጨማሪ ሥራ እንዲታይለት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ ተጨማሪ ስራ ነው የሚባል ቢሆን እንኳን ሥራው የተሰራው በተጠሪ አማካሪና ተቆጣጣሪ መሃንዲስ የስራ ትዕዛዝ መሰረት በመሆኑ ተጠሪ ክፍያ ከመክፈል ነፃ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የዋጋ ልዩነት የተፈጠረው አመልካች ሆነ ብለው ከመሃንዲስ ዋጋ በታች ዋጋ በማቅረብ ጨረታ በማሸነፉ ነው፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ ሥራ ሳይሰራ በጨረታ ካሸነፈበትና በግንባታ ሥራ ውሉ ከተገለፀው በላይ ዋጋ የምንከፍልበት ሁኔታ የለም፡፡ አመልካች በነጠላ ዋጋ በመግለፅ በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት ውል እስከተዋዋለ ድረስ በውሉ መሰረት ግንባታውን ሰርቶ ለማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ የአመልካች ጥያቄ ቅን ልቦናን መሰረት ያደረገ የውል አተረጓጎምና አፈፃፀም መርህን የተከተለ አይደለም፡፡ አመልካች ተጨማሪ ሥራ ሳይሰራ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ የግንባታ አሰራር ደንብንና ሌሎች የህግ ማዕቀፎችን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የክልሉ የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በበኩሉ ታህሳስ 12 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ በግንባታ ስራ ውሉ የተገለፀው የስራ መጠንና በተሰራው የስራ መጠን ላይ በመብለጥ ወይም በማነስ ተጠሪ በሞላው ዋጋ ምክንያት የመጣ አይደለም ልዩነቱ በስታንዳርድ ዲዛይኑ መሰረት ለጨረታ ቀርቦ የነበረው ቢል ኦፍ ኳንቲቲና የስራ መጠን ሥራው በዲዛይኑ መሰረት ከተሰራ በኂላ ከተገኘው ልኬት የመብለጥና (የማነስ) ልዩነት በማሳየቱ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ለተጠሪ ሥራ ክፍያ ለመክፈል ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ለሰራው የግንባታ ሥራ የጠየቀውን ክፍያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

1. ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም. ያደረጉት የግንባታ ውል መሰረታዊ ባህሪና ይዘት እንደዚሁም የውሉ አካል ተደርገው የሚያዙ አባሪዎችን በመመርመርና አመልካች የግንባታ ውሉ ሥራውን ያከናወነው በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ማየት ያስፈልጋል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገው የስራ ውል በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3244 በተሰጠው ትርጓሜ የሚሸፈን አንድ የመንግስት የሆነ ህንፃ ለመስራት ያደረገው የግንባታ ሥራ ውል ነው፡፡ ይህም መሆኑ ተጠሪ በግንባታ ሒደት ውስጥ የስራ ትዕዛዞችን እየሰጠ፣ የስራዎቹን አካሄድ የመወሰንና ስራው በሚፈቅደው አይነት እንዲፈፀም (አመልካችን) የስራ ተቋራጩን የማዘዝ፣ አመልካች በበኩሉ በተጠሪ በተሰጡት ፕላኖች አይነቶችና የዋጋና የስራ ማስታወቂያ መሰረት ጠንቅቆ የግንባታ ሥራውን የመስራት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3252 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ይህም የሚያሳየው የአመልካችና የተጠሪ የግንባታ የሥራ ውል አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የግንባታ ሥራ ውል ሰነድን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን፣ ተጠሪ የግንባታ ሥራው እንዲሰራ ያወጣው ፕላንና የግንባታው ንድፍ (ዲዛይን)፣ በግንባታ ስራው ሂደት፣ ተጠሪ ለአመልካች በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 3152 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3266(1) ድንጋጌዎች መሰረት የሰጣቸው ተጨማሪ የስራ ትዕዛዞች የግንባታ ሥራ ውሉ አካል ተደርገው የሚያዙ ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በመደበው ተቆጣጣሪ መሀንዲስ መሰረት ግንቦት 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገው ውል ከተገለፀው የስራ መጠንና የግንባታ ጥቅል ዋጋ በላይ፣ የግንባታ ሥራውን በግንባታው ንድፍ (ዲዛይን) መሰረት ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ የስራ ትዕዛዞችን እየሰጠ አመልካቹ በመጀመሪያው ውል ከተገለፀው የስራ መጠንና ዋጋ በላይ አርባ ዘጠኝ ፐርሰንት የሚደርስ ተጨማሪ የስራ መጠን ያከናወነ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ በወረዳው ፍ/ቤት ያረጋገጡት እስከ ሰበር ባቀረቡት ክርክር የማይካካዱበት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የግንባታ ሥራውን ሚያዝያ 9 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገው ልዩ የግንባታ ሥራ ውልና፣ የዚሁ ልዩ የግንባታ ሥራ ውል አካል በሆነው የግንባታው ንድፍ (ዲዛይን) እና አሰሪው(ተጠሪው) በግንባታ ሥራ ውሉ ሒደት በፅሁፍ በሰጠው የስራ ትዕዛዝ መሰረት በመሆኑ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የግንባታ ሥራ ውል ልዩ ባህሪና ይዘት ሣያገናዝብ፣ የአመልካችና የተጠሪ የግንባታ ሥራ ውል ግንቦት 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገው የስራ ውል ላይ የተገለፁት ሀያለ ቃሎች ብቻ እንደሆኑ በመግለፅና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1731 ድንጋጌን በመጥቀስ አመልካች የሰራው ተጨማሪ የግንባታ ሥራና የጠየቀው ክፍያ ከግንባታ ሥራ ውሉ ውጭ የቀረበ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔና ትርጉም፣ ከላይ የገለፅናቸውን የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3252 እና የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 3266(1) ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች የተጠሪ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ በፅሁፍ እንዲሰራ በሰጠው የስራ ትዕዛዝ መሰረት ለተሰራው ሥራ ክፍያ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ፣ በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የግንባታ ስራ ውል፣ የሚፈፀመውን የስራ መጠንና ልኬታ መሰረት በማድረግ ክፍያ የሚፈፀምበት የስራ ውል መሆኑን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡

www.abyssinialaw.com

ይህም የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3263 በሚደነግገው መሰረት አመልካች የህንፃውን ዲዛይን መሰረት ለመስራት የሰራው የስራ መጠን ተለክቶና ተረጋግጦ በጨረታ በአሸናፊነት ነጠላ ዋጋ መጠን እየተሰራ ለሰራው ሥራ ክፍያ የሚፈፀምለት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሚያሠራውን ህንፃ በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት የሚያስፈልገው የስራ መጠንን የገመቱት ባለሞያዎች የስራውን መጠን በማብዛት ወይም በመቀነስ፣ ትክክለኛ የሙያ ግምት አለማስቀመጣቸውና፣ አመልካች የግንባታ ሥራውን በዲዛይኑ መሰረት ሲያከናውን አንዳንድ የግንባታ ስራዎች በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው በላይ ከፍተኛ የስራ መጠን ጭማሪ ማሳየታቸው፣ አንዳንድ የግንባታ ስራዎች በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው በታች በዝቅተኛ የስራ መጠን የተከናወኑ መሆናቸው፣ በዚህ ምክንያት አመልካች የጠየቀው የግንባታ ስራ ክፍያ በግንባታ ሥራ ውሉ (ግንቦት 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገው ውል) ከተገለፀው በላይ እስከ አርባ ዘጠኝ ፐርሰንት የሚደርስ ጭማሪ ማሳየቱ በምስራቅ ጎጃም ዞን ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ተጠሪ የሚያሰራውን ህንፃ ዲዛይን፣ ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት ያስፈልጋል ተብሎ ሥራው ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪ መሃንዲስ የወጣው የስራ መጠን ግምት፣ አመልካች የግንባታ ስራውን በዲዛይኑ መሰረት ሲሰራ የሰራው የስራ መጠንና ለዚህ ሥራ መጠን በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ በመመርመርና በማጥናት ሙያዊ ማረጋገጫና ማስረጃ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የመደበው ተቆጣጣሪ መሃንዲስ እስከ አስር ፐርሰንት ድረስ ለሚሰጠው ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ ከመጠባበቂያ በጀት እስከ ሃያ አምስት ፐርሰንት ለሚሰጠው የስራ ትዕዛዝ ውሉ ተሻሽሎ ክፍያ እንደሚከፈልና ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ለተሰጠው የጭማሪ ሥራ ትዕዛዝ ሥራው የተሰራ መሆኑ ተመርምሮና ተጠንቶ ክፍያ እንደሚፈፀም የዞኑ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ለተጠሪ በሰጠው ሙያዊ ማብራሪያ እንደገለፀ፣ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

የዞኑ ከተማ ልማት መምሪያ የሰጠው ሙያዊ ማብራሪያና ማረጋገጫ በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3265 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አመልካች ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ሰርቶ ለማጠናቀቅ በተቆጣጣሪ መሃዲስ ተገምቶ ከነበረው ዋጋ ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ጭማሪ ካሳየ፣ አመልካች ሥራውን በተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ትዕዛዝ መሰረት በአግባቡ ካከናወነ በተጨማሪነት የሰራው ሥራ አሰሪው (ተጠሪ) ክፍያ እንዲከፍለው ጥያቄውን ለዳኞች በማቅረብ ማስወሰን እንደሚቻል የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3265 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም አመልካች በተሰጠው የህንፃ ዲዛይን መሰረት ግንባታውን በሚያከናውንበት ወቅት ተጠሪ በመደበው ተቆጣጣሪ መሃንዲስ የስራ ትዕዛዝ ላከናወነው ግንባታ ክፍያ ጭማሪው ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ቢሆንም፣ የግንባታ ሥራው፣ ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት መከናወን ያለበት አስፈላጊ በመሆኑና፣ አመልካች ሥራውን የሰራ መሆኑ በተጠሪ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ እና በዞኑ ስራ ከተማ ልማት መምሪያ በኩል የተረጋገጠ በመሆኑ፣ አመልካች ለሰራው ሥራ ክፍያ አልፈፅምም በማለት ከኃላፊነት ነፃ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፡፡

በመሆኑም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን የህግ ድንጋጌዎችን በመጥቀስና በመተርጐም አመልካች ሳከናወነው የግንባታ ሥራ ክፍያ አይከፈለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ፣ የፍ/ብሔር ህግ አንቀጽ 3244፣ አንቀጽ 3152(1) አንቀጽ 3265 እና አንቀጽ 3266(1) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. በምስራቅ ጎጃም ዞን የጎዛምን ወረዳ ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 83448

ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1.ወ/ሮ ሙሉወርቅ ኃ/ገብርኤል - የቀረበ የለም

2. በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ዲዛይንና አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ሽመልስ ኃ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ጽጌ መብራቴ - ቀረቡ

በሰ/መ/ቁጥር 84490 የቀረበው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች ሲካሄድ የነበረ መሆኑን ስለተገነዘብን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት አጣምረን በመመርመር ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመንግስት ቤቶችን ላይ የተፈጠረውን ችግር ለመፈታት ታስቦ ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ/ም የወጣውን መመሪያ አፈጻጸም ጋር ተይይዞ የተነሳውን የተከራይነት ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ ተከሳሾች የአሁኑ አመልካቾች ነበሩ፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 143 የሆነን የንግድ ቤት ከአሁኗ 1ኛ አመልካች በወር በብር 2500.00 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ሕዳር 07 ቀን 2003 ዓ.ም. በተደረገው ውል ተከራይተው በመስራት ላይ ባሉበት ሁኔታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ቢሮ በመንግስት ቤቶች ላይ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ሲል መመሪያ ቁጥር 3/2004 ማውጣቱን፣ይህንን መመሪያ መነሻ በማድረግም ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ ከአሁኗ ተጠሪ ጋር የኪራይ ውል አድርጎ በተጠሪ ስም የኪራይ ገንዘብ እየተከፈለ መቆየቱንና በኋላ ግን ውሉን አቋርጦ ለቀድሞ ተከራይ ለሆኑት 1ኛ አመልካች ቤቱ እንዲመለስ በማለት መወሰኑን ገልጸው ከ2ኛ አመልካች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል እንዳይቋረጥ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 2ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም በመመሪያው መሰረት እርምጃ ሲወሰድ የ1ኛ አመልካች ጉዳይ ያላግባብ የተስተናገደ መሆኑን በማጣራትና 1ኛ አመልካችም አዛውንትና የራሳቸው የሆነ ገቢ የሌላቸው መሆኑ ተረጋገጦ እና ይህ ደግሞ በመመሪያው መሰረት ውሉን ለማቋረጥ የማያስችል ምክንያት መሆኑ ታውቆ ከተጠሪ ጋር ያደረገውን ውል ማቋረጡን ገልፆ እርምጃው ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ የአሁኗ 1ኛ አመልካችም ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ክርክር በማቅረብ የተጠሪ ክስ ውድቅ

www.abyssinialaw.com

ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመርና 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆን ያለመሆኑን በማጣራት ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ አመልካች አዛውንትና ገቢ የሌላቸው መሆኑ መረጋገጡንና ይህ ምክንያት ደግሞ አመልካች ከመንግስት የተከራዩትን ንግድ ቤት ለሶስተኛ ወገን አከራይተው ገቢ ቢያገኙበትም ከቀበሌው ጋር ያላቸውን የተከራይነት ግንኙነት ቀሪ የማያደርገው መሆኑ በመመሪያው መመልከቱን በምክንያትነት ይዞ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጎ 1ኛ አመልካች የግል ቤት ያላቸውና በግቢያቸው ካሉት ሱቆችም ለልጅ ልጃቸው ሰጥተው የልጅ ልጃቸው  የንግድ ፈቃድ አውጥቶ የፎቶ ግራፍ ስራ የሚሰሩበት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ ቀበሌው ከተጠሪ ጋር ያደረገው የኪራይ ግንኙነት ሊቀጥል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የ1ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የደመደመው የፍሬ ነገር ጉዳይ ከስልጣኑ ውጪ መሆኑንና በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው የማስረጃ ይዘት ውጪ መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ለአሁኗ አመልካች የኪራይ ግንኙነት እንዲቀጥል ያደረገው በአግባቡ በማጣራት በመመሪያው መሰረት መሆኑና የመዋዋል ነጻነቱን በመጠቀም መሆኑን ጠቅሶ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ሲል መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም 2ኛ አመልካች 1ኛ አመልካች አዛውንትና ገቢ የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ኪራዩን ከ1ኛ አመልካች ጋር ለመቀጠል በመፈለግ ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል ማቋረጡ ያላግባብ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ መረጋገጡንና በመመሪያው መሰረት የኪራይ ውሉ ሊቀጥልላቸው የማይገባ መሆኑን እንዲሁም በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው ተጠሪ መሆናቸውን ዘርዝረው በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል ተብሎ በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም ተብሎ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር መስረተውት የነበረው የኪራይ ውል ተቋርጦ የነበረው በመመሪያ ቁጥር 3/2004 መሰረት ሲሆን አመልካች በመመሪያው መሰረት ጉዳዩ ያለመታየቱን በመግለፅ ለ2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻም ጉዳዩ እንደገና ታይቶ 1ኛ አመልካች አዛውንትና የራሳቸው ገቢ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እርምጃው እርምት ተወስዶ በተሳሳተ ውሳኔ ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረው የተከራይነት

www.abyssinialaw.com

መብት ቀሪ ሁኖ ከ1ኛ አመልካች ጋር የነበረው የኪራይ ውል እንዲቀጥል መደረጉን ነው፡፡የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል ያለው በስር ፍርድ ቤት መጣራት ሲደረግ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የተፃፈውን ደብዳቤ ይዘት በመመልከት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የወረዳው አስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር የካ/ወ1/06-003/6862/04 ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ.ም. ጽፎ የላከው ደብዳቤ ይዘት የአሁኗ አመልካች በግል ቤት ነዋሪ ሁነው የሚኖሩትም ከአራት የልጅ ልጆቻቸው ጋር መሆኑን ፣ በይዞታቸው በፊት በኩል ሱቅ ያለ ሁኖ በዚህ ሱቅ የልጅ ልጃቸው የሆነውን ቢኒያም ተስፋዬ በስሙ በተመዘገበ የንግድ ፈቃድ የፎቶ ቤት አገልግሎት የሚሰራበት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ የደብዳቤው ይዘት 1ኛ አመልካች የራሳቸው የሆነ የግል ይዞታ እንዳላቸውና በዚህ የግል ይዞታቸው ላይም የልጅ ልጃቸው የንግድ ፈቃድ አውጥቶ የሚሰራበት ሁኖ የንግድ ስራው የሚሰራበት ንብረት የ1ኛ አመልካች ስለመሆኑ ያረጋግጣል በሚል ምክንያት የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ አመልካች ገቢ አላቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ 1ኛ አመልካች የግል መኖሪያ ያላቸውና በዚህ ይዞታቸው ስር ሱቅ የሚገኝ መሆኑ ከመረጋገጡ ውጪ ከመመሪያውም በፊትም ሆነ በኋላ በሱቁ ገቢ በትክክል እያገኙበት የነበረ ወይም እያገኙ ያሉበት መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ 1ኛ አመልካች ሱቁን በማከራየት ገቢ ማግኘት ይችሉ የነበረ መሆኑን ግን የደብዳቤው ይዘት የሚያስገነዝብ ቢሆንም ሱቁ ተይዞ የንግድ ስራው የሚከናወነው በልጅ ልጃቸው ከመሆኑም በላይ ስራው መመሪያ ቁጥር 3/2004 ከመውጣቱ በፊት የተጀመረና ሲሰራ የቆየ ከመሆኑ አንፃር ለቤተሰብ የሰጡትን ሱቅ ለግላቸው የኪራይ ገንዘብ በመቀበል ለራሳቸው ገቢ ማድረግ ነበረባቸው ማለት በነባራዊው ሁኔታ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ውጤት ያላገናዘበ ምክንያት መሆኑ እሙን ነው፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 6.1 ስር አዛውንት የሆነ ከሆነና በማከራየት ከሚያገኙት ገቢ ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያለውን የኪራይ ውል እንዳይቋረጥ የሚያደርግ መሆኑ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን ቀድሞ እነዚህ ሁኔታዎች ሳይጣሩ የተሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ በአግባቡ ከተጣራ በኋላ ቀሪ እንዲሆን መደረጉም ከአመልካች ሃላፊነትና ተግባር አንጻር ሲታይ የሚነቀፍ ካለመሆኑም በላይ **በመመሪያው ላይ ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎችን** መሰረት አድርጎ ኪራዩን ከአመልካች ጋር ለመቀጠል በፈለገበት ሁኔታ ደግሞ 2ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር የኪራይ ግንኙነት እንዲቀጥል በፍርድ ኃይል ማስገደድ የመዋዋል ነጻነትን ጽንሰ ሀሳብ የሚጻረርና 2ኛ አመልካች ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን አገልግሎትም በተገቢው መንገድ እንዳይወጣ የማድረግ ውጤት የሚያስከትል ነው፡፡ በመሆኑም 1ኛ አመልካች ከመመሪያው በፊት በይዞታቸው ስር ያለውን ሱቅ ለልጅ ልጃቸው ሰጥተው የልጅ ልጃቸው የንግድ ስራ የሚሰሩበት መሆኑ ገቢ ያገኙ ይችሉ የነበረ መሆኑን ከሚያስገነዝብ በቀር በትክክል አመልካች ገቢ ነበራቸው፣ ይህንኑ ገቢም ለእለት መተዳደሪያቸው በማድረግ የሚኖሩ መሆኑን በማናቸውም መመዘኛ የማያሳይ ሁኖ እያለ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ አመልካች ገቢ ሊያገኙ በሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አሉ በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ የመመሪያውን ዓላማና መንፈስ ከመዋዋል ነጻነትና ከ2ኛ አመልካች ኃላፊነትና ተግባር ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18284 ነሐሴ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06113ሰኔ 26 ቀን 2004 ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18194 ሐምሌ 10 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. 2ኛ አመልካች ከ1ኛ አመልካች ጋር ያደረገውን ውል ሊያቋርጥ አይገባም፣ ከተጠሪ ጋር የኪራይ ውል እንዲያደርግ የሚገደድበት ምክንያት የለም በማለት በድምጽ ብልጫ ወስነናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁጥር 84490 ጋርም ይያያዝ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# የሀሳብ ልዩነት

ከሶስተኛው ተራ ቁጥርና በአራተኛው ተራ ቁጥር ሰማችን የተገለፀው ዳኞች አብላጫው ድምጽ በሰጠው ትርጉምና ውሣኔ የማንስማማ በመሆናችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡ ከስራ ባልደረቦቻችን የተለየንባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጀመሪያው ልዩነታችን የመመሪያ ቁጥር 3/2004 አንቀጽ 6.1 ይዘት መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም የተፈጻሚነት ወሰን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም ትክክል አየደለም የሚል ነው፡፡ መመሪያ ቁጥር 3/2004 የወጣበት መሰረታዊ ዓላማና የንግድ ስራ እንሰራበታለን በሚል ከመነግስት ቤት ተከራይተው እያኖሩበት ወይም የንግድ ስራ እያሰሩ ሣይሆን የተከራዩትን ቤት መልሰው በማከራየት ገንዘብ የሚሰበሰቡ ሰዎችን የኪራይ ውል በማቋረጥ ቤቱን የንግድ ስራ እያሰሩ በሚተዳደሩበት ግለሰቦች በቀጥታ ከመንግስት እንዲከራዩ ማድረግ ነው ይህም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 መሰረት የእኩልነትና እኩል የህግ ጥበቃና ዋስትና መበት ያላቸው ዜጎች አንደኛው የህዝብ ሀብት የሆነ የንግድ ማከናወኛ ቤት ከመንግስት በርካሽ

www.abyssinialaw.com

ዋጋ ተከራይቶ ለሌላው ዜጋ በከፍተኛ ዋጋ እያከራየ ትርፍ የሚያጋብስበትን ሁኔታ በመከላከልና በመቆጣጠር ህንጻውን ከተከራይ አከራይ ተከራይተው የንግድ ስራ የሚሰሩ ዜጎች በቀጥታ ከመንግስት የሚከራዩበትን ሁኔታ የመፍጠር ታስቦ የወጣ መመሪያ ነው፡፡

በዚህ መመሪያ አስገዳጅና ገዥነት ያለው መርህ ከመንግስት ቤት ተከራይቶ ለሌላ ሰው በማከራየት የሚኖር ሰው ከመንግስት ጋር ያለው የኪራይ ውል ተቋርጦ ህንጻውን ከተከራዩ ተከራይቶ ይኖር የነበረው ሰው በቀጥታ ከመንግስት የመከራየት መብቱን ማረጋገጥ ነው፡፡ መልሰ ሰጭም ይህ መመሪያ የወጣበት መሰረታዊ ዓላማና የመመሪያው ድንጋጌዎች መሰረት ከአመልካች ተከራይታ የነግድ ስራ ስትሰራበት የነበረውን ህንጻ የመከራየት መብቷ ተረጋግጦላታል፡፡ የመመሪያ ቁጥር 3/2004 ቁጥር 6.1 ሀይለ ቃል ይዘትን ዓላማው አጠቃላይ መመሪያ ቁጥር 2/2004 ከወጣበት መሰረታዊ ዓላማና የመመሪያው ቁጥር 4 እና ቁጥር 5 ከተገለፀው በልዩ ሁኔታ የተቀመጠ ነው፡፡ የመመሪያ ቁጥር 3/2004 አነቀጽ 6.1 "በራሱ ሳይሰራበት ለሶስተኛ ወገን ቤቱን በማከራየት በሚያገኙት ገቢ ብቻ የሚተዳደሩ የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ሰዎች እና በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎችና አዛውንቶች፣ ቤቱን ለሌላ ሰው አከራይተው በመገኘታቸው የኪራይ ውል የማይቋረጥባቸው መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ የዚህ ልዩ ሀይለ ቃል ዓላማ ከመንግስት ተከራይተው ለሌላ ሰው እያከራዩ ከሚያገኙት ገቢ ውጭ ሌላ መተዳደሪያ የሌላቸው በችግር ውስጥ ያሉ ዜጎች ችግራቸውን ለማቃለል በማሰብ ቤቱን ለሌላ ሰው አከራይተው ቢገኙም መንግስት ከእነሱ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል የሚያቋርጥ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ የመመሪያ ቁጥር 6.1 ሀይለ ቃል ልዩ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው በኢኮኖሚ አቅማቸው በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን መብት ለመጠበቅ ታስቦ የወጣ ነው፡፡ሊተረጎም የሚገባው በጠባቡ ነው፡፡ ይህ የመመሪያው ሀይለ ቃል እንደ አመልካች ያሉ ለመኖሪያ ቤትና ለንግድ ሥራ ድርጅት የሚሆን የግል ቤት ኖሯቸው ኪራይ አከራይተው ገቢ ሊያገኙበት የሚችለውን ሰርቪስ የመኖሪያ ቤት ለልጃቸው በመኖሪያነት ሰጥተውት የንግድ ድርጅት መስሪያ የሚሆነውን የግል ህንፃቸውን የልጅ ልጃቸው የፎቶ ግራፍ ንግድ ስራ እንዲሰራበት ሰጥተው የሚኖሩ ሰዎችን የሚጨምር አይደለም፡፡ የመመሪያ ቁጥር 3/2004 ቁጥር 6.1 ከመንግስት የተከራዩትን ህንፃ ለሌላ ሰው የሚያከራዩ ሰዎች አማራጭ የሌላቸውና በከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና የጤና ችግር ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ገቢ ለማስገኘት የሚችል ሰርቪስ የመኖሪያ ቤትና ለንግድ ስራ የሚሆን ክፍል ያላቸው መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች ከሚኖሩበት መኖሪያ ቤት በተጨማሪ ያሉ ሰርቪስ ቤቶች እና ለንግድ ስራ የሚውል ህንፃ በማከራየት ገቢ እንዳያገኙ የሚያግዳቸው ነገር የለም፡፡ የንብረቱ ባለሀብትነት መብታቸውን በፈለጉት መንገድ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ይኸውን ንብረት ለሌሎች በነፃ እንዲገለገሉበት ለቅቀው ከመንግስት የተከራዩትን ህንፃ እያከራዩ እንዲኖሩ ሊፈቅድላቸው አይገባም፡፡ ከመንግስት በንብረት ላይ አመልካች ያላቸውን መብት ያህል ተጠሪም ተነፃፃሪ የሆነ መብትና ጥያቄ ይኖራታል፡፡

2. ሁለተኛ ተጠሪም ቢሆን መመሪያ ቁጥር 3/2004 ለተጠሪ ያረጋገጠላትን መብት ተፈፃሚ ማድረግ ሲገባው የመመሪያ ቁጥር 3/2004 ቁጥር 6.1 ሀይለ ቃል በመመሪያው ከተካተተበት ዓላማና ከመመሪያው ይዘት ውጭ በመተርጎም የአመልካችን የተከራይነት መብት ለማስቀጠልና ተጠሪ በቀጥታ ከመንግስት የመከራየት መብት ለማረጋገጥ ከተጠሪ ጋር አድርጎት የነበረውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሰጠው ውሳኔ መመሪያውን መሰረት ያላደረገ ነው፡፡ ስለዚህ በመመሪያ መብትና ጥቅም የተረጋገጠላት

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመመሪያ ቁጥር 3/2004 የሚቃረንና መብቷን የሚጋፋ መሆኑ ታይቶ እንዲወሰንላት ክስ አቅርባለች፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ታይቶ ሊወሰንና ሊያልቅ የሚችል ነው፡፡ በፍርድ ሊታዩ የሚችሉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ህገወጥ ናቸው ተብለው እንዲወስንላቸው በውሳኔው መብታቸው የተነካባቸው ሰዎች ሊጠየቁ እንደሚችሉ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመመሪያ ቁጥር 3/2004 ተጠሪ ያገኘችውን መብት በመጋፋት ሁለተኛው ተጠሪ የሰጠውን ውሳኔ የሚያርም ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት የልዩነት ሀሳባችንን አስፍረናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 80642

ታህሣስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት - ጠበቃ

አቶ ማረን ወንደ ቀረበ

ተጠሪ ፡- ባርጉባ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ለተነሳው የይርጋ ክርክር ጉዳይ ተፈፃሚነት ካለው ህግ አንፃር በማየት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የመጓጓዣ ውል መሠረት አመልካች ከጃካርታ ጅቡቲ ወደብ የጫነውን የተጠሪን ንብረት አጓጉዞ እ..አ.ኤ በ02/06/09 ለተጠሪ ማስረከቡንና ተጠሪም እቃውን ከተረከበ ከ5 ወር ከ24 ቀናት በኃላ እ.ኤ.አ በ26/11/09 በተፈረመ የመተማመኛ ሰነድ መክፈል የሚገባውን የመጓጓዣ ዋጋ እ.ኤ.አ. በ10/01/2010 ለመክፈል ግዴታ የገባ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ በክርክር ሂደት የተረጋገጡ የፍሬ ነገር ጉዳዮች ናቸው፡፡

የአሁን አመልካች እቃዎችን ያጓጉዘበት ዋጋ በተጠሪ እንዲከፍለው መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የግራ ቀኛችንን ውል በሚገዛው የባህር ህግ አንቀጽ 146 እና 203 ድንጋጌዎች መሠረተ አንገፁ እቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንደለበት ተደንግጓል፡፡ ከሣሽ የሆነው የአሁን አመልካች ክሱን የመሠረተው ይህ በህጉ የተመለከተው የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኃላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የአሁን አመልካችም በዚህ በተጠሪ አመካኝነት ለቀረበበት የይረጋ ክርክር በቃል ክርክር ጊዜ ባቀረበው ክርክር ተከሣሹ በመካከሉ የዱቤ ክፍያ ሰነድ የፈረመ በመሆኑ የክፍያው ግዴታ በዓይነቱ ተቀይሯል፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ

www.abyssinialaw.com

አግባብነት ያለው የፍ/ብሔር ህጉ እንጂ የባህር ህግ አይደለም፡፡ ስለሆነም የፍ/ብሔር የይርጋ ዘመኑ 10 ዓመት ስለሆነ በይርጋ ሊቋረጥ አይችልም የሚለውን አስመዝግቧል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ በከሣሽ እና በተከሣሽ መካከል የተደረገው የዱቤ አገለግሎት ክፍያና የተደረገው ግራ ቀኙ በመጀመሪያ የባህር ህጉን መሠረት አድርገው የተዋዋሉትን እና በባህር ህግ መሠረት የሚታየውን የመጓጓዣ ውል መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ በመሆኑ ተከሣሽ የአሁን ተጠሪ በዱቤ ውሉ እንደተገለፀው የመጓጓዣ ገንዘቡን እከፍላለሁ ካሉበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ የአንድ ዓመት ጊዜ ያለፈ በመሆኑ በባህር ህጉ አንቀጽ 203 መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ይግባኙን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙ የመጓጓዣ ዋጋውን የክፍያ ሁኔታ በሚመለከት ያደረጉት የዱቤ አገልግሎት ውል ቀደም ሲል ሁለቱም ወገኖች ያደረጉትና በባህር ህጉ መሠረት የሚገዛውን ውል ያሻሻለ እንጂ የተካ ሆኖ ስላልተገኘ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የባህር ህግ እንጂ የአሁን አመልካች እንደሚለው በፍ/ብ/ሕግ የሚሸፈን አይደለም፡፡ ስለሆነም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ መባሉ አግባብ ነው በማለት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ብይን አጽንቶታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ይህንኑ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ደረጃ ካደረጉት የጽሑፍ ክርክር ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በገባው ግዴታ መሠረት እቃውን ጭኖና አጓጉዞ ለአሁን ተጠሪ ለሥር ከሣሽ እ.ኤ.አ. 20/06/09 ካስረከበ በኃላ እ.ኤ.አ. በ26/11/09 ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረግነው የዱቤ አገልገሎት ውል በዓይነቱ እና በግቡ ሁለቱም ወገኖች ቀደም ሲል በባህር ህጉ መሠረት ያደረጉትን ውል የተካ ነው ወይስ ያሻሻለ? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በቅድሚያ ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች አጥብቆ እንዲሚያነሣው ክርክር የባህር ህጉን መሠረት በማድረግ ሁለቱም ወገኖች የደረጉት ውል በኃላ በዱቤ አግልግሎት ውል ተተክቷል፡፡ ስለሆነም ለተነሣው የይርጋ ጊዜ አግባብነት ያለው ይህንኑ የተነሳውን ጉዳይ በሚገዛው በፍ/ብ/ሕግ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ከአንድ ውል የመነጨ ግዴታ በሌላ ውል የተተካ ስለሆነ ቀሪ ነው ለማለት ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1807(ሐ) እንደተደነገገው አመልካች ተጠሪ በመጀመሪያ በባህር ህግ እንዲገዛ አድርገው የተዋዋሉትን ውል በዱቤ አገልግሎት ውል እንዲተካ የመነጨና ማናቸውም መበትና ግዴታ እንዲተካ በማድረግ በባህር ህግ መሠረት ከሚታየው ውሉ የመነጨን ማናቸውም መብትና ግዴታ እንዲተካ በማድረግ በባህር ህጉ የሚገዛውን ውለታ ሙሉ በሙሉ ቀሪ ስለማድረጋቸውም ሆነ ስላለማድረጋቸው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 ጀምሮ በተቀመጡት መለኪያዎች አንፃር ሊታይ ይገባል፡፡

ከእነዚህም መከራከሪያዎች አንዱ ይተካል በተባለው እና ተተክቷል በሚባሉት ውሎች መካከል ያለው የውለታ ጉዳይም ሆነ የውለታው ምክንያት በይዘቱ አዲስ መሆኑ እንዳለበትና ይህንኑ በውለታውም አይነት ሆነ ከውለታው

ምክንያት አንዓር ታይቶ አዲስ የሆነው ውል ከዚህ ቀደም ተደርጎ በነበረው ውል ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በማያጣራጥር አኳኋን ሊያስቀር የሚችል ፈቃድ ከተዋዋይ ወገኖች እንዲኖር አስፈላጊ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 እና 1828 የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1829(ሀ) እንደተመለከተው በመጀመሪያው ውል የተመለከተን እዳ ለማረጋገጥ ሲባል አዲስ ሰነድ የማደራጀት ተግባር የውል መተካት አድራጐት ሊሆን እንደማይችል፤ ይህ ተግበር የውል መተካት አድራጎት እንዲሆን ከተፈለገ በውሉ ላይ በግልጽ መመልከት እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም ሁለቱም ወገኖች የሚንንዣ ዋጋ ክፍያን አስመልክቶ በተከታይ የደረጉት ውል በዓይነቱም ሆነ ለውለታው ምክንያት ከሆነው መመዘኛ አንዓር ሲታይ አዲስ ግዴታ የተካተተበት ባለመሆኑ፤ ይህንኑ የኃላኛው ውል በዓይነቱም ሆነ በውለታው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ከተመለከተው ግዴታ የተለዩ አይደለም እንጂ የመተካት ሃሣብ አላቸው ቢባል ይህንኑ የውል መተካት ጉዳይ በዚህ በኂላኛው የ ውል በግልጽና በማየሻማ አኳኃን የተደረገ ሆኖ ባለመገኘቱ እንዲሁም በዱቤ አገልግሎት ውሉ የተደረገው ከተጠሪ በተነፃፃሪነት የሚፈለግበትን የመንንዣ ዋጋ በውሉ በተመለከተው ጊዜ የነበረበት የመክፈል ግዴታ ለማራዘም ሲባል በእዳ ማረጋገጫ ሰነዱነቱ መደረጉን ይዘቱ አስረጂ ሆኖ በመገኘቱ ሁሉ ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የውሉ መተካት ተግባር የተፈፀመ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይልቁንም የአሁን ተጠሪ በባህር ህጉ መሠረት በሚገዛው ውል ላይ ለመክፈል ግዴታ ገብቶ የነበረበትን የክፍያ ጊዜ እ.አ.አ በ26/11/09 በተደረገ የዱቤ አገልግሎት ክፍያ ሰነድ እ.አ.አ. በ10/01/2010 እከፍላለሁ በማለት የክፍያ ጊዜን የሚያሻሽል ግዴታ የገባ በመሆኑ በባህር ህጉ የተመለከተው የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ በዚህ ከተሻሻለው የክፍያ ጊዜ እ.አ.አ. ከ10/01/2010 ጀምሮ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ስሌት ይርጋው ሊታሰብ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድም ሲታሰብ ክሱ እስከቀረበበት እስከ መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ይህ የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ አልፎታል፡፡ አመልካች ይህ የይርጋ ጊዜ ማለፉን ሣይክድ በመከራከሪያነት የሚቀርበው ከተሻሻለው የዱቤ ክፍያ ጊዜ ጀምሬ ሲታሰብ 10 ዓመት ያልሞላው ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም በማለት በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ብ/ሕገግ ነው ከሚለው የመነሻ ክርክር የመነጨ የክርክር መስመር ነው፡፡

ይህም ከላይ እንደተገለፀው ተቀባይነት ያለው የህግ ክርክር ባለመሆኑ የይርጋ ዘመኑ 1 ዓመት እንጂ 10 ዓመት አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበው ክስ በባህር ህጉ አንቀጽ 203 መሠረት የአንድ ዓመት የይርጋ ዘመን ያለፈው ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በኮ/መ/ቁ. 117281 በሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 80464

ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሴ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወይራ እንጨትና ብረታ ብረት ሥራ ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ

አቶ ወልደሥላሴ ብረቱ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደርና የንግድ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነገር ፈጅ-

አቶ ዮሐንስ ይረስህ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን ክርክር አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ናቸው ወይስ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከውል የመነጨን ክስ በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦ፤ ተጠሪም በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የአሁን ተጠሪ በድምሩ ብር 395,026.55 (ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ሃያ ስድስት ብር ከ55% ሣንቲም) ለአሁን አመልካች ይከፈል በሚል ተወስኖል፡፡

የአሁን ተጠሪ በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩላቸው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ውል አስተዳደራዊ ውል ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) እንደተደነገገው ተከሣሽ የሆነው መስሪያ ቤት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት አንዱ በመሆኑ ይህ የአስፈፃሚ አካል የገባውን አስተዳደራዊ ውል በሚመለከት የሚነሣው ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሌለው ስልጣን የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለውም የአሁን አመልካች በዚህ በፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ሥነ-ሥርዓታዊ ክርክርና መንስኤ የሆነው ውል አስተዳደራዊ ውል በሚለው ሥር የማይሸፈን መሆኑን መሠረት በማድረግ ጠቅሶ ክርክር በማቅረቡ ሲሆን፤ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው መባሉ በህጉ መሠረት መወሰኑን እንጂ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን አያሣይም በማለት የጽሑፍ ክርክሩን

www.abyssinialaw.com

አቅርቧል፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ሥነ-ሥርዓታዊ ክርክሩን በማስቀደም ያቀረበ ሲሆን፣ ይዘቱም የአሁን ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተወሰነ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት እርሱ በሌለበት ጉዳዩ ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት እንደገና እንዲታይለት ከሚያቀርብ በቀር በቀጥታ የይግባኝ ክርክር የማቅረብ መብት የሌለው መሆኑ እየታወቀ በዚህ ከሥነ-ሥርዓቱ ውጭ በሆነ አቀራረብ ውሣኔው መሻሩ የህግ መሠረት የሌለው ስለሆነ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተመሣሣይ የክርክር ነጥብ ከዚህ ቀደም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 36412 በቀረበው ጉዳይ ላይ በ13/2/01 ዓ.ም. ቀን በዋለው ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 ድንጋጌ ይዘት የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንደ ቋሚ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ አለመሆኑ ይልቁንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329 የተመለከተው ሥነ -ሠርዓታዊ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70(ሀ) መሠረት አንድ ጉዳይ ተከሣሹ በሌለበት የተሰጠ ከሆነ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ለመከራከር መብት የሌለው ከመሆኑ በቀር የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ከህግ አንፃር እንዲታይለት ይግባኝ የመጠየቅና በይግባኝ የማሰማት መብት ያለው መሆኑ በተብራራ አኳኋን ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በዚህም ጉዳይ ያሁን ተጠሪ ያደረገውና ያቀረበው ክርክር ቢኖር ተከሣሽ ቀረበም አልቀረበም አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየትና ለመዳኝት ሥልጣን ያለው በየትኛው ደረጃ የተደራጀ፣ (የተቋቋመ) ፍ/ቤት ነው? የሚለውን ነጥብ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 37፣ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 23(1)(ለ)፣ 244(3) አንፃር ተመልክቶ የጉዳዩ ባለቤት መሆኑንና አለመሆኑን ለይቶ መወሰን የዳኝነት ሥራ ተግባር የሚያስገድደው ሆኖ እያለ ይህንኑ በህግ የተመለከተ የዳኝነት ተግባር አልተወጣም፣ ይህ ከህጉ ጋር ተገናዝቦ ይታይ በማለት ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሐ/ቁ. 329 የተመለከተውን ሥነ- ሥርዓታዊ ድንጋጌ አፈፃፀም የጣሰ መሆኑን አያመለክትም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ክርክር ያስነሣው ጉዳይ የአስተዳደር ውል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3132 ላይ በህግ ተለይቶ በተደረገ ጊዜ ነው የሚለውን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ አንድ ውል የአስተዳደር ውል ነው ብሎ ህግ ተነግሯል የሚባለው ደግሞ በንብረት ህግ አንቀጽ 1444(2)፣ 1446 እና 1447(1) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመከተል ነው ሲሉ ያቀረቡት ክርክር እጅግ የጠበበ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132(ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት እና ዓላማ የተከተለ የትርጉም መስመር አይደለም ይልቁም በፍ/ህ/ቁ. 3132 እንደተመለከተው አንድ ውል "የአስተዳደር ውል" ነው በሚለው ማእቀፍ ሥር ይወድቃል ወይስ አይወድቅም ብሎ ለመወሰን መመዘኛ ተደርገው የተያዙት በህግ ወይም በተዋዋዮቹ ግልጽ የሆነ ቃል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ነው የተባለ እነደሆነና፣ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር ተያያዥና ለሥራ ውል አፈፃፀም የአስተዳደር ፍ/ቤቱን ተካፋይነት ያለማቋረጥ የሚጠይቅ መሆኑን ሁሉ የሚጨምር ነው፡፡ ከእነዚህም መስፈርቶች አንፃር አንድ ውል የአስተዳደር ውል ነው ለማለት የግድ በውሉ ላይ በግልጽ መነገር ብቻ ሣይሆን የውሉን ዓይነት የውለታውን ጉዳይ እንዲሁም የተዋዋዮችን ማንነት በማየት መለየት እንደሚገባ በዚሁ ህግ የተደነገገ በመሆኑ በዚሁ መሠረት የሚለይ እንጂ የአሁን አመልካች ከጠቀሷቸው የንብረት ህግ ድንጋጌዎች አንፃር ብቻ ታይቶ ሊወሰን ይገባል የሚለውን ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡

ከዚህም አንፃር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተለይ ከአሁን አመልካች ጋር ውለታ የገባው ማን ነው የሚለውንና የውለታውን ጉዳይ በማየት ውሉ የአስተዳደራዊ ውል ነው፡፡ ይህንኑ አስተዳደራዊ ውልም የገባው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ከሚገኙት አስፈፃሚ አካላት መካከል አንዱ የሆነው ተጠሪ የመሆኑን ፍሬ ጉዳዮች መነሻ አድርጎ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3132(ለ) እና በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በአግባቡ ተመልክቶና ተርጉሞ መሆኑን እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራሉ ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 115093 በቀን 12/04/2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 76951 በቀን 25/08/2004 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ ሁሉ ፀንቷል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 176341 በቀን 10/10/2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
3. በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የክርክር ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች  ናቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 78444

ጥቅምት 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኰንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አቶ አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥጋቡ ተፈራ ጠበቃ አቶ ታዬ ገብረመድህን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማስያዝ የተደረገውን ውል በድጋሚ ማስመዝገብን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ለወሰደው የብድር ገንዘብ መያዣ እንዲሆን የማይንቀሣቀሥ ንብረት የመያዥያ ውል ከአመልካች ጋር በ18-07-1989 ዓ.ም የተዋዋለ መሆኑንና የመያዣ ውሉ በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል መጋቢት 23 ቀን 1989 ዓ.ም እንደተመዘገበ ገልጿል፡፡ ተጠሪ የመያዣ ውሉ ምዝገባ እንዲታደሰ ተጠሪ መስከረም 17 ቀን 2003 ዓ.ም የሚመለከተውን የአስተዳደር አካል ጠይቋል፡፡ የአስተዳደር አካሉም ያለእኔ ፈቃድ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም መያዣውን በድጋሚ በመመዝገብ /ለተከሳሽ/ አመልካች አሳውቋል፡፡ አመልካች የመያዣ ውል ምዝገባ እንዲታደስለት የጠየቀውና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የተደነገገው አስር ዓመት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ የታደሰው የመያዣ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡

አመልካች በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ፣ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠኝ ሥልጣን መሠረት በመያዣው ላይ ያለኝን መብት ለመጠቀም ለተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ/ም እና መስከረም 24 ቀን 1994 ዓ/ም ማስጠንቀቂያ የሰጠሁ በመሆኑ ተጠሪ /ከሳሽ/ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ን በመጥቀስ ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ እንዳልደረሰው በመግለጽ በመከራከሩ፣ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ/ም የተፃፈ ማስጠንቀቂያ በአዋጅ ቁጥር 97/1996 አንቀጽ 3 በሚደነግገው መሠረት ለተጠሪ አድርሷል፡፡ አመልካች መስከረም 24 ቀን 1984 ዓ.ም የተፃፈውን ማስጠንቀቂያ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 መሠረት ለተጠሪ ሣይሆን ለሌላ ሰው እንዳደረሰ ማስረጃው ያሣያል፡፡ ስለዚህ አመልካች በሕግ በተደነገገው መሠረት መስከረም 24 ቀን 1994 ዓ.ም

ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ አልሰጠም፡፡ አመልካች ማስጠንቀቂያ በአግባቡ ካደረሰበት ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የመያዣ ውሉ በጊንቢ አስተዳደር ታድሶ እስከተመዘገበት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲሰላ ከአስራ ሁለት ዓመት በኋላ የመያዣ ውሉ የታደሰ መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለሆነም የመያዥያ ውሉ የታደሰው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የተደነገገው የአሥር ዓመት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ በመሆኑ የመያዣ ውሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1632/1/ መሠረት ሊሰረዝ የሚገባው ነው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የተደነገገው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ለተጠሪ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ፡፡ ይህም አመልካች በሕጉ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት በመብቴ መገልገል መጀመሬን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች በመብቴ መገልገል ከጀመርኩ በኋላ ከመያዣው ላይ ያለኝ መብት ቀሪ የማይሆን ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ይኸ የሰበር ችሎት የሰጠውን የሕግ ትርጉም ሳያገናዝብ በመያዣው ላይ ያለኝ መብት እንዲሰረዝና ቀሪ እንዲሆን የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆኑን በመግለፅ የሚያቀርበው ክርክር እውነትነት የለውም፡፡ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል ቢባል እንኳን፣ መያዣው የታደሰው መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም በመሆኑ ምዝገባው የታደሰው ከአስራ ሁለት ዓመት በኋላ ነው፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠው፣ መያዣውን የሰጠው ሰው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው መሆኑን በማመን የተከራከረ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ መዝገብ ጋር የሚመሳሰል ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ስለዚህ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ በስር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመያዣ ውሉ እድሳት ሊሰረዝና ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የመሠረትነውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮች መለየትና ከሕግ አንፃር የሚያስከትሉትን ውጤት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት ስንመለከተው ተጠሪ ከአመልካች ገንዘብ በብድር ሲወስድ፡ ለብድሩ ዋስትና ይሆን ዘንድ የማይንቀሣቀሥ ንብረቱን መጋቢት 18 ቀን 1989 ዓ.ም በተደረገ የመያዣ ውል አስይዟል፡፡ አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 1989 ዓ.ም የተዋዋሉት የመያዣ ውል መጋቢት 23 ቀን 1989 ዓ.ም በጊንቢ ከተማ አስተዳደር በኩል ተመዝግቧል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ በኋላ አመልካች ለተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም መያዣውን በሰላሣ ቀን ውስጥ ሐራጅ አውጥቶ የሚሸጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 3 መሠረት ማስጠንቀቂያ ለተጠሪ የሰጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ መስከረም 24 ቀን 1994 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ በማለት ያቀረበውን ክርክር ለማስረዳት በሕግ ተቀባይነትና ክብደት ያለው ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አረጋግጠዋል፡፡

አመልካች መጋቢት 23 ቀን 1989 ዓ.ም የተመዘገበው የመያዣ ውል እንዲታደስለት መስከረም 13 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የጊንቢ ከተማ አስተዳደር የጠያቀ መሆኑንና የጊንቢ ከተማ አስተዳደር የመያዣ ውሉን ምዝገባ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም በማደስ የመዘገበ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

2. ከላይ የገለፅናቸውና ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ይዘን አመልካች በመያዣው ላይ የሚኖረውን መብት ለመወሰን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር ድንጋጌዎች ይዘትና መሠረታዊ ባህሪ፣ የአዋጅ ቁጥር 97/90 ድንጋጌዎች ይዘትና በመያዣው ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት በማስመልከት ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የማይንቀሣቀሥ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም የመያዣ ውሉ በሕጉ የተመለከተው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የታደሰና በማይንቀሣቀሥ መዝገብ ውስጥ እንደተመዘገበ የተደረገ እንደሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን እንደሚራዘም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የሚደነግግ ሲሆን፣ የመያዣ ውሉ አዲሱ ምዝገባ ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ ወደፊት እስከ አስር ዓመት ውጤት የሚኖረው መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/3/ ደንግጓል፡፡

ከላይ ይዘታቸው በዝርዝር የተገለጹት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058 ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ በተለየ ሁኔታ፣ በባህሪው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ አለመሆኑን፣ ድንጋጌው የመያዣ ውል ቀሪ የሚሆንበት ወይም በሕግ ውድቅ ስለሚሆንበት /Lapse of mortgage right/ የሚደነግግ እንደሆነ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህም በመሆኑ ንብረቱን በመያዣነት የያዘው ባለገንዘብ በመያዣው ላይ ያለው መብት ቀሪ የሚሆነው፣ መያዣው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ የተደነገገው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመያዣው ላይ ያለውን መብት መገልገል ካልጀመረ እንደሆነ በተጠቀሰው መዝገብ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ይህም በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ በተደነገገው መሠረት ባንኮች በመያዣው ላይ ያለው መብታቸው ቀሪ የሚሆንባቸው በምን ሁኔታ ነው የሚለውን ነጥብ መመልከት የሚጠይቅ ነው፡፡ ባለገንዘቡ በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ ያለው የመያዣ መብት በሕጉ የተደነገገው አስር ዓመት በማለፉ ምክንያት ውድቅ ሆኖበታል /ቀሪ ሁኗል/ ወይም /Lapse/ አድርጓል ተብሎ ሲወሰን የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት በመያዣ መብቱ መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 ባንክ ለሰጠው

www.abyssinialaw.com

ብድር በመያዣ የያዘውን ንብረት፣ ብድሩ ያልተከፈለው መሆኑን የሰላሣ ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለመሸጥና የንብረቱን ባለሀብትነት ለገዥ ለማስተላለፍ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ባንክ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በመብቱ መገልገል ጀምሯል ተብሎ ሊወሰድ እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 በሰጠው ውሣኔ ግልፅ አድርጎታል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ቁጥሩ ከላይ በተገለፀው መዝገብ ባንክ ማስጠንቀቂያ የሰጠው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ የተደነገገው አስር ዓመት ሣያልፍ ከሆነ፣ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኂላ ቤቱን ሳይሸጥ አስር ዓመት ያለፈ ቢሆንም እንኳን፣ የቤቱ ሽያጭ ሣይጠናቀቅ አስር ዓመቱ ማለፉ ብቻውን በመያዣው ላይ ያለውን መብት ቀሪ /Lapse/ እንደማያደርገው ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 90/97 አንቀጽ 3 መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት በመብቱ መገልገል መጀመሩ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች በመብቱ በመገልገል ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ መያዣውን ሳይሸጥ አስራ ሁለት ዓመት ያለፈው ቢሆንም በመያዣው ላይ ያለው መብት ቀሪ እንደማይሆን /Lapse/ እንደማያደርግ ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 44800 ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ የተደነገገውን የአስር ዓመት ጊዜ እንደ ይርጋ ድንጋጌ በመቁጠር አመልካች ማስጠንቀቂያ ከሰጠበት ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ አስር ዓመት ያለፈው ስለሆነ አመልካች በመያዣው ላይ ያለው መብት ይሰረዛል በማለት የሰጡት ውሣኔ ከላይ በተገለፀው መዝገብ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያልተከተለና በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም አመልካች በመያዣ መብቱ መገልገል በመጀመሩ፣ በመያዣው ያለው መብት ቀሪ /Lapse/ የማይሆን በመሆኑና አመልካች መያዣያውን ለማሳደስ ካስመዘገበበት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አስር ዓመት የሚኖረው መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/3/ የተደነገገ በመሆኑ፣ የአመልካች በመያዣው ላይ ያለው መብት እንዲሰረዝ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በመያዣ መብቱ መገልገል በመጀመሩ፣ በመያዣው ላይ ያለው መብት ቀሪ አይሆንም /Lapse/ አያደርግም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የመያዥያ ውሉ በጊንቢ ከተማ አስተዳደር መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም በድጋሚ ማስመዝገቡ ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 69797
ታህሣሥ 04 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሂላላ ሱሌማን - ከጠበቃ ወልደስላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጎንደር ዩኒቨርሲቲ - ነ/ፈ አሸናፊ ልጃለም ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዳቦ አቅርቦት የተደረገውን የአስተዳደር ውል መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም. በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘት ሲታይም በመጋቢት ወር 2000 ዓ.ም. በወጣው የዳቦ ግዥ ውስን ጨረታ ለመሳተፍ የጨረታ ማስከረቢያ በC.P.O ብር 26,035.07 (ሃያ ስድስት ሺህ ሰላሳ አምስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) በወጋገን ባንክ ጎንደር ቅርንጫፍ አስይዘው የዳቦ አቅርቦት ውል ማሸነፋቸውን፣ በውሉም ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ክብደቱ 125 ግራም ለሆነ አንድ ዳቦ በብር 0.80 ሂሳብ ለተጠሪ ሶስት ካምፓሶች ለቁርስ፣ ለምሳና ለእራት ለማቅረብ ስምምነት አድርገው በድምሩ 811,363 (ስምንት መቶ አስራ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ሶስት) ዳቦ ማቅረባቸውን፣ በዚህ ሂደት ላይ እያሉም ተጠሪ ግንቦት 07 ቀን 2000 ዓ.ም. ላይ አዲስ የዳቦ ግዥ ውስን ጨረታ አውጥቶና አመልካች በጨረታው ላይ እንዳይሳተፉ በማድረግ ለሌላ ግለሰብ የዳቦ አቅርቦት ውሉን በመስጠት አዲሱ አቅራቢ ከግንቦት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ አቅርቦቱን መጀመሩን፣ አመልካች እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ብር 122,534.40 (አንድ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) ተጠሪ ከፍሏቸው የ658,195. ዳቦ ዋጋ የሆነውን ብር 526,556.00 (አምስት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር) ተጠሪ ያልከፈላቸውና እንዲከፍላቸው ቢጠይቃቸውም የመልካም ስራ አፈፃጸም ዋስትና መያዝ ከነበረበት መጠን በታች ነው በሚል ምክንያት ሊከፍላቸው ያልቻለ መሆኑን ዘርዝረው ዳቦ አቅርበው ያልተከፈላቸው ብር 526,556.00 እና ሕጋዊ ወለዱን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 26,035.07 ከክርክሩ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው በተፋጠነ ስርዓት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ለክሳቸውም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ለክሱ የመከላከያ ክርክር ለማቅረብ ይፈቅድለት ዘንድ በስርዓቱ መሰረት ጥያቄ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ተቀብሎ ተጠሪ የመካላከያ ክርክርና ማስረጃ እንዲያቀርብ የፈቀደለት ሲሆን ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ከአመልካች ጋር ውሉ መደረጉን ሳይክድ የውሉ ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ሆኖ ተጠሪ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ዳቦውን ሊያቀርቡና የዳቦውን ዋጋ 10% የሆነው ብር 245,036.00 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ከሰላሳ ስድስት ብር) ለመልካም ስራ አፈፃጸም ዋስትና

ማስከበሪያ ሊያስይዙ የውል ግዴታ ገብተው የዳቦ ዱቄት ዋጋ ጨመረ በሚል ምክንያት አቅርቦቱን መቀጠል እንደማይችሉ ታውቆ የሰሩበት ገንዘብ ታስቦ እንዲሰጣቸው ለተጠሪ ፕሬዝዳንት በአድራሻ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. መጻፋቸውን፣ ለአመልካች ሥራ አፈፃጸም ዋስትና አመልካች ሊያስይዙ ይገባ የነበረው ብር 245,036.00 ሆኖ ያላስያዙና ቢያስይዙ ኑሮ በዩኒቨርሲቲው ላይ የደረሰውን ኪሳራ መተኪያ ሊሆን ይችል እንደነበርና ይህ ኪሳራውን ይተካል ባይባልም ውሉ ስለሚሽር የመልካም ስራ አፈፃጸም ተቀንሶ ሌላው የሰሩበት ገንዘብ ቢከፈላቸው ተቃውሞ የሌለው መሆኑ የተነገራቸው መሆኑን ዘርዝሮ ይኼው ተፈፅሞ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈል እንዲወሰንለት ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት አቅርቧል፡፡ በዚህም ክሱ የአሁኗ አመልካች ለአርባ አንድ ቀናት ብቻ የዳቦ አቅርቦት ውሉን ፈፅመው አቅርቦቱ ለአፍታም ያህል ሊቋረጥ እንደማይገባው እየታወቀ በውሉ የገቡትን ቀሪውን 114 ቀናት ዳቦውን ላለማቅረብ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ/ም በጻፉት ደብዳቤ የአሁኗ አመልካች በማረጋገጣቸው ምክንያት ተጠሪ ሁለተኛ ጨረታ አውጥቶ ወ/ሮ ታደለች ጌታሁን የተባሉት ግለሰብ አንዱን ዳቦ በብር 1.31 ለማቅረብ ተጫርተው በማሸነፋቸው አመልካች አቀርባለሁ ካሉት ዋጋ በብር 0.51 ብልጫ እንዲያቀርቡ መደረጉን፣ በዚህም ምክንያት ተጠሪ ላይ ለአንድ መቶ አስራ አራት ቀሪ ቀናት የብር 0.51 ጉዳት በአንድ ዳቦ የደረሰበት ሁኖ በድምሩ ብር 1,148,846.40(አንድ ሚሊዩን አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ስድስት ብር ከአርባ ሳንቲም) ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ዝርዝሮ ይኼው ገንዘብ እንዲከፈለው ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በሰጡት መልስም የውሉ ጊዜ ከ08/08/2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 19/09/2000 ዓ.ም. ድረስ እንጂ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ያለመሆኑንና ከ19/09/2000 ዓ.ም. በኋላ ዳቦ ያላቀረቡበት ምክንያት ዩኒቨርሲቲው በ07/09/2000 ጨረታ አውጥቶና አመልካች በጨረታው ላይ እንዳይሳተፉ በማድረግ ከ20/09/2000 ጀምሮ ለሌላ ሰው ዳቦ አቅርቦት ውሉን በመስጠቱ ሆኖ ኪሳራው የደረሰው ከአመልካች ጋር የነበረውን ውል እንዲቀጥል ተጠሪ ባለማስቻሉ ምክንያት በመሆኑ አመልካች የፈፀሙት ጥፋት ሳይኖር ለኪሳራው ኃላፊ የሚሆኑበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት አመልካች ለአቀረቡት ዳቦ ዋጋውን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያትም በወቅቱ ከተከሰተው የዳቦ ዱቄት ዋጋ መናር ጋር ተዳምሮ አመልካች ግዴታቸውን እንዳይወጡ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረጉን ዘርዝረው የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ጊዜው ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ መሆኑ መረጋገጡን፣ ለውሉ ያለመፈጸም ምክንያት የሆኑት የአሁኗ አመልካች መሆናቸውን፣ ለውሉ ያለመፈፀምም በቂና ሕጋዊ ምክንያት በአመልካች በኩል ያለመቅረቡንና ዩኒቨርሲቲው ከሌላ ሰው ጋር ውል ማድረጉን ያለበትን ኃላፊነትን ለመወጣት የፈፀመው ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ውል ማፍረሱን እንደማያሳይ ገልፆ አመልካችን ለውሉ መፍረስ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት መጠን በተመለከተም ብር 1,068,225.60 መሆኑና ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ አመልካች ዳቦ አቅርበው በተጠሪ ያልተከፈላቸው ገንዘብ ለጨረታው ማስከበሪያና ለመልካም ስራ አፈፃጸም የተያዘባቸው ገንዘብ ሲቀናነስ ብር 797,153.93 (ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከዘጠና ሶስት ሳንቲም) መሆኑን ለይቶ ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ

ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሰኔ 08 ቀን 2003 ዓ.ም. በፃፉት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም የስር ፍርድ ቤት የውሉን ጊዜ በተመለከተ ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ/ም በቁጥር ጥበ/01/568/08/2000 የተጻፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሰው የደብዳቤውን አርዕትና ይዘት ባግባቡ ሳይመለከትና የተዋዋይ ወገኖችን ሐሳብ ሳያገናዘብ መሆኑን፣ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያቱ አመልካች ናቸው መባሉም የውሉን አንቀፅ 5.1 እና 6.2 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና ተጠሪ አመልካች ለአቀረቡት ዳቦ ክፍያውን በወቅቱ ያለመክፈሉን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑን፣በመንግስት ደረጃ እውቅና ያለው የዋጋ ግሽበት ስለመኖሩና የውሉን ሚዛን ስለማናወጡ ተረጋግጦ እያለ ይኼው ግምት ውስጥ ካለመግባቱም በላይ በውሉ አንቀጽ 8.2 እና 8.4 ድንጋጌዎች መሰረት ችግሩን ከተጠሪ ጋር በጋራ ለመፍታት አመልካች ጥያቄ አቅርበው እያለ ፈቃደኛ ያልሆነውና በውሉ ቃል መሰረት አመልካች ልፈፀም እያሉ ውሉ ሳይፈርስ በግንቦት 07 ቀን 2000 ዓ.ም. ጨረታ ያወጣው ተጠሪ መሆኑም ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነውን ወገን በትክክል በመለየት ረገድ ስህተት መፈፀሙን እንደሚያመላክት፣ ውሉ ሲደረግ የዳቦ ዱቄት ዋጋ ለውጥ ይኖረዋል ተብሎ ያልተገመተ ሲሆን ውሉ የአስተዳደር ውል እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ በተደነገጉት ድንጋጌዎች እና በጠቅላላ ውል ደንቦች የሚመራ በመሆኑ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት የሆነውን ተግባር የፈፀመው ተጠሪ በመሆኑ ኪሳራ መክፈል የነበረባቸው አመልካች ሁነው እያለ መታለፉ ያላግባብ መሆኑንና የውሉ ማፍረሻ ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች በውሉ ተገልፀው እያለ በአግባቡ ሳይታዩ መታለፋቸውን፣ አመልካች በሕጉ መሰረት ተጠሪን ሳያስጠነቅቅ የውሉን መሻር መብት ሊሰራበት የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ ያለመኖሩንና የኪሳራው ልክ ሲሰላም በበታች ፍርድ ቤቶች ስህተት መፈፀሙን ገልፀው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን የክርክር ይዘት በአጭሩ ያስቀመጠ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ከመስጠታቸውም በላይ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙን ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በቃል አከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልጉ አበይት ጭብጦች፡-

1. ውሉ ፈርሷል አልፈረሰም? ፈርሷል ከተባለስ ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው ማን ነው? እና
2. የኪሳራው ልክ ስንት መሆን አለበት? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ውሉ አልፈረሰም፣ ፈረሰ ከተባለም ምክንያቱ ተጠሪ ነው በማለት የሚከራከሩት የውሉ ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. እንጂ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ አይደለም፣ በትክክለኛው የውሉ ጊዜ የዳቦ አቅርቦት ግዴታዬን ተወጥቼአለሁ፣ የዳቦ ዱቄት ዋጋ በመጨመሩ ምክንያትም ተጠሪ ጋር ለመነጋገር ተደጋጋሚ ጥረት አድርጌ ተጠሪ ጥያቄዬን በውሉ

አግባብ ሳያስተናግድና በሁለተኛው ጨረታም እንዳልሳተፍ ከልክሎኛል በሚሉት ምክንያቶች ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የውሉ ዘመን ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ሆኖ አመልካች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊያቀርቡ የተዋዋሉትን የዳቦ አቅርቦት የዳቦ ዱቄት ዋጋ ጨምሯል በሚል ምክንያት ከግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ/ም በኋላ ማቅረብ እንደማይፈልጉ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በፃፉት ደብዳቤ በግልፅ ያሳወቁና ውሉንም ያፈረሱት አመልካች በመሆናቸው ለውሉ መፍረስ ምክንያት አመልካች ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍሬ ነገርንና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ግን ውሉ ስለመኖሩ ሳይካድ በውሉ ጊዜ ላይ ግራ ቀኙ መካካዳቸውን ገልፆና ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. በቁጥር ጥበ/01/586/2000 በተጻፈ ደብዳቤ አቅርቦቱ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ለአመልካች ተጠሪ ማሳወቁን፣ ሶስት እማኞች ባሉበት ይኼው ውል መገባቱን አረጋግጧል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተመሳሳይ ድምዳሜ የተያዘበት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የደብዳቤውን ይዘት በተዛባ መንገድ መመዝገባቸውና ከውል አመሰራረት ደንቦች ጋር ያለማገናዘባቸውን መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ክርክር የደብዳቤው ይዘት አመልካች በሚከራከሩት መልኩ ሆኖ ባለመገኘቱ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ይልቁንም ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. የተደረገው ውል አንቀፅ 8.5 ውሉ የጨረታ ሰነዱ አካል ሆኖ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 እና 2005 መሰረት በሕግ ፊት የጸና ስለመሆኑ በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን በጨረታ ሰነዱ ደግሞ የውሉ ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ስለመሆኑ የተጠቀሰ በመሆኑ አመልካች የውሉን ጊዜ እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በ08/08/2000 ዓ.ም. የተፈረመውን የውሉን ይዘት ባግባቡ ያገናዘበ አይደለም፡፡ አመልካች በግልጽ በተደረገው ጨረታ በሚሳተፉበት ጊዜ የውሉን ጊዜ በግልጽ አውቀው የነበረ ስለመሆኑ ከውሉ ይዘት የምንገነዘበው ከመሆኑም በላይ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ለዩኒቨርሲቲው በፃፉት ደብዳቤም ለሰባት ቀናት ብቻ ኣቅርቦቱን መቀጠል እንደሚችሉ፣ ከዚያ በኋላ መቀጠል እንደማይችሉ ያሳወቁ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ ጊዜም ሆነ በውሉ ወቅት ያደረጓቸውን ተግባራት መነሻ በማድረግ ስለውሉ ጊዜ የነበራቸውን ሐሳብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1734 ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ የውሉ ጊዜ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የውሉን ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው በማለት መወሰናቸው ከውሉ ሙሉ ይዘት፣ አመልካች ለተጠሪ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ከፃፉት ደብዳቤና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732፣1734 እና ስለውል አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ለውሉ መፍረስ ምክንያት ማን ነው የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ በመካካለቸው ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ የዳቦ አቅርቦት ውል ማድረጋቸውና አመልካች አቅርቦቱን የቀጠሉት እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በኋላ አቅርቦቱን ያልቀጠሉት የዳቦ ዱቄት ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ይህንኑ ችግር ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተወያይቶ ሊፈታ ባለመቻሉ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ የዳቦ ዱቄት ዋጋ መጨመር ለውሉ መፍረስ በምክንያትነት ሊጠቀስ እንደማይችልና አመልካችም አቅርቦቱን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለማቅረብ አውቀውና ወደው ግዴታ

www.abyssinialaw.com

መግባታቸውን ገልፆ ለውሉ መፍረስ ምክንያት አመልካች ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም አመልካች ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. የጻፉት ደብዳቤ ውሉን መቀጠል እንደማይችሉ በግልጽ ለዩኒቨርሲቲው ያሳወቁበት ስለመሆኑ ያረጋገጡበት ሲሆን አመልካችም ቢሆኑ ይህንኑ ደብዳቤ ይዘቱ ሌላ ስለመሆኑ ሳይጠቅሱ ደብዳቤውን የጻፉበት ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ችግሩን በጋራ ለመፍታት ዝግጁ ሁኖ ባለመገኘቱ ስለመሆኑ ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ በእርግጥ በውሉ አንቀጽ 8 ስር ልዩ ልዩ የጋራ ሁኔታዎችን የሚገዙ ንዑስ ድንጋጌዎች የተካተቱ ሲሆን የውሉ መሻሻል በተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት ሊሆን እንደሚችል በንኡስ ቁጥር 4 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የድንጋጌው ሙሉ ይዘት ሲታይ ይህ ውል ማሻሻያ ይደረግ ጥያቄ ቢቀርብ የሁለቱ ወገኖች ስምምነት ተጠይቆ ፈቃደኛነታቸው ከታወቀ ሊሻሻል ይችላል በሚል የተቀመጠ ሲሆን ድንጋጌው ፈቃደኝነት ባለው መልኩ የተቀመጠ በመሆኑ በተዋዋይ ወገኖች የሚቀርብ የውል ይሻሻል ጥያቄ ሁል ጊዜ ተቀባይነት እንደሚኖረው ወይም ይህ ጥያቄ ቀርቦ ባለበት ሁኔታ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን በውሉ መሰረት እንዲፈፀም ቢፈልግ ይህንኑ ከማድረግ የማይከለክለው ወይም ውሉን ለማፍረስ በቅድመ ሁኔታነት መፈፀም ያለበት ጉዳይ ስለመሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ውሉን ያቋረጠው አመልካች የዳቦ አቅርቦቱን የሚቀጥሉበትን የጊዜ ገደብ በግልጽ አስቀምጠው ደብዳቤ በመጻፋቸው ምክንያት በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው አመልካች ያስቀመጡት የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት ውስን ጨረታ አውጥቶ ሌላ ግለሰብ ዳቦ አቅርቦቱን እንዲቀጥል ማድረጉ ከዩኒቨርሲቲው ኃላፊነትና ግዴታ አንፃር ሲታይ የሚነቀፍበት ምክንያት ካለመኖሩም በላይ በውሉ አንቀፅ 8.2 ስር ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ጉዳዩ በአገሪቱ የፍትሃብሔር ሕግ እንደሚፈታ ስለመሆኑ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የዳቦ ዱቄት ዋጋ መናር የሚለውና በመንግስት የታወቀው የዋጋ ግሽበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሚያቀርቡት ለተማሪዎች ቁርስ፣ ምሳ እና እራት የሚሆን ዳቦ እንደመሆኑ መጠን የአቅርቦቱ ባህርይ ሲታይ ለአፍታ ጊዜ ያህል ሊቋረጥ የማይችል በመሆኑ በመንግስት የታወቀ የዋጋ ግሽበት ቢኖር እንኳ አቅርቦቱን ቀጥለው ኪሳራውን በፍ/ሕ/ቁጥር 3183(2) እና 3188(1) ድንጋጌዎች አግባብ ተጠሪ በከፊል እንዲችል የሚደረግበት ሕጋዊ መፍትሔ የነበረ በመሆኑ የዋጋ ግሽበቱ አመልካች አቅርቦቱን ወዲያውኑና ሙሉ በሙሉ እንዲያቋርጡ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ አመልካች ለአቀረቡት ዳቦ ተጠሪ ዋጋውን በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አልከፈለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክርም በአመልካች የዳቦ አቅርቦት ስራ ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ የሚኖረው መሆኑ ቢታመንም አመልካች ውሉን ለማቋረጥ ለተጠሪ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት ደብዳቤ ይህንኑ ምክንያት በመጥቀስ ውሉን ለማቋረጥ ስለመገደዳቸው ያልፃፉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ውሉን ያፈረሰው ተጠሪ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች በተለያዩ ጊዜያት ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጋር ለመወያየት ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ ስለመሆኑ ጠቅሰው የሚያቀርቡት ክርክር ሲታይም ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. በግልፅ ከፃፉት ደብዳቤ ይዘትና ከአቅርቦቱ ልዩ ባህርይ ሲታይ ለውሉ መፈረስ ምክንያቱ ተጠሪ ነው ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ውሉ የፈረሰና ለመፍረሱም ምክንያት አመልካች ናቸው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል አንዱን ዳቦ በብር 0.80 ለማቅረብ ተዋውለው እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. 811,363 ዳቦ ያቀረቡ መሆኑና ከግንቦት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ አቅርቦቱ በሌላ ግለሰብ እንዲቀጥል በተደረገው ውል ግን የአንድ

www.abyssinialaw.com

ዳቦ ዋጋ ብር 1.31 ሁኖ ተጠሪ ለአንድ ዳቦ ብር 0.51 ብልጫ ለሁለተኛ ጨረታ አሸናፊ እንዲከፍል የተገደደ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በክርክሩ ሂደት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለመከናወኑና ለሌላ ሰው ጨረታው ተላልፎ ሲሰጥም ተጠሪ ለዋጋ ጭማሪ መዳረጉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ የጉዳት ካሳ ጥያቄን መሰረት ያደረገውም ስራው በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ሙሉ በሙሉ ያለመተግበሩንና ድጋሚ ጨረታ ያስከተለውን ተጨማሪ ወጪ ነው፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል ውስጥ የውል ማስከበሪያ ዋስትና የጠቅላላ ዋጋውን 10% ብር 245,036.00 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ሰላሳ ስድስት ብር) አመልካች ለተጠሪ ማስያዝ እንደአለባቸው በአመልካች ግዴታነት በአንቀፅ 5.7 ስር በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን ከዚህ የገንዘብ መጠን ውጪ ለውሉ መዘግዬት ተብሎ የተጠቀሰው ለእንያንዳዱ ቀን የውሉን ዋጋ ብር 1/1000ኛ ታስቦ እንዲከፈል ውል ተቀባይ ግዴታ ያለው መሆኑን የሚሳይ የውሉ ድንጋጌ በውሉ አንቀፅ 5.10 ስር ተቀምጧል፡፡

የግራ ቀኙ ውል ከላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎችን ከመያዙ ውጪ አንዱ ወገን በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ግዴታውን ካልተወጣ ሌላው ወገን የጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑንና ሊጠየቅ የሚገባውን የጉዳት መጠን ምን ያህል እንደሆነ አይገልጽም፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ የመልካም ሥራ አፈጻጸም /ቦንድ/ ሰነድ መሆኑንና ይህም ከተጠሪ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመካስ ተብሎ የተገባ ግዴታ መሆኑን ተጠሪ ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ የሚከራከርበት ነጥብ ነው፡፡ የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ወይም የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ የውል አፈፃፀምን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የዋስትና ሰነድ መሆኑን፣ ይህም በባለገንዘብ እና በባለ እዳ መካከል የተደረገን ውል አፈፃፀም ለመጠበቅ የሚገባ ግዴታ መሆኑን ከሰነዱ አይነተኛ ዓላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ መሰረታዊ አላማ ስራው በውሉ መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ የሚገባ ግዴታ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. የተደረገው ውል በአንቀፅ 5.7 ስር ይህንኑ የሚያስገነዝብ ሲሆን አመልካች በወቅቱ ብር 245,036.00 ሙሉ በሙሉ ባያስይዙም ብር 26,035.07 አስይዘው ጨረታውን ማሸነፋቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህ ሲታይ የመልካም ስራ አፈፃፀም ቦንድ ስራው በስኬታማ ሁኔታ ባይጠናቀቅ በተጠሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ ጭምር ታስቦ የተገባ ግዴታ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህም አመልካችና ተጠሪ ስለጉዳት ካሳ ቀደም ብለው በውላቸው የገለፁት መጠን መኖሩን የሚያስረዳ ነው፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል አመልካች እንደ ውሉ ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው የተነሣ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት መጠኑን አስቀድመው ተምነው በውላቸው ላይ አስቀምጠዋል፡፡ ይህም ዓይነት ስምምነት በህግ የተፈቀደ እና ለተፈፃሚነቱ ለማናቸውም ጉድለት ነፃ ስለመሆኑ ያከራከረ ባለመሆኑ ይህም ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 እና 1889 እንደተደነገገው እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማካካስ የጉዳት ኪሣራ ገንዘብ መጠኑ በብር 245,036.00 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ሰላሳ ስድስት ብር) ብቻ እንዲወሰን በማድረግ ባደረጉት ስምምነት መሠረት በቃላቸው ሊታሰሩ እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካች ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት በመሆናቸውና በዚህም የተነሣ በአሁን ተጠሪ ላይ ጉዳት መድረሱ ቢታወቅም ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ የሆኑት የአሁን አመልካች በውሉ ከተመለከተው የጉዳት ኪሣራ ገንዘብ ጣሪያ በላይ ተጠሪን እንዲክሱ ሊገደዱ የሚቻልበት የህግ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ለተጠሪ ሊከፍል

በሚገባው የኪሣራ መጠን ላይ የተሰጠው የውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የጉዳት ኪሳራ መጠን ከብር 245,036.00 ሊበልጥ አይችልም ከተባለ አመልካች ለተጠሪ ዳቦ አቅርበው ያልተከፈላቸው ብር 526,556.00 (አምስት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስድሰት ብር) መኖሩ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠና ተጠሪም ያልካደው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች ይኼው ገንዘብ እንዲከፈላቸው በስር ፍርድ ቤትም ክስ የመሰረቱ በመሆኑ ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ የሚያስቀሩበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ በመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ማስያዝ ከሚገባቸው ገንዘብ ብር 245,036.00 ውስጥ ብር 26,035.07 ብር ያስያዙ በመሆኑ ማስያዝ ከሚገባቸው ገንዘብ ውሰጥ ብር 219,000.00 ያላስያዙ በመሆኑ ይሔው ገንዘብ ከብር 526,556.00 ሊቀነስ የሚገባው ሆኖ ስለአገኝን ገንዘቡ ተቀንሶ የሚመጣው ውጤት ብር 307,555.07 (ሶስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) ለአመልካች ተጠሪ ሊከፍል የሚገባው ገንዘብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 18461 ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64967 ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት በመሆናቸውና በዚህም የተነሣ በአሁን ተጠሪ ላይ ጉዳት መድረሱ ቢታወቅም ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ የሆኑት የአሁን አመልካች በውሉ ከተመለከተው የጉዳት ኪሣራ ገንዘብ ጣሪያ በላይ ተጠሪን እንዲክሱ ሊገደዱ የሚቻልበት የህግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡ አመልካች ብር 245,036.00 ሊያገኙ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ ዳቦ አቅርበው ካልተከፈላቸው ገንዘብ ውስጥ ብር 307,555.07 (ሶስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) ተጠሪ ሊከፍላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ማናቸውንም ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ህ

www.abyssinialaw.com

# የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 72017

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

አመልካች፡- አቶ ጕታ ኤጀታ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሙደሲር ረዲ - ጠበቃ አቶ መኮንን ኪዳን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 ድንጋጌ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሌላ ጉዳይ የፍርድ ባለእዳ ስለነበሩ ንብረታቸው የሆነውና በአዲስ አበባ አዲስ አዲስ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/15 ክልል የሚገኘው ዲዲስ መድኃኒት መደብር ተሸጦ ለእዳቸው ክፍያ እንዲውል በሐራጅ እንዲሸጥ ገዥዎች ተጋብዘዋል፡፡

በዚህም መሠረት የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ንብረት በብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ለመግዛት በሐራጁ ሽያጭ ተወዳድረው አሸናፊ መሆናቸው ተለይቷል፡፡

ይሁን እንጂ ይህንኑ የግዥ ዋጋ ክፍያ ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ ተከናውኖ አቶ አብዱ መሐመድ ይህንኑ ንብረት በብር1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ለመግዛት የጨረታው አሸናፊ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ እኚህ ሁለተኛ ገዥም እንደ አሸናፊነታቸው ያሸነፉበትን የንብረቱን ዋጋ ከፍለው ሊረከቡ ባለመቻላቸው ለሶስተኛ ጊዜ የሐራጅ ሽያጭ ሲደረግ ንብረቱ በብር 265,000.00 (ሁለት መቶ ስልሣ አምስት ሺህ ብር) ተሸጧል፡፡ በዚህም የሐራጅ ሽያጭ ዋጋ የንብረቱ ሽያጭ ተከናውኗል፡፡

ከዚህ ከኃላ የአሁን አመልካች በአንደኛ እና ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ በሐራጅ ሽያጩ ተወዳድረው ንብረቱን በብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ለመግዛት እንደቅደም ተከተሉ አሸናፊነታቸው ከታወቀ በኃላ በማፈግፈጋቸው ንብረቱ በሶስተኛ ሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ባሽቆለቆለ ዋጋ በብር 265,000.00 (ሁለት መቶ ስለሣ አምስት ሺህ ብር) እንዲሸጥ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 እንደተደነገገው በሐራጅ ሽያጩ ጊዜ የተከሰተውን የዋጋ ልዩነት 735,000 (ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር) ሁለቱም በአንድነትና

www.abyssinialaw.com

በነጠላ ሊከፍሉ ሲገባ በሥር በበየደረጃው ያሉት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች በሁለተኛው ሐራጅ ጊዜ አሸናፊነቱ የታወቀውን ብቻ ኃላፊ አድርገው በመጀመሪያው ሐራጅ ጊዜ ገዥነቱ የታወቀውን ከኃላፊነት ነፃ ማድረጋቸው ይህንኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ድንጋጌ አፈፃፀምን በአግባቡ የተከተለ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሊታረም ይገባል በማለት ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ መነሻ ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ የጽሁፍ ክርክራቸውን አጠናቀው ጉዳዩ ለምርመራ የቀረበ ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም በአፈፃፀም እንዲሸጥ በሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት በሁለት ተከታታይ የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ሁለት ተወዳዳሪዎች ተመሣሣይ የሐራጅ መግዣ ዋጋ ካቀረቡ በኃላ ሁለቱም ይህንኑ ያሸነፉበትን ዋጋ ሊከፍሉ ባለመቻላቸው ሶስተኛ ሐራጅ ተደርጎ ንብረቱ እነርሱ ካቀረቡት ባነሰ የመግዣ ዋጋ ከተሸጠ ይህንኑ የሽያጭ ዋጋ ልዩነቱን መክፈል ያለባቸው ሁለቱ ናቸው ወይስ በሁለተኛው ሐራጅ ጊዜ ተወዳድሮ ከመጀመሪያው የሐራጅ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው ጋር ተመሣሣይ የመግዣ ዋጋ ያቀረበው ብቻ ነው? ለሚለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 ድንጋጌ ቀጥተኛ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም፡፡

ያም ሆኖ የዚህ ድንጋጌ ግብ እና ዓላማ በሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ተወዳድሮ አሸናፊ መሆኑ ከተረጋገጠ በኃላ እንደአሸናፊነቱ የሽያጭ ዋጋውን ባለመክፈሉ የተነሣ ለሌላ ለሁለተኛ ሐራጅ መንስኤ ከሆነና በዚህም ሌላ (ሁለተኛ) ሐራጅ ጊዜ ንብረቱ ከመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ ዋጋ አንሶ ከተገኘ ይህን የዋጋ ልዩነት በካሣ መልክ የፍርድ ባለእዳው አዲያገኝ በማድረግ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ለንብረቱ ብር 1,000,000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ የመግዣ ዋጋ አቅርቦ አሸናፊነቱ ከተለየ በኃላ ዋጋውን አለመክፈሉ እና ለሁለተኛ ሐራጅ ሽያጭ መንስኤ መሆኑ ቢረጋገጥም፤ ሁለተኛው የሐራጅ ሽያጭ ተደርጎ በዚህ ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ አሸናፊ ሆኖ የተገኘው ገዥ ያቀረበው የመግዣ ዋጋ የአሁን ተጠሪ አቅርቦት ከነበረው የብር1,000,000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ የግዥ ዋጋ ጋር ተመሣሣይ እንጂ ያነሰ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም የተነሣ የአሁን ተጠሪ ገዥነቱ ከታወቀ በኃላ የመግዣ ዋጋውን አለማቅረቡ በፍርድ ባለእዳው ላይ ያስከተለው ጉዳት የለም፡፡

ከዚህም አንፃር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 የተመለከተው ድንጋጌ ቀጥተኛ ምላሽ የሚሰጥ ባይሆንም ክፍተቱን ለመሙላት የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያው ሐራጅ ጊዜ ገዥነቱን ካረጋገጠ በኂላ የግዥ ዋጋውን ባለመክፈሉ እና ለሁለተኛ ሐራጅ ሽያጭ ምክንያት መሆኑ ቢታወቅም ይህ መሆኑ በእራሱ በፍርድ ባለእዳው ላይ ያስከተለው ጉዳት እስከሌለ ድረስ በሁለተኛው ሐራጅ ሽያጭ ጊዜ አሸናፊነቱ ተለይቶ ካፈገፈገውና ለሶስተኛ ሐራጅ ሽያጭ ምክንያት ሆነው ንብረቱ ባነሠ ዋጋ እንዲሸጥ ቀጥተኛ ምክንያት ከሆነው እና ለልዩነቱ ብር 735,000.00 /ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር/ ኃላፊ ከሆነው ከአቶ አብዱ መሐመድ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የለበትም በሚል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 69945 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በተለያዩ የሐራጅ ሽያጮች ጊዜ ለተከሰተው የዋጋ ልዩነት የአሁን ተጠሪ ለአሁን አመልካች ለመክፈል የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የለበትም መባሉ በአግባብ ነው፡፡ ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር መዝገብ በሠበር መ/ቁ. 72017 ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተጠሪ ቤት ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ትእዛዙ ለተላፈላቸው ክፍሎች ይፃፍ፡፡
4. የዚህ ሰበር ጉዳይ ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 79555

ታህሳስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ቤተልሄም ፋርማሲ ቲዩካል ኃ/የተ/የግል/ማህበር አልቀረበም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ነገረ ፈጅ ምህረት ኃ/የሱስ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል በድሀ ደንብ መሠረት የሚቀርብበትን አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡

የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ለማቅርበው የ47,705.069 ብር (የአርባ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ አምስት ሺህ ስድሳ ዘጠኝ ብር) ክስ ሊከፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ብር 429,900.69 (አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር ከ69%) የሆነውን ገንዘብ ለመክፈል የገንዘብ አቅም ስለሌለኝ ክሱን በድሀ ደንብ እንዳቀርብ እንዲፈቀድ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ የተደረገው ስለድህነቴ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ሳይሰሙ ስለሆነ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ዳኝነቱ በሕግ አግባብ የተሰጠ ስለሆነ በሰበር ሊታረም የሚችል የሕግ ስህተት የለም የሚለውን ክርክሩን አቅርቧል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ክስ ለማቅረብ የፈለገ ወገን ከፍርዱ ለሚያገኘው የዳኝነት አገልግሎት መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የገንዘብ አቅም የሌለው ከሆነ ክሱን ያለዳኝነት ገንዘብ በደሀ ደንብ መሠረት የማቅረብ መብት እንዳለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 215 ተደንግጓል፡፡

ክሱን የሚያቀርበው ወገን ድሀ በመሆኑ ምክንያት የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክሱን አቅርቦ እንዲያሰማ ሊፈቅድለት ይገባል? የሚለው ጉዳይ ሊለይ የሚችልበት ዝርዝር አፈፃፀም ደንቡም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 467 እና ተከታዩ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

እነዚህ ደንቦች ተፈፃሚነታቸው ክስ ለማቅረብ በፈለገ የተፈጥሮ ሰውም ሆነ በሕግ ሰውነት ያላቸው ወገኖችም ጭምር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ድሀ ነኝ፤ መብቴን ለማስከበር ያለኝ ፍላጐቴ በዳኝነት ገንዘብ እንቅፋት ምክንያት ሊሰናከል አይገባም፡፡ ስለሆነም በድሀ ደንብ መሠረት ክሱን በነፃ እንዳሰማ ይፈቀድልኝ የሚል ማናቸውም ከሳሽ ድሀ መሆኑን ሊያመለክት የሚችል የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ይህም ከሳሹ የሚገኝበት የገንዘብ አቋም ከተረጋገጠ በኋላ ለክሱ ሊከፈል የሚገባው የዳኝነት ገንዘብ መጠን ከሳሹ ከሚገኝበት የገንዘብ አቋም አኳያ ተገናዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 467 መሠረት ድሀ የመሆኑና ያለመሆኑ ጉዳይ ሊለይ ይገባል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሕግ ሰውነት የተሰጠው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ድሀ መሆኑንና አለመሆኑን በመለየት በመነሻነት ሊረዳ የሚችለውን ከሳሹ የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ይህ ዓይነት ከሳሽም የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም ለመረዳት በምን የገንዘብ አቋም ደረጃ ላይ ይገኛል የሚለውን ለመወሰን የሚገባው አግባብነት ባለው የንግድ ሕግ መሠረት ካልሆነ በስተቀር በሰው ማስረጃ መለየት የሚቻል አይደለም፡፡ ስለሆነም ከሳሹ የሚገኝበትን ደረጃ ለመለየት ለጉዳዩ ተቀባይነት ያለው የማስረጃ ዓይነት በንግድ ሕጉ ስለገንዘብ አቋሙ/ደረጃው ለማረጋገጥ ያስችላል ተብሎ የሚቀርበው የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡ የሰው ማስረጃዎች ስለጉዳዩ የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በሕግ ዓይን ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካችም ስለምገኝበት የገንዘብ አቋም ሊያረጋግጥ ይችላል በሚል የኦዲት ማረጋገጫ እንዳቀረበ ገልፆ ቢከራከርም ይህ ማረጋገጫ ክሱ ከመቅረቡ 8 እና 7 ዓመት በፊት የነበረውን ሁኔታ የሚጠቅሱ በመሆኑ አሁን ያለበትን ደረጃ ሊያመለክት የሚችል አይደለም፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እንደተመለከተው የአንድ ሰው ፍትሕ የማግኘት መብቱ ሊከበር የሚችለው ይህንኑ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ለማስፈፀም ሲባል የተቀመጡትን ዝርዝር የክስ አቀራረብ ደንብም ጭምር ተሟልቶ ከተገኘ እንደሆነ ስለጉዳዩ የተዘረጋው የሕግ ማዕቀፍ አስረጂ ነው፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ከከሳሹ ማንነት አንፃር በማየት አመልካች ድሀ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከመለየት አንፃር የሰጡት ዳኝነት የማስረጃ አቀባበል ሥርዓትን የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**ው ሣ ኔ**

በፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 77257 ሚያዝያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 79465

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ - ነ/ፊጅ ሠለሞን ረታ ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አገኘው ገረመው - የቀረበ የለም

2. ኪንግናም ቦንጋ ሚዛን የመንገድ ስራ ድርጅት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌን አፈጻጸም የሚመለከት ሲሆን ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ በከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሠረተው ክስ ነው፡፡ በክሱም በቁጥር 3-05118 ደሕ በሚል መለያ በራሳቸው ንብረትነት የምትታወቀውንና የህዝብ ማመላለሻ የሆነችን መኪናቸውን ንብረትነቱ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የሆነውና በቁጥር UR 666 የሚታወቀው ሩሮ ማሽን በውሽውሽ ከተማ ከሚገኘው የ1ኛ ተጠሪ መኖሪያ ቤት አከባቢ በቆመችበት ሁኔታ ገጭቶ ጉዳት ያደረባት መሆኑን ጠቅሰውና ለተለያዩ ውጪዎች መዳረጋቸውን ጠቅሰው የወጪውን አይነትና መጠን ዘርዝረው በድምሩ ብር 93733.00 (ዘጠና ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ 2ኛ ተጠሪም ጉዳት አደረሰ የተባለው መኪና የራሱ መሆኑን አምኖ ተሽከርካሪው በአሁኑ አመልካች የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን ጠቅሶ በክሱ ውስጥ እንዲገባ ጠይቆ የአሁኑ አመልካችም ወደ ክሱ እንዲገባ ከተደረገ በኂላ በሰጠው መልስ ከአሁኑ አመልካች ጋር ያደረገው የመድን ውል ጉዳዩን የማይሸፍነው፣መድኑ የተገባው የ2ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ሳይሆን ከመንገድ ኮንስትራክሽን ስራ ጋር በተያያዘ ለሚደርስ ጉዳት መሆኑን ጠቅሶ በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ የሚከራከርበት አግባብ የሌለ መኑን ገልፆ ለጉዳዩ ተጠያቂነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን በአማራጭም የጉዳት ከሳ መጠኑ የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ 2ኛውን ተጠሪ በባለንብረትነቱ በ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ጉዳት አድርሷል በሚል ምክንያት፣አመልካችን ደግሞ ለጉዳዩ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከመድን ውሉ ይዘት መረዳቱን ገልጾ ለጉዳቱ ሁለቱንም ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን የጉዳት ካሳ መጠኑንም በርትዕ ወስኖ በድምሩ ብር 41,100.00 (አርባ አንድ ሺህ አንድ መቶ) በማድረግ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለ1ኛ ተጠሪ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡የአሁኑ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎች አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም

www.abyssinialaw.com

ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ያለው የመድን ሽፋን ውል ጉዳዩን የማይሸፍን ሁኖ እያለ ጉዳዩን ይሸፍናል ተብሎ አመልካች ካሳውን እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ጉዳዩን በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተገባው የመድን ሽፋን ውል የሚገዛው መሆኑን ዘርዝርው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው አመልካች ወደ ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሰረት እንዲገባ ሲደረግ በሰጠው መልስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል ጉዳዩን የማይሸፈን መሆኑን ገልጸ በተከራከረበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በ1ኛ ተጠሪ መዝገብ ላይ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት አደረሠ የተባለው መኪና የ2ኛ ተጠሪ የነበረ ሲሆን ይህ መኪና በአሁኑ አመልካች የመድን ሽፋን የነበረው መሆኑ አልተካደም፡፡አከራካሪው ነጥብ የመድን ሽፋን አድማሱ እስከምን ድረስና በምን ጉዳዮች ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገው ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሳ የሚችለው ክርክር ምን ድረስ ነው የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 23692 እና 78314 የሰጠውና በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በተጠቃሾቹ መዛግብት የክርክሩ ተካፋይ ሦስተኛ ወገን የሚያቀርበው ክርክር ሁለት ፈርጅ ሊይዝ የሚችል መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም "1ኛው ከተከሳሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሳሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሳሽ እግር በመተካት ተከሳሽ ለከሳሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፤ ኃላፊነት አለበት እንኳ ቢባል ሊከፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ከከሳሽ ጋር ንጽጽር ማድረግ፤ መሟገት የሚችልበት ክርክር ሲሆን ሌላው እና ሁለተኛው ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሳሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር የሚችልበት መንገድ ነው፡፡" ስለሆነም የድንጋጌው ይዘት ጣልቃገብ ሦስተኛ ወገን ተከሳሽ በክርክሩ ከገባ በኂላ መሟገት የሚችለው ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሳሽ ጋር ለመከራከር የሚያስችለው መብት የለውም የሚለው ድምዳሜ የሕግ መሠረት የለውም የሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡የሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 23692 እና 78314 ላይ ይህንን ትርጉም ለመስጠት መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ እና የሙግት አመራር ውጤታማነት እንዲሁም የድንጋጌ ቁጥር 43(1) እና 76 እንዲሁም የመሠረታዊ ሕጉ ድንጋጌዎች ውስጥ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1896፣ 1897፣ 1908 እና 1909 አፈጻጸም እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 687,688 እና 683 ድንጋጌዎች በክርክር አመራር ረገድ የሚፈፀሙበትን ሁኔታ እና ግብ መነሻ በማድረግ መሆኑ በፍርዱ ሀተታ ተገልጿል፡፡ ለማጠቃለል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 43 አስፈላጊነትም ተከታታይ ክስ ሳይኖር በአንድነት እንዲታይ በማድረግ የኃላፊነት እና መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት መስጠት ማስቻል እንደመሆኑ በተለይ ካሣ (indemnity) የመክፈል ግዴታ ያለበት አመልካችን መሰል የመድን ድርጅቶች ከከሳሹ

www.abyssinialaw.com

እና ተከሳሹ ጋር የሚኖራቸውን አጠቃላይ ክርክር ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ በውሳኔው ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የሚጠራ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ወገን ከመነሻውም ከተከሳሹ ጋር የሕግ ወይም የውል ግንኙነት የለኝም በማለት ክርክር ከአቀረበ የክርክሩ ተሳታፊ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡እንዲህ አይነት ክርክር እልባት ማግኘት ያለበት በተለየ ክስ እና የክርክር መዝገብ እንጂ ከሳሽ ባቀረበው መዝገብ ሊሆን አይገባም፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌ አላማም እንዲህ አይነት ክርክሮችን ሁሉ በአንድ አይነት መዝገብ አጠቃልሎ ለመወሰን ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡ይልቁንም ጣልቃ ገብ ከመነሻውም ክዶ በተከራከረበት ጉዳይ የተከሳሽንና የጣልቃ ገብን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ መስጠት ከሳሽ ያቀረበው ክስ ያላግባብ ጊዜና ወጪን እንዲጨምር የማድረግ ውጤት የሚኖረው ይሆናል፡፡ስለሆነም አመልካች ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር ያለውን የውል ግኙነት የካደ ሁኖ እያለ ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጎ በውጤቱም አመልካች ለካሳው ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ጋር ባልተጣጠመ መልኩ ሁኖ ስለአገኘን በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሥነ ስርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06440 ጥቅምት 27 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር09515 መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ/ም ባጸናው ውሳኔ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የመድን ውል ጉዳዩን ይሸፍናል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የመድን ውል መኖር ያለመኖሩ ከመነሻው አከራካሪ የሆነ በመሆኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሰረት የክርክሩ ተሳታፊ መደረግ አልነበረበትም ብለናል፡፡
3. 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ካሳውን ይክፈል የተባለው የውሳኔ ክፍል በዚህ ውሳኔ አልተነካም፣እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ ወደፊት የሚያቀርበው ሕጋዊ ጥያቄ ካለ ይህ ውሳኔ ቀሪ አያደርገውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመልስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

**የሀሣብ ልዩነት**

እኔ በሶስተኛ ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ ቁጥር 43 ላይ በሰጠው ትርጉም የማልስማማ በመሆኑ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43 የተከሣሽና የሶስተኛ ወገን ተከራካሪውን ክርክሮች በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች ከሣሹ ከተከሣሽ የሚያገኘውን መብትና ጥቅም እንዲሁ ክዶ ቢከራከርም ከሶስተኛ ወገን ተከራካሪው የሚያገኘውን መብትና ጥቅም ያለመሆኑን ወይም አለመሆኑን ተከሣሽ ከሶስተኛ ወገን ተከራካሪው የሚያገኘው ጥቅም ካለ መጠኑን ለይተው ከመወሰን የሚገድባቸው አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን የክርክሩ ተሣታፊ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ሃሣብ ያለኝ በመሆኑ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 83701

ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ ህንደያ እንድሪስ ወኪል አብዲ ዓሊ - ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የወጪና ኪሳራ አወሳሰን ሥርዓትን አስመልክቶ በተነሳ ክርክር ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በቀዳሚነት የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ጉዳይ በየትኛው ዓይነት መዝገብ ቀርቦ ሊታይ ይገባል? የሚለውን አስመልክቶ ያቀረበውን ክርክር አግባብነት ተመልክተናል፡፡

አመልካች ይህ ብር 10,000.00 እንድንከፍል የተወሰነብን የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው በአፈፃፀም መዝገብ ሆኖ ሳለ በተዘጋውና ዋናው ጉዳይ የታየበት መዝገብ ተንቀሳቅሶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ የአፈፃፀም መዝገቡ ደግሞ በበላይ ፍ/ቤት ታግዷል፡፡ ስለሆነም ይህ የወጭና ኪሳራ ጉዳይ የሚታይበት ሥርዓት ሳይኖር የተወሰነብን አወሳሰን ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁን እንጂ በአፈፃፀም ጉዳይ ቀርቦ ሊታይ የሚገባው ማናቸውም ጉዳይ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 ተደንግጓል፡፡

ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነው ፍርድ ከሚያካትታቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ፍርዱን ለማስወሰን ሲባል በክርክር ምክንያት የወጣው የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 183 በግልፅ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም ወጭና ኪሳራን ግን እንደሚከፍል በዋናው ጉዳይ ተለይቶ ከተወሰነ በኋላ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463 መሰረት የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ዋናው ፍርድ ባረፈበት መዝገብ ላይ ቀርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ስለቀረበው የወጭና ኪሣራ አስፈላጊነት፤ ስለመጠኑ እና በእርግጥም ወጭና ኪሳራ ስለመውጣቱ የበኩሉን ክርክር ካቀረበ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 464 እንደተመለከተው የወጭና ኪሳራ ልኩ ይወሰናል፡፡

www.abyssinialaw.com

እንግዲህ የወጭና ኪሳራ አወሳሰን ሥርዓት ይህ ከላይ የተመለከተው በመሆኑ የአሁን አመልካች የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው በአፈፃፀም መዝገብ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው፣ የፍርድ አፈፃፀምን ጉዳይ መነሻ ሀሳብ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤቱ በወጭና ኪሳራ መልክ የቀረበውን እና ለጠበቃ ተከፈለ የተባለውን የጥብቅና አበል በሚመለከት በማስረጃነት የቀረበው የጥብቅና ውል ከጊዜ ቅደም ተከተል አንፃርም ሆነ ከጠበቃው ማንነት አንፃር በአስረጅነቱ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ከገለፁ በኋላ በሌላ በኩል ጠበቃ ተስፋሁን የተባለ ሌላ ጠበቃ በዋናው ጉዳይ ጊዜ የነበረ መሆኑን መታመኑን እና የጥብቅና አበል መጠን ክርክር በተደረገበት የገንዘብ መጠን አስራት መነሻ ተደርጎ የቀረበውን ባለመከተል ጉዳዩን ለመከታተል ወጣ ሊባል የሚችለው የጥብቅና አበል መጠን ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ነው ሲል ስለመጠኑም የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 በፍ/ቤቱ የተሰጠውን ፍቅድ ሥልጣን ከጉዳዩ ጋር በማዛመድ ተመልክቶ የወሰነው በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ ባለመግኘታችን ምክንያት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የሐረሪ ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 02260 መስከረም 09 ቀን 2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የጥብቅና አበልን አስመልክቶ የሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት ፀንቷል፡፡
2. ቀደም ሲል በመ/ቁ 07208 የተጀመረው የአፈፃፀም ክስ ታግዶ እንዲቆይ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ የሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 74890

ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሚስጢር ሰለሞን በእራሱ ቀረበ

መልስ ሰጪ፡- 1ኛ. አቶ ፍቃዱ ካሣሁን ቀረቡ

2ኛ. አቶ አሊ ካሣሁን አልቀረቡም

3ኛ. አቶ ሙላለም ካሣሁን አልቀረቡም

4ኛ. አቶ በላይ ካሳሁን ቀረቡ

5ኛ. አቶ አባተ ካሳሁን አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ክርክርን ለማስረዳት ሲባል የቀረበን ማስረጃ ህጋዊነት አስመልክቶ ክርክር በቀረበ ጊዜ ይኸው ክርክር ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ክርክሩ በቀረበበት ፍ/ቤት ወይስ በሌላ የተለየ ፍ/ቤት የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ከግራ ቀኙ ጉዳይ አንፃር ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ከአባቴ በውርስ ላገኝ የሚገባውን በአባቴ በአቶ ሰለሞን ካሳሁን ስም ተመዝግበው የሚታወቁትን በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 06/02 በቁጥር 020 የሚታወቀውን ቤት እና የሰሌዳ ቁጥሩ 01-4142 አ.አ የሆነውን መኪና ይዘው ስለሚገኙ እነዚህ ንብረቶች ላይ መብት የሌላቸው ስለሆነ እንዲያስረክቡን ቢጠየቁ አባቴ መጋቢት 10 ቀን 1986 ዓ.ም አድርጎታል ባሉት የቁም ስጦታ ለእናታቸው ያስተላለፉና እነሱም የእናታቸው ወራሽ ስለሆኑ በንብረቱ ላይ መብት እንደላቸው ገልፀው ለማስረክብ እምቢተኛ ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው የቁም ኑዛዜ ስጦታ በአባቴ ያልተፈረመ እና በአደራረጉም ረገድ በህግ ተቀባይነት የለውም የሚሉበትን ምክንያት በመጥቀስ በንብረቱ ላይ መብት አያሰጥም፡፡ ስለሆነም የዚሁኑ ንብረቶች ካስገኙት የኪራይ ጥቅም ጋር እንዲያስረክቡ ይወስንልኝ የሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም በዚህ ክስ መነሻ የአሁኑ ተጠሪዎች ያላቸውን ክርክር እንዲያቀርቡ ካደረገና የመልሳቸውንም ዝርዝር ይዘት ሳይመለከት መልሳቸውን በጥቅል ከጠቀሰ በኃላ በፍ/ብ/መ/ቁ 34398 በሆነው መዝገብ ሐምሌ 07 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ፡- ተደረገ የተባለውን የቁም ስጦታ ህጋዊ ነው? አይደለም? ሊፈርስ ይገባል አይገባም? የሚለውን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያለው ሌላ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሳሽ ሰነዱ በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም ከሚሉት በቀር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት አቅርበው ፈራሽ ነው በሚል

የተወሰነበትን ውሳኔ አላቀረቡም በዚህም ግራ ቀኙ በሚከራከሩበት ፍ/ቤት ይኸው የቁም ስጦታ እንዲፈርስ ይደረግልን በማለት አልጠየቁም ስለሆነም በዚህ ሰነድ አማካኝነት ለሶስተኛ ወገን የተላለፈን ንብረት የአውራሽ አባቴ ስለሆነ ለእኔ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክስ ተገቢነትም ሆነ የህግ መሠረት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ይህም ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 በተመለከተው መሠረት በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ ረገድ ግድፈት ያለበት ባለመሆኑ ሰርዘለሁ በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት በመስጠቱ የተነሳ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ምክንያት የሆነውን፡

የሰበር አቤቱታ አቅረበዋል፡፡ በዚህ ሰበር ደረጃም ክርክር ባስነሳው "የቁም ስጦታ ላይ ክርክር ቀርቦበት እያለ ከሳሽ አላስፈረሰቺውም በሚል የአሁን አመልካች ክስ ውድቅ መድረጉ አግባብ ነው? አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙ ያላቸውን ክርክር በፅሁፍ አቀርበዋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ይዘት እንደተረዳነው የአሁን አመልካች ክሱን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤትና መኪና ግምት መነሻው በማድረግ ክርክሩ በያዘው የገንዘብ መጠን ላይ የተወሰነን የስልጣን ዓይነት መሰረት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከሳሽ የክስ አቀራረብ ሥርዓት ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 14(1) አንፃር ሲታይ በእርግጥ ክሱ የቀረበው ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 16 ፣ 9 ፣231(1)(ለ) አንፃር ሲታይ ከስልጣን አንፃር ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ሲሆን፣ በዚህ ረገድም ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን አልነቀፈውም፤ የአሁን ተጠሪዎችም ክርክር አላነሱበትም፡፡

ከላይ በተገለፀው አኳኋን አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየትና ለመወሰን የስረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት የቀረበን ክርክር ለማስረዳት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 የቀረበን የሰነድ ማስረጃ ህጋዊነትን አስመልክቶ የሚቀርብን ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 246 ፣ 247 ፣ 248 እንደተደነገገው አከራካሪ ነጥብ ያስረዳ መሆኑ ታውቆ ክርክሩ በሚሰማበት የክርክር ደረጃ (at the trail stage) በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና ለክርክሩ አግባብነት ያለውን ህግ ተፈፃሚ በማድረግ በዚያው ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት የሚወሰን እንጂ ክርክርን በማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ብቻ በመነጠል የዚህን ያለአግባብ የተነጠለውን የማስረጃ ህጋዊነት በሚመለከት በሌላ ፍ/ቤት ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ የሚያስችል ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

ግራ ቀኙ በየፊናቸው ያቀረቡት ክርክር ተመልክቶ ለመወሰን ይኸው የቁም ስጦታ ህጋዊነት (validity) ከማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት አንፃር አይቶ እና ለይቶ በመወሰን ላይ የተመረኮዘ እንደመሆኑ መጠን የአሁን አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ በቀረቡት ክስ ውስጥ ይኸው የቁም ሥጦታ ሰነድ እንዲፈርስ ይወሰንልን በማለት የተለየ ዳኝነት እንደጠየቁ የሚያስገድድ የክርክር አቀራረብ ሥርዓትም የለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት አከራካሪ ሆኖ የተገኘውን የቁም ኑዛዜ ሰነድ ህጋዊነት አስመልክቶ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት በሆነው ክስ ላይ ማቅረብ አይችሉም፤ ሊያቀርቡ የሚችሉት እራሱን በቻለ የዳኝነት ጥያቄ በሌላ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊሆን ይገባል በሚል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራልየመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34398 በቀን 07/11/2003 ዓ.ም. የሰጠው ብይን፤ እና ይህ ብይን በአግባቡ የተሰጠ ነው በሚል ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁ 115381 ህዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው የቁም ስጦታ ሰነድ ህጋዊ መሆንና አለመሆኑ ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት የሙግት ደረጃውን ጠብቆ ከግራ ቀኙ ክርክርና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር ተገናዝቦ ሊወሰን የሚገባ ስለሆነ በዚሁ መሰረት የዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት ጉዳዩን ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ደረጃ የቀረበውን ክርክር ለመከታተል ግራ ቀኙ ያወጡት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር 80723

ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር ነገረ ፈጅ ብርሃኑ ሚልካሳ ቀረበ

ተጠሪዎች፡-1. ዋቅቶሉ አብደሳ ክርክሩ በዚህ ሰበር ችሎት ተቋርጧል

2. የጊምቢ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነገረ ፈጅ አቶ አዲሱ ደሳለኝ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የተቋረጠ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት በሙግት ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማዛመድ በአግባቡ ታይቶ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ሲባል የቀረበ ነው፡፡

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በዚህ የሰበር መዝገብ 1ኛ ተጠሪ በሚል የተሰየመው በአቶ ዋቅቶሌ አብደላ በብድር የወሰደውን ገንዘብ እንደውሉ መልሶ ለመክፈል የተሳነውና ያልቻለ በመሆኑ ቀሪ የብድር ገንዘብ እስከ መጋቢት 13/2003 የታሰበ ወለድና የወለድ ቅጣት ብር 100,240.74 /አንድ መቶ ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር ከ74/100/ በአጠቃላይ ብር 146,994.44 /አንድ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ብር ከ74/100/ እንዲሁም ይኸው ዕዳ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር ይክፈለን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ተበዳሪው በብድር ለወለደው ገንዘብ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ በዚሁ ተበዳሪ ስም በካርታ ቁጥር 033/00/88 የተመዘገበውንና በግምቢ ከተማ ቀበሌ 03 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 667 የሆነውን መኖሪያ ቤት የግምቢ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከዕዳና እገዳ ነጻ መሆኑን በማረጋገጥ እና ለዚሁ ብድር የእኛ መያዣ መሆኑን መዝግቦ በማረጋገጡ ይህንኑ መያዣ ይዘን የብድር ገንዘቡን ለተበዳሪው ሰጥተናል፡፡ ሆኖም ይኸው ቤት በተበዳሪው ባለቤት በወ/ሮ ደሼ ተረፈ ስም በግምቢ ማዘጋጃ ቤት አማካኝነት ሌላ ካርታ ቁጥሩ 502/89 የሆነ ተዘጋጅቶ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለሰጠው ብድር መያዣ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት የልማት ባንኩ በሰጠው ብድር ምክንያት ይህንኑ ቤት የተረከበው መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ስለሆነም ማዘጋጃ ቤቱ በፈፀመው ጥፋት ምክንያት ጉዳት እንዲደርስብን ያደረገ ስለሆነ ለዕዳው ተጠያቂ በመሆኑ ከዋናው ተበዳሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡

በዚህ ክስ መነሻ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው ዋናው ተበዳሪ አሁን በ1ኛ ተራ ቁጥር በተጠሪነት የተጠቀሰው ተከራካሪ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ 10 ዓመት ካለፈው በኋላ ክሱ የቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ

www.abyssinialaw.com

1845 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ሲከራከር የአሁን 2ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተከሳሽነቱ በሰጠው መልስ ላይ ባንኩ በእኛ ላይ ክስ ለማቀረብ አይችልም ንብረቱን መውሰድ ይቻላል በማለት በፍሬ ነገሩ ረገድ ከመከራከሩ በቀር እንደተከሰሰ የይርጋ ክርክርን ጠቅሶ ያቀረበው ክርክር እንዳልነበረ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ላይ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሁለቱም ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 እና 3058 መሰረት በይርጋ ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡
በዚህ ውሣኔ መነሻ የአሁን አመልካች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደማይገባ ገልፆ ከታች ወደ ላይ በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነትን ያላገኘ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም ይገባል በማለትና ምክንያቱን በመዘርዘር ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ግራ ቀኙ ባሉበት በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚገባ መሆኑ ተጠቅሶ መጥሪያ ለ1ኛው ተጠሪ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ የተሰጠው ቢሆንም ይህንኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱን መጥሪያ በእራሱ ቸልተኝነት ወጭ አድርጎ ያለመውሰዱና ይህም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70/መ/ አንጻር ታይቶ ጥቅምት 28 ቀን 2005ዓ.ም በዋለው ችሎት በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው የሰበረ ክርክር ተሰርዞ ቀሪ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡
በሌላ በኩል አመልካች የአሁኑን ሁለተኛ ተጠሪ አስመልክቶ ይኸው 2ኛ ተጠሪ ይርጋን በሚመለከት በስር የከፍተኛ ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ጊዜ በማንሳት ያልተከራከረበት ስለሆነ ክርክር ባልቀረበበት ጉዳይ በዚሁ ተከራካሪ ወገን ላይ ያቀረብነው ክስ በይርጋ ውድቅ ነው መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የመከራከሪያ ነጥብነቱ ሲያቀርብ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው መልስ ስለይርጋ ጉዳይ 1ኛ ተከሣሽ የነበረው በማንሳት የተከራከረበት ስለሆነ እኛም እንድናነሳ አይጠበቅብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረው የአሁን አመልካች በሁለቱም ወገኖች ላይ በመሰረተው ክስ ሁለቱም ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው በሚል ሁለቱንም የከሰሳቸው ስለሆነ 1ኛው ተከሳሽ የነበረው ያነሳው የይርጋ ጊዜ ለሁለተኛ ተከሳሽም የሚጠቅም ይሆናል፡፡ ስለሆነም የብድር ውሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ መብቱን ለማስጠበቅ እንቅስቃሴ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ 10 ዓመት ያለፈው ስለሆነ በብድር ምክንያት ንብረት በመያዣነት ከተመዘገበና ይኸው የመያዣ ጉዳይ ውጤት የሚኖረው ለ10 ዓመት ብቻ በመሆኑ ይህ የ10 ዓመት ጊዜ ከመሙላቱ በፊት የመያዣ ውሉ እንዲታደስ ካልተደረገ በቀር ውጤት የሚያስከትለው ለ10 ዓመት ብቻ ሰለሆነ እንዲሁም ማስጠንቀቂያ ሰጠሁ የሚለው በዚሁ 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሆኖ ስላለተገኘ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በሚል በስር ፍ/ቤት መወሰኑ አግባብ ነው በማለት ውሣኔውን አጽንቶ ወስኗል፡፡
ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ላይ የአሁን አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

እኛም በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውስጥ ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር ጋር በማገናዘብ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በአንደኛ ተጠሪነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰየመው ጋር ተጣምሮ በተከሰሰ ጊዜ የይርጋ ክርክርን በማንሳት ያልተከራከረ ለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ የተረጋገጠ የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይኸው ተጠሪ ይርጋን ጠቅሶ ክርክር አለማቅረቡ ቢታወቅም የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በሚል ከ1ኛው ተጠሪ ጋር ተጣምሮ የተከሰሰ በመሆኑ 1ኛው ተጠሪ ባነሳው የይርጋ ክርክር ተጠቃሚ መሆኑ አይቀርም የሚለውን ምክንያት በመጥቀስ ነው ይህንኑ ተከሳሽም አስመልክቶ የቀረበው ክስ በ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ቀሪ ነው የሚለውን ውሣኔ ሊሰጥ የቻለው፡፡

ይሁን እንጂ በተለያዩ የመሰረታዊ ህጐች ክፍል ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ወገኖች ለገንዘብ ጠያቂው ወይም ከሳሽ በመሆን ለሚሰየመው ወገን  የአንድነትና የነጠላ ግዴታ አለባቸው በሚል የተቀመጡት የህግ ድንጋጌዎች መብትና ግዴታን በማቋቋም ረገድ ምክንያታቸውና መነሻ ሀሳባቸው ሁልጊዜም ተመሳሳይ መሆናቸው ታይቶ አይደለም የአንድነትና የነጠላው ኃላፊነት ከተለያዩ የህግ ክፍል እና ከተለያዩ ምክንያት ሊመነጭ ይችላልና፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ የአንደኛ ተጠሪ ኃላፊ ነው በሚል የቀረበው ክስ ከውል ህግ የመነጨ ሁለተኛው ተጠሪ ደግሞ ስለ ጉዳዩ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በሚል የቀረበበት ክስ ከሚጠበቅበት የስራ ግዴታ አንጻር የፈፀመው ድርጊት ጥፋት ነው በሚል ውል ሳይኖር በሚደረግ ኃላፊነት ህግ በሚገዛው ክፍል እንደሆነ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

የሁለቱም ዓይነት የኃላፊነት ምንጭ ከተለያዩ የህግ ክፍል የሚነሳ እንደመሆኑ እንደቅደም ተከተሉ የይርጋ ክርክር በተነሣ ጊዜ የይርጋ ዘመናቸው ጉዳዩን እንደሚሸፍነው የህግ ክፍሉ በተቀመጠው የይርጋ ዘመን መሰረት እየታዩ የሚወሰን በመሆኑ አንዱ ያነሳው የይርጋ ክርክር ለሌላውም ይጠቅመዋል ብሎ ለመተርጎም የሚቻል አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 36 እንደተመለከተው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ያለባቸውን ወገኖች አጣምሮ መክሰስ እንደሚቻል መደንገጉም ሁለቱንም ወገኖች ለየብቻ ከመክሰስ ይልቅ በአንድ መዝገብ አጣምሮ መክሰሱ በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ ጉዳዮችን ለመቋጨት ያስችላል በሚል እንጂ አንዱ ተከሳሽ የሚያቀርበው ክርክር ያለቅድመ ሁኔታ ለሌላውም ተጣምሮ ለተከሰሰው ተከሳሽ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑ ታይቶ አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ 1ኛው ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያነሳው የይርጋ ክርክር በዚሁ አቅራቢ ላይ ብቻ የሚወሰን እንጂ የአሁን 2ኛ ተጠሪም እንዳቀረበው አድርጎ ለመቁጠርና ለመውሰድ የሚያስችል ህግ ባለመኖሩ 2ኛ ተጠሪ የይርጋ ክርክርን አስመልክቶ ክርክር አቅርቧል ማለት አይቻልም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 እንደተመለከተው የይርጋ ክርክር መቅረብ በሚገባው ጊዜ ካልቀረበ እንዳተተው ክርክር ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 244/3/ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1852 የተደነገገ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የተሳሳተ የትርጉም መነሻ በመየዝ 1ኛው ተጠሪ ያቀረበው የይርጋ ጊዜ ለአሁን 2ኛ ተጠሪም የሚጠቅም ነው በማለት  ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 127608 በቀን 13/07/04ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 78660 በቀን 16/09/2003ዓ.ም የሰጠው ብይን ሁሉ ተሽሯል፡፡
2. በአሁን ሁለተኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በሚል እንደ ስርአቱ ክርክር ያልቀረበበት በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡
3. በይርጋ ቀሪ ነው በሚል የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአሁን አመልካች ከአሁን 2ኛ ተጠሪ ከግምቢ ማዘጋጃ ቤት ጋር ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ ታይቶ ተገቢው ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ጉዳዩን ወደ ምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
4. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡
   ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 84353

ጥር 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር ሂሣብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ

ነገረ ፈጆች አዲስ ቦጋለ እና ላዕከማሪያም ሊቁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወጋገን ባንክ አ/ማህበር ነገረ ፈጅ ገቢሳ ተሬሳ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አበዳሪ ወጋገን ባንክ ለጥቁር ዓብይ ኮንስትራክሽን ማህበር የሰጠው ብድር ባለመመለሱ ምክንያት ለብድር አመላለሱ ሲባል በመያዥ የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በሐራጅ ሲሸጥ ይህንም የሀራጅ ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበው ክርክር በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ባጭሩ፡ የፈረሰውን ጥቁር ዓባይ አ/ማህበር አመልካች በሂሣብ አጣሪነቱ ተረክቦ በማጣራት ላይ እያለ አበዳሪ ወጋገን ባንክ አ/ማህበር በህግ በተሰጠኝ ስልጣን በሐራጅ የመሸጥ መብት አለኝ በማለት የባለዕዳውን ንብረት በሐራጅ እሸጣለሁ በማለቱና ይህም በማጣራቱ ስራ ላይ ችግር ስላስከተለ የተጀመረው በሐራጅ የመሸጥ እንቅስቃሴ እንዲቆም ይደረግልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው የመከላከያ መልስ በጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር እና በተጠሪ ወጋገን ባንክ መካከል በተፈረመው የብድር ውል መሰረት ተበዳሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ በውሉ መሰረት ስላልከፈለ ለብድሩ አከፋፈል በመያዥ የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 በተሰጠን ስልጣን መሰረት በሐራጅ የመሸጥ ስልጣን ስላለው በህግ አግባብ በተቋቋመ የብድር ሰነድ ውል መነሻ ለብድር አመላለስ የተያዘን ንብረት የሐራጅ አሻሻጥን ምክንያት በማድረግ ፍ/ቤቱ ጣልቃ ገብቶ የማየት ስልጣን የለውም፡፡ ይህንንም በሚመለከት የፌደራል ሰበር ሰሚው ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ 70824 በሆነው ጉዳዩን ፍ/ቤት ተቀብሎ የመወሰን ስልጣን የለውም በሚል ትርጉምም የተሰጠበት ስለሆነ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በቅድሚያ ከሳሽ ክስ ያቀረበበትን ጉዳይ ይህ ፍ/ቤት ተቀብሎ ለማየትና ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን

ጭብጥ ይዞ ይህንኑ ነጥብ ከህጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ የተጠየቀው ዳኝነት በወጋገን ባንክ አ/ማህበር የተጀመረ የሐራጅ የመሸጥ እንቅስቃሴ እንዲቆም ትዕዛዝ እንዲሰጥ ነው፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 90/97 አንቀጽ 3 እና 4 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 እንደተሻሻለው ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዥነት በዋስትና የያዙትን ንብረት የብድር ዕዳው እንዲከፈለው በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈል ከቀረ ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይህንኑ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በሐራጅ የመሸጥና የባለቤትነት መብት ለገዥው የማዛወር ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ባንኩ በእነዚህ ህጐች መሰረት ንብረቱን በሐራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በአሻሻጡ ሂደት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 394-449 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባለመከተል ያደረሰው ጉዳት ካለ ለደረሰው ጉዳት ኪሣራ ከመጠየቅ በቀር የሐራጅ ሽያጭ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቆም ክስ የሚቀርብበት መብት እንደሌለና ፍ/ቤትም ተቀብሎ የማየት ስልጣን እንደሌለው በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 70824 የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ በዚህ አኳኋን ተተርጉሟል፡፡ ስለሆነም በባንኩ የተጀመረ የሐራጅ ሽያጭ እንቅስቃሴ እንዲቆም የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ፍ/ቤቱ የማየትና የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ስለሌለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 244/2//ሀ/ እና 244/2/ መሰረት መዝገቡ ተዘግቷል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን ላይ የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ጉዳዩ በይግባኝ መልስ ሰጭን ያስቀርባል ወይስ አያስቀርብም? የሚለውን ነጥብ አስመልክቶ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት የአሁን አመልካች የዕግድ ትዕዛዝ አሰጥቶ ስለነበረ የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ተረድቶ በህግ በተሰጠን ስልጣን መሰረት የሐራጅ ሽያጭ ተከናውኖ የተሸጠው ንብረት ስመ ሀብትነቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር አማካኝነት ወደ ገዥው ተዛውሯል፡፡ ካርታና ኘላንም ገዥው ወስዷል፡፡ የቀረው በዚህ ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት የንብረቱ ርክክብ ብቻ ስለሆነ የሐራጅ ሽያጭ እንቅስቃሴያቸው ይቁም በሚል የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ይነሳልን የሚል አቤቱታ በማቅረቡ የተነሣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ የዕግድ ትዕዛዝ ይነሳ አይነሳ በሚለው ነጥብ ላይ ከክርክር በኂላ ዋናውን ጉዳይ ተመልክቶ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ብይን በአገባቡ ስለሆነ የአሁን ተጠሪ የሆነውን መልስ ሰጭን የሚያስቀርብ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቶ የዕግድ ትዕዛዙም እንዲነሳ አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ዳኝነት በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በተመሳሳይ ጉዳይ በተባለው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 70824 ትርጉም የሰጠው የካቲት 27 ቀን 2004ዓ.ም ሲሆን ንብረቱ በሐራጅ የተሸጠው ደግሞ የካቲት 22 ቀን 2004ዓ.ም ስለሆነ የሰበር ሰሚው ችሎት ከሽያጩ በኂላ የሰጠው ትርጉም ወደ ኂላ ተመልሶ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም

በአዋጅ ቁጥር 25/84 መሰረት ከፈረሰው ድርጅት ገንዘብ የሚጠየቅ ባለመያዣ ገንዘብ ጠያቂ ወገን የሆነ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ከሌላው በተለየ ሁኔታ ክፍያ እንደሚፈፀምለት ተገልፆ እያለ በመያዣ የተያዘው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት የተሸጠ ነው የሚለውን በመያዝ ብቻ መወሰኑ አግባብነት የለውም ስለዚህ ማህበሩ በኪሣራ የፈረሰ በመሆኑ ማህበሩ ከፈረሰ ደግሞ ንብረት ገንዘብ አለን የሚሉ ወገኖች ከአዋጅ ቁጥር 25/84 አንፃር ፍ/ቤቶች አይተው የመወሰን ስልጣን እያላቸው ድርጅቱ ከመፍረሱ በፊት በወጋገን ባንክ በመያዥነት ንብረቱ ተይዟል በማለት በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በሰጠው ትርጉም

www.abyssinialaw.com

መሠረት መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመጥቀስ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ዳኝነት እንዲሻርለት መጠየቁን የሚያስረዳ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪም ለዚሁ የሰበር አቤቱታ በሰጡት መልስ ባጭሩ በግራ ቀኛችን መካከል ክርክሩ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም ከመጀመሩ በፊት የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 70824 ላይ ትርጉም የሰጠ ስለሆነ ትርጉሙ በእኛ ጉዳይ ላይም ተፈፃሚነት አለው፡፡ የንብረት የሐራጅ ሽያጭ ሥርዓት በሚገባ ተከናውኖና ተጠናቆ ለገዥው አዋርዲንግ ሌተር እስከሰጠንበት ድረስ አ/ማህበሩ የፈረሰ ስለመሆኑ አላሳወቀም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/84ም ቢሆን አመልካች የኪሣራ ጉዳይ ሥራ ሲያከናውን፤ የመክሰር ውሣኔን ለማሰጠት እና ለማሣወቅ አግባብነት ያላቸው የፍ/ብሔር እና የንግድ ሕጐች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በአዋጁ አንቀጽ 4 ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የመክሰር ሥርዓት በድርጅቱ ላይም ተፈፃሚ እንደሚሆን በአንቀጽ 40/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ የአሁን አመልካች የአ/ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ በተገኘበት ንብረቱ ከተሸጠ በኋላ አክሲዮን ማህበሩ ፈርሷል በማለት ክስ ከማቅረቡ በቀር በህጉ መሰረት ስለመፍረሱ አላሳወቁም በመሆኑም የሐራጅ ሽያጭ ሥርዓትን አሟልቶ በአዋጅ 97/90 እና 216/92 መሠረት በሕግ በተሰጠው ሥልጣን የሐራጁ ሽያጭ ማስፈፀሙ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያመለክትም በማለት የተከራከረበት ነው፡፡ የአሁን አመልካችም በሰጠው የመልስ መልስ ላይ  የአ/ማህበሩ ሥራ አስኪያጁ ድርጅቱ መፍረሱን የሚገልፅ ደብዳቤ ጽፏል፡፡ የማጣራት ሥራው እንዳለቀ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ሁሉ ቅድሚያ በመስጠት እንደምንከፍለው የአረጋገጥን ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል የሚለውንና በቅሬታው ላይ የገለፀውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት የሥር ፍ/ቤት ዳኝነቶች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ አለ ወይስ የለም? የሚለው በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡
ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው የጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ከአሁን ተጠሪ ላይ ገንዘብ በብድር መውሰዱን ይህን የብድር ገንዘብ በወሰደበት ጊዜ ለብድሩ ገንዘብ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 08 በአዲሱ አጠራር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 555 እና በባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ቁጥር ጂ አይ ኤስ 001895 የተመዘገበውን የማይንቀሣቀሰውን ንብረቱን በመያዣ ያስያዘ መሆኑንና በአበዳሪና ተበዳሪ መካከል በተደረገው የብድር ውል መሠረት ተበዳሪው የጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር የብድር ገንዘቡን ለመመለስ ያልቻለ የመሆኑ ጉዳይ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡
እንደዚሁም የአሁን ተጠሪ ከላይ የተመለከቱትን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ ለጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን ሰጥቶት የነበረውን የብድር ገንዘብ ሊመልስ ያልቻለ በመሆኑ ይህንኑ የብድር ገንዘብ ለማስመለስ ግራ ቀኙ ያደረጉትን የብድር ውል ስምምነት፣ ይህንኑ ስምምነት የሚገዛውን አዋጅ ቁጥር 97/90 አዋጅ ቁጥር 216/92 እንደተሻሻለ መሠረት በማድረግ በመያዣ የተያዘውን ንብረት አሸጦ ያበደረውን ገንዘብ ለመሰብሰብ በሥርዓቱ መሠረት የሐራጅ ሽያጭ ሥራ ባከናወነበት ጊዜ የአሁን አመልካች ይኸው የሐራጅ ሽያጭ ሊቆም ይገባል፤ ንብረቱ በአጣሪው እጅ ይገኛል በማለት የሐራጅ ሽያጩን ለማስቆም በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በዚህ በሰበር

www.abyssinialaw.com

ደረጃም ቢሆን የሐራጅ ሽያጩ የተጠናቀቀ ቢሆንም የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ክስ መመስረቱና አሁንም እየተከራከረ እንደሚገኝ ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡

ይሁን እንጂ በሕግ የተቋቋመ ባንክ በብድር የሰጠውን ገንዘብ ለማስመለስ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 መሠረት አስቀድሞ ለብድሩ አመላለስ ዋስትና ይሆኑ ዘንድ ከያዛቸው መያዣዎች መካከል አንዱን በመምረጥ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል፤ ለመሸጥ የተንቀሣቀሰበት የመያዣ ንብረት ከመሸጥ ድርጊቱ ይታቀብ፤ ይህም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልን በሚል በቀረበ ክስ መነሻ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 70824 በሆነው የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት " በመሠረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረት በሐራጅ መሸጥ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 የሕግ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ባንኩ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ.394- 449 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በአንቀጽ 6 በግልፅ አስፍሯል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 በተደረገው ማሻሻያም ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት የተቀበሉትን ንብረት የብድር እዳው እንዲከፈለው በተወሰነው ጊዜ ሣይከፈል ከቀረ ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመያዣ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዥው ለማዛወር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከአዋጁ ድንጋጌዎችም መረዳት የሚቻለው በአበዳሪው ባንክ በዋስትና የተያዘውን ንብረት የብድር ገንዘቡ ካልተመለሰለት ያለማንም ጣልቃ ገብነት አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን በመከተል በሐራጅ ሸጦ ለእዳው ክፍያ ማዋል እንደሚችልና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ሕጉን ባለመከተል የፈፀመው ስህተት ቢኖር በዚህም ባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለእዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የአዋጆቹ ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘትም ሲታይ የሕጉቹ ዓይነተኛ ዓላማ ባንኮች የሚሰጧቸውን ብድሮች በተቀላጠፈ አኳኋን ለመሰብሰብ እንዲችሉ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይህ ስለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በመግቢያው ላይ በግልጽ አስቀምጧል፡፡" የሚለውን ትርጉም በመስጠት አበዳሪ ባንክ በብድር ውሉ መሠረት ያበደረው የብድር ገንዘብ ባልተመለሰለት ጊዜ ይህንኑ የብድር ገንዘብ ለማስመለስ አስቀድሞ የያዘውን የመያዣ ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 ፣ 98/90 እና 216/98 በሚያዙት መሠረት በፎርክሎዠር በእራሱ የሐራጅ ሽያጭ ሥራ የማከናወን ሙሉ ሥልጣን እንዳለው እና ማንም ወገን የበኩሉን ምክንያት በመስጠትና በፍ/ቤት ዳኝነት አማካኝነት የሐራጅ ሽያጩን የማስቆም መብት እንደሌለው ይህ መሰል መብትም በፍ/ቤት ዘንድ ከቀረበ የሚቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የመያዣ ውሉንና ከላይ ከተጠቀሱት አዋጆች ዓላማ ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ ፍ/ቤት የሐራጅ ሽያጩን ለማስቆም የሚያስችል ስልጣን አይኖረውም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ የሐራጅ ሽያጩ ሊቆም ይገባል የተባለበት ምክንያት ከሰበር መ/ቁ. 70824 የተለየ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.224 መሠረት የአሁን አመልካች ከጠየቀው ዳኝነት አንፃር ይህ ከላይ የተጠቀሰው የሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም ቀጥተኛ ተፈፃሚት እንዳለው ተገንዝበናል፡፡

ለጠየቀው ዳኝነት በምክንያትነት ከጠቀሰው ክርክርም አኳያ እንዳየው ቢሆን የአሁን አመልካች በቀረበው ክርክር ተጠሪ መያዣ በመያዝ የብድር ገንዘብ ጠያቂ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/84 ከፈረሰው ድርጅት ገንዘብ ከሚጠይቁ ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በተለዩ ሁኔታ ታይቶ ተገቢው ክፍያ እንዲፈጽምለት ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ከዚህ ከፈረሰው ንብረት ገንዘብ አለን ከሚሉ ሌሎች ገንዘብ ከሚጠይቁ ወገኖች አንፃ አዋጅ ቁጥር 25/84 መሠረት ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው የመወሰን ስልጣን እያላቸው ድርጅቱ ከመፍረሱ በፊት በወጋገን ባንክ ንብረቱ በመያዣነት ተይዟል በማለት አዋጅ ቁጥር 97/90 እና ሰበር ሰሚው ችሎት አስቀድሞ በሰጠው ትርጉም መሠረት ብቻ ታይቶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ በማለት የሚከራከር በመሆኑ ይህ የአመልካች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 97/90 98/90 እና 216/92 የተመለከቱትን የህጐችን መሰረት ሃሣብ የሚደግፍ እንጂ በእነዚህ አዋጆች መሠረት በአበዳሪ ባንክ በተጠሪ አማካኝነት የተከናወነን የሐራጅ ሽያጭ ለማስቆምም ሆነ ለማስፈረስ የሚያስችል የህግ መሠረት ያለው ክርክር አይደለም፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/84 እና ከላይ በተመለከተቱ ከባንክ የብድር ማስፈፀሚያ አዋጆች መካከል ቅራኔ የለም እንጂ በህጐች መካከል ቀራኔ አለ እንኳ ቢባል በህጐች አተረጓጉም ደንቦች መሠረት ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የትኛው የህግ ክፍል ነው ለሚለወም ሕግ አዋጆች ከወጡበት ዘመን አንፃር ሲታይ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለውና ጉዳበዩን የሚገዛው የባንክ ብድር ማስፈፀሚያ የሆኑት አዋጆች በመሆናቸው ከላይ የተጠቀሰውን ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ የተሰጠውን ትርጉም አፈፃፀም የሚያስለውጥ የክርክር ነጥበ አይደለም፡፡
ምናልባትም የዚህ ክርክር እንደምታዊ ይዘቱና ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣው የመያዣ ንብረት በእኛ አማካኝነት ቢሸጥ ኖሮ ከፍተኛ ዋጋ ያወጣ ነበር የሚል ከሆነ ባንኩ ባደረገው የሐራጅ አሻሻጥ ሂደት በተፈፀመ ስህተት ምክንያት እንደ አባባሉ ሆኖ ከተገኘ የሥር ፍ/ቤቶች እንደሰጡትም ሆነ በሰበር ሰሚው ችሎት እንደተሰጠው ትርጉም በዚህ ረገድ የደረሰ ጉዳት ካለ በአዋጆች መሠረት ዳኝነት ከሚጠይቅ በቀር እንደቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የሐራጅ ሽያጩን ለማስቆምም ሆነ ማስፈረስ የሚያስችል መብት ሰጪ የክርክር ነጥብ ሆኖ አይገኝም፡፡

በመጨረሻም በአዋጅ ቁጥር 454/97 እንደተመለከተው ከአምስት ያላነሱ ዳኞች የተሰየሙበት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም ለተመሣሣይ ጉዳዮች ተፈፃሚነት እንዳለውና በየትኛውም ደረጃ ለሚገኝ የዳኝነት አካል የአስገዳጅነት ባህሪይ አለው በማለት የተቀመጠው የሕግ አነጋገር ተፈፃሚነቱ በተመሣሣይ ጉዳይ በሌሎች ወገኖች ክርክር በተፈጠረበት ጊዜ ይህንኑ አስመልክቶ በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ትርጉም አለ ወይስ የለም ከሚለው ነጥብ አንፃር ታይቶ ተፈፃሚ የሚሆን እንጂ ትርጉም የተሰጠበትንና የክርክር ምክንያት የሆነው ነገር መቼ ተፈፀመ ተደረገ ከሚለው የጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር እየታየ የሚፈፀም ባለመሆኑ የአሁን አመልካች ይፍረስ የተባለው ሐራጅ የተደረገው የሰበር ሰሚው ችሎት ትርጉም ከመስጠቱ ከአምስት ቀናት በፊት ስለሆነና የሰበር ሰሚው ትርጉም ወደ ኃላ ሂዶ ሊሰራ አይገባም በማለት ያቀረበው የአዋጅ ቁጥር 454/97 ትክክለኛ አፈፃፀም የተከተለ አይደለም፡፡
በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በፍ/ቤት አማካኝነት እንዲወሰንለት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተቀብለው የማየትና የመወሰን ስልጣን የላቸውም፤ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በማለት የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለመገኘታችን የሚከተለውን ወሣኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 192611 በቀን 30/11/2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ እና ይህንኑ ብይን በማጸናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 126468 ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሁሉ ፀንቷል፡፡
2. በህግ አግባብ በተደረገ የብድር ውል እና በህግ አግባብ በተቋቋመ የመያዣ ውል መነሻ አበዳሪ የአሁን ተጠሪ ወጋገን ባንክ በብድር የሰጠው የብድር ገንዘብ አለመመለሱን አረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 216/92 እንደተሻሻለው በመያዣ የያዘውን ንብረት በሐራጅ ሸጦ እዳውን የመሰብሰብ ተግባር ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲያከናውን በሕግ የተሰጠው ስልጣን በመሆኑ በዚህ አኳኃን የሐራጅ ሽያጩ በፍ/ቤት ይፍረስ ተብሎ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማየትም ሆነ ለመወሰን ስልጣን የላቸውም ተብሎ መወሰኑ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ የክርክር ደረጃ ያለውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 82427

ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ዩኒስ ቡራሌ ሲጋል የራይስ ጫት ላኪዎች ማህበር - ጠበቃ ነፃነት ጌታሁን ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ አብዲ አልሚ መሐመድ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተጠሪ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት በማህበሩ ደንብ መሰረት ተነስቷል ወይስ አልተነሳም የሚለውን ጭብጥ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሽንሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ማህበሩ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት አባላት ያሉትና በ1999 ዓ.ም. የተቋቋመ ነው፡፡ ተከሳሽ የማህበሩ ሊቀመንበር እንዲሆን በማህበሩ አባላት ተመርጦ ለሶስት ዓመት ማህበሩን በሊቀመንበርነት መርቷል፡፡ ተከሳሽ የማህበሩን ንብረትና ሰነድ ለግል ጥቅም ያዋለ በመሆኑ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት እንዲነሳ የማህበሩ አባላት ግንቦት 13 ቀን 2003 ዓ.ም. ባደረጉት ስብሰባ ወስነዋል፡፡ ስለዚህ የማህበሩን ዶክመንትና ንብረት እንዲያስረክብ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ አንድ የማህበሩ አባል ከአባልነት የሚወገድበት ሥርዓት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ተደንግጓል፡፡ የማህበሩ አባላት በሙሉ ድምፅ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆኜ እንድሰራ መርጠውኛል፡፡ ስለዚህ ከሊቀመንበርነት የምወገድበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤት የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11(2) የማህበሩ ሊቀመንበር ሥራውን በአግባቡ ለመፈፀም ካልቻለ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሊሰናበት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከሣሽ ከማህበሩ አባላት መካከል አንድመቶ ሃያ የሚሆኑ አባላት ተከሣሽ ከሊቀመንበርነቱ እንዲወገድ ውሣኔ የሰጡበት (የወሰኑ) መሆኑን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ አንዳንዶቹ አባላትም ፍርድ ቤት በመቅረብ ተከሣሽ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት የተነሣ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ተከሣሽ በማህበሩ አባላት ውሣኔና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ከማህበሩ ሊቀመንበርነት የተነሣ በመሆኑ ሰነዶችንና ሥልጣኑን አዲስ ለተመረጠው ሊቀመንበር ያስረክብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ መካሄዱንና

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ከሊቀመንበርነት መነሣቱን የሚያሣይ የሰነድ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ከማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል ሰባት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ፍርድ ቤት በመቅረብ ይህንን አረጋግጠዋል በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሸንሌ ዞን ዐቃቤ ሕግ ለሰበር ችሎቱ ደብዳቤ የፃፈ መሆኑን በመጥቀስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፡፡

አመልካች ተጠሪ በማህበሩ አባላት የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣቱ በማህበሩ አባላት ተረጋግጦ ከሊቀመንበርነቱ እንዲወገድ የማህበሩ አባላት የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ ወስነዋል፡፡ ይህም ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዩን አመልካች በሌለበት እንዲታይ ሲያደርግ ህጉን ተከትሎ መወሰን ሲገባው፣ አመልካች ቀርቦ መልስ አለመስጠቱን እንደምክንያት በመግለጽ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ የሻረው፣ አመልካች መጥሪያ ከደረሰው በኋላ ቀርቦ ባለመከራከሩና ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ፣ የሸንሌ ዞን ዐቃቤ ሕግ የፃፈውን ደብዳቤ በማገናዘብና ተጠሪ ከሊቀመንበርነት ተወግዷል የተባለው በአንድ የማህበሩ አነሳሽነትና በጥቂት የማህበሩ አባላት የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብስበን አዲስ ሊቀመንበር ሹመናል በማለት ማህበሩ ሣይጠራ እንደተጠራ አድርገው ባቀረቡት ማስረጃ መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ስለሆነ ተገቢነት የለውም፡፡

አመልካች ታህሣሥ 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ የማህበሩ ሊቀመንበር ከመሆን የተነሳ በመሆኑ ሰነዶችንና የማህበሩን ንብረቶች እንዲያስረክብ በማለት በሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሣኔ የሻረው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ የሻረው አመልካች በሰበር ችሎቱ ክርክሩን እንዲያቀርብ መጥሪያ ከደረሰው በኋላ ባለመቅረቡና ጉዳዩ በሌለበት የታየ በመሆኑ ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ /ተጠሪ/ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን መሰጠቱ ፍርዱ ለከሳሽ ወይም /በሰበር ደረጃ/ ለአመልካች በሚጠቅም መንገድ የመወሰኑን ሁኔታ በአስገዳጅነት የሚያስከትል እንዳልሆነ ከፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 70/ሀ/ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አመልካች ያቀረበውን የሰነድ ማስረጃዎችና የማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሜቴ አባላት የምስክርነት ቃል በመስማትና ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የሰጠውንና የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት የተፈፀሙ ስህተቶችን የማረም ስልጣን ባለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኩል ተመርምሮ የፀና መሆኑን ከውሣኔው ተረድተናል፡፡

የማህበሩ አባላት ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በማድረግ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11/2/ በሚደነግገው መሰረት ተጠሪ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት እንዲነሳ የወሰኑ መሆናቸውንና ለማህበሩም ሌላ ሊቀመንበር የሾሙ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የሽነሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ መዝኖ ውሣኔ የመስጠት ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ሀሰተኛ መሆኑን የሸንሌ ዞን ዐቃቤ ህግ ደብዳቤ ጽፎልኛል በማለት የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

በመሰረቱ ዐቃቤ ሕግ የጻፈው ደብዳቤ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመርመር በፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ በላይ ተአማኒነት እና ክብደት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ዐቃቤ ህግ የጻፈው ደብዳቤ አከራካሪው ጭብጥ ላይ ተጨማሪ ማጣራት የሚያስፈልገው መሆኑን የሚጠቁም ነው ከተባለ ጉዳዩ ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በኩል እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መመለስ ነበረበት፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በሸንሌ ዞን ዐቃቤ ሕግ በኩል የተጻፈውን ደብዳቤ ራሱ በመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ዕውነታ ውድቅ በማድረግ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

# የንግድ ህግ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.76394
ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ
ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ወርቁ ወ/ፃድቅ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የአቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወራሾች

1.ወ/ሮ ወዴ ምዕራቡሽ
2.ወ/ሪት ትርሲት ወ/ሥላሴ
3.ወ/ሪት እህቴ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ
4.ወ/ሪት ገነት ተስፋዬ ወ/ሥላሴ
5.አቶ ብሩክ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ
6.አቶ ብርሃኑ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ
7.አቶ ናስፍ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ

} አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ከሳሽ ሚያዚያ 28 ቀን 2002 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ከ1ኛ ተከሳሽ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተከሳሾች አውራሽ ጋር የሽርክና ውል የነበረን ሲሆን በውላችን መሰረትም ከመካከላችን አንደኛው ከሞተ መብቱ ለወራሽ እንደማይተላለፍ የተስማማን ሲሆን ተከሳሾች አቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ከሞቱ በኂላ በሽርክና ውል መነሻ የተቋቋመውን ድርጅት ተከራይተው የሚሰሩትን ሰዎች (ተከራዮች)

በማስለቀቅ ለራሳቸው ለመያዝ በሚያደርጉት ጥረት መግባባት ያልቻልን ስለሆነ በሽርክና ውሉ መሰረት ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ እንዲታዘዝ ሆኖ በሽምግልና እንዲታይ የማይስማሙ ከሆነ ደግሞ የሽርክና ውሉ ፈርሶ ድርሻችን ተለይቶ እንዲወሰን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መቃወሚያውም ከዚህ በፊት ከሳሽ በዚሁ ጉዳይ ላይ ክስ አቅርበው የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 40977 ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም ሲል መዝገቡን የዘጋው ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/5 መሰረት በዚያው ጉዳይ እንደገና ክስ ማቅረብ አይችሉም የሚል ሲሆን በአማራጭ ባቀረቡት መልስ ደግሞ በመካከላችን የሽርክና ውል የለም ብለው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 40977 ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩ ከመሆናቸውም ሌላ የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ አሁን ክስ ከቀረበበት ጉዳይ የተለየ

www.abyssinialaw.com

በመሆኑ ተከሳሾች የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/5ን ጠቅሰው ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው ፍርድ ከሳሽ የሽርክናው ማህበር ሰነዶች ናቸው በሚል ያቀረቡአቸው ውሎች ብቻ በመሆናቸውና የሽርክና ማህበር ነው የሚሉትም በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ስም የሌለው፣ በንግድ መዝገብ ያልተመዘገበ እና የመመስረቻ ጽሁፍ የሌለው በመሆኑ በከሳሽና በ1ኛ ተከሳሽ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ተከሳሾች አውራሽ መካከል የሽርክና ማህበር ውል የለም፡፡ የሽርክና ማህበር ባልተቋቋመበት ደግሞ እንዲፈርስ ጥያቄ ሊቀርብ ስለማይችል ከሳሽ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2) መሰረት ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍርድ ቤትም የይግባኝ ባዩን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን በማሰናበቱ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ብይን/ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የቅሬታ ነጥቡም ሲጠቃለል፡- ከሟች አቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ጋር ለመኪና ጋራዥ ሥራ የሚሆን ቦታ የአፈር ኪራይ እየከፈልን በህብረት ለመስራት ህዳር 17 ቀን 1967 ዓ.ም. የህብረት ስምምነት ውል ፈጽመን እየሰራን እያለ ቦታው ለውኃ ማጠራቀሚያ መንግስት ስለወሰደው በምትኩ በቀድሞ ከፍተኛ 23 በአሁን አጠራር ቂርቆስ ክ/ከ/ቀበሌ 08/09 ቦታ ተሰጥቶን ቁጥሩ 826 የሆነ ቤት ሰርተን የመጀመሪያውን ውል የካቲት 27 ቀን 1979 በተጻፈ አዲስ ውል በመተካት ስንዋዋል የንግድ ፈቃዱ በሟች ስም እንዲሆንና ተሻራኪዎቹ የጋራዡን ሥራ በአንድ መልክ እንድናስተዳድር፣ ፈቃዱ በስሙ የሆነው ተሻራኪ ቢሞት በህይወት

ባለው ተሻራኪ ስም እንዲሆንና በውርስ እንደማይተላለፍ በማድረግ ከ38 ዓመት በላይ የጋራ ባለሀብት በመሆን የቆየን ሆኖ ሳለና ክሱን ለማስረዳት በቂ ሰነዶችን አቅርቤ እያለሁ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረብኩትን ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 33(2) መሰረት ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡
ተጠሪዎች በሰጡት መልስ፡- አመልካች እና ሟች ተስፋዬ ወ/ሥላሴ የጋራ የሆነ ቤትም ሆነ ቦታ ኖሮአቸው አያውቁም፣ አመልካች የሽርክና ማህበር አለ የሚሉት በንግድ ህጉ መሰረት ያልተመዘገበ፣ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ የሌለው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉት ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ክስ ባቀረቡት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት የላቸውም ተብሎ ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33(2) መሰረት ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ክስ ሲያቀርቡ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 223 መሰረት በማስረጃነት የተለያዩ ውሎችንና ሌሎች ሰነዶችን ማቅረባቸውን የመ/ደ/ፍርድ ቤት ብይን ያመለክታል፡፡ የመጀመሪያው የውል ሰነድ ህዳር 17 ቀን በ1964 ዓ/ም የአሁኑ አመልካች፣ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ እና መንግሥቱ ጋሼ የተባሉ ሰው ሆነው አቶ ነጋሽ ወሰኔ ከተባሉ ሰው ለመኪና ጋራዥ የሚሆን ቦታ ወስደው በ1960 ዓ/ም ለመኪና ማቆሚያ የሚሆን ቤት መሥራታቸውን በመግለጽ እነ ካሳሁን ቦሰና የተባሉ ሌሎች 4 ሰዎች በደባልነት ገብተው የጋቢናና የባሊስትራ ሥራ እንዲሰሩ ስምምነት ያደረጉበት ነው፡፡ እንዲሁም በውሉ የተካተቱት ሁሉም ሰዎች በ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ ስም የንግድ ፈቃድ ወጥቶ የመንግስት ግብርም ሆነ ለባለይዞታው የሚከፈለውን የቦታ ኪራይ እያዋጡ ለመክፈል መስማማታቸውን ሰነዱ ይገልጻል፡፡ ከዚህ በኋላም የካቲት 27 ቀን 1979 ዓ/ም የአሁኑ አመልካች፣ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች

www.abyssinialaw.com

አውራሽና ወ/ሮ አሥራት መንግስቴ ሆነው ቀደም ሲል ያደረጉትን ውል በማሻሻል ‹‹ የንግድ የጋራ ሽርክና ውል ›› በሚል ባደረጉት ስምምነት ቀድሞ ጋራዡ የተቋቋመበትን ቦታ ለውኃ ማጠራቀሚያ እንዲሆን በመፈለጉ በምትኩ በከፍተኛ 23 ቀበሌ 09 ክልል ውስጥ ቦታ ተሰጥቶ የጋራዡን ስራ መቀጠላቸውን በመጥቀስ ማንኛውም ስራ ተሻራኪዎቹ በአንድ መልክ ሆነው ለማስተዳደር፣ የንግድ ፈቃዱ በስሙ የወጣ ሰው በሞት ቢለይ በህይወት ባሉ ተሻራኪዎች እንዲዛወር፣ ከጋራዡ ሥራ የሚገኘውንም ገቢ እያንዳንዱ ተዋዋይ በሥራው ድርሻው ተጠቃሚ እንዲሆን ከመስማማታቸውም በላይ ሌሎች መብቶችና ግዴታዎችንም አካትተዋል፡፡ ከተጠቀሱት ውሎች በተጨማሪ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የተለያዩ የመንግስት አካላት የጻፉአቸው ደብዳቤዎችን አመልካች በማስረጃነት ለስር ፍርድ ቤት ስለማቅረባቸው በክርክራቸው ገልጸዋል፡፡ በዚህ መልኩ የቀረበውን ክስ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ለማድረግ የጠቀሰውም በንግድ ህጉ መሰረት የተቋቋመ ማህበር የለም በሚል ነው፡፡ በንግድ ህጋችን ቁጥር 212(1) መሰረት የሚታወቁ የንግድ ማህበሮች 6 ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል አንዱ በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር 1 በፊደል (ለ) ስር የተጠቀሰው የእሽሙር ማህበር ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡ የእሽሙር ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሌለው እንዲሁም በጽሁፍ መረጋገጥና በሌሎች ንግድ ማህበሮች የተደነገጉት የማስታወቅና የማስመዝገብ ሥርዓቶች እንደማይፈጸሙበት በንግድ ህጉ አንቀጽ 272 ተጠቅሷል፡፡ ሸሪኮቹም እንደ ተራ ተዋዋይ ወገኖች የሚታዩ ናቸው፡፡ ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ ምክንያትም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርገውም በሸሪኮቹ ስም ነው፡፡ አመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ ያደረጉት የሽርክና ውል ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የእሽሙር ማህበር ባህርያት ጋር የሚመሳሰል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ከእሽሙር ማህበር ውጪ ያሉ ሌሎች በንግድ ህጉ የሚታወቁ ማህበራት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ነጥቦች በመጥቀስ በንግድ ህጉ መሰረት የተቋቋመ ማህበር ባለመኖሩ እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ የለም ሲሉ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/33(2)ን ጠቅሰው የአመልካችን ክስ በብይን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/53795 በቀን 08/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን እንዲሁም የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/116705 በቀን 9/05/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. በአመልካችና የ1ኛተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ መካከል የተቋቋመው የእሽሙር ማህበር በመሆኑ አመልካች ባላቸው የሽርክና ስምምነት መሰረት ክስ የማቅረብ መብት አላቸው ብለናል፡፡ ስለሆነም ፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ወደ ፍሬ ነገሩ በመግባት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን አግባብ ባለው ህግ መሰረት የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/341(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ 80599

ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጀሽዋ ኤነድ ካሌብ ኃ/የተ/የግል/ማህበር ጠበቃ አቶ ሙሉጌተ ገብሩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እንቁጣጣሽ አሰፋ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ ኃ/የተ/የግል ማህበር ስራውን የሚያከናውንበት የንግድ ቦታ መሆኑ በመታወቁ ምክንያት ብቻ በዚህ ቦታ ላይ የኪራይ መብትን እንዳቋቋመ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም? በዚህ የንግድ ቦታ ላይ የኪራይ መብት የለውም፤ ከተባለ ማህበሩ ፈርሶ ሂሳብ ተጣርቶ እስኪታወቅ ድረስ በዚሁ የንግድ ቦታ ላይ የኪራይ መብት ያለው ወገን በመብቱ ሊገለገልበት አይችልም ለማለት ከህግ የመነጨ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚሉትን አከራካሪ ነጥቦች ከግራ ቀኙ ክርክርና ስለዚሁ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ ከኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት በኪራይ ያገኘሁትን በቂ/ክ/ከ/ቁ/15/16 ከአከራይ ድርጅት ፊት ለፊት የሚገኘውን የመናፈሻ ቦታ የአሁን አመልካች የሆነው ኃ/የተ/የግል ማህበር ያለ አግባብ ይዞ ስለሚገኝ ለቆ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ሲሆን፤ የአሁን አመልካችም ለዚህ ለቀረበበት ክስ ማህበሩ ሳይፈርስ ድርጅቱ ያለበትን ቤትና ቦታ ይለቀቅልኝ ማለት አይቻልም፤ ከሳሽ የኪራይ ውሉን ከመፈረም በቀር በቦታው ላይ አንዳችም ነገር ኢንቨስት አላደረጉም፡፡ የድርጅቱን የቤት ግንባታና የውስጥ ቁሳቁሶች ያሟሉት ከሳሽ ሳይሆኑ የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ወ/ሮ ጃኪ አሰፋ ስለሆኑ ክሱን ያቀረቡት ያለአግባብ ነው በማለት መልስ ሰጥተውበታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ የአሁን ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን የመናፈሻ ቦታ በኪራይ ያገኙት ስለመሆኑ አልተካደም ይህንኑም ከሳሽ አባል ለሆኑበት ማህበር በአይነት መዋጮ አላደረጉም ተከሳሽ በዚሁ ክርክር ባስነሳው የመናፈሻ ቦታ ወጭ አድርጎ የማልማት ሥራ ሠርቶ ከሆነ ይህንኑ ወጭ በህግ አግባብ ከሚጠይቁ በቀር የመናፈሻ ቦታው ባለመብት ሊያደርገው አይችልም በማለት ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ፣ ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ማህበር አቋቁመው ማህበሩ በዚህ ቦታ ላይ ሥራውን እንዲሰራ ፈቅደዋል፡፡

ይህንኑ መናፈሻ ቦታ የሚፈልጉት ከሆነ መልሰው የግል ለማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንብ ወይም በመመሥረቻ ፅሑፍ ላይ እንዲካተት አላደረጉም። እንደ ክሳቸው ማህበሩ ሥራውን የሚያከናውንበትን የመናፈሻ ቦታ ያስረክብ ቢባል የማህበሩን ህልውና የሚነካ፤ ጥያቄው ከማህበሩ ትርፍና ኪሣራ ጋር የተያያዘ በመሆኑና የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚጠይቅ በመሆኑ የእያንዳንዱ ማህበርተኛ ትርፍና ዕዳ ተለየቶ ከመታወቁ በፊት የከሳሽ የኪራይ መብት ይከበር፤ ማህበሩ ለከሳሽ ይልቀቅ በሚል ሊወሰን አይገባም። የሚለውን ምክንያት በመስጠት በሥር ፍ/ቤት ከሳሽ ማህበሩ ከቤትና ከቦታው እንዲለቅ ይደረግልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ውድቅ ነው በማለት የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል።

በሁለተኛ ደረጃ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ሰሚውን የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ወሣኔን ያፀና የመጨረሻ ፍርድ በመስጠቱ የተነሣ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ እንደቻለ የጉዳዩ አመጣጥ አስረጅ ነው።

በዚህ ሰበር ደረጃም በአመልካች የሰበር አቤቱታ መነሻ ክርክር ባስነሣው ቦታ ላይ ሥራውን ሲያከናውን የቆየው ማህበር ፈርሶ ሂሣቡ እንዲጣራ ተወስኖ በጉዳዩም ላይ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶበታል። በዚህም መሠረት የማህበሩ ንብረት ተጣርቶ ሳይጠናቀቅ ማህበሩ አከራካሪውን የይዞታ ቦታ ለአሁን ተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚል በተያዘው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል።

እንግዲህ ጉዳዩ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ይህንኑ ጉዳይ እንደሚከተለው መርምረናል።

ከላይ ባጭር ባጭሩ እንደተጠቀሰውና በየደረጃው ባሉት የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ላይ እንደተመለከተው የዚሁ ክርክር ያስነሣው የመናፈሻ ቦታ ከኪራይ ውል በመነጨ የባለይዞታነት መብት ያላቸው የአሁን ተጠሪ ስለመሆናቸው የአሁን አመልካች ክዶ ያቀረበው ክርክር የለም። በመከላከያ መልሱ ላይ ካቀረባቸው ክርክሮች አንዱ ማህበሩ ሳይፈርስ ድርጅቱ ያለበትን ቤትና ቦታ ለቆ ለተከራይ እንዲያስረክብ ሊገደድ አይችልም የሚል ነው። ማህበሩ ከመፍረሱ በፊት እንዳባባሉ የመናፈሻ ቦታውን እንዲያስረክብ ሳለመገደድ ከሕግ የመነጨ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ድርጅት ወይም ማህበር በተከራይ ክስ አቅራቢነት በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ተወስኖ በዚህ ውሣኔ ላይ ከታች ወደ ላይ ባለው የክርክር መስመር እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት ደረሶ ይፍረስ በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በሚል የመጨረሻ ዳኝነት ያገኘ ጉዳይ ስለመሆኑ የአሁን አመልካች እራሱ ባቀረበው ክርክር ያረጋገጠው ጉዳይ ነው። ስለሆነም የመናፈሻ ቦታውን እንዳስረክብ ልገደድ አይገባም ለሚለው ክርክሩ መነሻ አድርጎ ከቀረባቸው ምክንያት አንዱ የሆነው በቅደመ ሁኔታነት ያቀረበው የማህበር መፍረስ ጉዳይ እንደ ክርክሩ በፍርድ ዕልባት ያገኘ ጉዳይ እንደመሆኑ ይህ የመከራከሪያ ነጥብ ማህበሩ ስራውን ሲያከናውን የነበረበትን የይዞታ ቦታ ለቆ ለማስረከብ እንዳይገደድ ለማድረግ የሚያስችል ሳይሆን ቀሪ መሆኑን ስለሚያመለክት ጭብጥ ለመመስረት በፍሬ ነገር መሰረትነቱ ያከተመ የክርክር ነጥብ ነው። ስለሆነም የማህበሩ ቅድሚያ መፍረስና አለመፍረስ ከሳሽ ለጠየቁት ዳኝነት አግባብነት ያለው ጉዳይ አይደለም።

ማህበሩም በፍርድ ከፈረሰ በኋላ የማህበሩ ሂሣብ በአሁኑ ሰአት አልተጠናቀቀም የሚባል ከሆነም የማህበሩ ሂሣብ ስራ የመጠናቀቁና ያለመጠናቀቁ ጉዳይ አሁን ግራ ቀኙን ካከራከረው ጉዳይ ጋር የሚያገናኘው ምክንያት

www.abyssinialaw.com

አይደለም፡፡ የሂሣብ ስራው ተጠናቆ ውጤቱ ቢታወቅ ይህንኑ ከኪራይ ውል የመነጨውን የአሁን ተጠሪን መብት ቀሪ የሚያደርግበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የሂሣብ ማጣራት ስራ የሚያስከትለው ውጤት እና የዚህ ክርክር ጉዳይ ውጤት በየራሳቸው ችለው የቆሙ እንጂ የመጀመሪያው የክርክር አይነት ለኋለኛው እንደቅድመ ሁኔታ ወይም እንደ መያዣ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም፡፡

ሁለተኛ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት አቅርቦ የነበረው በዚሁ የመናፈሻ ቦታ ላይ ለማስፋፋት ሥራ ከፍተኛ ወጭ አድርገው ያከናወኑት የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ሌላዋ የማህበሩ አባል ናቸው እንጂ የድርጅቱ ተከራይ አይደሉም የሚለው ሌላው የመከራከሪያ ነጥብ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው ይህ አይነት ወጭ ተደርጎ ከሆነ እራሱ በቻለ እኳኋን መብቱን የሚጠበቅበት በመሆኑና በሂሣብ ማጣራት ጉዳይም ተካቶ ሊወሰን የሚገባው እንጂ ለዚህ ግራ ቀኙን ካከራከረው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሆኖ አይገኝም፡፡

ከዚህም በቀር ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው እንደመሆኑ መጠን የዚህ ማህበር የሚጨበጥና የማይጨበጥ የሚንቀሣቀስና የማይንቀሣቀስ ንብረቶችን መብቶች ምን ምን እንደሆነ በማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍና በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰኑ እንጂ ማህበሩ ሥራውን የሚያከናውንበት የመናፈሻ ቦታ ላይ ከኪራይ የመነጨ መብት የሌለው መሆኑ እየታወቀ ማህበሩ ሥራውን የሚያከናውንበት ሌላ ቦታ መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይህ የሥራ ቦታ ከሌለ ማህበሩ ህልውና አለው ማለት አይቻልም የሚለውን ምክንያት በመያዝ ብቻ የማህበሩን መብትና ጥቅም ማቋቋም አይቻልም፡፡

በማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ ማህበሩ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የንግድ ሥራውን የሚያከናውንበትን የንግድ ቦታ የመከራየት መብትንም ሁሉ አካቶ ላለመያዙ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይልቁንም ከኪራይ መብት የመነጨ መብት ያላቸው የአሁን ተጠሪ ስለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤቶች በማስረጃ ያረጋጡት የፍሬ ነገር ጉዳይም ከመሆኑ በላይ አመልካች እራሱ የካደው አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማህበሩ የማህበሩ የስራ ቦታ በነበረው የመናፈሻ ቦታ ላይ ማህበሩ እንደማህበር ወይም የማህበሩ አባል ያወጣው ወጭ ካለ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ ክርክር ያስነሳው መናፈሻ ቦታ ከኪራይ ውል የተነሣ ህጋዊ ባለይዞታ የአሁን ተጠሪ እንጂ የአሁን አመልካች አለመሆኑን አረጋግጦ የአሁን አመልካች ለቆ ለአሁን ተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት በሰጠው መጨረሻ ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 71325 መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. በዚሁ ክርክር ባስነሳው የመናፈሻ ቦታ ላይ ማህበሩ ወይም በሌላ የማህበሩ አባል አማካኝነት በማስፋፋት ረገድ የወጣ ወጭ ካለ ይህንኑ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ የመናፈሻ ቦታውን የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ ለቆ ያስረክብ መባሉ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

www.abyssinialaw.com

4. በዚህ የሰበር ጉዳይ ክርክር እስከሚጠናቀቅ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 170065 በቀን 22/06/2003 ዓ.ም. እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 71325 መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ መሰረት አፈፃፀም እንዳይቀጥል በሚል ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ ለተላለፈላቸው ክፍሎች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

# ቤተሰብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.74734

ህዳር 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትዕግስት ሽባባው - ጠበቃቸው አቶ ኃ/ማርያም ኢትቻ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. እህት አለማው ወርቁ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ አበቡ ወርቁ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን የሰበር አመልካችም 3ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ክሱም ሟች አባታችን ያደረጉት ኑዛዜ እኛን ህጋዊ ወራሾች የነቀለን ከመሆኑም ሌላ ጉድለት ያለበት ስለሆነ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

3ኛ ተከሳሽም በሰጡት መልስ ሟች አባታችን ባደረጉት ኑዛዜ ያላቸውን ንብረት ለከሳሾችም ሆነ ለተከሳሾች የተናዘዙ ስለሆነ ኑዛዜው ከሳሾችን የሚነቅል ካለመሆኑም በላይ ጉድለት የሌለበት በመሆኑ ሊሻር አይገባም ብለዋል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም ክርክሩ የውርስ ሀብት የሚመለከት በመሆኑ ክሱ ከመቅረቡ በፊት የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ ድርሻ ሳይታወቅ ከሳሾች ባለመብት ሆነው ክስ ሊያቀርቡ ስለማይገባ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የስር ከሳሾችም ይግባኝ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ መልስ ሰጪዋ በወረዳ ፍርድ ቤት ደረጃ በሰጡት መልስ ውርስ ማጣራትን በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ከሳሾች በመጀመሪያ የሚደርሳቸውን የውርስ ንብረት ማጣራት ስለሚገባቸው ይሔው ሁኔታ በቅድሚያ ሳይፈጸም ክስ ሊያቀርቡ አይገባም ያለው ተቀባይነት የለውም፣ የግራ ቀኙን ወገን የሚያከራክረው በ23/07/1996 ዓ.ም. በጽሁፍ ተደርጓል የተባለው ኑዛዜም በህገ መሰረት በሰው ማስረጃዎች ተሟልቶ ያልቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ በማድረግ 1ኛ እና 2ኛ መልስ ሰጪዎች የአቶ ወርቁ ደስታ ወራሾች ስለመሆናቸው የቀረበውን የወራሽነት ማስረጃ ይግባኝ ባዮች ክደው ያልተከራከሩ በመሆኑ ይግባኝ ባዮችና 1ኛ እና 2ኛ መልስ ሰጪዎች በፍ/ህ/ቁ/842

www.abyssinialaw.com

መሰረት የሟች አባታቸውን ሀብትና ንብረት እኩል የመውረስ መብት አላቸው በሚል የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

በሥር 3ኛ ተከሳሽ ይግባኝ ጠያቂነት የግራ ቀኙን ወገን ያከራከረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ መልስ ሰጪዎች እንዲሻር የጠየቁት ኑዛዜ በፍ/ህ/ቁ/882 መሰረት ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ ከመሆኑም በላይ ሟች በፍላጎታቸው ያደረጉትና ወራሾችን ከውርስ የሚነቅል ባለመሆኑ ሊሻር አይገባም በሚል የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሥር ከሳሾችም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ኑዛዜው የህጉን መስፈርት የሚያሟላ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ኑዛዜው በኮምፒዩተር ተጻፈ እንጂ ማን እንደጻፈው አይገልጽም፣ በፍ/ህ/ቁ/881 መሰረት በኑዛዜው አራት ምስክሮች መፈረም ያለባቸው ሲሆን በሚያከራክረው ኑዛዜ ያሉትና የፈረሙት ምስክሮች 3 ብቻ ሲሆን 4ኛው ምስክር ሆኖ የተመዘገበው የፈረመው 4ኛ ተጠሪ ነው፡፡ እንዲሁም ከፍ/ህ/ቁ 882 አንጻር ሲታይም ኑዛዜው በሬጅስትራር ወይም አንድ ምስክር ባለበት ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው ሰው ፊት ያልተደረገ እና በ23/07/1996 ሌላ ቦታ ተደርጎ በ26/08/1996 ዓ.ም. የውል ምዝገባ ጽ/ቤት ማህተም የተመታበት በመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 881-882 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ባለመሆኑ የሚሻር ነው ሲል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አመልካችም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብም፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በ23/07/1996 ዓ/ም የተደረገው ኑዛዜ በፍ/ህ/ቁ/882 ስር በተደነገገው መሰረት ለምዕራብ ሸዋ ዞን ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ በ26/08/1996 ዓ.ም. ተመዝግቦ በማህተም የተረጋገጠ ህጋዊ ኑዛዜ ሆኖ እያለና ተጠሪዎችም ከውርስ ሀብት ስለመነቀላቸው ባላስረዱበት ኑዛዜው ይፈርሳል ሲል የወሰነው ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- በፍ/ህ/ቁ/881 መሰረት ኑዛዜ ሲደረግ ተናዛዡ እየተናገረ ሌላ ሰው ወይም ተናዛዡ ራሱ እየጻፈ በአራት ምስክሮች ፊት ተነቦ መፈረም ያለበት ሲሆን የሚያከራክረው ኑዛዜ ግን ተናዛዡ እየተናገረ ማን እንደጻፈው የሚገልጽ ካለመሆኑም ሌላ ምስክሮቹም ሶስት ብቻ ሲሆኑ ከእነርሱ ውስጥም አንዱ ኑዛዜ የተደረገለት ሰው ነው፣ ኑዛዜው በፍ/ህ/ቁ/882 መሰረት የተፈጸመ ነው ለማለት ደግሞ አንድ ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሥራውን በሚያካሂድበት ክፍል ውስጥ ተደርጎ በዚያው ቀን በኑዛዜው ላይ ሁለት ምስክሮች መፈረም ያለባቸው ሲሆን የሚያከራክረው ኑዛዜ ግን በ23/07/1996 ዓ.ም. ተደርጎ በ26/08/1996 ዓ/ም በባለሥልጣኑ ሳይፈረም ማህተም ብቻ የተደረገበት በመሆኑ ጉድለት ያለበት ነው፣ እንዲሁም ኑዛዜው ተወላጆችን (ተጠሪዎችን) የሚነቅል በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በመልስ መልሳቸው ኑዛዜው የተደረገው በፍ/ህ/ቁ/881 ሳይሆን በቁጥር 882 መሰረት በመሆኑና የተደረገውም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ሆኖ ሶስት ምስክሮች የፈሩመበት በመሆኑ

www.abyssinialaw.com

ተጠሪዎች በኑዛዜው አራት ምስክሮች ሊፈርሙበት ያስፈልጋል ያሉት ተቀባይነት የለውም፣ ኑዛዜው ተጠሪዎችን ከውርስ የሚነቅላቸው አይደለም ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- የግራ ቀኙን ወገኖች የሚያከራክረው በ23/07/1996 ዓ.ም. ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሊሻር የሚገባ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ኑዛዜ በህግ ፊት የጸና የሚሆነው ህጉ ያስቀመጣቸውን መለኪያዎች አሟልቶ ሲገኝ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/17058 የሰጠው ፍርድ ያስገነዝባል፡፡ ኑዛዜ የሚሰጥበት ሥርዓት እንደ ኑዛዜው ዓይነት የሚለያይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይም የግራ ቀኙን ወገኖች የሚያከራክረውን ኑዛዜ በፍ/ህ/ቁ 881 ግልጽ ኑዛዜን በተመለከተ ከተቀመጡት መስፈርቶች እና ተያያዥነት ካለው ከፍ/ህ/ቁ/882 ጋር በማገናዘብ ሊመረመር የሚገባ ነው፡፡

በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው ወይም ተናዛዡ የሚጽፈው ሲሆን ኑዛዜው ተናዛዡና አራት ምስክሮች ፊት መነበብ የሚገባው ነው፡፡ ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸውን ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ ኑዛዜው እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ ካልተገኘም ፈራሽ ነው፡፡ ሆኖም በግልጽ ኑዛዜ በፍ/ህ/ቁ 881 የምስክሮች ቁጥር አራት መሆን እንደሚገባ የተደነገገ ቢሆንም በፍ/ህ/ቁ 882 በተነገረው ዓይነት የተደረገ ኑዛዜ ከሆነ ደግሞ የምስክሮቹ ቁጥር ሁለት ከደረሰ በቂ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከምስክሮቹ መካከል አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሆኖ ኑዛዜው የተደረገው ዳኛው ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሥራቸውን በሚያካሂዱበት ክፍል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ኑዛዜው በፍ/ህ/ቁ 881 በተነገረው መሰረት አራት ምስክሮች ተሟልተው በተገኙበት የተደረገ ካለመሆኑም ሌላ በፍ/ህ/ቁ 882 መሰረት ተደርጓል ለማለትም ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኑዛዜው በ23/07/1996 ዓ.ም. ሌላ ቦታ ተደርጎ 26/08/1996 ዓ/ም ወደ ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ወደአለው አካል ቀርቦ ማህተም የተመታበት በመሆኑ ነው፡፡ በህጉ ኑዛዜው ዳኛ ፊት ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሠጠው ሰው ሥራውን በሚያካሂድበት ክፍል ውስጥ መደረግ አለበት ሲል በግልጽ የተደነገገውን ባለመከተል ሌላ ቦታ የተደረገውን ኑዛዜ ከቆይታ በኋላ ውል ለሚመዘግበው አካል አቅርቦ ማስመዝገብ ኑዛዜው በህግ ፊት ዋጋ ያለው እንዲሆን የሚያደርግ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 - 882 ሥር የተመለከቱ ሁኔታዎችን የሚያሟላ አይደለም በሚል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመሻር አመልካችና ተጠሪዎች የውርስ ሀብቱን እኩል የመካፈል መብት አላቸው ሲሉ በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 25092 በቀን 18/03/2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/108978 በቀን 20/02/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ሟች በ23/07/1997 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ የህጉን መስፈርት የሚያሟላ አይደለም በሚል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 74451

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ደረጀ ማዘንጊያ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፍሬ ህይወት ጴጥሮስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ክልል የሀዋሣ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመደበኛ ችሎትና የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኂላ ያቀረበችው የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ነው፡፡ ተጠሪ ስልሳ ሶስት ንብረቶችን ዘርዝራ ለመካፈል ጥያቄ ያቀረበች ሲሆን፣ በጋብቻ ውስጥ ያገኙትና ቅድመ ክፍያውን በጋራ የከፍሉት በስሜ የደረሰኝ ኮንደሚኒየም ቤት፣ ለመሸጥ ለመለወጥና ለመካፈል የማይቻል በመሆኑ ቀሪውን የቤቱን እዳ ክፍያ የእኔ ንብረት እንዲሆን ይወሰንልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ አመልካች በበኩሉ የኮንዶሚንየም ቤቱ በጋብቻ ወቅት የተገኘ የጋራ ንብረት ነው፡፡ ቤቱ የጋራ ንብረት እዳውም የጋራ እዳ ሆኖ እንዲወሰንና ቤቱ ተከራይቶ ለመንግስት መከፈል ያለበት እዳ እዲከፈል ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለኮንዶሚኒየም ቤቱ እስካሁን የተከፈለውን ክፍያ ግማሹን ቤቱን ለማስኔጥ የወጣው ወጭና ፓርቲሽን ለመሥራት የወጣው ወጭ ተሰልቶ ግማሹን ተጠሪ ለአመልካች ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አከራካሪው ኮንዶሚኒየም ቤት በጋብቻ ወቅት ያገኘነው የጋራ ንብረት መሆኑ አልተካደም፡፡ በሥር ፍርድ ቤትም ተረጋግጧል፡፡ ንብረቱ የጋራ ንብረት ከሆነ የቤተሰብ ህጉን በመከተል እንዲካፈል መወሰን ሲገባው ተጠሪ እንድትወስድ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የካቲት 28 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ለሰበር አቤቱታው በሰጠችው መልስ ኮንዶሚኒየም ቤቱ ለመሸጥ፣ ለመለወጥና ለመካፈል የማይመች ንብረት ነው፡፡ ውሳኔውም ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 85 እና ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ መንግስት ከሚሠራው ስራ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ለቤቱ የወጣውን ወጪ ግማሹን ለአመልካች በመክፈል ተጠሪ የኮዶሚኒየም ቤቱን እንድትወስድ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነውም አከራካሪው የኮንዶሚኒየም ቤት ተጠሪ በስሟ ያገኘችው ከአመልካች ጋር በትዳር ተሳስራ ስትኖር መሆኑን አላከራከረም፡፡ በተጠሪ ስም የተገኘው የኮንዶሚኒየም ቤት የቅድመ ክፍያ በጋብቻ ወቅት ካፈሩት የጋራ ንብረት የተከፈለ መሆኑን እና ቤቱን ለማሳመር እና የቤቱን ፓርቲሽን ለመስራት አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ወቅት ያፈሩትን ገንዘብ የተጠቀሙ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም ቤቱ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 72 መሠረት የባልና የሚስት የጋራ ሀብት እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የኮንዶሚኒየም ቤቱ እና ለቤቱ ሊከፈል የሚገባው እዳ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት እና የጋራ እዳ ከሆነ የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ ይሄ የጋራ ንብረት እና ዕዳ የሚካፈልበት ስርዓት በምን መልክ እንደሆነ መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ በሕግ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ቤተሰብ የመመስረት መብት በመጠቀም ጋብቻ የፈፀሙ ወንዶች እና ሴቶች በጋብቻው አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመን እና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በፍቺ ወቅት የጋራ ንብረት ከአመልካች ጋር ስትካፈል ኮንዶሚኒየም ቤቱን የመውሰድ ልዩ መብት እንዳላት በመግለፅ ያቀረበችው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የኮንዶሚኒየም ቤቱ እንደማንኛውም በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ባልና ሚስቱ ስለቤቱና ስለቀሪው ዕዳ አከፋፈል የሚስማሙ ከሆነ በስምምነታቸው መሰረት ሁለቱ የማይስማሙና በአይነት ለመካፈል የሚቻል ከሆነ በአይነት ማካፈል ከላይ የተገለፁት በሁለቱ መንገድ ቤቱን ለመካፈል የማይችል ከሆነ ቤቱ በሀራጅ ተሽጦ የቤቱ ቀሪ ዕዳ ለባንክ ተከፍሎ ቀሪውን ገንዘብ የጋራ ባለሀብት ለሆኑት አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ማድረግ እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 51893 ሀምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለኮንዶሚኒየም ቤቱ እስካሁን የወጣውን ወጭ ግማሽ ገንዘበ ለአመልካች ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር በማለት የሰጡት ውሣኔ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 72 አንቀጽ 102 እና አንቀጽ 103 ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ባልና ሚስት በፍች ወቅት እኩል መብት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የተደነገገውንና ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገበ ቁጥር 51893 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሀዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሣያርሙ ማሳለፋቸውና ማፅናታቸው ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ (በሰበር መዝገብ ቁጥር 51893) የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያልተከተለና የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 ድንጋጌን የሚጥስ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የሀዋሣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ስለኮንዶሚኒየም ቤቱ የሰጡት የውሣኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. የኮንዶሚኒየም ቤቱ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የኮንዶሚኒየም ቤቱን እና ቀሪው የባንክ ዕዳ አከፋፈል ስርአት ላይ ከተስማሙ በስምምነታቸው መሰረት ይፈፀም፡፡ አመልካችና ተጠሪ ካልተስማሙና ቤቱን በአይነት ለማካፈል የሚቻል ከሆነ አመልካችና ተጠሪ ቤቱን በአይነት ይካፈሉ ዕዳውን ይክፈሉ፡፡ ቤቱን ከላይ በተገለፁት ሁለት መንገዶች ለማካፈል የማይቻል ከሆነ በሀራጅ ተሽጦ ቀሪው የባንክ ዕዳ ከተከፈለ በኋላ የሚተርፈውን ገንዘበ አመልካችና ተጠሪ እኩል መካፈል ይገባቸዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 77169

ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንገሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-እነ አቶ ተሾመ ገበየሁ ከጠበቃ አያው ካሣዬ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሊሻንወርቅ ገበየሁ - ጠበቃ ሚደቅሳ ባየሣ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወራሽነት ድርሻ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪዎች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካቾች የስር አቤቱታ ይዘትም ወላጅ አባታቸው አቶ ገበየሁ ወልደአብ እና ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ ዘረፋ ኃይለኛ ወራሽ መሆናቸው መረጋገጡን ጠቅሰውና የአባታቸውና የእናታቸው የውርስ ንብረት መለየት ያለበት መሆኑን ገልጸው የውርስ ንብረቱ እንዲጣራ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡ ተጠሪዎችም በአመልካች ጥያቄ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ውርሱ እንዲጣራና የውርስ አጣሪ እንዲሾም የፈለጉ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማሳወቃቸው ፍርድ ቤቱን አጣሪውን ሹሞ ውርሱ እንዲጣራ ያደረገ ሲሆን አጣሪውም የውርስ ሪፖርቱን ለፍርድ ቤቱ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጎ የአሁኑ አመልካቾች የውርስ ሪፖርቱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን የገለጹ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ሟች ገበየሁ ወልደአብ የተዉት ኑዛዜ ቀድሞ በፍርድ ቤት ክርክር ተደርጎበት ፈራሽ ባልተባለበት ሁኔታ በውርስ አጣሪ መነቀፉ ያላግባብ ነው በማለት አስያየታቸውን የሰጡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ የውርስ ንብረት ለወራሾች መለየት ያለበት በኑዛዜው መሰረት መሆኑን፣የሟች ወ/ሮ ዘረፋ ኃይለኛ የውርስ ንብረት ግን በሕጉ መሰረት ለወራሾች ሊከፋፈል እንደሚገባ ገልጾ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት አሻሽሎ አፅድቆታል፡፡በዚህ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች ሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ ባደረጉት ኑዛዜ ተቃውሞ ማቅረብ እንደሚችሉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበት እያለ ኑዛዜው አመልካቾችን በመንግስት ባዶ ይዞታ ላይ ብቻ መብት እንዳላቸው በመግለጽ አመልካቾችን ከውርሱ የነቀለ በመሆኑና የንዳ መሆኑን ጠቅሰን ተከራክረን የበታች ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው ላይ ቀድሞ ክርክር ተደርጎ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የጸና ስለሆነ የሟቹ ንብረት በኑዛዜው መሰረት ክፍፍል ሊደረግበት ይገባል በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር ፍርድ

www.abyssinialaw.com

ቤቶች ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ሳያስተናግዱ በኑዛዜው ዙሪያ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት ውድቅ በማድረግ ብቻ ማለፋቸው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ የኑዛዜው ሕጋዊነት ቀድሞ ያለቀ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ክፍፍሉ የሚፈፀምበት አግባብ በኑዛዜ ነው በማለት መወሰናቸው ተገቢነት ያለው ጭብጥ በመያዝና ህጋዊ ምክንያት በመስጠት ነው ሲሉ ውሳኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጠተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ/ም ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያስጸደቁትንና ሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ በ24/1986 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ እንዲሻርላቸው በርካታ ምክንያቶችን በመጥቀስ የመቃወም አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቁኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካቾች ከአቀረቧቸው በርካታ ምክንያቶች ውስጥ ኑዛዜው የተደረገው ክፍፍል ባልተደረገበት የባልና ሚስት ንብረት በመሆኑ አፈጻጸሙን አስቸጋሪ የሚያደርገው ነው በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 865(2) ድንጋጌን ጠቅሶ ኑዛዜውን ፈራሽ ነው በማለት በመ/ቁጥር 72097 የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮና ጉዳዩን መርምሮ ኑዛዜው በጋራ ሀብት ላይ መደረጉ ኑዛዜውን እንዳይፈጸም የሚያደርገው ምክንያት ወይም ኑዛዜው በዚህ ምክንያት ውድቅ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ በመ/ቁጥር 03897 መወሰኑን እንዲሁም ይህ ውሳኔ በአመልካቾች አቤቱታ አቅራቢነት በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05986 ከመጽናቱም በላይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎትም በመ/ቁጥር 49226 በሆነው በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት መዝገቡን መዝጋቱን ነው፡፡እንግዲህ አመልካቾች በኑዛዜው ሕጋዊነት ላይ ክርክር ከማቅረብ የሚከለክል ሁኔታ የለም በማለት በሚከራከሩት የተጠሪ የኑዛዜ ወራሽነት በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ በውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጊዜ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡አመልካቾች አሁን ለዚህ ችሎት በሰጡት የመልስ መልስ ላይ ግልጽ በማድረግ የተከራከሩት አሁን ያቀረቡት ክርክር የኑዛዜውን ፎርማሊቲ በተመለከተ ሳይሆን ከሟች አባታቸው የውርስ ንብረት የተነቀሉና ከ1/4ኛ በታች ሊደርሰን አይገባም በማለት ነው በሚል ነው፡፡የአመልካቾች ክርክር ይህ ከሆነ ኑዛዜው አመልካቾችን ከውርስ ሀብቱ ነቅሏል? ወይስ አልነቀለም?፣ለአመልካቾች የተሰጠው ድርሻስ ከውርስ ንብረቱ ሊደርስ ይችል ከነበረው ንብረት ውስጥ ከ1/4ኛ በታች ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ የሕጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ነው ተብሎ በፍርድ ቤት መፅደቅ ኑዛዜው መብታቸውን ይነካል በማለት ክርክር የሚያቀርቡ ወገኖች ይህንኑ ክርክራቸውን በዳኝነት አካሉ ከማቅረብ የማይከለክሉ ስለመሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

አመልካቾች ባሁኑ የክርክር ደረጃ የሟች ኑዛዜ ከውርስ ነቅሎናል በማለት የሚቃወሙ ሲሆን ይህ የክርክር ነጥባቸው ግን በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለተጠሪ የተሰጠውን የኑዛዜ ወራሽነት ለማሰረዝ

www.abyssinialaw.com

ተቃውሞ ሲያቀርቡ ሟች አባታችን ኑዛዜ አላደረጉም፣ማድረጋቸውንም አልሰማንም፣ ኑዛዜው በሞቱ በአርባኛው ቀንም አልተነበበም፣ ሟቹ አባታችን ኑዛዜ ያደረጉበት ሀብት በሟች እናታችን የጋራ ሀብት ላይ በመሆኑ ተፈጻሚነት የለውም፣ ኑዛዜው የተደረገው የመንግስት ሀብት በሆነው ባዶ ቦታ ላይ በመሆኑ ሕጉን ይቃረናል በማለት ተከራክረው ፍርድ ቤቱ ሟቹ ባዶ ቦታው ላይ ያላቸውን የይዞታ መብት ለአመልካቾች መናዘዛቸው ሕጉን የሚቃረንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ውድቅ ያደረገባቸው መሆኑና ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ከመወሰኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ይህ የውሳኔ ክፍል ለአመልካቾች የተሰጠውን ባዶ ቦታ ተገቢነትን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አመልካቾች ይህ ባዶ ቦታ ይዞታ መብት ሊተላለፍላቸው ይገባል ተብሎ በፍርድ ከተቋጨ ደግሞ ኑዛዜው ከውርስ ንብረት ነቅሎናል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 መሰረት ከ1/4ኛ በታች ሊደርሰን አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክርም ቀድሞ ይሰጣቸው የተባለው የይዞታ መብት መጠንና የሟቹን ለተጠሪ ይተላለፍ የተባለውን የውርስ ንብረት ግምት በማነፃጸር በግልፅ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ ቀድሞውንም ቢሆንም የክርክር ነጥብ ለማድረግ እየቻሉ ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ማንሳታቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 216 እና 217 ድንጋጌዎች ይዘት፣ መንፈስና አላማ ውጪ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በፍርድ ቤት በጸደቀ ኑዛዜ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል ተብሎ የተወሰነው ማስረጃውን በመቃወም አቤቱታ አቅርቦ ክርክር ተካሂዶ የመቃወም አቤቱታ በዝርዝር ታይቶ ውድቅ የሆነበትን ወገን ሳይሆን በፍርድ ቤት የፀደቀን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የሚችን መብቶች ለመውሰድ ተገቢውን እንቅስቃሴ የሚያደርገው ወራሽ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ማስረጃው በተሰጠበት መዝገብ ላይ ተቃውሞ አቅርቦ የተቃውሞ ምክንያቶች በዝርዝር ታይተው ውድቅ ከሆኑና ኑዛዜው ተፈፃሚነት አለው ከተባለ በኋላ በንብረት ክፍፍሉ ጊዜም የቀድሞ የተቃውሞ መሰረት የሆኑትን ነጥቦችንና የተቃውሞ አቤቱታ በቀረበበት ወቅትም የክርክሩ አካል ሊሆኑ ይገባቸው የነበሩትን ነጥቦች ሁሉ እንደገና አንስቶ እንዲከራከር ማድረግ ክርክሩ መቋጫ እንዳይኖረው የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ከፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አይነተኛ ዓላማ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ በህጉ አግባብ ስለማድረጋቸው የተረጋገጠው ኑዛዜ ሊከበርላቸው ስለሚገባና ለአመልካቾችም በሕጉ በውርስ ለማስተላልፍ ክልከላ ያልተደረገበትን የይዞታ ቦታ እንዲሠጣቸው የተናዘዙ በመሆኑ አመልካቾች የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ አመልካቾች የኑዛዜውን ሕጋዊነት በተመለከተ የመቃወም ማመልከቻ በአቀረቡበት ጊዜ ተከራክረውበት ሟችም በኑዛዜው ላይ ለአመልካቾች ባዶ ቦታ መስጠት የሚችሉ መሆኑ ተጠቅሶ ኑዛዜው ተቀባይነት ከአገኘ በኋላ ከሟች ውርስ ተነቅለናል፣ ከ 1/4ኛ በታች ሊደርሰን አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ጉዳዩ ቀድሞ ያለቀ ነው በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸው ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 79551 የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 107569 ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ የውርስ ንብረት ሟቹ በ24/12/1986 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜ መሰረት ሊከፋፈል ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 74791

ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ውቢት ሕሩይ ተወካይ ሰብለ ገብሩ ቀረበ

ተጠሪ ፡- የሀዋሣ ከተማ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ዐ/ሕግ አቶ ዮሐንስ

አሉላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በሌሎች ወገኖች መካከል ይደረግ በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ሶስተኛ ወገን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት በቀረበው መቃወሚያ ላይ የተሰጠ ውሣኔን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሃዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የፍ/ባለመበት የነበረው የአሁን ተጠሪ ሲሆን የፍ/ባለእዳ ደግሞ የሰበር ክርክሩ አካል ያልሆነውና የአሁኗ አመልካች ባለቤት የነበረው አቶ ዝቋላ ሙሉጌታ የተባለ ግለሰብ ነው፡፡ አቶ ዝቋላ ሙሉጌታ ከሌሎች ተባባሪዎቿ ጋር ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በመገልገል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሣ ቅርንጫፍ ከሚገኘው የአሁኑ ተጠሪ ሒሣብ ውስጥ ወጪ አድርገው ለወሰዱት ገንዘብ በወንጀል የተቀጡ ከመሆኑም በላይ ከተባባሪዎቹ ጋር በድምሩ ብር 3,005,002.03 (ሶስት ሚሊዮን አምስት ሺህ ሁለት ብር 03/100) እንዲከፍል በፍ.መ.ቁ.. 09336 በ11/06/03 ውሣኔ የተሰጠበት ሲሆን ገንዘቡን ወጪ አድርገው ወስደዋል የተባሉበት ከ2001 ዓ.ም. መጨረሻ እስከ 2002 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ድንጋጌ መሠረት በ30/10/03 ዓ.ም. የተፃፈ መቃወሚያ ያቀረበችውም ተጠሪ ከላይ የተጠቀሰውን ፍርድ ለማስፈፀም ቁጥሩ 10106 የሆነ የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍቶ ፍ/ባለእዳው ሥም የሚታወቅ አንድ ቤት እና በፍ/ባለዕዳው ባለቤት ማለትም በአሁኗ አመልካች ስም የሚታወቅ ሌላ ቤት በሀራጅ ተሸጠው ለአፈፃፀም እንዲውሉ ጥያቄ አቅርቦ ትእዛዝ በመሰጠቱ ሲሆን የመቃወሚያው ይዘትም ባጭሩ እዳው የተጋቢዎች የጋራ እና ለትዳር ጥቅም የዋለ ሣይሆን የፍ/ባለእዳው በግሉ በወንጀል ድርጊት ምክንያት ያመጣው በመሆኑ ምክንያት በፍ/ባለእዳው ስም ከተመዘገበው ቤት ውስጥ ድርሻዬ በሆነው በግማሹ ላይ እና በስሜ በተመዘገበው የግል ንብረቴ በሆነው ቤት ላይ ሊፈፀም አይገባምውም የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ

www.abyssinialaw.com

በ08/11/03 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 72(1)እና (2) መሰረት ንብረቱ በእንዳቸው የተመዘገበ ቢሆንም የጋራቸው እንደሆነ እንደሚቆጠር በስሟ የተመዘገበ ቢሆንም የጋራቸው እንደሆነ እንደሚቆጠር በስሟ የተዘመገበው ቤት የግል ንብረቷ ስለመሆኑ ያቀረበችው ማስረጃ እንደሌለ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 79(1) እና (2) መሠረት ከተጋቢዎቹ በአንዱ ብቻ የመጣ እዳ ከተጋቢዎቹ የጋራ ሃብትና ከዚያም አልፎ እዳው ባልተሸፈነበት ጊዜ ከተጋቢዎቹ የግል ሀብት ጭምር ሊከፈል እንደሚችል በዝርዝር በመግለጽ መቃወሚያው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

የከተማው ከፍተኛ ፍ/ቤትም የመቃወሚያ ክርክሩን ከመረመረ በኃላ ተቃዋሚዋ በስሟ የተመዘገበው ቤት የግሏ መሆኑን ስላለስረዳች ሁለቱም ቤቶች የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ናቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 79(2) መሠረተ እዳው ለጋራ ጥቅም የዋለ መሆኑን የፍርድ ባለመብቱ ስላስረዱ ተቃዋሚዋ ከሁለቱም ቤቶች ያላት ድርሻ ለእዳው መክፈያነት ሊውል አይገባም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በፍ/ባለመብቱ ጠያቂነት የቀረበለትን ይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ከተጋቢዎቹ ከአንዳቸው በግል የሚጠይቀው እዳ የሚከፈለው ከባለእዳው ተጋቢ የግል ሀብት መሆኑ የግል ሃብቱ እዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ በጋራ ሃብታቸው መሆኑ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 79(1) ተደንግጐ የሚገኝ መሆኑን ገልፆ ግማሽ ድርሻዋ ሊጠበቅላት ይገባል ሲል የሥር ፍ/ቤት ግማሽ ድርሻዋ ሊጠበቅላት ይገባል ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በማሻሻል የፍ/ባለዕዳውን ንብረት እዳውን የማይሸፍን ከሆነ የጋራ ሃብታቸው ተሸጦ ለአፈፃፀም ሊውል ይገባል በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁኗ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበችው የጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል በማለት ሲሆን በ25/03/04 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ እዳው በአንዱ ተጋቢ የወንጀል ድርጊት የመጣ መሆኑ እንዳልተካደ፣ ከፍ/ባለእዳው ጋር ተጣልተው በ1999 ዓ.ም ጠፍታ ወደ ዱባይ እንደሄደች የፍ/ባለዕዳ በ2001 ዓ.ም. የመጥፋት ውሣኔ እንደተሠጠባት የመጥፋት ውሣኔ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 84(ሀ) መሠረት ጋብቻውን የሚያፈርስ ምክንያት እንደሆነ፣ ድጋሚ እንዳልተጋቡ፣ እዳው የመጣው ከመጥፋት ውሣኔው በኃላ ጋብቻው በፈረሰበት ጊዜ እንደሆነ እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 39837 የተሠጠው ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት እንዳለው የሚከራከር ነው፡፡ ተጠሪው በበኩሉ በ08/05/04 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠ በኃላ አመልካቿ ቀርባ የመጥፋት ውሣኔውን ከነ ውጤት ያሻረች በመሆኑ ምክንያት ፍቺ እንዳልተፈፀመና እዳውም የመጣው በጋብቻ ጊዜ እንደሆነ የሚቆጠረ መሆኑን ጋብቻው መፍረሱን አመልካች ያላስረዳች መሆኑን በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 39837 የተሰጠው ውሣኔ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ በአንዱ ተጋቢ የመጣ እዳ አከፋፈልን የሚመለከት በመሆኑ ምክንያት የሚደግፈው የአመልካችን ሣይሆን የተጠራን የክርክር አቋም መሆኑን እና በነዚህም ምክንያቶች አቤቱታው የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አለመሆኑን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን አመልካችም በ25/05/04 የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥታለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህም መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው እዳ የሥር የፍ/ባለእዳ በወንጀል ድርጊት ጭምር ጥፋተኛ በተባለበት ሁኔታ የመጣ የግል እዳ መሆኑ በተጠሪ ያልተካደና በማስረጃም የተረጋገጠ ሲሆን በአንድ በኩል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያው የቀረበለት የሃዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩን ቀጥለው የተመለከቱት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች በጉዳዩ ላይ የተለያየ ውሣኔ የሰጡት ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ እዳ ሊፈፀም ስለሚችልበት ሃብት በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 79 የተመለከተውን ድንጋጌ በተለየየ ሁኔታ በመተርጐም መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ በድንጋጌው ውስጥ ".....ከባል ወይም ከሚስት........" በሚል የተቀመጠው ሐረግ መነሻ የሚያደርገው የጋብቻ መኖርን በመሆኑ ድንጋጌው ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው እዳው የመጣው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በሰበር አቤቱታ በሥር ከፍ/ባለእዳ ጋር ተጣልታ በ1999 ዓ.ም ጠፍታ ወደ ዱባይ ሃገር መሄዷን የፍ/ባለእዳው በ2001 ዓ.ም የመጥፋት ውሣኔ እንደሰጠበት፣ የመጥፋት ውሣኔው በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 84(ሀ) መሠረት ጋብቻን የማፍረስ ውጤት እንደሚያስከትል ከዚህ በኃላ ተመልሰው እንዳልተጋቡ እና እዳው የመጣው ከመጥፋት ወሣኔው በኂላ ጋብቻው በፈረሰበት ጊዜ እንደሆነ በዝርዝር በመግለጽ የተከራከረች ሲሆን ተጠሪውም በሰጠው መልስ እነዚህን ፍሬ ነገሮች ሣይክድ ነገር ግን አመልካች የመጥፋት ውሣኔውን ያሻረችው በመሆኑና የመጥፋት ወሣኔው መሻር ደግሞ የጋብቻ መፍረስን ጨምሮ የመጥፋት ውሣኔው ያስከተላቸውን ውጤቶች የሚሽር በመሆኑ ምክንያት ወንጀሉ የተደረገውም ሆነ እዳው የመጣው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ እንደሆነ ግምት ስለሚወሰድበት እና ጋብቻው በሕጉ አግባብ የፈረሰ ስለመሆኑ ያቀረባቸው ማስረጃ ስለሌለ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ይሁን እንጂ የመጥፋት ውሣኔ ውጤት ማስከተል የሚያቆምባቸው ሁኔታዎች እና ጠፋ የተባለው ሰው መመለስ የሚያስከትለው ውጤት በፍ/ሕ/ቁ. 170 እና 171 የተመለከተ ሲሆን በተለይ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥኛ አግባብነት ያለው የፍ/ሕ/ቁ. 171 የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠበት በኃላ የሚመለስ ሰው በንብረቶቿ ላይ የነበረውን መብት መልሶ እንደሚጐናፀፍ የሚገልጽ ከመሆኑ በስተቀር ቀደም ሲል ጋብቻ የነበረው ከሆነ ጠፋ በመባሉ ምክንያት ፈርሶ የነበረው ጋብቻው ተመልሶ ሕይወት የሚዘራ ስለመሆኑ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የመጥፋት ውሣኔውን ማሻሯ የፈረሰውን ጋብቻ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮም ሆነ ከተመለሰችበት ቀን ጀምሮ መልሶ የሚያቋቁመው ባለመሆኑ እዳው የመጣው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ እንደሆነ ይገመታል በማለት ተጠሪው ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ጋብቻው በሕጉ አግባብ የፈረሰ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም በማለት ከተጠሪ የቀረበውን የክርክር ነጥብ በተመለከተ ከላይ እንደተገለፀው የመጥፋት ውሣኔ የሚያስከትለው የጋብቻ መፍረስ ውጤት ዘላቂነት ያለው እንጂ ጠፋ የተባለውን ሰው መመለስ ተከትሎ የሚሰረዝ ባለመሆኑ አመልካች ማቅረብ የሚጠበቅበት ማስረጃ አይኖርም፡፡ ይልቁንም አመልካች ከተመለሰች በኃላ የቀድሞ ባለቤቷ ከሆነው የሥር የፍ/ባለእዳ ጋር አዲስ ጋብቻ ፈጽመዋል ወይም በቀድሞው ሁኔታ በትዳር መኖር ቀጥለዋል ጠማል ከሆነ ይህንን ማስረዳት የሚጠበቅበት ተጠሪው ሲሆን በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህም ሁኔታ እዳው ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ በሥር የፍ/ባለእዳ በግል የመጣ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79 ድንጋጌ ለጉዳዩ አገባብነት ሊኖረው የሚችልበትም ሆነ ካልተከፍፈለው የጋራ ሃብት ውስጥ አመልካች ያላት ግማሽ ድርሻ ለእዳው ማስፈፀሚያ ሊሆን የሚችልበትን የሕግ አግባብ ባለመኖሩ የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ጉዳዩን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79 አፈፃፀም ጋር ያላግባብ በማያያዝ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ተቃዋሚ ከሁለቱም ቤቶች ያላት ድርሻ ለእዳው መክፈያ ሊውል አይገባም በማለት ለሰጠው ውሣኔ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 79 ድንጋጌ በምክንያትነት መጥቀሱ ስህተት ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ውሣኔው ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 55591 በ22/03/04 ዓ.ም. ያፀናው ውሣኔ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 10106 በ27/11/03 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 73247

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ልዑል ኪዳነማሪያም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ሰብለ ኪዳነ ማሪያም ጠበቃ ሙሉጌታ ፀግዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይገባኛል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች አቶ ሚካኤል ኪዳነ ማሪያምና አቶ አለም ገ/መስቀል ኪዳነ ማሪያም ከተባሉ ግለሰቦች ጋር በመሆን የሟች በሻይ ኪዳነ ማሪያምን የውርስ ንብረት በማጣራት የውርስ ንብረቱ ስመ ሀብቱ በወራሾች ስም እንዲዞር አድርገው የወራሽነት ማስረጃ በያዛቸው የአሁኑ ተጠሪዎች ይህ የወራሽነት ማስረጃ ተጠሪዎች በማያውቁት ሁኔታ በ26/07/1964 ዓ.ም. በስጦታ ባገኙት በአዲግራት ከተማ በ43 ካ.ሜትር ላይ በሰፈረው የንግድ ቤት ጭምር ተደርጎ ይኼው ንብረት ወደ ወራሾች ስም እንዲዞር መደረጉ ያላግባብ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አግባብ ባቀረቡት የተቃውሞ አቤቱታ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችና ሌሎች የወራሽነት ማስረጃውን የወሰዱት ወራሾች ለተጠሪዎች የተቀውሞ አቤቱታ በሰጡት መልስም የተጠሪዎች እናት ከሟች በሻይ ኪዳነ ማሪያም ጋር ትዳር ያልነበራቸው መሆኑን ቀድሞ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑን፣ በወራሽነት ማስረጃውም የሟቹ አስራ ሶስቱ ወራሾች ተጠቅሰው መገኘታቸውን፣አከራካሪው ቤት በስጦታ ተሰጥቶናል የሚሉትም ከእውነት የራቀ መሆኑንና ስጦታ ከሆነም በውልና ማስረጃ ቀርቦ በርስተ መዝገብ ካልተመዘገበ ዋጋ የሌለው መሆኑን ፣በቤቱና በቦታው ላይ ከተጠሪዎች እናት ጋር ተከራክረው የተጠሪዎች እናት መብት የሌላቸው መሆኑ መረጋገጡንና ውሳኔው ያልተለወጠ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት መጋቢት 26 ቀን 1964 ዓ.ም. ለተጠሪዎች ስጦታ ተደርጎ በጥር 08 ቀን 1972 ዓ;ም በቤተዘመድ ሽምግልና ጸድቆ ያለ መሆኑ እንዲሁም በፍርድ ቤት ፀድቆ እስከ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ደርሶ መፅደቁ መረጋገጡን በምክንያት ይዞ አከራካሪው የንግድ ቤት ለተጠሪዎች ሊሆን ይገባል ሲል በዚህ ረገድ የተሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ ክፍል እንዲሰረዝ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካችና ሌሎች ወራሾች ይግባኛቸውን ለአዲግራት ማእ/ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ክርክሩን ያስነሳው የንግድ ድርጅት ቤት በሟች በሻይ ኪዳነ ማሪያም ስም

እስከሆነ ድረስ አመልካችና ሌሎች ወራሾች የያዙት የወራሽነት ሰርተፊኬት ተጠሪዎች መብታቸውን ከማስከበር የሚከለክል ምክንያት በሌለበት ሁኔታ እንዲሰረዝ መወሰኑ ያላግባብ ነው፣ተጠሪዎች ንብረቱ ላይ ክስ በማቅረብ መብታቸውን ሊያስጠብቁ ይችላሉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ ከተጠሪዎች እናት ጋር ቀድሞ ተከራክረው በፍርድ ጉዳዩ አልቆ እያለ ይኼው ታልፎ ንብረቱ የተጠሪዎች ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪዎች እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ያነሱት ተቃውሞ በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች አመልካችና ሌሎች የስር የተቃውሞ አቤቱታ ተጠሪዎች የነበሩት ወራሾች በአከራካሪው ቤት ላይ ያገኙት የወራሽነት ስርተፊኬት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው የሚጠይቁት በአዲግራት ከተማ በ43 ካ/ሜትር ስፋት ባለው ቦታ በሰፈረው የንግድ ቤትን በ1964 ዓ.ም. አባታቸው ሟች ባሻይ ኪዳነ ማሪያም በስጦታ የሰጧቸውና ስጦታውም በሕጉ አግባብ ፀድቆ ያለ መሆኑን ገልፀው መሆኑን፣አመልካች በንብረቱ ላይ ከተጠሪዎች ወላጅ እናት ጋር ተከራክረን ያለቀ ነው ቢሉም ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከአመልካች እናት ጋር ሲከራከሩ የነበሩበት በሌላ ንብረት ከመሆኑም በላይ ክርክሩ ተደርጓል ቢባልም ተጠሪዎችን የማይመለከት መሆኑን ጠቅሰው የአመልካችን ክርክር ያለፉት መሆኑን፣አመልካች የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ክስ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር163/1993 ግንቦት 02 ቀን 1993 ዓ.ም. በ26/07/1964 ዓ.ም. የተደረገው ስጦታ ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰኑን፣ከዚህ ጊዜ በፊትም በ1972 ዓ.ም. ስጦታው በሕጉ አግባብ የፀደቀ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ወራሽ ከሕግ ውጪ፣ ወራሽነት በሌለው መብት ላይ የወራሽነት ሰርቲፊኬት ማስረጃ መያዙ ከተረጋገጠ ይኼው ማስረጃ ሊሰረዝ እንደሚገባ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ክርክር ዳግም ክስ ሊቀርብበት የማይገባው በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች በተመሳሳይ ፍሬ ነገሮችና የህግ ነጥቦች ላይ ክርክር ተደርጎ እልባት ማግኘቱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 5(1) ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ከተጠሪዎች እናት ጋር ክርክር አድርገው የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት ካለመሆኑ በላይ በቤቱ ላይ ሟቹ ስጦታ ያደረጉት ልጆቻቸው ስለመሆናቸው የተረጋገጠው ለተጠሪዎች በመሆኑ የተጠሪዎች እናት በንብረቱ ላይ መብት የላቸውም ተብሎ

www.abyssinialaw.com

መወሰኑ ተጠሪዎች የሚያነሱትን የሕግ ክርክር ዋጋ የሚያሳጣበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪዎቸ አለን የሚሉት የስጦታ ውል በተለያዩ ጊዜያትና ፍርድ ቤቶች ጸድቆ ተጠሪዎች በአከራካሪው ንብረት ላይ መብት ያላቸው መሆኑ መረጋገጡ አመልካች እና ሌሎች ወራሾች በንብረቱ ላይ የወሰዱትን የወራሽነት ማስረጃ ለመሻር ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በንብረቱ ላይ በ1984 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ተረክቤአለሁ የሚሉት የመከራከሪያ ነጥብ የክርክሩን ሂደትና ይዘት ያላገናዘበና በበታች ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ ግልፅ የሆነ መከራከሪያ ሳያቀርቡ በዚህ የሰበር ደረጃ ያነሱት አዲስ ክርክር በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) ድንጋጌ አንጻር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 42006 ሚያዚያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 46439 ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በአከራካሪው የንግድ ድርጅት ቤት ላይ የወሰዱት የወራሽነት ሰርቲፊኬት ማስረጃ እንዲሰረዝ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ጥ

www.abyssinialaw.com

# ጉምሩክ/ግብር ታክስ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 71070

መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- ተሾአብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ አወቀ ውቤ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐ/ሕግ ኃ/መለኮት አበበ ቀረቡ

መዝገቡን ምርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የይርጋ የጊዜ ገደብ አቆጣጠርን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ከቱርክ አገር ዘጠና ሶስት ጥቅል (በንድል) የአርማታ ብረት ለማስገባት ታክስና ቀረጥ ከፍያለሁ፡፡ በመጀመሪያ ዙር ሰላሣ ስድስት ጥቅል ብረት ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም ተረክቤ ወስጃለሁ፡፡ በሁለተኛው ዙር አምሳ አራት ጥቅል ብረት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ወስጃለሁ፡፡ በሁለት ዙር ይገባል ተብሎ ከሚጠበቀው ዘጠና ሶስት ጥቅል ሶስት ጥቅል ብረት መጥፋቱ ተረጋግጦ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ደብዳቤ ተፅፎ ዋጋው ከኢንሹራንስ ኩባንያው ተከፍሎኛል፡፡ተጠሪ ዴክራላሲዮን እንድበተን መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም ጠይቋል፡፡ ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም ተጠሪ ማስረጃ ሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ በስህተት የከፈልኩት ብር 273,503.92 (ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሶስት ብር ከዘጠና ሁለት ሣንቲም) እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጠልኝ በማለት የቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ የተለያዩ መከራከሪያዎችን ያቀረበ ሲሆን በዋናነት ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባና የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈፅሞበት ዕቃውን ከተረከበ ከስድስት ወር በኋላ ከሣሽ ያቀረበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በሁለት ዙር የሚገባውን ጥቅል ብረት ከተረከበ የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ያላቀረበ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሀምሌ 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አለቀ የሚባለው ዲክላራሲዮን ከተበተነበት ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ የስድስት ወር ጊዜ ያላለፈ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ወሣኔ መሠረታዊ የህግ

www.abyssinialaw.com

ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈፀመ የሚባለው አመልካች ዕቃዎችን ተረክቦ የወሰደበት ጊዜ ነው፡፡ ዕቃዎቹ የተለቀቁት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ ክስ ያቀረበው የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መስከረም 30 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ግራ ቀኙ በፅሑፍ ካቀረቡት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሚያዚያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰምቷል፡፡ የቃል ክርክሩ ግልባጭ ተያይዟል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው በዕቃዎች አሰያየም፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሒሣብ አሰራር ሥህተት ምክንያት በአብላጫ የተከፈለ የቀረጥና የታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ ተጣርቶ በብልጫ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ለከፋዩ ተመላሽ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 66 ንዑስ አንቀፅ 1 ገዥነት ያለው መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም በዚህ መሠረታዊ መርህ መሠረት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አጠናቅቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ወጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ከቀረበ ብቻ እንደሆነ የአዋጁ አንቀፅ 66 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት የሕግ ጭብጥ ለይርጋ የጊዜ ገደብ ለመቁጠር " የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተጠናቀቀ" የሚባለው ምን አይነት ተግባራት ተፈፅመው ሲጠናቀቁ ነው" የሚለው ነው፡፡ ይህንን ነጥሎ መወሰን " የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት " ለሚለው ቃል አዋጅ ቁጥር 622/2001 የሰጠውን ትርጓሜ ፣ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 17 " የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ማለት ወደ አገር የሚገባ ፣ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ የጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውም የጉምሩክ አፈፃፀም ሒደት እንደሆነ ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 66 ንዑስ አንቀፅ 29 እና በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 2/17/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ጉዳይ አድርገው የሚደነግጉት ዕቃዉ የጉምሩክ ሥርዓት አሟልቶ ወደ አገር የገባበት ወይም ከአገር የወጣበትን ጊዜ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተመላሽ ታክስና ቀረጥ ከፍየበታለሁ የሚለው ዘጠና ሶስት ጥቅል /በንድል/ የቶንድኖ ብረት ወደ አገር ውስጥ የሚገባው በሁለት ዙር መሆኑና አመልካች በመጀመሪያው ዙር የተጫነውን ሰላሣ ስድስት ጥቅል /በንድል/ የቶንዲኖ ብረት ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም የጉምሩክ ሥርዓት በማሟላት ተረክቦ የወሰደና ወደ አገር ውስጥ ያስገባ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሁለተኛው ዙር የመጣለትን ሀምሣ አራት ጥቅል ብረት ፣ መሟላት የሚገባውን ፎርማሊቲ በማሟላት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ ማስገባቱ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የሚጠብቀው ህጋዊ ሥርዓት አሟልቶ የያዘው በሶስተኛ ዙር የሚገባ ጭነት /ዕቃ /የለም፡፡ አመልካች በሁለተኛው ዙር ውጭ አገር እንዲላክለት ካዘዘው ዕቃ ውስጥ ሶስት ጥቅል ብረት የጠፋ መሆኑ ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 66/2/ እና አንቀፅ 2/17/ መሠረት አመልካች በሁለተኛው ዙር ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን ብረት ከጉምሩክ መጋዘን በማውጣት  አስፈላጊ የሆኑ ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ተረክቦ ወደ አገር ውስጥ ካስገባበት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ትርፍ ቀረጥና ታክስ ከፍየበታለሁ በማለት ተመላሽ ገንዘብ የጠየቀበትን ዕቃ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈፀመው የጉምሩክ ሥርዓት ተጠናቅቋል፡፡ አመልካች ተመላሽ ሒሣብ ካለው ከዚህ ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ወራት ውስጥ መጠየቅ ሲገባው ፣ ይህ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ጥያቄውን እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ አመልካች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተጠናቅቋል መባል የሚገባው ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ቀን ሣይሆን ዴክላራሲዮን ከተበተነበት ቀን ጀምሮ መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የአዋጅ ቁጥር  622/2001 አንቀፅ 66/2/ እና አንቀፅ 2/17/ ድንጋጌ ይዘት ፣ መንፈስና ዓላማ እንዲሁም ህግ አውጭው አዋጁን ሲያውጅ ያሰባቸውን መሠረታዊ ዓላማዎች ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ጥያቄ በይርጋ የጊዜ ገደብ ያለፈበት ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው  ሣ  ኔ</u>**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 76976

መስከረም 22 ቀን 2005ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ አጥሉ ሀብታሙ

ተጠሪ፡- አቶ ሊሻን ከተማ ገብሬ - ተወካይ መሀመድ ሸህ ዑመር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ለጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ የእኔ ንብረት የሆነችውን የሰሌዳ ቁጥር 2-0086 የሆነች ፒጆ መኪና በሌባ ተሰርቃ ስናፈላልግ ተከሳሽ/አመልካች/ መኪናዋ ኮንትሮባንድ ዕቃ ጭና ይዣታለሁ በማለት በቁጥጥር ስር አድርጎ ይዟታል፡፡ መኪናዋ ተሰርቃ የጠፋች መሆኑን ብገልፅለትም ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ካልከፈልክ በማለት የያዛት ስለሆነ መኪናየን እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች መኪናዋ የተያዘችው ህዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ቀረጥና ግብር ያልተከፈለባቸው የልጆች ነጠላ ጫማ አምስት ካርቶን የልብስ ሣሙና እና 68 ካርቶን ፌስታል ጭና ከቀብሪቢያ ወደ ጅጅጋ ስታጓጉዝ አየር ማረፊያ አካባቢ ተይዛለች፡፡ ከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 109 መሰረት እድሉ ተሰጥቶታል፡፡ ስለዚህ ክሱ ህጋዊ መሰረትና ምክንያት የሌለው በመሆኑ ይዘጋልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ ከፍሎ መኪናው ይለቀቅለት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ፍርድ ቤቱ ከስልጣኑ ውጭ ቅጣት ወስኗል በማለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች የካቲት 12 ቀን 2004ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ጉዳዩ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚያልቅ በመሆኑ የቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት መመሪያ አውጥቷል፡፡ መኪናዋ ስታጓጉዝ የተገኘችው ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ ክልከላ የተደረገበት ዕቃ/ፌስታል/ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ተጠሪ መክፈል የሚገባው ብር 10,000 ሣይሆን ብር 50,000 ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በህግ በተሰጠው ፈቅደ ስልጣን መሰረት ያወጣውን መመሪያ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 28 ቀን 2009ዓ.ም በተሰጠ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የሰጡት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 109 ንዑስ አንቀፅ 1 ለፍርድ ቤቱ ቅጣት ለማክበድና ለመቅለል ስልጣን የሚሰጥ ፈቃጅነት ያለው ድንጋጌ መሆኑን በማገናዘብና ድንጋጌው እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ስለሚል ቅጣቱን

www.abyssinialaw.com

ዝቅ አድርጎ መወሰንን ስለማይከለክል ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 29 ቀን 2004ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 109 ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸውን መመሪያዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ቁጥጥር ስር የዋለችው ፒጆ መኪና በሌባ ተሰርቃ እንደጠፋችበት ክርክርና ማስረጃ አቅርቧል፡፡ በሌላ በኩል ንብረትነቷ የተጠሪ የሆነችው መኪና የተያዘችው የጉምሩክ ቀርጥና ታክስ ያልተከፈለበትና ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ በህግ ክልከላ የተደረገበትን ዕቃ ስታጓጉዝ መሆኑን አመልካች በማስረጃ ያረጋገጠ መሆኑን በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገልጿል፡፡ የማጓጓዥያው ባለቤት በተፈፀመው ወንጀል ከራሱ ዕውቀት ወይም ፈቃድ ውጭ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ የተፈፀመው ወንጀል ክብደት እየታየ ከብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ እስከ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ተቀጥቶ ማጓጓዥያው እንደሚመለስለት የአዋጅ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 1 በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የማጓጓዥያው ባለቤት ከአስር ሺህ እስከ ሀምሣ ሺህ ብር ባለው ሬንጅ ውስጥ ሊከፍለው ስለሚገባ መቀጮ ዝርዝር አፈፃፀም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ስለመሆኑ ድንጋጌው በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት መመሪያ ቁጥር 50/2003 በማውጣት ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማጓጓዥያው የተያዘው ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ ዕቃ ከሆነ የማጓጓዥያው ኃላፊ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ መቀጮ ከፍሎ መጓጓዥያው የሚለቀቅለት መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የተጠሪ መኪና ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ ክልከላ የተደረገበት ስልሣ ስምንት ካርቶን ፌስታል ይዞ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 622 አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ባወጣው መመሪያ ቁጥር 50/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በብር 50,000/ ሀምሣ ሺህ ብር/ መቀጮ መቀጣት እንዳለበት በግልፅ ተደንግጎ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ ብቻ መቀጮ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ በአዋጁ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሰጠውን አስገዳጅነት ያለው መመሪያ የማውጣት ስልጣን የሚጋፋና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ መቀጮ ከፍሎ መኪናውን ይረከብ በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 80296

ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሳምሶን መንግስቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያቃቤ ህግ ወኪል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ የውጭ ምንዛሬ ያለፈቃድ ከአገር የማስወጣት ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን በመጀመሪያ የታያው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጸ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እንዲሁም መንገደኞች የውጭ ምንዛሬ ወደ ኢትዮጵያ ይዘው ስለሚገቡበትና ስለሚወጡበት በብሔራዊ ባንክ ግንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም የወጣውን መመሪያ አንቀጽ 3 በመተላለፍ ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡30 በቦሌ አየር መንገድ ከአገር ሊወጣ ሲል 5000 ዩሮ /አምስት ሺህ ዩሮ/ ይዞ ሊወጣ ሲል በኤክስሬይ ፍተሻ የተገኘ በመሆኑ በህገወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሬ (ዕቃ) ማውጣትና የመያዝ ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

አመልካች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የወንጀል ክሱን ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የሰው ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ተጠሪ ሰነድ ማስረጃውንና ከአመልካች እጅ የተገኘውን (5000 ዩሮ) በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ለጉምሩክ አሳውቀው ዴክራላሲዮን ተሰጥቷቸው ያስገቡ መሆኑንና የውጭ ምንዛሬው ከቦርሣቸው ውስጥ ሲገኝባቸው ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የተሰጠውን ዴክላራሲዮን ያልያዙ መሆኑንና ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ ያልነበረው መሆኑን ያስረዳልኛል የሚላቸውን የመከላከያ ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

www.abyssinialaw.com

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረና ከወሰነ በኋላ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ለመውጣት የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ በመውጣት ላይ እያለ ተይዟል፡፡ ተከሳሽ ውጭ ምንዛሬውን ይዞ የገባው አሳውቆና አስመዝግቦ በመሆኑ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ለመውጣት የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የውጭ ምንዛሬ ለማውጣት ይዞ ቢገኝ የውጭ ምንዛሬውን የማውጣት መብቱን ከሚያሳጣው በስተቀር በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብቱን እንደማያሳጣው ጉዳዩ የወንጀል ኃላፊነት እንደማያስከትል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 47935 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ እንደዚሁም ተከሳሽ በበኩል የተፈፀመው ተግባር ተከሳሽ አሳውቆና አስመዝግቦ ወደ አገር ይዞት የገባውን የውጭ ምንዛሬ ይዞ መውጣት መብት እንዳለው በመቁጠር የፈፀመውና ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ ከቀረበበት ወንጀል ክስ በነፃ ይሰናበታል፡፡ ከሳሽ ከተሰሳሽ እጅ የያዘውን ዩሮ /የውጭ ምንዛሬ/ በተያዘበት ቀን ባለው ምንዛሬ በማሰብ በብር ለተከሳሽ ክፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ መልስ ሰጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ ሲወጣ ሲል ተይዟል፡፡ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ሊወጣ ሲሞክር ዲክላራሲዮኑ ከተፃፈ የስድስት ወራት ጊዜ አልፎታል፡፡ አመልካች መልስ ሰጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ ሲገባ የነበረው መመሪያ መልስ ሰጭ ይዞ ለመውጣት በሚሞክርበት ጊዜ የተቀየረ ሲሆን በጉዳዩ ተፈፃሚ የሚሆነው ነው መልስ ሰጭ ለማውጣት ሲሞክር ፀንቶ ስራ ላይ የነበረው መመሪያ ነው፡፡ መልስ ሰጭ የውጭ ምንዛሬው ገደብና ቁጥጥር የሚደረግበት እቃ መሆኑን ያውቃል፡፡ ህጉን በመተላለፍ የውጭ ምንዛሬ ለማውጣት ሲሞክር በኤክስሬይ ማሽን የተያዘ በመሆኑና የተከሰሰበትን ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት በአንድ ዓመት ከስድሰት ውር ጽኑ እስራት እንዲቀጣና በተያዘው 5000 ዩሮ እንዲወረስ ወስኗል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣቱ አፈፃፀም ለሁለት አመት ተገድቦ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 195/1/ መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ሰበር አቤቱታ በጉዳዩ የስር ፍርድ ቤት የከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ ይዘት ከዘረዘረ በኋላ እኔ የውጭ ምንዛሬውን ይዤ ለመወጣት ስሞክር ስራ ላይ የነበረው መመሪያ መጀመሪያ ዩሮውን አስመስግቤ ወደ አገር ውስጥ ሳስገባ ያልነበረ ነው፡፡ የውጭ ምንዛሬ ይዤ በምወጣበት ጊዜ አልፏል የሚባል ከሆነም በወቅቱ በነበረው የኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ከሚሰጠኝ በስተቀር ወንጀል ሰርተሀል ተብሎ ሊወረሰብኝ አይገባም፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 47935 የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ነሐሴ 25 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች 5000 ዩሮ ከአገር ለማውጣት የተያዙት በኤክስሬ ምርመራ ነው፡፡ ገንዘቡን ወደ አገር ውስጥ ሳስገባ አስመዝግቤአለሁ በማለት ዴክላራሲዮን ያቀረቡት ገንዘቡ በፍተሻ ከተያዘ በኋላ ነው፡፡ ያቀረቡት ዴክራላሲዮን ከስድስት ወራት በላይ ያለፈው ከመሆኑም በላይ አመልካች ይዞት ወደ አገር ውስጥ ያስገባቸውን ዩሮ ቁጥር የሚገልጽ አይደለም፡፡ አመልካች ወንጀል የፈፀመው ያውም ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ ሲያስገባ ሳይሆን ይዞ ለመውጣት በሞከረበት ቀን /ጊዜ/ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚ የሚሆነው ወንጀሉ

ሲፈፀም ፀንቶ ሲሰራበት የነበረው ህግና መመሪያ ነው፡፡ አመልካች ሰበር ችሎት በፍ/ብሔር ጉዳይ የሰጠውን ውሣኔ ለወንጀል ጉዳይ መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡ የህግ መሰረት ያለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች ጥፋተኛ መባሉና ገንዘቡም እንዲወረስ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ለሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የውጭ ምንዛሬ በህገወጥ መንገድ ይዞ ሲወጣ የተያዘ ጥፋተኛ በመሆኑ ገንዘቡ በወርስ ለመንግስት ገቢ ይሁን በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር የውጭ ምንዛሬ ይዞ መውጣት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 የሚያስጠይቅ መሆኑ የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ስለሚገባበትና ስለሚወጣበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 መመሪያ የማውጣት ስልጣን ያለው መሆኑን ከህግ ማእቀፎቹ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ 5000 ዩሮ ከአገር ለማስወጣት ሲሞክር ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በፍተሻ የተያዘው ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ያለ ህጋዊ እውቅናና ፈቃድ የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር ሲያወጣ ተይዟል በማለት የተከሰሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 25 በሚደነግገው መሰረት ወንጀሉ ተፈፀመበት ቦታና ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ ማለትም ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በመጥቀስ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የብሔራዊ ባንኩ መመሪያ ተፈፃሚነት ይኖረዋል በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የህግ ትርጉም የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀል ህጉ አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጸ 2 መሰረት ያደረገና የህግ አተረጓጎም ስህተት የሌለበት በመሆኑ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ወደ አገር ውስጥ ይዞ ሲገባ የነበረው መመሪያ ሌላ ስለነበረ የውጭ ምንዛሬውን ይዤ ስውጣ ጸንቶ ስራ ላይ ያለው መመሪያ በእኔ ጉዳይ ተፈፃሚነትና ተጠቃሽነት ሊኖረው አይገባም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም ፡፡

2. አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ከአገር ሲያወጣ የተያዘው በፍተሻ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን በፈቃድ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ መሆኑን ከአገር ይዞ ለመውጣት የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ያለፈበት በመሆኑ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ለመውጣት እንዲፈቀድለት አሳውቆና ጥያቄ አቅርቦ ሳይሆን በቦርሳው ውስጥ በማድረግ ይዞ ሲወጣ በኤክስሬይ ፍተሻ ስለተደረገበት የተያዘ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህም የአመልካች አድራጎት ያለፈቃድ የውጭ ምንዛሬ ይዞ የመወጣት ወንጀል የሚያቋቁም ስለመሆኑ ከላይ የተገለፁት የህግ ማዕቀፎችና ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 23/2/ ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በወንጀል ህጉ አንቀጽ 81 ስር የሚወድቅና የውጭ ምንዛሬውን ሳያስፈቅድ ይዞ መወጣት ወንጀል መሆኑን አላውቅም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ሆኖም ህግ አለማወቅ ይቅርታን የማያሰጥ መሆኑን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 81 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ በመሆኑና የአመልካች አድራጎት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 81 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የማይሸፍን መሆኑን በስር ፍርድ ቤትና

www.abyssinialaw.com

በይግባኝና በሰበር ከቀረበው ክርክር ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች በተከሰሰኩበት ወንጀል ጥፋተኛ መባሌ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

3. አመልካች ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 45435 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና ወ/ሮ እየሩሳሌም ወንዴን በማከራከር ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የህግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት እንዳለው በመዘርዘርና በስር ፍርድ ቤትና በሰበር የተከራከረ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ይህንን መዝገብ በመጥቀስ አመልካችን ከወንጀል ነፃ ያደረገው መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሆኖም በሰበር መዝገብ ቁጥር 45935 በመሰረተ ባህሪው ጭብጥ የፍትሐብሔር ክርክር የተስተናገደበት መዝገብ ሲሆን የያዝነው ጉዳይ ወንጀል ተፈፀሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚል ጭብጥ ያያዘ የወንጀል መዝገብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመዝገብ ቁጥር 45935 የውጭ ምንዛሬው በተከራካሪው እጅ የነበረ ሳይሆን ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ተቀብሎ በእጁ ይዞት ያቆየው ሲሆን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ይዞት የወጣውን 5000 ዩሮ በእጅ ይዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ስለዚህ አመልካች ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት በሌለው ሰበር መዝገብ ቁጥር 45435 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በመሆኑም አመልካች ከህግ ውጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ የመውጣት ወንጀል ሲፈጽም የተያዘነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 195 ንዑስ አንቀጽ  መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በህገወጥ መንገድ ከአገር ሲያወጣ የተገኘው 5000 ዩሮ /አምስት ሺህ ዩሮ/ በውርስ ለመንግስት ገቢ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

www.abyssinialaw.com

# ንብረት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 75414

ጥቅምት 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ዋሪቴ ሰቡሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር ተወካይ አቶ ቡርቃ ፊጂሶ - ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ አየለች ሞሲሳ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነውን የመጨረሻ ፍርድ የሰጠው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በሚል የሰጠውን ዳኝነት ካከራከረው የጉዳይ ይዘት አንፃር ተመልክቶ አግባብነቱን ለማየት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ሲሆን ፤ ይዘቱም የግል ንብረቴ በሆነው ቤቴ ላይ 1ኛ ተጠሪ የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ ለ2ኛዋ ተጠሪ የሰጣት ስለሆነ ይኸው ካርታና ኘላን ሊሰረዝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ በ2ኛ ተጠሪ ስም ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ ለመስጠት የሚያስችል ማስረጃ በ2ኛ ተጠሪ መቅረቡንና ይህንኑ መሠረት አድርገን የሰጠን ስለሆነ የከሣሽ ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው ገልፆ ተከራክሯል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪም በበኩላቸው ይህ ክስ የቀረበበትን ቤት ባለቤታቸው አቶ አንኮ ሐዊያ በ1981 ዓ.ም ገዝቶታል፡፡ ከዚህ በኋላም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ ሚስትነቴንና የወራሽነት መብት በፍ/ቤት በማረጋገጤ ምክንያት የከተማው አስተዳደር ቤቱን ወደ ስሜ ያዞረው ስለሆነ የንብረቱ ባለመብት እኔ ነኝ የሚል ክርክር አቅርባለች፡፡

ፍ/ቤቱም ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የማን ነው? የሚለውን ነጥብ ለመለየት በሁለቱም ወገኖች የቀረበውን የቤት ግዥ የፅሑፍ ውል ሰነድ ፤ ግብር የተከፈለበትን ደረሰኝ እና የሰው ማስረጃዎችን ቃል ከተመለከተና ከሰማ በኋላ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በየፊናቸው ያቀረቧቸው ማስረጃዎችን

የማስረዳት ጥንካሬውን መርምሮና የተሻለ ማስረጃ ማን አቅርቧል የሚለውን ለመለየት ማስረጃውን መዝኖ ይኸው ቤት የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ የሆኑት የወ/ሮ ዋሪቴ ሱቡሳ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ ቤት የወ/ሮ ዋሪቶ መሆኑ እየታወቀ የከተማው አስተዳደር ያለአንዳች ማስረጃ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ ለ2ኛ ተጠሪ በመስጠቱ ምክንያት 2ኛ ተጠሪ ያለአግባብ የንብረቱ ባለቤት እንድትሆን ያደረጋት በመሆኑ የሰጠው ካርታና ኘላን ሊሰረዝ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የምዕራብ  አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘን ረገድ ተመሳሳይ ትንታኔ ተከትሎ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አፅንቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ በከተማው ውስጥ የሚገኙ መሬቶችን ቤቶችን ማስተዳደርና መቆጣጠር የባለይዞታነትና የባለቤትነት ማስረጃ መስጠት የከተማው አስተዳዳር ሥልጣን ነው፡፡ የከተማው አስተዳደርም ይህንኑ ክርክር የተነሣበትን ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ የሰጠው በዚሁ ሥልጣኑ መሠረት በመሆኑ ይህ ካርታና ኘላን የተሰጠው በስህተት ፣ አግባብ ባልሆነ መንገድ ነው የሚባል ከሆነ እራሱ ይሰርዘው ዘንድ ጥያቄው ለከተማው አስተዳደር ከሚቀርብ በቀር በፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር ሊወድቅ የሚችል ጉዳይ አይደለም ስለሆነም በገልጆታ ከተማ አስተዳደር የተሰጠው ካርታና ኘላን በመደበኛ ፍ/ቤት ሊሰረዝ አይገባም በማለት የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስለጉዳዩ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡትን የክርክር ይዘት ተከትለው የሚያብራሩ በመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አነሳስ እና አመጣጥ ከላይ በአጭር በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን ፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሣኔው እንደገለፀው በአንድ ከተማ ውስጥ የሚገኝን መሬት የማስተዳደር የመሬትን ስሪትን እና በስሪቱ መሠረት የተገነቡ መሆኑን በማረጋገጥ የተገነባው ንብረት /ቤት/ የባለቤት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን የመስጠት የከተማው አስተዳደር በአስተዳደር ረገድ ለከተማው አስተዳደር የተሰጠ ተግባርና ሥልጣን ስለመሆኑ ይህ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሚስማማበት ጉዳይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ በዚህ ጉዳይ የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር አከናወነ የተባለው ተግባር ከዚህ በላይ የከተማው አስተዳደር የአስተዳደር ሥልጣን ነው በተባለው ሥር ሊወድቅ  ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ነጥብ ግን ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በከተማ አስተዳደር ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሆነ የቤት የባለቤትነት መብት ከአንዱ ወደ ሌላው በሚተላለፍበት ጊዜ ንብረቱን ለማስተላለፍ የሚያስችል ህጋዊ ተግባር የተከናወነ መሆኑን በማረጋገጥ የዚሁ ንብረት የባለቤትነት መብት ከአንድ ወደ ሌላው የተላለፈ መሆኑን የሚያረጋግጠውን የንብረት ምዝገባ ተግባር ማከናወን ነው፡፡ በዚህ አኳኂን  አረጋግጦ የምዝገባ ሥርዓቱን አከናውኖ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላኑን ንብረቱ በተላለፈለት ሰው ስም አዘጋጅቶ በሰጠ ጊዜ በስሙ

www.abyssinialaw.com

ካርታና ኘላን ተዘጋጅቶ የተሰጠው ሰው የዚሁ ንብረት ባለቤት እንደሆነ በህጉ ግምት እንደተወሰደ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 1195 ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በዚሁ መሠረት በህጉ የሚወሰደውን የግምት አይነት ተከታይ በሆነው ድንጋጌ በተቃራኒ ማስረጃ ማስተባበል እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ጋር በተያያዘ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ አስቀድሞ በከተማው አስተዳደር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 የተሰጠውን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ የማስተባበል ሥራ የሚከናወነውና ፤ በህጉ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ግምት ቀሪ የመሆኑና ያለመሆኑ ጉዳይ የሚረጋገጠው በፍ/ቤት የዳኝነት ተግባር ጭምር ነው፡፡

ከዚህ አንፃር አሁን በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ የተነሣውን ጉዳይ ለአመልካች ክርክር ያስነሳው ቤት ባለቤት የአሁን አመልካች እንደሆኑ የሥር የወረዳ እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ እንደተረጋገጠ ገልፆዋል፡፡ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር በዚሁ የአመልካች መሆኑ በተረጋገጠው ቤት ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን በ2ኛ ተጠሪ ስም አዘጋጅቶ ሊሰጥ የቻለው 2ኛ ተጠሪ ስለጠየቀችው እንጂ የዚህን ቤት ባለቤትነት መብት ከንብረቱ ባለቤት ወደ 2ኛ ተጠሪ የተላለፈ መሆኑን የሚያሳይ ህጋዊ ተግባር /juridical act/ መቅረቡን አረጋግጦ እንዳልሆነ በግራ ቀኙ ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

ይህም ከሆነ ምንም እንኳ ማዘጋጃ ቤቱ በእራሱ እምነት የዚሁ ንብረት ባለበት 2ኛ ተጠሪ መሆኗን አረጋግጫለሁ በማለት የባለቤትነት የምስክር ወረቀት የሰጠ መሆኑ ቢታወቅም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 እንደተደነገገው የአሁን አመልካች ይህ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ሊሰጥ የቻለው የንብረት ባለሀብትነት መብት ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እንዴት መተላለፍ እንዳለበት በህጉ የተመለከተውን ደንብና ሥርዓት ሳይከተል ስለሆነ የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆኑ የህግ ግምት መውሰጃ የሆነው የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ቀሪ ነው ፤ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 ፣ 1196 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 231/1/ሀ/ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በፍ/ቤት ሊረጋገጥ የሚችል የዳኝነት ጥያቄ እንጂ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ አይደለም ለማለት የሚያበቃ አይደለም ከዚህ አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በማግኘታችን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 129383 በቀን 16/04/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙን ያከራከረው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ በመሆኑ ይኸው የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር ሥልጣኑ ጉዳዩን ተመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ እንደተመለከለተው አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን መልሰናል፡፡
3. የዚህ የፌደራል ሰበር ሰሚ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 75343

ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ በላይ ሀሰን አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመንገድ ሥራ ምክንያት ለጠፋ ንብረት /የባህርዛፍ አትክልት/ የሚከፈልን የካሣ የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች መንገድ ሲሰራ፣ ቁጥሩ 4500 የሆነ የባህርዛፍ አትክልት ላይ ውድመት ያደረሰበት መሆኑን ገልፆ ብር 165,000 /አንድ መቶ ስልሣ አምስት ሺህ ብር/ ካሣ ተከሣሹ (አመልካች) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ተጠሪ ባህርዛፍ የተከለው ከመንገዱ መጠበቅ የሚገባውን ርቀት ሣይጠብቅ በመሆኑ በደንብ ቁ. 6/1936 መሠረት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም፡፡ የተጠየቀው የካሣ መጠን የተጋነነ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የባህርዛፍ አትክልቱ የተተከለበትን ሁኔታ፣ በመንገድ ሥራው ምክንያት የወደመው ባህርዛፍ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብለት በማድረግ አመልካች ለተጠሪ ብር 17,942.00 /አስራ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ሁለት ብር/ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ተጠሪ ባህርዛፍ ወደመብኝ የሚለው ከዋና መንገድ መሐል መስመር ወደግራና ወደ ቀኝ አስራ አምስት ሜትር ስፋት ያለው መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ አስራ አምስት ሜትር ወደ ግራና ቀኝ አትክልት እንዳይተከል አዋጅ ቁጥር 65/36 የሚከለክል በመሆኑና ተጠሪ ይህንን የህግ ክልከላ በመተላለፍ፣ መጠበቅ የሚገባውን እርቀት ሣይጠብቅ ለተከለው ባህርዛፍ ግምት የመክፍል ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ያቀረበው ክርክር አላግባብ ውድቅ ተደርጓል፡፡ አመልካች እንዲከፍል የተወሰነው የካሣ መጠን የተጋነነ ነው በማለት የሰበር አቤቱታ አቀርበዋል፡፡ አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፣ እኔ ባህርዛፍ ስተክል ከመንገዱ መጠበቅ የሚገባኝን ርቀት በመጠበቅ ነው የተከልኩት፡፡ አመልካች በመንገድ ሥራ ለወደመው ባህርዛፍ በተሟላ ሁኔታ ካሣ

www.abyssinialaw.com

እንዲከፍል አልተወሰነበትም። ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም አመልካች በሰበር አቤቱታው ያቀረበውን ክርክር በማጠናከር ሚያዚያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የህግ ማእቀፎች ጋር በማገናዘብ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለሙያዎቹን በመመደብ ያረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ ማየት አስፈላጊ ነው። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጭብጥ ከቦታው ድረስ በመሄድ እንዲያጣራለት የመደበው ባለሙያ፣ ተጠሪ በመንገድ ሥራ ምክንያት በመንቀል ጉዳት የደረሰበት ባህርዛፍ አትክልት የተከለበት መሬት በህጋዊ መንገድ የተሰጠው የይዞታ መሬት መሆኑን አረጋግጧል። በተጠሪ የእርሻ ቦታ አዋስኖኝ የሚያልፈው መንገድ፣ ተጠሪ የባህርዛፍ አትክልቱን በሚተክልበት ጊዜና አመልካች መንገዱን ለማስፋት የሚቆፍርበት ጊዜ የነበረው ደረጃ ተመሣሣይ አለመሆኑ ተረጋግጧል።

ተጠሪ ባህርዛፉን በሚተክልበት ወቅት በተጠሪ የይዞታ መሬት አዋሣኝ የነበረው መንገድ የተንታ ወረዳን ከዞኑ ከተማ ደሴ ጋር ለማገናኘት ታስቦ የተገነባ መንገድ እንደነበርና መንገዱ የተንታ ወረዳን ከአዲስ አበባ ጋር የሚያገናኝ መንገድ እንዳልነበር ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። አመልካች የዚህን መንገድ ደረጃ ከፍ በማድረግ ተንታን ከአዲስ አበባ ጋር ለማገናኘት የሚችል መንገድ ለመገንባት ባደረገው እንቅስቃሴ ተጠሪ የመንገዱ አዋሣኝ በሆነው የይዞታ መሬት ላይ የተከለውን የባህርዛፍ አትክልት የወደመበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል።

2. ተጠሪ ካሣ የጠየቀበትን ባህርዛፍ ሲተክል በእርሻ መሬት ይዞታው አዋሣኝ ላይ ተገንብቶ አገልግሎት ሲሰጥ የኖረው መንገድ ወረዳውን ከዞኑ ዋና ከተማ የሚያገናኝ መንገድ እንደነበር የተረጋገጠ ነው። የዚህ አይነት መንገድ ደረጃው የአውራ ጎዳና መንገድ እንዳልሆነና መካከለኛ መንገድ በሚለው ደረጃ ውስጥ የሚሸፈን መሆኑ የጎዳናዎችና መንገዶች አከፋፈል አዋጅ ቁጥር 66/1936 የአንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎችን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል። ተጠሪ ባህርዛፍ ሲተክል፣ የመንገዱ ደረጃ መካከለኛ የነበረ በመሆኑ ተጠሪ ከግራና ከቀኝ እስከ አስራ ሶስት ሜትር ርቀት የመጠበቅ ግዴታ የለበትም። ተጠሪ ለተከለው ባህርዛፍ ካሣ እንዲያገኝ የተወሰነው ደረጃው መካከለኛ ከነበረው መንገድ ከአራት እስከ አምስት ሜትር ያለውን ርቀት በመጠበቅ የተከላቸው የባህርዛፍ ተክሎችና ቅጥያ ብቻ እንደሆነ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል።

አመልካች ተጠሪ ቢያንስ አስራ ሁለት ሜትር ርቀት ሣይጠብቅ ባርህዛፍ የተከለ በመሆኑ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው የሰበር ክርክር አከራካሪው መንገድ በመጀመሪያ አውራ ጎዳና ያልነበረና መካከለኛ መንገድ የነበረ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡትን

ፍሬ ጉዳይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ መንገዱ መጀመሪያ ወረዳን ከዞኑ ዋና ከተማ የሚያገናኝ የነበረ መሆኑንና አመልካች መንገዱን በማስፋትና ደረጃውን ከፍ በማድረግ ወረዳውን ከአዲስ አበባ ጋር ለማገናኘት የሚችል መንገድ ሲገነባ ለተጠሪ በይዞታው በተከለው ባህርዛፍ ላይ ጉዳት ማድረሱ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ስለመንገዶችና ድልድዮች አጠባበቅ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 65/1936 አንቀጽ 2(ሀ) እና የጎዳናዎችና መንገዶች አከፋፈል አዋጅ ቁጥር 66/1936 አንቀጽ 1(ለ) ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

3. የካሣውን መጠን በተመለከተ አመልካች በሚሠራው መንገድ ተጠሪ የወደመበት ባህርዛፍ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ ፣ የባህርዛፉ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ ቀርቦለት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በመንገድ ሥራው ምክንያት ከወደመበት ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ የማግኘት መብት የለው መሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የህግ ማእቀፎች በተለይም ከአዋጅ ቁጥር 455/1997/ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የካሣ መጠን ከላይ የጠቀስነውን የህገ መንግስት ድንጋጌ መሠረት ያደረገና አመልካች ለሰበር ችሎት የካሣውን መጠን በተመለከተ የሚያቀርበው ክርክር የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ክርክር በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ከላይ በገለጽናቸው ምክንያቶች የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአማራ ክልል የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሰኔ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ ቁ. 81081

ጥር 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ወ/ሮ ፍሬ ሕይወት መብራህቱ ገ/መድህን ጠበቃ ኃይሉ ደቤሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ መብራህቱ ገ/መድህን
2. ወ/ሮ ደስታ ወልደጋብር } ጠበቆች አቶ ሐጐስ አብርሃና ደባባ አመንሲሣ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የሌላ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረትን ይዞ ሲጠቀም የነበረ ሰው ቤቱን ለማደስ ወጪ ማውጣቱ ቢረጋገጥ ውጪውን የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት የሆነው ሰው የሚተካበት ሕጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩንና በሕጉ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ተከሳሾች ደግሞ የአሁኑ ተጠሪዎች ናቸው፡፡የአመልካች ክስ ተጠሪዎች ወደ አሜሪካን አገር ሲሄዱ ንብረትነቱ የተጠሪዎች የሆነውንና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 ክልል ውስጥ የሚገኘውን በቁጥሩ 593 የሚታወቀውን ቤት ይዘው ሲኖሩ የእድሳትና የማሻሻያ ፈቃድ በማውጣት የቤቱን ይዞታ በማሻሻል ከፍተኛ ወጪ ማውጣታቸውን ገልፀውና ወጪ የወጣባቸውን ምክንያቶችን አይነትና የወጪውን መጠን በመዘርዘር በድምሩ ብር 265,812.92(ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሁለት ብር ከዘጠና ሁለት ሳንቲም) ማውጣታቸውን ጠቅሰው ከቤቱ ግምት ጋር ተቻችሎ የቤቱ ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸውና ከቤቱ ግምት የሚተርፈውን ወጪ ደግሞ ተጠሪዎች እንዲተኩላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የአመልካች የወጪ ይተካልኝ ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው መሆኑንና ወጪውም የተጋነነ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማትና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራትም አድርጎ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ቤቱን ይዘው እድሳት አደረግሁ በሚሉበት ጊዜ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ህጋዊ መብት እንደነበራቸውና ቤቱን የመመለስ ህጋዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን እያወቁ እድሳት ማድረጋቸውና እድሳቱም አስፈላጊነቱ ታምኖበት የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያለመቅረቡን በምክንያትነት ይዞ ሁሉንም የወጪ ድምር ለአመልካች እንዲከፈል መወሰን ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጾና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169፣2170 እና 2174

www.abyssinialaw.com

ድንጋጌዎችን በዋቢነት ጠቅሶ በርትዕ ብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ ብር) ለአመልካች እንዲተካላቸው ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪዎችን ቤት ለማደሳቸው ተረጋግጦ የወጪው መጠንም በሁለት አካላት ተጣርቶ በአንደኛው አካል ብር 42,338.80፣በሌላኛው የመንግስት አካል ደግሞ ብር 63,942.43 መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት አነስተኛውን የወጪ ግምት እንኳን ሳይዝ በመቅረት በርትዕ ብር 15,000.00(አስራ አምስት ሺህ ብር) ብቻ ለወጪ እንዲታሰብ ማድረጉ ያላግባብ ስለሆነ ውሳኔው ተሽሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በጠየቁት መሰረት እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች አወጣሁ የሚሉት ወጪ በሁለት አካላት ተገምቶ በቀረበበት ሁኔታ አነስተኛው ግምት ሳይያዝ ታልፎ በርትዕ ብር 15,000.00 ብቻ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ የአመልካች ቅሬታ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ያለበት ያለመሆኑና የሕግ መሰረትም የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪዎቸ ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ተጠሪዎች አሜሪካን አገር ሲሄዱ የተጠሪዎች ንብረት የሆነውን ቤት ይዘው ሲጠቀሙ በቆዩበት ጊዜ ቤቱን ለማደስና ለማሻሻል ወጪ በማውጣታቸው ወጪው እንዲተካላቸው፣ ከቤቱ ግምትና አመልካች ከአወጡት ወጪ አንጻርም ሲታይ ወጪው ከፍተኛ በመሆኑ ስም ሃብቱ ለአመልካች ሊዛወር ይገባል በሚል ምክንያት ነው፡፡ተጠሪዎች የአመልካችን ወጪ የሕግ መሰረት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረውም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት የወጪው መጠን በሚመለከታቸው አካላት ተገምቶ እንዲቀርብለት በማድረግና ከሕግ ጋር በማገናዘብ የአመልካችን አብዛኛውን ጥያቄ ውድቅ አድርጎ በተጠሪዎች ሊተካላቸው የሚገባውን የወጪ መጠን በርትዕ የወሰነ መሆኑን ከውሳኔው ይዘት ተመልክተናል፡፡የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የወጪ ይተካልኝ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች ወጪ ያወጡት ቤቱ ለተጠሪዎች የሚመለስ መሆኑን በሚያውቁበት ወቅት መሆኑንና ወጪውም አስፈላጊ የነበረ ስለመሆኑ ያለመረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ቤቱ ባይታደስ ኑሮ በጠቅላላ በቤቱ ይዘት ላይ ጉዳት ይደርስበት የነበረ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ ያለመኖሩንና ቤቱ ስለተጎዳ የቤቱን ህልውና ለማቆየት በቅን ልቦና አድሼአለሁ የሚል ክርክርም አመልካች ያላቀረቡ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

www.abyssinialaw.com

በመስረቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ያሉት ያላግባብ ስለመበልጸግ ጉዳይን በሚገዙት ደንቦች ስር ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2168 ድንጋጌ ይዘት ሲታይም አንድ ሰው ለተወሰነ ጊዜ በእጁ ያቆየውን እቃ እንዲመለስ የተገደደ እንደሆነ ለሕግ ወይም ለውል ተቃራኒ የሚሆን ድንጋጌ ከሌለ በቀር የተባለውን እቃ ከመለዋወጥ የተነሳ ያሉት መብቶችና ግዴታዎች ከድንጋጌው ቀጥለው ባሉት ደንቦች መሰረት የሚወሰን መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ ስር ከሰፈሩት ደንቦች መካከል አንዱ የሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169 ስር የተቀመጠው ደግሞ የያዘውን እቃ እንዲመልስ የተገደደ ሰው በእቃው ላይ ያደረገው ወጪ ሊመለስለት የሚገባው ወጪው የግድ አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑና ወጪው አስፈላጊ ሳይሆን ከቀረ ወይም ወጪው እቃውን እንዲመለስ በተገደደው ሰው ወይም ተገዳጁ ኃላፊ በሚሆንበት ሰው ጥፋት ምክንያት ከሆነ ወጪው ሊመለስ የማይችል መሆኑን ያሳያል፡፡ሕጉ በአንቀጽ 2171(1) ስርም ለእቃው የተደረገው ወጪ የእቃውን ዋጋ ግምት ከፍ አድርጎት እንደሆነም እቃውን ለመመለስ የተገደደው ሰው ስለዚሁ ጉዳይ ያወጣው ገንዘብ ሊመልስለት እንደሚገባ የደነገገ ሲሆን ይህ ወጪ በክፉ ልቦና ስለመደረጉ የተረጋገጠ ወይም ርትዕም የሚያስገድድ ከሆነ ደግሞ ዳኞች ወጪውን ለመቀነስ ወይም ጭራሹን ለማስቀረት የሚችሉበት አግባብ መኖሩንን የተጠቃሹ ድንጋጌ ቀጣይ የሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2172((1) ይዘት ያሳያል፡፡ይህ ድንጋጌ አንድን ወጪ በክፉ ልቦና የተደረገ ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብም ወጪው በተደረገበት ጊዜ ወጪውን የሚጠይቅ ሰው እቃውን ለመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያውቅ እንደነበረ ወይም ማወቅ ይገባው የነበረና ርትዕም ሲያስገድድ መሆኑን በመለኪያነት አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ አንድ ሰው የሌላ ሰው ንብረት ይዞ ሲጠቀም ከቆየና ንብረቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ንብረቱን ከጥፋት ወይም ከብልሽት ለማዳን ሲል ተገቢውን ወጪ ቢያወጣ ይኼው ወጪ በሕጋዊ ባለሃብቱ እንዲተካለት መጠየቅ የሚችልበት አግባብ የሚኖረው ወጪው የግድ አስፈላጊ ከሆነና በቅን ልቦና የተደረገ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የሚያስገነዝቡ ሲሆን በክፉ ልቦና የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠውን ወጪ ግን እቃውን እንዲመለስ የተደረገ ሰው ሊቀነስበት ወይም ጭራሹንም ዳኞች ሊያስቀሩት የሚችሉ ስለመሆኑ ሕግ ስልጣን የሰጣቸው መሆኑን ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የተጠሪዎችን ቤት ይዘው ሲኖሩ ወጪውን ያወጡት ቤቱን ለተጠሪዎች የመመለስ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በሚያውቁበት ወይም ማወቅ ይገባቸው በነበረ ጊዜ መሆኑና ወጪውንም በክፉ ልቦና ያደረጉት መሆኑን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ይህ ችሎትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 አግባብ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን እንዳሉ የሚቀበላቸው ሁኖ አግኝቷል፡፡ከዚህ አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡን ፍሬ ነገሮችን ይዘን ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169፣2171 እና 2172 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው አመልካች አወጣሁ የሚሉት ወጪ ሙሉ በሙሉ ሊተካላቸው ይገባ የነበረ ወይም ፍርድ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት መቀነስ የማይችልበት ሁኖ አላገኘነውም፡፡የስር ፍርድ ቤት በሁለት አካላት ተረጋግጦ የቀረበለት የወጪ ግምት እያለ አነስተኛ የተባለውን ብር 42,338.92 እንኳን መሰረት አድርጎ ውሳኔ ሳይሰጥ የወጪ መጠኑ ብር 15,000.00(አስራ አምስት ሺህ ብር) ብቻ እንዲሆን መወሰኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2171 እና 2172(1) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት ያለ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32917 መጋቢት 07 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 107559 ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የተጠሪዎች ሕጋዊ ሃብት የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይዘው ሲጠቀሙ አወጣሁ የሚሉት ወጪ የግድ አስፈላጊ የነበረ በመሆኑ ወይም በቅን ልቦና ያደረጉት ስለመሆኑ ያለማስረዳታቸውን መሰረት አድርገውና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169፣2171 እና 2172(1) ድንጋጌዎች አንጻር በመመልከት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ህዳር 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 81406

ጥር 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1. አቶ አህመድ ኢብራሂም } ጠበቃ ሙሉጌታ ታደሰ ቀረቡ

2. አቶ ሰኢድ ሃገረላዊ

ተጠሪ፡- አቶ አመሀ ተ/ወይኒ ጠበቃ ሐጎስ አበረሃ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለመኪና ግዥ የተከፈለ ነው የተባለን ገንዘብ ከማስመለስ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ አመልካቾቹ ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ተከሳሾቹ አብረው በንግድ ስራ የተሰማሩ መሆናቸውን 2ኛ ተከሳሽ አ/አበባ በነበሩበት በ26/07/03 ለከሳሽ መኪና እንደሚሸጡላቸው ከከሳሽ ጋር ተነጋግረው የመኪናው ዋጋ በ1ኛ ተከሳሽ በኩል እንዲልክላቸው በገለጹት መሰረት ከሳሽ በ28/07/03 ብር 750,000.00 በወጋገን ባንክ ተ/ሀይማኖት ቅርንጫፍ በኩል የላኩላቸው መሆኑን ተከሳሾቹ መኪናውን ሳይልኩ እንደቀሩና ገንዘቡንም እንዲመልሱ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ እንደቀሩ የሚገልጽ ሆኖ ለክሱ ኃላፊ የሚሆነው ተከሳሽ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 36/5/ መሰረት ተለይቶ ብር 750,000.00 ከወለድና ክሱ ካስከተለው ወጪ ጋር እንዲከፍል ውሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ ተከሳሾቹ በበኩላቸው መኪና ለመሸጥ 2ኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር እንዳልተነጋገሩ ከከሳሽ ጋር የቆየ የንግድ ግንኙነት የነበራቸው በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ አ/አበባ ውስጥ የተነጋገሩት ከከሳሽ ስለሚፈለግ የእዳ መጠንና እዳው ስለሚከፈልበት ሁኔታ እንደሆነ ከሳሽ የሞባይል ቀፎዎችን ከተከሳሾች በካሽ እና በዱቤ ይገዙ ስለነበረ የብር 850,000.00 ዕዳ ይፈለግባቸው እንደነበር ከዚህ ውስጥ በ05/05/03 ብር100,000.00 በ2ኛ ተከሳሽ ስም በንብ ባንክ ወደ ጅጅጋ እንደላኩ በክሱ የተጠቀሰው ገንዘብም ከከሳሽ የሚፈለግ ቀሪ ዕዳ እንደሆነ ከሳሽ ክስ ሊያቀርቡ የቻሉት የሞባይል ቀፎ ዋጋ በመውረዱ ገንዘብ እንዲመለስላቸው ጠይቀው ተከሳሾች ባለመስማማታቸው እንደሆነ እና በከሳሽ በምስክርነት የተቆጠሩት ግለሰቦች ከከሳሽ ጋር አብረው የሞባይል ቀፎዎችን ከተከሳሾች ሲገዙ የነበሩ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና የጽሑፍ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሹ ብር 750,000.00 የላኩት ለመኪና ግዥ ነው ወይስ ከተከሳሾቹ ጋር በነበራቸው የሞባይል ቀፎ ሽያጭ ንግድ ግንኙነት ነው? የሚል ጭብጥ

www.abyssinialaw.com

መስርቶ ከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ ስለመኪና ሽያጭ ጉዳይ መስማማታቸውን ያስረዳሉ ተብለው የተሰየሙት የከሳሽ ምስክሮች ከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ ተገናኝተው ተነጋግረዋል ስለተባለበት ሰዓት እና የተለየበት እንዲሁም ስለተሽከርካሪው ዓይነት እና ዋጋ የሰጡት ምስክርነት ልዩነቶች የሚታይበት መሆኑን እነዚህ ልዩነቶችም ከሳሽ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ተነጋግረናል ባሉበት ጊዜና ቦታ ምስክሮቹ ያልነበሩና በጥናት እንደቀረቡ የሚያመለክት መሆኑን ከሳሽ መኪና ለመግዛት ተስማሙበት ውል እንኳ የሌላቸው መሆኑን እና ምንም ውል ሳይኖር መኪና ለመግዛት ብር 750,000.00 እንዲሁ ይሰጣሉ ብሎ ለማመን የሚከብድ መሆኑን በዝርዝር ገልጾ ከሳሽ ገንዘቡን የላኩት የነበረባቸውን ዕዳ ለመክፈል እንጂ ለመኪና ግዥ ነው ማለት አልተቻለም ሲል ክሱ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽ የመኪና ግዥ ውል በጽሑፍ ባያቀርቡም የሀዋላ ሰነዱን በማስረጃነት እንዳቀረቡ ተከሳሾቹ ገንዘቡን መቀበላቸውን አምነው ምክንያቱን የካዱ በመሆኑ ከከሳሽ የሚፈልጉት እዳ ስለመኖሩ በጽሑፍ እስካላስረዱ ድረስ ገንዘቡን የማይመልሱበት ምክንያት እንደማይኖር እና ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ቀረበበትን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ምስክሮችን በመስማት እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት እንዳልሆነ በዝርዝር ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ተከሳሾቹ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ወይም ሊሻር ይገባል በማለት ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ክርክር ያስቀርባል በመባል ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን መሰረት በማድረግና በማጠናከር በሰበር ደረጃ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

ጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ ተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ ቀረበበት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በስር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ ማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘት ከ2ኛ አመልካች ጋር የመኪና ሽጭ ውል ማድረጋቸውንና የሽያጩን ዋጋ 2ኛ አመልካች በጠየቁት መሰረት በ1ኛ አመልካች ስም በባንክ መላካቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሰረቱ አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የማስረዳት ሸክም እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ 2001/1/ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተከሳሾ በከሳሽ የተላከውን ገንዘብ መቀበላቸውን አምነው ለገንዘቡ መላክ ምክንያት የሆነው ግን ከሳሽ እንደገለጹት የመኪና ሽያጭ ውል አለመሆኑን ክደው ተከራክረዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የመኪና ሽያጭ ውል ተደርጎ የነበረ መሆኑን እና ገንዘቡም የተላከው በዚሁ ውል ምክንያት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቀው ከከሳሽ ወገን ነው፡፡ የውሉን መኖር ለማስረዳት ከሰሽ የሰሟቸው ምስክሮች በጥናት የቀረቡ ናቸው በሚል ከፍተኛ ፍ/ቤት ምስክርነታቸውን ውድቅ ያደረገ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ይህንን የከፍተኛ ፍርድ ቤት አቋም ወይም ትችት በዝምታ በማለፍ ከሳሽ የሚና ግዥ ውል በጽሑፍ ባያቀርቡም የሀዋላ ሰነድ አቅርበዋል ሲል በውሳኔው ላይ አስፍሮአል፡፡ በመሰረቱ የሀዋላ ሰነዱ በተከሳሾቹ ያልተካደውን የገንዘቡን መላክ እና በተከሳሾች እጅ መግባት የሚገልጽ ከመሆኑ ወጪ ስለተላከበት ምክንያት የሚጠቁመው ነገር አለመኖሩ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ የሀዋላ ሰነዱን በማዘጋጀት በማቅረብ ማስረዳት ሸከማቸውን የተወጡት የገንዘቡን መላክ ምክንያት መሆኑን በተመለከተ ጭምር

www.abyssinialaw.com

እንደሆነ አድርጎ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የያዘውና ለውሳኔው መሰረት ያደረገው አቋም ከላይ የተጠቀሰው ፍ/ሕ/ቁ 2001/1/ ድንጋጌ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩን ለማስረዳት መቅረብ የሚገባውን የማስረጃ አይነት በተመለከተ ግዙፍነት ያላቸው የተንቀሳቃሽ ንብረቶች ባለሀብትነት ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን በእጅ ባደረገ ጊዜ የተላለፈለት እንደሚሆን በፍ/ሕ/ቁ 1186/1/ የተደነገገ ሲሆን ልዩ የሆኑ አንዳንድ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱት የህጎች ድንጋጌዎች የተጠበቀ መሆናቸውም በፍ/ህ/ቁ 1186/2/ ተመልክቷል፡፡ መኪና ደግሞ ከልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች የሚመደል በመሆኑ ባለሀብትነት የማስተላለፉ ጉዳይ በተለይ ሕጎች የሚመራ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አንድ ተሽከርካሪ ባለሀብትነት እንዲተላለፍለት የሚጠይቅ ሰው አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሰነዶች በተጨማሪ ተሽከርካሪው ከውጪ ሀገር የገባ ከሆነ የጉምሩክ ዴክላራሲዮን በሀገር ውስጥ የተሰራ ከሆነ ተገዛበትን ኢንቮይስ እንዲሁም ከቀድሞ ባለንብረት በግዥ የተላለፈለት ከሆነ ደግሞ የዝውውሩን ህጋዊነት ለማስረዳት በሚመለከተው አካል የተሰጠ ወይም ተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ እንደሚጠበቅበት ስለተሽከርካሪ መለያ መመርመሪያና መመዝገቢያ በወጣው አዋጅ ቁጥሩ 681/2002 በአንቀጽ 6 ስር በሚገኙ አራት ንዑሳን ቁጥሮች በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በተለይም አዋጁ አንቀጽ 6/3/ እና 6/4/ ድንጋጌዎች ጥምሩ ንባብ እንድ ተሽከርካሪ በቀድሞ ባለንብረት በሽያጭ ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑ ተረጋግጦ የባለሀብትነት ዝውውሩ ሊፈፀም የሚችለው ውሉ በጽሑፍ በተደርገ ጊዜ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችልነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም ከሳሽ የመኪና ሽያጭ መደረጉን ለማስረዳት ማቅረብ የሚጠበቅባቸው የሽያጭ ውሉ የተደረገበትን ሰነድ ሆኖ እያለ እና የዚህ ዓይነቱን ሰነድ ደግሞ ያላቀረቡ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከሳሽ የሀዋላ ሰነዱን ማቅረባቸው በቂ ነው ሲል ሰጠው ውሳኔ የክሱን እና የፍ/ሕ/ቁ 2001/1/ ድንጋጌን ይዘት ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለውሳኔው በምክንያትነት የጠቀሰው ሌላኛው ነጥብ ተከሳሾቹ ገንዘቡን መቀበላቸውን አምነው ምክንያቱን ከመካድ በስተቀር ከከሳሽ የሚፈልጉት ዕዳ ስለመኖሩ ያቀረቡት የጽሑፍ ማስረጃ ሳይኖር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ምስክሮቹን በመስማት እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ ሳይኖር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ምስክሮችን በመስማት እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ ተከሳሾቹ በማስረጃነት ያቀረቡት ምስክሮችን ብቻ ሳይሆን የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ንግድ ፈቃድ እና ከሳሽ ቀደም ሲል ብር 100,000 በባንክ የላኩበትን ሰነድ ጭምር ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አከራካሪ ሆኖ ቀረበን አንድ ፍሬ ነገር ማስረዳት ስለሚቻልበት የማስረጃ ዓይነት አግባብነት ባለው ሕግ በተለይ የተቀመጠ ግልጽ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ እንደዚህ ዓይነቱን ፍሬ ነገር በምስክር ጭምር ማስረዳት እንደሚቻል ከፍ/ሕ/ቁ 2002 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ስለነበረው የንግድ ግንኙነት ሁኔታ እና ከግንኙነቱ ስለመነጨው የገንዘብ ዕዳ በምስክሮች ማስረዳትን የሚከለክል ድንጋጌ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ምስክሮችን በመስማት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ አቅራረብ ስርዓት አይደለም ከማለት በስተቀር የዚህ ዓይነቱን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ተገቢነት የሚያሰጠው የትኛው ሕግ ወይም ድንጋጌ እንደሆነ በውሳኔው አልገለጸም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ ረገድ ለውሳኔ በምክንያትነት የጠቀሰው ነጥብ የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመጨረሻም በዚህ መዝገብ ለክርክር የቀረበው ጉዳይ በግለሰቦች መካከል የሚደረግ የብር 750,000 ግምት ያለው ክርክር በመሆኑ እና የዚህ ዓይነቱ ክርክር ደግሞ ተመርምሮ አልባት ማግኘት የሚገባው የጉዳዩን ዋነኛ ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ በግራ ቀኙ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ለክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥ አግባብነት ካላቸው ህጎች አንፃር በመሆኑ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና ከንግድ ፈቃድና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ጋር ተያይዞ በሰበር ደረጃ በተጠሪ መልስ ላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በዚህ ውሳኔ ላይ ማስፈሩን እና መመርመሩን አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃላል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የስር ተከሳሾች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ ለስር ከሳሽ ሊከፍሉ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ ከላይ በዝርዝር በሰፈሩት ምክንያቶች ሁሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 75752 በ22/09/04 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 107977 በ08/03/04 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ የስር መዝገብ ይመለስ፡፡
4. ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይምለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.79394

ጥቅምት 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አብደላ ኢብራሂም

ተጠሪ፡- አቶ ኡሶ አብዲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በኮምቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃሉ፡- ከተከሳሽ ከአምስት ዓመት በፊት ብር 500 ተበድሬ ገንዘቡን እስከምመልስ ድረስ ተከሳሽ መሬቴን ይዞ እንዲቆይ በመያዣ ሰጥቼው ከሁለት ዓመት በኋላ ገንዘቡን በሽማግሌዎች ፊት ሰጥቼው ከለቀቀልኝ በኋላ የተቀበለውን ገንዘብ ለሽማግሌዎች መልሶ እንደገና መሬቴን በመያዝ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ለቆ እንዲወጣ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- ከሳሽን በወንድምነት ድሬው መሬቱን በስጦታ የሰጠኝ ሲሆን ለመሬቱም ከተከሳሽ የተቀበልኩት ገንዘብ የለም፡፡ በዚሁ መሬት በ1992 ዓ.ም. ጫት ተክየበት ከሁለተኛ ሚስቴ ጋር ስንጋባ የሰጠኂት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክረዋል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ፡- ከሳሽ መሬቱን በመያዣ ስለመስጠታቸው በፍ/ህ/ቁ/2005 መሰረት በጽሁፍ ማስረጃ ያላረጋገጡ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ የስር ከሳሽም በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የይግባኝ ባዩን ይግባኝ በፍብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመዝጋቱ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገን ካራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ለጊዜው በመቸገሩ ምክንያት ብር 500 ተበድረው ይዞታቸውን ለዕዳ ማስያዛቸውን በግራቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 መሰረት የገጠር መሬት ይዞታን አርሶ አደር በዕዳ ለማያስዝ አይችልም፣ በስጦታም ቢሆን በአዋጁ መሰረት የገጠር መሬትን ከቤተሰብ አባል ውጪ አሳልፎ መስጠት የሚቻል አይሆንም በሚል ተጠሪ ከአመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ እንዲመልሱና አመልካችም መሬቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- የሚያከራክረውን ይዞታ አመልካች ለ11 ዓመት ይዤ የቆየሁ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በሚል ያቀረብኩት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገው ተገቢ አይደለም፣ተጠሪው መሬቱን በ1992 ዓ/ም በስጦታ ያስተላለፈልኝ ስለመሆኑ ከማመኑም ሌላ የቀበሌ ኮሚቴዎችና የአካባቢ ሽማግሌዎች አረጋግጠው እያሉ እንድለቅለት የተወሰነው አግባብ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪውም በሰጡት መልስ፡- አመልካች ይዞታውን በስጦታ አግኝቻለሁ ይበል እንጂ የተደረገለት ስጦታ የለም፣ ብር 500 ያበደረኝ ገንዘቡን እስከምመልስ ድረስ መሬቴን በመያዣነት ይዞ ነው፡፡ የገጠር መሬትን በዕዳ ማስያዝም ሆነ ከቤተሰብ አባል ውጪ በስጦታ ማስተላለፍ እንደማይቻል በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 የተደነገገ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ክስ የቀረበበትን መሬት ለቅቀው እንዲወጡ የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በወረዳ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክርና ከቀረቡት የግራ ቀኙ ምስክሮች አመሰካከር የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አመልካች ለተጠሪው ብር 500 በማበደር ለዚሁም የብድር ዕዳ የተጠሪውን መሬት መያዛቸውን ነው፡፡ አንድ ውል የሚጸና ውል ነው ለማለት ሶስት መሰረታዊ የሆኑ ሁኔታዎች እንደሚያስፈልጉ የፍ/ህ/ቁ.1678 የሚደነግግ ሲሆን እነዚህም ሁኔታዎች በድንጋጌው- (ሀ-ሐ) የተመለከቱት፡- ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር ፣ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ መሆንና፣ የውሉ አጻጻፍ ፎርም በህግ በታዘዘ ጊዜ ይህኑ ልዩ ፎርም አሟልቶ መገኘት ናቸው፡፡ ውሉ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንደሚገባው የሚያስገነዝበው በፊደል (ለ) ስር ሲሆን በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ደግሞ ህገ ወጥ ውል (unlawful contract) ይሆናል፡፡ አንድ ውል የተደረገበት መሰረታዊ ጉዳይ ( object of contract) በህግ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ ውሉ በህግ ፊት ምንም ዓይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል (void contract) ይሆናል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት ውል ተጠሪው የገጠር መሬት ይዞታውን በመያዣ በመስጠት ገንዘብ የተበደሩ ሲሆን መያዣ በተሰጠበት በ1992 ዓ.ም. የክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ባለመውጣቱ ተፈጻሚ የነበረው የአዋጅ ቁጥር 89/1989 ነው፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(3) በተሠጠው ትርጉም መሰረት ‹‹ የይዞታ ባለመብት ›› ማለት ማንኛውም አርሶ አደር የገጠር መሬትን ለግብርና ሥራ ለማዋል ፣ለማከራየት እና ይዞታው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ለቤተሰብ አባሉ ለማውረስ የሚኖረው መብት ሲሆን ይህም አርሶ አደሩ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት ማፍራትና ይህንኑ ንብረት መሸጥ፣መለወጥና ማውረስ እንደማይጨምር የተጠቀሰ ሲሆን አርሶ አደሩ የይዞታ መሬቱን በዕዳ እንዲያስይዝ በህግ መብት አልተሰጠውም፡፡ አዋጅ ቁጥር 89/1989 ከተሻረ በኋላ በሥራ ላይ ባለው አዋጅ ቁጥር 456/97 በአንቀጽ 8(2) የገጠር መሬት መብትን አርሶ አደሮች በከፊል አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች እነርሱን በማያፈናቅል መልኩ ሌላ አርሶ አደር ወይም ባለሀብት በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር በሚወጣው አዋጅ የጊዜ ገደብ ከይዞታቸው ላይ ለተፈላጊው ልማት በቂ የሆነ መሬት የማከራየት መብት የሰጣቸው ሲሆን በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 5 ደግሞ ማንኛውም ባለይዞታ የገጠር መሬት የመጠቀም መብቱን ለቤተሰብ አባል የማውረስ መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በዚህ በተጠቀሰው አዋጅም ቢሆን ባለይዞታ የሆነ አርሶ አደር ይዞታውን ላለበት ዕዳ በመያዣነት እንዲያስይዝ ወይም በስጦታ ለቤተሰብ አባል ላልሆነ ሰው ለማስተላለፍ መብት አልተሰጠውም፡፡ አሁን በስራ ላይ ባለው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999ም ቢሆን የገጠር መሬትን በመያዣነት መስጠትም ሆነ ከቤተሰብ አባል ወጪ በስጦታ ማስተላለፍ የማይቻል መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪው ገንዘብ ሰጥተው መሬቱን በመያዣ ከያዙ በኋላ በስጦታ አግኝቻለሁ በሚል ያቀረቡት ክርክር የቤተሰብ አባል መሆናቸውን ባላረጋገጡበት ከመሆኑም ሌላ በህግ ባልተሰጠ መብት የገጠር መሬትን መያዣ በማድረግ ገንዘቡን ያበደሩ ስለሆነ ውሉ ህገ ወጥ

www.abyssinialaw.com

( unlawful contract) ነው፡፡ ህገ ወጥ ውል ደግሞ በፍ/ህ/ቁ/1716 መሰረት በህግ ፊት ውጤት የማይኖረው ፈራሽ ውል ነው፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ምላሽ ማግኘት ያለበት አመልካች ያቀረቡት የይርጋ ክርክር ነው፡፡ አመልካች ይርጋውን መቃወሚያ ያደረጉት ይዞታውን በ1992 ዓ.ም. ይዤ ለ11 ዓመት የጫት ተክል በመትከል የምገለገልበት ነው በሚል ነው፡፡ በእርግጥ የመሬት ይዞታውን ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስ መያዛቸውን ክርክሩ ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/ 43226 የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የፍ/ህ/ቁ/1678፣1716 እና 1718ን በመተርጎም የውሉ መሰረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነውን ወል (unlawful contract) በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን እንደሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑና የግራ ቀኙን ወገኖች የሚያከራክራቸውም ህገ ወጥ(unlawful contract) ውል በመሆኑ የይርጋው ክርክርም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ ክርክር ውድቅ በማድረግ የመያዣ ውሉ ህገ ወጥ ነው በሚል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/132904 በቀን 29/08/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪው የገጠር መሬት ለዕዳ መያዣ በማድረግ የገቡት ውል ህገ ወጥ ውል (unlawful contract) በመሆኑ በህግ ፊት ወጤት ስለማይኖረው ተፈጻሚነት የለውም ሲል የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ወድቅ በማድረግ አመልካች ያበደሩትን ብር 500 ከተጠሪ ተቀብለው በዕዳ የያዙትን የተጠሪውን መሬት እንዲለቁ የወሰነው ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በአፈጻጸም መ/ቁ. 15265 ሲካሄድ የነበረው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

# ከውል ውጭ ኃላፊነት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.77238

ህዳር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም - ነ/ፈ፟ጅ በፍቃዱ መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሤ ረፈራ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ድርጅት ከሳሽነት የተጀመረው በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪም ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- ተከሳሽ የከሳሽ ድርጅት ንብረት የሆነውንና ከአዲስ አበባ ወደ ጅማ የተዘረጋውን ኦፕቲካል ፋይበር የሚባል ኬብል በ1/2 ሜትር ጥልቀት መሬት ውስጥ መቀበሩን እያወቀና እያየ በ10/06/2001 ዓ.ም. ከረፋዱ 4፡30 ሲሆን ይዞታውን በዶማ በመቆፈር መስመሩ እንዲቋረጥ በማድረግ በብር 48,998.72 የሚገመት ጉዳት ያደረሰ ሲሆን ተከሳሽም ጉዳት ማድረሱን በማመን መስመሩን ለመጠገን ሲባል ለጥገና፣ ለባለሙያዎችና ለጉልበት ሠራተኞች እንዲሁም ለትራንስፖርት የወጣውን ወጪ ለመክፈል በ08/07/2001 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ከሳሽ ድርጅትን በመጠየቁ ከሳሽም ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ጨምሮ ብር 48,998.72 እንደሚፈለግበት ቢያሳውቅም ገንዘቡን ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- የወሊሶ ከተማ አስተዳደር በ1997 ዓ.ም. 1,888 ካሬ ሜትር የሆነ የከተማ ቦታ ከነፕላኑ ሲሰጠኝ በአዋጅ ቁጥር 464/1994 አንቀጽ 3(3) መሰረት በሰጠኝ መሬት ውስጥ የከሳሽ ንብረት የሆነው ኦፕቲካል ፋይበር ኬብል መኖሩን ሳላልነገረኝ ማወቅ የምችልበት ሁኔታ የለም፣ መስመሩ ከዋናው መንገድ ከ15 ሜትር በላይ መራቅ እንደሌለበት እየታወቀ 150 ሜትር ርቀት ላይ የተቀበረ ሲሆን በቦታው የተቀበረ ስለመሆኑ ከሳሽ ድርጅት ያደረገው ምልክት የለም፣ጉዳቱን በማመን ደብዳቤ ጽፏል የተባለውም ቢሆን በአገር ንብረት ላይ ደርሷል የተባለውን ጉዳት በተመለከተ በቅንነት የተጻፈ እንጂ እያወቅኩና እያየሁኝ ጉዳቱን አድርሻለሁ በሚል የተጻፈ አይደለም፡፡ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም እንጂ አለብህ የሚያሠኝ በቂ ምክንያት ቢኖር ከሳሽ ያቀረበው የጉዳት ግምት የተጋነነ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ከፍተኛው ፍርድ ቤትም የከተማ አስተዳደር መሬቱን ለተከሳሽ ሲሠጥ የኬብል መስመር ስለመኖሩ የነገረው መሆን አለመሆኑን ማረጋገጫ እንዲልክ ጠይቆ አስተዳደሩም የከሳሽ ድርጅት ካርታ ለከተማው አስተዳደር ያልተሠጠው በመሆኑ ለተከሳሽ መስመሩ ስለመኖሩ ያልተነገረው መሆኑን በመግለጹ ፍርድ ቤቱም ለተከሳሽ በተሰጠውም ፕላን የኬብል መስመር ስለመኖሩ ስላልተገለጸ ተከሳሽ የኬብል መስመሩ በቦታው ስለመኖሩ ያውቅ ነበር ወይም አይቷል ለማለት አይቻልም፣ ተከሳሽ ለከሳሽ በጻፈው ደብዳቤም ጉዳቱን አምኗል በሚል ከሳሽ ያቀረበው ክርክርም ቢሆን ከደብዳቤው ይዘት መገንዘብ የተቻለው መስመሩ ከመንገድ 150 ሜትር ርቆ ያለ በመሆኑ ማወቅ አለመቻሉንና ጉዳቱ የደረሰውም የልማት ሥራ እየተሰራ በመሆኑ ኬብሉ የተጠገነበትን ወጪ እንዲሁም ለባለሙያና ለጉልበት ሰራተኞች ትራንስፖርትን ጨምሮ የወጣውን ልክፈል የሚልና ከሳሽ ያቀረበው የወጪ ግምት የተጋነነ ነው የሚል በመሆኑ ጉዳቱን አምኗል ለማለት የሚቻል አይሆንም ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ በነጻ አሰናብቶታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- በአዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 3(3) የግንባታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በመሬት ውስጥ ኬብል መዘርጋቱንና አለመዘርጋቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት የወሊሶ ከተማ አስተዳደርና የግንባታ ፈቃድ ጠያቂው አካል (የተጠሪው ግዴታ) መሆኑ በግልጽ የተቀመጠውን ድንጋጌ በማለፍ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 49/1989 አንቀጽ 23(1) መሰረት ኬብል ስለመዘርጋቱ የከተማው አስተዳደርም ሆነ ተጠሪው አመልካች ድርጅትን ጠይቀው ማረጋገጥ እንዳለባቸው የተጣለባቸው የህግ ግዴታ ሆኖ እያለ መታለፉ ያለአግባብ ነው፣
- ተጠሪው የልማት ሥራ ሲሠራ በቸልተኝነት ጉዳት ማድረሱን አምኖ ግምቱ ተቀንሶ ለመክፈል መከራከሩ ግልጽ ሆኖ ባለበት በቀረበው ክስ መሰረት አምኗል የሚያሰኝ አይደለም በሚል አመልካች ያቀረብኩትን ክስ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ ፡-

- ከከተማው አስተዳደር በተሰጠኝ ቦታ ኬብል የተዘረጋ ስለመሆኑ የተገለጸልኝ ነገር ባለመኖሩ ተጠሪው በመሬት ውስጥ ኬብሉ የተዘረጋ ስለመሆኑ የማወቅ ግዴታ አለበት በሚል አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣
- በሥር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ያመንኩት ጉዳት መድረሱን እንጂ ጉዳቱ የደረሰው በተጠሪው ጥፋት ነው በሚል አይደለም፣ሲል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡-

- ተጠሪው በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም?

- ተጠሪው ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት ቢባል የሚከፍለው የኪሳራው መጠን ምን ያህል መሆን አለበት? የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አንደኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪው የከተማው አስተዳደር በሠጠው የከተማ ቦታ ቁፋሮ ሲያካሂድ የአመልካች ንብረት የሆነው ኦፕቲካል ፋይበር ኬብል መቁረጡን ነው፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤቶች በንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪው ኃላፊነት የለበትም በሚል የወሰኑት ለተጠሪው በተሠጠው ፕላን ላይ ኬብል ስለመኖሩ የተደረገ ምልክት የለም፣ የከተማው አስተዳደርም መስመሩ ስለመኖሩ ለተጠሪው የገለጸው ነገር ባለመኖሩ እያወቀ ወይም እያየ ጉዳት አድርሷል ለማለት አይቻልም በሚል ነው፡፡ እነዚህን ፍርድ ቤቶቹ የጠቀሱአቸውን ምክንያቶች የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌትሪክ ሀይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 464/1997 እና አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች አንጻር መመርመር የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ አዋጅ ቁጥር 464/1997 በአንቀጽ 3(3) ሥር የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳደር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን ወይም የኤሌትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እና ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታ ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌው በቴሌኮሙኒኬሽንና በአሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ በግንባታ ወቅት ጉዳት እንዳይደርስ አስቀድሞ እንዲያረጋግጡ ግዴታ የጣለው በፌዴራልና በክልል አስተዳደር አካላት ብቻ ሳይሆን የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ላይ ጭምር ነው፡፡ ተጠሪውም በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽን አውታር ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የተጣለበትን አስቀድሞ የማረጋገጥ ግዴታ ሳይወጣ ቦታውን በቸልነኝነት በመቆፈሩ ምክንያት ጉዳቱ ሊደርስ ችሏል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ እያወቀም ሆነ በቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰው የሚቀጣ ስለመሆኑም ተደንግጓል ፡፡

ወደ ፍትሐብሄር ህጉ ስንመለስ አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ሳይኖር በራሱ ጥፋት(አስቦ ወይም በቸልተኝነት) በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ኃላፊ እንደሆነ በቁጥር 2027(1) ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም በህግ በትክክል ተገልጾ የተመለከተውን ልዩ ድንጋጌ፣ ልዩ ደንብና ሥርዓት የጣሰ ሰው ደግሞ ጥፋተኛ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ህ/ቁ 2035(1) ተመልክቷል፡፡ በአዋጁም ሆነ በፍትሐብሔር ህጉ በዚህ መልኩ ተደንግጎ እያለ ተጠሪው ጉዳት ማድረሱን ባልካደበት ጉዳት የደረሰበት ኬብል በቦታው ስለመኖሩ ለተጠሪው የከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት አላስታወቀም፣ እንዲሁም አመልካች ድርጅት በቦታው ላይ ያደረገው ምልክት የለም የሚሉትን ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች በመጥቀስ በተጠሪው የተጣለበትን የህግ ግዴታ ባለማገናዘብ ድርጊቱን የፈጸመው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ስለመሆኑ ስላልተረጋጠ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም ሲሉ የወሰኑት በአዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 3(3) የተደነገገውን እና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የፍትሐብሄር ህግ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ማንም ሰው ከራሱ ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረገው ጉዳት ኪሳራ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በፍ/ህ/ቁ/2028 በአስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገ ሲሆን ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ መሆኑ በህግ የታወቀ ሰው ደግሞ የሚከፍለው የጉዳት ካሳ መጠን ኃላፊነቱ ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ በማመዛዘን ስለመሆኑ ከፍ/ህ/ቁ 2090(1) እና 2091 ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው በአመልካች የኬብል መስመር ላይ ጉዳት ማድረሱን በማመን ልዩ ልዩ የጥገና ወጪዎችን ለመክፈል በጻፈው ደብዳቤ ከአመልካች በኩል የቀረበው የኪሳራ መጠን የተጋነነ መሆኑን ስለመግለጹ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የደብዳቤውን ይዘት በፍርድ ላይ ካሰፈረው መገንዘብ የተቻለ ከመሆኑም ሌላ ተጠሪው ከሥር ጀምሮ ባደረገው ክርክርም የጉዳቱ መጠን ግምት የተጋነነ መሆኑን በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪው በአመልካች በኩል የቀረበውን የኪሳራ መጠን ግምት እስከተቃወመ ድረስም ግምቱ የተጋነነ ነው የሚልበትን ምክንያት እና አመልካችም ለግምቱ ምክንያት ያደረጋቸውን ሁኔታዎች የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን መወሰን የሚገባ ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱን ባልካደበት ተጠሪውን ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም በሚል በነጻ ያሰናበቱት በአዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 3(3) የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ግንባታ ከማከናወኑ በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን እና የኤሌትሪክ አውታሮች ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የተደነገገውን እንዲሁም ከውል ወጪ ኃላፊነት ሊከተል ስለሚችልበት ሁኔታ በፍ/ህ/ቁ/2027(1)፣ 2028፣ እና 2035 የተደነገጉትን ሁኔታዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/21371 በቀን 07/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/112894 በቀን 28/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪው በአመልካች ንብረት ላይ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡ ስለሆነም በደረሰው የጉዳት መጠን ላይ የግራ ቀኙን ወገኖች በማከራከርና የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማት፣ እንዲሁም ተገቢ ሆኖ ከተገኘም በገለልተኛ ባለሙያ በማጣራት በጉዳዩ ላይ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

# የዳኝነት ሥልጣን

የሰ/መ/ቁ. 77479

ጥቅምት 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢት/ያ ኦርቶዶክስ ቅድስት ሥላሴ መንፈሣዊ ኮሌጅ ነገረ ፈጅ ፀዳለ ዳና

ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አሰገድ ሣህሉ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ግራ ቀኙን ያከራከረው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ሲባል በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ሲሆን ፍሬ ቃሉም፡- ለ2003 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የዲግሪ ፕሮግራም መሥፈርት አሟልቼ ትምህርቱን እየተከታተልኩ እያለ፣ ማስታወቂያ በወጣበት ጊዜ ያልነበረነ መሥፈርት መሠረት በማድረግ ወደ ማታው የትምህርት ፕሮግራም ያዛወረኝ ከመሆኑም በላይ የአባልነት ማስረጃ በአጥቢያ ቤተክርሲቲያን ማቅረቤ እየታወቀ ትክክለኛ ማስረጃ አላቀረብክም በማለት እንዲሁም ለብዙ ቀናት በትምህርት ገበታ ላይ አልተገኘህም በሚሉ ምክንያቶች ትምህርቴን እንዳቋርጥ ስለወሰነ ትምህርቴን እንድቀጥል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ኮሌጁ የኢት/ያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክስቲያን እምነቷን ለማስፋፋት እና አማኞቿን ለማስተማር ሲባል የተቋቋመ ኃይማኖታዊ ኮሌጁ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ፍ/ቤት ውሣኔ ለመስጠት አይችልም፡፡ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን አለው ከተባለ በሃይማኖታዊ ጉዳዩ ጣልቃ እንደመግባት ይቆጠራል ስለዚህ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ስለሌለው መዝገቡ ይዘጋልኝ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ካስቀደመ በኃላ በአማራጭም ከሣሽ ላቀረበው የፍሬ ጉዳይ ክርክር የበኩሉን ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ስልጣንን በሚመለከት የቀረበው ክርክር ተመልክቶ የኮሌጁ ዋና ዓላማ መንፈሣዊ ትምህርት መስጠት የመሆኑ እውነታ

www.abyssinialaw.com

ብቻውን ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ከመወሰን ሊያግደው የሚችል አይደለም፡፡ ከሣሽ ከትምህርት ገበታው የተሰናበተው በአግባቡ ነው ወይስ አይደደለም? የሚለውን ጉዳይ የግለሰብ መብትን ከህገ መንግስቱና ከሌሎች ህጐች አንፃር ማስከበር መሆኑን ስለሚያመለክት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ የሚል ብይን ከሰጠ በኃላ በመቀጠልም ከሣሽ ቤተክርስትያኗ አስተምሮት ወጥና አራማጅ ነው ወይስ አይለም? ለምልመላ የሚያበቃውን ማስረጃ ከትክክለኛው የሰበካ ጉባኤ አቅርቧል ወይስ አልቀረበም? ከትምህርት ገበታው ስለመቆየቱ ተረጋግጧል ወይስ አልተረጋጠም? በሚሉት አከራካሪ ነጥቦች ላይ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ሐምሌ 07 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የኢት/ያ ኦርቶዶክስ ቤተክስርስቲያን የማትቀበለውን ትምህርት ከሣሹ ስለሚያራምዱ በተከሣሽ ምስክሮች በሚገባ አልተረጋገጠም፡፡ ለምለመላ አስፈላጊ የሆነው የደብር ማስረጃ ከሣሹ ካቀረበ በኃላ በማታለል መሆኑ ተገልፆ የተሰረዘው ከሣሹ ከትምህርት ከታገደ በኃላ ስለሆነ ለማገዱ ተግባር መሠረት ነው ለማለት የማይችል በመሆኑ በላይ በሥራ ኃላፊ በሚፃፍ የዘፈቀደ ደብዳቤ የተማሪ የመማር መብት ሊገደብ አይገባም እንዲሁም ከትምህርት ቀርቷል ተባለ እንጂ ለመቅረቱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም ከሣሹ የማታ ትምህርቱን እዲቀጥል ይደረግ በማለት ዳኝነት ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን የይግባኝ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እንደተደነገገው ከላይ የተመለከተው ፍርድ ጉድለት ያለበት ባለመሆኑ ተጠሪን መጠራት አያስፈለግም በማለት መዝገቡን ዘግቶ አመልካችን አሰናብቶታል፡፡ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም አመልካች በዚህ የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚላቸውን ነጥቦች በመዘርዘር የሰበር አቤቱታውን በማቅረቡ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ነጥብ በመመለከት ተጠሪው ቀርቦ ክርክሩን እንዲያሰማ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የአሁን ተጠሪ ተከሣሹ ኮሌጅ በእራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለሆነ ሊከስም ሊከሰስም ስለሚችል በስልጣን ረገድ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ፍርድ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልሱን በፅሑፍ ያቀረበ ቢሆንም ይዘቱ በሰበር ቅሬታው ከገለፀው የተለየ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ በቀደም ተከተል የተጠቀሰው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ መደበኛ ፍ/ቤቶች በክሱ ደረጃ የቀረበላቸውን ጉዳይ ተቀብለው ወደ ዋናው የክርክር ይዘት ዘልቀውበት ከመግባታቸው በፊት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በቅድሚያ የመመርመርና የማየት ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ ኢት/ያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ሥር ተደንግጓል፡፡ ዝርዝር ህግ በሆነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4 ላይም ቢሆን መደበኛ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ማናቸውም ጉዳይ ያለገደብ ተቀብለው ለማስተናገድ የሚያስችል ስልጣን እንደሌላቸው ተመልክቷል፡፡

ከዚህ በቀር አንድ ሰው በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰን የሚችለው ከህግ የመነጨ መብት ያለው መሆኑን በክሱ ዝርዝር በፍሬ ነገር ደረጃ ማመልከት የቻለ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(2) ተደንግጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ አንፃር አሁን የቀረበውን ጉዳይ ስንመለከት ከሣሹ የአሁን ተጠሪ ለትምህርት ከገባበት ኮሌጅ ያለአግባብ የተሰናበት ስለመሆኑ ገልፆ ከቀረበው የፍሬ ጉዳይ ክርክር አንፃር ማጣቀሻ ሊሆን የሚችል የአገሪቱ የህግ ማእቀፍ አካል የሆነን ህግ መሠረት አድርጎ ክርክሩን አላቀረበም፡፡

በፍ/ቤት ሊከበር የሚችል መብት በሌላ የዳኝነት አካል እንዲታይ ካልተደረገ በቀር ከህግ የመነጨ መብት ሊሆን እንደሚገባ ከላይ እንደተመለከተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(2) በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ይልቁንም ክስ የቀረበበት ኮሌጅ ከተቋቋመበት ዓላማ፣ በኮሌጁ ከሚሰጠው የትምህርት ይዘት ይህንንም መነሻ በማድረግ ለተማሪነት ማንን እንደሚመለምል፣ለምልመላው ማሟያ የሆኑ መስፈርቶች፤ እነዚህ መስፈርቶች መሟላትና አለመሟላታቸውን በኮሌጁ ትምህርት ተካፋይ የሆኑ ተማሪዎች በትምህርት አቀባበል ሂደት ሊገልጿቸው ስለሚገቡ የዲሲፒሊን ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ ኮሌጆችን ለአቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን የተተው ከመሆኑ በቀር ይህንን ጉዳይ ሁሉ ሊሸፍን የሚችል ዝርዝር ህግ በህግ አውጭው በኩል የተቀረፀ አይደለም፡፡

የተለያዩ ሙያዎችንና ክህሎቶችን ለማስረጽ እንዲቻል በሚል የተቋቋሙት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንኳ ለትምህርት ነፃነት ሲባል በተመሣሣይ ከላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች አስመልክቶ ክርክር ቢነሣ እንኳ እንደማናቸውም ጉዳይ ያለገደብ በፍርድ ቤት ቀርበው ሊታዩ የማይችሉ ጉዳዮች እንደሆኑ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 ለአብነት ማሣያ ነው፡፡

ስለሆነም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከትምህርት ገበታው የተሰናበተው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የግለሰብ መብቱን ስለሚመለከት ከህገ መንግስቱ አንፃር ማስከበር ስለሆነ የሚለውን ትርጉም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 የግለስብ ፍትህ የማግኘት መብት በፍርድ ሊያልቁ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑ ተገልፆ የተደነገገ መሆኑን ያላገናዘበና ከሌሎች ህጐች አንፃር በሚል በደፈናው ከመግለጽ ውጭ በየትኛው የህግ ዘርፍ ሥር እንደተመለከተም ያልተገለፀና ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተውም የግራ ቀኙን ጉዳይ የሚገዛ በህጋችን ማእቀፍ የተካተተ ዝርዝር ህግ የሌለ ከመሆኑ አንፃር ሁሉ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 36114 በ24/7/2003 እና በሐምሌ 07/2003 ዓ.ም የተሰጡት ብይን እና ፍርድ ተሽረዋል፡፡
2. የከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በኮ/መ/ቁ. 115269 በ28/03/2004 የሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት የሆነውም ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
3. ከሣሽ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 እንደተደነገገው በፌዴራል ፍ/ቤቶች አማካኝነት በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 43511

ጥቅምት 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የሟች የአቶ ዋሲሁን መኮንን ሚስትና ወራሾች

1. ወ/ሮ ወ/ጻዲቅ ደሜ
2. ወ/ሮ መሰረት ዋሲሁን
3. አቶ ተስፋዬ ዋሲሁን
4. አቶ አበበ ዋሲሁን
5. ወ/ሪት ፋሲካ ዋሲሁን
6. ወ/ሪት የሺመቤት ዋሲሁን
7. አቶ ተሾመ ዋሲሁን
8. ወ/ሪት ሃና ዋሲሁን

ወኪል ጌትነት ዋሲሁን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጄንሲ - ነ/ፈጅ ጌታቸው ምንተስቶት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንግድ ቤት ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጄንሲ ሲሆን በዚህ አካል አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኑ አመልካቾች አባት ሲሆኑ ጊዜውም ጥቅምት 13 ቀን 1988 ዓ/ም ነው፡፡ የአመልካቾች አባት አቤቱታ ይዘት ሲታይም በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 7፣ ቀበሌ 34፣ የቤት ቁጥር 703 የሆነውን ንግድ ቤት በደርግ መንግስት ከአዋጅ ውጪ የተወሰደባቸው መሆኑን ገልጸው ንግድ ቤቱ እንዲመለስላቸው ይወሰን ዘንድ መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ከአቤቱታቸው ጋርም የቤቱን ባለሃብትነትና ቤቱ ከአዋጁ ውጪ ስለመወረሱ ያሳያሉ ያሏቸውን በርካታ የሰነድ ማስረጃዎች አያይዘው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ኤጀንሲም የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት አቤቱታ ስለቀረበበት ንግድ ቤት በዝርዝር መግለጫ በማዘጋጀትና ከመስሪያ ቤቱ ሕጋዊ ውክልና በተሰጠው ሰው አማካኝነት ምላሽ እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ በወቅቱ በሰጠው ምላሽ ንግድ ቤቱ በመንግስት እጅ ያለ መሆኑን በመግለፅ ነገር ግን በምን ሁኔታ ሊወረስ እንደቻለ ማረጋገጫ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ መልስ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አቤቱታ የቀረበለት ኤጀንሲ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ምላሽ በመመልከትና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ጉዳዩን ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን

www.abyssinialaw.com

መርምሮ አቤቱታ የቀረበበት ንግድ ቤት ለአመልካቾች አባት እንዲመለስላቸው ሲል በመ/ቁጥር 20/ነ2/497/9987/93 በቀን 15/05/1993 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ በወቅቱ ስያሜ ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ተብሎ የሚታወቀው አካል በመሰል ጉዳዮች የይግባኝ ስልጣን ለአለው የፕራይቬራይዜሽን ቦርድ ይግባኙን አቅርቦ ቦርዱም ጉዳዩን አመልካቾች በሌሉበት አይቶ ንግድ ቤቱ ለአመልካቾች አውራሽ እንዲመለስ በማለት የተሰጠውን የኤጀንሲውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም የሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የኤጀንሲው ቦርድ ውሳኔ አስተዳደራዊ ከመሆኑ ባሻገር ይህንን አስተዳደራዊ ውሳኔ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል ወይም አልተፈጸመበትም ለማለት ችሎቱ ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት ወደ ፍሬ ጉዳዩ ሳይገባ መዝገቡን ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ዘግቶታል፡፡

ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስነሳ ነው በማለት ለሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ ጥያቄ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ያጡ ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርበው ምክር ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ የኤጂንሲው ቦርድ ዳኝነት መሰል አካል (Quasi judicial body) በመሆኑና ይህ አካል የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዳኝነት ስልጣኑ ማየት እንደሚችል በመግለጽ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣ 803(ሀ))፣ አዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 2(3)፣ 5(3) እና አዋጅ ቁጥር 87/86 አንቀፅ 8(5) ድንጋጌዎች በዋቢነት በመጥቀስ ጉዳዩን ሰበር ችሎት እንዲመለከተው በሙሉ ድምጽ በመወሰን ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ የሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 87/1986 አንቀጽ 8(5) መሰረት የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔው ላይ ለመድረስ የተከተለው አካሄድ የሕግን አግባብ የተከተለ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ ሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደሌለውና የኤጀንሲው ቦርድ ጉዳዩን በይግባኝ ሲመለከት የተከተለው አካሄድም አግባብነት ያለው መሆኑን ጠቅሶ እንዲሁም አከራካሪው የንግድ ቤት ለአመልካቾች የሚመለስበት ሕጋዊ አግባብም እንደሌለ ዘርዝሮ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ጉዳዩን የሰበር ችሎት ለመዳኘት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የመነጨ ስልጣን ያለው መሆኑን ጠቅሰውና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? እና፣
2. ከተባለስ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ስርዓቱን የተከተለ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ሁነው አግኝቷቸዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ ቦርድ ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘትና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ምክንያት የካቲት 09 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ለሰበር ችሎቱ አቅርበው አጣሪው የሰበር ችሎት የኤጀንሲው ቦርድ የሚሰጠው ውሳኔ አስተዳደራዊ በመሆኑ ጉዳዩ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይም አልተፈፀመም ለማለት ችሎቱ ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት መዝገቡን ዘግቶት ጉዳዩ እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ደርሶ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጉዳዩን መርምሮ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው መሆኑን በመዘርዘር የወሰነና ጉዳዩ በችሎቱ እንዲታይ የመለሰ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 62(1) መሰረት ሕገ መንግስትን የመተርጎም ስልጣን ያለው አካል ሲሆን የዚህን አካል ስልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀፅ 3(1) ስርም ህገ መንግስትን የመተርጎም ስልጣን የምክር ቤቱ መሆኑ በግልጽ ሰፍሯል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 56(1) ስር ደግሞ ምክር ቤቱ በቀረበለት ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስርም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ውሳኔውን የማክበርና የመፈፀም ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ተቀምጧል፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከላይ በተገለፁት የሕግ ማዕቀፎች በተሰጠው ስልጣን መሰረት አመልካቾች ያቀረቡትን ጥያቄ መርምሮ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ዘርዝሮ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ለጉዳዩ የመጨረሻ ሲሆን በዚህ ችሎትም ሆነ በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት መከበርና መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 56 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ነገረ ፈጅ ይህ ችሎት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት የሚያቀርቡት ተቃውሞ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የሠጠውን ውሳኔ ይዘትና የአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀፅ 56 ድንጋጌን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ ቦርድ የኤጂንሲውን ውሳኔ የሻረው የአሁኑን አመልካቾችን ጠርቶና ተገቢውን ክርክርና ማስረጃ እንዲያስሙ በማድረግ ያለመሆኑን ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ይህ የኤጀንሲው ቦርድ አካሄድ በአዋጅ ቁጥር 87/1986 እና ይህንኑ አዋጅ ተከትሎ በወጡትና ስራ ላይ በነበሩት የቦርዱ መመሪያዎች ተገቢ ነው በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 87/1986 በአንቀጽ 8 ስር የኤጀንሲውን ቦርድ ስልጣንና ተግባር የዘረዘረ ሲሆን በተጠቃሹ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አምስት ስር የኤጀንሲውን ውሳኔ በሚመለከት ከማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚቀርብለትን ይግባኝ ሕጋዊነቱን መርምሮ መወሰን ከስልጣንና ተግባራቱ አንዱ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡ ይህ ድንጋጌ የኤጀንሲው ቦርድ ይግባኙን ሲመረምር ሊከተለው ስለሚገባው ስነ ስርዓት በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ ይሁን እንጂ የአዋጁ አንቀጽ 9 የቦርዱ ስብሰባ የሚመራበትን ስርዓት የሚደነግግ ሲሆን ስብሰባው የሚመራበትን ደንብ ቦርዱ ሊያወጣ እንደሚችል ደግሞ በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር

www.abyssinialaw.com

አራት ድንጋጌ ስር ያስቀምጣል፡፡ ይህ አካል ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል እንደመሆኑ መጠን የሚሰጠው ውሳኔ የተፈጻሚነት ኃይል ያለው ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በመ/ቁጥር 63627 በቀረበው ጉዳይ ላይ ሰጥቶታል፡፡ ቦርዱ ከፊል ውሳኔ ሰጪ አካል እንደመሆኑ መጠን የሚሰጠው ውሳኔ የሕጉን ስርዓት ተከትሎ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠለት የክርክር አመራርና አሰጣጥ ስርዓት እስከሌለ ድረስ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት የተጠበቁትን ፍትህ የማግኘት፣ የመሰማትና በእኩል ሚዛን የመታየት መብት ሊያከብር ይገባል፡፡ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሊጠበቁ ከሚገባቸው ሕገ መንግስታዊ መብቶች አንዱ ደግሞ ክርክር የማቅረብና ማስረጃ የማሰማት መብት ነው፡፡ ይህ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የግድ ከሚላቸው የስነ ስርዓት አካሄዶች አንዱ ነው፡፡ ክርክሩን በአግባቡ እንዲያቀርብ እድል ያላገኘ ሰው በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 የተከበረለት ፍትህ የማግኘት መብቱ ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የመሰማት መብት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሊከበር የሚገባው መብት ነው፡፡ የመሰማት መብት ከመጀመሪያው ክርክር ጀምሮ እስከመጨረሻው የዳኝነት ሰጪ አካል መከበር ያለበት ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱና ስለ ክርክር አመራር በተደነገጉት እንደፍትሐብሔር ስነ ስርአት አይነት ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ የሆነ መደበኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያላቸው አካላት በይግባኙ የክርክር ሂደት የተከራከሪ ወገኖችን የመሰማት መብት ሳያከብሩ ውሳኔ የሚሰጡበት ሂደት መኖር እንደሌለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337፣ 338፣ 339 እና ከሌሎች ስለ ማስረጃ አቀራረብ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ ጉዳዩን በይግባኝ ሲመለከት አመልካቾች በአካል አስቀርቦ የመሰማት መብታቸውን በመጠበቅ ጉዳዩን የመረመረ ስላለመሆኑ ተጠሪም የሚክደው ፍሬ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የኤጀንሲው ቦርድ የአፈጻጸም መመሪያ 001/88 አንቀፅ 8.1 እስከ 8.6 እና ከአንቀጽ 9.1 -9.4.3 እንዲሁም 11.4 ስር ባሉት ድንጋጌዎች የአቤቱታ አመዘጋገብ፣ ማጣራትና ውሳኔ አሰጣጥ እንዴት መሆን እንዳለበት በዝርዝር የተቀመጠ በመሆኑ የኤጀንሲው ቦርድ የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን የፍርድ አሰጣጥ ስነ ስርዓት ባለመከተሉ ብቻ የሕግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት አይቻልም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠቃሹ መመሪያ ምንጭ ማድረግ ያለበት አዋጅ ቁጥር 87/87 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሲሆን በዚህ ረገድ የክርክር አመራርን በተመለከተ ስነ ስርዓት ሕጉን ቦርዱ እንደሚያወጣ የሚያሳይ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 9 የአማርኛ ቅጂው ርእሱ "የቦርዱ ስብሰባ" በሚል የተቀረፀ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ "Meetings of the board" በሚል የተቀመጠ እና በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር አራት ድንጋጌ ስር ደግሞ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል ተብሎ መደንገጉን የድንጋጌው የአማርኛ ትርጉም ሲያሳይ፣ የእንግሊዝኛው ትርጉምም "The Board may determine its own rules of procedure." በሚል ሰፍሯል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አዋጁ የይግባኝ ክርክር አመራር ስርዓትን በተመለከተ ግልፅ የሆነ ድንጋጌ ያላስቀመጠና ለቦርዱ ደንቡን እንዲያወጣ ስልጣኑን የሰጠውም የራሱን ስብሰባ በተመለከተ እንጂ የክርክር አመራሩን፣ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት ሂደትንና አተገባበሩን በተመለከተ ያለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አለ የሚለው መመሪያ በይግባኝ ክርክር ሂደት ሊሰሙ የሚገባቸውን ሰዎችን መብታቸው ሳይጠበቅ እንዲያልፍ ለማድረግ ሥልጣን ባለው አካል የወጣ ነው ለማለት የማያስችልና መመሪያው ስልጣን ባለው አካል የወጣ ነው ቢባል እንኳ ይዘቱና መንፈሱ

www.abyssinialaw.com

ሲታይ የክርክር አመራሩ ሂደት የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን የሚገድብ ሳይሆን ቦርዱ ጉዳዩን ሕጋዊ ስርዓቱን በመጠበቅ ለራሱ አሰራር አመቺ ነው ባለው መንገድ እንዲመራ ለማስቻል ነው ተብሎ የሚታመን ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የሚከናወን የክርክር አመራር በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 37 እና ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የተከበረውን ፍትህ የማግኘት እና የመሰማት መብቶችን የመሸርሸር ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አካሄድ አይደለም፡፡ የኤጀንሲው ቦርድ ይግባኙን የተመለከተውና ውሳኔ የሰጠው የአመልካቾችን የመሰማት መብት ሳያከብር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ስለ ክርክር አመራር በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተደነገገውን ስርዓት የጣሰ ሲሆን በክርክር አመራር ሂደት የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን ያለመጠበቅ ደግሞ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ በመሆኑም የኤጀንሲው ቦርድ ይግባኙን የተመለከተው ሕጋዊ ስርዓትን ተከትሎ ባለመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግሰት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ በጉዳዩ ላይ ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ/ም በቀድሞው ወረዳ 7 ቀበሌ 34፣ ቁጥር 703 የሆነ ንግድ ቤት ለአመልካቾች አውራሽ አቶ ዋሲሁን መኮንን እንዳይመለስ በማለት የሰጠው ውሳኔ የአመልካቾች የመሰማት መብት ሳይጠበቅ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሸሯል፡፡

2. የፕራይቬይታዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ በመ/ቁጥር 20/ነ2/497/9987/93 በቀን 15/05/1993 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ 9ተገቢ መሆን ያለመሆኑን አመልካቾች ባሉበት አጣርቶና የአመልካቾችን የመሰማት መብት በሕጉ አግባብ በመጠበቅ እንዲመለከተውና ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 75034

ህዳር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ - ነ/ፈጅ መስፍን አበበ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መኮንን ተክሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከአቃቤ ሕግ ሙያ ጋር ተያይዞ የተነሳውን የስራ መደብና ቦታ ዝውውርን መቃወምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረቱት ክስ ይዘት ሲታይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት በአቤቱታ ምርመራና ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት በምርመራና ክስ ኤክስፐርትነት የስራ መደብ ታክስን ጨምሮ ብር 4,210.00 ደመወዝ እየተከፈላቸው ለሁለት አመታት ያገለገሉ መሆኑን፣ የአካል ጉዳተኛ መሆናቸውንና በ2002 ዓ.ም እና 2003 ዓ/ም በተደረገ የስራ አፈጻጸም ግምገማ የላቀ የስራ አፈጻጸም ውጤት ያላቸው መሆኑን ገልጸው አመልካች ያላግባብ ወደ ልደታ ክፍለ ከተማ ንቃተ ሕግ መፍጠር ንኡስ የስራ ሂደት ተጠሪ ተዛውረው በሕግ ኤክስፐርትነት እንዲሰሩ በማድረግ ከቀድሞው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ብር 425.00 እንዲቀነስ በማድረጉ ከሕግ ውጪ የተደረገና የተከናወነ ተግባር ነው፣ መድሎም ተፈጽሟል ተብሎ እና አንባቢ ተመድቦላቸው ወደ ቀድሞው ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም አመልካች ዝውውሩን ለመፈጸም ስልጣን እንደአለውና ጉዳዩም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሊታይ የማይገባው እና በከተማው ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር እንደሚወድቅ ገልጾ ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲዘጋ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ የተሻለ ውጤት ሊያስመዝገቡ ይችላሉ ተብሎ በታመነው የስራ መደብ ላይ እንዲመደቡ መደረጉንና በደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ረገድም የስራ ቦታው የትራንስፖርት አበል የማያስፈልገው በመሆኑ ምክንያት ይኸው አበል ከመቀነሱ ውጪ የተቀነሰ ደመወዝ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በቃል ክርክር ወቅት ከአዋጅ ቁጥር 568/2000 አንጻር የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደአለው ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 568/2000 መሆኑና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 2(7) ስር ደግሞ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት የሚችል መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ መደንገጉን ጠቅሶ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ተቃውሞ ያለፈው ሲሆን ፍሬ ነገሩን መርምሮም የተጠሪ ዝውውር በአድሎአዊ

ተግባር የተፈጸመ ሳላለመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 7(2) ድንጋጌ መሰረት የማስረዳት ሸክሙን አልተወጣም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ዝውውሩን ሽሮ ተጠሪ ቀድሞ ይሰሩበት ወደ ነበረው ቦታና የምርመራና ክስ ኤክስፐርትነት የስራ መደብ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በፍርድ ቤቱ የታየው ከስልጣኑ ውጪና ባልተረጋጠ ፍሬ ነገር ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁጥር 568/2000 መሰረት በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው በማለት ያቀረበው ተቃውሞ ታልፎ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዓቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 24/1999 መሰረት አስተናግደው ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በፍርድ የሚያልቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት የሚሰሩት በአቃቤ ሕግነት ሙያ መሆኑን፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ ከሚሰሩበት፤ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የፍትህ ጽ/ቤት የአቤቱታ ምርመራና ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት በምርመራና ክስ ኤክስፐርት የስራ መደብ ወደ ልደታ ክፍለ ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት ንቃተ ሕግ መፍጠር ንዑስ የስራ ሂደት አመልካች ያላግባብ አዛውሯል፣ ከቀድሞው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ብር 425.00 እንዲቀንስ በማድረጉ ዝውውሩ ከሕግ ውጪ ነው፣ አካል ጉዳተኛ በመሆኔም መድሎ ተፈጽሟል በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ በአቃቤ ሕግነት ተሹመው የሚሰሩ መሆኑን ሳይክድ ዝውውሩ ስራና ሰራተኛን ለማገናኘት የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሊታይ እንደማይገባና በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ወይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የሚታይ መሆኑን ገልጾ መከራከሩን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በአቃቤ ሕግነት ተሹመው የሚሰሩ የአመልካች ሰራተኛ መሆናቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን ክስ ለመዳኘት የቻሉት የአዋጅ ቁጥር 568/2000 አንቀጽ 2(7) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ፍርድ ቤት ማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ወይም የክልል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 10(1) ስርም በአዋጁ ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ባለመከበራቸው ምክንያት መብቱ የተነካበት ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ ወይም አካል ጉዳተኛ አባል የሆነበት የአካል ጉዳተኞች ማህበር ወይም አካል ጉዳተኛው አባል የሆነበት የሰራተኛ ማህበር ወይም አዋጁን የሚያስፈጽም አግባብ ያለው አካል ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ እንደሚችል የተቀመጠ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 3 ደግሞ አዋጁ በማንኛውም ስራ ፈላጊ አካል ጉዳተኛ ወይም አካል

www.abyssinialaw.com

ጉዳተኛ ሰራተኛና በአሰሪ መካከል በሚኖር የስራ ስምሪት ግንኙነት ላይ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ተደንግጓል። እንዲሁም አዋጁ የአካል ጉዳተኞችን የስራ መብት መጠበቁና አድሎም መከልከሉን እንደ ቅደም ተከተላቸው በአንቀፅ 4 እና 5 ስር በዝርዝር አስቀምጧል። እንግዲህ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያሳዩት በሹመት የሚያዙ የስራ መደቦችን ሁሉ በተመለከተ በአዋጁ ለመግዛት የታሰበ ያለመሆኑን ነው። ይህ ማለት ግን በአዋጁ የተቀመጡት የአካል ጉዳተኛ መብቶችን ተሿሚ የሆነውን አካል ጉዳተኛ የሚያስተዳድረው አካል ሊያከብራቸው አይገባም ማለት አይደለም። በመሆኑም ተሿሚ የሆነውን የአካል ጉዳተኛ ጉዳይ በአዋጁ አንቀጽ 2(7) መሰረት ፍርድ ቤት ሊመለከተው ይገባል ከተባለ በተለይም በዳኝነት ስራ ወይም በአቃቤ ሕግነት ስራ የተሰማሩትን አካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በዚህ ረገድ በሕግ አግባብ የተቋቋሙት አካላት እንዳይመለከቱ የማድረግ ውጤትን የሚያስከትል ነው። ስለሆነም አዋጅ ቁጥር 568/2000 ስለ አካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት የወጣ አዋጅ ሁኖ በአዋጁ፣ አግባብ ባለው ደንብና መመሪያ የተከበሩ መብቶችን የሚነካ ተግባር ሲፈጸም በፍርድ የሚያልቅበት አግባብ ያለ መሆኑን የሚደነግግ ቢሆንም ተሿሚ የሆኑ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ግን ጉዳዩ በፍርድ ቤት ክስ የሚቀርብበት ሳይሆን በዚህ ረገድ በሕግ ተለይተው ለተቋቋሙት አካላት የሚቀርብና እነዚህ አካላትም አዋጁንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሰረት አድርገው ጉዳዩን የሚያስተዳደሩበት ስለመሆኑ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ የምንረዳው ጉዳይ ነው።

ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ባለው የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዐቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 24/1999 አንቀፅ 2(4) ዐቃቤ ሕግ ማለት በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር የፍትህ አስተዳደር እንዲያገለግል በደንቡ አንቀጽ 4 በተመለከቱት ደረጃዎች በአንዱ የተሾመ ሰራተኛ መሆኑን ትርጉም የተሠጠበት ጉዳይ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 አንቀጽ 2(5(ሐ)) ድንጋጌ ሲታይም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ዳኞችና አቃቢያነ ሕግን እንደማያካትት የተደነገገ ሲሆን የእነዚህ ባለሙያዎችን ጉዳይ በተመለከተ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት የሚያስተናግድበት አግባብ አይኖርም። ከእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች በግልጽ መረዳት የሚቻለው የአቃቢያነ ሕግ ስራ የሚገኘው በሹመት መሆኑን ሲሆን ጉዳዩን የሚገዛው የተለየ ሕግም በደንብ ቁጥር 24/1999 ወጥቶ ስራ ላይ ያለ መሆኑንና ይህ ደንብ በሕግ አግባብ ያልተለወጠ መሆኑን ነው። ደንቡ የዐቃቤነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ መቋቋሙን በአንቀፅ 44 በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን በአንቀጽ 46 ስር ደግሞ ስለጉባኤው ስልጣንና ተግባር ዘርዝሮ አስቀምጧል። ከጉባኤው ስልጣንና ተግባራት መካከል አንዱ ደግሞ ደረጃቸው ከምክትል ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ በታች የሆኑ አቃቤያነ ሕግን ቅጥር፣ ዝውውርና የደረጃ እድገት በሚመለከት ውሳኔ መስጠት ስለመሆኑ ደንቡ በአንቀጽ 46(3) ድንጋጌ ስር አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል። ደንቡ የይግባኝ መብትን በተመለከተም በአንቀፅ 41 ስር አስቀምጧል። ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ደንብ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ የከተማውን አቃቤያነ ሕግን በተመለከተ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ምክንያት የተለየ ሕግ ባልወጣበት ሁኔታና አዋጅ ቁጥር 568/2000 በሕግ ተዋረድ ከደንቡ በላይ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም አዋጁ ደንቡን ሙሉ በሙሉ የተካበት መንገድ ያለ ስለመሆኑ በግልጽ የሚያሳይ ድንጋጌ ሳይኖር በአዋጅ ቁጥር 568/2000 መሰረት የአካል ጉዳተኞች አቃቤያነ ሕግ የዝውውር ጉዳይ የአድሎ ተግባር የተፈፀመ ነው ተብሎ ስለተገለጸ ብቻ በፍርድ እንዲያልቅ የሚደረግበት አግባብ የለም። ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በአቃቤያነ ሕግነት ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኛ እና ስራው ሹመት ሁኖ የተለየ የሕግ ማዕቀፍ በሆነው በደንብ ቁጥር 24/1999 የሚገዛ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 568/2000 ይዘትና መንፈስ አዛምደው ሳይመለከቱ ጉዳዩ በፍርድ

ቤት ቀጥታ ክስ የሚቀርብበትና እልባት የሚሰጥበት ነው በሚል ምክንያት ጉዳዩን መዳኘታቸው በሕጉ ባልተሰጣቸው ስልጣን ሁኖ ስለአገኘን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4፣ 9 እና 231(1(ለ)) ድንጋጌዎች አኳያ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00746 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 111843 ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪ አካል ጉዳተኛ ቢሆኑም በደንብ ቁጥር 24/1999 መሰረት ተሹመው የሚሰሩ በመሆኑ አከራካሪው ጉዳያቸው በደንቡ መሰረት ስልጣን ባለው አካል ከሚታይ በስተቀር በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ብለናል፡፡

3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 75788
ህዳር 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካቾች፡- ፡- 1ኛ/ አቶ በረከት ኃ/ኪሮስ
2ኛ/ አቶ ዮሐንስ ኃ/ኪሮስ
3ኛ/ አቶ አስቻለው ስሜ -
} ጠበቃ አቶ ለገሰ ማሞ ቀረቡ

ተጠሪች፡- አቶ ኀይቶም ኃ/ኪሮስ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር መነሻ የሆነው የአሁኖቹ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች እንዲሁም በክርክሩ ሂደት በሞት የተለየችው የምስራች ኃ/ኪሮስ የሟች አባታችን የአቶ ኃ/ኪሮስ አባይ ውርስ ይጣራልን ሲሉ በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አንዳቸው በሌላኛው ላይ ያቀረቡት ክስ መሆኑን የአሁኑ 2ኛ አመልካች ክሱን ያቀረበው በአሁኑ 1ኛ አመልካች እና በምስራች ኃ/ኪሮስ ላይ መሆኑን የምስራች ኃ/ኪሮስ ክስ ያቀረበችው ደግሞ በአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ መሆኑን ፍ/ቤቱም ለሁለቱ ክሶች የተከፈቱትን ሁለት መዝገቦች በማጣመር ውርሱ እንዲጣራ ያደረገ ቢሆንም የምስራች ኃ/ኪሮስ ባቀረበችው ይግባኝ መነሻ የአሁኑ 2ኛ አመልካች የውርስ ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመወሰኑ የአሁኑ 2ኛ አመልካች ከክርክሩ ውጪ መሆኑን በምስራች ኃ/ኪሮስ ከሳሽነት እና በአሁኑ 1ኛ አመልካች ተከሳሽነት በመ.ቁ. 17994 የተጣራው ውርስ በአፈፃፀም ደረጃ ደርሶ የምስራች ኃ/ኪሮስ በሟች ባለቤት በወ/ሮ ዘላለም ስሜ ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ ድርጅት (የውርስ ሀብት) በሀራጅ ለማሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ጉዳዩ በቀጠሮ እያለ የምስራች ኃ/ኪሮስ በ12/11/02 በሞት በመለየቷ ምክንያት የጨረታው ሂደት ተቋርጦ መዝገቡ መዘጋቱን ከዚህ በኋላ በተከሳሽነቱ ሲከራከር የነበረው የአሁኑ 1ኛ አመልካች እና ቀደም ሲል ከክርክሩ ውጪ ተደርጎ የነበረው የአሁኑ 2ኛ አመልካች የሟች የምስራች ኃ/ኪሮስ ተተኪ ወራሾች መሆናቸውን በ05/12/02 በፍ/ቤት ያረጋገጡበትን ማስረጃ በመያዝ በ10/12/02 ቀርበውና ጉዳዩን አንቀሳቅሰው የውርስ ሀብቱ በሀራጅ እንዲሸጥ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ቀሪ ተደርጐ ድርጅቱን በስምምነት ሸጠው ለመቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ፍ/ቤቱ በመቀበሉ ድርጅቱን በስምምነት አጉታቸው ነው ለተባለው ለአሁኑ 3ኛ አመልካች መሸጣቸውን ገልፀው የሽያጭ ውሉን ይዘው በ12/12/02 በመቅረባቸው ፍ/ቤቱ የሽያጩን ውሉን አጽድቆ በውሉ መሰረት እንዲፈጸም በዚሁ ዕለት ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቶ ያሰናበታቸው መሆኑን ከዚህ በኋላ የስር በመቃወም አመልካች (የአሁኑ ተጠሪ) የአቶ ኃ/ኪሮስ አባይ ወራሽ

www.abyssinialaw.com

ስለመሆኑ ማስረጃ በማያያዝ የስር በመ/ተጠሪዎች (የአሁኖቹ አመልካቾች) ወራሽ መሆኔን እያወቁ እና የሟች የምስራች ኃ/ኪሮስ ውርስም በሕጉ አግባብ ሳይጣራ በ10/12/02 እና በ12/12/02 የሰጡት ትዕዛዝ መብቴን የሚነካ በመሆኑ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 358-360 መሰረት እንዲነሳ ይወሰንልኝ ሲል መቃወሚያ ማቅረቡን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ የመ/ተጠሪዎች ተተኪ ወራሽ ነን ብለው መዝገብ ከማንቀሳቀስ ውጪ የየምስራች ኃ/ኪሮስ ውርስ በሕጉ መሰረት እንዲጣራ እንዳደረጉ በ10/12/02 እና በ12/12/02 የተሰጡት ትዕዛዞች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 3 መሰረት እንደፍርድ እንደሚቆጠሩ እና ወደ 3ኛ የመ/ተጠሪ የስም ዝውውሩ አለመፈፀሙን ከከተማው አስተዳደር እንዳረጋገጠ በዝርዝር በመግለፅ በመ.ቁ 17994 በ21/03/04 በሰጠው ውሳኔ በ10/12/02 እና በ12/12/02 ሰጥቷቸው የነበሩትን ትዕዛዞች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360 መሰረት መሰረዙን ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 11312 በ04/04/04 በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበለትን ይግባኝ ሳይቀበለው መቅረቱን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም አመልካቾች የሚኖሩት በደቡብ ክልል ተጠሪ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በመሆኑ ምክንያት በተለያዩ ክልሎች በሚኖሩ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የተነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን የፌ/ፍ/ቤቶች መሆኑን በመግለፅ በመ.ቁ. 56046 27/04/04 ጉዳዩን ማሰናበቱን የክርክሩ ሂደት ያስረዳል፡፡

አመልካቾች በ1/05/04 አዘጋጅተው ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ተከራካሪ ወገን የሚባሉት ከሳሽ እና ተከሳሽ እንጂ በመቃወም አመልካች ጭምር ስላልሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የአሁኑ ተጠሪን በተከራካሪ ወገንነት መፈረጁ ስህተት ነው በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው በስረነገር ውሳኔ ላይ እንጂ በ10/12/02 እና በ12/12/02 በተሰጡት ዓይነት የአፈፃፀም ትዕዛዞች ላይ አይደለም 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የሽያጩን ገንዘብ የተቀበሉ የሰነድ እና የንብረት ርክክብ የተደረገ እና ውሉ እና ትዕዛዙ ከማህደሩ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በ12/12/02 የተሰጠው ትዕዛዝ ተፈፅሟል እነዚህ ሁኔታዎችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንዳለባቸው የሚያረጋግጡ በመሆኑ እንዲሻሩ ይወሰንልን የሚል ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ በ7/9/04 በተፃፈ ማመልከቻ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ ለማቅረብ የቻልኩት የአባቴ ኃ/ኪሮስ አባይ እና የእህቴ የምስራች ኃ/ኪሮስ ውርስ እንዲጣራልኝ በከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መስርቼ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የፍ.ሥ.ሥሕ.ቁ 7 ድንጋጌን ጠቅሰው መቃወሚያ በማቅረባቸው እና ክስ ያቀረብኩበት መ.ቁ 10067 በመቃወሚያው መሰረት በመዘጋቱ ነው፣ ትዕዛዞቹ እንደፍርድ የሚቆጠሩ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት የለውም የስም ዝውውር አልተፈፀመም በመ.ቁ 23149 በ20/12/02 ዕግድ አሰጥቻለሁ ወራሽ መሆኔን እያወቁ እና ውርስ ሳይጣራ አመልካቾቹ ውሉን አቅርበው ያስፀደቁት ከቅን ልቦና ውጪ ነው 3ኛ አመልካች የ1ኛ እና የ2ኛ አመልካቾች የእናት ወገን አጐት ነው በ10/12/02 በተደረገው ውል በአንቀጽ 2.2. መሰረት ስም እስኪዛወር ድረስ ብር 50,000 በገዥው እጅ እንደሚቆይ ስለተገለፀ ክፍያ ተፈጽሟል የተባለው ሀሰት ነው በዚህም ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ውሳኔዎች ስህተት የሌለባቸው በመሆኑ እንዲፀኑ ይወሰንልኝ በማለት መልስ ሰጥቶ እና አመልካቾችም በ29/09/04 የተፃፈ የመ/መልስ አቅርበው የጽሁፍ ክርክሩ በዚሁ ተጠናቋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በክርክሩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ያሰናበተው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት በሀገራችን ፍ/ቤቶች በተለያየ ደረጃ እና እርከን ተዋቅረው የሚገኙ ሲሆን ይህ አወቃቀር የክልል እና የፌዴራል ፍ/ቤቶችንም የሚያጠቃልል ነው፡፡ በተለያየ ደረጃ እና እርከን ተዋቅረው ከሚገኙት መካከል እያንዳንዱ ፍ/ቤት የሚያስተናግዳቸው የጉዳይ ዓይነቶች የሚወሰነው ለየፍ/ቤቱ በሕግ ተለይቶ

በተሰጠ የስረ ነገር እና የግዛት ስልጣን ነው፡፡ የግዛት ስልጣን በዋነኛነት መሰረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበትን ቦታ ለተከራካሪ ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት እና መሰል ሁኔታዎችን ሲሆን የስረ ነገር ስልጣን መሰረት የሚያደርገው ግን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣ የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደት እና መጠን የጉዳዩን የውስብስበነት ደረጃ እና መሰል ነጥቦችን በመሆኑ በጉዳዮች አመራር ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው እና በጥንቃቄ መጤን የሚገባው ነው፡፡ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 9 እና 10 ድንጋጌዎች ተገናዝበው ሲታዩም ሕጉ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ከግዛት ስልጣን ይልቅ ለስረ ነገር ስልጣን መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ የፍ/ቤቶች ስልጣን ሌላው ገጽታ ፍርድን የማስፈፀም ስልጣን ነው፡፡ ፍርድን የማስፈጸም ጉዳይ በስረ ነገር ክርክሩ ተረጋግጠው የፍርድ ኃይል ያገኙት የተከራካሪ ወገኖች መብት እና ግዴታ በስነ ስርዓት ሕጉ የተደነገገውን የአፈፃፀም ስርዓት ተከትለው እንዲፈፀሙ ከማድረግ ውጪ አዲስ መብት እና ግዴታ የሚቋቋምበት ባለመሆኑ ብዙ ሲያከራክር አይታይም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 371 ላይ እንደተመለከተው የማስፈፀም ስልጣን የስረ ነገር ስልጣንን የሚከተል ነው፡፡ ተገቢ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙም ስረ ነገሩን የወሰነው ፍ/ቤት አፈፃፀሙን በውክልና ወደ ሌላ ፍ/ቤት ሊመራው እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 372 የተመለከተ ሲሆን በላይኛው እርከን የሚገኙ ፍ/ቤቶች የአፈፃፀም ጉዳዮችን በውክልና በታችኛው እርከን ለሚገኙ ፍ/ቤቶች ጭምር የሚያስተላልፉባቸው አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ ሁኔታም ፍርድን የማስፈፀም ስልጣን ከስረ ነገር ስልጣን በእጅጉ የተለየ እና የስረ ነገር ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ጭምር በውክልና ሊሰጥ የሚችል መሆኑን መገንዘብ በሚያስችል ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ያለው ጉዳዩ በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ግለሰቦች የሚከራከሩበት መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ እንደተባለው ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች በሆኑ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑ በአዋጁ 25/1988 አንቀጽ 5(2) ስር ተመልክቷል፡፡ አዋጁ በዚህ ሁኔታ የደነገገው የስረ ነገር ስልጣንን ነው፡፡ ለሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ግን የተነሳው ከስረ ነገር ፍርድ ሳይሆን ከፍርድ አፈፃፀም ትዕዛዞች መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ሰበር ችሎቱ የጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) ድንጋጌ ፍርድ የማስፈፀም ስልጣንን የሚገዛ አይደለም፡፡ ለአፈፃፀም የቀረበውን የስረ ነገር ፍርድ የሰጠው የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርዱን የማስፈፀም ስልጣን የሚኖረውም ይኸው ፍ/ቤት ነው፡፡ በአፈፃፀም ደረጃ ወደ ጉዳይ የገባው ተከራካሪ ወገን የሌላ ክልል ነዋሪ መሆኑ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 371 የተደነገገውን ፍርድን የማስፈፀም ስልጣን የሚነካ አይደለም፡፡ በዚህም ሁኔታ ሰበር ችሎቱ አቤቱታውን ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው ስልጣን የለኝም በማለት ያሰናበተው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሌላ ክልል ነዋሪ የሆነ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ደረጃ ወደ ክርክሩ መግባቱ ጉዳዩን ወደ ፌዴራል ጉዳይነት ይለውጠዋል የሚባል ቢሆን ኖሮ ሰበር ችሎቱ አቤቱታውን አስተናግዶ የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች በሆኑ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የተነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም ? በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት የሚገባው ሆኖ እያለ ጉዳዩ በፌ/ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ በመሆኑ የሰበር አቤቱታውን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ማሰናበቱ አቋሙ እና ትዕዛዙ የማይጣጣሙ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ ከላይ በዝርዝር በተገለፀው ሁኔታ የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሁለት የተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ግለሰቦች ተከራካሪ የሆኑባቸውን ጉዳዮች የማየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2)

www.abyssinialaw.com

መሰረት የፌ/ፍ/ቤት በመሆኑ የሰበር አቤቱታውን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 56046 በ27/04/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ በዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑን ተገንዝቦ ጉዳዩን በማንቀሳቀስ የአሁኖቹ አመልካቾች አቅርበውለት የነበረውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 341(1) መሰረት ወደ ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲመለስ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. እልባት ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይምለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 81963

ታህሳስ 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አስፋው ጉደታ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው ጊዜያዊ/ኮንትራት/ የሰራተኛ ቅጥር ግንኙነት የመነጨን ክርክር እንደጊዜው ቅደም ተከተል በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የአሁን አመልካችን ካሰናበተው፤ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 515/99 የተቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤትም ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ ካደረገው፤ የአመልካች ጉዳይ በየትኛው የዳኝነት አካል ሊታይ ይገባል? የሚለውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ በሆኑት በየደረጃው በተሰጡት ዳኝነቶች እና በግራ ቀኙ ክርክር እንደተረጋገጠው አመልካች የአሁን ተጠሪ ቋሚ ሰራተኛ አይደለም፡፡ ግንኙነቱ በጊዜያዊ የቅጥር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ተጠሪም በአዋጅ ቁጥር 515/99 የሚገዛ መንግስታዊ መ/ቤት ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡

አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት የሆነውን ክስ በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤት ከማቅረቡ በፊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የአሰሪና ሰራተኛን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት ስልጣን ባለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማቅረቡና ችሎቱም ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ዳኝነት ከዚህ የሰበር ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው ባይሆንም ከላይ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው አሰሪው የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሰረት የሚተዳደር በመሆኑ የግራ ቀኙ ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ሊዳኝ የሚችል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ የአሰሪና ሰራተኛ ችሎቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ዳኝነት በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የአሁን አመልካችን ፍትህ ለማግኘት መብት በሚያጣብብ አኳኋን በስልጣን ረገድ የተሳሳተ ዳኝነት ሰጥቷል በመሆኑም አመልካች ፍትህ የማግኘት መብቱን የት ያረጋግጥ? ፍትህ የመግኘት መብቱ ተነፍጓል፤ ለሚለው መደምደሚያ መነሻ ሊሆን የሚችል ዳኝነት አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት የሚገዛ፣ የሚተዳደር መ/ቤት ይሁን እንጂ በእርሱ እና በሰራተኞች መካከል ከስራ ግንኙነት የመነጨ ክርክር በተነሳ ጊዜ በማን እና በምን አኳኋን መሰረት ሊስተናገድ እንደሚችል በሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 2(1) ስር የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤቱ ሥልጣን በፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ በሚሰራ ሰራተኛ ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ በሆነው በይ/መ/ቁ 01371/2004 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት የአመልካችን ጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ሠራተኛ መሆን መነሻ አድርጎ ጉዳዩን ለማየት በህግ ተለይቶ የተሰጠን ሥልጣን የለም በሚል የሰጠው ብይንም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ይልቁንም የአዋጅ ቁጥር 515/99 የተፈፀሚነት ወሰን በቋሚ ሰራተኞች ላይ የተወሰነ በመሆኑ የተነሳ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ጉዳይን ጭምር ሊሸፈን ያልቻለ መሆኑ ታይቶ ይህንኑ ክፍተት ለመሙላት በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 22(3) መሰረት የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ በመስከረም ወር 2000 ወጥቷል፡፡ ይህ መመሪያ ቀጣሪ በሆነውና በጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኛ መካከል ሊነሱ ሚችሉትን ክርክሮች ሁሉ አይቶ መብትና ግዴታን በመወሰን ረገድ በተሟላ አኳኋን የወጣ መመሪያ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የዚህኑ መመሪያ አፈፃፀም በሚመለከት ቀጣሪው በሚሰጠው ውሳኔ ተቀጣሪው ካልተስማማ አቤቱታውን ወይም ይግባኙን ለመደበኛው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል በሚል የተደነገገው ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንዳለው ተረድተናል፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች የአዋጅ ቁጥር 515/99 የአፈፃፀም ወሰን፣ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 22(3) መሰረት የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ለማውጣት ከተፈለገበት ዓላማ እና የተፈፃሚነት ወሰን አንፃር አገናዝቦ ሲታይ መ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ጉዳዩን ለፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤት መቅረብ የሚገባው እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ሆነ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንፃር እንደቅደም ተከተሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 01371/2004 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ተመልክቶ ይኸው ብይን በህግም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 80357 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ሁሉ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩን ሥልጣን ላለው አካል አቅርቦ የማሰማት መብቱን ይህ ፍርድ አያግደውም ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ጉዳይ ክርክር የተነሳ ግራ ቀኙ ሳወጡት ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 80005

ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ኦላኒ በክረ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ቦጋለ ዱንፋ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጅማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የስራ ግንኙነትንና ተፈፃሚነት ያለውን ህግ የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የጥበቃ ስራ መደብ ላይ ተመድቦ ሲሰራ ከየካቲት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ከስራና ከደመወዝ ያገደኝ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደስራዬ ይመልሰኝ በማለት ለወረዳው ፍ/ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሰራተኞቹ በሲቪል ሰርቪስ ህግ (አዋጅ ቁጥር 515/99) መሰረት የሚተዳደሩ በመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን የለውም፡፡ ተጠሪ የኤጀንሲውን ሰራተኛ በመደብደቡ ከስራ የተሰናበተ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለኝ፣ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 377/96 ነው በማለት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ተጠሪን ያለአግባብ ከስራ ያሰናበተው በመሆኑ ወደ ስራው ይመለስ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች አዋጅ ቁጥር 553/1999 በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ሰራተኞቹን የሚያስተዳድረው በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረታዊ መርሆዎች መሰረት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት መብቱን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ማቅረብ ሲገባው ለጅማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ማቅረቡና የበታች ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ተቀብለው መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ተጠሪ በዲሲፕሊን ኮሚቴ የተሰጠብኝ ውሳኔ የለም የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሀምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን አመልካች ያነሳውን መቃወሚያ በማለፍ ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 553/1999 ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ የተቋቋመ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የአመልካች ዋና ዳይሬክተርም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህግን መሰረታዊ መርሆዎች በመከተል ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች የሚቀጥርና የሚያስተዳድር መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 553/1999 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም የአመልካች ሰራተኞችን መሰረታዊ መብትና ግዴታ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድና የስራ ስንብት ህጋዊነት በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆነው የህግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ሳይሆን አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

የጅማ ዞን ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 515/1999 የሚተዳደሩ የፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች የሚያቀርቡትን አቤቱታ የመቀበልና ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አልተሰጣቸውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በመቀበል ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለን የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን የለንም በማለት መዝጋት ሲገባቸው፣ አመልካች በራሱ ገቢ የሚተዳደር መስሪያ ቤት ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 377/1996 ነው በማለት ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የጅማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት የሚታይ በመሆኑ የጅማ ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 83425

ጥር 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአብጃታ ሻላ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር - ጠበቃ ተሾመ ቢራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአብጃታ ሻላ ሶዳ አሽ መሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር ስለ ተወካይ ጃራ ኡሻ ቀረቡ

1. ነጋዎ ጤፎ
2. አሚኖ ኡሻ
3. አሉታ ዋዶ
4. አቡ መሰቶ
5. ገበኦ ኤዱ
6. ሁሰን ማሉ
7. ቦኔ ሳክሎ
8. በዳሶ ቡዱ
9. ሁሴን ናኔሶ
10. አሊዬ ደቀቦ
11. ኢቲሶ በሩሻ
12. ቡሊ ሂርጳ
13. ከድር ሀጂ
14. ጢቤሶ ሮባ
15. ዳቤ ገልገሎ
16. ተሹቴ ቡዱ
17. አበሻ ሳፋኦ
18. ሁሴን ዳባ
19. ቱና ጢንቤ
20. መንግስቱ ሂንሴኔ
21. አማን ሀ/ሃሰን
22. ፈረዳ ቡታ
23. ግርማ ጎሴ
24. ጎዳና ቡላ
25. ጎዳና ሹቤ
26. ጎሴ ሻሌ
27. ወልዳዩ ሄርጳ
28. ኮርማ በዳሶ
29. ገመዳ ለገቶ
30. ሀሰን ዳለቻ
31. ሮባ ቱኔ
32. ታደለ ውብሸት
33. ቡዴ ቦረማ
34. ጠና ወቲቻ
35. ተሾመ ነገዎ
36. ተሹቴ ቢልቢላ
37. ገመዳ ሮባ
38. ገነሞ ቡልቃ
39. ቦንሶ ያሴ
40. ለሜቻ ተካልኝ
41. ገመዳ ዋታ
42. በቀለ ወልደማሪያ
43. ጃርጌ ሂንሴኔ
44. ጢሊሳ ማንዳዩ
45. ቱኬ ጎበና
46. የኔነሽ መንግስቱ
47. ይልማ ሞላ
48. ዋሪ ጅሩ
49. ወልዴ ጉተማ
50. ታደሰ በለጠ
51. ሊቃስ ለቤና
52. ቂፋ ገመዳ
53. ቂፋ ጀንጃሳ
54. ቃበቶ ጉዩ
55. ሂርጰ ሁልፌ
56. ሀይለኛው ወርቁ
57. ደጃ ጃንጄሳ
58. ደበበ ተክሌ
59. ግርማ ቡኪ
60. ገመቹ ጩራ
61. ገመዲ ገነሞ
62. አህመድ አደም
63. በለጠ አለማየሁ
64. ብርሃኑ ወዬሶ
65. በዳኔ ሚንጆሶ
66. አቤ ቡኑሼ
96. አንበሳ ጉዬ
97. ይርጋ ገበየሁ
98. ኩርኩሩ መቺሳ
128. ዋሪ በሪሳ
129. ዋዩ ሹቶ
130. ሂርጰ ጃርሶ

www.abyssinialaw.com

67. አማን ስቴሳ
68. አበበ ደጀኔ
69. አቡሽ ማካንጎ
70. አበባ ቅጣው
71. አዱኛ ጉደታ
72. አበባ ቱራ
73. ዮሐንስ አየለ
74. ዋዶ ሀሰን
75. ተስፋዬ ሰይፉ
76. ወርቂ ገብሬ
77. እሸቱ ላታሞ
78. ጌታቸው ሐይሉ
79. ጃራ ኡሻ
80. ወለሳ ሙክታር
81. ጸሐይ ከበደ
82. ቶላ ወቲቻ
83. ሽታዬ ደምሴ
84. ሽመልስ ዳያሮ
85. ማስረሻ ወልዴ
86. መንገሻ ዋሌ
87. መሀመድ ዳውድ
88. ዮሴፍ ከሌቻ
89. አንለይ ገላው
90. አስረስ ቸኮል
91. አየለች በላቸው
92. በዳሶ ፉሪ
93. ቦንሶ ቶላ
94. በለጠ ባዶቦ
95. አሊ አብዱልቃድር
99. አደም ነገዎ
100. ግርማ ማሞ
101. አደም ከድር
102. መልከቶ ጢንቢሴ
103. ኩባ ሺግዳ
104. ካሪም ደቀቦ
105. ጃልዳ ገመዳ
106. ዱሌ ዳዲ
107. አበቡ ገመዳ
108. ቂፋ ገመዳ ጌሳሞ
109. አማን ሃጂ ጠደቻ
110. ሀቡ ገዳ
111. ባቲ ጡና
112. ነቢ ገባባ
113. ፈዩ ቢልቢላ
114. ሀጂ ጣደቻ
115. አማኖ ገመቹ
116. አቡ ቡታ
117. ሞገስ ዶያሮ
118. ገመዲ ጌላ
119. ሂርጶ ሌንጂሶ
120. ሀቢቦ ገልገሉ
121. ለማ ሀይሉ
122. ዋሪዩ ኡሼጦ
123. አቡ ቲያ
124. አብድልቃድር ጎበና
125. ቂፋ ደቀቢ
126. ለሜቻ ጋጉሮ
127. ጎዳና ገባባ
131. አቢቲ ዋሪ
132. ጃውሮ ዳሉ
133. ቃዎ ሜጢ
134. ገመዳ ዴቢሳ
135. አኑሎ ፈይሳ
136. ደስታ ደለቻ
137. ሌንጮ ገመዳ
138. ይርዳው አለሙ
139. ንጉሱ ጆሮ
140. ጌትነት መታፈሪያ
141. ቢልቢላ ቂጦ
142. ቂፋ ገረጂ
143. ብደላ እንድሪስ
144. ቀበቶ ገመዳ
145. ሚኤሶ ዳለቻ
146. አቤል ዳለቻ
147. ዋሪ ኤገቶ
148. ሜሻ ገዳ
149. ዲማ ኤንቶ
150. አብጃቶ ደገላ
151. ደቀቦ ኤገቶ
152. ዶኒ ዶሪ
153. ዋሾ ጎሴ
154. ጃልዶ ዋሪ
155. ደስታ ቡሎ
156. ወይንሸት ታደለ
157. ዱሬቲ ኤቢሳ
158. ዘቢደሩ አለማየሁ
159. ፈይሳ ጅሩ
160. ተሾመ ዋቁሼ
161. ሚኢሶ ደለቻ
162. አልማዝ በዳሶ
163. ሙሰማ ሀምሳ
164. ኮርማ ባቲ
165. ቲኬ ባሩሽ

www.abyssinialaw.com

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጡረታ መብት ይጠበቅልን ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በቦርድ ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ከ158 በላይ የሆኑትን ሰራተኞች በመወከል ሲሆን ሰራተኞቹ ከ1979 ዓ.ም ወይም በጊዜያዊነት የስራ መደብ ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በማህበሩ በአባልነት ተመዝግበው እንደሚገኙ፣ ማህበሩ በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 11(4/ሠ) ስር የሰራተኛው የአገልግሎት ዘመን እና የሰራተኛው የጡረታ መዋጮ 4% እና ከማህበሩ በተጠቀሰው መሰረት ሲፈፅሙ ከሰራተኞቹ አብዛኛዎቹ ለረዥም ጊዜያት በጊዜያዊነት ቅጥር የስራ መደብ ላይ ላገለገሉበት ጊዜ ለጡረታ ሳይመዘገብ በቋሚነት ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ብቻ በመመዝገብ ላይ ስለሆነ ይህ አፈፃፀም ትክክል ያልሆነ መሆኑ ተገልፆላቸው በማህበሩ ሰራተኞች መካከል ልዩነት ሳይፈጥር አካሄዱን በማስተካከል የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 11(4/ሠ) ድንጋጌ በሚያዘው መሰረት የጡረታ ጊዜያአቸውን በጊዜያዊነት ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በመመዝገብ የጡረታ መዋጮ ከሰራተኛው ደመወዝ የሚቆረጥ 4% ፣ ከማህበሩ ተቆራጭ የሚደረገው መዋጮ 6% በመሰብሰብ ከባንክ ወለድ ጋር ለጡረታና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በመላክ ገቢ እንዲሆንላቸው ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የሌለው መሆኑንና ማህበሩ ክስ የመሰረተላቸው ሰራተኞች ጊዜአዊ ሰራተኞች በመሆናቸው ለቋሚ ሰራተኞች የተጠበቀውን የጡረታ መብት ለመጠየቅ ክስ ለመመስረት መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ማህበሩ ክስ ያቀረበላቸው ሰራተኞች በኮንትራትና በቀን ስራ እንዲሁም በጊዜአዊነት የተቀጠሩ በመሆናቸው የአገልግሎት ዘመናቸው እና የስራ ልምዳቸው የተቆራረጠ በመሆኑ የስራ ልምድ ማስረጃ ለመስጠትም አስቸጋሪ መሆኑንና ሰራተኞቹ በኮንትራት ያገለገሉት ጊዜ ለጡረታ እንዲያዝላቸው የማድረግ ስልጣን የተከሳሽ ድርጅት ያለመሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ቦርዱም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ በቦርዱ ስልጣን የሚወድቅ አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶት የነበረው ሲሆን ማህበሩ በዚህ የቦርዱ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን እንዳለው በመግለፅ ውሳኔ በመስጠቱ ጉዳዩ ለቦርዱ የተመለሰለት ሲሆን ቦርዱም ጉዳዩን ማየት በመቀጠል ጉዳዩን መርምሮና አጣርቶ ክሱ የሚመለከታቸው ሰራተኞች ሁሉ የጡረታ ጊዜያቸው ሊቆጠር የሚገባው ስራቸውን ሳያቋርጡ መስራት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ አመልካች ድርጅት በእጁ ያለውን ማስረጃ መርምሮ እንዲያስብላቸውና ከሰራተኞቹ የሚሰበስበውን መዋጮ 4% እና የአመልካች መዋጮ 6% አንድ ላይ በማጣመር ለሚመለከተው አካል ማሳወቅና ገቢ ማድረግ እንዲችል፣ ጡረታው ሊቆጠር ከሚገባው ጊዜና ቀን ጀምሮ እንዲቆጥርላቸውና እንዲፈጸምላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የጡረታ መብት ይጠበቅልኝ ሁኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተከበሩት መብቶችን ለማየት ስልጣን ለተሰጠው ቦርድ ቀርቦ መወሰኑ ያላግባብ መሆኑና ተጠሪ ክስ የመሰረተላቸው ሰራተኞች የኮንትራት ሰራተኞች በመሆናቸው ለቋሚ ሰራተኞች የተጠበቀላቸው መብት እንዲጠበቅላቸው የተወሰነው ከሕግ ውጪ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም

www.abyssinialaw.com

ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል የተባለው ቦርዱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የነበረው መሆን ያለመሆኑን፣ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም የመባሉን በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 11(1(ሀ)(ሠ)) መሰረት ተጠሪዎች ስራቸውን መስራት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ይቆጠርላቸው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ዳኝነት የተጠየቁት የጡረታ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ነው፡፡ ቦርዱ ይህንኑ የተጠሪዎች ጥያቄ አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልነበረው መሆኑን ገልፆ ክሱን ዘግቶ የነበረ ሲሆን ጉዳዩን እንደገና አይቶ ሊወስን የቻለው በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሠረት መሆኑን በውሳኔው ላይ ጠቅሷል፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ አሁን እንደገና ማየት ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የተመለከተው ጉዳዩ የስልጣን ጥያቄ በመሆኑና የስልጣን ጥያቄ ደግሞ በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ክርክሩ ባለበት በማናቸውም ደረጃ በፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት መነሳት የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9 እና 231 /1/ለ/ ድንጋጌዎች ስር ከተመለከቱት ድንጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10፣ 22 እና አዋጅ ቁጥር 454/1997 2/1/ ከተሰጠው ስልጣን አኳያ ነው በመሆኑም ችሎቱ ተመሳሳይ ለሆኑ ጉዳዮች በአገሪቱ ወጥ የሆነ የፍርድ አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲሰጥ በሕግ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑና የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ደግሞ በሕጉ አግባብ ጉዳዩን የመዳኘት ያለመዳኘታቸውን በዳኝነት ሥልጣኑ መቆጣጠር ያለበት በመሆኑ የስልጣን ጥያቄውን አሁን ክርክሩ ባለበት ደረጃም ቢሆንም ማየቱን ስነ ሥርዓታዊ የማያደርገው ሕጋዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

ከዚህ አንጻር ቦርዱ ጉዳዩን ለመወሰን ስልጣን ያለው መሆን ያለመሆኑን ስንመለከት ለቋሚ ቦርድ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተለይተው የተሰጡት የዳኝነት ስልጣን ጉዳዮች በአዋጁ አንቀጽ 142 እና 147 ድንጋጌዎች ስር የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ከተዘረዘሩት ጉዳዮች መካከል ደግሞ የሠራተኛ የጡረታ መብት ይከበር ጥያቄ በቦርዱ ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ስለጡረታ መብትን የሚገዛው አዋጅ ቁጥር 345/1995 ሲታይም ከአሰሪያቸው ጋር ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሰራተኞች የጡረታ መብታቸውም የሚገዛበት አግባብ መኖሩን አያሳይም፡፡ ተጠሪዎች ሥራ ሲጀምሩ አመልካች ድርጅት የመንግስት ሙሉ ይዞታ ነበር ቢባል እንኳን የተጠሪዎችን የጡረታ መብት ይከበርልን ጥያቄ በቦርድ የሚዳኝበት አግባብ ስለመኖሩ ለመንግስት ሰራተኞች የጡረታ መብት ይደነግጉ የነበሩት አዋጅ ቁጥር 209/1955 እና ማሻሻያዎቹ አያሳዩም አመልካች በመንግስትና በሌላ አካል በአክሲዮንነት ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮም ቢሆንም እንደማንኛውም የግል ድርጅት የሚታይ በመሆኑ ለግል ድርጅት ሰራተኞች የጡረታ መብት አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንጻር ጉዳዩ የሚታይ በመሆኑ በዚህ አዋጅ በተዘረጋው ስርዓት መሠረት የሚታይ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አግባብ የግል ድርጅት ሰራተኞች የጡረታ መብት ጥያቄ ላይ

www.abyssinialaw.com

ስልጣን ያለው አካል የግል ድርጅት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 53/1/ ስር በግልጽ የተመለከተ ሲሆን ይህ አካል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 202/2003 ተቋቋሞ ስራውን የሚሰራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ከሰኔ 07 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ የግል ድርጅት የሚሰራ ሰራተኛ በአዋጅ ቁጥር 715/2003 አግባብ ለጡረታ መብት ብቁ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው የግል ድርጅቶች ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተቋቋመው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች አዋጅ ቁጥር 715/2003 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት የሚከራከሩት ክሱ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ሲሆን አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ስለግል ድርጅቶች ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ግልጽ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ አልነበረም፡፡ ቀድሞውኑ በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ ድርጅቶች ወደ ግል ሲዞሩም የሰራተኞችን መብትና ጥቅም በተመለከተ የሚነሳበት አግባብ ሊኖር አይገባም ከሚባል በስተቀር የጡረታ መብቱን በተመለከተ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተቋቋመው ቦርድ ለመዳኘት ስልጣን የሚያሰጥ አይሆንም ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 147/2/ እና አንቀጽ 142/ሀ/ ድንጋጌ መሠረት ቦርዱ ስለደመወዝና ስለሌሎች ጥቅሞች አወሳሰን በሚል በአማርኛው ቅጅ የተቀመጠው የሰራተኞችን የጡረታ መብት ሁሉ ሊያጠቃልል የሚችል ነው በማለት ተጠሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር በድንጋጌው "wages and other benefits" በሚል ከተጠቀሰው የእንግሊዘኛ ቅጂ እና ለጡረታ መብት ብቁ መሆን ያለመሆኑ ለመወሰን የሰራተኛውን የተለያዩ ማስረጃዎችን መያዝና ማጠናቀርን የጡረታ አበል መጠንና የአከፋፈሉን ሁኔታ እንዲሁም ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን የሚገዛ ዝርዝር ሕግ እንዲኖር የሚጠይቅ ጉዳይ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ "ሌሎች ጥቅሞች" የሚለው የድንጋጌው ሐረግ የጡረታ መብትን ሁሉ ይጨምራል ብሎ መተርጎም ከጡረታ መብት አጠቃላይ ዓላማና ለመብቱ ብቁ ለመሆን መማላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ጋር አብሮ የማይሄድ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 147/2/ እና አንቀጽ 142/1/ሀ/ ድንጋጌዎች ከአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 53 እና ከደንብ ቁጥር 202 አንቀጽ 5/7/ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የተቋቋመው ቦርድ የግል ድርጅቶች ሰራተኞች ለጡረታ መብት ብቁ መሆን ያለመሆናቸውን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው ስልጣን ያለው መሆኑን የማያሳይ ሆኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ ተጠሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪዎች ሊከበርልን ይገባል የሚሉት የጡረታ መብት ሊወሰን የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በተቋቋመው ቦርድ ባለመሆኑ ጉዳዩ ቦርድ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ 730/01/2004 በቀን 18/12/2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 151939 መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪዎች የጡረታ መብት ይከበርልኝ ጥያቄ በቋሚ ቦርድ ታይቶ የሚወሰን አይደለም ብለናል፡፡
3. በክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ይለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

www.abyssinialaw.com

# ወንጀል

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 77097

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1.አቶ ሀይላይ ተክሉ

2. አቶ ተክላይ ገ/ሊባኖስ } ጠበቃቸው አበበ መስፍን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የመቀሌ ከተማ ሰሜን ምድብ ዐ/ህግ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የአሁኑ የሰበር ተጠሪ የአሁን የሰበር አመልካቾችን ጨምሮ በ 8 ተከሳሾች ላይ ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ/ም ያቀረበው ክስ፡- ተከሳሾች በትግራይ መንገዶች ባለሥልጣን የመኪና ግዥ የጨረታ የቴክኒክ ኮሚቴ ሆነው ሲሰሩ መሥሪያ ቤቱ ያወጣውን ባለ 11 ቴክኒካል መስፈርቶችን ወደ ጎን በመተው ከተጠየቀው መለኪያ በታች ያቀረበውን ሐግቤስ የተባለው ተወዳዳሪ ድርጅት ቅናሽ ዋጋ አቅርቧል በሚል ጨረታውን እንዲያሸንፍ አድርገው መስፈርት ያላሟላ መኪና እንዲገዛ በማድረጋቸው መኪናው የሚፈለገውን አገልግሎት ሳይሰጥ የተበላሸ በመሆኑ መንግሥት አስፈላጊ ያልሆነ ወጪ እንዲያወጣ በማድረግ በወ/ህ/አ/ 420/2/ የተደነገገውን በመተላለፋቸው ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾችም ባቀረቡት የክስ መቃወሚያ፡- ከሳሽ ጠቅሶ ያቀረበብን የወንጀል ህግ አንቀጽ 420 /2/ በእስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የእስራት ጊዜውም በወንጀል ህግ አንቀጽ 106(1) ሥር እንደተደነገገው ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት በመሆኑና የቀላል እስራት ይርጋ ዘመንም በወ/ህ/አንቀጽ 217(1)(ሠ) መሰረት አምስት ዓመት በመሆኑ ከሳሽ የወንጀሉ ድርጊት ተፈጽሟል በማለት በክሱ ከጠቀሰበት 29/04/1997 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት እስከ 11/12/2002 ዓ/ም ድረስ አምስት ዓመት ከስምንት ወር ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽም የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተ በሰጠው መልስ፡- ተከሳሾች የተከሰሱበት ወንጀል እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጣ ቢሆንም ወንጀሉን ስለመፈጸማቸው የታወቀው በ29/04/1997 ዓ.ም. ሳይሆን በ14/04/2001 ዓ.ም. ነው፡፡ በክሱ የተጠቀሰው ቀን 29/4/1997 ዓ.ም. ተከሳሾች የሚሰሩበት መ/ቤት ጨረታ ያወጣበት ሲሆን

www.abyssinialaw.com

ጉዳዩ የታወቀበት 14/04/2001 ዓ.ም. በመሆኑ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም የይርጋ ጊዜው ያላለፈ ስለሆነ ያቀረቡት የክስ መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም፡- ከሳሽ ተከሳሾች ወንጀሉን የፈጸሙት በ29/04/1997 ዓ/ም ሲሆን የወንጀሉ ድርጊት የታወቀው ደግሞ በ14/4/2001 ዓ/ም ነው ቢልም የክልሉ ኦዲተር ለክልሉ ፍትህ ቢሮ በ24/9/2001 ዓ.ም. የጻፈው ደብዳቤ በ14/4/2001 ዓ/ም መሆኑን አይገልጽም፣ በክሱ ወንጀሉ ተፈጽሟል የተባለው በ29/04/1997 ዓ/ም በመሆኑ ከሳሽ ክሱን መመስረት የሚገባው በ29/04/1997 ዓ/ም ነው፣ ተከሳሾች የተከሰሱበት ወንጀልም እስከ ሶስት ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ከአንድ ዓመት በላይ የሚያስቀጣው ቀላል እስራትም የይርጋው ዘመን አምስት ዓመት በመሆኑ ወንጀሉ ከተፈጸመበት ከ29/04/1997 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስም ያለው ጊዜ ሲቆጠር ከአምስት ዓመት በላይ ስለሆነ ክሱ በወ/ህ/አ/ 216 (ሠ) መሰረት በይርጋ የሚታገድ ነው ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የመቀሌ ከተማ ማዕከላዊ ፍርድ ቤትም፡- ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ይግባኝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(1) መሰረት በመሰረዙ ይግባኝ ባይም በሥር ፍርድ ቤቶች ብይን ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኂላ በሰጠው ፍርድ፡- በዚህ ጉዳይ ወንጀሉ ተፈጽሟል የተባለው በ29/04/1997 ዓ.ም. በመሆኑ ክሱ እስከቀረበበት እስከ 11/12/2002 ዓ/ም ያለው ጊዜ የሚቆጠር ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው ፖሊስና ዐቃቤ ህግ ምርመራ ማጣራት የጀመሩት በ14/04 2001 ዓ.ም. መሆኑን የምርመራ መዝገቡ የሚሳይ ሲሆን የምርመራው መጀመር የይርጋውን መቆጠር የሚያቋርጥ

ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 221 ስለሚደነግግ አመልካች ያቀረበው ክስ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ያላለፈበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በሚል የስር ፍርድ ቤቶችን ብይን ሽሯል፡፡

አመልካቾችም በክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲሉ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- ፖሊስ በተጠርጣሪዎች ላይ ምርምራ ለማድረግ ከፍርድ ቤት የመያዣ ወይም የብርበራ ትዕዛዝ ሳያገኝ የምርምራ መቅደም በ14/04/2001 ዓ.ም. መክፈቱን በመግለጹ ብቻ የይርጋ መቆጠርን ያቋርጠዋል በሚል ሰበር ሰሚው ችሎት መወሰኑ በወ/ህ/አ/219 እና 221 የተደነገገውን የሚቃረን ነው፣ ፖሊስ በአመልካቾች ላይ ምርመራ ጀምሯል ሊባል የሚችለውም በጉዳዩ ላይ የተከሳሽነት ቃላችንን እንድንሰጥ ደብዳቤ ከተጻፈልን ከ27/05/2002 ዓ.ም. ጀምሮ ስለሚሆን ወንጀሉ ተፈጸመ ከተባለበት ከ29/04/1997 ዓ/ም ጀምሮ ደብዳቤው እስከተጻፈበት ድረስም ያለው ጊዜ ሲቆጠር አምስት ዓመት ያለፈው ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው የሚሉ ናቸው ፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በጉዳዩ ላይ መልሱን እንዲያቀርብ ታዞ መጥሪያ የደረሰው ቢሆንም ቀርቦ መልስ ያልሰጠ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- በአመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪው አመልካቾች የተጣለባቸውን የስራ ኃላፊነት ባለመወጣት በመንግሥት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል በወንጀል ህግ አንቀጽ 420(2) ሥር ክስ ያቀረበባቸው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኞች ሆነው ቢገኙ ሊወሰንባቸው የሚችለው ቀላል እስራቱና መቀጮው በህጉ እስከተወሰነው ከፍተኛው ቅጣት ሊደርስ እንደሚችል ከድንጋጌው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ቀላል እስራትም ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጣ መሆኑን የወንጀል ህግ አንቀጽ 106(1) የሚደነግግ ሲሆን በወንጀሉ ከባድነት የተነሳ በህጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ ወይም ወንጀለኛው በተደጋጋሚ ሲቀጣ ቀላል እስራቱ አስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል የድንጋጌው 2ኛው ፓራግራፍ ያመለክታል፡፡

ከአንድ ዓመት በላይ ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አምስት ዓመት መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 217(1)(ሠ) ስር የተደነገገ ሲሆን የይርጋ ዘመኑም መቆጠር የሚጀምረው ጥፋተኛው የወንጀሉን ድርጊት ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 219(2) ይደነግጋል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ወንጀሉን ፈጽመዋል በሚል በክሱ የተጠቀሰው 29/04/1997 ዓ/ም ሲሆን ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበባቸው እስከ 11/12/2002 ዓ/ም ያለው ጊዜ ሲቆጠርም የክስ ማቅረቢያው አምስት ዓመት ማለፉ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ወንጀሉ ተፈጽሟል የተባለው በ29/04/1997 ዓ/ም ቢሆንም ወንጀሉ መፈጸሙ የታወቀውና ፖሊስ ምርመራ እንዲያጣራባቸው የተደረገው በ14/4/2001 ዓ/ም ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ፖሊስ በአመልካቾች ላይ ከ14/04/2001 ዓ/ም ጀምሮ ምርመራ ማድረጉ እስከተረጋገጠ ድረስም በወንጀል ህግ አንቀጽ 221 እንደተደነገገው የይርጋ ዘመኑን መቆጠር የሚያቋርጠው ሆኖ ይርጋው እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ይሆናል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ ፖሊስ ምርመራ ማጣራት የጀመረው በ14/4/2001 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ በወ/ህ/አንቀጽ 221 መሰረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም በሚል የሰጠው ፍርድ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 44044 በቀን 19/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(2)(ለ)(2) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ያላለፈበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡

   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 77842

ታህሣስ 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች :- አቶ ሳሚ ሁሴን አልቀረበም

ተጠሪ :- የፌደራል ዐቃቤ ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች በ1996 ዓ.ም በወጣው በወንጀል ህግ አንቀጽ 693(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በተለያዩ ጊዜ ለአንድ ሰው በቂ ስንቅ ሣይኖረው የተለያዩ ቼክ ቆርጦ ሰባት ዓይነት እራሱን የቻለ ጥፋት/offence/ ፈጽሟል በሚል የተሰጠውን የጥፋተኝነትና ውሣኔ አግባብነት ለማየት በሚል ነው፡፡

በአሁን አመልካች ላይ የፌዴራል ዐ/ሕግ ባቀረበው የወንጀል ክስ ዝርዝር እንደተመለከተው አመልካች በቂ ስንቅ ሣይኖረው ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በተየያዩ ቦታ የተለያዩ ቼክ አቶ ማስረሻ ምንጃር ለተባለ አንድ ግለሰብ ብቻ ቆርጦ በመስጠቱ በ1996 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የሚያዝበት ገንዘብ ሣይኖረው ቼክ ማውጣት ሰባት እራሱን የቻለ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ክስ አቅርቦበታል፡፡

የአሁን አመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክሶች ይዘት እንደተረዳና እንደ ክሱ አቀራረብ ሰባቱንም ጥፋቶች ለመፈጸሙ አመኖ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.134(1) መሠረት የእምነት ቃሉን ሰጥቷል የሚለውን በመያዝ በወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ነው በሚል የጥፋተኝነት ውሣኔ እንደተሰጠ እና ለእነዚህም ጥፋቶች በህጉ የተመለከተው የቅጣት ወለል እና ጣሪያ፣ የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና ተደራራቢ ወንጀል ተፈጽሞ በተገኘ ጊዜ ቅጣት የሚወሰንበትን ሥርዐት ሁሉ በማገናዘብ የአሁን አመልካች ቀደም ሲል በተመሣሣይ አኳኋን ፈጽሟል የተባለውን 8ኛ ጥፋት ከግምት ወስጥ በማስገባት በአጠቃላይ በ25 ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ዓይነትና ዘመን እንደተጣለበት ከውሣኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

የአሁን አመልካችም ከቀረበበት ተደራራቢ የወንጀል ክስ ከባድነት አንፃር በህግ ባለሙያ ታግዞ ባለመከራከሩ ምክንያት እግ እንደ ህጉ አነጋገር የወንጀል አድራጐቱን ስለመፈፀሙ የእምነት ቃል መስጠቱ ሣይረጋገጥ አምኗል

በሚል የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አግባብ አይደለም የሚልበትን ዝርዝር ምክንያት በኪር አቤቱታ ላይ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

የአሁን ተጠሪም በክሱ አሠማም ሂደት የአመልካችን የመከራከር መብት ሊያጣብብ የሚችል የክርክር ጉድለት ያለመፈጸሙንና የፋጥተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔው በህግ መሠረት ታይቶ የተሰጠ ነው የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ በበኩሉ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው  በወንጀል ጉዳይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 134(1) እንደተደነገገው ተከሣሹ የተከሰበበትን የወንጀል ክስ ይዘት በሚገባ ተረድቶ አድራጐቱን  እንደቀረበበት የወንጀል ክስ ዝርዝር መፈፀሙን አምኖ የእምነት ቃል በሰጠ ጊዜ ይህ የእምነት ቃል ለቀረበበት የወንጀል ክስ ማስረጃ ሆኖ በዚሁ ማስረጃ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠት የሚቻልበት ሥርዓት ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አኳኋን ተከሣሹ የሚሰጠው የእምነት ቃል በማስረጃነቱ ተይዞ የሚሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ ውሣኔውን በሰጠው ፍ/ቤቱ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ የተሰማው ወገን በህገ-መንግስቱም አንቀጽ 20(6) ሆነ በዝርዝር በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት ከታች ወደ ላይ በይግባኝ የመከራከር መብቱን ለማስጠበቅ የይግባኝ አቤቱታ የሚያቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

በዚህ መሠረት በይግባኝ በሚቀርበው መከራከሪያ ነጥብነቱ እንደ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 134(1) ድንጋጌ አነጋገር የወንጀሉን አድራጐት ለመፈፀሙ የእምነት ቃል አልሰጠሁም፤ ነገር ግን እንዳመንኩ ተደርጎ ጥፋተኛ ነህ ተብያለሁ በማለት ቅሬታ የቀረበ እንደሆነ ተከሳሹ ተላልፎታል በሚል የተጠቀሠበት ድንጋጌ ሥር የተቋቋመውን የወንጀል ዝርዝር ተከሣሹ በአፈፃፀሙ ረገድ የሰጠውን ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታ በማገናዘብ በእርግጥም እንደ ክሱ የወንጀሉን አድራጐት ፈጽሞታል ወይስ አልፈፀመውም የሚለውን ለመለየት ተከሣሹ ሰጠ የተባለው ዝርዝር የእምነት ቃል በመዝገቡ ላይ ሠፍሮ ካልተገኘ በቀር የበላይ ፍ/ቤቶች ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት አያስችላቸውም፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይም ተከሣሹ የአሁን አመልካች ሰባቱንም ጥፋቶች ለመፈፀሙ በደፈናው አምኗል በሚል በመዝገቡ ላይ ከመመዝገቡ በቀር ስለማመኑ የሰጠው ዝርዝር ቃል አልሰፈረም፡፡

ይህ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 134(1) ከተመለከተው ድንጋጌ ትክክለኛ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የተነሣው ክርክር እንደ ተጠበቀ ሆኖ ተከሣሹ ስለወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም አምኗል በሚል ቃል መስጠቱን ቢታወቅም እንኳን ፍ/ቤቱ እንደነገሩ አግባብነት በዚህ በተከሣሹ የእምነት ቃል ማስረጃ ላይ ሣይወሰን ስለ ጉዳዩ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ማስረጃ በመስማቱ ሙሉ የክርክር አካሄዱን ተከቶሉ ውሣኔ መስጠት የሚችልበትም ሥርዓት ተከታይ በሆነው ንዑስ ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡

ከዚህም አንፃር የአሁን አመልካች በአጭር ጊዜ ለአንድ ግለሰብ በተለያዩ ጊዜና ቦታ ሰባት ዓይነት ቼክ ቆርጦ ሊሰጥ ከቻለበት ሁኔታ አንፃር ለቼኩ መሰጠት ምክንያት የሆነው መስተጋብር ወይም ግንኙነት፣ እንዲሁም በዚህ ሁሉ ሂደት ቼኩን ቆርጦ በሰጠው ሰው እና ተበዳይ በተባለው ተቀባይ መካከል የነበራቸው የሃሣብ ሁኔታን ሊያመላክት የሚችል በዐ/ሕግ ማስረጃ የሚረጋገጥ የፍሬ ነገር ጉዳይ ካልተገኘ በቀር በወ/መ/ሕ/ቁ. 23 መነሻ

www.abyssinialaw.com

የተቀመጡትን ዝርዝር የወንጀል አፈፃፀም ደንቦች ተከትሎ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ውሣኔ መስጠት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ የከሣሽን የመደመጥ እና ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብቱን በማስጠበቅ ረገድ ከተዘረጋው ትክክለኛ የሙግት አካሄድ አንፃር ሲታይ መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል መዘገብ ቁጥር 101259 ጥር 2003 ዓ.ም እና ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 66805 ታህሣስ 09 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ የፌዴራል ዐ/ሕግ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበውን ሰባት ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ተከሣሹ ስለመፈፀሙና አለመፈፀሙን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.134 መሠረት የሚሰጠውን ዝርዝር ቃል፤ እንዲሁም ዐ/ሕግ ክሱን ለማስረዳት ዘርዝሮ ያቀረበውን ማስረጃ በመስማትና ሙሉ የክርክር አካሄድን በመከተል በጉዳሉ ላይ ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን ወደ ሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይህንኑ እንዲያውቁት የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ከመሸኛ ጋር ለበታች ፍ/ቤቶች ይተላለፍላቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 73514

ህዳር 6 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- ተስፋዬ ጡምሮ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን - ዐቃቤ ህግ ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡

ተጠሪ አመልካች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ ቁጥር 419 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ፣ ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ሰርቷል፡፡ ተከሳሽ የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ በወር ብር 420 (አራት መቶ ሃያ ብር) እና ብር 530 (አምስት መቶ ሰላሳ ብር) እየተከፈለው የቆየ ቢሆንም፣ በመንግስት ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሲያገኝ ከነበረው ገቢ ጋር የማይመጣጠን ብር 1,167,637.60 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከስልሳ ሳንቲም) በዳሽን ባንክ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በወጋገን ባንክና በንብ ባንክ ሲያንቀሳቅስ በመቆየቱና የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ. 2-78716 የቤት አውቶሞቢል መኪና በስሙ በመገኘቱ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ የመገኘት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ አመልካች የክሱ ግልባጭ ከደረሰውና ከተነበበለት በኋላ የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ለማስረዳት አመልካች ሲያንቀሳቅስ ስለነበረው ሒሳብ የሚያሳዩ ከተለያዩ ባንኮች የተሰጠውን የሂሳብ ማመዛዘኛ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ አመልካች በተጠሪ የቀረበበትን የሰነድ ማስረጃ መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብል የስር ፍ/ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሾጌ የሲሚንቶ ውጤቶች የሁለገብ የህብረት ስራ ማህበር የሚባል በህግ የተመዘገበና ዕውቅና ያለው ድርጅት

www.abyssinialaw.com

የሚሰጣቸው የሲሚንቶ ውጤቶች ዋጋ በመቀበል በስሙ ሒሳብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች ናቸው በማለት የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በስሙ በተለያዩ ባንኮች ሲያንቀሳቅስ የነበረው በወንጀል ክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብና መኪና ምንጩ ህጋዊ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች አጠራጣሪ ናቸው በማለት አመልካች በ1997 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ይዞ የተገኘ ጥፋተኛ ነው ብሎ፣ አመልካች በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 66,660 መቀጮ እንዲቀጣ፡፡ መኪናውና በባንክ የተገኘው ብር 27,330 (ሃያ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ብር) እንዲወረሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አቅርቦ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ጥቅምት 2 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ እኔ የመንግስት ሰራተኛ የነበርኩት ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ/ም መሆኑ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ በግልፅ ተጠቅሷል፡፡ አዲሱ የወንጀል ህግ በስራ ላይ እንዲውል ህግ አውጭው የደነገገው ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ይህም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 419 ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ በማድረግ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 የተደነገገውን መርህ የሚጥስ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ፍርድ የተሰጠብኝ መሆኑን ያሳያል፡፡ የታርጋ ቁጥር ኮድ 2-78716 የሆነችው መኪና የተገዛቸው በ2002 ዓ.ም መሆኑና ምንጩም የታወቀ መሆኑን አስረድቼ እያለ ለመንግስት ውርስ እንድትሆን መወሰኑ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ በነፃ እንድሰናበት በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የወንጀል ህጉ ወደኋላ ተመልሶ ሊሰራ አይገባም በማለት ያቀረበውን መከራከሪያ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 130 መሰረት በመጀመሪያ ክስ መቃወሚያ አድርጎ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ በሰበር ደረጃ ይህንን መከራከሪያ አድርጎ እንዲያቀርብ የሚፈቅድለት ህግ የሌለ በመሆኑ ክርክሩ ውድቅ እንዲደረግልን፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን 1992 እስከ 1996 ዓ/ም ባለው ጊዜ ብቻ እንደተፈፀመ አድርጎ ያቀረበው ክርክር የወንጀሉን ባህሪ ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች የወንጀል ምርመራ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስና እስከተከሰሰበት ድረስ የወንጀል ድርጊቱ ተፈፅሞ ተጠናቅቋል ለማለት ስለማይችል የአመልካቹ የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው እስከ 1996 ዓ.ም መሆኑን ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ መሆናቸው ከ1996 ዓ.ም በኋላ ከቆመ፣ በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ምርመራ እስከተጣራበትና ክስ እስከቀረበበት ድረስ ወንጀሉ የሚቀጥልበት ሁኔታ የለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም (1) ተጠሪ አመልካች በ1997 ዓ.ም ሥራ ላይ የዋለው የወንጀል ህግ በእኔ ላይ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ፣ በዚህ ህግ መሰረት ልከሰስና ልቀጣ አይገባኝም በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 130 መሰረት በመጀመሪያ ክስ መቃወሚያነት

ያላቀረበው በመሆኑ አሁን ይህንን ነጥብ የሰበር መከራከሪያ ሊያደርገው አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? (2) የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በ1997 ዓ.ም የወጣውንና ግንቦት 1 ቀን 1997 የፀናውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ ተገኝቷል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- የወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ፎርምና ይዘት በመቃወም፣ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችል መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 130 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ፡-

- ጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት እየታየ ያለመሆኑን፣
- ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን ወይም በይቅርታ ወይም በምህረት የተለቀቀ መሆኑን፣
- ጉዳዩ ከሌሎቹ ተከሳሾች ጋር መጣመሩ መብቱን የሚያጣብብ መሆኑን፣
- ዐ/ህግ የወንጀል ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆነውን ፈቃድ ሳያሟላ የወንጀል ክስ ማቅረቡን፣
- በሌላ ፍ/ቤት የተያዘው ጉዳይ ካላለቀ የወንጀል ክስ ለማቅረብ የማይችል መሆኑንና ለድርጊቱ በኃላፊነት የማይጠየቅ መሆኑን በመጀመሪያ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርብ እንደሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት መቃወሚያዎች ተከሳሽ ወዲያውኑ ማቅረብ እንዳለበት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት የወንጀል ክስ መቃወሚያዎች አመላካች (indicative provision) እንጅ ሁሉንም በመቃወሚያነት ሊቀርቡ የሚችሉ ጉዳዮችን በሙሉ የሚዘረዝር (exhaustive provision) ድንጋጌ አይደለም፡፡ አመልካች የሰበር መከራከሪያ ያደረገው ነጥብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130(2) የተመለከተ አይደለም ሆኖም ተጠሪ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ከመጽናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ/ም በፊት 1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም እንደሆነ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ በግልፅ አስፍሮታል፡፡

የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ዳኞች ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ፀንቶ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሳኔ ለመስጠት የማይከለክሉና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) የተጣለባቸውን ሰብአዊ መብት የማስከበር ግዴታቸውን የሚወጡበት አንደኛው መንገድ በመሆኑና የወንጀል ክስ የቀረበበት ድርጊት በወንጀለኝነት የሚደነግግ ግልጽ የወንጀል ህግ ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ዳኞች በመመርመር የህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 የተደነገገውን መሰረታዊ መርህ የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ስልጣን በማናቸውም

www.abyssinialaw.com

ደረጃ በሚገኝ ፍ/ቤት የተሰየሙ ዳኞች ያላቸው በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፣ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የፀደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ የሚፀናው በልዩ መፅሐፍ በነጋሪት ታትሞ ከወጣ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 3 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የመንግስት ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች በሙስና ወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆኑበት ወንጀል ዝርዝርና መሰረታዊ መርሆችን የሚደነግግ ከአንቀጽ 402 እስከ አንቀጽ 419 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም እና ከዚያ በኋላ የመንግስት ሰራተኛ በሆኑ ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህንንም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2" የወንጀል ህጉ ድርጊቱ በዚህ ህግ መሰረት ወንጀል ሆኖ በተሻረው የወንጀል ህግ ግን እንደወንጀል ካልተቆጠረና የተፈፀመው ይህ ህግ ከመጽናቱ በፊት ከሆነ ሊያስቀጣ አይችልም" በማለት ደንግጎታል፡፡

ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም መሆኑን በግልጽ አስፍሯል፡፡ የወንጀል ህጉ በፀናበትና ስራ ላይ በዋለበት ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካች የመንግስት ሰራተኛ እንዳልነበረ የተጠሪ የክስ ማመልከቻ ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረበው አመልካች የወንጀል ህጉ ከመጽናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት የመንግስት ሰራተኛ የነበረ መሆኑንና አመልካች ምርመራ በተጣራበት 2001 ዓ.ም በስሙ የተለያዩ ባንኮች ሒሳብ ከፍቶ ሲያንቀሳቅስ የነበረውን ገንዘብና በስሙ የገዛትን መኪና ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ሲያገኝ ከነበረው ደመወዝ ጋር በማመዛዘን ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ይዟል በማለት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ እንደማይችል በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም አገራችን ባፀደቀችው ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 "No one shalll be held guilty of any criminal offence on account of any act or omission which did not constitute a criminal offence under national or international law, at the time which the criminal offence was committed" በሚል መንገድ ተደንግጓል፡፡

አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው የኢፌዲሪ ወንጀል ህግ ከመጽናቱ በፊት ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት የነበራቸው የወንጀል የህግ ማዕቀፎች በ1949 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግና በ1974 ዓ.ም የወጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ቁጥር 214/1974 ናቸው፡፡ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተደነገገውና ይዘቱ የተዘረዘረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት ባላቸው የወንጀል ህግ ማዕቀፎች የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተደነገገ ድርጊት አይደለም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ከመፅናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት የመንግስት ሰራተኛ በነበረውና የወንጀል ህጉ ከመፅናቱ በፊት የመንግስት ስራውን ለቅቆ በንግድ ስራ መሰማራቱ በክርክር ሂደት

www.abyssinialaw.com

በተገለፀው አመልካች ላይ የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 በመጥቀስ ያቀረበው ክስ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 የዓለም አቀፉን የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን መሰረታዊ የወንጀል ህግ መርህ የሚጥስና የአመልካችን መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የተገለፀውን የህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ በማስፈፀም የተጠሪን የወንጀል ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ በመገኘት የሙስና ወንጀል፣ የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) 1 መሰረት በመሻር አመልካች በነፃ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) 1 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በነፃ እንዲሰናበት የተወሰነ በመሆኑ በሌላ ጉዳይ ካልታሰረ በስተቀር በዚህ ጉዳይ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት የመፈቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡
3. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የወሰኑት የገንዘብ መቀጮና በአመልካች ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብና ቁጥር 2-78716 ኢ.አ የሆነችው መኪና እንዲወረስ የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 74237

ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ተጠሪ፡- አብካለ እንደሻው ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም 1ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ፤-ተከሳሽ በተጨማሪ እሴት ታክስ ቁ.1079.39005 እና በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር( TIN) 00512280 ለከሳሽ መሥሪያ ቤት ግብር ከፋይ ሲሆን፤ ግብይት ሲያካሂድ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማከናውን የህግ ግዴታው ሆኖ እያለ በ07/08/2003 ዓ/ም ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት በተደረገው ድንገተኛ ክትትል ድርጅቱ ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ሲያከናውን በመገኘቱ በወ/ህ/ቁ/ 34(1) ፣አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56(1) እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣውን አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 22(1) እና 50(ለ)(1) የተደነገገውን በመተላለፉ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅትም ክስ የቀረበበትን ወንጀል አለመፈጸሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የግራ ቀኙ ማስረጃዎችን ፍርድ ቤቱ በመስማትና በመመዘን በሰጠው ፍርድ የከሳሽ ማስረጃዎች ያስረዱትን ፍሬ ነገሮች ተከሳሽ ድርጅት ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች በቂ በሆነ ሁኔታ አስተባብሏል በሚል በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.149(2) መሰረት በነጻ አሰናብቶታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ የሥር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)ለ)(2) መሰረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በሥር ፍርድ ቤቶች ወሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም ሲጠቃልል፡- ተጠሪው ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ያከናወነ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጦበት እያለ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ፍርድ ቤቶቹ ማስተላለፍ ሲገባቸው በወ/ህ/አንቀጽ 34(1) አንድ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል የሚጠየቀው ከድርጅቱ ሀላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ማራመድ ሲሆን ይህንኑ በአንቀፁ የተቀመጠውን ሁኔታ ባለማገናዘብ ከክሱ በነጻ እንዲሰናበት የወሰኑት ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- አንድ የንግድ ማህበር ወይም ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ/285/1994 እና ማሻሻያውን አዋጅ ቁ.609/2001 ተላልፏል በሚል በወንጀል ጥፋኛ ሊሰኝና ሊቀጣ የሚችለው የተጣሉበትን መሰረታዊ የግብር ከፋይነት ግዴታዎችን በመጣስ ሥርዓቱን በሚጻረር ህገ ወጥ የግብይት አሰራር ዘርግቶ ሲገኝ ወይም አሰራሩ ህገ ወጥ ግብይትን የሚያበረታታ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፣በዚህ ጉዳይም አንድ ዕለት ተፈጸመ በተባለና በተጨባጭም ባላተፈጸመ ስህተት ብቻ አዋጁን በሚጻረር መልኩ ህገ ወጥ የግብይት ሥርዓት ዘርግቷል ሊያሰኝና በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56(1) እንደተሻሻለው አንቀጽ 22(1) ሊያስቀጣ የሚችል አንድም ሁኔታ ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ በመገንዘብ በነጻ ያሰናበቱ ስለሆነ ውሳኔው የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው በሚል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- ተጠሪው ከቀረበበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማቱን የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሚያመለክት ሲሆን እነዚህ ሁለቱም ምስክሮች ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለው ወቅት በተጠሪ ድርጅት ጭማቂ (ጅውስ) የጠጡና ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይቱ የተፈጸመ ስለመሆኑ ያስረዳሉ በሚል የቀረቡ ናቸው፡፡ ምስክሮቹም ለሥር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያስረዱት ፍሬ ነገር- ድንገተኛ ፍተሻ ለማድረግ ሶስት ሆነው ወደ ተጠሪው ድርጅት ሄደው ሶስት ጭማቂ (ጅውስ) አዘው ጭማቂው ከመጣላቸው በኋላ ጠጥተው ብር 30 ለአስተናጋጁ ሰጥተው መልሱን ሲጠባበቁ ከቆዩ በኋላ አስተናጋጁም ዝም በማለቱ መልስ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ የሚመለስ ገንዘብ አለመኖሩን በመግለጹ ከ3-5 ደቂቃ ያህል ቆይተው ወደ ገንዘብ ያዥ (ካሸር) አስተናጋጁን ይዘው ሄደው የተቆረጠ ደረሰኝ መኖሩንና አለመኖሩን በመጠየቅና የተቆረጠ ደረሰኝ አለመኖሩን ማረጋገጣቸውንና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ጥራዝ (ፓድ) የጭማቂው ሽያጭ አለመመዝገቡን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምስክሮቹ የድርጅቱ ሥራ አስያኪያጅ በቦታው የነበሩ ስለመሆናቸው ለሥር ፍርድ ቤት ማስረዳታቸውን ፍርድ ቤቱ በፍርዱ ላይ አስፍሯል፡፡

የተጠሪ ምስክሮች ደግሞ ለስር ፍርድ ቤት ያስረዱት ፍሬ ነገሮች ፡-ተጠሪው ደርጅት ግብይት የሚያካሂደው በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መሆኑን፣ የድርጅቱ ሰራተኞችም በየዕለቱ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን ተከትለው እንዲሰሩ ተጠሪው ቅስቀሳ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከቀረቡት 2 የመከላከያ ማስረጃዎች 1ኛው የመከላከያ ማስረጃ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለው ዕለት በቦታው ባለመኖሩ ምክንያት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መቆረጡንና አለመቆረጡን እንደማያውቅ ማስረዳቱን፣ እንዲሁም 2ኛ የመከላከያ ምስክር ደግሞ በጊዜው የተሸጡ ጭማቂዎች ሶስት ብቻ እንደሆኑና በደረሰኝ ቁጥር 20925 ሁለት ጫማቂዎች፣ በደረሰኝ ቁጥር 20929 ደግሞ አንድ ጭማቂ የተሸጠ ስለመሆኑ ማስረዳቱን የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርዱ አመልክቷል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤትም እነዚህን የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ 3ኛ ተከሳሽ የነበረውን የተከሳሽ ድርጅት(ሐሮኒ ኢንተርናሽናል ሆቴል)ሥራ አስኪያጅ ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ምክንያት ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ ግብይት ወይም ሽያጭ ተፈጽሟል በሚል የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ አስተላልፎባቸዋል፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይ ሊሆን የሚችልበትን አግባብ የሚደነግግ ሲሆን በዚሁ ደንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (1) በሁለተኛው ፓራግራፍ አንድ ደርጅት ወንጀል እንዳደረገ

www.abyssinialaw.com

ተቆጥሮ የሚቀጣው ከህላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ፣ወይም ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት ፣በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ የተጠሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተከሰው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ እስከተሰጠባቸው ድረስም በወንጀል ህግ አንቀጽ 34(1) በሁለተኛ ፓራግራፍ መሰረትም ተጠሪው ድርጅት የወንጀሉ ተካፋይ እንደሆነ የሚቆጠር በመሆኑም ተጠሪው ድርጅት በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 34(1) አዋጅ ቁጥር 285/1995 አንቀጽ 56(1) ስር ጥፋተኛ መሆን ያለበት ነው፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ድርጅት ለግብሩ አከፋፈል የሚያገለግሉ ደረሰኞች የህትመት ፈቃድ ከአመልካች መ/ቤት በማግኘትና በሥራ ላይ በማዋል የሚጠበቅበትን አሟልቶ በመገኘት ለመንግሥት ገቢ መሆን ያለበትን ገንዘብ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ያመች ዘንድም ለድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በመቅጠር ስለ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሽያጭ ደረሰኝም ለሰራተኞቹ ትምህርትና ጥንቃቄ እንዲያደረጉ ተገቢውን ጥረት ስለማድረጉ የአመልካች ምስክሮች ከሳረዱት በተሻለ ሁኔታ የተጠሪው ምስክሮች ክሱን አስተባብለዋል በሚል ክክሱ ተጠሪው ድርጅት በነጻ እንዲሰናበት የወሰኑት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34(1) እና አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56(1) የተደነገገውን እና ይህ ችሎት የወንጀል ጥፋት በአንድ ድርጅት ተፈጽሟል ሊባል ስለሚችልበት ሁኔታ በተመሳሳይ ጉዳይ በሰ/መ/ቁ/48850 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ሀ) መሰረት በመሻር ተጠሪው ድርጅት በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽና እና በአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 56(1) ሥር ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 74237

ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐ/ሕግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- እብካለ እንዳሻው ጠ/ንግድ ኃ.የተ.የግል ማህበር - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ተብሎ ሲሆን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>ቅ ጣ ት</u>

ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1/ን የተላለፈ ጥፋተኛ የተባለ ሲሆን አጥፊ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት አለበት፡፡ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወ/ሕ/አንቀጽ 88/2/ ስር ያሉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህን ሁኔታዎች ተመልክቷል፣ አመዛዝኗልም፡፡

ተጠሪ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሲሆን ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ድርጊት የሚያስቀጣው ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በማያንስ እና ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከሁለት እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት መሆኑን አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለ ያሳያል፡፡ በተጠሪ አይነት ሰው ላይ ቅጣት የሚወሰንበትን አግባብ ደግሞ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 90 መሠረት መሆኑን የወንጀል ህጉ የሚገልፅ ሲሆን የሕግ ሰውነት ባለው አካል ላይ የገንዘብ ቅጣት እና እስራት በሚጣልበት ጊዜ የእስራት ቅጣቱ ሁኔታ ወደ ገንዘብ በመቀየር መሆኑን የአንቀጹ ንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ ይገልፃል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት እስከ አምስት አመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር አስር ሺህ፣ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ እስከ ብር ሃያ ሺህ፣ እስከ አስር ዓመት ለሚያስቀጣ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ፣ ከአስር ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ እስከተመለከተው ከፍተኛ ወሰን ማለትም እስከ ብር አምስት መቶ ሺህ ድረስ የገንዘብ መቀጮው ሊደርስ እንደሚችል ሕጉ ያሣያል፡፡ እንዲሁም የገንዘብ ቅጣትም በንዑስ ቁጥር አራት ድንጋጌ እንደተደነገገው እስከ አምስት እጥፍ እንደሚደርስ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90/3/ ድንጋጌ መሠረት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት እስከ ብር 20,000.00 ድረስ የገንዘብ ቅጣት እንደሚቀየር ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የተጠሪን የድርጊት አፈፃፀም ስንመለከተው ቀላል ተብሎ ሊመደብ የሚገባ በመሆኑ በአመልካች ላይ ሊጣል የሚገባው የገንዘብ መቀጮ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ ሁኖ የእስራት ቅጣቱን ደግሞ የሁለት አመት ጽኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህ የሁለት አመት ጽኑ የእስራት ቅጣት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90/3/ በተደነገገው ስሌት መሠረት ወደ ገንዘብ ሲቀየር የሚመጣው ብር 8,000.00 በመሆኑ እና ይህ ከገንዘብ መቀጮ ከብር 10,000.00 ጋር ሲደመር የሚመጣው ውጤት ብር 18,000.00 /አስራ ስምንት ሺህ ብር/ ተጠሪን የሚያርም፣ ሌሎችን የሚያስተምርና የሚያስጠንቅቅ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርግ፣ አመልካችም ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡

መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ.75387

ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች ፡- 1. አቶ ወርቁ ፍቃዱ ቀረቡ

2. አቶ ሹሜ አራርሶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቤ/ጉ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ክርክር ሲሆን የተጀመረውም በቤ/ጉ/ክልል በመተከል ዞን በቡላን ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የወረዳው ዐ/ሕግ በቁጥር 1569/2/89 በ28/11/03 በተፃፈ ማመልከቻ በአሁኖቹ አመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/እና 433 ስር የተደነገገውን ተላልፈው በ28/11/03 ከቀኑ 5. ሰዓት ላይ ከሚመለከተው ባለስልጣን ሳያስፈቅዱና ፈቃድ ሳይኖራቸው ከቡላን ወረዳ ደቢና ባሩዳ ቀበሌ 15 የቀንድ ከብቶችን ገዝተውና በመኪና ጭነው ወደ ታግኒ ከተማ ሲጓዙ ኬላ ላይ በመያዛቸው ያለፈቃድ ከብት የማዘዋወር ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ፍ/ቤቱም የዐ/ሕግን የሰው ማስረጃ እና የተከሳሾቹን የጽሑፍ መከላከያ ከመረመረ በኂላ በተከሳሾቹ ላይ በተከሰሱበት ድንጋጌ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በነፍስ ወከፍ የብር 1,200 መቀጮ ከወሰነ በኂላ በኤግዚቢትነት የተያዙት 15 ከብቶች ተሸጠው የጠባቂዎች አበል ከተቀነሰ በኂላ የሽያጩ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ በቀጣይ እርከን ለሚገኙ የክልሉ ፍ/ቤቶች ያቀረቡት ይግባኝ እና አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ሲሆን በ18/04/04 ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘትም በኤግዝቢትነት የተያዙት የቀንድ ከብቶች በወንጀል የተገኙ ናቸው ባልተባለበት እና አመልካቾቹ ጥፋተኛ የተባሉበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 433 ድንጋጌ የንብረት መውረስን ባልደነገገበት ሁኔታ ከብቶቹ ተወርሰው ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውና በበላይ ፍ/ቤቶች የፀናው ትእዛዝ ከወንጀል ድርጊቶች ጋር ተያይዞ ንብረት ስለሚወረስበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ የተመለከተውን መርህ የሚጥስ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በ26/06/04 በተፃፈ ማመልከቻ በሰጠው መልስ የውርስ ትእዛዙ ዋና ቅጣት ሳይሆን ተጨማሪ ቅጣት መሆኑ የዚህ ዓይነቱ የውርስ ትእዛዝ በወ/ሕ. አ. 761/ሀ/ 791 እንዲሁም በፌዴራል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/200 በአንቀጽ 60 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ያለውና የወንጀል ሕጉን መርህ

www.abyssinialaw.com

መሰረት ያደረገ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጐ የውርስ ትእዛዙ የተሰጠው በአግባቡ ነው ተብሎ እንዲፀና ተከራክሮአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡

በዚህም መሠረት አመልካቾቹ በተከሰሱበት ድንጋጌ የተሰጠባቸውን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ተቀብለው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አቤቱታ ያቀረቡት በውርስ ትእዛዙ ላይ ብቻ ሲሆን ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘውም ይኸው ነጥብ ነው፡፡ በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ ሊደረግ የሚችልባቸው ሁኔዎች በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ተደንግገው የሚገኙ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መካከልም በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ ፍ/ቤቱ የወንጀለኛው ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወረስ ሊወስን የሚችል ስለመሆኑ /አንቀጽ 98/ ፣አንድ ሰው ለወንጀል ስራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳው ወይም ወንጀሉን ለፈፀመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው ወይም ሊሰጠው የታቀደው ማናቸውም ጥቅም ሁሉ ለመንግስት ገቢ ስለሚሆንበት አግባብ /አንቀጽ 100/ እና ወንጀልን ለመፈፀም ያገለገሉ ወይም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች ስለሚወረሱበት አግባብ /አንቀጽ 140/ በመሠረታዊነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ና የቅጣት ውሳኔን ተከትሎ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰን የሚችሉትና የሚገባቸው እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ጥፋተኞች የተባሉበት የወ.ሕ.አ. 433 ድንጋጌ የንብረት ውርስን አልደነገገም፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የሚሰጥ የጥፋተኛነት ውሳኔ የንብረት መወረስን ወይም ለመንግስት ገቢ መደረግን የሚያስከትል መሆኑን የሚገልጽ ሌላ ድንጋጌ የለም፡፡ በአመልካቾቹ ላይ ክሱን ያቀረበው የቡለን ወረዳ ዐ/ሕግ የጥፋተኛነት ውሳኔን ተከትሎ ባቀረበው የቅጣት አስተያየት ከብቶቹ በውርስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ ያቀረበው ጥያቄ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ሆነ ቀጥሎ ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች ለንብረት ውርሱ ውሳኔ መሠረት ያደረጉትን ድንጋጌ በውሳኔአቸው አልገለጹም፡፡ ከብቶቹ ተሸጠው ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ከላይ ከተጠቀሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 98፣ 100 እና 140 ድንጋጌዎች በአንዳቸውም ቢሆን የሚሸፈን ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ በመልሱ የጠቀሳቸው በደንብ መተላለፍ ክፍል የሚገኙት የወ.ሕ. አ. 761(ሀ) እና 791 ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት እንደሌላቸው ከይዞታቸው መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ የፌዴራል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2000 አንቀጽ 60 ድንጋጌ አመልካቾቹ ያልተከሰሱበትና ጥፋተኛ ያልተባሉበት በመሆኑ ለንብረት ውርስ ውሳኔው መሠረት ሊሆን የሚችሉበት አግባብ አልተገኘም ፡፡ በመሠረቱ የወንጀል ሕግ ስለልዩ ልዩ ወንጀሎችና በወንጀል አድራጊዎች ላይ ስለሚፈፀሙት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች በዝርዝር እንደሚደነግግ እና ፍ/ቤቶች በሕግ ከተደነገጉት በቀር ሌሎች ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን እንደማይችሉ በወ.ሕ.አ. 2 (1) እና (2) ተመልክተዋል፡፡ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግን ጨምሮ ፍ/ቤቶች በወንጀል ረገድ የሚሰጡት ማናቸውም ውሳኔ በወ/ሕ/አ. 2 የተደነገገውን የሕጋዊነት መርህ መሰረት ያደረገ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህም ሁኔታ በኤግዚቢትነት የተያዙት ከብቶች ተሸጠው የጠባቂዎች አበል ከተቀነሰ በኋላ የሽያጩ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ /ውሳኔ/ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በኤግዚቢትነት የተያዙት ከብቶች ተሸጠው ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ይሁን በማለት የቡላን ወረዳ ፍ/ቤት በወ.መ.ቁ. 01035 በ04/12/03 የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 05832 በ11/12/03 የቤ/ጉ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 03253 በ04/03/04 እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03391 በ04/04/04 ከሰጡት ትእዛዝ ውስጥ የንብረት ውርሱን የሚመለከተው ክፍል በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በኤግዚቢትነት የተመዝገቡት 15 የቀንድ ከብቶች ከተሸጡበት ገንዘብ ውስጥ የጠባቂዎች አበል ተቀንሶ ለመንግስት ገቢ የተደረገው መጠን ለአመልካቾቹ ተመላሽ እንዲደረግ ወስነናል፡፡ የውሳኔው ቅጂ ይላክ፡፡
3. በበዓል ምክንያት ውሳኔው በአዳሪ በ17/05/05 ተነገረ
4. ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 82572

ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- መሪጌታ ፍቅረ ማርያም ካሴ ጠበቃ ማርታ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቤንች ማጂ ዞን ዐ/ሕግ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች በቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ መባሉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? እንዲሁም የተጣለበት የቅጣት መጠን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት በአግባቡ ተሰልቷል ወይስ አልተሰላም የሚሉትን ነጥቦች ለማየት በሚል ነው፡፡

በዚህ አከራካሪ ነጥብም ላይ ግራ ቀኙ በዚህ የሰበር ደረጃ በበኩላቸው ያላቸውን ክርክር በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

እኛም በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ የአሁን አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ እና ተጠሪ ዐ/ሕግ ለሰበር አቤቱታው ከሰጠው መልስ ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የሰው ህይወት ለማጥፋት አስቦና አቅዶ የፀቡ መነሻ ምን እንደሆነ ባልታወቀ ምክንያት ተነሳስቶ ሚዛን ከተማ ዕድገት ቀበሌ ውስጥ ልዩ ስሙ ሸኮ በር አካባቢ ወ/ሮ ጥንቅሽ መታፈሪያን ሰርቪስ ቤት ከዲማ የመጣ መሆኑንና የመጣውም በገብርኤል ቤተክርስቲያን በቅስና ሊያገለግል ተቀጥሮ እንደሆነ ትክክለኛ ስሙን በመቀየር ቄስ ዘካርያስ ነኝ በማለት ህዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም ከተከራየ በኂላ ህዳር 08 ቀን 2004 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ 7፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ቀን አብሮት ሲዘዋወር የነበረውን ሟች ሽፈራው ደሳለኝን ከተከራየው ቤት ውስጥ በመጫኛ ገመድ አንቆ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ አንገላቶ በጭካኔና ነውረኛ በሆነ መንገድ አንቆ ገድሏል በሚል በግፍ ሰው አገዳደል ወንጀል ክስ ተከሷል፡፡

ተከሣሹ የአሁን አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ የዐ/ሕግ የሰው ማስረጃዎች ቀርበው ተሰምተዋል፡፡ ሟች ታንቆ የተገደለበትም መጫኛ በኢግዚቢትነት ቀርቧል፡፡ የአስከሬን

www.abyssinialaw.com

ምርመራ ውጤቱንም የሚገልፅ ከሚዛን አማን ሆስፒታል የሰነድ ማስረጃ እና ሟች ሞቶ የተገኘበትን ሁኔታ የሚገልፅ ፎቶ ግራፍ በገላጭ ማስረጃነት ቀርቧል፡፡

በዐ/ሕግ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች እንደ ክሱ አቀራረብ ተከሣሹ ሌሊት በግምት 7፡00 ሰዓት አካባቢ ሲሆን ለሟች ሞት ምክንያት የሆነውን ድርጊት የፈፀመው የአሁን አመልካች ነው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችለውን ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ከሟች የተሰማውን ጩኸት ይህንን ጩኸት ሰምተው ሟች ሞቶ ወደ ተገኘበት ቤት ሄደው በሩን ቢደበድቡ ፤ ቢያንኳኩ ተከሣሹ መብራት አጥፍቶ ድምፅ እንዳልሰጠ ፤ በኋላ በሩን በቁልፍ ከኋላ በኩል እንደሚቆልፉበት ሲገልፁለት ሟች ታሞብኝ ነው ማለቱንና መብራት ያጠፋው ይጋጭብኛል በማለት እንደሆነ ሁሉ አስረድተዋል፡፡ አመልካች ይህንን ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት ለአቀደው ተግባር ዝግጅት ይሆን ዘንድ ስሙን በመቀየር ፤ የመጣበትም ተግባር ለቅስና አገልግሎት መሆኑን የመጣበትም አድራሻ ከትክክለኛው አድራሻ የተለየ መሆኑን ሁሉ ገልፆ ሟች ሞቶ የተገኘበትን ቤት መከራየቱንና ሟች ሞቶ ከቤት ውስጥ ከመገኘቱ በፊት ይኸው አመልካች በቤት አለመገኘቱን በጊዜው ከሁለቱ በቀር ሌላ ሰው አለመኖሩን ይልቁንም መጥፋቱን በኋላም በክትትል ከትክክለኛው አድራሻ መያዙን ሁሉ ገልፀው የመሰከሩ ሲሆን፤ የሟችን አሟሟት ሁኔታ ይገልፃል በተባለው የሟች አስከሬን ምርመራ ውጤት ላይ ደግሞ በሟች አንገት ላይ የመታነቅ ምልክት የነበረ እና ከቀኝ አይኑ የመመታትና የመበለዝ ምልክት የነበረ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሟች በሞተበት ጊዜ የተገኘው መጫኛም በችሎት የቀረበው መሆኑ በሰው ማስረጃዎችም ተነግሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም ከዚህ በላይ በዐ/ሕግ በኩል ክሱን ለማስረዳት የቀረበውን ማስረጃ ከክሱ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ተከሣሹ የአሁን አመልካች የወንጀሉን ድርጊት የፈፀመ ለመሆኑ ሊያረጋግጥ የሚችል አጥጋቢ ማስረጃ መሆኑን ጠቅሶ ይከላከል ሲል በይኗል፡፡ ይህም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ቀርቦ የተሰማ የታየ እና የተመረመረ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበን ክስ ለማስረዳት ባለው የማስረጃነት ክብደት በመመርመር ረገድ ባለው ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማረጋገጥና የተረጋገጠውን ጉዳይ በማስረጃነት በመመዘኑ ሥልጣን በመገልገል የሰጠው ዳኝነት በመሆኑ የአሁን አመልካች በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም የሚለው ክርክሩ የማስረጃ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 እንደተደነገገው ከላይ የሠፈረው የዐ/ሕግ ማስረጃ የቀረበውን የወንጀል ጉዳይ ለማስረዳት በወንጀል ጉዳይ መቅረብ ከሚገባው የማስረጃ የማስረዳት ሁኔታ /standard of proof/ አንፃር ይታይ ቢባልም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 የተመለከተውን ድንጋጌ በመፈፀም ረገድ የሥር ፍ/ቤት የህግ ስህተት መፈፀሙን የሚያመለክት ሆኖ አልተገኘም፡፡

የአሁን አመልካችም እከላከላለሁ በማለት የሰው ማስረጃዎችን አቅርቦ ቢያሰማም እነዚህ የሰው ማስረጃዎች ከፊሎቹ ስለጉዳዩ ምንም የሚያውቁት ጉዳይ አለመኖሩን ቀሪዎቹ ደግሞ በዐ/ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ጉዳይ ለማስተባበል የማይችል መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ማስረጃውን መዝኖ ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ከላይ እንደተመለከተው ይህ ማስረጃውን የመመዘን የዳኝነት ሥራ እንጂ የህግ ጥያቄን የሚያስነሳ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል በወ/መ/ሕ/ቁ 539/1/ ሥር የተመለከቱ ንዑሳን የህግ ክፍሎች እያሉ በየትኛው ንዑስ ክፍል የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፌ ድርጊቱን የፈፀምኩ ለመሆኑ በግልፅ ተጠቅሶ ባለመከላከሌ የተነሣ ክሱን በመከላከል ረገድ መብቴን አጣቧል በማለት ይከራከር እንጂ በቀረበበት የወንጀል ክስ ዝርዝር ላይ የተገለፁት ፍሬ ጉዳዮች በሙሉ የአመልካች አድራጉት ሰውን ለመግደል አስቦ አመቺ ጊዜና ቦታ መርጦ ሟችን የገደለው

www.abyssinialaw.com

መሆኑና አገዳደሉም ቢሆን ጭካኔንና ነውረኛነትን የተላበሰ መሆኑ ሁሉ የተገለፁ በመሆኑ አድራጎቱ በወ/ሕ/ቁ 539/1/ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ በሚል እንደሆነ እጅግ ግልፅ የሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111 እና 112 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አፈፃፀም ያልጣሰ በመሆኑ በዚህ በኩል ያቀረበውም የክርክር ነጥብ የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን አመልካች በወ/ሕ/ቁ 539/1/ሀ/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ሟችን በመግደሉ በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ነው በሚል የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ በአግባቡ ከመሆኑ በቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል በዚህ አጥፊ ላይ ተገቢውን ቅጣት ለመጣል የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ተቀብሎ በመረመረበት ጊዜ በአሁን አመልካች በኩል አንድ የቅጣት ማቅለያ መቅረቡን አረጋግጦ ተቀብሏል፡፡ ሆኖም የዚህ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ሊያስቀንስ የሚችል ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 16/7/ ስር በግልፅ ተመልክቶ እያለ ሁለት እርከን ብቻ መቀነሱ ይህንኑ የቅጣት መመሪያ ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ዐ/ሕግም ይህንኑ ተገንዝቦ በዚህ ረገድ ቅጣቱ ተስተካክሎ ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌለው ገልፆ መልሱን በፅሑፍ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በቅጣት አጣጣል ረገድ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ የተገለፁትን ሁሉ በማየት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10698 ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 50062 መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 50278 ሰኔ 12 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ሁሉ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ላይ በሥር በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. የአሁን አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር የተቀመጠውን የቅጣት ዓይነት መነሻ በማድረግ ፣ እና ዝቅተኛውን የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት በመያዝ በቅጣቱ መመሪያ አንቀጽ 13/8/ ላይ የተመለከተውን እርከን 38 የወደቀ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት መወሰኑን ተቀብለን ከዚሁ እርከን ላይ በፍርድ ሐተታው ላይ እንደተገለፀው ሶስት እርከን በአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሲቀነስ 35 እርከን ላይ የሚወድቅ በመሆኑ በዚሁ እርከን ላይ የተቀመጠውን የቅጣት አንጓ በማየት አመልካች ከህዳር 19 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ በአስራ ዘጠኝ ዓመት (በ19 ዓመት) ፅኑ እስራት ይቀጣ በማለት አሻሽለን ወስነናል፡፡
4. በዚህ ተሻሽሎ በተወሰነው የቅጣት ውሣኔ መሠረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለሚዛን ማረምና ማነፅ ተቋም ትዕዛዝ ይድረሰው ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ዲ

www.abyssinialaw.com

# ባንክና
# ኢንሹራንስ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 76977

ህዳር 7 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኒያላ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ነገረ ፈጅ አቶ ዮሴፍ ገብሬ ቀረቡ

ተጠሪዎች- 1. አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ነገረ ፈጅ አቶ አወል ማስረሻ

2. አቶ እንድሪስ አደም በሌሉበት ተወስኗል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ ጉዳዩ በንብረት ላይ በደረሰ ጉዳት የኢንሹራንስ ሰጭው ያለበትን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበው የዳረጎት ክስ ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቁጥሩ 3-16776 ኢት የሆነው የሁለተኛ ተጠሪ መኪና የመድን ሽፋን የሰጠሁትን የሰሌዳ ቁጥር 3-35774 /ኢት/ የሆነ መኪና ግንቦት 9 ቀን 2000 ዓ.ም በመግጨት ጉዳት አድርሶበታል፡፡ መኪናውን ለማስጠገን ብር 30,556.52 /ሰላሳ ሺህ አምስት መቶ ሀምሣ ስድስት ብር ከሀምሳ ሁለት ሳንቲም/ አውጥቻለሁ፡፡ ስለዚህ ይህንን ገንዘብ ይተኩልኝ በማለት በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ጉዳት ያደረሰው መኪና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የመድን ሽፋን ሰጥቷል፡፡ በክርክሩም የሶስተኛ ወገን ተከራካሪ ሆኖ ይጠራልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በክርክሩ ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ እንዲሆን ተጠርቶ ገብቶ ለጉዳቱ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና ኃላፊነት አለብህ ከተባልኩም የምከፍለው ካሳ መጠን ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ያነሰ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል ፡፡

የስር ፍርድ ቤት ጉዳት ያደረሰውን የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 (ኢት) የሆነው ተሽከርካሪ ይሽከረክር በነበረው በሁለተኛው ተጠሪ ሹፌር ጥፋት ነው በማለት አመልካች ክስ ያቀረበቡትን ገንዘብ ለአንደኛ ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች የካቲት 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈው የሰበር አቤቱታ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሰሌዳ ቁጥር ኢት 3-16776 ለሆነው መኪናና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-07520 ኢት ለሆነው ተሳቢ ነው። የአንደኛ ተጠሪ መኪና የተገኘው ተሽካርካሪውን የሚያንቀሳቅሰው ሞተር በተገጠመለት የሰሌዳ ቁጥር 3-16776/ኢት/ ሳይሆን ከዚህ መኪና ጋር ተገጥሞ ሲጎተት በነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን ባልሰጠው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-06469 (ኢት) በሆነው ተሳቢ ተገጭቶ ነው። ስለዚህ የቀረበውን ክርክርና የፅሑፍ ማስረጃ በአግባቡ ሳይመረምር አመልካችን በኃላፊነት ይጠይቃል በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

ተጠሪ በበኩሉ ሰኔ 10 ቀን 2004 ዓ.ም አመልካች የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776 ኢት ለሆነው መኪና ከነተሳቢው የመድን ሽፋን እንደሰጠ አምኗል። የሰሌዳ ቁጥሩ 3-06469 የሆነው ተሳቢ መኪና ነው። ይህ ተሳቢ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው መኪና እየተጎተተ ሲሄድ ጉዳት ማድረሱ ካልተለየ የመኪና ላይ የተጫነ እቃ ወይም የሚጎተት አካል የደረሰው ጉዳት ባለመኪናውና ለመኪናው የመድን ሽፋን የሰጠው ሰው በኃላፊነት መጠየቃቸው ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል። አመልካች የመድን ሽፋን በሰጠሁት የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 (ኢት) እና ጉዳት በደረሰበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-35774 (ኢት) መካከል ምንም አይነት አካላዊ ንኪኪ የለም። ስለዚህ የመድን ሽፋን ባልሰጠሁት አካል ጋር ተገምቶ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የምንጠየቅበት ምክንያት የለም በማለት ሐምሌ 5 ቀን 2004 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተሳቢ የሰሌዳ ቁጥር 3-06469(ኢት) በአንደኛ ተጠሪ ደንበኛ ላይ ያደረሰውን ጉዳት የመሸፈን ኃላፊነት አለበት በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክርና ባቀረቡት ማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮች መመልከት ተገቢ ነው። አመልካች የተጠሪ ንብረት ለሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776 (ኢት) ለሆነ የጭነት መኪናና በዚሁ መኪና ለሚጎተተው የተሳቢ ቁጥሩ 3-07520 (ኢት) ለሆነው ተጎታች ሀምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በተፈረመ የመድን ውል በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ተረድተናል። ከዚህ በተጨማሪ የአንደኛ ተጠሪ ደንበኛ መኪና በሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-35774 (ኢት) የሆነው መኪና የተጎዳው የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 (ኢት) ከሆነው መኪና ጋር ተገጥሞ ሲጎተት በነበረው የተሳቢ ቁጥሩ 3-06469 /ኢት/ በሆነው ተጎታች የኋላ ክፍል ተገጭቶ መሆኑን በትራፊክ ፕላን መግለጫና በትራፊክ ፖሊስ በተሰጠው የምስክርነት ቃል የተረጋገጠ መሆኑን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን መዝገብ ቁጥር 169698 በማስቀረብ ተረድተናል። ይህም አመልካች የመድን ሽፋን የተሰጠውን የተሳቢ ቁጥር 3-07520 /ኢት/ የሆነው ተጎታች ሣይሆን የመድን ሽፋን ያልተሰጠውን የተሳቢ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-06469 /ኢት/ የሆነው ተጎታች በማንቀሣቀስ ላይ እያለ፣ የተሳቢው የኋላ ክፍል የአንደኛ ተጠሪ መኪናን በመግጨት ጉዳት ያደረሰበት መሆኑን የሚያሣይ ነው።

www.abyssinialaw.com

2. ከላይ የገለፅናቸው ፍሬ ጉዳዮች የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 /ኢት/ በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲጎተት በነበረው የተሳቢ ቁጥሩ 3-66469 ኢት የሆነው ተጎታች ለደረሰው ጉዳት፣ የባለሞተሩ መኪና ባለሀብት የሆነው ሁለተኛ ተጠሪ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን ከፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081/1/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ አደጋው የደረሰው በሁለተኛው ሠራተኛ /ሹፌር/ ጥፋት መሆኑ ስለተረጋገጠ ሁለተኛ ተጠሪ በፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 2130 ድንጋጌ መሠረት ጉዳቱን የመሸፈን ኃላፊነት ይኖርበታል።

በሌላ በኩል አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-16776/ኢት/ የሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ሲንቀሣቀስ ለሚያደርሰው ጉዳትና፣ ይህ መኪና ተጎታች በሚጎትትበት ጊዜ የተሳቢ ቁጥሩ 3-07520 /ኢት/ የሆነውን ተጎታች ብቻ ሲያንቀሣቅስ በተጎታቹ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ለመሆን የመድን ውል ተዋውሏል። አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 /ኢት/ የሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ማናቸውንም አይነት ተጎታች ሲያንቀሣቅስ፣ በተጎታቹ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ለመውሰድ አልተስማማም። ኢንሹራንስ ሰጭው በውሉ ለተመለከተው አደጋ ብቻ መድን ለገባው ሰው መድን እንደሚሆን በንግድ ሕግ ቁጥር 663 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል። እንደዚሁም ኢንሹራንስ ሰጭው በውሉ ውስጥ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ወይም በውሉ የተስማሙበት ቀን በደረሰ ጊዜ የተስማሙበትን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ እንዳለበትና ይህ ግዴታው በውለታው ከተጠቀሰው ሊበልጥ እንደማይችል "የኢንሹራንስ ሰጭው ግዴታ" በሚል ርዕስ ባለው በንግድ ሕግ ቁጥር 665 ተደንግጓል። አመልካች የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776 /ኢ.ት/ የሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ መኪና የተሳቢ ቁጥሩ 3-07520/ኢት/ የሆነውን ተጎታች ሲጎትት፣ በተጎታቹ ለሚደርሰው ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን፣ ከዚህ የመድን ሽፋን ከሰጠው ተጎታች ውጭ ሌላ ተሳቢ ሲጎትት፣ በተጎታች የሚደርስ ማናቸውንም ጉዳት ለመሸፈን የመድን ውል አልተዋዋለም። ይህ ከሆነ የአንደኛ ተጠሪ ደንበኛ መኪና ጉዳት የደረሰበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776/ኢት/ በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ተገጭቶ ሣይሆን፣ በዚህ ባለሞተር መኪና ሲጎተት የነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን ያልሰጠው የሰሌዳ ቁጥር 3-06469 /ኢት/ በሆነው ተሳቢ የኋላ ክፍል ተገጭቶ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል።

ስለሆነም አመልካች ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ከገባው የመድን ውል ውጭ፣ የሁለተኛው ተጠሪ መኪና የመድን ሽፋን የሌለውን ቁጥሩ 3-06469/ኢት/ የሆነውን ተሳቢ እየጎተተ ሲያንቀሳቅስ በተሳቢው ግጭት ላደረሰው ጉዳት አመልካች በኃላፊነት ይጠይቃል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የንግድ ህጉን አንቀጽ 663 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 665 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል።

2. በአንደኛው ተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች በኃላፊነት አይጠየቅም በማለት በንግድ ሕግ አንቀጽ 633/1/ እና አንቀጽ 665/1/ መሠረት ወስነናል።

3. በአንደኛው ተጠሪ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት ያለበት ሁለተኛው ተጠሪ ነው በማለት ወስነናል።

www.abyssinialaw.com

4. ሁለተኛው ተጠሪ አንደኛ ተጠሪ የደንበኛውን መኪና ለማስጠገን ያወጣውን ብር 30,556.62 /ሰላሣ ሺህ አምስት መቶ ሀምሳ ስድስት ብር ከስልሳ ሁለት ሣንቲም/ ከኅዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለዳኝነት፣ ለጠበቃ አበልና ኪሣራ የወሰነውን ብር 3,102 /ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሁለት ብር/ ከጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአንደኛው ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

# አፈፃፀም

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 79860

ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

ተኽሊት ይምሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ራኬብ መለሰ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ ለመንግስት እንዲወረስ ከተወሰነው ከአንድ አጥፊ ንብረት ውስጥ ለቤተሰብ ህይወትና መተዳደሪያ ሊውል የሚገባው ድርሻ ሊሸፍናቸው የሚገባቸውን የወጪ አይነቶችንና መጠናቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 81406 በሆነውና ታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. በተሰጠው የወንጀል ጉዳይ የፍርድ ባለመብት በመሆኑ በወንጀል ጉዳዩ 3ኛ ተከሳሽ የነበሩትና አጥፊነታቸው ተረጋግጦ ንብረታቸው ለመንግስት ውርስ እንዲሆን የተወሰነባቸው የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ጌቱ ወርቁ ንብረቶችን አይነታቸውን ዘርዝሮ ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ የአስከፈተው የአፈጻጸም ማመልከቻ ነው፡፡የአፈፃፀም መዝገብ የተቀበረለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳው ጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን የአሁኗ አመልካች በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ ሰኔ 09 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ የመቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በዋናው የወንጀል ጉዳይ ላይ አቶ ጌቱ ወርቁ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸው በመረጋገጡ ምክንያት ሀብታቸው /ንብረታቸው/ በመንግስት እንዲወረስ ፍርድ ማረፉን፣በፍርዱ ላይ የልጆቹና የሶስተኛ ወገኖች መብት የተጠበቀ መሆኑንና እነዚህ መብቶች ከታዩና ከተመረመሩ በኋላ የአቶ ጌቱ ወርቁ ግማሽ ድርሻ ላይ የሚቀነሰው ከተቀነሰ በኋላ ተራፊ የሆነው ድርሻው ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ መወሰኑን ዘርዝሮ የአሁኗ አመልካች ሚስት በመሆናቸው ግማሽ ድርሻቸው እንዲጠበቅላቸው የፍርድ አፈጻጸሙን የያዘው ችሎት የወሰነ ሲሆን የልጆቹን መብት በተመለከተም በዋናው የወንጀል ጉዳይ ለተቀረው የቤተሰብ ሕይወትና መተዳደሪያ ወይም አስፈላጊ ለሆኑት የእለት ምግብና ለኑሮአቸው መደገፊያ የሆኑ ልዩ ልዩ ገቢዎች ሊወረሱ እንደማይችሉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 98(1(ለ)) መደንገጉንና ይህም በፍርድ አፈጻጸም ሂደትም የፍርድ ባለእዳ ልጆች መብት የተጠበቀ መሆኑንና የፍርድ ባለእዳው የእድሜ ልክ ፍርደኛ ቢሆንም በልጆች አስተዳደግ ላይ በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ሊወጡ እንደሚገባ እንደሚያስገነዝብ ፍርድ ቤቱ መረዳቱን ጠቅሶ ለህምክና፣ ለትምህርት፣ ለትራንስፖርት የስድስት ወር ወጪአቸው

ሊወረስ እንደማይገባ እንዲሁም ለመጠለያ፣ ለልብስና ለምግብ የሚያስፈልጋቸው ወጪ ለልጆቹ ሕይወትና መተዳደሪያቸው ወይም አስፈላጊ የሆኑ የእለት ምግብ ፣ለኑሮአቸው መደገፊያ አስፈላጊ በመሆናቸው ልጆቹ ራሳቸውን እስከሚችሉ ማለትም አስራ ስምንት አመት እስከሚሞላቸው ድረስ ወጪዎቹ ሊወረሱ እንደማይገባ፣ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ ተብሎ የቀረበው ግን በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይት እንደሌለው ገልጾና ለህክምና የስድስት ወር ወጪያቸው በወር ብር 1500.00 ሲታሰብ ለእያንዳንዳቸው ብር 900.00፣ የትምህርት ክፍያ የስድስት ወር ወጪ ለእያንዳንዱ ልጅ ብር 6243.00፣የትራንስፖርት ወጪ ብር 1000.00 ሲሆን እንደሚገባና በአንድ ልጅ ለ6 ወር ብር 3000.00 ሲሆን እንደሚገባ፣ለልብስና ለቀለብ የቀረበው ወጪም በወር ለአንድ ልጅ ብር 1500.00 ሲሆን እንደሚገባና ስሌቱም ልጆቹ አስራ ስምንት አመት እስከሚሞላቸው ሲታሰብ እንደሚገባ ገልጾ ለምስጋና ጌቱ ለልብስና ለቀለብ ብር 190,500.00፣ለአማንድ ጌቱ ደግሞ ብር 217,500.00 በጠቅላላ የሁለቱ ልጆቹ ወጪ ብር 428,286.00 እንደሚሆን እና የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ጌቱ ወርቁ ከወጪው ግማሹን የመሸፈን ግዴታ እንደአለባቸው ደምድሞ ብር 214,143.00(ሁለት መቶ አስራ አራት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሶስት ብር) ለመንግስት ውርስ ከሚሆነው ከፍርድ ባለእዳው ንብረት ላይ እንዲቀነስ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ የውሳኔ ክፍል የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱቱ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ያቀረቡት የቅድሚያ ግዥ መብት መታለፉ ያላግባብ ነው፣የልጆች የትምህርት፣ የሕክምናና የትንስፖርት ወጪ የስድስት ወር ብቻ ታስቦ ሌላው ተቀባይነት ማጣቱ ከልጆቹ መብትና ጥቅም አንፃር ያልታየ ነው በማለት ዘርዝረው ውሳኔው እንዲታረም ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የቅድሚያ መብት የመታለፉና የልጆቹ የህክምና፣ የትምህርትና የትራንስፖርት ወጪ ለስድስት ወር ብቻ እንዲታሰብ የመደረጉን አግባብነት ከወ/መ/ሕ/አንቀፅ 98(1(ለ)) ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር ተብሎ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፍርድ ባለእዳው ንብረት እንዲወርስ በወንጀል ችሎት ውሳኔ ያረፈበት መሆኑና የሶስተኛ ወገኖችና የልጆች መብት ግን የተጠበቀ መሆኑ በዋናው ፍርድ ጭምር የሰፈረ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን፣አመልካች የፍርድ ባለእዳ ባለቤት ሲሆኑ እንዲወረስ በተወሰነው ንብረት ላይ ግማሽ ድርሻ ያላቸው መሆኑና በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ አቤቱታ ሊያቀርቡ የቻሉት መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና የልጆቹ የቀለብ፣የልብስ፣ የትምህርት ፣የህክምና እና ትራንስፖርት ወጪ ለመንግስት ውርስ ከሚሆነው የፍርድ ባለእዳው ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀነስላቸው መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ግማሽ ድርሻ የጠበቀላቸው ቢሆንም ስለቅድሚያ ግዥ ጥያቄ ግን በትዕዛዙ ላይ ያሰፈረው ነገረ የሌለ ሁኖ የልጆችን የትምህርት፣ የህክምና እና የትራንስፖርት ወጪ ግን ለስድስት ወር ብቻ እንዲታሰብላቸው፣ ቀለብና ልብስ ግን እድሜአቸው አካለ መጠን እስከሚደርሱ ድረስ በወር ብር 1500.00 እንዲታሰብላቸው ስሌት ይዞ የወሰነ መሆኑን ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን በሚመለከተው መልኩ ተመልክተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**አመልካች ያቀረቡን የቅድሚያ መብት ጥያቄ በተመለከተ፡-** አመልካች ለጥያቄአቸው መሰረት ያደረጉት ከፍርድ ባለእዳ ጋር ያላቸውን የጋራ ባለሃብትነት መብት ነው፡፡ ይህ መብት መሰረቱ ጋብቻ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የክርክሩ ምንጭ የወንጀል ጉዳይ በመሆኑ ይህንኑ የሚገዛው ቀጥተኛ ሕግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 98(ለ(መ)) ሁኖ የሶስተኛ ወገኖች መብት የሚጠበቅበትን አግባብ ከሚደነግግ በስተቀር እነዚህ ወገኖች በንብረቱ ላይ የቅድሚያ ግዥ መብት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በግልጽ አይደነገግም፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ የአመልካች የቅድሚያ መብት ጥያቄ ቢጠበቅላቸው ተቃውሞ የሌለው መሆኑን በስር ፍርድ ቤት አስተያየት የሰጠ ከመሆኑም በላይ በዚህ የሰበር ደረጃም በጉዳዩ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን የመልሱ ይዘት ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች የቅድሚያ ግዥ መብት የማይጠበቅበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ጥያቄ በዝምታ ማለፋቸው ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡

**የልጆችን የትምህርት፣የህክምና እና የትራንስፖርት ወጪን በተመለከተ** ፡-በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች የቀረበውን መጠን የተጋነነ መሆኑን አስልተው ተገቢ ነው ያሉትን መጠን ለይተው ወስነዋል፡፡ የወንጀለኛውን ንብረት መወረስን በተመለከተ የሚደነግገው የወንጀል ህግ አንቀፅ 98(3(ለ)) ስር ቢያንስ ለስድስት ወር ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ልዩ ሁኔታዎችን አይቶ ይገባል ብሎ በሚገምተው ምክንያት ለተገለጸና በቂ አስተያየት ሊሰጠው ተገቢ በሆነ ውሳኔ ከዚህ ለሚበልጥ ጊዜ ለተቀጪው ቤተሰብ ሕይወትና ለመተዳደሪያቸው ወይም አስፈላጊ የሆኑት የእለት ምግብና ለኑሮአቸው መደጐሚያ የሆኑ ልዩ ልዩ ገቢዎች ሲሆኑ እንዳይወረሱ ለማድረግ እንደሚገባ ሕጉ ያሳያል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አቀራረፅ፣ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የተቀጪው ቤተሰብ ሕይወትና መተዳደሪያ ወይም አስፈላጊ የሆኑት  የእለት ምግብና ለኑሮአቸው መደገፊያ የሆኑ ለልዩ ልዩ ገቢዎች የሚሆኑትን የወንጀለኛውን ንብረቶች ለመንግስት ውርስ እንዳይሆኑ ለማድረግ የሚቻለው ቢያንስ የስድስት ወራት ጊዜአትን መነሻ አድርጎ መሆኑን፣ከዚህ ወራት በላይ ደግሞ እንደነገሩ ሁኔታ መወሰን የሚችልበት አግባብ መኖሩን ነው፡፡ በመሆኑን ፍርድ ቤቱ ከስድስት ወራት ላላነሰ ጊዜ እንዲወስን ሕጉ ግዴታ ከሚጥልበት በስተቀር ከዚህ በላይ ለሆነው ጊዜ ወይም ለማንኛውም  ጉዳይ የተቀጪው ንብረት ከውርስ ቀሪ እንዲሆን ለማድረግ የማይቻል መሆኑን ሕጉ ያሳያል፡፡ የሕጉ መሰረታዊ ዓላማም ጥፋት ያልሰሩ የተቀጪው ቤተሰቦች ያላግባብ እንዳይጎዱ መጠበቅና ወንጀለኛው በተገቢው መንገድ እንዲታረም እና ቅጣቱ ሌላውን እንዲያስተምር በማድረግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87 እና 1 ስር የተመለከተውን ለማሳካት ነው ተብሎ ይታሳባል፡፡ በመሆኑም የወ/ሕ/አንቀጽ 98(3((ለ)) ድንጋጌ በፍርድ ቤቱ ላይ የሚጥለው ግዴታ አነስተኛ የጊዜ ገደብ ስድስት ወር ከመሆኑ ውጪ ለተቀጪው ቤተሰብ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ለረዥም ጊዜአት እንዲሆኑ እንዲታሰቡ አይደለም፡፡

ለስድስት ወር የተያዘው ወጪ መጠን ያነሰ ነው የሚለው የአመልካች የቅሬታ ነጥብ ሲታይ በማስረጃ የሚነጥርና ይህንኑ ለማድረግ በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች የሚያከናውኑትና በፍቅድ ስልጣናቸው (Discretionary power) ስር የሚወድቅ እንጂ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት በተሰጠው የመሰረታዊ ህግ ስህተት የማረም ስልጣን ስር የሚወድቅና የመሰረታዊ ህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ሁኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ቅሬታቸቸውን ከሕጻናቱ የትህምርት  እና የህክምና ሕገ መንግስታዊ መብት ጋር አያያዝው ያቀረቡት ቅሬታ ሲታይም ህጻናቱ ከአባታቸው ድርሻ የስድስት ወር ወጪ እንዲያገኙ በመደረጉ ምክንያት ብቻ ይኼው የትምህርትና የህክምና መብታቸው አደጋ

ላይ የሚድቅበት አጋጣሚ ወደፊት የሚከሰት መሆኑን የሚጠቁሙ መነሻ የክርክር ነጥቦችን በማስረጃ ያመላከቱበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የክርክሩ ሂደት በግልፅ የሚያሳየው ጉዳይ ሁኖ ስለአገኘን የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም ብለናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የትምርት፣የህክምና እና የትራንስፖርት ወጪ ለህጻናቱ ለስድስት ወር ብቻ እንዲታሰብ ማለፋቸውን ገልፀው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 98(3(ለ)) ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ስልጣን አድማስ ያላገናዘበ ሁኖ ስለአገኘን ቅሬታውን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 175740 ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 115859 መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የግማሽ ድርሻ በሆኑባቸው ንብረቶች የቅድሚያ ግዥ መብት ቢያገኙ ተጠሪ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን የገለጸ በመሆኑ ይኼው መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ብለናል፡፡
3. የልጆችን የትምህርት፣የሕክምና እና የትራንስፖርት ወጪን በተመለከተ የበታች ፍርድ ቤቶች ለስድስት ወር ብቻ እንዲሆን ማሰባቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 98(3(ለ)) ድንጋጌ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.81616

ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሪታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ አ.ማ ነ/ፊጅ ሰላማዊት አዳነ ቀርቧል

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ሰላማዊት ጥላሁን
2. አቶ ነጋሲ በርሔ
} ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በት/ብ/ክ/መንግስት የአክሱም ዞን ማእከላዊ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው የፍርድ አፈፀም ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚያ ፍ/ቤት አመልካች የፍርድ አፈፀም ከሣሽ በመሆን ተጠሪዎች ላይ በፍ/ቤት ላስፈረደው ውሣኔ አፈፀም እንዲውልለት በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ በተሽከርካሪ ሰ.ቁ. 3-27506 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ ተይዞ በሀራጅ ተሸጦ እዳው እንዲከፈለው ፍ/ቤቱን ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ተጠቃሹ ተሽከርካሪ በሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት በኩል እንዲታገድ ትእዛዝ ሲያስተላለፍ ተሽከርካሪዋ ቀደም ብላ በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በሌላ ምክንያት የታገደች መሆኑ በጽሑፍ ተገልፆለታል፡፡ ከዚህ በኃላ ተሽከርካሪዋ ቀደም ብላ በሌላ ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ የተሰጠባት የአፈፃፀም ከሣሽ (የአሁኑ አመልካች) ጭምር በጉዳዩ ተከራካሪ ወገን በሆነበት መዝገብ ላይ መሆኑን ፍ/ቤቱ ተገንዝቤያለሁ በማለት ይህ ቀደም ብሎ የተሰጠው እግድ ሣይነሣ ተሽከርካሪዋን ሽጦ ለፍርድ አፈፀሙ ማዋል ስለማይችል የአፈፃፀሙ ከሣሽ ሌላ የንብረት ዝርዝር እስከሚያቀርብ ድረስ ለጊዜው መዝገቡን በመዝጋት ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዘ ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢቀያርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንን ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ ተሽከርካሪዋ ላይ የቅድሚያ መብት አለኝ የሚል ወገን ሣይኖር ፍ/ቤቱ በራሱ በሌላ ፍ/ቤት የተሰጠው እግድ ሣይነሣ እንዲሸጥ ማዘዝ አይቻልም በማለት የሰጠው ትእዛዝ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በተሽከርካሪዋ ላይ ከአመልካች የቀደመ መብት ያለው 3ኛ ወገን ስለመኖሩ አልተረጋገጠም እንጂ ቢኖርም ይህ መኪናዋ እንዳትሸጥ የሚከለክል አለመሆኑን መኪናዋንም በዋስትና ይዘን በዚህ ምክንያት ከማንም በፊት ያሣገደው አመልካች ሆኖ እያለ በሌላ

ፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሣይነሣ በመኪናዋ ላይ ውሣኔውን ማስፈፀም አይቻልም መባሉ ከሕግና ሥነ ሥርዓት ውጪ በመሆኑ ትእዛዙ ተሽሮ አፈፃፀሙ በመኪናው ላይ እንዲቀጥል እንዲታዘዝላቸውና ወጭና ኪሣራ እንዲከፈላቸው ጭምር ጠይቋል፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም አመልካች መኪናዋን በዋስትና በመያዝ ለተጠሪ አበድሮ የነበረው ገንዘብ መኪናዋን የገዛት አቶ ደረጀ ወንድሙ የሚባል ከፍሎ ካጠናቀቀ በኃላ አመልካች የመኪናዋን ሊብሬ ሊያስረክበው ፊቃደኛ ባለመሆኑ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት መ.ቁ. 179925 በሆነው ላይ አመልካች መኪናዋን በዋስትና ይዞ ያበደረው ገንዘብ የተከፈለው በመሆኑ የመኪውን ሊብሬ እዳውን ለከፈለውና መኪናውን ለገዛው ሰው እንዲያስረክብ ተወስኖበታል፡፡ ሊብሬውንም በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት አፈፃፀም መ.ቁ. 195425 በሆነው ላይ አመልካች መኪናውን ለገዛው ሠው በፍርድ ቤት ትእዛዝ አስረክቧል፡፡ ይህ ውሣኔና ትእዛዝ በሕግ አግባብ ባልተሻረበት ሁኔታ አመልካች ከቅን -ልቦና ውጪ እያቀረበ ያለው ክርክር ውድቅ ተደርጎ በቂ ኪሣራ ተቆርጦላቸው እንዲሰናበቱ የሚል ነው፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከለይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክሩ መነሻ የሆነችው መኪና ላይ ቀደም ብሎ በሌላ ፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሣይነሣ መኪናዋን እንድትሸጥ ማድረግ አይቻልም መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነችው መኪና ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ከሰጠው የእግድ ትእዛዝ ቀደም ብሎ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ራሱ የክርክሩ ተካፋይ በሆነበት መዝገብ ላይ የታገደች መሆኑ በአመልካች አልተካደም፡፡ ይህ ደግሞ በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ተከራክሮ ያጣውን ወይም የተከለከለውን መብት ከሕግ ስነ-ሥርዓትና ቅን -ልቦና ውጭ በሆነ አኳኃን ፍርዱን በሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ለመጐናፀፍ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ መኪናዋ ለፍርዱ አፈፃፀም ተከብራና ተይዛ የምትሸጥበት የሕግ አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ ይህ ከወዲሁ የሚታወቅ ከሆነም ፍ/ቤቱ በመኪዋ ላይ መብት አለን የሚሉ ወገኖችን ክርክር የግድ የሚጠብቅበት ሁኔታም አይኖርም፡፡

በተጨማሪም መኪናዋን ቀደም ብዬ ከማንም በፊት በዋስትና ይዣለሁ የሚለው ክርክርም ቢሆን በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ ክርክር ከመሆኑ ባሻገር ይህም ቢሆን በዚህ መዝገብ ላይ ሊነሣ የሚገባው ክርክር ሣይሆን አመልካች ራሱ የክርክሩ ተካፋይ በነበረበት የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቦች ላይ ሊነሣ የሚገባው ክርክር ነው ሲጠቃለል በሥር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ላይ የተፈጠረ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሣ ኔ**

1. በዚህ ጉዳይ የአክሱም ዞን ማእከላዊ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 17188 ሚያዚያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 52873 ሰኔ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

# አእምሯዊ ንብረት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.78856

ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወዳጆችና ቤተሰቦች ማህበር ጠበቃ አቶ ታዬ ወጂ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ኤሊያስ አሰጋኸኝ ጠበቃቸው አቶ ያለልኝ ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካችም 1ኛ ተከሳሽ፣የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ ከሳሽ የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ/ም ያቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ በቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑትን ሰዎች ለማሰብ ሐውልት ለማሰራት የሐውልት ኪነ ቅርጽ አወዳድሮ ለመምረጥ ባወጣው ጨረታ ተወዳዳሪ በመሆን ያዘጋጀሁትን ቅርጽ በ1990 ዓ/ም ያስረከብኩ ቢሆንም ተከሳሹ ቅርጹን ከተረከበ በኋላ ማሸነፍ አለማሸነፌን ሳይገልጽልኝ እያመላለሰኝ ከቆየ በኋላ የራሱ ቅርጽ እንደሆነ በማስመሰል ለመገናኛ ብዙኃን ያሰራጨ በመሆኑ፣ 2ኛ ተከሳሽም የቅርጹን ምስል የያዙትን 60,000 ቴምበሮች በማሳተም አንዱን በብር 3.00 በመሸጥ ብር 180,000 የሰበሰበ ስለሆነ ተከሳሾቹ የከሳሽን የፈጠራ መብት በመጣስ ከቅርጹ ማግኘት የሚገባኝን ብር 100,000 በማሳጣት የብር 280,000 ጉዳት ያደረሱብኝ ስለሆነ የሂሊና ጉዳት ብር 150,000 ጨምረው በድምሩ ብር 580,000 እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተከሳሾችም ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በ12/04/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በብይን ውደቅ ማድረጉን ከፍርዱ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ 1ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ፡-1ኛተከሳሽ የተቋቋመው በ1995 ዓ/ም ሲሆን ከሳሽ ቅርጹን ሰጥቻለሁ የሚለው በ1990 ዓ/ም በመሆኑ ከከሳሽ የተቀበልኩት ቅርጽ የለም፣በቴምብር የወጣው ቅርጽና ከሳሽ የኔ ነው የሚለው ቅርጽም ይለያያል፣ከከሳሽ ጋር ከውል ወይም ከውል ወጪ የመነጨ ግንኙነት ስለሌለን ክሱ ተቀባይነት የለውም፣ ከክሱ ጋር ያቀረባቸው ማስረጃዎችም አግባብነት ያላቸው አይደሉም በሚል ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በበኩሉ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው መልስ፡- ወጣ ስለተባለው ጨረታ የማውቀው ነገር የለም፣1ኛ ተከሳሽ ቴምብሮች እንዲታተሙለት በሚል ሶስት ምስሎችን በመላኩና ትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴርም እንዲታተሙ ትዕዛዝ በመስጠቱ ታትመዋል፣በታተሙት ቴምብሮች ላይ ያለው ምስልና የከሳሽ ሥራ የሚለያዩ ናቸው፣የካሳው መጠንም የተጋነነ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሰጠው ፍርድ፡- የአዲስ አበባ የደርግ አፈናና ጭፍጨፋ ተፋራጆች ሰብአዊ መብት ማህበር የተባለው በቀይ ሽብር ለሞቱት ሰዎች የመታሰቢያ ሐውልት ለማሰራት የወድድር ማስታወቂያ ማውጣቱን፣ከሳሽም

www.abyssinialaw.com

በዚሁ ማስታወቂያ መሰረት የሐውልት ቅርጽ ሰርቶ ለማህበሩ ማስረከቡን ፣በማስታወቂያው ከ1ኛ-3ኛ የወጡት አሸናፊዎች የገንዘብ ሽልማት እንደሚሰጣቸውና ከሽልማቱ በኂላ ማህበሩ የቅርጹ ባለቤት እንደሚሆን መገለጹን ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ፤እንዲሁም ቅርጹን ከከሳሽ የተረከበው የአዲስ አበባ የደርግ አፈናና ጭፍጨፋ ተፋራጆች ሰብአዊ መብት የተባለው ማህበር ቢሆንም በኂላ ግን ቅርጹ የሰማዕታት ሐውልት ግንባታ ማህበር እጅ መቆየቱንና ከሳሽም ቅርጹን በተመለከተ ሲደራደር የነበረው ከዚሁ ማህበር ጋር መሆኑን በ07/11/2000 ዓ.ም. ከተጻፈ ማስረጃ መረጋገጡን፣ተከሳሾችም የከሳሽ ሥራ አዲስ (0riginal) አለመሆኑን በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩንና የተከሳሾች ምስክሮች የከሳሽ ሥራ ባለ ሶስት አውታር መጠን (dimension) መሆኑንና በቴምብሮቹ የታተመው ባለሁለት አውታር ነው ቢሉም 1ኛ ተከሳሽም የከሳሽን ቅርጽ ጨምሮ ሶስት ዲዛይኖችን ለ2ኛ ተከሳሽ እንዲታተሙ በሚል ስለመላኩ መረጋገጡን በፍርዱ ላይ በማስፈር 1ኛተከሳሽም ቅርጹ የከሳሽ መሆኑን እያወቀ የከሳሽ ሥራ የሆነውን ባለ ሶስት አውታር ወደ ባለ ሁለት አውታር በመቀየር ለ2ኛ ተከሳሽ አሳልፎ በመስጠቱና 2ኛ ተከሳሽም ቅርጹን በቴምብሮቹ ላይ በማተሙ 1ኛ ተከሳሽ ለተፈጸመው የቅጂ መብት ጥሰት ሀላፊነት አለበት፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ግን በራሱ መርጦ የከሳሽ ሥራ የሆነውን ቅርጽ ያላተመና የቅርጽ ምስሉ ሲላክለትም 1ኛ ተከሳሽ የቅርጹ ባለቤት ስለመሆን ስላለመሆኑና የማጣራት ግዴታ ያለበት ባለመሆኑ ለክሱ ሀላፊነት የለበትም በማለት አሰናብቶታል፡፡

የካሳ መጠንን በተመለከተም ከሳሽ ከቅርጹ 100,000 ማግኘት የሚችል ስለመሆኑ በማስረጃ ያላረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ ቅርጹ ለቀይ ሽብር ሰማዕታት በሚል የተሰራ በመሆኑ ለሌላ አካል ተሸጦ ገቢ ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቅ አይደለም፣ እንዲሁም በጨረታዉ ላሸነፈው ተወዳዳሪ የሚከፈለው የሽልማት ገንዘብ መጠንም ብር 12,900.00 ብቻ በመሆኑ ብር 100,000.00 ማግኘት እችል ነበር ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 34(4) መሰረት የሞራል ጉዳት ካሳ መነሻ ብር 100,000.00 እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡
የስር 1ኛ ተከሳሽም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቶታል፡፡
የሰበር አቤቱታም የቀረበው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ እና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች በዋናነት ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- ተጠሪው ቅርጹን ለአመልካች አስረክቤአለሁ የሚለው በ1990 ዓ/ም ሆኖ ክሱን ያቀረበው ደግሞ በ16/06/2002 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ በፍ/ህ/ቁ/1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በሚል ያቀረብኩትን የመ/ደ/መቃወሚያ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም፣
- በቴምብሮቹ ላይ እንዲታተም የተደረገው ተጠሪው የፈጠራ መብት ባለቤትነት አግኝቼበታለሁ ከሚለው የቅርጽ ሥራ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው በባለሙያ ምስክሮች ተረጋግጦ እያለ የተጠሪ ሥራ ነው በሚል ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት አለብህ በሚል የሞራል ካሳ እንድከፍል የተወሰነው ተቀባይነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- ክስ ያቀረብኩት የቅጂ መብት ተጥሶብኛል በሚል ከህግ የመነጨውን መብት መሰረት በማድረግ ነው እንጂ ከውል በመነጨ መብት መነሻ ባለመሆኑ አግባብነት ያለው በፍትሐብሔር ህጉ ከውል ወጪ ሀላፊነት በተመለከተው ክፍል የተደነገገው የክስ ማቅረቢያ የ2 ዓመት ይርጋ እንጂ ስለውሎች ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው በፍ/ህ/ቁ/1845 ሥር የተመለከተው የይርጋ ጊዜ አይደለም ፡፡ ክሱም የቅጂ መብቴ

ነሐሴ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ተጥሶብኛል በሚል የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. የቀረበ በመሆኑ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት የቀረበ ነው፡፡ በቴምብር ታትሞ የወጣው ባለ ሁለት አዉታር (dimension ) ሲሆን የተጠሪ ደግሞ ባለሶስት አውታር ሥራ ነው በሚል አመልካች ያቀረበው ክርክርም ቢሆን ማንኛውም በምድር ላይ ያለ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ነገር በወረቀት ላይ ወይም በፎቶ ግራፍ ምስል ሲወጣ ከባለሶስት አውታር ወደ ባለሁለት አውታር መቀየሩ ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ክርክሩ ተገቢነት የለውም በሚል በከፍተኛውና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

- ተጠሪው ያቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው? ወይስ አይደለም?
- ክሱ በይርጋ አይታገድም ቢባል አመልካች ለክሱ ሀላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አንደኛውን ጭብጥ በተመለከተ ፡- የአመልካች ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ስለውሎች በጠቅላላው ክፍል በፍ/ህ/ቁ/1845 ስር የተደነገገው የ10 ዓመት ይርጋ ሲሆን ተጠሪው ቅርጹን ካቀረበበት ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ ሲቆጠርም መብቱን ሊጠይቅ የሚችልበት የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ አልፏል በሚል ሲሆን ተጠሪው የሚከራከረው ግን የተጣሰው ከህግ የመነጨ መብት እንጂ ከውል የመነጨ መብት ባለመሆኑ ተፈጻሚነት የሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/2143(1) ስር ከውል ወጪ ሀላፊነትን በሚመለከት ካሳ ለመጠየቅ የተደነገገው የሁለት ዓመት ጊዜ ሲሆን ይኸው መብት ከተጣሰ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም የሁለት ዓመት የክስ ማቅረቢያ ጊዜው አላለፈም በሚል ነው፡፡

ሆኖም ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ የተቻለው ቀደም ሲል የነበረው ማህበር ባወጣው ጨረታ መነሻ ተጠሪውም በጨረታው ተወዳዳሪ በመሆን የፈጠራ ሥራውን ማስታወቂያውን ላወጣው ለቀድሞ ማህበር ስለማስረከቡና ማህበሩም ስለመቀበሉ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡ የውል አቀራረብና አቀባበል በፍ/ህ/ቁ/1681(1) በተደነገገው መሰረት ፈቃድን በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሳ ግዴታን ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ጭምር የሚደረግ በመሆኑ በተጠሪውና በቀድሞው ማህበር መካከል ግልጽ በሆነ ሁኔታ የተደረገ የጽሁፍ ውል ባይኖርም ፈቃድን በቃል በመግለጽ የውል ስምምነት ተደርጓል ለማለት የሚቻል ከመሆኑም በላይ ማህበሩ የተጠሪውን ሥራ መቀበሉ በመካከላቸው የውል ግንኙነት መመስረቱን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከተጠሪው ጋር የተደረገ የውል ስምምነት የለም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ተጠሪውም ቢሆን ከአመልካች ጋር ያለው ግኙኑነት በውል ላይ የተመሰረት ሆኖ እያለ ከህግ በመነጨው መብት ላይ አመልካች ጥሰት የፈጸመ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋ ጊዜ ከውል ውጪ ሀላፊነት ሊኖር ስለሚችልበት አግባብ በፍትሐብሔር ህግ ክፍል የተደነገገው የካሳ ክስ ለማቅረብ የተቀመጠው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው በማለት ያቀረበው ክርክርም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንቶያች የተነሳ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የውል ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ጉዳዩን ስለውሎች በጠቅላላው በተደነገገው ክፍል በሚገኘው በፍ/ህ/ቁ/1845 ይርጋ መሰረት መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ህ/ቁ/1845 ድንጋጌ መሰረት ህግ በሌላ አኳን ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ከላመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ መብት ያለው ወገን መብቱን በ10 ዓመት ወስጥ ካልጠየቀ መብቱ ቀሪ እንደሚሆን በግልጽ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ

www.abyssinialaw.com

ጉዳይ የአመልካች የቀድሞ ማህበር የተጠሪውን ቅርጽ የተቀበለው በ1990 ዓ.ም. መሆኑን ከክርክሩ መረዳት የተቻለ ሲሆን ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት እስከ የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ከ10 ዓመት በላይ ነው፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ምላሽ ማግኘት ያለበት ግን የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካች ጊዜው መቆጠር ያለበት ተጠሪው ቅርጹን ገቢ ካደረገበት ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ ነው ሲል ተጠሪው ግን መብቱ መጣሱን ያወቅኩት ከነሐሴ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ስለሆነ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም ክስ እስከቀረበበት እስከ የካቲት 16/2002 ዓ.ም. ሁለት ዓመት አላለፈውም በሚል ይከራከራል፡፡ ሆኖም የሰማዕታት ሐውልት ግንባታ ማህበር ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ለሆነው የመታሰቢያ ቀን ቴምብሮቹ እንዲታተሙ የትራንስፖርትና መገኛኛ ሚኒስቴር ለፖስታ አገልግሎት ድርጅት ደብዳቤ የጻፈው ታህሳስ 02/2000 ዓ.ም. መሆኑን ከቀረቡት ማስረጃዎች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪው ቴምብሮቹ የራሱ የፈጠራ ቅርጽ ምስል ተደርጎባቸው መታተማቸውን ሊያውቅ ይችላል ተብሎ የሚወሰደውም ከመታሰቢያው ቀን ማለትም ከግንቦት 19/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን ተጠሪውም ከውል የመነጨውን መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው አመልካች በውሉ ግዴታ መሰረት ባለመፈጸም መሥራቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በተመሳሳይ ጭብጥ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ.67376 በቀን 30/11/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ተጠሪው ቅርጹ ለ3ኛ ወገን ተላልፎ ምስሉ በቴምብሮች ወጥቶና ተባዝቶ ለገበያ መዋሉን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲቆጠር 10 ዓመት ያላለፈው በመሆኑ አመልካች ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በከፍተኛው ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች የተጠሪው የፈጠራ ሥራ ባለሶስት አውታር መሆኑንና በቴምብሮቹ ምስሉ ወጥቶ የተባዛው ባለሁለት አውታር ነው በሚል ቢከራከርም ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቴምብሮቹ ታትሞ የወጣው ምስል የተጠሪው ኦርጅናል ሥራ መሆኑንና ተጠሪውም ለዚሁ ስራ ባለቤት ስለመሆኑ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጡን በፍርዱ ላይ የገለጸ ሲሆን በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በመመልከት አጽንቶታል፡፡ የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የማጣራትና የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶችም ያረጋገጡአቸውን ፍሬ ነገሮችን ይህ ችሎትም የሚቀበላቸው ናቸው፡፡ አንድ የመጨረሻ ፍርድ/ውሳኔ ያገኘን ጉዳይ ይህ ችሎት ማረም የሚችለው በፍርዱ/በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተመለከተ ሲሆን በዚህ በህግ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት ማስረጃን የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባለቸው ፍርድ ቤቶች በተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች መሰረት ክርክሩን እንደመረመርነው በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/90008 በቀን 27/07/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሠጠውን ፍርድ እና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/72497 በቀን 16/04/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ተጠሪው ባለቤት የሆነበትን የቅርጽ ስራ በውሉ መሰረት ለመክፈል የተስማማውን ክፍያ ለተጠሪው ሳይከፍል በቴምብሮች ተባዝቶ ለገበያ እንዲቀርብ በማድረጉ የቅጂ መብት ጥሷል ተብሎ የሞራል ካሳ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ለተጠሪው እንዲከፍል የተወሰነበት የቅጅና ተዛማጅ መብቶችን በተመለከተ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 34(4) ስር የተደነገገውን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ህጋዊ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ጥ

www.abyssinialaw.com

# ልዩ ልዩ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 61221

መስከረም 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- . አቶ አከለ ምህረቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጡረታ መብት አከባበር ጋር ተያይዞ የተነሳውን የመሰየም ውጤት የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ላይ ተጠሪ በሰጠው ውሳኔ የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ለዚህ አካል ባቀረቡት አቤቱታ ከሰላሳ አመታት በላይ በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገሉ ቢሆንም ተጠሪ መስሪያ ቤት ግንቦት 6 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የሶስት አመት ፅኑ እስራት የተፈረደባቸው በመሆኑ በጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 መሰረት ከ1995 ዓ/ም በፊት የሰጡት አገልግሎት የማይያዝ ስለሆነ ለዘለቄታ ጡረታ መብት ብቁ እንዳልሆኑ ገልፆ የወሰነባቸው መሆኑን፣ ከእስር ከተፈቱ በኋላ ወደ መደበኛ ስራቸው ተመልሰው እስከ ጥር ወር 2002 ዓ/ም ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተው ከየካቲት 01 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ መገለላቸውን አሰሪው መስሪያ ቤታቸው መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም. እና ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው ደንብ መሰረት እድሜአቸው ከሃምሳ በላይ እና አገልግሎታቸው ከሃያ አምስት አመታት በላይ አገልግሎት የሰጡ የመንግስት ሰራተኞች የእድሜ ልክ የጡረታ አበል እንደሚከፈላቸው ተወስኖ የአመልካች መስሪያ ቤትም የጡረታ መብቱ እንዲከበርላቸው የጠየቀላቸው መሆኑን፣ አዋጅ ቁጥር 345/1995 በስራ ላይ ከዋለ በኋላ የጡረታ መብት ጥያቄ የቀረበ በመሆኑ መብታቸውን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ አሰሪው መስሪያ ቤት የጠበቀላቸው ቢሆንም ተጠሪ መስሪያ ቤት ተገቢውን ያልፈፀመ መሆኑን፣ በወንጀል ተከሰው በነበሩበት ጉዳይ የመሰየም ውሳኔ ከሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ የተሰጠላቸው መሆኑንና በአዋጅ ቁጥር 345/1995 በተሻረው አዋጅ ቁጥር 5/1967 መሰረት መብታቸው የሚገደብበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ዘርዝረው የዘላቂ የጡረታ መብት እንዲከበርላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም አመልካች ከመታሰራቸው በፊትም ሆነ በኋላ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥረው መስራታቸውን ሳይክድ የአመልካች የዘላቂ ጡረታ መብት ሊከበርላቸው አይገባም በማለት የሚከራከረው ከመታሰራቸው በፊት ያገለገሉበት ጊዜ ሊቆጠር አይገባም፣ መሰየም ውጤቱ ወደፊት ነው እንጂ ወደኋላ አይደለም በሚል ምክንያት

ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የመሰየም ውጤት ወደፊት እንጂ ወደኋላ ሊሄድ እንደማይችል ገልፆ አመልካች ያላቸው መብት ከእስር ከተፈቱ በኋላ ያገለገሉበት የሰባት አመት ከዘጠኝ ወራት አገልግሎት የሚያስገኝላቸው መብት ዘላቂ የጡረታ መብት ሳይሆን እንደገና ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ከስራ እስከተሰናበቱ ጊዜ ድረስ ከደመወዛቸው እየተቆረጠ ሲጠራቀም የነበረው 4% የጡረታ መዋጮ ነው ተብሎ በተጠሪ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የመሰየም ውጤት ወደፊት እንጂ ወደኋላ አይሰራም ተብሎ መወሰኑ ስለመሰየም የተደነገጉትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች እስራቱን ከጨረሱ በኋላ ወደቀድሞ መስሪያ ቤታቸው ተመልሰው ስራ ከመጀመራቸውና ከመሰየማቸው አንፃር ከእስራት በፊት ያበረከቱት አገልግሎት ሊታሰብ አይገባም ተብሎ በኤጀንሲው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት የቀረበ ሲሆን በነገረ ፈጁ አማካይኝት ባቀረበው የፅሁፍ ክርክር ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ የመሰየም ውጤት ወደፊት እንጂ ወደኋላ ሊሆን እንደማይችል፤ መሰየም ለጡረታ መብትም ሊሰራ የማይችል መሆኑን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በጡረታ መለያ ቁጥር ሰ/130745 የተመዘገቡና ከየካቲት 08 ቀን 1967 እስከ ህዳር 21 ቀን 1989 ዓ/ም ድረስ ለ22 አመታት ያህል በፍትህ ሚኒስቴር አገልግለው በወንጀል ተከሰው ከህዳር 22 ቀን 1989 እስከ የካቲት 08 ቀን 1994 ዓ/ም ድረስ በ5 አመታት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተወስኖባቸው የእስር ጊዜአቸውን በመጨረስ የተፈቱ መሆኑን፣ ከእስር ከተፈቱ በኋላም ከግንቦት 01 ቀን 1994 ዓ.ም. እስከ ጥር 30 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ ለሰባት አመታት ከዘጠኝ ወራት ያህል በመንግስት መስሪያ ቤት ሲያገለሉ ቆይተው ከየካቲት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ መስሪያ ቤቱ ባካሄደው የአሰራር ለውጥ ማሻሻያ ጥናት መሰረት የተገለሉ መሆኑን፣ ከሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ የተሰየሙ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የዘላቂ ጡረታ መብት ተጠቃሚነት ሊከበርልኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩት መሰየሙ ውጤቱ ከእስር በፊት የነበረውን የአገልግሎት ዘመን እንዲቆጠር ያደርገዋል፣ ይህ ጊዜ ከተያዘ የሃያ አምስት አመታት የአገልግሎት ዘመንና የሃምሳ አመት እድሜ ቅድመ ሁኔታ ይሟላልኛል በሚል ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች በመነሳት በሕጉ ረገድ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ጉዳይ የመሰየም ውጤት ወደፊት ነው? ወይስ ወደኋላ? የሚለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ይህንኑ ጭብጥ ከመመለሳችን በፊት የተጠሪ ነገረ ፈጅ ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ችሎት አመልካች ሊያቀርቡ አይችሉም ወይም ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት በሰ/መ/ቁጥር 18342 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመጥቀስ ያቀረቡትን ተቃውሞ ተመልክተናል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ስር እንደተመለከተው ከአምስት ያላነሱ የዚህ ችሎት ዳኞች ተሰይመው የሚሰጡት የሕግ ትርጉም ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማናቸውም እርከን የሚገኝን ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ነው፡፡ አንድ የሕግ ትርጉም ለተመሳሳይ ጉዳይ ገዥነት እንዲኖረው ለማድረግ ደግሞ በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ጉዳዮቹ መመሳሰል ያለባቸው ስለመሆኑ ከአስገዳጅ የሕግ ትርጉም ፅንሰ ሀሳብ የምንገነዘበው ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በሰ.መ.ቁጥር 18342 የተሰጠው የህግ ትርጉም የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ስለሰጠና ውሳኔውም ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስላስተናገደው የቀረበ አቤቱታ ሲሆን የሰበር ሰሚ ችሎትም በህግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፣ የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡ ውሳኔው ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱም ቢሆንም ሊቀርብ የሚገባ አይደለም የሚል ይዘት የለውም፡፡ ለዚህ ውሳኔ መነሻ የሆነው በግለሰቦች የቀረበው ክርክር ደግሞ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ማህበራዊ ዋስትና ያላግባብ ከእኛ ሂሳብ አውጥቶ የወሰደውን ገንዘብ በሚመለከት የጡረታ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣንም ሆነ ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ክስ አቅርበን በስማችን ውሳኔ ስለመስጠቱ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም፣ የአገልግሎት ዘመናችን ተቀንሶብናል ወይም ያለአግባብ እድሜአችን ጡረታ ሳይደርስ በጡረታ እንድንገለል ተደርጓል በሚል ያቀረብነው ክስ ስለሌለ በጡረታ ሕጉ መሰረት የሚታይ ጉዳይ የለም፣ አመልካች ያላግባብ ከሂሳባችን አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ ተቀብሎ ወደ ነበረበት ሂሳብ እንዲያስገባ በሚል የቀረበውን ክስ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ ግን ቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የቀረበበት ወይም የይግባኝ አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በሚል በቀጥታ ለዚህ ችሎት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በተነሳበት ጊዜ ስራ ላይ በነበረው ሕግ አግባብ ማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው ከተባለ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 በተመለከተው አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ከማቀረብ የሚከለክል ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 18342 የተሰጠው ትርጉም የሰበርን ስልጣንም የሚጨምር አይደለም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ነገረ ፈጅ የሰ/መ/ቁጥር 18342"ን" መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ተቃውሞ በመዝገቡ ላይ ያሉትን መሰረታዊ የክርክር ነጥቦችንና ጉዳዩ መታየት የጀመረበትን አካሄድ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በመሰረታዊነት የሚለይ መሆኑና ሰበር ችሎቱ በሕገ መንግስቱ በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን የማረም ስልጣን ያለው መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ስለአገኘን ተቃውሞውን አልተቀበልነውም፡፡

ወደዋናው ጭብጥ ስንመለስም በመሰረቱ የጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/1955 በአዋጅ ቁጥር 5/1967 እንደተሻሻለው አንቀጽ 34 አንድ የመንግስት ሰራተኛ ወይም ጡረተኛ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ሲረጋገጥና ቢያንስ የሶስት አመት የፅኑ እስራት ቅጣት ሲወሰንበት የጡረታ መብቱን እንደሚያጣ ወይም በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል እንደሚቋረጥ ደንግጓል፡፡ አመልካች ይህ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 የተሻረ በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 345/1995 በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ለቀረበ ጥያቄ ተፈፃሚነት የለውም በማለት

www.abyssinialaw.com

የሚከራከሩ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በአዋጅ ቁጥር 209/1955፣ በአዋጅ ቁጥር 5/1967 እንደተሻሻለ የተገኙት መብቶችና ግዴታዎች ቀሪ ያልሆኑ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 52/1/ ስር የተደነገገ በመሆኑ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ በመ/ቁጥር 50590 እና 50591 በቀረቡት ጉዳዮች ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ በዚህ በኩል የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመሰየም ውጤትን በተመለከተ የቀረበውን ክርክርና በይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተሰጠውን ውሳኔ ሕጋዊነት ስንመለከትም መሰየም አንድ ተቀጪ በዋናው ቅጣት ወይም በዋናው ቅጣትና ተጨማሪው ቅጣት ምክንያት አጥቶት የነበረውን ንፁህ ሰው ሆኖ የመገመት መብቱን እንደገና መልሶ የሚያገኝበትንና ተወስኖበት የነበረው ዋናው ቅጣትም ሆነ ተጨማሪ ቅጣት ተመዝግቦበት ከነበረው ከግል የፍርድ ሰሌዳው ላይ ተሰርዞ ለሶስተኛ ወገኖች ይኸው ሁኔታ የሚገለፅበትንና የሚታወቅበትን አግባብ የሚመለከት የሕግ አካሄድ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 232 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ከአስቀመጡት መንፈስና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 235(1) ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ተቀጥቶ የነበረው ሰው ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ተወስኖበት የነበረው የመብት፣ የማዕረግ፣ ወይም የችሎታ ማጣት ለወደፊቱ ቀሪ ሆኖለት ሕዝባዊ መብቱንና ቤተሰብ የማስተዳደርና የሙያ ስራ መስራት መብቱን እንደገና ለመያዝ ችሎታ ይኖረዋል በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ማንም ተቀጪ በመሰየሙ ሊያገኝ የሚችለው መብት ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን መብት ሳይሆን ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት ሊጠበቅበት የሚገባውን መብት ብቻ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች ከመሰየማቸው በፊት በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገሉበት አገልግሎት ጊዜ በመሰየማቸው ምክንያት ዋጋ እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ከላይ ስለመሰየምና ውጤቱ በሕጉ በግልፅ የተመለከተውን መሰፈርት መሰረት ያላደረገ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሰሚው ጉባኤ መሰየም ውጤቱ ወደፊት እንጂ ከመሰየም አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖ የነበረውን መብት መልሶ ማግኘት አይደለም በማለት አመልካች ከየካቲት 08 ቀን 1967 እስከ ህዳር 21 ቀን 1989 ዓ/ም ድረስ ያገለገሉት የአገልግሎት ዘመን ሊያዝላቸው አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. መሰየም ውጤት የሚኖረው ተቀጪው ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት እንጂ ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣቱ አጥቶት የነበረውን መብት አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 72928

ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አበራ ኪዳኔ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የጋሞ ጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ማህበራዊ ዋስትና ቅ/ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች ለመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ባቀረቡት አቤቱታ የትውልድ ዘመናቸው 1943 መሆኑን በመጥቀስ በ30/07/2003 ዓ.ም. ዕድሜያቸው 60 ዓመት ስለሚሞላ ከ01/08/2003 ጀምሮ የዘለቄታ የጡረታ ባለመብት መሆናቸው ታዉቆ የጡረታ አበል እንዲወሰንላቸው የጠየቁ ሲሆን ኤጀንሲውም አመልካች በጋሞ ጎፋ ዞን ሥራና ከተማ ልማት በ1986 ዓ/ም ሲቀጠሩ የትውልድ ዘመናቸው 1943 ዓ.ም. ነው በሚል በሕይወት ታሪክ ፎርም የሞሉ ቢሆንም በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ የትውልድ ዘመናቸው በ27/7/1933 በሚል የሞሉ ስለሆነ በጡረታ መገለል የነበረባቸውም በ01/08/1988 ዓ.ም. ነው፡፡ በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀጥረው ከ01/03/1958-30/01/1969 በሚሰሩበት ወቅትም ገንዘብ በማጉደላቸው በወንጀል ተከሰው በ3 ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 500 የተቀጡ ስለሆነ በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 የመጀመሪያው አገልግሎታቸው ውድቅ የሚደረግ በመሆኑ የሚቆጠረውም ከ20/10/1986-30/07/1988 ዓ.ም. ያለው ነው፡፡ ይህም ጊዜ 1 ዓመት ከ9 ወር ከ11 ቀን ስለሚሆን ሊከፈላቸው የሚገባው የዘለቄታ የጡረታ አበል ሳይሆን የዳረጎት ክፍያ ነው በሚል የወሰነ ሲሆን፣ ከ01/9/1988-30/07/2003 ዓ.ም. ድረስ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ ለፈጸሙት አገልግሎትም የከፈሉት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ሊደረግላቸው ይገባል ብሏል፡፡

አመልካችም በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ያቀረቡ ቢሆንም ጉባዔው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የኤጀንሲውን ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም ፡- በወንጀል የተሰጠብኝ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በመሰየም ተሰርዞ እያለ የአገልግሎት ዘመኔ ውድቅ መደረጉ፣ እንዲሁም የትውልድ ዘመኔ 1933 ዓ/ም ሳይሆን 1943 ዓ/ም ስለመሆኑ በፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ተረጋግጦ እያለ ተቀባይነት የሚኖረው የትውልድ ዘመን 1933 ዓ/ም ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪው መሥሪያ ቤት በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- አንድ የመንግስት ሰራተኛ በጡረታ ከመንግስት ሥራ የሚሰናበተው ሰራተኛው በሚያቀርበው የልደት ዘመን ማስረጃ ሳይሆን በመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲቀጠር በሞላው የህይወት ታሪክና የልደት ዘመን መሰረት ነው፣ መሰየም የታጣውን መብት እንደገና የሚያስገኝ አይደለም በማለት የኤጀንሲውና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በህጉ መሰረት ደረጃውን ጠብቆ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በዚህ ጉዳይ የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ጉባኤ ውሳኔ የሰጠው ሐምሌ 18 ቀን 2003 ዓ.ም. ሲሆን ውሳኔው በተሰጠበትም ወቅት ተፈጻሚ የነበረው ስለመንግስት ሰራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 714/2003 ነው፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 56 (1) መሰረት በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለመብት ቅሬታውን በአዋጁ አንቀጽ 57 ለተቋቋመው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ በንዑስ አንቀጽ 4 ደግሞ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን የተደነገገ ሲሆን ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን የሚያምን ተከራካሪ ደግሞ ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ተጠቅሷል፡፡ ከድንጋጌው የመጨረሻ ክፍል መገንዘብ የተቻለውም የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ውሳኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ መሆኑንና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑ ሲታመን ግን በይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መቅረብ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ አመልካች ቅሬታቸውን ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማቅረብ ሲገባቸው በሰበር ለዚህ ችሎት ማቅረባቸው ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በህጉ የተቀመጠውን የአቀራረብ ደረጃ ጠብቆ የቀረበ ባለመሆኑ ውድቅ አድርገናል፡፡
2. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 80964

ጥቅምት 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አበራ ቦከን - ጠበቃ ሀቢቢ ረጋሣ ቀረቡ

2. አቶ አየለ ታደሰ - ቀረቡ

3. አቶ ተስፋዬ ቅጣው - ቀረቡ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 80965 እና 80966 ከዚህ መዝገብ ጋር እንዲጣመሩ የተደረጉ በመሆኑ ሶስቱንም መዛግብት በመመርመር ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከጡረታ መብት ጋር የተያያዘ የእድሜ አቆጣጠርንና ውጤቱን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በአመልካች ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ለየብቻቸው ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መስከረም 29 ቀን 2004 ዓ.ም. በቁጥር ጡ/ይ/1/1/870/2004 የሰጠውን ውሳኔ የተቃወሙ ሲሆን የይግባኝ ቅሬታው ይዘትም ከኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አክሲዮን ማህበር የሰው ኃይል አስተዳደር መምሪያ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ የጡረታ መውጪያ ጊዜን ለማሳወቅ ተብሎ በተፃፈልኝ ደብዳቤ የልደት ዘመንህ እ.ኤ.አ 1944 ተብሎ የተላከና እድሜዬ ለጡረታ የሚደርሰው እ.ኤ.አ ጃኑዋሪ 1/2004 እንደሆነና ያለኝን የአመት እረፍት ከሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም. በፊት እንድወስድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል፣ ይሁን እንጂ እኔ በዚህ ድርጅት የተቀጠርኩት እ.ኤ.አ በ05/04/71 በመሆኑ ስቀጠር እድሜዬ 17 እንደነበርና የልደት ዘመኤም ሐምሌ 19 ቀን 1946 ዓ.ም. በመሆኑ በተሰጠኝ ደብዳቤ እንደተመለከተው ከሰባት አመት በፊት ወደ ኋላ ጡረታ መውጣት እንደአለብኝ የሚገልጽ በመሆኑ የጡረታ አበሉና የአገልግሎት ዘመን የሚቀንስ ነው፣ በተቀጠርኩበት ጊዜ የቅጥር ፎርሙ የተሞላው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሁኖ በወቅቱ የነበሩት አሰሪዎች የውጪ አገር ዜጎች በመሆናቸው የዘመን አቆጣጠሩ በምን እንደሞሉት የማላውቅ ነበር፣ ጡረታም የምወጣው ወደፊት ሐምሌ 20 ቀን 2006 ዓ.ም. በመሆኑ የልደት ዘመኑ 1946 ዓ.ም መሆኑ ታውቆልኝ የጡረታ መውጪያ ጊዜ ይስተካከልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ለኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ይዘት ደግሞ በኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አ.ማ እ.ኤ.አ ጥር 14 ቀን 1972 ዓ.ም. የተቀጠርኩ ሲሆን በወቅቱ እድሜዬ 20 ዓመት፣ የተወለድኩት ሰኔ 12 ቀን 1944 ዓ.ም. ሁኖ እያለ ከአሰሪ ድርጅቱ የተሰጠኝ ደብዳቤ ከሰባት አመት በላይ ወደ ኋላ ጡረታ መውጣት እንዳለብኝ የሚገለጽ በመሆኑ በጡረታ አበልና በአገልግሎት ዘመኑ ላይ ቅነሳ የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ የትውልድ ዘመኔ እ.ኤ.አ 1944

ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሰኔ 12 ቀን 1944 ስለሆነ ለጡረታ መውጫ እድሜ ላይ ያልደረስኩ በመሆኑ በተቀጠርኩበት ጊዜ የቅጥር ፎርሙ የተሞላው በእንግሊዝኛ ቋንቋና በነበሩት የውጪ አገር አሰሪዎች ሁኖ የዘመኑ አቆጣጠሩ በምን እንደተሞላ የማላውቅ በመሆኑ ታውቆ ትክክለኛው የልደት ዘመኔ ሰኔ 12 ቀን 1944 ዓ.ም. ሊያዝልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ሶስተኛ ተጠሪ ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ይዘቱ ሲታይም የጡረታ መውጪያ ጊዜ አያያዝ ላይ እንደ አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ችግሩ የተከሰተበት መንገድ ተመሳሳይ መሆኑን ገልጸው ትክክለኛው የትውልድ ዘመናቸው ነሐሴ 25 ቀን 1943 ዓ.ም. ሁኖ እንዲያዝላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪዎች ይግባኝ በተናጠል በሰጠው መልስም የልደት ዘመን የሚያዘው ሰራተኛው ለስራው ሲቀጠር በሞላው ፎርም ላይ የተመዘገበ የልደት ዘመን መሆኑን ገልጾ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በጡረታ መለያ ቁጥር ድ/543275 መመዝገባቸውንና የተጠሪ የልደት ዘመን በፎረንሲክ የምርመራ ውጤት መሰረት እ.ኤ.አ 1944 ተወለድኩ ብለው የሞሉና ይህንን የሚቀይር የተሞላ የልደት ዘመን የሌለ በመሆኑ ይኼው የልደት ዘመን እንዲያዝላቸው መደረጉን፣ የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም በጡረታ መለያ ቁጥር ድ/529780 የተመዘገቡና እ.ኤ.አ በ14/1/1972 በሞሉት የህይወት ታሪክ ፎርም ላይ እ.አ.አ 1944 የተወለዱ መሆኑን ገልፀው የሞሉ መሆኑን እና ሶስተኛ ተጠሪ በጡረታ መለያ ቁጥር ድ/407412 የተመዘገቡና በእ.ኤ.አ በ4/07/1973 የሞሉት የህይወት ታሪክ ፎርም ላይ እ.ኤ.አ 1941 ተወለድኩ ብለው የሞሉና ይህን የሚቀየር የተሞላ የልደት ዘመን የሌለ በመሆኑ ይኼው የትውልድ ዘመን እንዲያዝላቸው የተደረገ መሆኑን ዘርዝሮ በሕጉ አግባብ የተከናወነ ተግባር ስለሆነ የኤጀንሲው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የኤጀንሲው ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮ በማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የአፈፃጸም መመሪያ ለጡረታ ተግባር የሚያዘው እድሜ በቅድሚያ በተሞላ የስራ መጠየቂያ ወይም የሕይወት ታሪክ መግለጫ ቅጽ ወይም የተያዥ መስጫ ወይም የምዝገባ ቅፅ ላይ የተመዘገበ የልደት ዘመን መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ በኢትዮጵያ ፐልፐና ወረቀት አክሲዮን ማህበር እ.ኤ.አ. በ05/04/1971 ለስራ ሲቀጠሩ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም ላይ የተመዘገበው የልደት ዘመን ስርዝ ድልዝ ያለው በመሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በ26/8/2002 በቁጥ ፌሮ/1-1/31/7452/2002 በተጻፈ ደብዳቤ አባሪ ሆኖ በተላከው የሰነድ የምርመራ ውጤት መግለጫ ላይ በአቶ አበራ ቦከን ስም በተዘጋጀው ሰነድ ላይ በእንግሊዝኛ የልደት ዘመን በሚለው ፊት 1954 በሚል የተጻፉ ቁጥሮች ቀደም ሲል 1944 በሚል ከተጻፈ በኋላ ተደልዘውና ተለውጠው አሁን እንደሚታየው 1954 የተደረገ መሆኑ መረጋገጡን፣ 2ኛ ተጠሪም እ.ኤ.አ. በ14/1/1972 ለስራ ሲቀጠሩ በሞሉት ፎርም ላይ የልደት ዘመን ስርዝ ድልዝ በመሆኑ በፎረንሲክ ምርምራ ተብሎ በእንግሊዝኛ የትውልድ ዘመን በሚለው ቃል ፊት ያለው 1952 በሚል የተፃፉ ቁጥሮች ቀደም ሲል 1944 ከተፃፈ በኋላ ተደልዘውና ተለውጠው አሁን እንደሚታየው 1952 የተደረገ መሆኑን የፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በ26/08/2002 ዓ.ም. በቁጥር ፌሮ/1-1/31/7452/2002 በተፃፈ ደብዳቤ ያረጋገጠ መሆኑን፣ ሶስተኛ ተጠሪን በተመለከተም በእ.ኤ.አ በ4/7/1973 ሲቀጠሩ በሞሉት የህይወት ታሪክ ፎርም ላይ የልደት ዘመን ስርዝ ድልዝ ያለው በመሆኑ በፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርምራ በእንግሊዝኛ የልደት ዘመን በሚል ከተቀመጠው ቃል ፊት ለፊት 1951 በሚል የተፃፉ ቁጥሮች ቀደም ሲል 1941 በሚል ከተፃፈ በኋላ ተደልዘውና ተለውጠው አሁን እንደሚታየው 1951 የተደረገ መሆኑን በ26/08/2002 ዓ.ም. በቁጥር ፌሮ/1-1/31/7452/2002 በተፃፈ ደብዳቤ መግለፁን በመጥቀስና 1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 12 ቀን በሞሉት የመንግስት የሆኑ ድርጅቶች ሰራተኞች የግል አገልግሎትና የቤተሰብ ሁኔታ መግለጫ ቅጽም ላይ የትውልድ ዘመናቸውን 1946 ዓ.ም. በሚል የመዘገቡት፣ ሁለተኛ ተጠሪም እ.ኤ.አ 1952 በሚል

የመዘገቡት፣ ሶስተኛ ተጠሪ ደግሞ 1943 በሚል የመዘገቡት ቅድሚያ እንደሌለው ገልፆ የአመልካችን የትውልድ ዘመን አያያዝን በተመለከተ ኤጀንሲው የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ ከዚህም በኂላ የአሁኑ ተጠሪዎች በተናጠል የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የአመልካቾች እድሜ ስርዝ ድልዝ ያለው መሆኑ ቢረጋገጠም ማን እና እንዴት ሊሰረዝ እንደቻለ ሳይረጋገጥ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ያለመሆኑና የሕግ ግምቱንም ያልተከተለ መሆኑን ጠቅሶ በጉዳዩ ላይ በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የልደት ዘመኑ በማን እና እንዴት እንደተሰረዘ አጣርቶ እንዲወስን በማለት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ የቀረበው የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ሆኖ እያለ ፍሬ ነገሩን ማጣራቱና ማስረጃን መመዘኑ ከስልጣኑ ውጪ መሆኑን እንዲሁም ተጠሪዎች የተወለዱበት ዘመን መጀመሪያ ሲቀጠሩ በትክክል የተሞላና በኂላ ደግሞ የተሰረዘና የተለወጠ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በኂላ የተሞላውን የትውልድ ዘመን እንዴት እንደተሞላና የቀድሞውን ማን እንደሰረዘው እንዲጣራ ማድረግ ለጉዳዩ አወሳሰን አስፈላጊ ያልሆነ ነጥብ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 4(1)፣ 54(1)፣ 56(4) ድንጋጌዎችን ይዘት ያላገናዘበ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአዋጅ ቁጥር 714/2003 በአንቀጽ 4(1) መሰረት ለመንግስት ሰራተኛ ለጡረታ የሚያዝ የልደት ዘመን የመንግስት ሰራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር ያስመዘገበው የልደት ዘመን መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ የፍትሐብሔር ችሎት በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 56(4) መሰረት ፍርድ ቤቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተቶችን ብቻ በይግባኝ እንዲያይ ተደንግጎ እያለ በፍሬ ነገር ላይ ጉባኤው ሌሎች ማስረጃዎችን እንደገና መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ሲቀጠሩ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም ላይ ያለው የትውልድ ዘመን ተሰርዞና ተደልዞ የተለወጠና ቅድሚያ የሞሉት የትውልድ ዘመን ስንት እንደነበር በፎረንሲክ ምርምራ መረጋገጡን፣ ተጠሪዎች የትውልድ ዘመኑ ላይ እ.ኤ.አ አቆጣጠር የተሞላ ስለነበር የተከሰተ ችግር እንጂ ቀድሞ ሲሞሉት የነበረውን በመለወጥ የተከሰተ ችግር ያለመሆኑና በቅጥር ጊዜ በነበረው የቋንቋ ችግር መከሰቱን ገልጸው የአመልካች ኤጀንሲ ውሳኔ በጡረታ አበል መጠኑና በአገልግሎት ዘመናቸው ላይ ችግር የሚያስከትልባቸው መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን፣ አመልካች በአንፃሩ የተጠሪዎች የትውልድ ዘመን በተገቢው መንገድ ተረጋግጦ እያለ እንዴት እንደተሰረዘና ማን እንደሰረዘው ይረጋገጥ ተብሎ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ መሆኑንና የራሱ እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት የተከናወነ መሆኑን ገልጾ የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሰረቱ ለመንግስት ሰራተኛ ለጡረታ የሚያዝ የልደት ዘመን የመንግስት ሰራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበው የልደት ዘመን መሆኑን አዋጅ ቁጥር 714/2003 በአንቀጽ 4(1) ስር በግልጽ ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የሚያሳየው አመልካች መስሪያ ቤት ለመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አበል ውሳኔ የሚሰጠው በአዋጁ መሰረት ሰራተኛው በመጀመሪያ ጊዜ በመንግስት መስሪያ ቤት ሲቀጠር የሞላውን የልደት ዘመን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተጠቃሹ አዋጅ አዋጁን ለማስፈፀም በተመለከተ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ለአመልካች ኤጀንሲ መሰጠቱን በአንቀፅ 60(2) ስር ሰፈሯል፡፡ አመልካች በዚህ አግባብም የልደት ዘመንን አያያዝና ሌሎች አፈፃፀሞችን በተመለከተ መመሪያ ስራ ላይ ማዋሉም በክርክሩ ሂደት ክርክር ያልቀረበበት ጉዳይ ነው፡፡ ኤጀንሲው በአዋጁ ለሚሰጡ ለማናቸውም አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸውን የማረጋገጥና የአበሉን መጠንና አይነት የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 54(1) ስር በግልጽ የሰፈረ ሲሆን በዚህ ረገድ ውሳኔ ሲሰጥም የራሱን የመረጃ ማህደር፣ በአዋጁ አንቀጽ 53 መሰረት የሚተላለፉን መረጃዎችንና እንደ አግባብነቱ ባለመብቱ የሚያቀርባቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ መሆኑን አንቀጽ 54(2) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በኤጀንሲው ማህደርና በሚቀርበው ሌላ ማስረጃ ልዩነት ቢፈጠር ደግሞ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ የሚወስነው ኤጀንሲው ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 54(3) ድንጋጌ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ አዋጁ የኤጀንሲው ውሳኔ በኤጀንሲው ዳግም የሚታይበትን ስርዓት የዘረጋ ሲሆን ዝርዝር ሁኔታዎችንም በአንቀጽ 55 ስር አስፍሯል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ሁሉ ይግባኙን የሚያቀርበው ለኤጀንሲው ጉባኤ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 56(1) ይገልፃል፡፡፡ የኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 56(4) ስር በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችልም ይኼው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙ የሚቀርበው በፍሬ ነገር ክርክር ወይም በማስረጃ ምዘና ሳይሆን በመሰረታዊ የህግ ስህተት ላይ ብቻ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች መስሪያ ቤት የተጠሪዎችን የልደት ዘመን የያዘው ማህደሩን በመመልከትና በማህደሩ የተከሰቱን ችግሮች በማጣራት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤትም በተጠሪዎች የህይወት ታሪክ ላይ ቀድሞ የተሞላው ትክክለኛ ዘመን የለየው ሲሆን በኂላ ተሞልቶ የተገኘው ግን የቀድሞው ተሰርዞ የተቀመጠ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ለጉባኤው እንዲመለስ ያደረገው የትውልድ ዘመኑ በተለያዩ ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፣ ማህደሩ በአሰሪ እጅ ባለበት ሁኔታ የሰረዘው ማን ነው የሚለው ጥያቄም የሕግ ግምት ነው፣ ተጠሪዎች በኂላ ሞላን የሚሉት ወይም ስርዝ ነው የተባለው የትውልድ ዘመን ቀድሞ እ.ኤ.አ ተሞልቶ ስለነበር ይህንኑ ለማስተካከል ተብሎ ሊሆን ይችላል የሚሉትን ነጥቦችን በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለውሳኔ መሰረት ያደረጋቸው ምክንያቶች በይዘታቸው ሲታዩ የፍሬነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳዩን የሚመለከቱ ሲሆን ያላግባብ የገባውና በትክክል ሰራተኞቹ ሲቀጠሩ የተሞላው የልደት ዘመን በፎረንሲክ ምርምራ እስከተለየ ድረስ በኂላ የገባውን የልደት ዘመን ማን ሰረዘው፣ እንዴት ተሰረዘ የሚለውን ማጣራቱ በተጠሪዎች የጡረታ መብት ውሳኔ ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ኤጀንሲው የሰራተኛውን ማህደር በመመርመርና የመብቱ ተጠቃሚ የሚያቀርበውን ማስረጃ መመርምሮ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የትኛው እንደሆነ ለይቶ መወሰን እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 54(3) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በፎረንሲክ

www.abyssinialaw.com

ምርመራ መሰረት ተጠሪዎች ሊያዝልን ይገባል በማለት የሚጠቅሱት የልደት ዘመን በቅጥር ጊዜ የተሞላ ያለመሆኑ ተረጋግጦ እያለና ኤጀንሲውም የተጠሪዎችን አለን የሚሉትን ማስረጃ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሳይቀበለው መቅረቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ የትውልድ ዘመኑን የሰረዘው ማን ነው?፣ እንዴት ተሰረዘ? የሚለው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ማድረግ ኤጀንሲው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያልተቀበለውን ማስረጃ እንዲቀበል የማስገደድ ኃይል ያለው ውሳኔ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 56(4) ድንጋጌ መሰረት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ሁኖ እያለ አመልካች መስሪያ ቤት ፍሬ ነገሩን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ድምዳሜ ላይ የደረሰበትን የተጠሪዎችን የትውልድ ዘመን እንደገና እንዲጣራ ማድረጉ ያለሥልጣኑ የተሠጠ ውሳኔ ሁኖ አግኝተናል፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መዳኘት ያለበት ደግሞ በሕጉ ተለይቶ በተሰጠው ስልጣን አድማስ ውስጥ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያሳየን ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 ድንጋጌ መሰረት አንድ ጉዳይ ውሳኔውን ለሰጠው አካል እንዲመለስ የሚደረገውም ለውሳኔ አሰጣጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በሕጉ በተመለከተው የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ስርዓት መሰረት ሳይጣሩና የክርክሩ አካሄድ ሳይሟላ ውሳኔ ተሰጥቶ ሲገኝ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ የበላይ ፍርድ ቤት መሪ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለውም በሕጉ ስልጣን ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት መሰል አካል እንዲጣራ ሊያደርግ እንደሚችል የመሰረታዊ ሕግ መመዘኛዎች የሚያሳዩን ጉዳይ ሲሆን ይህንን መሪ ትእዛዝ ሲሰጥ ግን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያለው አካል በፍሬ ነገር ደረጃ በሕጉ አግባብ የደመደመውን ፍሬ ነገር ውድቅ የሚያደርግበት ስልጣን ሊኖረው አይችልም፡፡ ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 4(1)፣ 54፣ እና 56(4) ድንጋጌዎችን እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 75355፣ በመ/ቁጥር 74770 እና በመ/ቁጥር 74769 ሚያዚያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጣቸው ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በጉዳዮቹ ላይ የመንግስት ሰራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መስከረም 13 ቀን 2004 ዓ/ም፣ ጥቅምት 25 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጣቸው ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>**

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁጥር 80965 እና 80966 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 78945

መስከረም 22 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡- መምህር ባዬ ዋናያ የዳ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ መምህራን በዲስፕሊን ግድፈት ከስራ እንዲባረሩ የሚሰጥ ውሣኔ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚቀርብበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት ይግባኙን ያቀረቡት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ የተጠሪ የይግባኝ አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ ከዩኒቨርሲቲው ያላግባብ ከስራ እንደተባረሩ ገልፀው ወደ ስራ እንዲመለሱና ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ከሰጠው መልስም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ በየኒቨርሲቲው ቦርድ ሳይሰጥ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት መቅረቡ ያላግባብ መሆኑና ይግባኙ መቅረብ የሚገባው ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ እንጂ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት መሆኑን ገልፆ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የአስተዳደር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 2(8) ስር መደንገጉን ገልፆ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ተቃውሞ ሳይቀበለው ያለፈ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ መምህር ከስራ የተሰናበቱት ያለግባብ ነው በሚል ምክንያት ተሰጠ የተባለውን ውሣኔ መሻሩን ገልፆ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለሱና ያልተከፈላቸው ውዝፍ ደመወዝ በሕጉ አግባብ እንዲከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የዩኒቨርሲቲውን መምህራን የዲሲፕሊን ግድፈትን በተመለከተ ጉዳዩ የሚገዛው በደንብ ቁጥር 1/2002 ሁኖ በስንብት ውሣኔ ቅሬታ ያለው የአካዳሚክ ሰራተኛ ቅሬታውን ማቅረብ ያለበት ለየኒቨርሲቲው ቦርድ ሁኖ እያለና በቦርዱ የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየቱ ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም

በማለት ያቀረበው ተቃውሞ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 በተዘረጋው ስርዓት መሠረት የመጨረሻ ፍርድ አግኝተዋል ወይስ አላገኙም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 መሠረት ወደ አስተዳደር ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ ያለብኝ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ከሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ለማቅረብ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው ስርዓት ተፈቅዶልኛል በማለት ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 2(8) ስር የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ተብሎ የሚመደብ በመሆኑና በዚህ ባለስልጣን በሚሰጠው ውሣኔ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ይገባኝ ማቅረብ ይቻላል በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው የዩኒቨርሲቲው አካዳሚ ሰራተኞች የዲስፕሊን አፈፃፀም ደንብ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 33(4) ይግባኙ የሚቀርበው ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ መሆኑንና ይህ አካል የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ) ድንጋጌ ያሣያል በማለት መሆኑን ተረድተናል፡፡

እኛም ይህንኑ የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ በአዋጅ ቁጥር 65/2001 አንቀጽ 22(3)፣ 44(ጎ) መሠረት ለዩኒቨርሲቲ ቦርድ ከተሰጡት ኃላፊነቶችና ተግባራት አንፃር ተመልክተናል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 32 ሥር የአካዳሚክ ስራተኞች ግዴታዎች የተዘረዘሩ ሲሆን የተጠቃሹ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ ደግሞ ተቋማቱ በዚህ አንቀጽና አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተመሠረተና የአካዳሚክ ስራተኞችን ያሣተፈ የአካዳሚክ ሠራተኞች የዲስፕሊን ደንብ አውጥተው ተግባራዊ ማድረግ የሚኖርባቸው መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ በዚህ የአዋጁ አግባብም አመልካች ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ስራተኞች የዲሲፕሊን ደንብ ቁጥር 1/2002 አውጥቶ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ ደንብ የአካዳሚክ ስራተኞች የዲሲፕሊን ጥፋቶችና ቅጣቶች፣ የዲሲፕሊን ክስ አመሰራረት፣ የምርመራ አፈፃፀምና ውሣኔ አሰጣጥ፣ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት፣ የይግባኝ ምክንያቶችና የጊዜ ገደብን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ ደንቡ የአካዳሚክ ስራተኛ የዲሲፕሊን ግድፈት ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ውሣኔ የሚሰጡበትን አግባብ በአንቀጽ 32 ያስቀመጠ ሲሆን ይህ አካል ከስራ የመባረርን ውሣኔ አስመልክቶ በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አስመልክቶ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ሰራተኛ ጉዳዩ እንዲታይለት ይግባኙን በአስር ቀናት ውስጥ ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሊያቀርብ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ) መሠረትም የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከተው ስርዓት አመልካች ዩኒቨርቲው በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 32(3) መሠረት የአካዳሚክ ሰራተኞችን የዲስፕሊን ግድፈት ለመግዛት የዘረጋው ሰርዓት ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 650/2001 ከአዋጅ ቁጥር 515/1999 በኋላ የወጣ በመሆኑና የሚገዛው ጉዳይም ተለይቶ የተሰጠው በመሆኑ በአዋጅ በተካተቱት ጉዳዮች ከማንኛውም አቻ ሕግ የበላይ ገዥነት የሚኖረው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያለቸው የሕግ አተረጓጉም ደንቦች የሚያሣዩን ሐቅ ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካች ዩኒቨርሲቲ

www.abyssinialaw.com

አካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ ከአዋጅ ቁጥር 515/1999 ቀዳሚ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 650/2001 በመሆኑ በዚህ አዋጅ የተዘረጋው ስርዓት ሊከበር ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ይግባኙን ለቦርዱ ሣያቀርቡ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ያቀረቡት መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ የሚያሣይ ከመሆኑም በላይ በሰበር የክርክር ደረጃ መልሣቸውን ለማሻሻል ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅትም ይህንኑ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ምክንያት የሰበር መልሣቸውን ለማሻሻል ያቀረቡት ጥያቄም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 አንፃር ሲታይ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ አልፈነዋል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ ቀርቦ ያልታየ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው ውሣኔውን በሰ/መ/ቁጥር 26480 ከተሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር አዞምዶ ለመወሰን ሲባል ሲሆን በዚህ የሰበር መዝገብ የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ክርክር የተነሣበት ጊዜ፣ የተከራካሪ ወገኖች የሚገዙበት ሕግ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር የማይገናኝና በመሠረታዊ ነጥቦች ጉዳዮቹ የተለያዩ መሆናቸው ግልጽ ከመሆኑም በላይ አሁን በተያዘው ጉዳይ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ግንኙነት የሌለውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 46402 ከመጥቀሱ ውጪ ጉዳዩ የመጨረሻ የአስተዳደር ውሣኔ ያገኘ መሆን ያለመሆኑን፣ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ስልጣን ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ነ) ድንጋጌ አኳያ ታይቶ መፍትሔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባሁኑ የክርክር ደረጃ በዚህ ረገድ ምላሽ የሚሰጠበት ጉዳይ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ባሁኑ የክርክር ደረጃ መታየት ያለበት አቢይ ነጥብ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 መሠረት በተዘረጋው ስርዓት ይግባኛቸውን አሟጠው ጨርሰዋል ወይስ አልጨረሱም? የሚል በመሆኑ ይህን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ የይግባኝ ስርዓታቸውን ለሚመለከተው አካል አቀርበው ያልጨረሱ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች በአስተዳደራዊ አካላት መታየት ያለበትን የይግባኝ ስርዓት ያልጨረሰ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ ደግሞ በፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ አይኖርም፡፡

በአጠቃላይ የተጠሪ ይግባኝ ወደ አስተዳደር ፍርድ ቤት የሄደው ስርዓቱን ጠብቆ ይግባኙን ሣይጨርስ በመሆኑ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔና ይህንኑ ውሣኔ ያፀናው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትእዛዝ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 32(3) እና አመልካች ዩኒቨርሲቲው ያወጣውን ደንብ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 34(4) ድንጋጌዎችን የጣሰና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 01247/2004 ታህሣስ 05 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ብይን እንዲሁም ይኸው አካል ታህሣስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 75990 መጋቢት 12 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ብይንና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 32(3) መሠረት ዩኒቨርሲቲው ባወጣው የአካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ደንብ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 33(4) መሠረት ይግባኙን ማቅረብ ያለባቸው ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ሣይሆን ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 81215

ጥር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ ነ/ፈጅ ጌጡ ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐ/ህግ ሜሮን አንማው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጉምሩክ ወንጀል ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት የአሽከርካሪ ባለቤት ወይም አሽከርካሪ በቅጣት ረገድ ተሽከርካሪው በመንግሥት እንዲወረስ ውሳኔ ከተሰጠበትና የወንጀል ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት ተሽከርካሪው በባንክ መያዣነት መያዙ ከተረጋገጠ በሕግ ፊት ቅድሚያ ሊጠበቅ የሚገባው በወንጀሉ ጉዳይ ተሽከርካሪው ውርስ እንዲሆን የተሰጠው ውሳኔ ነው ወይስ ወይም የመያዣ መብቱ ነው? የሚለውን የሕግ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በመቀሌ ከተማ ማዕከላዊ ፍ/ቤት ሚያዚያ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ በክሱ ላይም ንብረትነቷ የአቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና የሆነች የኮድ ቁጥር 3-29644 አ.አ አይሱዚ የጭነት መኪና አቶ ብርሔ ሓጎስ ከከሳሽ ባንኩ ሲበደሩ መኪናዋን አስይዘው ብር 90,000.00 /ዘጠና ሺህ/ መበደራቸውንና በየወሩ ብር 2,905.00 እየከፈሉ ክፍያውን በማቋረጣቸው መኪናዋ በፎርክሎጀር ሕግ መሠረት ተሸጣ ለእዳው የሽያጭ ገንዘቡ ገቢ እንዲሆን በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ትዕዛዝ የተሰጠባት መኪና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የመቀሌ ቅርንጫፍ ጠይቆ መኪናዋ ቦንዳ ጭና በመገኘቷ የተወረሰች መሆኑን ለባንኩ የገለፀላቸው መሆኑን ገልጾ በመኪናው ላይ ከማንኛውም ወገን ቅድሚያ ያለው በመሆኑ መኪናውን ተጠሪ እንዲያስረክብ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ክስ በሰጠው መልስም ንብረትነቷ የአቶ በርሔ ሐጎስ አድሃና የሆነች ኮድ 3-29644 አ.አ አይሱዚ መኪና ባለንብረቱ በገንዘብ ተከሶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንደሚገኝ፣ የመኪናዋ ባለቤት አቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና መስከረም 28 ቀን 2002 ዓ.ም ጣልቃ ገብተው ወጋገን ባንክ በቁጥር 126/ተሰአ/2002 በ3/2/02 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በማይጨው ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 13144 ሲከራከር ቆይቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ5/02/2002 ዓ.ም በመ/ቁጥር 48628 ተጠቃሹ መኪና በተጠሪ እጅ ሊቆይ እንደሚገባ መወሰኑን ገልጾ በመከራከሩ ፍርድ ቤቱ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተያዘው ጉዳይ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 197/2/ መሠረት አቆይቶ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ግንቦት 05 ቀን 2003 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠቱን የስር ፍ/ቤት ከተገለፀለት በኋላ የተዘጋውን መዝገብ ሲያንቀሳቅስ

የአሁኑ ተጠሪ መልሱን ለማሻሻል ጥያቄ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ፈቅዶለት ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው መልሱ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አከራካሪዋ መኪና በወንጀሉ ጉዳይ ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን የወሰነ መሆኑንና ይህ ደግሞ አመልካች በመኪናዋ ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሶ በመጨረሻ ፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ክሱ መቀጠል የለበትም ሲል ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ጉዳዩ የተለያየ ስለሆነ የመጨረሻ ፍርድ አግኝቷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ የመያዣ መብቱ ቅድሚያ እንዲጠበቅለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው መኪና በጉምሩክ ወንጀል ምክንያት ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠባት መሆኑን በምክንያትነት ይዞ በመኪናዋ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244/2/መ/ መሠረት ሌላ ክርክር የሚቀርብባት አግባብ የለም ሲል ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 32/2/፣ 244/2/ለ/መ/ ድንጋጌዎች ጠቅሶ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም መኪናዋ ለባንክ ብድር ለመያዣነት የተሰጠች ሆኖ እያለ ከመያዣው በኋላ ለተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን መወሰኑ ለቅድሚያ መብት ጥያቄው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የማያስችል መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ አንድ ጉዳይ ቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ነው ለማለት መሟላት የሚገባቸውን መመዘኛዎችንና የመያዣ መብትን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በብድር መያዣነት የያዘው ተሸከርካሪ የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲወረስ ቀደም ሲል በመወሰኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 32/2/፣ 244/2/ለ/መ/ መሠረት አመልካች ሌላ ክስ ማቅረብ አይችልም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3059/2/ እና ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 98/3/መ/ እና አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 95/2/ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስም አመልካች የመያዣ መብት ሊጠቀም የሚችለው በፍትሐብሔር ጉዳዮች እንጂ በወንጀል ጉዳዮች ያለመሆኑንና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሠረት በማይጨው ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብም ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ሲያጣ ቆይቶ የመጨረሻ ፍርድ ሲሰጥ የቅድሚያ መብትን መሠረት አድርጎ ክስ መመስረቱ ሕጋዊ አካሄድ ያለመሆኑን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ለአቶ በርሔ ሓጎስ መስከረም 02 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገና በተወሰነ ጊዜ በሚከፈል የብድር ውል ብር 90,000.00 /ዘጠና ሺህ ብር/ ሲሰጥ ንብረትነቱ የተበዳሪው የሆነውንና አሁን ክርክር ያስነሳውን ቁጥሩ 3-29644 የሆነውን አይሱዙ ተሸከርካሪ በአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በመያዣነት ማስመዝገቡን፣ ይህ ሆኖ እያለ ግን መኪናው የኮንትሮባንድ እቃ

በ24/06/2001 ዓ.ም ጭኖ በመገኘቱ የንብረቱ ባለቤት የሆነው አቶ በርሔ ሓጎስ በተጠሪ መስሪያ ቤት ዓቃቤ ህግ በትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው ክርክሩ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ከተካሄደ በኂላ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁጥር 48628 በሆነው መዝገብ ግንቦት 05 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቶ በርሔ ሓጎስ ላይ የተጣለውን የሶስት አመት ቀላል እስራትና የብር 5,000.00 የገንዘብ መቀጮ በማጽናት መኪናውን በተመለከተ ደግሞ ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን የታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣ አመልካች በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የወንጀሉ ክርክር ሲካሄድም አመልካች በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ይፈቀድለት ዘንድ ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ጠይቆ የነበረ መሆኑን ሰ/መ/ቁጥር 48628 ከተያያዘው አቤቱታ የተረጋገጠ መሆኑንና አመልካች በስር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 08782 ያቀረበውና ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ የፍትሐብሔር ክርክርን መሠረት ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ የክርክር ሒደት በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው አከራከሪዋ መኪና ለብድር መያዣነት አመልካች የያዛት የወንጀል ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት መሆኑንና ተጠሪም የአመልካች ክርክርና የዳኝነት ጥያቄ ሥነ ሥርታዊ አይደለም የሚለውን ጥብቅ ክርክር ከማቅረቡ ውጪ በመኪናዋ ላይ አመልካች በሕጉ አግባብ ያቋቋመው የመያዣ ውል የለም በማለት የማይከራከር መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ምላሽ የሚያስፈልገው የሕግ ጥያቄ በመያዣ የተያዘ ተሽከርካሪ ከመያዣው በኂላ በኮንትሮባንድ ወንጀል ምክንያት ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን በፍ/ቤት የመጨረሻ ፍርድ ከአረፈበት ባለመያዣው በተሽከርካሪው ላይ ያለው መብት በምን አግባብ ሊከበር ይገባል? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ መብት በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር የፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣2857/1/ እና 3059 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሕግ አግባብ የተቋቋመው የመያዣ ውል መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ይኼው መብት ያለው ሰው ከሌላው ሰው የቀደመ መብት ያለው መሆኑን የተጠቃሾቹ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ያስረዳል፡፡ የፎርክሎዠር ሕጎቻችን ሲታዩ ደግሞ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች እዳው ሳይከፈለው በቀረ ጊዜ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪው በመስጠት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በመያዣ የያዘውን ንብረት በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም ሌላ መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ከመያዣው ሽያጭ ዋጋ ከሌሎች ባለገንዞቦች ቀድሞ የመቀበል መብት እንዳለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2857/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ለብድር አከፋፈል በመያዣነት በያዛቸው ንብረቶች ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም የወንጀል ሕጉን በመተላለፍ ለሚፈፀም ድርጊት ወንጀሉ የተፈፀመበት ንብረት ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን ቢወሰንና ይኼው ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን የተወሰነበት ንብረት በመያዣ የተያዘ መሆኑ ቢረጋገጥ የመያዣ መብት ያለው ሰው መብት በምን አግባብ ሊከበር እንደሚችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 98 ድንጋጌ በግልጽ የሚያስቀምጠው ድንጋጌ የለም፡፡ የኮንትሮባንድ ወንጀሎችን በተመለከተ በልዩ ሁኔታ የሚገዛው አዋጅ ቁጥር 622/2001 ወይም ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጐችም ቢሆኑ በዚህ ረገድ ግልጽ ድንጋጌ ይዘው አናገኛቸውም፡፡ በሕጉ ማዕቀፍ ያለው ሁኔታ በዚህ መልክ ግልጽ ያልሆነ ከሆነ ደግሞ በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ስር ያለውን አግባብ በመመልከት ጉዳዩን እልባት መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ ተቀባይነት ካላቸው የህግ አተረጓጎም ደንቦች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

የአሰሪና ሠራተኛን ጉዳዩ በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት በቅጥር ላይ ከተመሠረተ የሥራ ግንኙነት የሚመነጭ የሠራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚኖረው በአንቀጽ 167 ላይ ተመልክቷል፡፡ የዚህ የሕግ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳየው በቅጥር ላይ ከተመሰረተ የሥራ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውንም የሠራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የተደነገገ እንደመሆኑ መጠን የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች አቋም ተራ ገንዘብ ጠያቂዎች /ordinary creditors/ ወይንም እንደ አመልካች በመያዣ ብድር የሰጠ ባለገንዘብ /secured creditors/ ሆኑም አልሆኑ የሠራተኛው የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ስለተደነገገ ከባንክ ጭምር ቅድሚያ መብት ያላቸው ሠራተኞች መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን በዚህ የሕግ ማዕቀፍ የሕግ አውጪው ለማሣካት ያሰበው የሠራተኞች ክፍያ ጥያቄዎች ከሠራተኛው የዕለት መተዳደሪያ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ሠራተኛው ለሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንዲያገኝ ማድረግ ስለመሆኑ ይታመናል፡፡ ሌላው የሕግ ማዕቀፍ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 80 ስር እንደተመለከተው ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር ሰብሳቢው መብት ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሐብት ላይ ከማናቸውም ሌሎች እዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል በማለት ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ይህም የሚያሳየው ከግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ሁሉ የመያዣ መብት ያላቸው ሰዎች ቅድሚያ መብት እንዳላቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ያለው አጠቃላይ ሁኔታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በወንጀል ሕጉ ላይ ለመንግሥት እንዲወረስ ውሳኔ በሚሰጥበት ንብረት ላይ የመያዣ መብት ስላላቸው ሰዎች መብት ግን በግልጽ የተመለከተ ድንጋጌ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለፀው የወንጀል ሕጉን አይነተኛ ዓላማ ከመያዣ ሕጎች መሠረታዊ ዓላማ እና አዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 91/2/ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ለጉዳዩ እልባት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ የመያዣ ውል መሠረታዊ ዓላማ የንግድ እንቅስቃሴ ዋስትና እንዲኖረው ማስቻል መሆኑ የሚታመን ሲሆን የወንጀል ሕጉ ደግሞ ለጠቅላላው ሕዝብ ሠላምና ደህንነት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ባንኮች የሕዝብ መብትና ጥቅም ያላቸው ተቋማት መሆናቸው ክርክር የሚቀርብበት ጉዳይ አለመሆኑ የሚታመን ነው፡፡ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የአገሪቱ የገቢ ማሰባሰብ ስርዓት ሕጋዊ እንዲሆን ማስቻል መሆኑ አዋጅ ቁጥር 578/200 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የግብር እና ታክስ ህጐች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 80 ድንጋጌ ስር መያዣ ያላቸው ሰዎች ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑ በግልጽ ከተደነገገ ግብር አስገቢ መስሪያ ቤት ሕጉን ለማስከበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ አጥፊዎችን በፍ/ቤት ሲያስቀጣና አጥፊዎች ወንጀሉን የፈፀሙባቸውን ንብረቶች በሕጉ አግባብ ለመንግሥት እንዲወረሱ በሕጉ አግባብ ከተወሰነ በዚህ ንብረት ላይ መብት ያላቸው ሰዎች መብት ንብረቱ በወንጀል ምክንያት ለመንግሥት ገቢ እንዲሆኑ መወሰኑ ብቻ መያዣ ያላቸው ሰዎች መብት ዋጋ የሚያጣበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑ የሕግ አውጪው ሐሳብ መሆኑን የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች አንድ ላይ ሲታዩ የሚያስረዱን ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በአከራካሪው ንብረት ላይ ከወንጀል ድርጊቱ በፊት ሕጋዊ የሆነ የመያዣ መብት ያቋቋመ ስለመሆኑ ክርክር ያልቀረበበት ጉዳይ በመሆኑና ይኼው መብት ከመያዣው በኂላ ተበዳሪው በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ውጤት አልባ የሚሆንበት ሕጋዊ አግባብ ሊኖር ስለማይገባ የአመልካች መብት ከተጠሪ ክስና ሕጋዊ ውጤት ቅድሚያ ጥበቃ ሊሰጠው ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አቅጣጫ በማየት እልባት መስጠት ሲገባቸው ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን ድንጋጌዎች በመጥቀስ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

www.abyssinialaw.com

ሌላው እልባት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የተጠሪ መብት በምን አግባብ ሊከበር ይገባል የሚል ነው፡፡ የወንጀል ድርጊቱን የፈፀሙት ግለሰብ በተሽከርካሪው የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀማቸው ከተረጋገጠ የውርስ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚገባው በተሽከርካሪው ላይ ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የመያዣ መብት ያለው ወገን መብቱን ቀድሞ እንዲያስከበር ከተደረገ ከመያዣ ባለመብቱ የሚተርፈው የንብረቱ ግምት ወይም በወንጀሉ ምክንያት እንዲወረስ የተባለው ንብረት በመያዣው ውል መነሻ ሙሉ በሙሉ በመያዣ ሰጪው የሚያወድ ከሆነ ተራፊው የመያዣ ንብረቱ ግምት ለመንግሥት የማይመለስበት ወይም ተራፊ ከሌለ ደግሞ ውርስ እንዲሆን በወንጀል ጉዳይ ተወስኖበት የነበረው የንብረቱ ግምት ይህል ድረስ በአጥፊው ሌላ ንብረት ላይ መንግሥት አፈጻጽሙን እንዲቀጥል የማይደረግበት አግባብ ሊኖር አይገባም፡፡ ምክንያቱም አጥፊው በወንጀል ተግባሩ አትራፊ ሊሆን አይገባውምና፡፡ በመሆኑም አመልካች የሚፈልገውን የብድር እዳ የአከራካሪው መኪና ዋጋ ሸፍኖ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ ተራፊውን ገንዘብ ለመንግሥት እንዲወረስ ማድረጉ ወይም የሚተርፍ ነገር ከሌለው ንብረቱ ይወረስ ተብሎ በተወሰነበት ጊዜ በነበረው ግምት ያህል በሌላ የወንጀል ድርጊቱ አጥፊ የግል ንብረት ላይ አፈፃፀሙን እንዲቀጥል ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የመያዣ መብት የተቋቋመበት ተሽከርካሪ በኮንትሮባንድ ተግባር ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን ውሳኔ ከተሰጠ መያዣ ሰጪው ቅድሚያ መብት ያለው በመሆኑና ይሄው መብቱ ሊከበርለት የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ስለሚቻል አመልካች በአከራካሪው ንብረት ላይ የቅድሚያ መብት ስላለኝ በዚህ ንብረት ላይ የወንጀል ውርስ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረበውን አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት መቅረታቸው በአግባቡ ስላልሆነ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና የሆነች የኮድ ቁጥር 3-29644 አ.አ አይሱዚ የጭነት መኪና የኮንትሮባንድ ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት በአመልካች በሕግ አግባብ የመያዣ መብት የተቋቋመባት መሆኑ ስለተረጋገጠ ለብድር ገንዘቡ መመለሻ ቅድሚያ ልትውል ይገባል ብለናል፡፡ በተበዳሪው ላይ አመልካች የሚፈልገው የብድር መጠን ከመኪናው ዋጋ በታች ከሆነ ተራፊው ገንዘብ ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን፣ መኪናው ላይ የሚመለስ ወይም ተራፊ ገንዘብ ከሌለ ደግሞ መንግሥት መኪናው ይወረስ ተብሎ በወንጀል ጉዳይ ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ የነበረውን ዋጋ ያህል ከአቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና የግል ንብረት ላይ አፈፃፀሙን ቀጥሎ ተጠሪ ለመንግሥት ገንዘቡን ገቢ ማስደረግ ይችላል በማለት ወስነናል፡፡
3. የክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 78414

ጥቅምት 07 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነ/ፈጅ ፍሬው ሃይሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.አቶ ቶላ መገርሣ
2.አቶ ታምራት ኃይሌ } ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ግዴታን ባለመወጣት በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ የሲቪል ሰራተኛ በጥፋቱ ምክንያት የመንግስት ንብረት መጥፋቱ ሲረጋገጥ በሕግ ፊት ስላላው የፍትሐብሔር ሓላፊነትን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቸው ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ተጠሪዎች በአመልካች መስሪያ ቤት በጥበቃ ሰራተኛነት በማገልገል ላይ ሳሉ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 አካባቢ ከሚገኘው የአመልካች መጋዝን በሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም. ሌሊት የጥበቃ ተረኛ በነበሩበት ወቅት የአመልካች የሆኑ መለያቸው 70×168 PR የሆኑ እያንዳንዳቸው ብር 1977.39 የሚያወጡ አስራ ሶስት ብሪጅስቶን ጎማዎችን ያጠፉ መሆኑንና ተጠሪዎችም የስራ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ሳቢያ ለፈፀሙት ወንጀል በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን ገልፆ ተጠሪዎች የጎማዎቹን ዋጋ ብር 25,706.07 (ሃያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ስድስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም በአመልካች መስሪያ ቤት በጥበቃ ስራ ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ ንብረቶቹን ለስራ የተረከበው ግለሰብ ሌላ መሆኑን ፣በወንጀል ጉዳይ የመሰከሩት ምስክርም እቃው ጠፋ በተባለበት ወቅት ያልነበሩና ያላዩ መሆናቸው መታወቁን፣መጋዝኑ ዝግ ሁኖ ማደሩ መረጋገጡን፣የገንዘብ መጠኑ ከፍ ያለ በመሆኑ በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ እንደማይችል፣በርክክብ ሰነዱም ለተተኪ የጥበቃ ሰራተኞች በሰላም ማስረከባቸውንና ክሱም በማስረጃ ያለመደገፉን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች በወንጀል የተቀጡ ስለመሆኑ

ቢረጋገጠም ጠፉ የተባሉትን ንብረቶች የወሰዱ ስለመሆኑ የወንጀል ውሳኔው እንደማያሳይ፣ንብረት ቢጠፋ ተጠሪዎች የጠፋውን ንብረት ለአመልካች ለመክፈል የተደረገ ስምምነት ወይም ውል የሌለ መሆኑና በጠፉት ንብረቶች ተጠሪዎች የበለፀጉበት ሁኔታ ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪዎችን ከክሱ በነጻ አሰናብቷቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣት በወንጀል ጥፋተኛ ሁነው ተገኝተው እያለና የወንጀል ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ደግሞ ጎማዎቹ መጥፋታቸው ተረጋግጦ እያለ ተጠሪዎች ለፍትሐ ብሔር ክሱ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ምላሽ የሚያስፈልገው የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪዎች በአመልካች መስሪያ ቤት በጥበቃ ሰራተኛነት በማገልገል ላይ ሳሉ ጠፉ ለተባሉ ጎማዎች የስራ ኃላፊነታቸውን አልተወጡም በማለት በወንጀል ከተቀጡ በኂላ ተጠሪዎች የጠፉትን ጎማዎች ግምት እንዲከፍሉ በቀረበባቸው ክስ ጎማዎቹን ወስደው ባለመበልጸጋቸው ወይም ጎማዎቹ ቢጠፉ ለመክፈል ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል ባለመኖሩ የሚከፈሉት ግዴታ የለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ጎማዎች መጥፋታቸውና የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣት በወንጀል የተቀጡ ስለመሆኑ ሳይክዱ ለጎማዎቹ ግምት ኃላፊነት የለብንም በማለት የሚከራከሩት ንብረቶቹን ስለመረከባችን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፣መጋዘኑም አልተሰበረም፣ለወንጀሉ ጉዳይ ምስክርነት የሰጠው ግለሰብም ጉዳዩን ሳይመለከት ነው የመሰከረው የሚሉትን ምክንያቶችን በመጥቀስ ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የቻለውም የወንጀሉ ውሳኔ ተጠሪዎችን ጎማዎቹን ስለመውሰዳቸው አይሳይም፣ ንብረቶቹ ሲጠፉም ለመክፈል ስምምነት ውል የለም፣ እንዲሁም ተጠሪዎች ስለመበልፀጋቸው የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በሚሉ ምክንያቶች ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተጠሪዎች አከራካሪ እቃዎቹን ለአመልካች መስሪያ ቤት እስከሚያስረክቡ ጊዜ ድረስ በጥበቃ ላይ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ በንብረቶቹ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት፣ብልሽት ወይንም መጥፋት በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህ ችግር እንዳይከሰት ተገቢውን የጥበቃ ስራ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይታመናል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው መስሪያ ቤት ለስራ እቃዎቹን ሲረከብ የሚፈርመበት ዋናው ምክንያትም ይህንኑ ግዴታውን ካልተወጣ ኃላፊነት ሊከተልበት ስለሚገባውና የእቃዎቹን ግምት በማወቅ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲወጣ ለማስቻል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 እና በሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች የተካተቱት ድንጋጌዎች ይዘት፣መንፈስና ዓላማ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪዎች የአመልካችን ንብረቶች ያሉበትን መጋዝን ሲጠብቁ በመጋዝኑ ውስጥ ያሉት እቃዎች እንዳይጠፉ፣እንዳይሰረቁም ሆነ ሌላ ጉዳት እንዳይደርስባቸው

www.abyssinialaw.com

ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠበቅባቸው በሥራ ሰዓት ሲሆን ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት ከተጠሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት ውጪ በሆነ ምክንያት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭና በተጠሪዎች እጅ ባልነበሩበት ጊዜ የጠፉ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ ይህንኑ ግዴታቸውን የተወጡ ስለመሆኑ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን መዝነው ያረጋገጡት ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካች ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን ሳይወጡ ቀርተው በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ስለመሆኑ የሚሳይ የውሳኔ ግልባጭ ያቀረበና ተጠሪዎቹም ቢሆኑ በወንጀል ጉዳይ ላይ የምስክርነት ቃል የሰጠውን ምስክር ጉዳዩን አይውቅም ብለው ከመከራከራቸው ውጪ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ በስርአቱ መሰረት መለወጡን ገልጸው አልተከራከሩም፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣት ኀማዎቹ እንዲጠፉ ስለማድረጋቸው በወንጀል ችሎት ውሳኔ መረጋገጡን በቀላሉ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ቀጥሎ መታየት ያለበት አቢይ ነጥብ በወንጀል ችሎት የተሠጠ ውሳኔ በፍትሐ ብሔር ክርክር ጊዜ ስላላው የማስረጃነት ዋጋ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ እና በፍትሃብሔር ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ የሚመዘኑበት መርህ የተለያየ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማሰረጃ የሚመዘነው ጥብቅ በሆነ መንገድ ሲሆን በፍትሐብሄር ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ ደግሞ ከተከራካሪ ወገኖች መካከል የተሻለ ያስረዳ የትኛው ወገን ነው? የሚለው መለኪያ ተይዞ የማስረጃው ክብደት የሚለይበት ስርአት በመሆኑ የማስረጃ አመዛዘኑ መርህ ከወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አመዛዘን መርህ የላላ ነው፡፡ እነዚህ ተቀባይነት ባለቸው የማስረጃ ሕግ ደንቦች የሚታወቁ የማስረጃ አመዛዘን መርሆች አንዱ በሌላው ላይ ስላለው ውጤት ሲታይም በፍትሃብሔር ሕጋችን ቁጥር 2149 ስር የተመለከው ድንጋጌ ምላሽ ይሰጠናል፡፡ ይኸውም በፍትሃብሔር በኩል ጥፋት ተደርጎአል ብሎ ለመወሰን በወንጀል ፍርድ ተከሳሹ ነፃ መለቀቁ ወይም በወንጀል አያስከስሰውም ተብሎ መበየኑ ዳኞቹን አያግዳቸውም በሚል ሓይለ ቃል በያዘ መንገድ ተቀምጧል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበው ከወንጀል ክስ ነጻ መሰናበት የፍትሐብሔር ተጠያቂነትን ቀሪ የማያደርገው መሆኑን ነው፡፡ የድንጋጌው ተቃራኒ ንባብ ሲታይም በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው በፍትሐብሔር ተጠያቂ መደረግ ያለበት መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህም በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ በጥብቅ መንገድ የሚመዘን እስከሆነ ድረስ የላላ የማስረጃ ምዝና ስርዓትን ለሚጠይቀው የፍትሃብሔር ጉዳይ በቂ ዋጋ እንደአለው ተደርጎ መወሰድ አለበት የሚለው የማስረጃ ሕግ ደንብ መሆኑን የሚያሳየን ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የተሰጠውን ውሳኔ ይዘት ከላይ ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ሳያገናዝቡ መወሰናቸው ያላግበብ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪዎች ስለመበልጸጋቸውና ንብረቶቹ ሲጎድሉ ለመክፈል ስምምነት ያለማድረጋቸው ከሃላፊነት ነፃ ለማድረግ በምክንያትነት መጠቀሱም በአመልካች ላይ በሕጉ ያልተጣሉ ግዴታዎች በመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 93529 ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117394 የካቲት 14 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች የስራ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት በአመልካች ጎማዎች ላይ ላደረሱት ጉድለት በአንድነትና በነጠላ ብር 25,706.07 (ሃያ አምስት ሺኅ ሰባት መቶ ስድስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 74036

መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ጠበቃ ይልማ አቻሜ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ ነ/ፈጅ መዓዛ ገ/ልዑል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በተጠሪ የታገደ ገንዘብ ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በይግባኝ ደረጃ የታየው በተጠሪ ቦርድ ነው፡፡ በዚህ ቦርድ ይግባኝ ባይ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የይግባኝ አቤቱታው ዋና ሐሳብም አመልካች የአዋጅ ቁጥር 621/2001 ተግባራዊ መሆን ከመጀመሩ በፊትና ደንብ ቁጥር 168/2001 በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ድርጅቱ በልዩ ልዩ ሁኔታ በህጋዊ መንገዶች ከውጭ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ኤጂንሲው በቁጥር01/chsa-2980/N1146 ታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፈው ደብደቤ በድርጅቱ የባንክ ሂሳቦች ላይ የጣለውን እገዳ በቦርዱ እንዲነሳ እና በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን በተጻረረ መንገድ የተከናወነ እገዳ ከምዝገባችን ቀድሞ የተጣለብን መሆኑና ድርጅታችን ያልሰራበት ገንዘብ እንኳን ቢኖር ከለጋሾች ጋር በገባነው ስምምነት መሰረት ሊመለስላቸው ሲገባ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ድርጅቱ ለረዥም ጊዜ በወለድ ያጠራቀመው ገንዘብ በጅምላ በመታገዱ ቦርዱ ይህንኑ አውቆ እገዳውን እንዲያነሳልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በአዋጁ መሰረት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡንና የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ደግሞ ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ገቢ ምንጭ መጠቀም እንደማይችል አዋጁ የሚከለክል መሆኑንና በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከውጭ የሰበሰበው በርካታ ገንዘብ የነበረው ከመሆኑም በላይ አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በኋላ በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን፣አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ.ም. በኋላ በቀድሞ ሕጎች የተገኙ መብትና ግዴታዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት አዋጁን የማይቃረኑ ብቻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 111(1) መደንገጉንና ድርጅቱ ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ በመሆኑ ገንዘቡን ለተሰማራበት ዓላማ መጠቀም የማይችል መሆኑን፣በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከአገር ውስጥ ምንጭ 90% የሚያመነጭ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡንና ከመመዝገቡ በፊት ከውጭ ምንጭ የሰበሰበው **ስምንት ሚሊዮን** ብር የነበረው ቢሆንም በአዋጁ መሰረት ገንዘቡን መጠቀም ስለማይችል በኤጂንሲው መታገዱን፣በአዋጁ መሰረት ገንዘቡን ለሌላ ድርጅት ማስተላለፍ ቢቻልም ኤጂንሲው የወሰደው አቋም ግን በየአመቱ **90%** ከአገር ውስጥ

www.abyssinialaw.com

አመንጭቶ ለኤጄንሲው ሲያቀርብ ቀሪው 10% ደግሞ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ እየተለቀቀለት መንቀሳቀስ እንዲችል የሚያደርግ መሆኑን ዘርዝሮ ይግባኙ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ቦርዱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 104 በተዘረጋው የይግባኝ ስርዓት መሰረት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የቦርዱ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ አከራካሪውን ገንዘብ ለማገድ ሕጉ ስልጣን የማይሰጠው መሆኑና እግዳውም የተደረገው አመልካች ድርጅት ሕጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በልዩ ልዩ ሁኔታና ሕጋዊ መንገዶች ከውጭ ምንጭ የተገኘ ገንዘብ የሚታገድበት ሕጋዊ አግባብ የለም ብሎ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 111(1)፣አዋጁን ለማስፈፀም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከወጣው ደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀፅ 10(2) እና የፍትህ ሚኒስትር መጋቢት 16 ቀን 2001 ለተለያዩ የፌዴራልና የክልል አካላት በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምር ድረስ ነባር የበጎ አድጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቀድም ሲል ሲሰሩ በነበረበት ሁኔታ ስራቸውን መቀጠል እንደሚችሉ በመግለጽ ከፃፈው ደብዳቤ አንፃር ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለቦርዱ አቤቱታውን ሊያቀርብ የቻለው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመፅናቱ በፊትም ሆነ የምስክር ወረቀት እስከተሰጠበት እስከ ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ከውጭ የተሰበሰበውን ገንዘብ ያላግባብ ኤጄንሲው አግዶብኛል፣ይህንን ለማድረግ አዋጁም ሆነ ደንቡ አይፈቅዱለትም፤ስልጣን አይሰጡትም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሠበር ቅሬታም ተጠሪ በሕጉ ስልጣን ያልተሰጠው ከመሆኑም በላይ የአዋጁንና የደንቡን ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍትህ ሚኒስቴር መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈውን ደብዳቤ ይዘት ባላገናዘበ መልኩ እገዳውን ማከናወኑን ዝርዝሮ መከራከሩን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከውጪ የሚሰበሰበው ገንዘብን መሰረት በማድረግ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ትርጉም፣ አይነታቸውንና ዓላማቸውን ለይቶ ገደብ ያደረገ ስለመሆኑ የሚያመላክቱ ድንጋጌዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ ይህንኑ መለኪያ መሰረት አድርጎም አዋጁ ሶስት አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በአገሪቱ የህግ ማዕቀፍ የሚታወቁ መሆኑን የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ ቁጥር (2)፣ ንዑስ ቁጥር (3) እና ንዑስ ቁጥር (4) ድንጋጌዎች እንደየ ቅደም ተከተላቸው ሲታዩም የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት፣የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት እና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት በሕጉ የሚታወቁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማህበራት አይነቶች መሆናቸውን በመጥቀስ ትርጓሜአቸውን አስቀምጠው እናገኛለን፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማህበራት አይነት የሚወሰነው

www.abyssinialaw.com

በመሰረታዊነት የገቢ ምንጭን በመመርኮዝ ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ኢትዮጵያዊ ነው ተብሎ ሊመደብ የሚገባው በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት መመስረቱ ብቻ ሳይሆን ከውጪ ምንጮች የሚገኘው የገቢ መጠን ከጠቅላላ ገቢው አስር ከመቶ (10%) የማይበልጥ ሲሆን ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከጠቅላላ ገቢው ከአስር ከመቶ በላይ የሆነውን ገቢ ከውጭ ምንጮች ስለማግኘቱ ከተረጋገጠ የኢትዮጵያ ነዋሪ ተብሎ እንደማይመደብ በአዋጁ አንቀፅ 2(2) እና 2(3) የተቀመጡት የትርጓሜ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ሕጉ በዚህ ረገድ ያስቀመጠው የትርጉም መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚሰማራበትን ዓላማ ለመለየትም መለኪያ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 14 ድንጋጌ ከላይ ከተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ተጣምሮ ሲነበብ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጁ አንቀፅ 14(2) የበጎ አድራጎት ማህበራትና ድርጅቶችን ዓላማዎች የዘረዘረ ሲሆን በአንቀፁ ንኡስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ስር ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተለይተው የተሰጡትን ዓላማዎችን አስቀምጧል፡፡ በዚህ ንኡስ ድንጋጌ መሰረት ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ብቻ ተለይተው የተሰጡት አላማዎች የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታታት፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጾታ እና የሐይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፣ የሕጻናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፣ የግጭት አፈታትን ወይም እርቅን ማስፋፋት እና የፍትህና የሕግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር ስለመሆናቸው በግልጽ ተለይቶ ተደንግጓል፡፡ አዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አይነትና ዓላማቸውን ለይቶ ከማስቀመጡም በላይ አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ እንደሚችል፣ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች፣ የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች እንዲሁም አዋጁ የሚፀናበትን ጊዜ እንደየቅደም ተከተላቸው በአንቀፅ 109፣110፣111 እና በአንቀፅ 112 ስር አስቀምጧል፡፡ በዚኅ አግባብም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 አውጥቶ ከጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደረገ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 621/2001 ደግሞ ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 112 በግልጽ ያሳያል፡፡ የአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንዑስ ቁጥር (1) ድንጋጌ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረነ ድረስ ብቻ እንደሚቀጥል ሲደነግግ የንዑስ ቁጥር(2) ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ድርጅት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሁኖ ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ.ም. መመዝገቡንና አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በኂላ በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው፤አቤቱታውን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የተጠሪ መስሪያ ቤት ቦርድና ጉዳዩን በይግባኝ እንዲመለከት በአዋጁ አንቀፅ 104(3) መሰረት ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ አመልካችም በርካታ ገንዘብ ከውጭ ምንጮች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከጸና በሁዋላ መሰብሰቡን ሳይክድ አንዱ የክርክር ነጥብ አድርጎ የሚያቀርበው ጉዳይ አመልካች ድርጅት አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊትም ሆነ ከወጣ በኂላ በውጭ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ተመዝግቦ አያውቅም፣ዜግነቱም ኢትዮጵያዊ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በማህበርነት ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጅ

www.abyssinialaw.com

ቁጥር 621/2001 ከወጣ በኋላ በአዋጁ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ዳግም የተመዘገበ በመሆኑ አዋጁ ከጸና በኋላ በአዋጁ ለኢትዮጵያ ማህበር በተፈቀዱት ዓላማዎች መስራት ያለበት በአዋጁ መሰረት በመሆኑ ቀድሞ የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሁኖ ያለማወቁ የአዋጁ ቁጥር 621/2001 አፈጻጸም ላይ የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

እንዲሁም አዋጁ በአንቀጽ 108 ስር አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወደ ሌላ በጎ አድራጎት ድርጅት አይነት ሊቀይር ከፈለገ የሚችል ስለመሆኑ የሚሳይ ሲሆን አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 18(3) ድንጋጌ ስር ደግሞ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ከውጪ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ በሕጉ አግባብ ኢትዮጵያዊ ለመባል የማይችል ስለመሆኑ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ መሰረት እንደገና መመዝገቡ ከውጭ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወደ ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንደተቀየረ አያስቆጥረውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅት ኢትዮጵያዊ ለመባል መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና ለኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በሕጉ የተፈቀዱለትን ዓላማዎች አይነት ሳይለይ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደደለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ነጥብ ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ተፈጻሚነት የሚኖረው በአዋጁ መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ አግኝቶ ከተመዘገበ በኋላ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጅ አመልካች አዋጁ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በሕጉ አግባብ ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጁ ከወጣ በኋላ ዳግሞ ተመዝግቦ በአዋጁ ለኢትዮጵያዊ ድርጅት ወይም ማህበር የተፈቀዱትን ዓላማዎችን ይዞ እንደሚንቀሳቀስ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አዋጁ ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ከውጭ ምንጭ ከ10% በጀት በላይ መሰብሰብ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የአዋጁን አንቀጽ 2(2)(3)፣14(5) እና የደንብ ቁጥር 18(3) ድንጋጌዎችን አንድ ላይ በምናነብበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክርም የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ ስላላገኘን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ገንዘቡ በችሮታ ጊዜ የተሰበሰበ በመሆኑ አዋጁንና ደንቡን ይቃረናል ሊባል አይችልም በማለትም ክርክር አቅርቧል፡፡ለዚሁ ክርክሩ መሰረት የሚያደርጋቸው የሕግ ድንጋጌዎቹም የአዋጁ አንቀፅ 111(1) እና የደንቡን አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 111 ርዕሱ "የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች" በሚል የተቀመጠ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ንዑስ አንቀፅ አንድ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረነ ድረስ እንደሚቀጥል ሲያስቀምጥ፣ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ ያለባቸው ስለመሆኑ በአስገዳጅ መልኩ ደንግጓል፡፡ የደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 10(2) ደግሞ የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ከአንድ አመት በኋላ ይሆናል ሲል አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩ ቅራኔ ያላቸው ናቸው ለማለት የሚቻል ሳይሆን እርስ በእርሳቸው የተጣጣሙ ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በመሸጋገሪያ ጊዜው ውስጥ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በሕጉ ከተመለተከው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ የሚፈቀድበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም የመሻጋገሪያ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ቀደም ሲል በነበሩ ሕጎች የተገኙ መብቶች እና ግዴታዎች አዲስ ሕግ ሲወጣ አከራካሪ

www.abyssinialaw.com

እንዳይሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ግልጽ ምላሽ ለመስጠት ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩም ቀደም ሲል ለተገኙት መብቶችና ግዴታዎች ተፈፃሚነት ያጣው ሕግ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ሳይሆን በአዲሱ ሕግ እንዲሸፈኑ መደረጉን የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ የሕግ ማዕቀፍ የሌለውና ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 ዓላማ ጋር አንድ ላይ የማይሄድና የማይጣጣም በመሆኑና እንደአይነታቸውና ባሕርያቸው በተለያዩ ድንጋጌዎች ስለሚገዙ አዋጁ በወጣ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አስፈላጊ መሆኑ መደንገጉ አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጁ የተከለከሉ ዓላማዎችን በቀድሞው ሕግ መሰረት ማከናወን መቀጠል የማይቻል ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. የፍትሕ ሚኒስቴር ፃፈ የሚለውን ደብዳቤ ይዘት ጠቅሶ ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተውም የደብዳቤው ይዘት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መፅደቁን አስታውሶ መንግስት በአዋጁ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የሚመዘግብና የሚከታተል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጄንሲ ለማቋቋም በሂደት ላይ ያለ ስለመሆኑ ጠቅሶ ኤጄንሲው ተቋቁሞ በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምሩ ድረስ ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከዚህ በፊት ይሰሩ በነበሩበት ሁኔታ እየሰሩ መቀጠል እንደሚችሉ ለሚመለከታቸው የአስፈጻሚ አካላት ሰርኩላሩ መተላለፉን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሰርኩላር ይዘቱ የሚስገነዝበው የአዋጁን አፈጻጸም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኤጀንሲው እስከሚቋቋም ድረስ የሚመለከታቸው አካላት ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ተግባራት የሚያሳይና አዋጁን ለማስፈፀም ይቋቋማል የተባለው ኤጀንሲ ከተቋቋመ በኋላ ግን ሁሉም ነገር በአዋጁ መሰረት መሰራት ያለበት መሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 2(2) እና 111(2)፣በደንቡ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌዎች መሰረት በችሮታው ጊዜ የራሱን አደረጃጀት በማስተካከል ያልተጠናቀቁ ስራዎችን ለማጠናቀቅ እንዲችል ሕጉ በሰጠው ችሮታ ጊዜ መንቀሳቀስ የሚገባበት እንጂ ገቢውን ከአዋጁ ይዘትና መንፈስ ውጪ እንዲሰበስብ እድል የሚሰጠውና የአዋጁን አላማ ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ተፈጻሚ የሚሆን አይሆንም፡፡

አመልካች የአንድ ድርጅት ወይም ማህበርን ገቢ በማየት ዓላማ ሊወሰን አይችልም፣ዓላማው የሚወሰነው በመተዳደሪያ ደንቡ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተውም የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ዓላማ በመተዳደሪያ ደንቡ መጠቀስ ያለመጠቀሱ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 2(2)(3)(4)) እና 14(5) ድንጋጌዎች መሰረት ዋነኛው ነጥብ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከውጪ የሚያሰባስበው የገንዘብ መጠን ከገቢው 10% በላይ ከሆነ በሕጉ ተለይተው ለኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበራት በተሰጡ ዓላማዎች ላይ መሰማራት አይችልም ተብሎ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

ተጠሪ በሕግ ተቋቁሞ አዋጅ ቁጥር 621/2001 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ያወጣቸውን ደንቦች ለማስፈጸም የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 ስር ከተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባራት ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈጸም እንደሚችል በተጠቃሹ አንቀፅ ፊደል "ቸ" ስር ከተቀመጠው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ማየት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ለኤጀንሲው የተሰጠውን ስልጣን ስንመለከተው በተጠቃሹ የአዋጁ ድንጋጌ የንብረት ጥበቃ ወይም እገዳ ተግባር የሚፈፀመው ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም በማህበር መፈጸሙ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ያገደው በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በአመልካች ተፈጽሟል በሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም

በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ዓላማ አመልካች ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያደርገው ሁኖ እያለ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ከውጪ ምንጭ በርካታ ገንዘብ ሰብስቧል፣አመልካች ዓላማው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ሁኖ እስከተመዘገበ ድረስ ይህንኑ ከውጪ የተገኘውን ገንዘብ ለዓላማው ማስፈፀሚያነት ሊያውለው አይችልም በሚል ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ መፍትሔው ምን እንደሆነ አዋጁን ለማስፈፅም የወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ምላሽ ይሰጣል፡፡ ይህ የደንቡ ድንጋጌ በኢትዮጵያ ውስጥ በአዋጁ መሰረት ፈቃድ አግኝቶ የተመዘገበ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በበላይ አካሉ ውሳኔ ወደ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሊቀየርና የምስክር ወረቀት ሊያገኝ እንደሚችል በንዑስ ቁጥር አንድ በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን ማንኛውም የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሲለወጥ በባለቤትነቱ ስር ያለን ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት ለተለወጠው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊያስተላልፍ እንደማይችል፣በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ለመለወጥ ያመለከተ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የነበረው ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት በድርጅቱ የበላይ አካል ወይም **በኤጀንሲው ውሳኔ** ተመሳሳይ ዓላማ ላለው የውጪ የበጎ አድራጎ ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተላለፍ እንዳለበት የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሶስት እንደ የቅደም ተከተላቸው ሓይለ ቃልን በያዘ አቀራረፅ ያስቀመጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችን አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅት ህጉ ከመፅናቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከሕግ ውጪ ከውጭ ምንጭ የሰበሰበውን ገንዘብ ተጠሪ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተመሳሳይ ዓላማ ላለው ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፍ እንዳለበት የደንቡ አንቀጽ 18(3) በግልጽ ያሳያል፡፡ እንግዲህ በአመልካች የተፈፀመው ተግባር ላይ ተጠሪ በሕጉ ሊያደርገው ይገባ የነበረው ገንዘቡን ከማገድ የበለጠ ውጤት ያለውን፤ ገንዘቡን ለሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፉን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በህጉ ከተቀመጠው ያነሰ እርምጃ ተጠሪ መውሰዱ አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር ለተጠሪ በሕግ ከተሠጠው ስልጣን አድማስ ውጪ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ሊሆን የሚችለው በሕጉ ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር ውጪ ተፈጽሞ ሲገኝ እንጂ በውጤቱ በሕጉ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር ከሚያስከትለው ያነሰና ፍትሐዊ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ እርምጃ በመፈፀሙ ተግባሩ ከስልጣኑና ከተግባሩ አድማስ ውጪ ነው ለማለት የሚያስደፍርበት ሕጋዊ ምክንያትና አግባብ የለም፡፡ በሕግ ያልተከለከለን ተግባር መፈፀም ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብም የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ስልጣንና የተወሰደውን እርምጃ መሰረት አድርጎ ያቀረበው ክርክርም ከአዋጁ አንቀጽ 90 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም በደንቡ አንቀጽ 18(3) ስር ከተመለተከቱት እርምጃዎች ውጤት አኳያ ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካች ተግባር ከአዋጅ ቁጥር ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 2(2፣3፣እና 4)፣6፣ 14(5)፣90፣111 እና 112፣እንዲሁም ከደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10(2)፣18(3) እና 36 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ ገንዘቡ በተጠሪ እንዳይታገድ የሚያደርግበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ ገንዘቡን ማገዱም ሆነ አመልካች ከአገር ውስጥ የገቢ ምንጭ 90% ያህሉን መሰብሰቡ እየተረጋገጠ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ 10%

www.abyssinialaw.com

እንዲለቀቅለት መደረጉ ሕጋዊ ከሚባልና በውጤቱም ፍትሃዊ ነው ተብሎ ከሚደመደም በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በተጠሪ ቦርድ ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 108144 ጥቅምት 13 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ውሣኔው በ9/02/05 ዓ.ም. ተነበበ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**የሃሣብ ልዩነት**

እኔ በአራተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የህግ ትርጉምና ውሣኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡ በዚህ መዝገብ የቀረበው የህግ አተረጓጉም ጥያቄና ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 75877 ከቀረበው የህግ አተረጓጎም ጥያቄና ክርክር ጋር ተመሣሣይነት ይዘት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም የሥራ ባለደረቦቼ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 እና ደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎችን በመተርጎም ሒደት የምለይባቸውን መሠረታዊ ምክንያቶች በሰበር መዝገብ ቁጥር 75877 በዝርዝር የፃፍኩ በመሆኑ በዚህ መዝገብ በድጋሚ መፃፍ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ አብላጫው ድምጽ ከሰጠው የህግ ትርጉም ውሣኔ የምለይባቸውን ዝርዝር ምክንያቶች ለመረዳት በሰ/መ/ቁ. 75877 የፃፍኩትን ልዩነት ሃሣብ ማንበብ እንደሚያስፈልግ እየገለጽኩ ተጠሪ አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ በፊት ከውጭ ምንጭ ያሰባሰበውን ገንዘብ ለማገድ የሚያስችለው ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 621/2001 እና ደንብ ቁጥር 168/2002 አልተሰጠውም በማለት በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ